# አጠቃላይ የነገረ መለኮት ትምህርት

# ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ

3ኛ መጽሐፍ

## ጥናት 7. ትምህርተ ድኅነት

በቄስ ኮሊን ማንሰል

አቶ ፍትሐ አምላክ እንየው
1999 ዓ.ም.
Ato Fithamlak Enyew
2007

አቶ ፍትሐ አምላክ እንየው
የፖ.ሣ.ቁ. 122663 አዲስ አበባ
Ato Fithamlak Enyew
122663 ADDIS ABABA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ደራሲው ቄስ ኮሊን ሬይ ድሞክ ማንሰል ዋናውን ጽሑፍ ጻፉ::
አቶ ፍትሐ አምላክ እንየው የአማርኛውን ቅጂ የዋናውን መጽሐፍ መንፈስ ሳይለቅ አሻሽለዋል::

**Author: The Reverend Colin Maunsell wrote the original Manuscript.**
**Ato Fithamlak Enyew corrected and improved the Amharic but without changing the intention of the original.**

የሽፋን ሥዕል
በወንድወሰን ገ/ትንሣኤ

**በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ**
PRINTED BY COMMERCIAL PRINTING ENTERPRISE



# የቄስ ማንሰል ዐጭር የሕይወት ታሪክ

ቄስ ኮሊን ሬይ ድሞክ ማንሰል ለወላጆቻቸው ዐምስተኛና የመጨረሻ ልጅ በመሆን በእንግሊዝ አገር ባዝ (BATH) በምትባል ከተማ እ.ኤ.አ. በ1933 ተወለዱ:: ወላጆቻቸው የቤተ ክርስቲያን አባሎች የነበሩ ሲሆን፥ በቤተሰቡ በመጀመሪያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነችው፥ ከሁለት ወንድማማቾችና ከሁለት እኅትማማቾች መካከል አንደኛዋ እኅታቸው ነበረች:: ከሁሉ አስቀድሞ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ለቄስ ማንሰል የነገረቻቸውና የጸለየችላቸው በቤት ውስጥ ሞግዚት ሆና የምትሠራ አንዲት ወጣት ነበረች::

ቄስ ማንሰል ወደ ትምህርት ዓለም የገቡት ገና የዐምስት ዓመት ልጅ በነበሩበት ጊዜ ነው:: ወቅቱ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረበት ጊዜ ነበረና ከከተማ ውጭ ሰላማዊ በሆነ ስፍራ በሚገኝ አንድ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው በዐዳሪነት መማር ጀመሩ:: በ1947 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በ13 ዓመታቸው ዊንቼስተር ኮሌጅ ገብተው ከፍተኛ ትምህርት መከታተል ጀመሩ:: በዊንቼስተር ኮሌጅ ይማሩ በነበሩባቸው ዓመታት ውስጥ ጌታን አግኝተው ለሚስዮን አገልግሎት ተጠሩ:: ቄስ ማንሰል የ14 ዓመት ወጣት ሳሉ በእኅታቸው ድጋፍና ወጪ፥ በእንግሊዝ አገር የቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማኅበር ባዘጋጀውና በመራው የመርከብ ሽርሽር እንዲሳተፉ ተደረገ:: በዚሁ የሽርሽር መርሐ ግብር ላይ በቀረበ መልእክት ቄስ ማንሰል ወደ ጌታ ተሳቡ:: ከሁለት ዓመት በኋላ፥ እሁድ ቀን መጽሐፍ ቅዱስ ሲያጠኑ በማርቆስ ወንጌል 15፥16 ላይ፥ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ተብሎ በተጻፈው ጥቅስ ልባቸው በጣም ተነካ:: ቄስ ማንሰል ሚስዮናዊ እንደሚሆኑ፥ አንድ ቀን ከትውልድ አገራቸው ወጥተው በሌላ አገርና በእንግዳ ባህል ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ እንደሚሄዱ አስቀድመው ተገንዝበው ነበር:: በዚህ መሠረት ስለ ጥሪአቸው ምክር ለመቀበል ወደ አንድ ሚስዮናዊ ድርጅት ሄዱ፤ ያ ድርጅት በመጀመሪያ ቢ.ሲ. ኤም ኤስ (BCMS)፥ አሁን ደግሞ ክሮስሊንክስ (CROSSLINKS) እየተባለ የሚጠራው ሲሆን፥ በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ «ሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር» በሚባለው ስም ይታወቅ ነበር:: ቄስ ማንሰል ወዲያውኑ በአርሲ ክፍለ አገር በሚገኝ አንድ ስፍራ ይሠራ ለነበረ አንድ የዕርሻ ባለሙያ ደብዳቤ እንዲጽፉ ምክር ተሰጣቸው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልባቸው ወደ ኢትዮጵያ እያዘነበለ ሄደ::

በዊንቼስተር ኮሌጅ የጀመሩትን ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ቄስ ማንሰል በ1951 እ.ኤ.አ. ለብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ወደ ግብፅ ሄዱ:: በዚያም ከቤተ መንግሥት የመሃንዲሶች ቡድን አባላት ጋር የሁለት ዓመት አገልግሎት ሰጡ:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ ብቻቸውን ሳሉ ከአንድ ክርስቲያን ምን እንደሚጠበቅና በእምነት መጽናት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በይበልጥ መማር ጀመሩ:: ቄስ ማንሰል በመጀመሪያዋ ሌሊት፥ በጦር ሰፈሩ ውስጥ በነበረችው ዐልጋቸው አጠገብ ተንበርክከው መጸለያቸው፥ በክርስቶስ በማያምኑ ብዙ ሰዎች ፊት ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመመስከር ምንም ዐይነት ዕፍረት እንደማይሰማቸው አሳየ:: በወታደራዊው ሥልጠና አንድ ክፍል ውስጥ፥ ወታደሮቹ በሕዝብ ፊት ንግግር ማድረግን በይፋ እንዲለማመዱና እንዲሠለጥኑ ይደረግ ነበር:: ያ ትምህርት ቄስ ማንሰል ለወደፊት የስብከትና የትምህርት አገልግሎታቸው ግልጽ የሆነ ድምፅ እንዲኖራቸው አድርጓል::

ቀጥሎም ቄስ ማንሰል በ1953 እ.ኤ.አ. የምህንድስና ትምህርት ለመከታተል ኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ገቡ:: በዚህ ኮርስ ላይ ተቸግረው የነበሩት በተለይ፣ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ የቄስ ማንሰል ሙያ መሃንዲስነት አለመሆኑን ሲያስተውሉ ነው:: በኬምብሪጅ ሲ አይ ሲሲዩ (CICCU) ኢቫሱ (EVASUE) ከተባለው የዩኒቨርሲቲ ምእመናን ተማሪዎች ኅብረት ጋር ስለ ሚስዮን አገልግሎት ሲጸልዩ፣ ስለ ጥሪው በመጠኑ ቀዝቅዞ የነበረው ልባቸው እንደገና ተቀጣጠለ:: ቄስ ማንሰል ከ69 ወጣቶች ጋር በውጭ አገር ያገለግሉ ዘንድ ለሁለተኛ ጊዜ ራሳቸውን ለጌታ አስረከቡ:: በተጨማሪም ቄስ ማንሰል ስፖርተኛ ስለነበሩ «ስኳሽ»፣ «ቴኒስ» እና በመጠኑም የእግር ኳስ መጫወት ያስደስታቸው ነበር:: ቄስ ማንሰል በ1956 እ.ኤ.አ. በ«B.A.»፣ በ1969 ደግሞ በ«M.A.» ተመርቀዋል::

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ቄስ ማንሰል ስለ «ሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር» እና ስለ ኢትዮጵያ ለማወቅ የነበራቸው ፍላጎት እየጨመረና እያደገ ሄደ:: በተለይም የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያንን ቅርንጫፎች በኢትዮጵያ ውስጥ በማቋቋም ፈንታ፣ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መታደስ ላይ ያተኩር በነበረው በድርጅቱ ዓላማ ተማርከው ነበር:: ቄስ ማንሰል በኢትዮጵያ ለማገልገል ራሳቸውን መስጠት ሲፈልጉ፣ በመጀመሪያ በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የቅስናን አገልግሎት ቅጽ በመሙላት የቅስና ማዕርግን እንዲቀበሉ ምክር ተሰጣቸው:: በቴንደል የትምህርተ መለኮት ኮሌጅ ያሳለፏቸው የሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት (1956-58 እ.ኤ.አ.) ለሕይወታቸው በጣም አስፈላጊና መሠረታውያን ነበሩ:: በዚያ ተቋም ውስጥ ዋናው መምህራቸው ዶ/ር ጂም ፓከር የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ይበልጥ አስተካክለው እንዲረዱ አደረጓቸው:: በእኒህ ታላቅ መምህር መሪነት አስተሳሰባቸውንና የአጻጻፍ ዘዴያቸውን ልዩ የሚያደርገውን የግልጽነት ባሕርይ ተላበሱ:: ቄስ ማንሰል በሰኔ ወር 1958 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. ከቀሰሱ በኋላ፣ በደቡብ ምሥራቅ እንግሊዝ አገር ለሁለት ዓመት ረዳት ቄስ በመሆን አገለገሉ::

የቄስ ማንሰል ወላጆች ልጃቸው ወደ ውጭ አገር እንዲሄድ የተሰጠውን የአገልግሎት ጥሪ በእምነት ተቀብለው ደገፉት:: ካገኟቸው ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ጋር አንዳንድ ተጨማሪ ኮርሶችን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ቄስ ማንሰል በሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር አስተዳዳሪነት በመጋቢት ወር 1961 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. ወደ ኢትዮጵያ በመርከብ ተጓዙ:: በዚያም ዓመት በ0ፄ ኀይለ ሥላሴ ሥልጣን የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ወጣ:: ይህ ክሥተት የተፈጸመው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንዳጋጣሚ አልነበረም::

በ1934 እ.ኤ.አ. የሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር የመጀመሪያ ሚስዮናውያን ኢትዮጵያ በደረሱ ጊዜ፣ የድርጅታቸው መርሐ፣ በራእይ 1፡9 ላይ «ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር» ተብሎ የተጻፈው ጥቅስ ነበረ:: ዓላማቸው ከጥንት ጀምሮ የተቋቋመችዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንድትታደስ መርዳት እንጂ የራሳቸውን ቅርንጫፍ አብያተ ክርስቲያናት ማቋቋም አልነበረም:: ለዚህም ዋና ትኩረታቸው መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማርና ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል በይበልጥ እንዲያውቅ የሚረዱ ማብራሪያዎችን መጻፍ ነበረ:: በአዲስ አበባ ከተጀመረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በኋላ፣ ከእነርሱ ጋር ዐብረዋቸው በሚሠሩ አገልጋዮች ላይ ስደት ሲደርስባቸው፣ ሚስዮናውያኑ ወደ ፍቼ ሄደው፣ የወንዶችና የሴቶች መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን መሥራት ቻሉ:: እዚያም በጸሎትና በእምነት እየተጉ ቆዩ::

የስራዊተ ክርስቶስ ማኅበር መሪ ዳዊት እስቶክስና ባለቤታቸው በአገልግሎት ምክንያት ወደ ጎንደር ሄደው ነበር:: እዚያም ሲኖሩ ሳለ ቄስ ማንሰል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በሚስተር እስቶክስ መሪነት እየኖሩ አማርኛ እንዲማሩ ተወሰነ:: ከሁለት ዓመት በኋላም ወደ ፍቼ ሄደው በዚያ መኖር ሲጀምሩ፥ ከወንጌላዊ ደበሌ ፈይሳ ጋር ለመገናኘትና ለመተዋወቅ በቁ:: መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ክርስቲያናውያት መጻሕፍትን ለሕዝብ በማሠራጨትና በመሸጥ ከወንጌላዊ ደበሌ ጋር ዐብረው ለማገልገል ተስማሙ:: ወዲያውኑም ከመንግሥት ፈቃድ አግኝተው በላንድሮቨር መኪና ከገበያ ወደ ገበያ እየተዘዋወሩ አገልግሎታቸውን ጀመሩ:: ወንጌልንም ሰበኩ:: ቄስ ማንሰል በአማርኛ ሲሰብኩ፥ ወንጌላዊ ደበሌ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ ይተረጉሙ ነበር:: በዚህ መንገድ በመተባበር ሁለቱ ጓደኛሞች ከዐሥራ አራቱ ክፍለ አገሮች መካከል በዐሥራ አንዱ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ዐርሰዋል:: ሁለቱ ጓደኛሞች ወደ ገበያዎች ብቻ ሳይሆን፥ ወደ ትምህርት ቤቶችና ወደ ብዙ ሌሎች ድርጅቶችም ሄደው አገልግሎት ሰጥተዋል:: እጅግ በጣም ሩቅ ወደ ሆኑ መንደሮችና ገዳሞች ሳይቀር በመሄድ አገልግለዋል:: ማታ ማታ ድንኳን ተተክሎ ቄስ ማንሰል በድንኳን፥ ወንጌላዊ ደበሌ ደግሞ በመኪና ውስጥ ተኝተው ያድሩ ነበር:: ለአራት ሳምንት ያህል የሚያስፈልጋቸውን ምግብና የመኪና ነዳጅ፥ መጻሕፍትም ጭምር መኪና ውስጥ ጭነው መያዝና መሄድ ነበረባቸው:: ከወር በኋላ ወደ ፍቼ ተመልሰው ዕረፍት ያደርጋሉ:: ከዕረፍት በኋላ፥ መኪናው ሲስተካከል፥ መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎች መጻሕፍትን ጭነው እንደገና ጉዞአቸውን ይቀጥሉ ነበር:: በጉዞአቸው ወቅት ብዙ አስገራሚ ሁኔታዎች አጋጥሟቸዋል:: ቄስ ማንሰልና ወንጌላዊ ደበሌ አገልግሎት በሰጡበት አንድ ቦታ ነዋሪዎቹ፥ «የእናንተ መኪና በዚህ መንገድ ሲያልፍ በ20 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሦስተኛው ነው» ብለዋቸዋል:: ይህም ለአገልግሎት የተዘዋወሩባቸው ቦታዎች ምን ያህል ሩቅና ፍጹም ገጠራማ እንደነበሩ የሚያመለክት ነው:: በሌላ ጊዜ ደግሞ ወንጌላዊ ደበሌ ከአዲስ አበባ አዲስ የመኪና ዕቃ እስከሚያመጣ ድረስ፥ የሚገለገሉባት መኪና በዕርሻ ውስጥ ተበላሽታ ቆማ ትቄይ ነበር:: ቄስ ማንሰል ኢትዮጵያን፥ ሕዝቡን፥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዐቷን እያወቁ የሄዱት በዚህ ዐይነት መንገድ ነበር:: በተለይ የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀታቸውንም እያሻሻሉ ሄዱ::

ቀጥሎም እግዚአብሔር አስደናቂ የሆነ አንድ ዕድል አመቻቸ:: ለድርጅታቸው አባላት በእምነት የታያቸውን በር ከፈተላቸው:: በዚህ ጊዜ ቄስ ማንሰል ሁለት ዓመት ለሚያህል ጊዜ በእንግሊዝ አገር ታመው ቄዩ:: ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ 6 ዓመት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ትምህርት ቤት ከ6ኛ-11ኛ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ አስተምረዋል:: በተለያዩ ጊዜያትም በካቴድራሉ ውስጥ በስብከት አገልግለዋል:: በተለይ በወጣት ስብሰባዎች እየተገኙ በሰጡት አገልግሎት ሁሉ የታወቁና የተወደዱ መምህር ለመሆን በቅተዋል:: እሑድ እሑድ ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ፍላጎት ለነበራቸው መነኰሳትና ዲያቆናት መጽሐፍ ቅዱስ አስተምረዋል:: ቄስ ማንሰል ራሳቸው እንደመሰከሩት፥ ይህ ጊዜ በሕይወታቸው ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት የታየበት ዘመን ነበረ:: ሴቶችን ለማገልገልም በሮች ሲከፈቱ፥ ከድርጅታቸው ሁለት ወይም ሦስት ሴት አገልጋዮች ሴቶችን የማስተማር ልዩ ዕድል አገኙ:: ሚስ ቤንሶን የሚባሉ ሴት አገልጋይ በሴቶች ማኅበር ውስጥ እንዲያስተምሩ ሲደረግ፥ ሚስ ጃርቪስ የሚባሉ አንዲት ሌላ አገልጋይ በቅድስት ሥላሴ አመራር ሥር በነበረው በሰበታ በሚገኘው ጌቴሴማኒ የሴቶች ገዳም ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲያስተምሩ ተጋበዙ::

በ1973 እ.ኤ.አ. ሚስ ሄዘል ኮሊንዝ የሚባሉ አንዲት ሚስዮናዊት ወደ አዲስ አበባ መጡ። እርሳቸውም በእንግሊዝ አገር በሴቶች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስተማሪነትና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከልም ያገለግሉ ነበር። 6 ወር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በሴቶች ገዳም ውስጥ ለማስተማር ወደ ሰበታ ሄዱ። ዐርብ ዐርብ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ በሴቶች ማኅበር ውስጥ ቀስ በቀስ በወር አንድ ጊዜ የማስተማር ፕሮግራም ጀመሩ። ሚስ ቤንሰንና ሚስ ጃርቪስ ጡረታ ሲወጡ ሚስ ሄዘል በሰበታና በሴቶች ማኅበር ውስጥ ይሰጡት የነበረውን አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ቀጠሉ።

በ1975 እ.ኤ.አ. በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት፥ የሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር ከኢትዮጵያ ወጣ። ቄስ ማንሰል ከአንድ ኢትዮጵያዊ ጓደኛቸው ጋር ወደ ባዝ (BATH) ማለትም ወደ ራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በአማርኛ ቋንቋ ለማዘጋጀት አንድ ዓመት አሳለፉ። የመዝገበ ቃላቱ ጽሑፎች በልዩ ልዩ ሰዎች ቢጻፉም፥ አዘጋጁ ቄስ ማንሰል ነበሩ። መዝገበ ቃላቱ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታትሞ፥ ወደ ሁለት ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተተርጕሟል። ቀጥሎም ቄስ ማንሰል በቤተ እስራኤል መካከል በሚሠራ አንድ ሌላ ድርጅት አመራር ሥር በመሆን ወደ ጎንደር ተመልሰው መጡ። እዚያም በሚስዮን ትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪ ሆኑ። ሚስ ሄዘልም እንደዚሁ በዚያ ድርጅት ሥር ሆነው ለአገልግሎት ወደ ጎንደር ስለተላኩ፥ ሁለቱም እንደገና ተገናኙ። ከሁለት ዓመት በኋላ ሴቶች በፖለቲካው ችግር ምክንያት በድርጅቱ ትእዛዝ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ሲደረግ፥ ቄስ ማንሰል ለ18 ወራት በጎንደር ጳጳስ አመራርና ቍጥጥር ኮርሶችን እያዘጋጁ መነኰሳትንና ካህናትን ለማስተማር ቈዩ።

የቄስ ማንሰል የሥራ ፈቃድ መታደስ ስላልቻለና እንደዚሁም በመነኰሳትና በካህናት መካከል እንዲሠሩ አስቀድሞ የተከፈቱላቸው በሮች ስለተዘጉባቸው፥ በ47 ዓመት ዕድሜያቸው የ40 ዓመት ዕድሜ የነበራችውን ሚስ ሄዘልን ለማግባት ጊዜው እንደደረሰ ተገነዘቡ። የጋብቻቸው ሥርዐት በ1981 እ.ኤ.አ. በእንግሊዝ አገር ከተፈጸመ በኋላ፥ 6 ወር በባዝ (BATH) በቄስ ማንሰል ቤተ ክርስቲያን የትዳር ሕይወታቸውን ጀምረው ከቈዩ በኋላ በሰራዊተ ክርስቶስ ማኅበር ትእዛዝ ወደ ፖርቱጋል ተላኩ። ሁሉ እንደ ሐሳባቸው ባይፈጸምም እንኳ፥ እዚያም እያገለገሉ ሳሉ እግዚአብሔር ወደ አንድ የተወሰነ ርምጃ መራቸው። ይኸውም ዐብረው የመጽሐፍ ቅዱስን ማብራሪያዎች እንዲጽፉ ነው። ይህም የመጣው፥ ከፖርቱጋል የቃለ እግዚአብሔር አንባቢዎች ማኅበርና ከፖርቱጋል ኢቫሱ (EVASUE) ጋር ከነበራቸው ግንኙነት የተነሣ ነበረ። ከእነዚህ ሁለት ድርጅቶች ጋር በመተባበር፥ ቄስ ማንሰል ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ሄዘል ጋር የአራት ዓመት ሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ኮርስ በፖርቱጋል ቋንቋ ጻፉ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ፥ ያንኑ ኮርስ ለኢትዮጵያውያን በአማርኛ ቋንቋ እንዲያዘጋጁ የእግዚአብሔር ጥሪ መሆኑ ለቄስ ማንሰል በጸሎት ጊዜ ተገለጠላቸው። በፖርቱጋል ገና ያልፈጸሙትን ሥራቸውን ከጨረሱ በኋላ፥ ቄስ ማንሰልና ባለቤታቸው አጠቃላይ ሁኔታውን ለማጥናት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አንድ ወር ቈዩ። በዚህ ቈይታቸው እግዚአብሔር መጻሕፍትን ለመጻፍና ለማዘጋጀት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ በሩን እንደሚከፍትላቸው ግልጽ ሆነላቸው።

ወደ ፖርቱጋል ተመልሰው 3 ወር ከቈዩ በኋላ ቄስ ማንሰል የልብ ድካም ሕማም ታመሙ። ባልና ሚስቱም ጥሪያቸው ተቃውሞ ያጋጠመው መሰላቸው። ከተወሰኑ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ለሦስት ወር ጽኑ የእምነት ትግልን

ታገሉ:: እግዚአብሔር በጸጋው ጸሎታቸውን ሰማ:: እርሳቸውንም አስነሣቸው:: በዚያ አገር ውስጥ የነበረውን አገልግሎታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ለ8 ወራት ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሰው፥ ቄስ ማንሰልና ባለቤታቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ዝግጅት ጀመሩ:: በ1991 እ.ኤ.አ. እርሳቸውና ባለቤታቸው ወደ ተወደደችው አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ:: ወደሚጸልዩላቸው አብያተ ክርስቲያናት፥ ወደ ግል ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸውም ሲጽፉ፥ በደብዳቤያቸው ራስጌ፥ «እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ፥ እጅግ ደስተኞች ሆንን:: ...እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን፥ ደስም አለን» የሚለውን በመዝ. 125(126)፥1:3 ላይ ተጽፎ የሚገኘውን ጥቅስ አስፍረው ልከዋል:: ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ለእነርሱ ወደ ቤት እንደመመለስ የሚቈጠር ነበርና::

ኢትዮጵያ ሲደርሱ በፖለቲካው ሁኔታና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ነገር እንደተለወጠ ተረዱ:: በከፊል ተከፍተውላቸው የነበሩ አንዳንድ የአገልግሎት በሮች ከጥቂት ወሮች በኋላ ተዘጉባቸው:: ሆኖም ለአገልግሎቱ በእግዚአብሔር እንደተጠሩ ዐውቀው ስለነበር ተስፋ አልቈረጡም:: በእውነት እግዚአብሔር ሁሉን በመቈጣጠር ሁኔታውን በአስደናቂ ዐይነት አስተካከለላቸው:: ተስማሚ ቤት አዘጋጀላቸው:: ቄስ ማንሰልም ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ አገኙ:: ከዚያም በኋላ በጡረታ ጊዜያቸው በኢትዮጵያ እየኖሩ አገልግሎቱን እንዲቀጥሉ መንገዱ ተመቻቸ::

እግዚአብሔር ለቄስ ማንሰልና ለባለቤታቸው ለሄዘል ያሳያቸው፥ ብዙ የማስተማር ተግባርን በይፋ እንዲያከናውኑ ሳይሆን፥ በግል የመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መጻሕፍትን መጻፍና ማዘጋጀት ዋና ተግባራቸው እንዲሆን ነው:: ስለዚህ ቄስ ማንሰል እግዚአብሔር ለእርሳቸውና ለባለቤታቸው ያሳያቸውን ወደ ተግባር ለመተርጐም መጻሕፍትን በመጻፍና በማዘጋጀት ሥራ ተሰማሩ::

የጽሑፍ ሥራውን ጀምረው ሳለ፥ እግዚአብሔር ድንገት ሳይታሰብ በዚህ ሥራ ሊሳተፍ ከሚችል አንድ ሰው ጋር ቄስ ማንሰልን እንዲገናኙ አደረገ:: ቄስ ማንሰል ከዚህ ሰው ጋር የተዋወቁት፥ ከብዙ ዓመታት በፊት በጎጃም ውስጥ ያገለግሉ በነበረበት ወቅት ነው:: ይህ ሰው ፍትሐ አምላክ እንየው ይባላል:: በዚያን ጊዜ ከገጠር ሄዶ በደብረ ማርቆስ ከተማ በመማር ላይ ስለነበረ፥ ቄስ ማንሰል ለተወሰነ ጊዜ በራሳቸው የመኖሪያ ግቢ ውስጥ አንድ ክፍል ሰጥተውት በመጠለያ ሲደግፉትና በትምህርቱም ሆነ በሕይወቱ እንዲበረታ ጠቃሚ የሆኑ መንፈሳዊና አባታዊ ምክሮችን ሲሰጡት ቈይተዋል::

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት ሁለቱ ተለያይተው ለረጅም ዓመታት ሳይገናኙ ቈዩ:: አስቀድሞ በፍትሐ አምላክ ልብ ውስጥ የተዘራው የቃሉ ዘር ማደግ ሲጀምርና የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ፥ የቄስ ማንሰልና የፍትሐ አምላክ የቈየ ግንኙነት እንደገና ሕይወት ዘራ:: ቄስ ማንሰል ከባለቤታቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጥተው ጥቂት ከቈዩ በኋላ፥ በአንድ ሚስዮናዊ ጓደኛቸው አማካይነት ከፍትሐ አምላክ ጋር ተገናኙ:: ወዲያውኑም ቄስ ማንሰል እርሳቸውና ባለቤታቸው ከእግዚአብሔር ስለተቀበሉት የጽሑፍ አገልግሎት ራእይ ያላቸውን ሐሳብ ሲገልጹለት፥ ፍትሐ አምላክ ሐሳባቸውን በጋለ ስሜት በመደገፍ፥ «ረጅም ጊዜ ሳንገናኝ ቈይተን እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ ሁኔታ እንድንገናኝ ያደረገው፥ ዐብረን የምንሠራው ብዙ የእርሱ ሥራ እንዳለ አስቦ ሳይሆን አይቀርም» አለ:: እንደተባለውም ቄስ ማንሰልና ባለቤታቸው በሚያከናውኑት የጽሑፍ ሥራ ውስጥ ፍትሐ አምላክ

ተሳታፊ መሆን ጀመረ:: የተጻፉ ጽሑፎችን በማረምና በማስተካከል ከእግዚአብሔር የተሰጠው ልዩ ችሎታ እያደገና እየሰፋ ሄደ:: በዚህ ዐይነት መንገድ በአንድነት የሚከናወነው የጽሑፍ አገልግሎት በስፋት ቀጥሎ፥ የፍትሐ አምላክ ኀላፊነት እየጨመረ ሄዶ የአገልግሎቱ ዋና ረዳትና አርታዒ ሆነ:: በመጨረሻም ቄስ ማንሰል ከዕለተ ዕረፍታቸው በፊት አገልግሎቱ ለወደፊትም በተሳካ መንገድ ይቀጥል ዘንድ፥ በተለይ በነገረ መለኮት መጻሕፍቶቻቸው ላይ ያላቸውን የደራሲነት መብት ለፍትሐ አምላክ በሕጋዊ መንገድ አስተላልፈዋል::

ቄስ ማንሰልና ባለቤታቸው በመጀመሪያ የጻፉት «የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ» የሚባለው መጽሐፍ በ60 ጥናቶች የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ዋና ዋና ርምጃዎች ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ያሳያል:: ቀጥሎም ቄስ ማንሰልና ባለቤታቸው ሄዘል በፖርቱጋል አገር አዘጋጅተውት የነበረውን የ4 ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለኢትዮጵያውያን በሚሆን መልክ በአማርኛ ቋንቋ ለመጻፍ ወስነው ሥራውን ጀመሩ:: «በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር» በሚል ርእስ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ4 መጻሕፍት መልክ ታትሞ ወጣ:: የጥናቱ ዝግጅት በጥያቄዎችና በማስታወሻዎች መሠረት አንባቢን በ4 ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ እንዲያጠና ይመራዋል::

ከጽሑፉ ሥራ ጋር ጎን ለጎን ቄስ ማንሰል ከልዩ ልዩ ማኅበራት ወይም ቡድኖች የአገልግሎት ጥሪ ሲቀርብላቸው፥ በተለያዩ ጊዜያት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ሥልጠና ሰጥተዋል:: አንዳንድ ጊዜ ከባለቤታቸው ከሄዘል ጋር ዐብረው ስለ ጋብቻና ስለ ጋብቻ ሕይወት ለማስተማር ተጋብዘው አስተምረዋል:: በተጨማሪም በቅዱስ ማቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ዐልፎ ዐልፎ መስበክ፥ በመኖሪያ ቦታቸው አካባቢ በጎረቤቶች መካከል ስለ ክርስቶስ መመስከርና እንዲሁም በማንኛውም ሁኔታና ቦታ ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ በታላቅ የደስታ ስሜት የሚከናወኑ የቄስ ማንሰል የአገልግሎት አካላት ነበሩ::

የአራት ዓመቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅት ተጠናቆ ከታተመ በኋላ ቄስ ማንሰል ከባለቤታቸው ጋር የተወሰኑ የአዕማድ መጻሕፍትን እንደገና ዐርሞና አስተካክሎ በማሳተም፥ አዳዲስ መጻሕፍትንም በመጻፍ ተግባር ላይ አተኰሩ:: አዕማድ መጻሕፍት በአራት ድርጅቶች ትብብር የተዘጋጁ መጻሕፍት ናቸው:: ብሉይ ኪዳን፥ አዲስ ኪዳን፥ የክርስትና ትምህርትና የክርስትና ኑሮ አዕማድ ናቸው:: ከአዕማድ መጻሕፍት መካከል በተለይ «እግዚአብሔር ወልድ»፥ «ከባቢሎን ምርኮ መልስ»፥ «የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር» እና «አስደናቂው ልውውጥ» ቄስ ማንሰል የጻፏቸው መጻሕፍት ናቸው:: «አስደናቂው ልውውጥ» በክርስቶስ በማመን ላይ የተመሠረተው የጽድቅ መንገድ ምን እንደሆነ ስለሚያሳይ፥ ከጻፏቸው መጻሕፍት ሁሉ የሚወዱት መጽሐፍ ነው፤ ከጥልቅ የልባቸው ክፍል የፈሰሰ ነውና::

ለሁለተኛ ጊዜ የልብ ሕማም ሲነሣባቸው፥ ቄስ ማንሰል ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሰው በመሄድ፥ ከባድ የቀዶ ጥገና ህክምና ተደረገላቸው:: እግዚአብሔር በጸጋው እንደገና ከሞት አፋፍ መለሳቸው:: ህክምናቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ከመጡ በኋላ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ታርሞና ተሻሽሎ እንደገና የሚታተምበት ጊዜ እንደደረሰ ተገነዘቡ:: ቄስ ማንሰል 150 አዳዲስ ቃላትንና ማብራሪያዎችን ጽፈው ሲያዘጋጁና ጠቅላላ አቀራረቡን ሲያሻሽሉ፥ ባለቤታቸው ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን አንብበው በማመሳከር አስተካከሉ፤ ተጨማሪ ካርታዎችንም ሣሉ:: መዝገበ

ቃላቱ በአዲስ አቀራረብ ለ6ኛ ጊዜ በ1993 ዓ.ም. ታትሞ ወጣ፤ አሁን ግን ወደ 8ኛ ዕትም ደርሷል።

በ1998 እ.ኤ.አ. የጽሑፉን አገልግሎት የሚመለከት አንድ ትልቅ ጥሪ ለቄስ ማንሰል ቀረበ። ይኸውም፥ የአጠቃላይ ነገረ መለኮት መጽሐፍ ለኢትዮጵያውያን እንዲያዘጋጁ ነው። መጽሐፉ የምዕራባውያን ትምህርተ መለኮት የትርጉም መጽሐፍ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያውያን ትብብር ለኢትዮጵያውያን የሚጻፍ መጽሐፍ መሆን እንዳለበት ቄስ ማንሰል ተገነዘቡ። ስለዚህ ጥሪውን የተቀበሉት ከብዙ የሐሳብ መብላላትና ከጸሎት በኋላ ነበረ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ዐብረዋቸው እንዲሠሩ ልዩ ልዩ ችሎታ የነበራቸውን ሰዎች አስነሣላቸው። አንድ ኢትዮጵያዊ ጓደኛቸው፥ «የነገረ መለኮት መጽሐፍ ለኢትዮጵያውያን ማዘጋጀት ካሰቡ፥ ከተለመዱት ከምዕራባውያን ሰባት ክፍሎች ይልቅ ሥላሴያዊውን ስም ተከትሎ መጻፍ ይሻላል» በማለት ቄስ ማንሰልን መከሯቸው። በዚህ ዐይነት «ትምህርተ እግዚአብሔር» በ2003 እ.ኤ.አ.፥ «ትምህርተ ክርስቶስ» በ2006 እ.ኤ.አ. ታትመው ወጡ።

«ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» በሚል ርእስ ሦስተኛውን መጽሐፍ መጻፍ ከጀመሩ በኋላ፥ ቄስ ማንሰል ታመው ወደ እንግሊዝ አገር ሄዱ። ምርመራ ተደርጎላቸው ከባድ የካንሰር በሽታ እንዳለባቸው ታወቀ። የጀመሩት መጽሐፍ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የተገኘውን የመዳን ሥራ በሰው ልብ እንዴት እውን እንደሚያደርግ ስለሚያብራራ፥ የጤናቸው ጉዳይ ይበልጥ አሳሳቢ እየሆነ በመምጣቱ፥ በተለይ ወሳኝ የሆነውን የዚህን መጽሐፍ ክፍል ጽፈው ለመጨረስ በእግዚአብሔር ኀይል ብዙ ታግለዋል። በእንግሊዝ አገር የሚደረግላቸውን ህክምና ከጨረሱ በኋላ ስላልተሻላቸው፥ በፍጥነት ወደሚወዷትና ብዙውን የአገልግሎት ዘመናቸውን ወዳሳለፉባት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ። ምክንያቱም ለእርሳቸው ከኢትዮጵያ ምድር ወዳገለገሉት ጌታ መሄድ የዘወትር ምኞታቸው ነበር። በመጨረሻ ምእመናን ወደ ሰማያዊው ክብር እንደሚደርሱ ስለተሰጣቸው ዋስትና የሚገልጸውን የመጨረሻውን ምዕራፍ ጽፈው እንደጨረሱ፥ ዐብረዋቸው ይሠሩ ከነበሩት ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን ካመሰገኑ በኋላ፥ ጥቂት ቀናት ቈይተው በሴፕቴምበር (September 8th) 2005 እ.ኤ.አ. ወደ ጌታ ክብር ገቡ።

የቄስ ማንሰል አስከሬን በሚወዷቸው በኢትዮጵያውያን መካከል በጉለሌ መካነ መቃብር ተቀብሯል። በመቃብሩ ላይ፥ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የድርጅቱ መርሖ የነበረው፥ «ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ተቀርጾ ይገኛል። እውነት ነው፤ የቄስ ማንሰል ምድራዊ ሕይወት አብቅቷል፤ አንደበታቸውም ጸጥ ብሎአል። በዕብራውያን 11፥4 ላይ፥ «ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል» ተብሎ ለአቤል እንደተመሰከረለት ሁሉ፥ ቄስ ማንሰልም በሕይወት ምስክርነታቸውና በጽሑፍ ሥራ አገልግሎት ባስመዘገቡት ውጤት ከሞቱ በኋላ ዘወትር የሚናገር ሕያው የሆነ ቀሪ ቅርስ ትተው ዐልፈዋል።

# መቅድም

«ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» ቄስ ማንሰል ሊጽፏቸው ዕቅድ ከያዙላቸው የትምህርተ መለኮት መጻሕፍት ውስጥ ሦስተኛው መጽሐፍ ነው። የመጀመሪያው መጽሐፍ «ትምህርተ እግዚአብሔር» በ1995 ዓ.ም.፥ ሁለተኛው «ትምህርተ ክርስቶስ» ደግሞ በ1998 ዓ.ም. ታትመው መውጣታቸው ይታወቃል። ሦስተኛው መጽሐፍ የአንደኛውና የሁለተኛው ተከታይ በመሆኑ በዕቅዱ መሠረት በምዕራፍ 78 ይጀምራል።

«ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» በከባድና በረጅም ምጥ የተወለደ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ እንዲወለድ ውድ ባለቤቴ መላ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ መሆናቸውን መናገር ተገቢ ይመስለኛል። «ትምህርተ ድኅነት» የተባለውን የመጽሐፉን ዋና ክፍል በመጻፍ ላይ ሳሉ፥ ቄስ ማንሰል በጸና ታመው ለልዩ ህክምና ወደ እንግሊዝ አገር መሄድ ነበረባቸው። ከባድ ሕመም ቢያማቸውም፥ እንግሊዝ አገር በዘመድ ቤትም ሆነ በሆኪም ቤት ሳሉ የጽሑፍ ሥራቸውን ቀጠሉ። አንዳንድ ጊዜ ለተወሰነ ምዕራፍ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ይዘት ወይም አቀራረብ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ሌሊት ስለነበረ፥ «ከእግዚአብሔር የተቀበልሁትን ሳልረሳ መጻፍ አለብኝ» በማለት በሚቀጥለው ቀን ተነሥተው ይጽፉ ነበር። ሳምንት በሳምንት እየተተካ ጊዜው እያለፈ ሲሄድ፥ ቄስ ማንሰል ሕመሙ ጸንቶባቸው ድካም ቢበረታባቸውም፥ ሀኪሞቻቸው እስከሚገርማቸው ድረስ የጀመሩትን ጽፈው ለመጨረስ ከባድ ተጋድሎ አድርገዋል። የትምህርተ መለኮትን «አክሊል» ተግባር በእግዚአብሔር ኃይል እንዲጨርሱ ቊርጥ ውሳኔ አድርገው ነበርና። እግዚአብሔርም የልባቸውን ምኞት ፈጸመላቸው። ከዕለተ ዕረፍታቸው ጥቂት ቀናት በፊት ከባድ ትግል አድርገው ወደ መጨረሻው ምዕራፍ ደረሱ።

ቄስ ማንሰል በመጀመሪያ ያቀዱት፥ እያንዳንዱ መጽሐፍ ሦስት ሦስት ጥናት ኖሮት እንዲዘጋጅ ነው። በዚህም መሠረት ሦስተኛው መጽሐፍ «ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን» እና «ትምህርተ ሥነ ፍጻሜ» የተባሉት አርእስት ተጨምረውበት ሊቀርብ ነበር የታሰበው። በ7ኛው ጥናት የተጠቀሱ አንዳንድ አርእስት በዝርዝር መተንተን የነበረባቸው በ8ኛው ወይም በ9ኛው ጥናት ውስጥ ነው፤ ለምሳሌ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በስፋት ማተት የተፈለገው፥ ተግባራዊነታቸው በሚረጋገጥበት በመጽሐፉ ባልተካተተው «ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን» በሚለው ርእስ ሥር ነበር። ነገር ግን ይህን ዕቅድ በታሰበው አኳኋን የሚፈጽሙበት ጊዜ አልተሰጣቸውም። እንደዚህም ቢሆን፥ ቄስ ማንሰል ልክ እንደጻፉት መጽሐፉ ታትሞ እንዲወጣ ተወስኗል። የባለቤቴ ጽኑ ተስፋና ምኞት የተሻለና የተሟላ የትምህርተ መለኮት መጽሐፍ እንዲጽፍ እግዚአብሔር አንድ ኢትዮጵያዊ ያስነሣል የሚል ነበረ።

በሦስተኛው መጽሐፍ ዝግጅት የተሳተፉትን ሁሉ በባለቤቴ ስም ማመስገን እፈልጋለሁ። ረቂቅ ጽሑፉን በጥንቃቄ አንብበው ጠቃሚ አስተያየት ለሰጡንና ገንቢ የማሻሻያ ሐሳቦችን ላቀረቡልን፥ ረቂቁን ለገለበጡትና በኮምፒዩተር ለጻፉት፥ የሽፋን ሥዕል ላዘጋጀው፥ ላሳታሚውና ለማተሚያ ድርጅቱ፥ ስለ

መጽሐፉ አጠቃላይ የዝግጅት ሂደት ለጸለዩትም ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ቄስ ማንሰል ሦስተኛውን መጽሐፍ ማዘጋጀት ሲጀምሩ፥ ዋናውን የመጽሐፉን ክፍል ጽፈው እስከሚጨርሱት ድረስ ወደ ጌታ ክብር እንደሚገቡ አልታሰበም ነበር:: ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ለተዘጋጀላቸው ድኅነት አሁን በሰማይ ጌታን በምስጋና እያከበሩት እንዳሉ አምናለሁ:: በምድርም የዚህ መጽሐፍ አማካይነት አንባብያን በድኅነታቸው ስለተገለጠላቸው አስደናቂ የእግዚአብሔር ጸጋ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ቢሰጡ፥ የባለቤቴ ልባዊ ፍላጎት ተፈጸመ ማለት ነው::

ይህን መጽሐፍ በባለቤቴ ስም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሳበረክት፥ የሐዋርያው ጳውሎስን ቃለ ቡራኬ በመጥቀስ ነው:- «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን:: አሜን::»

ሄዘል ማንሰል
አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም.

«የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና
ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥ እንደ ምሕረቱ
መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና
በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን...»

ቲቶ 3፥ ፡5

# ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ

## ማውጫ


ገጽ

**መግቢያ** 17

**ጥናት 7- ትምህርተ ድኅነት** 23

**ክፍል 1- ትምህርተ ግብረ መንፈስ ቅዱስ** ........ 23
- ምዕራፍ 78- የድኅነት ዐውድ ........ 23
- ምዕራፍ 79- የእግዚአብሔር መንፈስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ........ 31
- ምዕራፍ 80- መንፈስ ቅዱስና የጋርዮሽ ጸጋ ........ 40
- ምዕራፍ 81- መንፈስ ቅዱስና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 48
- ምእራፍ 82- መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ሥላሴ ........ 62
- ምዕራፍ 83- መንፈስ ቅዱስና የድኅነት ጸጋ ........ 72

**ክፍል 2- መንፈስ ቅዱስና የሰው ድኅነት** ........ 84
- ምዕራፍ 84- የሰው ድኅነት በክርስቶስ መሆኑ ........ 84
- ምዕራፍ 85- የሰው ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ..... 94
- ምዕራፍ 86- የግብረ መንፈስ ቅዱስ ቅደም ተከተል ........ 110
- ምዕራፍ 87- የእግዚአብሔር ጥሪና የሰው ዳግም ልደት ........ 117
- ምዕራፍ 88- ንስሓ መግባትና እምነት ........ 131
- ምዕራፍ 89- ጽድቅና ቅድስና፥ የቅድስና ደረጃ ........ 148
- ምዕራፍ 90- ልጅነት ........ 165
- ምዕራፍ 91- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ........ 173
- ምዕራፍ 92- ቅድስና ........ 191
- ምዕራፍ 93- ዋስትና ........ 214

**መረጃዎች**
1. የእንግሊዝኛና የሌሎች ቋንቋዎች ቃላት ........ 217
2. የሰዎች ስምና የአርእስት ማውጫ ........ 220
3. ማብራሪያ የተሰጠባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ........ 224

# መግቢያ

የሦስቱ የነገረ መለኮት መጻሕፍት አርእስት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው:-

1ኛ መጽሐፍ - ትምህርተ እግዚአብሔር

ጥናት 1 - ትምህርተ አስተርእዮ

ጥናት 2 - ትምህርተ ባሕርየ እግዚአብሔር

ጥናት 3 - ትምህርተ ፍጥረት

2ኛ መጽሐፍ - ትምህርተ ክርስቶስ

ጥናት 4 - ትምህርተ ሰብእ

ጥናት 5 - ትምህርተ ሥጋዌ

ጥናት 6 - ትምህርተ ግብረ ክርስቶስ

3ኛ መጽሐፍ - ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ

ጥናት 7 - ትምህርተ ድኅነት

የአንደኛው መጽሐፍ መግቢያና አርእስቱ፥ ሀ) የነገረ መለኮት ዐውድ፥ ለ) አጠቃላይ የነገረ መለኮት ጥናት አርእስት፥ ሐ) አጠቃላይ የነገረ መለኮት ትምህርት ዘዴ፥ መ) የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃቀም፥ ሠ) የልዩ ልዩ መጻሕፍት አጠቃቀም፥ ረ) ጥቅም ላይ የዋሉ መጻሕፍት ምኅፃረ ቃላት የሚሉ ናቸው። ለእነዚህ አርእስት በ2ኛውና በዚህ በ3ኛው መጻሕፍትም በተለይ የተጠቀምንባቸው መጻሕፍት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው:-

ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች መጻሕፍት

<u>በአማርኛ</u>

መቅመቃ. - «የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት» በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1992 ዓ.ም. ታትሞ እንደገና የተዘጋጀ 6ኛ ዕትም

ቀ.አ. - ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1980 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የታተመ

ት.መ. - «ትምህርተ መለኮት» በአቶ ዓሥራት ገ/ማርያም በ1991 ዓ.ም. የታተመ

ት.እግ. - ትምህርተ እግዚአብሔር፤ አጠቃላይ የነገረ መለኮት ትምህርት 1ኛ መጽሐፍ በ1995 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የታተመ

አ.መ.ት. - አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ተተርጉሞ በ1993 ዓ.ም. የታተመ

አስደናቂው ልውውጥ - አዕማድ መጻሕፍት ቊጥር 21 1992 ዓ.ም. ብርሃነ ሕይወት መጻሕፍት

እምነታችን - የዌስትምንስተር ሃይማኖታዊ መግለጫ በ1983 ዓ.ም. በቄስ ኃይሉ መኰንን ተተርጉሞ የታተመ። ይህ ትርጉም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሲጠቀስ፥ አንዳንድ ቃላትን ከማሻሻል በስተቀር ዋና ትርጒሙ አልተለወጠም

የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር - አዕማድ መጻሕፍት ቊጥር 24 1994 ዓ.ም. ብርሃነ ሕይወት መጻሕፍት

**በእንግሊዝኛ**

**BAVINCK** Our Reasonable Faith. Herman Bavinck. 1956. Eerdmans Publishing Company.

**BERKHOF** Systematic Theology. L. Berkhof. 15th Printing 1953. Eerdmans Publishing Company.

**CT** Concise Theology, J.I. Packer 1993 IVP.

**GRUDEM** Systematic Theology. Wayne Grudem 1954. IVP.

**HODGE** Systematic Theology (Abridged edition). Charles Hodge. 1998 Baker Book House Company.

**NIDCC** The New International Dictionary of the Christian Church 1974, British edition by Paternoster Press LTD.

**RR** A New Systematic Theology of the Christian Faith. Robert L. Reymond.


**ማስታወሻ**

በጥናት 7 የተጠቀምንባቸው ሌሎች መጻሕፍት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።


**J.I.P.** Keep in Step with the Spirit. J.I. Packer. 1984. IVP.

**THS** The Holy Spirit. Sinclair Ferguson. 1996. IVP.

**PGR** The Message of Salvation. Philip Graham Ryken. 2001. IVP.

# ጥናት 7 - ትምህርተ ድኅነት

## የምዕራፎች ማውጫ


ገጽ

**ክፍል 1 - ትምህርተ ግብረ መንፈስ ቅዱስ** 23

**ምዕራፍ 78 - የድኅነት ዐውድ** ........ 23
- ሀ) ስለ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት ........ 23
- ለ) የግብረ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት ጥቅም ........ 25
- ሐ) መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ልብ ውስጥ በመኖሩ የሚገኝ ቅድስና ........ 25
- መ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ........ 26
- ሠ) ግብረ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 26
- ረ) የመንፈስ ቅዱስ አሠራርና ምልክቶቹ ........ 26

**ምዕራፍ 79 - የእግዚአብሔር መንፈስ በብሉይ ኪዳን ዘመን** ........ 31
- ሀ) ሩአኽና ፍጥረት ........ 32
- ለ) ሩአኽህና መግቦተ እግዚአብሔር ........ 33
- ሐ) ሩአኽህና አዲስ ልደት ........ 34
- መ) ሩአኽህና የእግዚአብሔር ቃል ........ 35
- ሠ) ሩአኽህና አካልነቱ ........ 36
- ረ) ሩአኽና ክርስቶስ ........ 38

**ምዕራፍ 80 - መንፈስ ቅዱስና የጋርዮሽ ጸጋ** ........ 40
- ሀ) የጸጋ ሰፊ ይዘት ........ 40
- ለ) የጸጋ አስተሳሰብ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 40
- ሐ) የጋርዮሽ ጸጋና ልዩ ጸጋ ........ 41
- መ) የጋርዮሽ ጸጋ ፍሬና መሣሪያዎቹ ........ 43
- ሠ) የጋርዮሽ ጸጋና ክርስቲያናዊ ኑሮ ........ 46

**ምዕራፍ 81 - መንፈስ ቅዱስና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ** ........ 48
- ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ፅንሰት፥ ልደትና እድገት ውስጥ ........ 50
- ለ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ጥምቀት፥ መፈተንና አገልግሎት ........ 52
- ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ሞት፥ ትንሣኤና ዕርገት ........ 57
- መ) የመንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ አገልግሎት ተከታታይነት ........ 60

**ምዕራፍ 82 - መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ሥላሴ** ........ 62
- ሀ) የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ........ 63
- ለ) የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክነት ........ 66
- ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ሥርፀት ........ 66
- መ) ግብረ መንፈስ ቅዱስ ........ 69

ምዕራፍ 83 - መንፈስ ቅዱስና የድኅነት ጸጋ ..... 72
ሀ) የድኅነት ጸጋ ዐውድ ..... 72
ለ) የድኅነት ጸጋ አስፈላጊነት ..... 73
ሐ) የድኅነት ጸጋ አሠራር ..... 79

## ክፍል 2 - መንፈስ ቅዱስና የሰው ድኅነት

ምዕራፍ 84 - የሰው ድኅነት በክርስቶስ መሆኑ ..... 84
ሀ) አማኙ በክርስቶስ ..... 84
ለ) ክርስቶስ በአማኙ ..... 88
ሐ) ክርስቶስ ከአማኙ ጋር ..... 91
መ) አንድነቱን በሚመለከት የተፈጠሩ ስሕተቶች ..... 91

ምዕራፍ 85 - የሰው ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ..... 94
ሀ) ምርጫ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መገኘቱ ..... 95
ለ) ስለ ምርጫ የተሰጡ ልዩ ልዩ አስተያየቶች ..... 99
ሐ) ስለ ምርጫ የሚሰነዘረው ተቃውሞ ..... 104
መ) ምርጫ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ምሥጢራዊ ተመክሮ ..... 107

ምዕራፍ 86 - የግብረ መንፈስ ቅዱስ ቅደም ተከተል ..... 110
ሀ) የድኅነት ቅደም ተከተል መሠረታዊ ጥቅስ ..... 110
ለ) የድኅነት ቅደም ተከተል ውቅር ..... 111
ሐ) የድኅነት ቅደም ተከተል አምስት ክፍሎች ..... 114

ምዕራፍ 87 - የእግዚአብሔር ጥሪና የሰው ዳግም ልደት ..... 117
ሀ) የወንጌል ጥሪ ..... 117
ለ) የሰው ዳግም ልደት ..... 120

ምዕራፍ 88 - ንስሐ መግባትና እምነት ..... 131
ሀ) የንስሐና የእምነት ግንኙነት ..... 132
ለ) የእውነተኛ ንስሐ ደረጃዎች ..... 133
ሐ) የእውነተኛ እምነት ደረጃዎች ..... 137
መ) ንስሐና እምነት የክርስቲያን አኗኗር ባሕርያት መሆናቸው ..... 144

ምዕራፍ 89 - ጽድቅና ቅድስና፣ የቅድስና ደረጃ ..... 148
ሀ) የጽድቅ ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው ..... 153
ለ) የጽድቅ መሠረት የክርስቶስ ደም ነው ..... 154
ሐ) የጽድቅ መገኛ የክርስቶስ ሕይወት ነው ..... 154
መ) የጽድቅ ማረጋገጫ መልካም ሥራ ነው ..... 155
ሠ) የጽድቅ መንገድ እምነት ብቻ ነው ..... 156
ረ) የቅድስና ደረጃ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ነው ..... 162

ምዕራፍ 90 - ልጅነት ............ 165
ሀ) የልጅነት ምንጭ ............ 166
ለ) የልጅነት ሁኔታ ............ 166
ሐ) የልጅነት በረከት ............ 167
መ) የልጅነት ኀላፊነት ............ 170

ምዕራፍ 91 - የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ............ 173
ሀ) የበዓለ ኀምሳ ቀንና አማኙ ............ 174
ለ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአማኙ ሕይወት ............ 177
ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ............ 183
መ) መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ኑሮ ............ 188

ምዕራፍ 92 - ቅድስና ............ 191
ሀ) የቅድስና ዐውድ ............ 195
ለ) ቅድስና በሮም መልእክት ምዕራፍ 6-8 ............ 197
ሐ) ቅድስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ............ 202
መ) ቅድስና፣ ሰባቱ መንፈሳውያን ሐቆች ............ 207
ሠ) ምእመናን ሁሉ ለቅድስና ተጠርተዋል ............ 210
ረ) ምእመናን ሁሉ በአንድ መንገድ ለቅድስና ተጠርተዋል ............ 210
ሰ) ፍጹም የሆነ ቅድስና በዚህ ዓለም አይገኝም ............ 211
ሸ) ምእመናን ሁሉ ለእድገት ተጠርተዋል ............ 211
ቀ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ነፍስ ፍጹም የሚሆነው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው ............ 211
በ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥጋ ፍጹም የሚሆነው በዓለም ፍጻሜ ነው ............ 212

ምዕራፍ 93 - ዋስትና ............ 214
ሀ) ከፍጹም ብክለት ነጻ ስለ መውጣት ............ 214
ለ) የእግዚአብሔር ምርጫ ............ 214
ሐ) ውጤታማ ማስተስረያ ............ 215
መ) ሊቃወሙት የማይቻል ጸጋ ............ 215
ሠ) ለቅዱሳን የሚደረግ ጥበቃ ............ 215

# ጥናት 7 - ትምህርተ ድኅነት
# ክፍል 1 - ትምህርተ ግብረ መንፈስ ቅዱስ
# ምዕራፍ 78 - የድኅነት ዐውድ

«ትምህርተ እግዚአብሔር» የመጀመሪያ መጽሐፋችን፥ «ትምህርተ ክርስቶስ» ሁለተኛ መጽሐፋችን ሲሆን፥ «ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» ደግሞ ሦስተኛ መጽሐፋችን ነው፤ ይህ የትምህርተ መለኮት አዲስና ያልተለመደ አከፋፈል አይደለም፤ ምክንያቱም «የሐዋርያት ሥርዐተ ሃይማኖት» እና «የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት» እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በማለት በሦስት አንቀጾች ትምህርተ ሥላሴን ያብራራሉ (1)::

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሁሉ ወደ ፍጻሜ ማድረስ ሲሆን፥ በተለይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተላቸውን ሰዎች የዘለዓለም ሕይወት እንዲወርሱ ማድረግ ዋና ተግባሩ ነው:: እንግዲህ ግብረ መንፈስ ቅዱስ የድኅነት (2) ዐውድ ነው:: በልዩ ልዩ ስፍራ ላይ የእግዚአብሔር ሥራ በአብ ዐቃጅነት፥ በወልድ አደራጅነትና በመንፈስ ቅዱስ ፈጻሚነት የሚከናወን መሆኑን ገልጠናል ወይም አብ እንደሚያቅድ፥ ወልድ የአብን ዕቅድ እንደሚያደራጅ፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ዕቅዱን ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው ገልጠናል:: ስለዚህ አብ ዐቃጅ፥ ወልድ አደራጅ፥ መንፈስ ቅዱስ ፈጻሚ መባሉ ግልጥ ነው::

በትምህርታችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ከዚህ በፊት አንዳንድ አሳቦችን ጽፈናል፤ በተለይ በትምህርተ አስተርእዮ «መጽሐፍ ቅዱስና እስትንፋሰ እግዚአብሔር» በሚለው በምዕራፍ 7፥ በትምህርተ ሥላሴ ስለ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክነት፥ አካላዊነትና ሥርጸት (ም.25ሐ3)፥ በትምህርተ ፍጥረት ስለ መንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ (ም.30መ) እና በትምህርተ ግብረ ክርስቶስ በኢየሱስ ትሥጉት፥ ጥምቀት፥ አገልግሎትና ትንሣኤ (ም.53 እና 54) ስለ መንፈስ ቅዱስ ሚና አትተናል::

አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በህላዌ፥ በባሕርይ፥ በመለኮትና በፈቃድ አንድ ሲሆኑ፥ በግብር (በሥራ) አንድ ዓላማ አላቸው:: ይሁን እንጂ ይህ አንድነት እያለ በአካል፥ በስምና በግብር ሦስትነት አላቸውና አንድነታቸውን ሳንረሳ፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና የሥራ አፈጻጸም ለየብቻቸው ማጥናት ይገባናል:: ሥራውን ስንመረምርም፥ በፍጥረት (3ኛው ጥናት)፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ በጋርዮሽ ጸጋ፥ በክርስቶስ ምድራዊ ኑሮ፥ በሰው ሕይወትና በዚህ ጥናት ባልተካተቱት በቤተ ክርስቲያንና በሥነ ፍጻሜ ከፍለን ብንመለከተው የበለጠ አመቺ ይሆናል:: ይህን ስናደርግ ግን ሁሉም የተያያዘና የአንድ እግዚአብሔር ሥራ መሆኑን እንገነዘባለን:: ዝርዝር አሳቦች ውስጥ ከመግባታችን በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ነጥቦችን ከአጠቃላይ አመለካከት አንጻር በዐጭሩ እናቀርባለን (3)::

## ሀ) ስለ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት (4)

1. ማንነቱ፤ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን እንደ እግዚአብሔር እስትንፋስ፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ እንደ ክርስቶስ እንደራሴ ይገለጣል::

2. አሠራሩ፤ በብሉይ ኪዳን መንፈሱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሚሠራበት ጊዜ ሕይወትን የሚሰጥ ኀይል ሲሆን፥ በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላይ ያድራል፤ በክርስቶስም ለሚያምኑት ይሰጣል::

3. አገልግሎቱ፤ ሀ) በብሉይ ኪዳን ዘመን

1) መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት የእግዚአብሔር ትእዛዛት እንዲፈጸሙ (ዘፍ. 1+2፤ ኢዮብ 26+13፤ መዝ. 33+6፤ 104+30)+

2) ሰዎች ሕይወት እንዲኖራቸው (ዘፍ. 2+7፤ ኢዮብ 32+8፤ 33+4)+

3) ሰዎች እንደየጥሪአቸው እንዲሠሩ:- ለምሳሌ የኪነ ጥበብ ሠራተኞች (ዘጸ. 31+2-5)+ መሳፍንት (መሳ. 3+10፤ 15+14)+ ነገሥታት (1ሳሙ. 10+6:10፤ 16+13)+

4) ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙና እንዲናገሩ (ሕዝ. 2+2፤ 3+12:14፤ 2ጴጥ. 1+21)+

5) ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲጻፉ (2ጢሞ. 3+16-17)+

6) ሰዎች በውስጣዊ ሕይወታቸው እንዲታደሱና እንዲለወጡ (መዝ. 51+10-11፤ ሕዝ. 36+25-27፤ 37+1-14) አድርጓል::

ለ) በአዲስ ኪዳን ዘመን

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይፈጽም ከነበረው ሥራ ብዙ ነገርን ሲቀጥል ሳለ በተለይም:-

7) ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመሆን እየመሰከረ ለተከታዮቹ ክብሩን በማሳየት (ዮሐ. 15+26፤ 16+14)+

8) ሰዎች ከፊት ይልቅ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲያስተውሉ በማብራራት (1ቆሮ. 2+12-15፤ ኤፌ. 3+16-19)+

9) ዳግመኛ ተወልደው (ዮሐ. 3+5) እየታደሱ እንዲለወጡና ለመንፈሳዊ ምስክርነትና አገልግሎት ሁሉ እንዲበቁ (ሐ.ሥ. 1+8፤ ሮም 8+9-14፤ ቲቶ 3+7)+

10) የእግዚአብሔር ልጆችና ወራሾች መሆናቸውን እንዲያውቁ (ሮም 8+9:15-17፤ ቲቶ 3+5-7) እና ለቤዛ ቀን እንዲታተሙ (ኤፌ. 1+13፤ 4+30) እያደረገ የእግዚአብሔርን ዕቅድና የክርስቶስን መሥዋዕት ዓላማ ይፈጽማል::

4. የበዓለ ኀምሳ ትርጉም፤ በዚህ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ትንሣኤ ያመኑትን በመሙላት የሚከተሉትን እግዚአብሔር እንዳከናወነ አረጋግጧል፤

ሀ) የተሰቀለውን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታና ክርስቶስ ማድረጉን (ሐ.ሥ. 2+36)+

ለ) የአዲስ ኪዳኑን ዘመን ማስገባቱን (ሐ.ሥ. 2+17)+

ሐ) ሕዝቡ ከእስራኤል ብቻ ሳይሆን ሥጋ ከለበሱት ሁሉ መጠራቱን (ሐ.ሥ. 2+17)+

መ) አንዳንድ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ+ ሕዝቡ ሁሉ በመንፈሳዊ ስጦታዎች መሳተፋቸውን (ሐ.ሥ. 2+17-18)+

ሠ) ይህ የመጨረሻ ቀን እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ መቀጠሉን (ሐ.ሥ. 2+19-20)+

ረ) ምእመናን ሁሉ በአንድ መንፈስ በመጠመቃቸው አንድ ሕዝብና አንድ አካል መሆናቸውን (ሐ.ሥ. 2+1፤ ሮም 8+9፤ 1ቆሮ. 12+12-13)+

ሰ) የጌታን ስም በእምነት የሚጠሩ ሁሉ መዳናቸውን (ሐ.ሥ. 2+21፤ ገላ. 3+3-5)::

አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲድን ሦስት ደረጃዎች አሉ፤ በመጀመሪያ ሲያምን ከኀጢአት በደል፥ ቀጥሎ ከኀጢአት ኀይል፥ በመጨረሻ በትንሣኤው በኀጢአት ከመኖር ይድናል:: በዚህ ጥናት እነዚህን ሦስት ደረጃዎች በዝርዝር እንመረምራለን::

## ለ) የግብረ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት ጥቅም

ይህ ትምህርት:-

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሥልጣን፥ ከእምነት እንደ ጽድቅ መንገድና ከአለኝታ እንደ አማኙ መብት በስተኋላ ይቆማል::

2. በአማኙ ሕይወት (ዳግም ልደትና የሰው መመለስ፥ እምነትና አለኝታ፥ ቅድስናና መለወጥ፥ ስጦታዎችና አገልግሎት፥ ማሰላሰልና ጸሎት) እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት (ኅብረት፥ አምልኮት፥ ስብከት፥ ምሥጢራትና ተልእኮ) ሊኖር የሚገባውን ማስተዋል ወስኖ ይመራል::

3. መንፈሳዊ እንቅስቃሴን በልዩ ልዩ አመለካከት በማቃለል፥ የድርጅትን አስተዳደር ለመጠበቅ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን በማዳፈን፥ ደንብንና ልማድን በመጠበቅ፥ የሰውን ልብ ሁኔታ ቸል በማለትና የሃይማኖትን ትውፊት በመከተል፥ መታደስን ባለመፈለግ ቤተ ክርስቲያንን የሚያዳክሙ ዝንባሌዎችን ይቃወማል (5)::

## ሐ) መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ልብ ውስጥ በመኖሩ የሚገኝ ቅድስና

1. መሠረታዊ አሳቡ፤ ቅድስና ኀጢአትን መቃወም ብቻ ወይም ኀጢአትን ወዲያውኑ ማጥፋት ሳይሆን፥ የሰውነትን (የሥጋን) ሥራ እያዳከመ መግደልንና ወደ ክርስቶስ መልክ ተለውጦ ማደግን የሚመለከት ነው፤ ይህም ከኀጢአት ነጻ መውጣት ነው፤ ሮም 8፥11:29::

2. ዘዴው፤ ዝም ብሎ በመቀመጥ የእግዚአብሔርን እንቅስቃሴ መጠበቅ ወይም ያለ ዕረፍት ሁሉንም የሙከራ ዐይነት መፈተሽ ሳይሆን፥ በሰው ልብ ከሚሠራ መንፈስ ጋር በአክብሮት እንደ ቃሉ መተባበር ነው፤ ፊል. 2፥12-13፤ ቆላ. 1፥29::

3. ሕጉ፤ የትእዛዛትን ዝርዝር ማዘጋጀት ወይም ተመችቶና መስሎ መኖር ሳይሆን (6)፥ እንደ እግዚአብሔር ልጅና ወራሽ ሆኖ በነጻነት ሕግ መራመድ ነው::

4. መገምገሚያዎቹ፤ ስለ ሃይማኖት መለፍለፍ ወይም በስጦታዎች መኵራት ሳይሆን፥ በፍቅርና በትሕትና ከኀጢአት ጋር ባለው ትግል ማደግ ነው::

5. ክሥተቶቹ፤ ሀ) በአማኙ ውስጥ ለውጥ አለ፤ ለ) ለውጡ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ሲገናኝ ይገለጣል፤ ይዳብራልም፤ ሐ) ለውጡ የሚመጣው በአማኙ ኀይል ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር ነው፤ መ) ለውጡ እያደገ ሲሄድ፥ ፍጥነቱም ዐይነቱም የተለያዩ ይሆናሉ፤ ሠ) አማኙ ወደ ፊት ባይሄድ፥ ወደ ኋላ በመመለስ ላይ ነው፤ ረ) አማኙ «ማሳዘን» ይችላል፤ ኤፌ. 4፥30፤ ሰ) ሰው መንፈስ ቅዱስን ካሳዘነ ለንስሓ ስፍራ ላያገኝ ይችላል፤ ዕብ. 12፥16-17::

## መ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

1. መሠረታዊ አሳብ፤ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ እንድታድግ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ችሎታዎች ናቸው::

2. ዐይነቶች፤ አንዳንዶች በመንፈስ ቅዱስ የሚቀደሱ በሰው ዘንድ የሚገኙ የተፈጥሮ ችሎታዎች ወይም የጠባይ ሁኔታዎች ሲሆኑ፥ ሌሎች በሰው ተፈጥሮ ወይም ጠባይ ውስጥ ምንም መሠረት የሌላቸው ከመንፈስ ቅዱስ በቀጥታ የሚሰጡ ናቸው::

3. በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ስጦታዎች (ፈውስ፥ ተአምራት፥ በልሳኖች መናገርና መተርጐማቸው፤ 1ቆሮ. 12፥9-11)፤ እነዚህ ስጦታዎች ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የሚቋረጡ ስለ መሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም፤ ሆኖም በአሁኑ ዘመን በየቤተ ክርስቲያኑ የሚታዩ እንግዳ ክሥተቶች ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ የተገኙ ናቸው ማለቱ አጠራጣሪ እንደሆነ መግለጽ አይከብድም::

## ሠ) ግብረ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

አበው በትምህርተ ሥላሴ የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም አምላክነት የተቀበሉት ቢሆንም፥ ከአብና ከወልድ ጋር መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚገናኝ ተከራክረዋል:: አስቀድመን እንዳየነው የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት መንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረጹን ዐወጀ:: ምዕራባውያን ግን ቀስ በቀስ «... እና ከወልድ» ጋር ብለው በመጨመራቸው በእነርሱና በምሥራቃውያን መካከል ለመለያየት ምክንያት ሆነና ከ1017 ዓ.ም. ጀምሮ መለያየቱ ጸንቷል (7)::

አውግስጢኖስ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት በአብና በወልድ መካከል ያለ የፍቅራቸው ትስስር ነው ብሎ በማስተማሩ፥ ለምዕራባውያን መሠረታዊ አሳብ ሆነ:: ከዚህም ጋር የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት እንደሚሠራ ጸጋ ተመለከቱት፤ ሆኖም በዚህ አስተሳሰብ ጸጋ እንደ ኢአካላዊ ረቂቅ ኀይል የሚታሰብ ሆነ::

የተሐድሶ ዘመን መሪዎችና ተከታዮቻቸው በመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ላይ አተኵረዋልና፥ አካላዊነቱ ለክርስቲያናዊ ታዛዥነት መሠረታዊ አስተሳሰብ ሆኗል:: ባለፉት መቶ ዓመታት በጰንጠቆስጤያውያንና በካሪዝማቲኮች ዘንድ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከፍ ያለ አጽንዖት ተሰጥቷል:: ሌሎችም በተሐድሶ ዘመን እንቅስቃሴዎች ወቅት ለሚታየው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ትኵረት ይሰጣሉ:: የተወሰኑት ደግሞ በዓለም ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ሁሉ «የጋርዮሽ ጸጋ» እያሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ሲያስተምሩ፥ አንዳንዶች ግን መንፈስ ቅዱስ በዓለም በሚገኙት ሃይማኖቶች ሁሉ ቀስቃሽ በመሆኑ፥ ሰዎች ሁሉ ወደ አንድ አምላክ እየተጓዙ ወደ አንድ ሃይማኖት ደርሰው በአንድነት እንደሚኖሩ ተስፋ ያደርጋሉ:: እንግዲህ በእውነትም ሆነ በሐሰት በዚህ ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ስም ከቀድሞው የበለጠ ሳይጠቀስ አይቀርም::

## ረ) የመንፈስ ቅዱስ አሠራርና ምልክቶቹ

መንፈስ ቅዱስ እንደ መኪና አይሠራም፤ አካላዊ ቢሆንም እንደ ሰው አይሠራም:: ብዙ ጊዜ ሰው በሥራው፥ በአገሩ ባህል፥ በእድገቱ ገጠመኝ፥ በዘመኑ አስተሳሰብ፥ በግል ተፈጥሮውና ጠባዩ ተወስኖ ይኖራል:: መንፈስ

ቅዱስ ግን በዚህ ዓለም ሁኔታና አካሄድ አይወሰንም:: ሐዋርያው ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲያስተምር፥ «አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፤ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው» ብሏል፤ 1ቆሮ. 12፥6::

በእግዚአብሔር ፊት እያንዳንዱ ሰው ዋጋ አለውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን በየስማቸው ሲጠራቸው፥ እንደየሁኔታቸውና እንደየጠባያቸው ያነጋግራቸውና ይፈውሳቸው ነበር:: መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ የእያንዳንዱን ማንነት ያከብራል:: በዚህ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በጌዴዎንና በሶምሶን ላይ፥ በሳኦልና በዳዊት ላይ ሲወርድ፥ ለኢሳይያስና ለሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ቃል ሲገልጥ፥ ልድያንና የፊልጵስዩስን ወህኒ ቤት ጠባቂ ወደ እምነት ሲመራቸው አሠራሩና የአሠራሩ ውጤት አንድ ዐይነት አልነበሩም::

ብዙ ዐይነት መንፈስ አለ፤ የዓለም መንፈስ አለ፤ ክፉ መንፈስ አለ፤ ሐሰተኛ መንፈስ አለ፤ ጋኔን አለ፤ የእነዚህ ሁሉ መሪ ሰይጣንም አለና ከእነዚህ መናፍስት መካከል መንፈስ ቅዱስንና ሥራውን መለየት ቀላል አይደለም:: ስለዚህ ጉዳይ ስናስብ በመጀመሪያ ማሰብ የሚገባን መንፈስ ቅዱስ፥ ቅዱስ መንፈስ ነውና ሥራው ሁሉ የቅድስና ባሕርይና ውጤት ይኖረዋል:: ሌሎች መናፍስትም ሁሉ የክፋት ጠባይና ውጤት አላቸው:: ሆኖም ሰው ክፉ ስለሆነ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ሲሠራ በውጤቱ ከመልካሙ ጋር ቅዱስ የማይሆን ነገር ሊደባለቅ ይችላል::

አንዳንዶች «እኔ መንፈስ ነኝ» ወይም «አፌ የእግዚአብሔር አፍ፥ እጄ የእግዚአብሔር እጅ... ወዘተ» እያሉ ስሜታቸውና አሳባቸው፥ እንደዚሁም ድርጊታቸውና ንግግራቸው ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበሉት መሆኑን ስለሚያምኑ፥ መታረምንና መገሠጽን አይፈልጉምና አመራራቸውና «ትምህርታቸው» በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲገመገም ፈቃደኞች አይደሉም:: «...ሌሎችም ይለዩአቸው» (... ሌሎቹ ደግሞ የተነገረውን በጥንቃቄ ይመዝኑ)፥ «መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ፤ መልካሙንም ያዙ» የተባሉትን ትእዛዛት ማክበር አይወዱም፤ 1ቆሮ. 14፥29፤ 1ተሰ. 5፥19-21::

አንዳንዶች ደግሞ ምእመናን ሲሰበሰቡ ማናቸውንም ዐይነት ድርጊት፥ በተለይም ጩኸትን፥ ልዩ የሆነ የሰውነት እንቅስቃሴን፥ መዝለልን የመሳሰለ ከተለመደው ውጭ የሆነ ድርጊትን፥ በመሬት ላይ መውደቅን እንደ መንፈሳዊ ነገር ወይም እንደ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ይቈጥሩታል:: በእውነት መንፈስ ቅዱስ ከእነዚህና ከመሳሰሉት እንግዳ ክሥተቶች በስተኋላ ሊኖር ወይም ላይኖር ይችላል፤ እነዚህ ክሥተቶች የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለማስተዋል አይረዱንም (8)::

አንዳንዶች ደግሞ ሰይጣንን ከስብሰባቸው ማባረር እንዳለባቸው ስለሚያስቡ፥ ለዚህ ተግባር ልዩ ልዩ ጸሎትና ሥርዐት ይኖራቸዋል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን፥ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና» ብሎ ለእርሱ መገኘት አጽንዖት ሰጠ እንጂ፥ «ሰይጣን ይገኛል» አላለም፤ ማቴ. 18፥20:: ክርስቶስ ሰይጣንን ከሕዝብ ለማባረር እንደዚህ አላደረገም፤ በዚህ ፈንታ ከትምህርቱ ወይም ከመገኘቱ የተነሣ አጋንንት ሲጮኹ ከሰዎች አስወጥቷቸዋል፤ ሐዋርያትም እንደዚሁ አድርገዋል:: በዚህ ሥርዐት የሚያምኑ ሰዎች ሁለት ነገሮችን የረሱ ይመስላል፤ እነርሱም፥ ሀ) ክርስቶስ ሰይጣንን ያሰረው መሆኑንና ከዚህም የተነሣ እንቅስቃሴው ውሱን መሆኑን

(ማቴ. 12፥29)፥ ለ) ሰይጣን በተንኰልና በኀይል ሰዎችን፥ ምእመናንንም እንኳ በብዙ መንገድ ስለሚፈታተናቸው በአንድ ዐይነት ጸሎት ወይም ሥርዐት ብቻ ሊወገድ እንደሚችል ማሰብ በቂ አለመሆኑን (9)።

ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ» ብሎ የአንደኛውን መልእክት አራተኛ ምዕራፍ ይጀምራል። ከዚህም በኋላ የእውነተኛውን የእግዚአብሔርን ሥራ ምልክቶች ይዘረዝራል፤ ምልክቶቹም የሚከተሉት ናቸው:-

1. መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ከፍ ከፍ ያደርጋልና ሥራውን ያብራራል። ዮሐንስ፥ «የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው» (ቊ.2)። እንግዲህ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፥ ፍጹም ሰው መሆኑን፥ ለሰው ኀጢአት አንድ ጊዜ ለዘለዓለም መሥዋዕት ማቅረቡንና በሁሉ ላይ ጌታ መሆኑን የሚገልጥ፥ በጥሩ አኳኋን የሚያስተምር ሰውና ትምህርቱም ከእግዚአብሔር መንፈስ መሆናቸውን ማመን እንችላለን፤ ዮሐ. 15፥26፤ 16፥14።

2. መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር እንጂ ከዓለም አይደለምና እንደ ዓለም አይናገርም። ዮሐንስ፥ «ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ... እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ፤ ዓለሙም ይሰማቸዋል» ይላል፤ ቊ. 4-5። ሐዋርያው ሁለት ዐይነት መናፍስትን ያነጻጽራል። ዓለም ሲል፥ «... በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዐይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም» ብሎ በመግለጡ፥ ሰው ወይም ትምህርቱ የዓለምን መንፈስ ቢቃወም፥ ከእግዚአብሔር መሆኑን ይገልጣል፤ 1ዮሐ. 2፥15-16።

3. መንፈስ ቅዱስ በይበልጥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠኑ ሰዎችን ይመራል። ዮሐንስ፥ «እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም» ብሏል፤ ቊ.6። መንፈስ ቅዱስ በብዙ ጸሐፊዎች ቢጠቀምም፥ ከጸሐፊዎቹ ሁሉ በስተ ጀርባ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ እርሱ ራሱ ነውና ሰዎችን ወደ ቃሉ ይመራቸዋል፤ እንዲወዱትም ያደርጋቸዋል፤ በዚህ ምክንያት የእነ ዮሐንስን ቃል ይሰማሉ። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል የማይወድ፥ የሚቃወምም ከእግዚአብሔር አይደለም። በእግዚአብሔር የተባረኩ ሰዎች ግን የሐዋርያትን ትምህርት መስማትና መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ይወዳሉ፤ ሐ.ሥ. 2፥42፤ 17፥10-11።

4. መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው። በመሠረቱ ሁለት መንፈሶች አሉ፤ ዮሐንስ፥ «የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን» በማለት ይለያቸዋል፤ ቊ. 6። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን የእውነት መንፈስ ብሎ አከበረው፤ ዮሐ. 14፥17፤ 15፥26፤ 16፥13። ሰው በእውነት መንፈስ መሠረት መራመድን ሲለምድ፥ በዓለም ያለው የሐሰት «ሽታ» ሊሸተው ይችላል። ሐዋርያው፥ «እናንተስ ከእርሱ (ከአብ) የተቀበላችሁት ቅባት (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ) በእናንተ ይኖራል፤ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደሆነ፥ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ» በማለት ጽፏል፤ 1ዮሐ. 2፥27። ሐዋርያው በዚህ መልእክት አንባቢዎቹን

ቢያስተምርም፥ እውነተኛ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት አላቸውና በቅባቱ መሠረት እውነትን ከሐሰት መለየት ይችላሉ።

5. መንፈስ ቅዱስ የፍቅር መንፈስ ነው። በሰው ዘንድ ያለው መንፈስ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው በፍቅር ሲሠራ ሥራው ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያሳያል። ዮሐንስ፥ «ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ...» በማለት ከቍጥር 7-21 የእውነተኛ ፍቅርን ምንነት ያብራራል። በተጨማሪም፥ «እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፤ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኗል። ከመንፈሱ ስለሰጠን፥ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን» በማለት የፍቅርንና የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ መኖር አንድ አድርጎ ይገልጣቸዋል፤ ቍ.12-13። ሐዋርያው ፍቅርን በዚህ ዐይነት በሰፊው ስለገለጠው ከመንፈስ ቅዱስ ምልክቶች ዋና አድርጎ የቈጠረው ይመስላል።

ከእግዚአብሔር የሚገኘው ፍቅር ከጓደኞች የወዳጅነት ፍቅር እጅግ የተለየ ነው፤ በሽፍቶች መካከል እንኳ አንድ ዐይነት ወዳጅነት ሊገኝ ይችላልና። ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን» ብሎ በማስጠንቀቁ ልዩ ልዩ ዐይነት «ፍቅር» እንዳለ ያሳስበናል፤ ሮም 12፥9።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው (ቍ. 8:16) በማለቱ ባሕርዩን ይገልጣልና ማንኛ ውንም ነገር ሲያደርግ፥ ሲፈርድ እንኳ (ቍ. 17) ፍቅሩ አይለየውም። እግዚአብሔር ፍቅሩን የገለጠው በሕይወት እንኖር ዘንድ አንድ ልጁን ወደ ዓለም (ቍ. 9) ስለ ኀጢአታችን ማስተስረያ ይሆን ዘንድ (ቍ. 10) እና የዓለም መድኀኒት ይሆን ዘንድ (ቍ. 14) በመላክ ነው። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን» (ቍ. 19) በማለቱ ለእግዚአብሔር ፍቅር ትክክለኛው አጸፋ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን (ቍ. 16)፥ ቀጥሎም ወንድሞቻችንን መውደድ ነው፤ ቍ. 7:11:12። እግዚአብሔርን መውደድና ሰውን መውደድ የተያያዙ ናቸው፤ ቍ. 20-21። እውነተኛ የሆነ የሰው ፍቅር የሚመነጨው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አይደለም (ቍ. 7:10:19)፤ ይኸውም ይህ ዐይነቱ ፍቅር የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ ከሰው ደግነት የተነሣ የሚገኝ አይደለም ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍቅሩን በዚህ ዐይነት የሚገልጠው ዳግመኛ ለተወለዱ (ቍ. 9) እና በእግዚአብሔር ለሚያምኑት (ቍ. 15) በመሆኑ፥ እግዚአብሔርን ያውቁታል (ቍ. 7:16)፤ ይህ ፍቅር ፍጹም ሲሆን ፍርሀትን ያስቀራል፤ ቍ. 17-18። እግዚአብሔር በእኛ እንደሚኖር፥ እኛም በእርሱ እንደምንኖር የምናውቀው «ከመንፈሱ ስለ ሰጠን» (ቍ. 13) ማለት መንፈስ ቅዱስን ስለሰጠን ነው።

እንግዲህ በመናፍስት መካከል ያለውን ልዩነት ለይተን ማወቅ እንድንችል እግዚአብሔር እነዚህን አምስት ምልክቶች ሰጥቶናል። ከእነዚህ ምልክቶች ውስጥ አንዱ ወይም ሌላው ምልክት ለብቻው ያለ ሊመስለን ይችላል፤ አንዱ ምልክት ብቻ ታይቶ ሌሎች ምልክቶች ካልተገኙ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑ ያጠራጥራል። ሆኖም ምእመናን የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ስለተቀበሉ፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መለየት እንደሚችሉ ተገንዝበው በተስፋ መኖር ይገባቸዋል፤ 1ዮሐ. 2፥26-27።

# ማስታወሻ

(1) «ት.እግ.» ም.27ለ ይመ.

(2) በዚህ ጥናት ደኅንነት በሚለው በተለመደው አማርኛ ቃል ፈንታ ድኅነት የሚለውን የግእዝ ቃል እንጠቀማለን:: ይህንም የምናደርገው፥ 1ኛ የተለመደውን የኢትዮጵያ ትምህርተ መለኮት ጥናት ተከታታይነት ለመጠበቅ፥ 2ኛ የጸጥታ ጉዳይን ከሚመለከተው የ«ደኅንነት» ትርጒምና ከመሳሰሉት ሌሎች ዘመናዊ አባባሎች ትምህርታችንን ለመለየት ነው:: ይህንም ስናደርግ ድኽነት ከሚለው ቃል ድኅነትን ለመለየት ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: በአጠራሩም ልዩነቱ በድኽነት «ኽ» ይጠብቃል፤ በድኅነት ላይ ግን «ኅ» ይላላል:: በሌሎች ጥናቶች ብዙ ጊዜ ደኅንነት የሚለውን ቃል ተጠቅመንበታል::

(3) በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ የተጻፈው በተለይ ባልታተሙት የዶክተር ፓከር የትምህርተ መለኮት ማስታወሻዎች ላይ የተመሠረተ ነው::

(4) ይህ ትምህርት በእንግሊዝኛ Pneumatology ይባላል፤ Pneuma በግሪክ ቋንቋ መንፈስ፥ ነፋስ፥ እስትንፋስ ማለት ነው፤ የ1ኛውን መጽሐፍ መግቢያ ለ7 ይመ.

(5) እነዚህ አራት ዝንባሌዎች በእንግሊዝኛ Nationalism, Institutionalism, Formalism እና Traditionalism ተብለው ሊተረጐሙ ይችላሉ::

(6) እነዚህ ስሕተቶች በእንግሊዝኛ Legalism እና Antinomianism ይባላሉ::

(7) ም.27ሀ5 ይመ.

(8) Jonathan Edwards ከ1740-1742 በቤተ ክርስቲያኑ ስለ ተነሣው የተሐድሶ እንቅስቃሴ ሲጽፍ እነዚህን ክሥተቶች በሰፊው አብራርቷቸዋል:: Jonathan Edwards on Revival በThe Banner of Truth Trust በ1995 የታተመ ገጽ 89-108 ይመ.

(9) ስለ ሰይጣን፥ ስለ አሠራሩና ስለ መሸነፉ ም. 34 ይመ.

# ምዕራፍ 79 - የእግዚአብሔር መንፈስ በብሉይ ኪዳን ዘመን

ንጉሥ ዳዊት፥ «ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ» ብሎ 1000 ዓመት ያህል ላይ ከክርስቶስ በፊት ጸለየ፤ መዝ. 51፥11:: ንጉሥ ዳዊት እንደዚህ ሲጸልይ ምን ዐይነት አሳብ እንዳለው በይበልጥ ለመረዳት የ«ቅዱስ» እና የ«መንፈስ» ትርጉም ምን እንደሚመስል ማጥናት ይረዳናል:: ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ ጥሪው በቀረበበት በአስፈሪው ራእይ ውስጥ እግዚአብሔር በቅድስናው ሲገለጥለት፥ «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» የሚሉትን የሱራፌልን ቃላት ሰማ:: ነቢዩ በራእዩ የእግዚአብሔርን ልዕልና፥ ግርማና ክብር በከፊል ተረዳ:: በታላቁ መቅደስ ውስጥ ነቢዩ ኢሳይያስ እጅግ ታናሽ ሰው ነበረ፤ የእግዚአብሔር ልብስ ዘርፍ ግን ሕንጻውን ሁሉ ሞላና እግዚአብሔር ራሱ ከመቅደሱ በላይ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር:: ሱራፌል በእግዚአብሔር አጠገብ ሆነው ሲያገለግሉት፥ የእግዚአብሔርን ፊት ለማየት እንኳ አይደፍሩምና በሁለት ክንፎች ፊቶቻቸውን ይሸፍኑ ነበር:: ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ በማለታቸው፥ እግዚአብሔር ከእነርሱና ከፍጥረት ሁሉ በላይ የተለየ በመሆኑ ወደሉት:: ድምፃቸውም ከፍ ያለ ስለነበረ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ፤ ቤቱንም ጢስ ሞላበት:: ነቢዩ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በክብሩ ተገልጦ በማየቱ የእርሱን ታላቅነት፥ የራሱንም ታናሽነት እየተረዳ፥ የገዛ ራሱና የሕዝቡ ኀጢአት ርኵሰት ተሰምቶት «ጠፍቻለሁና ወዮልኝ» አለ፤ ኢሳ. 6፥1-5:: እንግዲህ «ቅዱስ» የሚለው ቃል የተለየና ከፍ ያለ ማለት ነው፤ በግብረገባዊነቱም ንጽሕናን ያመለክታል::

«መንፈስ» ተብለው የሚተረጐሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ሩአኽ (ዕብራይስጥ) እና ፕኑማ (ግሪክ) ናቸው (1):: ቃላቱ የተመሠረቱት ከነፋስ ወይም ከትንፋሽ አወጣጥ በመሆኑ፥ በእንቅስቃሴ ላይ ያለውን አየር ያመለክታሉ::

በግሪክ ፍልስፍና ፕኑማ እጅግ እንደተጠለለና እንደተጣራ ቍሳዊ ነገር ይታሰብ ነበር:: ለምሳሌ፥ ኢስጦኢኮች በፍልስፍናቸው ፕኑማ እንደ ነፍስ ሁነት ሆኖ ሰውነትን ሁሉ እንደሚዳስስ ጒልበት ሰጪ ኀይልና ሕይወትን እንደሚሰጥ ነገር ቈጠሩት:: ብዙ ሰዎች ስለ ሩአኽ ሲናገሩ ዋና አሳባቸው ኢቍሳዊነት ቢሆንም፥ በብሉይ ኪዳን ቃሉ አየር በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ያሳስባል:: ለምሳሌ፥ «እነሆም፥ ዐውሎ ነፋስ («ሩአኽ») ከምድረ በዳ መጥቶ የቤቱን አራት ማዕዘን መታው» ተብሎ ተጽፏል፤ ኢዮብ 1፥19:: እንደዚሁም በሰዎች ዘንድ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ክብር ሁሉ ስታይ ሩአኽ አልባ ሆነች (የምትናገረው ጠፋባት)፤ 1ነገ. 10፥5:: ክፉ ሰዎችም በእግዚአብሔር ሩአኽ ይጠፋሉ፤ ኢዮብ 4፥9:: እዚህ ላይ ዋናው አሳብ ሕያው ጒልበት ሰጪ ኀይል እንጂ ኢቍሳዊነት አይደለም:: ኢሳይያስ፥ «ግብጻውያን ሰዎች እንጂ አምላክ አይደሉም፤ ፈረሶቻቸውም ሥጋ እንጂ «ሩአኽ» አይደሉም» ይላል፤ ኢሳ. 31፥3:: ትኵረቱ በቍሳዊነትና በኢቍሳዊነት መካከል ባለው ልዩነት ላይ ሳይሆን፥ በድክመትና በጒልበት ሰጪ ኀይል መካከል ነው::

የሩአኽ ሥራ ውጤት ከባሕርዩ ጋር ይስማማል:: ሩአኽ በላያቸው ሲወርድ፥ ሰዎች ከተፈጥሯቸው በተለየ ኀይል ተይዘው በሰዎች መካከል ያልተለመዱ ነገሮችን ያደርጋሉ፤ ደካሞች ለሥራ ይነሣሉ፤ ልዩ ሰብአዊ ችሎታዎች ይታያሉ፤ ተመስጦም ሊገኝ ይችላል:: የእግዚአብሔር ሩአኽ

ለፍጥረትም ሆነ ለፍርድ የእግዚአብሔር ዓላማ የሚፈጸምበት፥ ሊቃወሙት የማይቻል የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው:: በሩአኹ የሰማይ ሠራዊት ተፈጠረ (መዝ. 33፥6)፤ ጎቶንያልና ሶምሶን ኀይልን አገኙ (መሳ. 3፥10፤ 14፥6)፤ ነቢያትም ተነጥቀው በሌሎች ስፍራዎች ተገኙ፤ 1ነገ. 18፥12፤ ሕዝ. 3፥12:14፤ 11፥1:: ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ሩአኽ ሲገልጥ፥ «የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይነፍስበታልና ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ በእውነት ሕዝቡ ሣር ነው»፤ «እርሱ የእግዚአብሔር ሩአኽ እንደሚነዳው እንደ ጐርፍ ፈሳሽ ይመጣል» ብሎ ሊቃወሙት የማይቻል ኀይል አድርጎ ያሳየዋል፤ ኢሳ. 40፥7፤ 59፥19::

እንግዲህ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ጥቅሶች ሩአኽ የእግዚአብሔርን ጉልበት ሰጪ ኀይል ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር በአካላዊ መንገድ መገናኘቱንም ጭምር ያሳያል:: ይህም አንድ ትልቅ ጥያቄ ያስነሣል፤ ጥያቄውም እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን አሠራር ብቻ ይገልጣሉ ወይስ በእግዚአብሔር ህላዌ ዘንድ ልዩ አካላት መኖራቸውንም ያሳያሉ? የሚል ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ እነዚህ ጥቅሶች ለትምህርተ ሥላሴ መሠረት ሊሆኑ ይችላሉን? ይህን ለማጥናት በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሩአኽ ሥራ መመርመር ይገባናል (2)::

## ሀ) ሩአኽና ፍጥረት

«ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም (ምድርም ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች)፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔር ሩአኽ በውሃ (በውሆች) ላይ ሰፍፎ (ይረብብ፥ ይሰፍፍ) ነበር»፤ ዘፍ. 1፥2:: አንዳንዶች በዚህ ጥቅስ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ አይታያቸውም:: ሆኖም በቍጥር አንድ ላይ፥ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» እና በቍጥር ሦስት «እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ» ስለሚል፥ እግዚአብሔር በሩአኹ አማካይነት የፍጥረት ሥራውን ፍጻሜ ላይ እንዳደረሰ ማሰብ አመክንዮታዊ ይመስላል:: «ባዶ» እና «ሰፈፈ» ተብለው የሚተረጐሙት የዕብራይስጥ ቃላትም በኦሪት ዘዳግም 32፥10-11 ላይ በአንድነት ይገኛሉ:: እዚያ ሕዝቡን ከግብጽ የሚያወጣ «እርሱን (ሕዝቡን) በምድረ በዳ፥ ባዶና ጭው ባለ በረሓ ውስጥ አገኘው... ንስር... በጫጩቶቿ ላይ እንደምትረብብ (እንደምትሰፍፍ)...» (አ.መ.ት.) ብሎ ሕዝቡን «ባዶ» በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚጠብቅ በፍጥረት ምሳሌነት ይገልጣል:: የእግዚአብሔር ሩአኽ ባልተፈጸመ ፍጥረት ላይ እንደሰፈፈ ሁሉ፥ ወደ ሙሉ ድኅነት ባልደረሰ ሕዝብም ላይ በመሰፈፉ በእግዚአብሔር ሩአኽ የፍጥረትና የቤዛነት ሥራ ግንኙነት መኖሩ እዚህ ላይ ይታያል:: ኢዮብም፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ (ሩአኽ) ፈጠረኝ፤ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ» ሲል ኦሪት ዘፍጥረት 1፥2ን እና 2፥7ን ያሳስባል፤ ኢዮብ 33፥4:: መዝሙረኛው፥ «ሩአኽን ትልካለህ ይፈጠራሉም» ብሎ የፍጥረትን ታሪክ ያሳስባል፤ መዝ. 104፥30::

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በፍጥረት ስለ ሩአኽ ሥራ ብዙ ጥቅሶችን አናገኝምና ሥራው ብዙ አልተብራራም:: ሆኖም የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ የተጀመረውን ማደራጀትና መፈጸም መሆኑ በፍጥረት ታሪክ ተገልጧል:: ይህ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሚና መሆኑ በአዲስ ኪዳን ይታያል:: በአዲስ ኪዳን አብ ይልካል፤ ወልድ ይመጣል፤ መንፈሱ ወልድን ያጸድቃል (1ጢሞ. 3፥16)፤ አብም ያቅዳል፤ ወልድ ለሰዎች ይሠዋል፤ መንፈስም ሰዎችን ይቀድሳቸዋል፤ 1ጴጥ. 1፥1-2::

### ለ) ሩአኽና መግቦተ እግዚአብሔር

ሩአኽ የነፋስን ወይም የአየርን እንቅስቃሴ በማሳሰብ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ያንጸባርቃል:: የእግዚአብሔር ሩአኽ በሕዝቡ መካከል በኀይል የሚገኝበትን ሁኔታ ይገልጣል:: ሕዝቅኤል፥ «ፊቴንም ከእነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አልሸሽግም፤ መንፈሴንም በእስራኤል ቤት ላይ አፍስሻለሁና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር» በማለቱ በእግዚአብሔር ፊትና በእግዚአብሔር መንፈስ መካከል የተቀራረበ የአሳብ ግንኙነት እንዳለ ያሳያል፤ ሕዝ. 39፥29 (ም. 37፥1-14 እንደዚህ ያለውን መንፈስን የማፍሰስ ተግባር በትንቢት መልክ ይነግራል)::

የእግዚአብሔር ሩአኽ በመግቦተ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መንገድ በኀይል ይገለጣል:: ሰዎች በሩአኽ ኀይል ከተፈጥሮታዊ ጉልበትና ማስተዋል ባሻገር ብዙ ነገርን ያደርጋሉ:: ፈርዖን፥ «በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ (ሩአኽ) ያለበትን እንደዚህ ያለ ሰው እናገኛለንን?... እንደ አንተ ያለ ብልኀ ዐዋቂም ሰው የለም፤ እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሃል» ብሎ ዮሴፍን በመንግሥቱ ጉዳይ ሁሉ ላይ ሾመው፤ ዘፍ. 41፥38-39:: ከአንድ ሺህ ሦስት መቶ ዓመታት በኋላም ለዳንኤል በንጉሥ ብልጣሶር ፊት እንደሚከተለው ተመሰከረለት፥ «መልካም መንፈስ፥ ዕውቀትም ማስተዋልም፥ ሕልምንም መተርጐም፥ እንቆቅልሽንም መግለጥ፥ የተቋጠረውንም መፍታት... በዳንኤል ዘንድ ተገኝቷል»፤ ዳን. 5፥12:: በዮሴፍ፥ በዳንኤልም ላይ ለመንግሥታዊ አስተዳደር የታየው ብቃት በሚመጣው መሲሕ ላይ በሙላት እንደሚገኝ ለማረጋገጥ፥ «...የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኀይል መንፈስ፥ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል:: እግዚአብሔርን በመፍራት ደስታውን ያያል:: ዐይኑም እንደምታይ አይፈርድም፤ ጆሮውም እንደምትሰማ አይበይንም፤ ነገር ግን ለድኾች በጽድቅ ይፈርዳል፤ ለምድርም የዋሆች በቅንነት ይበይናል፤ በአፉም በትር ምድርን ይመታል፤ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል:: የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ፥ የጐኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል» በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ተናገረ፤ ኢሳ. 11፥1-5::

እግዚአብሔር ከግብጽ በጠራው ሕዝብ መካከል ዕቅዱ እንዲፈጸም መጀመሪያ ለሙሴ፥ በኋላም ለሰባው ሽማግሌዎች እንዲበይኑ አምላካዊው መንፈስ ተሰጠ፤ ዘኍ. 11፥25:: እንግዲህ የእግዚአብሔር መንፈስ ላልተደራጀ ፍጥረት ሥርዐትና ግብ እንዳደረገ ሁሉ፥ ለሕዝቡም አዲስ ሆኖ ከአደጋ አፋፍ ላይ ሲሆን፥ ማኅበራዊ ትርምስ ውስጥ እንዳይገባ ትክክለኛ አስተዳደርን፥ ሥርዐትንና እድገትን ከግብጽ በወጡት ወገኖች መካከል አደራጀ፤ ኢሳ. 63፥7-14 ይመ.::

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ዕቅድ እየተከታተለ ሳለ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ እንደ ባስልኤልና እንደ ኤልያብ ላሉት ሰዎች የኪነ ጥበብ ስጦታዎችን ሰጠ፤ ዘጸ. 31፥1-11፤ 35፥30-35:: በመገናኛ ድንኳኑ የእነርሱ ሥራ የውበትን ደስታ ለሰዎች ሲሰጥ፥ የፈጣሪውን አስተዳደርና ክብር፥ ለፍጥረቱም ያሉትን ግቦች ገለጠ:: ከዚህም የተነሣ የአዲስ ፍጥረትን ሥራ በሕዝቡ ዘንድ መጀመር እንደሚገባ ታላቅ ፍንጭ ተሰጠ:: በገነት፥ በመገናኛ ድንኳንና በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን የሚያመልክ በቅድስናው ስፍራ የቅድስና ውበት ያገኛል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ውበት ወደ ማስላሰል ይመራል፤ 1ዜ.መ. 16፥29፤ መዝ.

96፥9:: በመጨረሻው ቤተ መቅደስም በእግዚአብሔር መንፈስ በተሞላው ሰው ይህ ምሳሌነት ፍጻሜውን አገኘ፤ ዮሐ. 2፥19-22፤ 3፥34::

## ሐ) ሩአኽና አዲስ ልደት

ከዚህ በላይ እንዳየነው የእግዚአብሔር መንፈስ ስጦታዎች የሕዝቡን ብሔራዊ አስተዳደር በተሳካ ሁኔታ እንዲፈጸም አስቻሉ:: ከዚህም ጋር ሥራው ግብረገባዊና ድኅነታዊ ነው፤ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ «ቅዱስ መንፈስህ» ተብሏልና፤ መዝ. 51፥11:: ኢሳይያስ ከግብጽ የመውጣትን ታሪክ ሲያብራራ ይህን ሐቅ እንደሚከተለው ይገልጸዋል:-

«...በፍቅሩና በምሕረቱ ዋጃቸው... እነርሱ ግን ዐመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አሳዘኑ... ከዚያም ሕዝቡ የጥንቱን ዘመን የሙሴንና የሕዝቡን ጊዜ እንዲህ በማለት አስታወሱ... ቅዱስ መንፈሱንም በመካከላቸው ያኖረ የት አለ?»፤ ኢሳ. 63፥7-14 አ.መ.ት. ይመ. በተለይም ቍ. 9-11:: እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በምድረ በዳ በሕዝቡ መካከል እንደኖረ ያሳያል (ቍ.11)፤ ሕዝቡንም መራ (ቍ.13-14)፤ ሆኖም «ዐመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አሳዘኑ» (ቍ.10)::

በዚህ አሳብ ምናልባት ከሌሎች የብሉይ ኪዳን አንቀጾች ይልቅ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ኀይል (ወይም እንደ እግዚአብሔር ክንድ) ሳይሆን፥ ራሱን እንደቻለ እንደ አንድ አካላዊ መንፈስ ይገለጣል:: ይህም የሚሆነው በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ነው፤ 1ኛ፥ ጥቅሱ እግዚአብሔር በሰማያትና በሕዝቡ መካከል ሲኖር ልዩነት እንዳለ፤ 2ኛ፥ ማሳዘን የሚለው ግስ የሚያሳዝንና የሚያዝን አካላት እንዳሉ ያሳስባል:: ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» በማለት የኢሳይያስን ቃል በአካላዊ አገላለጥ የተመለከተው ይመስላል፤ ኤፌ. 4፥30::

ንጉሥ ዳዊት በማመንዘሩ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ሲወሰድበት ሥጋት ውስጥ የገባው፥ እንደ ንጉሥ ሳኦል ተነውሮ እንዳይወድቅ ሳይሆን አይቀርም፤ 1ሳሙ. 16፥14:: ሆኖም ፍርሀቱ ይህ ብቻ አልነበረም፤ ምክንያቱም ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በማደሩ ብቻ በልቡ የንጽሕናንና የመዳንን ደስታ፥ በመንፈሱም ቅንነትንና ታዛዥነትን (እሽታን) ማወቅ ይችል ነበር፤ መዝ. 51፥10-12::

የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ በሰው ልብ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዴት እንደነበረ ስንመረምር፥ አመለካከታችን ሚዛናዊ መሆን አለበት:: በአንድ በኩል ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትሥጉት፥ መሥዋዕታዊ ሞት፥ ትንሣኤ፥ ዕርገትና በአብ ቀኝ መቀመጥ የተነሣ የአዲስ ኪዳኑ አሠራር ከብሉይ ኪዳኑ አሠራር እጅግ የተለየና ከፍ ያለ መሆኑን መካድ አንችልም:: ይህም በበዓለ ኀምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ይታያል፤ በመልእክታቱም ውስጥ ተብራርቷል:: በሌላ በኩል ግን በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ተከታታይነትና ተያያዥነት እንዳለ መካድ አይገባንም፤ ምክንያቱም ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን አዲስን ልብ አገኙ፤ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬም በሕይወታቸው ታይቶ ለእኛ ምሳሌዎች ሆኑ::

እግዚአብሔር የሚፈልገው ፍሬ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ብቻ ይገኛል፤ «የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው» ተብሏል፤ ገላ. 5፥22-23:: ይህ ዐይነት

ፍሬ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ሕይወትም ይታያል። ወደ ጽድቅ የሚያደርስ እምነት በአብርሃምና በዳዊት ታሪክ ለአብነት ተጠቅሷል፤ በተለይ ሮም ምዕራፍ 4 ይህን ይገልጻል። የሰዎች መንፈሳዊ አኗኗር በብዙ አንቀጾች ውስጥ አድናቆት ተሰጥቶት ይታያል፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 11፤ ያዕቆብ 2፥14-26፤ 5፥10-11:17-18 ይመ.። እነዚያ ሰዎች በመንፈስ መመላለስ እንዴት እንደሆነ ዐወቁ። ከዚህም የተነሣ የአዲስ ኪዳን ምእመናን ማንኛውም ችግር አጋጥሟቸው መዝሙረ ዳዊትን ሲያነቡ፥ ለችግራቸው የሆነ ልመናን አያጡም፤ ለማመስገን ሲፈልጉም በሰፊ ልብ ስሜታቸውን በተጻፉት ቃላት ተጠቅመው ይገልጻሉ፤ እነዳዊት የቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ በልባቸው ዐውቀውት ነበርና።

አንዳንድ ሰዎች ዳግመኛ መወለድ (ወይም አዲስ ልደት) በክርስቶስ ሥራ ላይ የተመሠረተ ነውና በአዲስ ኪዳን ዘመን ብቻ ይታወቃል ይላሉ፤ ዮሐ. 3፥12-15። ክርስቶስም፥ «በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል» ብሎ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ተናገረ፤ ማቴ. 11፥11። እውነት ነው፤ ዳግመኛ መወለድ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር የተያያዘ መሆኑን እንማራለን (1ጴጥ. 1፥3-5)፤ ሆኖም የብሉይ ኪዳን ዘመን ምእመናን በእምነት መንገድ የዳኑት በክርስቶስ ሥራ ነበረ። እነርሱ ይህን ያዩት ከሩቅ ነው፤ ዮሐ. 8፥56። ክርስቶስም፥ «ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ» እና «አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን?» በማለቱ ዳግመኛ ስለ መወለድ የተሰጠው ትምህርት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም መገለጡን ለኒቆዲሞስ አሳሰበው፤ ዮሐ. 3፥7-10። ሙሴ፥ «በሕይወትም እንድትኖር አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እንድትወድድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን፥ የዘርህንም ልብ ይገርዛል» ብሎ በማስተማሩ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለድኅነት በሰው ልብ ውስጥ አዲስ ልደትን የሚመስል ሥራ ይሠራ እንደነበር አሳየ። ይህንም በማድረጉ ዳግመኛ መወለድ በክርስቶስ ትንሣኤ ሕይወት መሳተፍ ነው ለሚለው የአዲስ ኪዳን ትምህርት በር ከፈተ፤ ዘዳ. 30፥6። ነቢዩ ሕዝቅኤልም ሰዎች ከኀጢአታቸው ሲመለሱ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሠራውን ሥራ ለመግለጥ፥ «...አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ...» በማለት የዳግመኛ መወለድን ሥራ በዝርዝር አብራርቶታል፤ ሕዝ. 36፥24-28። ኒቆዲሞስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ሲገናኝ፥ የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ ከልቡ ባለማወቁ የክርስቶስን ትምህርት ማስተዋል የከበደበት ይመስላል። ሐዋርያት ግን ብዙ ነገርን ገና ባያስተውሉም፥ ክርስቶስን ሲከተሉ የልብ ለውጥ መኖሩን ያውቁ ነበር፤ ማቴ. 16፥15-17፤ ዮሐ. 6፥66-69፤15፥3።

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለውን ተከታታይነት ስንመረምር፥ በሁለት ቃል ኪዳኖች መካከል ከፍ ያለ ልዩነት እንዳለ መርሳት የለብንም፤ ይህንም ልዩነት ለወደፊት በዝርዝር እናጠናዋለን።

## መ) ሩእኸና የእግዚአብሔር ቃል

ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ፥ «ከእነርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር፤ በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ በአፍህም ውስጥ ያደረግሁት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ ከአፍህ፥ ከዘርህም አፍ፥ ከዘር ዘርህም አፍ አያልፍም ይላል እግዚአብሔር» ብሎ በመጻፍ፥ የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ቃል የተያያዙ መሆናቸውን አረጋገጠ፤ ኢሳ. 59፥21። ከኢሳይያስ

በፊትም ንጉሥ ዳዊት በመጨረሻ ቃሉ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፤ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ» ብሎ ይህን ግንኙነት ማወቁን አረጋገጠ፤ 2ሳሙ. 23፥2:: ደግሞም እግዚአብሔር ለኤርምያስ፥ «እነሆ፥ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ» በማለት በዐጭሩ እስትንፋስ እግዚአብሔርን (3) ገልጦታል፤ ኤር. 1፥9:: ኤርምያስም የእግዚአብሔርን ቃል በተናገረ ጊዜ ብዙ ተቃዋሚዎች ሲነሡበት፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆን የተስፋ ቃልን ሰጠው፤ ኤር. 1፥19::

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ትኩረቱ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር ላይ ሳይሆን፥ በቃሉ ፍሬ አሳብ ላይ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲጽፍ መዳን የሚገኝበት ጥበብ እንዳለባቸውና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ የተዘጋጀ እንዲሆን ለትምህርትና ለተግሣጽ፥ ልብንም ለማቅናት፥ በጽድቅም ላለው ምክር ጠቃሚ እንደሆነ ያሳስባል፤ 2ጢሞ. 3፥15-17:: ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል መናገር (እና መጻፍ) እንዴት ቻሉ? ተብሎ ቢጠየቅም፥ መልሱ «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» የሚለው ነው፤ 2ጴጥ. 1፥21:: እንግዲህ ሐዋርያት ስለ ብሉይ ኪዳን ዘመን አስተርእዮ ሲናገሩ፥ የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ በሚናገሩ የእግዚአብሔር ሰዎች አማካይነት የመጣ መሆኑን አረጋግጠዋል:: ሐዋርያትም የእስትንፋሰ እግዚአብሔርን ትምህርት ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ወረሱት እንጂ እነርሱ አልጀመሩትም::

የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው መንፈስ ላይ ዐድሮ፥ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል እስኪናገርና እስኪጽፍ ድረስ የአመራሩ ሁኔታ ምሥጢር ነው:: በፍጥረት፥ በትሥጉትና በድኅነት የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምሥጢራዊ እንደሚሆን ሁሉ (መዝ. 139፥7-16፤ ሉቃ. 1፥35፤ ዮሐ. 3፥8-9)፥ በአስተርእዮም እንዲሁ ምሥጢራዊ ነው:: ሆኖም የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ውጤት በፍጥረት፥ በትሥጉትና በድኅነት እንደሚታይ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ቃልም በእጃችን እንዳለ እናውቃለን::

እግዚአብሔር በህልሞች፥ በራእዮች፥ በግል አብርሆትና በሰው ጥናት፥ በተለመዱትና ባልተለመዱት የመግቦተ እግዚአብሔር ተግባራት ራሱን ይገልጣል (4):: እግዚአብሔር በሰው አማካይነት ሲሠራ፥ የሰው ልዩ ጠባይ ስለማይጠፋ፥ የግል ጠባይ በአነጋገር፥ በአጻጻፍና በድርጊት በይበልጥ ይታያል:: ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በእነዚህ ሰዎች ላይ ሲያድር የሚናገሩትና የሚጽፉት የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: ይሁን እንጂ የአስተርእዮ መንገድ ምሥጢር ነው፤ መጽሐፈ መክብብ እንደሚለው:- «የነፋስን መንገድ እንደማታውቅ፥ ሕይወት ወይም መንፈስ በእናት ማሕፀን ውስጥ ወደሚገኘው አካል እንዴት እንደሚገባም እንደማታውቅ ሁሉ፥ ሁሉን ሠሪ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራም ማስተዋል አትችልም»፤ መክ. 11፥5 አ.መ.ት.::

## ሠ) ሩአኽና አካልነቱ

በጠቅላላው ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሩአኽ ሥራ ከእግዚአብሔር ህላዌ ጋር የተያያዘ መሆኑ እንደተገለጠ አይተናል:: አንዳንድ ጊዜ ይህ ሥራ በዕቅዱ መሠረት በሰው ላይ ሲፈጸም እንደ እግዚአብሔር ኀይል በጉልበት ይገለጣል፤ መሳ. 11፥29፤ 14፥6፤ 1ሳሙ. 16፥13:: በሌሎች ጊዜያት ግን ይህ ኀይል ወደ ሰው ገብቶ ከሰው መንፈስ ጋር ይገናኛል፤ ግንኙነቱም አካላዊ ሆኗል፤ መሳ. 6፥34፤

2ሳሙ. 23፥2፤ 1ዜ.መ. 12፥18፤ 2ዜ.መ. 24፥20:: እንግዲህ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ቅዱስ ግብረገባዊ ትስስር ያበጃልና አካሄዳቸው ሊያሳዝነው ይችላል::

ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስና የእግዚአብሔር ኀይል አንድ ነገር አይደለም:: ሆኖም የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት መልክ ነው ወይስ በሥላሴ ትምህርት እንደሚታየው በእግዚአብሔር ዘንድ ራሱን የቻለ አካል ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም::

ከሐዋርያት ዘመን በኋላ በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንፈስ አካልነትና የወልድን አካልነት በብሉይ ኪዳን ትምህርት ውስጥ ማግኘት ከፍ ያለ ፍላጎት ነበረ፤ ምክንያቱም የዚህ መገኘት የአይሁድን ተቃውሞ መሠረተ ቢስ ያደርገዋል:: ከዚህም የተነሣ የዚህ አመለካከት ባለቤት የሆኑት «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» የሚለው አረፍተ ነገርና ተመሳሳይ አንቀጾች በእግዚአብሔር ዘንድ ከአንድ በላይ የቍጥር ብዛት እንዳለ ያሳያሉ ለማለት ቸኰሉ (5):: የተሐድሶ ሊቃውንት ግን ማናቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ በግልጥ የሚያስተምረውንና በአመክንዮታዊ አስተሳሰብ የሚያስከትለውን ውጤት ለትምህርተ መለኮታቸው ተቀበሉት:: ሆኖም ሊበራሎች በአስተሳሰባቸው መሠረት አጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርተ መለኮትን ለማግኘት እንደሚቻል ሰዎችን እንዲጠራጠሩ በማድረግ፥ ብሉይ ኪዳን የሩአኽን አካልነት የሚያሳይ ፍንጭ እንኳ አይሰጥም ወደ ማለት ብዙ ሰዎችን አድርሰዋል::

1) የሩአኽ ሥራ አምላካዊ ነውን? መልሱ አዎ! ነው የሚለው ነው::

2) የሩአኽ ሥራ አካላዊ ነውን? የዚህም መልስ አዎ! የሚለው ነው፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን ሲመራ፥ በአመክንዮታውያን ቃላትና ምክንያቶች የሚናገር ራሱ ሩአኽ አካላዊ ነው::

3) የሩአኽ ሥራ የተለየ የአንድ አካል ሥራ ነው ወይስ የእግዚአብሔር አንድ ዐይነት አሠራር? እኛም የአዲስ ኪዳን ሰዎች በመሆናችን በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ ሲል፥ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እናውቃለን:: ጥያቄው ግን ብሉይ ኪዳንን ብቻ በማንበብ፥ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ሲል ከሦስቱ አካላት አንዱ መሆኑን ማወቅ ይችላልን? የሚለው ነው:: ኢሳይያስ ስለ መሲሑ ሲናገር፥ «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፤ ከሥሩም ቍጥቋጥ ያፈራል:: የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኀይል፥ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል...» በማለቱ የእግዚአብሔር መንፈስ በሙላቱ የሚገለጠው በመሲሑ ላይ ሲያርፍ መሆኑን እናስተውላለን፤ ኢሳ. 11፥1-2:: ይህ ትንቢት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተፈጸመ ለእኛ ለአዲስ ኪዳን ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ማንነትና ሥራ በሙላቱ ተገልጧል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቶስን በትንቢት አገልግሎታቸው ስለገለጡት የብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደሚከተለው አተተ፤ «ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፥ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር:: ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ»፤ 1ጴጥ. 1፥10-12:: እንግዲህ ለእነዚህ ነቢያት ስለ ክርስቶስ መምጣት፥ መከራና ክብር ብዙ ነገር አልተገለጠላቸውም፤ እንደዚሁም ስለ እግዚአብሔር መንፈስ አካልነትና ሥራ ብዙ ነገር ለእነርሱ ገና

ግልጥ አለመሆኑ አስገራሚ አይደለም፤ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ በሙላቱ አልተገለጠምና:: በዚህ አስተሳሰብ መሠረት እስከ በዓለ ኀምሳ ቀን ድረስ የኢዩኤል 2፥28-32 እና የሕዝቅኤል 36፥25-27 አንቀጾችን ትንቢቶች ሐዋርያት የተረዷቸው አይመስልም::

ቢ.ቢ. ዋርፊልድ ስለ ቅድስት ሥላሴ የጻፈው ሚዛናዊ ምሳሌ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካልነት በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን አስተሳሰብ እንድናስተውል ሊረዳን ይችላል (6):-

«ብሉይ ኪዳን በብዙ ሀብት ያጌጠ ነገር ግን በደበዘዘ ብርሃን የሚታይ አዳራሽን ሊመስል ይችላል:: ጥሩ መብራት ሲበራ ቀድሞ ያልነበረውን ነገር ለአዳራሹ ምንም አይጨምርም፤ ሆኖም አስቀድሞ በጭንቅ የታየውንና ያልተለየውንም እንኳ ቢሆን በግልጥ እንዲታይ ያደርጋል:: የቅድስት ሥላሴ ምሥጢር በብሉይ ኪዳን ጕልቶ ባይገለጥም፥ ከብሉይ ኪዳን አስተርእዮ በስተ ጀርባ አለ፤ ዐልፎ ዐልፎ እንዲያውም ለመታየት የሚቀረው ትንሽ ብቻ ነው:: እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን አስተርእዮ በሚከተለውም ዘመን ሳይለወጥ እንዲሁ ይፈጸማል፤ ይሰፋል፤ ይስፋፋልም::»

## ረ) ሩኣኽና ክርስቶስ

በብሉይ ኪዳን አስተርእዮ ስለ አብ (ዮሐ. 1፥18፤ 14፥6) እና ስለ ወልድ (ዕብ. 1፥1-2፤ 11፥39-40፤ ኤፌ. 3፥1-13) ያልተሟላ ሁኔታ እንደነበረ ሁሉ፥ ስለ ሩኣኽም ሥራው ቢታይም እንኳ ማንነቱ በሚገባ የተብራራ አልነበረም:: ነቢያት የተቀበሉት አስተርእዮ ውሱን እንደነበር ዐወቁ (1ጴጥ. 1፥10-12)፤ ሙሴም በእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ላይ መንፈሱ እንዲወርድ ቢመኝም፥ የተመኘው እውን የሆነው ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በኋላ ነው፤ ዘኍ. 11፥29:: ነቢያትም በዓለም ሰዎች ሁሉ ላይና በእያንዳንዱ አማኝ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚወርድበትን የአዲስ ኪዳንን ዘመን ይጠባበቁ ነበር፤ ኢዩ. 2፥28-32፤ ሕዝ. 36፥24-32::

የእግዚአብሔር መንፈስ ማንነት በብሉይ ኪዳን ዘመን በሙላት ለምን አልተገለጠም? ለሚለው ጥያቄ መልስ በአዲስ ኪዳን አንዳንድ ፍንጮችን እናገኛለን፤ «ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና» ተብሎ በመጻፉ የመንፈስ ቅዱስ አስተርእዮ ምሉእ የሚሆነው የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ሲፈጸም እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ዮሐ. 7፥39::

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፥ ስለ ክርስቶስ የመመስከር ሥራ እንጂ ስለ ራሱ የመናገር ሥራ አይደለም:: ክርስቶስ፥ «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል:: እርሱ ያከብረኛል፤ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና:: ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ:- ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ» ብሎ ስለ መንፈስ ቅዱስ መስክሯል፤ ዮሐ. 16፥13-15:: እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የሚገልጠው ከክርስቶስ ጋር በመኖሩና ለእርሱ በመሥራቱ ነው እንጂ ያለ ክርስቶስ አይደለም፤ ዮሐ. 14፥17፤ 15፥26-27:: መንፈስ ቅዱስ በታማኝ ልጆች ሁሉ ላይ ከማረፉና በእነርሱ ላይ ከመኖሩ በፊት መጀመሪያ በክርስቶስ ላይ ዐረፈ:: መጥምቁ ዮሐንስ፥ «በውሃ አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ:- መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ» በማለቱ የመንፈስ ቅዱስን አስተርእዮ ቅደም ተከተል ገለጠ፤ ዮሐ. 1፥33::

እንግዲህ በብሉይ ኪዳን ዘመን የኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ምሉእ የሆነውን የአዲስ ኪዳንን አስተርእዮ ለረጅም ጊዜ ይጠባበቁ ነበር:: ነቢያት በየጊዜው ተነሥተዋል፤ ሆኖም ከነቢዩ ሚልክያስ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ያለ አዲስ ነቢይና ያለ ተጨማሪ አስተርእዮ አራት መቶ ዓመታት ዐልፈዋል:: በእነዚህ ዓመታት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ መሲሕ የሚመጣበት ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን ገና አልደረሰም ነበር፤ ኢሳ. 11፥1-2፤ 42፥1-4፤ 61፥1-3::

የአዲስ ኪዳን ጎሕ ሲቀድድ ግን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአዲስ ዐይነት በድንገት ይታያል:: መልአኩ ገብርኤል፥ «በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል» ብሎ ትንቢት በመጥምቁ ዮሐንስ እንደገና እንደሚነገር ለዘካርያስ ገለጠለት፤ ሉቃ. 1፥15:: መልአኩም፥ «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል» ብሎ አዲሱ ፍጥረት በድንግል ማርያም ማሕፀን እንደሚጀመር መሰከረላት፤ ሉቃ. 1፥35:: በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና ስለ ማርያምና ስለ ልጇ ትንቢት ተናገረች፤ ቀጥሎም ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ስለ ክርስቶስና ስለ ልጁ ስለ ዮሐንስ ትንቢት ተናገረ፤ ሉቃ. 1፥41:67:: ጊዜው ከመድረሱ በፊት መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ስምዖን በመንፈስ ቅዱስ አስተርእዮን ተቀብሎ፥ በእርሱም ተመርቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባና ሕፃኑን ኢየሱስን ተቀብሎ ዐቀፈው፤ እግዚአብሔርንም ካመሰገነ በኋላ በድኅነት የክርስቶስን የአገልግሎት ተጋድሎ ተረድቶ ዮሴፍንና እናቱን ሲባርክ፥ «በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል» የሚለውን ከባድ የትንቢት ቃል ለማርያም ተናገረ፤ ሉቃ. 2፥25-35:: እንግዲህ በገብርኤል ትንቢት፥ በድንግል ማርያም መፅነስ፥ በኤልሳቤጥ፥ በዘካርያስና በስምዖን ምስክርነት የድኅነት ቀን ጎሕ በተወለደው በልጁ በኢየሱስ እንደቀደደ ሉቃስ በወንጌሉ ገልጦልናል:: ብዙ ትንቢት የተነገረለት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያርፍበት መሲሕ መጥቶ ነበርና፤ ኢሳ. 11፥2::

በኢየሱስ መምጣትም የሩአኽ ቀን ብርሃን በመጨረሻ ታየ::

# ማስታወሻ

(1) በዚህ ምዕራፍ የሚገኘው በተለይ «The Holy Spirit» (መንፈስ ቅዱስ) ከሚለው መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ በSinclair Ferguson በተጻፈውና IVP ባሳተመው ላይ የተመረኰዘ ነው:: የዚህ መጽሐፍ ምኅፃረ ቃል THS ነው::

(2) በም.25ለ1 «የሥስትነት አገላለጥ በብሉይ ኪዳን» በሚለው ርእስ በተወሰነ አመለካከት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሰጥተናል::

(3) ስለ እስትንፋስ እግዚአብሔር ም.7 ይመ.

(4) ም.2 ይመ.

(5) ስለዚህ አተረጓጐም በም.22ሀ1፤ በም.25ለ1 አትተናል::

(6) የB.B. Warfield (1851-1921) ምሳሌ ከTHS ገጽ 29 ተተርጕሟል::

# ምዕራፍ 80 - መንፈስ ቅዱስና የጋርዮሽ ጸጋ

ሰው በኀጢአት ሲወድቅ፥ እግዚአብሔር ሰውን ለምን አላጠፋውም? ተብሎ ቢጠየቅ፥ መልሱ ጸጋ በሚለው በአንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ይጠቃለላል:: ጸጋ ማለት ምንም ሊደረግላቸው ለማይገባቸው ፍቅርን ማሳየት ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሰውን ሲወድ በርኅራኄ ይመለከተዋልና መልካም ነገርን ያደርግለታል፤ ይህ ጸጋው ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ኀጢአት ለሚሠራ ሕዝቡ ቃል ኪዳኑን እንዲጠብቅ መልካም ፈቃዱን በብዙ ምሕረት እያሳየ ጸጋውን ገለጠ፤ ይህም በተለይ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 4-11፤ በኢሳይያስ ምዕራፍ 40-55፤ በትንቢተ ሆሴዕና በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 16 እና 36 ላይ ተጽፎ ይታያል:: በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ሥራ አማካይነትና ኀጢአተኞች በዚህ ሥራ ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር አንድ በማድረጋቸው ለእነርሱ በነጻ በሚሰጥ ድኅነት ይታያል፤ ይህም በ130 ጥቅሶች የተገለጠ ሲሆን ከታወቁት አንቀጾች መካከል ኤፌሶን 2፥8-10 እና 1ኛ ዮሐንስ 4፥8-10 ዋናዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ:: ጳውሎስ ጸጋ ተብሎ በተተረጐመው በግሪኩ ቃል ሲጠቀም፥ ዮሐንስ ፍቅር ተብሎ በተተረጐመው በግሪኩ ቃል ይጠቀማል፤ ሆኖም በብዙ አንቀጾች የሁለቱም አሳብ አንድ ነው፤ ጸጋ ከፍቅር ትርጒሞች መካከል አንዱ ነውና (1)::

## ሀ) የጸጋ ሰፊ ይዘት

ለጸጋ ተቃራኒ አሳብ እንዳለ አንዳንድ ጊዜ ቢታሰብም፥ በጸጋ ውስጥ እጅግ ሰፋ ያለ አመለካከት እንዳለ መረዳት ይገባናል፤ ጸጋ የሚከተሉትን አሳቦች ያጠቃልላል:-

1. በግለ ሰብ ላይ እግዚአብሔር መልካም ፈቃድና ጽኑ ተግባር ያለው መሆኑን (1ቆሮ. 15፥10)፥

2. እግዚአብሔር ለምእመናን የሚሠራ መሆኑንና በክርስቶስ አማካይነት በእነርሱ ውስጥ መኖሩን (ሮም 8፥31፤ ቆላ. 1፥27)፥

3. ሰው ገና ሳያምን በሰው አስቀድሞ መሥራቱና ካመነ በኋላም በሰው ትብብር ይህንኑ ተግባር መቀጠሉን ( «... ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና»፤ ፊል. 2፥12-13፤ ፊል. 1፥29፤ ኤፌ. 1፥6-8፤ 2፥5-10)፥

4. በነጻ የሚሠራ መሆኑንና ከምእመናን አለመወሰዱን (ፊል. 1፥6-7)፥

5. በቀጥታም ሆነ በአመክንዮታዊ መንገድ የሰውን ልብ የሚለውጥ መሆኑን (ገላ. 1፥15-16፤ ሐ.ሥ. 16፥14)::

## ለ) የጸጋ አስተሳሰብ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ጸጋ እጅግ ሰፊ የሆነ አስተሳሰብ ስላለበት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልዩ ልዩ አሳብ መገኘቱ አስገራሚ አይደለም:: የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው የሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ነው:: በተለይ አራት አስተሳሰቦችን ቀጥሎ በዐጭሩ እናቀርባለን (2):-

1. አውግስጢኖስና ተከታዮቹ «እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገውን እምነትና ፍቅር ይሰጣል» በማለት የፔላጊዮስን ትምህርት እየተቃወሙ የሰው

ሁለንተና በኀጢአት በመበከሉ (3) ሰው ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ሊድን እንደማይችል አስተማሩ። አውግስጢኖስ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋ እስከ መጨረሻ መቃወም የማይችል በመሆኑ ላይ አተኮረ። ሆኖም የአውግስጢኖስ ተከታዮች ሰው ካመነ በኋላ እስከ መጨረሻ በእምነት ባለመጽናቱ ዘለዓለማዊ ርስትን መውረስ እንደማይችልም አስተማሩ።

2. በመጀመሪያ የግሪክ አበው፥ በኋላ ደግሞ አርሜኒዮሳውያን የፔላጊዮስን ትምህርት በከፊል በመከተላቸው፥ ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ የእምነትን አጸፋ ለመስጠት ይችላል፤ ነጻ ፈቃድ አለውና። ሆኖም እልከኞች የእግዚአብሔርን ጸጋ በመቃወም ለጸጋው ትክክለኛ አጸፋ አይሰጡም።

3. ከአውግስጢኖስ በኋላ ብዙ ጊዜ ቈይተው የተነሡ ምዕራባውያን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አማካይነት ጸጋን በመስጠቱ ላይ አተኮሩ። ሰው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ በመተባበሩ ተጨማሪ ጸጋን ሊያገኝ ይችላል፤ ሆኖም እስከ መጨረሻ የመታገሥ ጸጋ የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ እንጂ ሰው ራሱ ይህን በሥራው ማግኘት የማይችል መሆኑን አስተምረዋል። እንደ ግሪካውያን አበው በእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰንና በጸጋው መካከል ያለውን አመክንዮታዊ ግንኙነት አልተረዱም። አጽንዖታቸው ጸጋ የሰው ነፍስ ጠባይ በመሆኑ ላይ እንጂ ከእግዚአብሔር ለኀጢአተኞች የተሰጠ በመሆኑ ላይ አልነበረም፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ በሰው ነፍስ እንደሚኖር ወይም ለሰው ነፍስ የሚሰጥ ችሎታ ሆኖ እንደሚታሰብ የሚያሳይ ነው።

4. የተሐድሶ ተከታዮች የአውግስጢኖስን ትምህርት ተመልክተው ስለ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የሰጠውን የእርሱን ትምህርት ተዉ። በትምህርታቸው መሠረት እግዚአብሔር እምነትን ይሰጣልና ሰው በዚህ እምነት ይጸድቃል፤ ለዘለዓለምም ክብር ይጠበቃል። ሰው ይህን ርስት የሚወርሰው በራሱ ሥራ ወይም በወሮታ ወይም በሌላ ሰው ትሩፋት ሳይሆን፥ እንዲሁ በክርስቶስ ባለው ጸጋ ብቻ ነው። የተሐድሶ ተከታዮች ስለ ጽድቅ በሚናገሩበት ጊዜ ጸጋ በሚለው ቃል የሚጠቀሙ ሲሆን፥ በሌላ ዐውድ ደግሞ በጸጋ ፈንታ ብዙ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ይጠቅሳሉ፤ ጸጋ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለሰው ይሰጣልና።

## ሐ) የጋርዮሽ ጸጋና ልዩ ጸጋ

የእግዚአብሔርን መንፈስ ሥራ በብሉይ ኪዳን በመረመርንበት ጊዜ፥ ምንም እንኳ ዋናው ሥራ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የተፈጸመ ቢሆንም፥ ብዙ መልካም ሥራ በአሕዛብ መካከል መሥራቱን አይተናል፤ «እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው፤ ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው» ተብሎ ተጽፏልና፤ መዝ. 145፥9። ከዚህም የተነሣ በሰው ሁሉ ዘንድ የመልካምነት፥ የእውነትና የውበት ፍንጮች ይታያሉ፤ ምድር የተረገመች ብትሆንም፥ ጥሩ የእህል አዝመራና አስደሳች የዘር ፍሬዎች ትሰጣለች፤ ልዩ ልዩ እንስሳት ትዕግሥትን፥ ታማኝነትን፥ ገርነትንና የመሳሰሉትን መልካም ጠባያት ያሳያሉ፤ ኀጢአተኛ የሆነ ሰው በመጠኑ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍጥረቱ ያውቃል፤ በማናቸውም ሃይማኖት ውስጥ ከፊል እውነት ከስሕተት ጋር ተደባልቆ ይገኛል፤ ሰው ልዩ ልዩ ችሎታዎች ይኖሩታል፤ በአግባብና በትክክልም መጠነኛ ኑሮን መኖር ይመርጣል፤ በሰው አመለካከት አንዳንዱ ለጓደኞቹ መልካም ነገርን ያደርጋል። ይህን የሚያደርገው ግን ያለ ኀጢአት አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን አምኖ ለእግዚአብሔር በፍቅር አልሠራም። ሰዎች ብዙ ኀጢአት ለመሥራት ሲፈልጉ፥ እግዚአብሔር ይገታቸዋል፤ አንዳንድ ጊዜ ግን ለክፉ የልብ ዝንባሌያቸው አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤ ሮም 1፥24:26:28። እንግዲህ

የእግዚአብሔር ጸጋ የባሕርይ ገንዘቡ ሆኖ ከባሕርያቱ መካከል አንዱ ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋ በሁለት ከፍሎ መመርመር የተለመደ ሆኗል። ለሰዎች ሁሉ የሚሰጠው ጸጋ የጋርዮሽ ጸጋ ሲባል፥ በምርጫ ለሚድኑት የሚሰጠው ጸጋ ደግሞ፥ ልዩ ጸጋ ወይም የሚያድን ጸጋ ተብሎ ተጠርቷል (4)።

ልዩ ጸጋ ለሚድኑት ብቻ የሚሰጥ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድና ሥራ ነው፤ ይህ ጸጋ የሚታየው:- 1ኛ፥ በክርስቶስ በራሱና ለኀጢአተኞች ባደረገላቸው (ዮሐ. 1፥14:17፤ ኤፌ. 2፥6-7፤ ቲቶ 2፥11)፥ 2ኛ፥ ኀጢአተኞች ድኅነትን እንዲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ በሚሠራው ሥራ (ሮም 3፥ 24፤ ቲቶ 3፥5-7)፥ 3ኛ፥ ላመኑት በመንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ሁሉ (ሐ.ሥ. 11፥23፤ 18፥27፤ ሮም 5፥17፤ 2ቆሮ. 9፥8-9:14፤ ኤፌ. 4፥7፤ 1ጴጥ. 3፥7፤ ያዕ. 4፥6-7) ነው። ይህ ጸጋ የሚሠራ ጸጋም ጭምር እንጂ የእግዚአብሔር መልካም አስተያየት ብቻ አይደለም፤ 2ቆሮ. 12፥9፤ 2ጢሞ. 2፥1። በዚህ አመለካከት መሠረት ደግሞ እስጢፋኖስ «መንፈስ ቅዱስ የሞላበት» እና «ጸጋንና ኀይልን ተሞልቶ» የነበረ ሰው በመባሉ፥ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በጸጋ ሙላት መካከል ብዙ ልዩነት አይታይም፤ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ መንፈስ ተብሏልና፤ ሐ.ሥ. 6፥5:8፤ ዕብ. 10፥29። እንግዲህ ትምህርተ ድኅነት በተለይ የሚያተኩረው በልዩ ጸጋ ላይ ነውና በሚከተሉት ምዕራፎች በዝርዝር እናጠናዋለን።

የጋርዮሽ ጸጋ ለሚያምኑት ብቻ ሳይሆን፥ ከኀጢአት የተነሣ በተረገመች ዓለም ውስጥ ለሚኖሩ ሁሉ የሚሰጥ የእግዚአብሔር መልካም አስተያየትና በረከት ነው። የልዩ ጸጋ ተካፋዮች ብዙ የጋርዮሽን ጸጋ ከእግዚአብሔር እንደሚቀበሉ መርሳት አይገባቸውም። እግዚአብሔር ምግብንና ልብስን የሚሰጥ፥ ሁሉን በሕይወት የሚጠብቅ፥ ሁሉን የሚታደግና ከክርስቶስ ጋር ሁሉን ነገር እንዲያው የሚሰጥ አምላካቸው ነው፤ 1ጢሞ. 6፥8:13:17፤ ሮም 8፥32። የልዩ ጸጋ ዐውድ የጋርዮሽ ጸጋ ነው፤ ምክንያቱም የጋርዮሽ ጸጋ ባይገኝ ኖሮ ሕይወት አይገኝም ነበር። አንዳንዶች የጋርዮሽ ጸጋ ሰውን ወደ ድኅነት ለማስገባት የእግዚአብሔር ቀዳሚ ርምጃ ነው ይላሉ፤ ይሁን እንጂ አዳማዊ ጠባይ ያለው ሰው በጋርዮሽ ጸጋ ቢኖርም፥ የእግዚአብሔርን ነገር ፈጽሞ ባለማስተዋሉና «የሞተ» በመሆኑ ይህ ጸጋ ወደ ድኅነት መንገድ አይመራውም፤ 1ቆሮ. 2፥14፤ ኤፌ. 2፥1-3። በወንጌል ካመነ በኋላ ግን ሰው የጋርዮሽ ጸጋን በአዲስ ብርሃን ስለሚመለከተው፥ ከነዳዊት ጋር ስለ ጋርዮሽ ጸጋ እግዚአብሔርን ይወድሰዋል።

የሚያድን ጸጋ በእግዚአብሔር ለተመረጡት ብቻ ይሰጣል፤ ይህም የሚሆነው በክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት መሠረት ነው። የጸጋ ቃል ኪዳን በመሠረቱ መንፈሳዊ ቢሆንም፥ በረከቱ የሚታየው በምድራዊ ሁኔታም ጭምር ነው። በጸጋ ቃል ኪዳን ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር አብረው የሚኖሩ፥ እንደዚሁም ከትምህርታቸውና ከአካሄዳቸው መልካም ነገርን የሚማሩ፥ በምድራዊ ሁኔታ በረከትን ይቀበላሉ። ስለዚህ በቀጥታ ሳይሆን፥ በምእመናን አማካይነት ከክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት ጥቅም ያገኛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ ከክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት የጋርዮሽ ጸጋን በረከቶች የሚቀበሉ ስለ መሆኑ አያስተምርም። ምክንያቱም ይህ የኀጢአትን በደል አያስርዝም፤ የኀጢአት ይቅርታንም አያስገኝም፤ የቅጣት ፍርድንም ለጊዜው ቢያዘገየውም እንኳ አያስቀረውም። ምናልባት «እግዚአብሔር ቊጣውን ሊያሳይ፥ ኀይሉንም ሊገልጥ ወዶ፥ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ይገልጥ ዘንድ፥ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቊጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግሥት» ማቈየት መቻሉ (ሮም 9፥22-23) ለጋርዮሽ ጸጋ በረከቶች ምክንያት ሊሆን ይችላል (5)።

## መ) የጋርዮሽ ጸጋ ፍሬና መሣሪያዎቹ

የጋርዮሽ ጸጋ ፍሬ በርካታና ሰፊ በመሆኑ አሳጥረን ልንገልጠው እንሞክራለን (6)።

1. ምድራዊ በረከቶችን በመስጠት

እግዚአብሔር፥ «... በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሓይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኀጢአተኞች ላይ ዝናቡን ያዘንባልና» የሚለውና ብዙ ሌሎች ጥቅሶች እግዚአብሔር መልካም ነገርን ለሰዎች ሁሉ እንደሚያደርግና በርኅራኄ እንደሚመለከታቸው፥ ከዚህም የተነሣ ሰው በበኩሉ ለሌሎች ሰዎች መልካም ነገርን እንዲያደርግ ያስተምራሉ፤ ማቴ. 5፥44-45፤ ሉቃ. 6፥35-36፤ 16፥15፤ ሐ.ሥ. 14፥16-17። የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ነው፤ መዝ. 145፥9:15-16።

የጋርዮሽ ጸጋ ለማያምኑት ሊዳረስ የሚችለው በእግዚአብሔር ሰዎች ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ በዮሴፍ ምክንያት ጸጋው ለጲጥፋራ ቤት ሁሉ (ዘፍ. 39፥1-5)፥ በኋላም ለግብጻውያን ሁሉ ተዳርሷል፤ ዘፍ. 47፥25።

እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር ሁሉ መልካም ነበረ። በሰው ውድቀት ምክንያት ምድር የተረገመችና የተበከለች ብትሆንም፥ ሁሉም ሰው መልካምን ነገር ሁሉ አትረፍርፎ ከሚሰጠው ከእግዚአብሔር በምስጋናና በደስታ መቀበል አለበት፤ 1ጢሞ. 4፥3-4፤ 6፥17። በፍጥረት ውስጥ ውበት አለ፤ ሰውም ይህን ተመልክቶ ስለ መግቦተ እግዚአብሔር ያስተውላል፤ ማቴ. 6፥28-29።

እግዚአብሔር፥ ለምድር፥ ለእንስሳትና ለሰዎች የሰንበትን ዕረፍት መርሕ ደንግጓል፤ ዘጸ. 23፥10-12።

2. ፍርድን በማዘግየት

የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነው፤ ነገር ግን በጸጋው መሠረት እግዚአብሔር በሰዎች ላይ የኀጢአት ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ከኀጢአታቸው እንዲመለሱ ብዙ ዓመታትን ይሰጣቸዋል፤ ዘፍ. 2፥17፤ 3፥17-19። አሞራውያን ከከነዓን እንዳይጠፉ እግዚአብሔር ሦስት ትውልድን ሰጣቸው (ዘፍ. 15፥16)፤ ለክፉው ንጉሥ ለአክዓብም ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት ጸጋውን አሳየ፤ 1ነገ. 20፥27-29 (በአ.መ.ት.ም. 21፥27-29)።

ሰዎች ከኀጢአታቸው እንዲመለሱ እግዚአብሔር ጊዜ የሚሰጣቸው መሆኑ ግልጥ ነው፤ እስከ መጨረሻ እንቢተኞችና እልከኞች ከሆኑ ግን በጽድቁ መሠረት ቍጣውን ይገልጥባቸዋል፤ ዘፍ. 6፥3፤ ኢሳ. 48፥9፤ ኤር. 7፥23-25፤ ሉቃ. 13፥6-9፤ ሐ.ሥ. 17፥30፤ ሮም 2፥4፤ 9፥22-23፤ 1ጴጥ. 3፥20፤ 2ጴጥ. 3፥9።

3. ክፋትን በመግታት

እግዚአብሔር በጸጋው ሰዎችን ባይገታቸው ኖሮ፥ እንደ ልባቸው ፍትወት ኀጢአትን ሁሉ ይሠሩ ነበር፤ እውነት ነው፤ እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለርኵሰት፥ ለሚያስነውር ምኞትና ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤ መዝ. 81፥12፤ ሮም 1፥24:26:28። በእነዚህ ሰዎች ላይ የልባቸው ክፋት ከልክ ዐልፎ ይገለጣል፤ መዝ. 14፥3-6፤ ሮም 1፥29-32፤ 3፥10-18። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥም ሆነ በውጭ ከሰው

ጋር የሚታገል ቢሆንም፥ ይህ ወደ ንስሓ አያደርስም፤ ዘፍ. 6፥3፤ ኢሳ. 63፥10፤ ሐ.ሥ. 7፥51:: አንዳንድ ጊዜም የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ሕይወት ሲሠራ ይቈይና በኋላ ሰውዬውን ይተወዋል፤ 1ሳሙ. 16፥14፤ ዕብ. 6፥4-6::

እግዚአብሔር ኀጢአትን በልዩ ልዩ መንገድ ይገታል፤ በሰማያዊ ስፍራ የሰይጣንን ሥራ ይወስናል (ኢዮብ 1፥12፤2፥6)፤ የሚቃወሙትን ያዋርዳል፤ 2ነገ. 19፥27-28::

ሰው ፍጡር በመሆኑ አጠቃላይ አስተርእዮን (7) ይቀበላልና «በልባቸው የተጻፈው የሕግ ሥራ» የሚለው ኅሊናውን ያነሣሣል፤ ሮም 2፥14-15:: በክፉት መንገድ ለመራመድ የወሰኑ ሰዎች እንኳ «ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ» ያውቃሉ፤ ሮም 1፥32:: ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው ደግሞ የባለ ሥልጣናትን ቅጣት ይፈራሉ (ሮም 13፥1-4)፥ ሌሎችም እንደ ፈሪሳውያን የተራውን ሕዝብ አሳብ ሊፈሩ ይችላሉ፤ ማቴ. 21፥26:: ብዙዎቹ ደግሞ ሰው የሚዘራውን እንደሚያጭድ በትክክል ያምናሉና የክፉ ሥራን ውጤት በመፍራት ክፋትን ላለመፈጸም ጥረት ያደርጋሉ፤ ምሳ. 22፥8፤ ገላ. 6፥7::

4. መልካሙን በመጠበቅና በማስፋፋት

የማያምኑ በምድራዊ አስተሳሰብ መልካም ነገር ማድረግ ይችላሉና መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ይናገራል:: ከእስራኤል ነገሥታት ብዙዎች ከልብ የእግዚአብሔር ሰዎች አልነበሩም፤ ነገር ግን «መልካም» እንዳደረጉ ተመስክሮላቸዋል፤ ለምሳሌ፥ ኢዩ (2ነገ. 10፥28-31)፥ ኢዮአስ (2ነገ. 12፥1-4 እና 2ዜ.መ. 24፥17-25) እና አሜስያስ (2ነገ. 14፥3 እና 2ዜ.መ. 25፥2) ይገኙበታል:: ክርስቶስ፥ ኀጢአተኞች እንኳ መልካም ለሚያደርጉላቸው መልካም እንደሚያደርጉ ተናገረ (ሉቃ. 6፥33)፤ ገዦችም «ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና» በመባላቸው በምድራዊ አስተሳሰብ ብዙ ሰዎች መልካም እንደሚያደርጉ ግልጥ ነው፤ ይህም ከጋርዮሽ ጸጋ የተነሣ የሚሆን ነው፤ ሮም 13፥3:: ሆኖም ይህ ዐይነቱ መልካም ሥራ ሰዎችን እንዲድኑ አያደርግም ወይም የሚድኑ መሆናቸውን አያሳይም፤ ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ናቸውና ሰው የሚሠራው በእምነት ላይ ካልተመሠረተ በቀር ኀጢአት አለበት፤ ሮም 3፥23፤ 14፥23::

በማያምኑ መካከል የጋርዮሽ ጸጋ በተለይ ከአራት ነገሮች ሊመነጭ ይችላል:-

ሀ) ሰው አጠቃላይ አስተርእዮ ስላለው ዓለምን በመመርመር ብዙ ነገርን ያገኛል፤ ይማራል፤ ያውቃልምና ለሰው ጥቅም ከሳይንስ (ከሥነ ፍጥረት) ብዙ ነገርን እያገኘ መሥራት ይችላል:: እውነት ነው፤ የሰው ልብ ክፉ በመሆኑ ዕውቀቱን ብዙ ጊዜ በክፉት ላይ ቢያውለውም፥ በአጠቃላይ አመለካከት ዕውቀትን ማግኘት ለሰው መልካም እንደሆነ ይታሰባል::

ለ) ከዕውቀት ጋር ኪነ ጥበብና ልዩ ልዩ የፈጠራ ችሎታ ለሰው ብዙ ደስታን ሊያስገኝ ይችላል፤ ሰው አዳዲስ ነገሮችን ማድረግ ይሞክራል፤ ልዩ ልዩ ነገርንም «መፍጠር» ይችላል:: ይህም ብዙ ጊዜ የሚሆነው በሚያምኑት መካከል ሳይሆን፥ በማያምኑት ዘንድ ነው:: ይህ ዐይነቱ የጋርዮሽ ጸጋ ከመጀመሪያ ተገኝቷል፤ ዩባል በገናን ለሚደረድሩትና መለከትን ለሚነፉት አባት ነበረ፤ ቱባልቃይንም ከናስና ከብረት ቀጥቅጦ ዕቃን ሠራ፤ ዘፍ. 4፥21-22:: ይህ ዐይነቱ «የፈጠራ ሥራ» በተለይ በሥዕል፥ በቅርጻቅርጽ፥ በሥነ ጽሑፍ (በግጥም፥ በቅኔ)፥ በሙዚቃ፥ በውዝዋዜና በስፖርት... ወዘተ ዛሬም ሊታይ ይችላል::

ሐ) አስተዳደር የጋርዮሽ ጸጋ ታላቅ መሣሪያ ነው:: እውነት ነው፤ አንዳንድ መንግሥታት በሕዝቦቻቸው ላይ ብዙ ሥቃይ ያመጣሉ:: ቢሆንም መጽሐፈ መሳፍንት እንደሚያስተምረው ንጉሥ በሌለበት ዘመን ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርጋልና አገር ሕገ ወጥ ሆኖ ክፋት ይበዛበታል፤ መሳ. 17፥6፤ 18፥1፤ 19፥1፤ 21፥25:: አስተዳደር የተለያየ ነውና አስተዳደር ባለበት ሕግና ሥርዐት ይኖራል፤ ይህም ለሰው በረከት ነው:: አስተዳደር ከጥፋት ውሃ ጀምሮ ተመሥርቷልና (ዘፍ. 9፥6) ሥልጣን ሁሉ በእግዚአብሔር ተሰጥቷል፥ ስለዚህ ሰው በአስተዳደር ውስጥ በተገቢው ረገድ መሳተፍ ይገባዋል፤ ማቴ. 22፥21፤ ሮም 13፥1-7፤ 1ጴጥ. 2፥13-14::

መ) ሃይማኖት ለሰዎች ሁሉ የሚሰጥ የጋርዮሽ ጸጋ መሣሪያ ነው:: ይህን በእውነተኛ ሃይማኖት አመለካከትና እውነተኛ ባልሆነ ሃይማኖት አመለካከት መሠረት ልንመለከተው እንችላለን::

ምእመናን «ስለ ሰዎች ሁሉ፥ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ» እንዲጸልዩ ታዝዘዋልና እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ስለሚሰማ ለሚጸልዩላቸው በረከት እንደሚሆን ማመን ተገቢ ነው፤ 1ጢሞ. 2፥1-2:: ክርስቶስ፥ «ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ» ብሎ በማዘዙ ምእመናን የእግዚአብሔርን ምሳሌ በመከተላቸው፥ ልዩ ልዩ በረከት ለእነዚህ አሳዳጆች እንደሚሰጥ ማሰብ አይከብድም፤ ማቴ. 5፥44-45:: ልዩ ልዩ ሰዎች በክርስቶስ ባያምኑም፥ ወደ ፈጣሪያቸው ሲጮኹ እግዚአብሔር ልመናቸውን ይሰማል:: የነነዌ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር በጮኹ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሊፈጽም የተናገረውን ክፉ ነገር አላደረገባቸውም፤ ዮናስ 3፥10:: እንደዚሁም ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሕዝብ መካከል የማይቈጠሩ ቢሆንም፥ ሌሎች ሰዎች ወደ ፈጣሪያቸው ሲጸልዩ፥ በመልኩ በመፈጠራቸው የሚሰማቸው መሆኑ ከባሕርዩ ጋር ይስማማል፤ መዝ. 145፥9:: ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ስለምናደርግ ነው» ባለው መሠረት እግዚአብሔር አማኞችን በእምነታቸው ከኀጢአት ሲያድናቸው፥ የማያምኑትንም ከልዩ ልዩ ዐይነት ችግርና መከራ እንደሚያወጣቸው ያሳያል፤ 1ጢሞ. 4፥10:: ይህ ሁሉ የጋርዮሽ ጸጋ ነው::

እውነተኛ ያልሆነ ሃይማኖትን ስንመለከት ግን ሰዎች በፈጣሪያቸው ፊንታ የተፈጠረውን ሲያመልኩ የእግዚአብሔር ቍጣ እንጂ ጸጋው አያድርባቸውም፤ ሮም 1፥18-23:: አንዳንድ ሃይማኖቶችን ስንመረምር ግን መጠነኛ እውነቶችን እናገኝባቸዋለን፤ ለምሳሌ፥ ለአባሎቻቸው በንጽሕና እንዲኖሩ፥ ግብረገባዊ ኑሮን እንዲከተሉ፥ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ፥ እውነትን እንዲናገሩ... ወዘተ ትእዛዝ ይሰጣሉ:: ይህ ወደ ድኅነት አያደርሳቸውም፤ ነገር ግን በምድራዊ ሁኔታ ሲታይ በረከት ይሆንላቸዋልና እንደ ጋርዮሽ ጸጋ ልንመለከተው እንችላለን::

ሌሎች ደግሞ በሁሉም ሃይማኖት ደግነት ስላለ፥ በእነርሱ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አለና ሃይማኖት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ይመራል ይላሉ (8):: ስለዚህ አስተሳሰብ ጥቂት ነገሮችን አንሥተን በዐጭሩ መመልከት ይገባናል::

1) አንድ ሊቅ፥ «በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ከዓለም ጋር ስላለው ግንኙነት ብዙ ጸሓፊዎች ቢጽፉም፥ መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ በዓለም ሁሉ እንደሚሠራ በግልጥ የሚናገር አንድ ጥቅስ እንኳ በአዲስ ኪዳን አይገኝም» (9) ብሎ ጽፏል::

2) መንፈስ ቅዱስ በእውነተኛው ሃይማኖትና በሥርዐቱ ውስጥ እንጂ በሌሎች ሃይማኖቶችና ሥርዐቶቻቸው ውስጥ አይገኝም::

3) የጋርዮሽ ጸጋ የሚያድነው ጸጋ ዐውድ ቢሆንም፥ ወደ እግዚአብሔር የማዳን ሥራ ሰውን አያስገባም፤ ሰው በአዳም ዕውር (1ቆሮ. 2፥14፤ 2ቆሮ. 4፥3-4)፥ ልቡ እጅግ ክፉ (ኤር. 19፥7)፥ ፈቃዱም ዐመፀኛ (1ጴጥ. 3፥18) ነውና።

4) የጋርዮሽ ጸጋ የክርስቶስን ማንነትና ሥራ አይገልጥም።

5) ሰው የሚድነው ወደ ክርስቶስ በመሄድ ብቻ ነው (ማቴ. 11፥28)፤ ከእርሱ በቀር መካከለኛ (አስታራቂ፥ 1ጢሞ. 2፥5)፥ ለድነት የሚጠራ ስም (ሐ.ሥ. 4፥12) ወይም ወደ አብ መሄጃ መንገድ (ዮሐ. 14፥6) የለምና።

## ሠ) የጋርዮሽ ጸጋና ክርስቲያናዊ ኑሮ

የሰው ሁለንተና ከአዳም ውድቀት የተነሣ እንደተበከለ የማያምኑት በሰዎች ዘንድ መልካምነት ከየት እንደሚመጣ ብዙ አይጠይቁምና የጋርዮሽ ጸጋ የመዳን ተቀዳሚ ሥራ መሆኑን ሊያስተምሩ ይችላሉ። እንግዲህ የጋርዮሽ ጸጋ ትምህርት ከትምህርተ ሰብእ እና ከትምህርተ ድነት ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ የጋርዮሽ ጸጋን ሥራ በማያምኑት ሰዎች ሕይወት ለማየት ስንፈልግ ሦስት ነገሮችን ማድረግ ይገባናል (10)፦

1. በጋርዮሽ ጸጋ ሰዎች ብዙ ዕውቀት፥ ብዙ ችሎታ፥ ጥሩ ጠባይና ከምድራዊ አመለካከት አንጻር መልካምነት ሊታይባቸው ይችላል። ሆኖም በክርስቶስ ካላመኑ የእግዚአብሔርና የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች (ሮም 5፥10፤ ፊል. 3፥18-19፤ ያዕ. 4፥4)፥ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች (ማቴ. 12፥30) እና እንደ ሌሎች የቍጣ ልጆች ናቸው፤ ኤፌ. 2፥3። ስለዚህ እነርሱ እንደ ሌሎች በክርስቶስ መዳን እንደሚያስፈልጋቸው መርሳት የለብንም።

2. የማያምኑት መልካም ነገሮችን ሲያደርጉ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ከዚያ በስተ ጀርባ እንዳለ በማወቅ ለእግዚአብሔር ክብርን ልንሰጥ ይገባል።

3. በጠቅላላው የጋርዮሽን ጸጋ ሥራ እየተመለከትን እግዚአብሔር በኀይሉና በጸጋው የሚያደርግልንን እያስተዋልን፥ በጋርዮሽ ጸጋ መልካም ተግባራት ውስጥ በምንችለው መጠን እንሳተፍ፤ ለዚህ ጸጋ ባለቤት ለእግዚአብሔርም ምስጋናና ውዳሴ እናቅርብ!

# ማስታወሻ

(1) የእግዚአብሔር ፍቅር ለኀጢአተኞች በሦስት ቃላት በተለይ ይገለጣል፤ እነርሱም ፍቅር፥ ምሕረትና ትዕግሥት ናቸው። ም.24 ቍ.2 ይመ.

(2) ስለ ጸጋ እነዚህ አስተሳሰቦች ባልታተሙት በዶክተር ፓከር ማስታወሻዎችና በበርክኾፍ ገጽ 429 ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

(3) ም. 43ሐ ይመ.

(4) በእንግሊዝኛ የጋርዮሽ ጸጋ Common Grace ሲባል፥ ልዩ ጸጋ ደግሞ Special Grace ወይም Saving Grace የሚያድን ጸጋ ይባላል። ሆኖም እንደ ጸሓፊዎቹ አመለካከት መጠነኛ የሆነ ልዩ ልዩ አስተሳሰብ ለእነዚህ ቃላት ሊሰጥ ይችላል። በርክኾፍ ገጽ 432-435 ይመ.

(5) Berkhof የሐዋርያውን አቀራረብ ተከትሎ ይህን አሳብ በጥንቃቄ ገልጦታል፤ ገጽ 437-439 ይመ.

(6) ይህ በተለይ ከBerkhof ገጽ 441-444፥ ከGrudem 657-662 እና ከዶክተር ፓከር ማስታወሻዎች የተገኘ ነው።

(7) ም. 2ሀ ይመ.

(8) THS ም. 11 ገጽ 242-248 ይመ.

(9) W . H. Griffith Thomas በPrinceton በ1913 ዓ.ም. THS ገጽ 244 ይመ.

(10) ይህ ክፍል በተለይ በGrudem ገጽ 665 ላይ የተመሠረተ ነው።

# ምዕራፍ 81 - መንፈስ ቅዱስና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በ1ኛው መጽሐፍ ምዕራፍ 25-28 የእግዚአብሔርን አንድነት በሦስትነት መረመርን:: የአብን፥ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ግንኙነት በማጠቃለል ስንገልጥ፥ 1ኛ፥ ፍጹም ኅብረት አላቸው፤ 2ኛ፥ እያንዳንዱ በሌላው ውስጥ ይኖራል፤ 3ኛ፥ በሦስቱ መካከል አምላካዊ ሕይወትና ኀይል አለ ብለናል (ም. 26መ):: በተጨማሪም ህላዌያዊ ሦስትነት በግብራዊ ሦስትነት እንደሚገለጥ ስናስብ፥ እኛ ሦስቱን አካላት በግብራቸው እናውቃቸዋለን:: ከአካላቱ የአንዱን ሥራ ስንመረምር፥ ሌሎቹ በፍቅር፥ በፈቃድና በግብ አብረው እንዳሉበት እናምናለን:: በዚህ ምዕራፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲኖር ሳለ ከእርሱ ጋር የመንፈስ ቅዱስ ግንኙነትና አገልግሎት እንዴት እንደነበረ እናጠናለን:: እንደ ትምህርተ ሥላሴ ጥናት ሁሉ፥ ይህ ምንም እንኳ ምሥጢር ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ለማወቅ በትሕትና ማንበብ ይገባናል::

አራቱ ወንጌሎች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ታሪክ፥ ትምህርትና አገልግሎት ይገልጣሉ:: በዚህም በተለያየ ጊዜ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያስተማረውን ይጠቅሳሉ:: አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ላይ ማተኰር አይወዱም፤ እንደዚህ የሚያደርጉት በክርስቶስ አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ ካለ፥ ክርስቶስ ኀይል ያለው ፍጹም አምላክ አልነበረም እንዳይባል ከመፍራት የተነሣ ሊሆን ይችላል:: ይህ ፍርሀት ግን መሠረተ ቢስ ነው፤ አስቀድሞም ብዙ ጊዜ እንደተገለጠ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያተኵረው በፍጹም አምላክነቱ ላይ ነው (ም. 26ሀ2 እና ም. 55ለ ይመ.):: በሌላ አንጻር ግን ስለ ሦስቱ አካላት አንድነትና ግንኙነት ስናስብ፥ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ባይታይ ኖሮ፥ ቃል ሥጋ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ለምን ቀረ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችል ነበር:: ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ከአብ ስለ ወልድ ልዩ ምስክርነት ከሰማይ እንደተሰጠ ሁሉ (ማቴ. 3፥17፤ 17፥5፤ ዮሐ. 12፥28)፥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትም በክርስቶስ ሕይወት ታሪክ ሲገለጥ ማየት አስገራሚ አይደለም::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጨረሻው እራት በኋላ ስለ መንፈስ ቅዱስ በሰፊው አስተምሯል፤ ዮሐ. ም. 14-16:: ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ ከሄደ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ስለሚኖረው አገልግሎት በዚያን ጊዜ የገለጠላቸው ሲሆን፥ እስከዚያ ጊዜ ድረስም መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት እንደነበረ አንዳንድ ፍንጮችን ሰጣቸው (1)::

እርሱ፥ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» በማለቱ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ቢያንስ ሦስት ነገሮችን መረዳት እንችላለን፤ ዮሐ. 15፥26-27:-

1) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተለይ ስለ ክርስቶስ መመስከር ነው:: ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው፥ አንባቢዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያምኑና አምነውም በስሙ ሕይወት እንዲያገኙ ነበር፤ 20፥31:: በዚህ ዐይነት ዮሐንስ ለዓላማው ምስክሮችን ይፈልግ ነበርና የክርስቶስ ተአምራት «ምልክቶች» በመሆናቸው (2፥11፤ 20፥30) የክርስቶስን ማንነትና ግብር የሚገልጡ

ምስክሮች ነበሩ። እንደዚሁም ክርስቶስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ሆኖ በክርስቶስ ላይ በመውረድ፥ በእርሱም ላይ በመኖር እርሱ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ መሆኑን መሰከረ፤ ዮሐ. 1፥32-34።

2) መንፈስ ቅዱስ ምስክር ሲሆን «አጽናኝ» ነው፤ አጽናኝ የግሪኩን ቃል «ጰራቅሊጦስ»ን (ፓራክሊቶስ) ይተረጉማል (2)። ጰራቅሊጦስ የሚለው ቃል «ፓራ» (አጠገብ) እና «ካሌው» (መጥራት) ከሚሉት ሁለት ቃላት የተገኘ ነው። መንፈስ ቅዱስ በአጠገባችን ሲገኝ፥ ክርስቶስ ለሐዋርያት አጽናኝ እንደነበረ ሁሉ፥ እርሱም ለእኛ አጽናኝ ነው፤ እንዴት ሊሆን ይችላል? ተብሎ ቢጠየቅም መልሱ መንፈስ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ማንነትና ግብር የሚመሰክር በመሆኑ ነው የሚለው ይሆናል።

በክርስቶስ ዘመን የነበረው የ«ምስክር» አገልግሎት እንዴት እንደነበር ማሰብ አሳቡን ለመረዳት ይረዳናል። ሰው በዳኛ ፊት ሲቆም፥ በአጠገቡ የሚቆመው ጠበቃ ሳይሆን፥ ምስክር ነበረና የዳኛ ተግባር ምስክሮችን በመጠየቅ ወደ እውነት መድረስ ነበረ። እንግዲህ ክርስቲያን በሰይጣን ስለ ኀጢአቱ ሲከሰስ፥ በፍርድ ቤት ምሳሌነት ክርስቶስ ምስክሩ ነው፤ ምስክር የሚያደርገውም እርሱ ራሱ ደሙን በማፍሰስ የኀጢአተኛ ማስተስረያ መሆኑ ነው፤ 1ዮሐ. 2፥1-2።

3) መንፈስ ቅዱስ ዋናው ምስክር ሲሆን፥ ምስክር ለመሆን የቻለውም ከመጀመሪያ ከክርስቶስ ጋር ስለነበረ ነው። ክርስቶስ፥ «እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» ብሎ ሲነግራቸው «ደግሞ» በማለቱ መንፈስ ቅዱስን ያመለክታልና ሐዋርያት ከመጀመሪያ (በጥምቀት ጊዜ ወደ አገልግሎቱ በይፋ ከመግባቱ ጀምሮ) ከክርስቶስ ጋር እንደነበሩ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም ከመጀመሪያ አብሮ ከእርሱ ጋር ነበረ፤ 15፥27። እንግዲህ ክርስቶስን በሚመለከት መንፈስ ቅዱስና ሐዋርያት ተመሳሳይ አገልግሎት አላቸው፤ ምስክሮች ናቸውና። ለዚህ አገልግሎት ያበቃቸው መስፈርት አንድ ነው፤ ከመጀመሪያ ከክርስቶስ ጋር የነበሩ መሆናቸው። ይህን ጥቅስ እንደዚህ ስናስተውል ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፥ «ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን» የሚለው ምሥጢራዊ ሐረግ ግልጥ ይሆናል፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላይ በማደሩ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር እንደነበረ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም በእነርሱ ዘንድ ይኖር ነበር፤ ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላም በውስጣቸው መኖሩ ይታያል፤ ዮሐ. 14፥17።

ከክርስቶስ ጋር ከመጀመሪያ በመኖሩ፥ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ዋና ምስክር መሆኑ ፍጹም ተገቢ ነው። በቀጰዶቅያ የታላቁ የቂሣርያ አባት በዝል (330-379 ዓ.ም. ገደማ) መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ዘንድ ስለ መገኘቱ ሲናገር፥ «የማይለይ ጓደኛ ... በመንፈስ ቅዱስ ፊት የክርስቶስ የሥራ እንቅስቃሴ ሁሉ ተገልጦ ታየ» ብሏል (3)። ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከሞተበት፥ በኋላም ወደ ሰማያዊ ክብሩ እስከተመለሰበት ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ አልተለየም። እንደዚህ ሲባል ግብራዊ አንድነቱን ለመግለጥ እንጂ ባሕርያዊ አንድነቱ ምንጊዜም ይኖራል። ከዚህም የተነሣ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ውስጥ ለመኖር ሲመጣ፥ እንደ ክርስቶስ መንፈስ ይመጣልና መንፈሱ ካላቸው ክርስቶስ አላቸው። መንፈስ ቅዱስ የሌለው ሰው የክርስቶስ አይደለም። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚከተለው ጽፏል:-

«እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን፥ ሰውነታችሁ

በኀጢአት ምክንያት የሞተ ነው፤ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው»፤ ሮም 8+9-10:: እዚህ ላይ «የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ» መኖር፥ «የክርስቶስ መንፈስ» ያለውና «ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ» መሆን የሚሉት ሦስት አባባሎች የመንፈስ ቅዱስን አንድ እውነት ማመልከታቸው ግልጥ ነው:: እንግዲህ በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ግብራዊ አንድነት አለ:: መንፈስ ቅዱስም ይህ አንድነት ያለው ሆኖ የተገኘው ከክርስቶስ ጋር ከመጀመሪያ ስለነበረ ነው፤ ዮሐ. 15+27::

ነቢዩ ኢሳይያስ የሚመጣው መሲሕ የመንፈስ ቅዱስ ሰው መሆኑን ገልጦ ነበር፤ ኢሳ. 11+2፤ 42+1፤ 61+1:: አዲስ ኪዳንም ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ የተከናወነውን የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት በዝርዝር ይጠቅሳል:: ይህንም በመከታተል ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት በይበልጥ እናስተውላለን፤ ይህንም በተለይ በሦስት ደረጃዎች ከፍለን እናጠናዋለን:-

## ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ፅንሰት፥ ልደትና እድገት ውስጥ

በምዕራፍ 79ረ ላይ እንዳየነው መንፈስ ቅዱስ በአራት መቶ ዓመታት ውስጥ በነቢይ አማካይነት ሲናገር ከቈየ በኋላ፥ ስለ ክርስቶስ ፅንሰትና ልደት በልዩ ልዩ መንገድ አዲስ አስተርእዮ ሰጠ፤ ዋና ሥራውም ድንግል ማርያም፥ «ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች» የሚለው ነው፤ ማቴ. 1+18:: ማርያም ለመፅነስ የቻለችው መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ላይ ስለመጣና የልዑል ኀይል ስለጸለላት ነበር፤ ሉቃ. 1+31:35:: አዲስ ኪዳን በትሥጉት ውስጥ ስለነበረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ብዙ አይገልጥም፤ ሆኖም በጌታ የልደት ታሪክ ልዩ ልዩ ፍንጮች ስለሚገኙ፥ እነርሱን ብንመረምራቸው ለጥናታችን ይረዳናል::

1. መንፈስ ቅዱስ በድንግል ማርያም ላይ በ«መምጣቱ» ሲል፥ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር መንፈስ በሳኦልና በዳዊት ላይ መውረዱን ያሳስባል፤ 1ሳሙ. 10+6:10፤ 16+13:: መንፈስ ቅዱስ በሰው ላይ ሲመጣ የመጣበትን የዚያኑ ሰው ሕይወት እንደ ልብስ ተጐናጽፎ ለራሱ ዓላማ ይጠቀምበታል::

አብዛኛውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን ታሪክ በማዳን ሥራ እግዚአብሔር አዲስ እንቅስቃሴ ሲጀምር፥ መካን ሴት ልጅ እንድትወልድ ማድረጉን እናያለን፤ ዘፍ. 17+15-19፤ 18+9-14፤ መሳ. 13+1-24፤ 1ሳሙ. 1+1-20፤ ሉቃ. 1+5-25:: አሁን ግን መካንነት ገና ያልታየባት፥ ወንድ የማታውቅ አንዲት ድንግል ሴት በአስገራሚ ሁኔታ ፀንሳ ተገኝታለች፤ ይህም የመሲሑ ዘመን ለመግባቱ ምልክት ነው፤ ኢሳ. 7+14፤ ማቴ. 1+23::

2. «የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል» በማለቱ በብሉይ ኪዳን ዘመን በፍጥረት የነበረውን የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ፥ ሕዝብ መጠበቅንና ክብር መግለጥን ያሳስባል:: የእግዚአብሔር መንፈስ በፍጥረት ሥራ ጊዜ በውሃ ላይ ይረብብ ነበር (ዘፍ. 1+2)፤ ንስር ጫጩቶቿን አውጥታ በእነርሱ ላይ እንደምትረብብ፥ እስራኤልን በምድረ በዳ ጠበቀው (ዘዳ. 32+11)፤ በደመና ጋረዳቸው (ዘጸ. 13+21፤ 14+19-20፤ ኢሳ. 63+10-11)፤ በደመና መልክም በክብር የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነው፤ ሞላውም፤ ዘጸ. 40+34-35:: ያ ክብር በቤተ መቅደስ ለኢሳይያስ ተገለጠ (ኢሳ. 6+1-4)፤ ሕዝቅኤልም፥ ክብሩ ከቤተ መቅደስ ሲወጣ አየ (ሕዝ. 10+1-22) ደግሞም በአዲሱ መቅደስ እንደሚመለስ በራእይ ታየው (ሕዝ. 43+1-5):: በዘሩባቤል ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ሲሠራ፥ ምንም እንኳ

የእግዚአብሔር ክብር ባይኖርም፥ ከፊተኛው የበለጠ ክብር እንደሚሞላው (ሐጌ 2፥7-9) እና ጌታ ወደ መቅደሱ በድንገት እንደሚመጣ (ሚል. 3፥1-5) ተነግሯል። በአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ የዚያ ክብር ትንቢት ፍጻሜ ነው። ክብሩ በመቅደሱ ውስጥ ቢሰወርም (ዮሐ. 2፥19-22)፥ አንዳንድ ጊዜ ይታይ ነበር (ዮሐ. 1፥14)፥ በተለይም በውላጤ ራእዩ ወቅት፤ ሉቃ. 9፥28-36። በዚያ ጊዜ ደመና መጥቶ እነጴጥሮስን ሲጋርዳቸው፥ እግዚአብሔር በደመና ውስጥ በመናገሩ፥ ደመናው የብሉይ ኪዳን ክብር ደመና መሆኑ ግልጥ ነው። የሉቃስ «ጋረደ» እና የመልአኩ ገብርኤል «ይጸልልሻል» ግስ በግሪክ ቋንቋ አንድ ነው፤ በሌላ ጊዜም በወንጌሉ ውስጥ በዚህ ቃል አለመጠቀሙ ጥልቅ አሳብ እንዳለበት ያሳያል። በዚህ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር በኢየሩሳሌም ስለሚፈጸመው መውጣቱ ይነጋገሩ ነበር። «መውጣቱ» የሚለው ቃል ደግሞ የእስራኤልን ከግብጽ መውጣት ያሳስባልና በክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ በማተኮር የመሥዋዕቱን ሥራ ያብራራል።

«ይጸልልሻል» የሚለው ቃል እንግዲህ ፍጥረትንና መውጣትን በማንጸባረቅ በትሥጉት መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን ሥራ በሁለት መንገድ እንድንመለከተው ይመራናል። 1ኛ፥ የአዲስ ፍጥረት አምላካዊ ሥራ ነው። የመጀመሪያው ፍጥረት ከማይታየው ተገኘ (ዕብ. 11፥3)፥ ሁለተኛው የተገኘው ግን ከማርያም ሥጋ ነበር። የእግዚአብሔር ዓላማ ለመጀመሪያው ፍጥረት «ባዶነት» መልክና ሥርዐት ባመጣው «ሁለተኛው ሰው» አማካይነት ሁሉን ማደስ ነው። 2ኛ፥ የአዲሱ ማውጣት ማለት የማዳን ሥራ መጀመሩ ነው። በማሕፀን ሳለ፥ ሲጠመቅ፥ ሲፈተን፥ ወደ ናዝሬት ሲሄድና በሌላውም ሕይወቱ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ «ረበበ»፤ ሉቃ. 1፥35፤ 3፥22፤ 4፥1:14-18:28-30። ይህም እግዚአብሔር ከግብጽ ለጠራው «ልጁ» ያሳየውን እንክብካቤ ያሳያል (ዘዳ. 8፥1-10፤ ሕዝ. 16፥1-14፤ ሆሴዕ 11፥1)፤ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድም ኢየሱስ ሕፃን በነበረ ጊዜ በግብጽ ተቀመጠ፤ ከዚያም ተጠርቶ ወጣ፤ ማቴ. 2፥13-15:20።

መንፈስ ቅዱስ በድንግል ማርያም ላይ የመጣውና የረበበው እንድትወልድ ብቻ ሳይሆን፥ መልአኩ፥ «ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» በማለቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዓላማ ከእርሷ የሚወለደው በቅድስናና በንጽሕና እንዲጠበቅ ጭምር መሆኑን ለማሳየት ነው፤ ሉቃ. 1፥35። እንግዲህ በትሥጉት መንፈስ ቅዱስ ከሚያከናውነው ሥራ ውስጥ ቢያንስ በአምስት ነጥቦች ላይ ማተኮር እንችላለን:-

ሀ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የኢየሱስ መፀነስ እግዚአብሔር በልዕልናው አዲስ ሥራ መጀመሩን ያሳያል፤ ይህም «ከወንድ ፈቃድ» የተነሣ የሚሆን አልነበረም፤ ዮሐ. 1፥13።

ለ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቃሉ የነሣው ትስብእታዊ ጠባይ ከድንግል ማርያም ተገኘ። ይህም የእኛ ትስብእታዊ ጠባይ በመሆኑ መቀደስ እንዲችል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ ነበረ። እርሱ «በኀጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ» ሲሆን (ሮም 8፥3-4)፥ «ቅዱስና ያለ ተንኰል፥ ነውርም የሌለበት» (ዕብ. 7፥26)፥ በአንድ ቃልም «ቅዱሱ» ነበረ፤ ሉቃ. 1፥35፤ ሐ.ሥ. 4፥27።

ከዚህ በላይ አዲስ ኪዳን በድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ የተሠራውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ባያብራራ፥ የሚያስከትለው ውጤት ግልጥ ነው።

ሐ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስ መፀነስ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ የሚለው ትምህርት ተቀባይነት እንዳያገኝ ያደርጋል (4)። በዚህ ፈንታ ትክክለኛው ትምህርት የእግዚአብሔር ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሰው ሆነ የሚለው ነው። በዚህ ዐይነት፥ «እኔ ከላይ ነኝ» የሚለው የክርስቶስ ምስክርነት ልደቱን ያብራራል፤ ዮሐ. 8፥23።

መ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስ መፀነስ በአንድ በኩል ከሰው ድካም ጋር ራሱን አንድ ማድረጉን ሲያሳይ፥ በሌላ በኩል ከድንግል ማርያም የተወለደው አካልነትን ያገኘው ከአዳም ሳይሆን ከእግዚአብሔር በመሆኑ፥ በአዳም ኀጢአት እንዳልተበከለ፥ በደልም እንዳልነበረበት ይገልጣል (5)። ክርስቶስ «ኋለኛው አዳም» እና «ከሰማይ የመጣ ሰው» ነው (1ቆሮ. 15፥45:47-49)፤ ክርስቶስ፥ «እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም» ብሏልና፤ ዮሐ. 8፥23።

ሠ) በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስ መፀነስ፥ ለወልድ በአብ መላክ መንገድን አመቻቸ። በዚህ ዐይነት በትሥጉት የሦስቱ አካላት ሥራ ይታያል።

ሉቃስ ብላቴናው ኢየሱስ በቤተ መቅደስ መምህራኑን በጥበቡ ማስገረሙን ከተረከ በኋላ፥ «ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር» ብሎ ጽፏል፤ ሉቃ. 2፥52። ይህም ጥበብ የተገኘው የእግዚአብሔርን ቃል ከማሰላሰል (መዝ. 119፥99-100) እና ከመንፈስ ቅዱስ የኅብረት ሥራ የተነሣ መሆኑን ማሰብ አይከብድም፤ ኢሳ. 11፥1-3። መንፈስ ቅዱስ ይህን እንዴት ፈጸመው? ተብሎ ቢጠየቅም፥ መልሱ በእግዚአብሔር አገልጋይ ላይ እግዚአብሔር መንፈሱን እንደሚያደርግበት መገለጡ ነው (ኢሳ. 42፥1)፤ በትንቢቱም አገልጋዩ፥ «የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ ዐውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል፤ ማለዳ ማለዳ ያነቃኛል፤ እንደ ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል። ጌታ እግዚአብሔር ጆሮዬን ከፍቷል...» ብሎ ተናግሯል፤ ኢሳ. 50፥4-5። ከዚህ በስተ ጀርባ በአብና በወልድ መካከል የነበረው የማይቋረጥ አንድነት ነበረው፤ የዐሥራ ሁለቱ ዓመት ልጅም፥ «...በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?» በማለት ከጠየቀ በኋላ፥ «በአባቴ ቤት» ብሎ በመናገር በዚህ ልዩ አንድነት ላይ አተኩሯል፤ ሉቃ. 2፥49።

«ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት፥ በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር» የሚለው የሉቃስ ምስክርነት የክርስቶስን ተገቢ የሆነ የዕድሜ አካሄድ ያሳያል፤ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ጋር የተያያዘ መሆኑን ማሰብ አስቸጋሪ አይሆንም። ኢሬኔዎስ፥ እንዲህ በማለት ጽፏል:- «እርሱ (ኢየሱስ) በሰው ሕይወት ደረጃ ሁሉ ዐለፈ። ሕፃንነትን እየቀደሰ ለሕፃናት ሕፃን ሆነ። የልጅ ፍቅርን፥ የጽድቅንና የመታዘዝን አርኣያነት እያሳየ በሌሎች ልጆች መካከል ልጅ ሆኖ ልጅነትን ቀደሰ። በወጣቶች መካከል ወጣት ሆኖ ምሳሌ ሆናቸው፤ ለጌታውም (ለእግዚአብሔርም) ቀደሳቸው» (6)።

## ለ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ጥምቀት፥ መፈተንና አገልግሎት

### 1. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ጥምቀት

«ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፤ መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ» ሉቃ. 3፥21-22።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በወንጌልና በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ከፍ ያለ ስፍራ አለው። አሁንም መንፈስ ቅዱስን ከሚመለከት አቅጣጫ የክርስቶስን ጥምቀት እንመለከተዋለን።

መጥምቁ ዮሐንስ ለጥቂት ወራት ሰዎች ለመሲሑ መምጣት ዝግጁዎች እንዲሆኑ የኀጢአት ይቅርታ እንዲያገኙ ንስሓ ገብተው በውሃ እንዲጠመቁ ሰብኮ ነበር። የትምህርቱ ዋና መልእክትም፡- «እኔስ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን... እርሱ (ክርስቶስ) በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል...» የሚል ነበር፤ ሉቃ. 3፥16።

ከዕለታት አንድ ቀን ሕዝቡ ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ከናዝሬት መጥቶ ከሕዝቡ ጋር ራሱን አንድ በማድረግ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። ይህንም በማድረጉ ራሱን ለድኅነት አገልግሎት አቀረበ። ዮሐንስ ካጠመቀውና ከውሃ ከወጣ በኋላ ኢየሱስ ሲጸልይ ሳለ ሰማይ ተከፈተ፤ ማቴ. 3፥16፤ ማር. 1፥9-10። በመጽሐፍ ቅዱስ «ሰማያት ተከፈቱ» የሚለው አዲስ አስተርእዮ ወዲያው እንደሚሰጥ የሚያረጋግጥ የዐዋጅ መልእክት ነው፤ ራእ. 4፥1፤ 19፥11።

«መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ» በማለቱ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላይ ለምን እንደወረደና በዚህ አኳኋን ለምን እንደወረደ ጥያቄ ይፈጥራል። ኢየሱስ ከጥምቀቱ በኋላ ይጸልይ ነበርና ይህ የጸሎቱ መልስ እንደሆነ ማመን እንችላለን።

ክርስቶስ ለታላቁ የሕይወት አገልግሎት ራሱን አቅርቦ ነበር። ስለዚህ ስናስብ መጥምቁ ዮሐንስ ነቢይ ነበርና ክርስቶስ ከእርሱ የሚበልጥ ነቢይ እንደሚሆን ዐወቀ፤ ዘዳ. 18፥18፤ ዮሐ. 1፥21-25። ሉቃስም፥ «ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር» ብሎ በመጻፉ፥ ይህ አገላለጥ የክርስቶስን ክህነት የሚያሳስብ ይሆናል፤ ሉቃ. 3፥23፤ ዘኁ. 4፥3። ይህ በዚህ መልክ ታየም አልታየም፥ ከፈተናው ከተመለሰ በኋላ መጥምቁ ዮሐንስ፥ «እነሆ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ በመመስከሩ ኢየሱስ ለሰው ኀጢአት መሥዋዕትን በማቅረብ የካህንን ሥራ እንደሚፈጽም ማወቁን አሳየ፤ ዮሐ. 1፥29:36። ርግቡም በክርስቶስ ላይ ሲወርድ፥ «የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተ ደስ ይለኛል» የሚለው ድምፅ ከአብ ሲመጣ፥ «አንተ ልጄ ነህ» (መዝ. 2፥7) እና «ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ» (ኢሳ. 42፥1) የሚሉትን አረፍተ ነገሮች በመሰንዘር ክርስቶስ ንጉሥ መሆኑን ይገልጣል። እንግዲህ ክርስቶስ ራሱን ለጥምቀት ሲያቀርብ ሥራው የነቢይ፥ የካህንና የንጉሥ ሥራ መሆኑን ዐወቀ፤ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ወርዶ ይህንኑ መሰከረ፤ አረጋግጦም ዐተመለት፤ ዮሐ. 6፥27።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልጅነቱ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለተረዳ መሲሕና ነቢይ፥ ካህንና ንጉሥ እንደሚሆን ዐውቆ ነበር። ከዚህም ጋር የሃይማኖት መሪዎችና የዓለም ሰዎች በሰይጣን መሪነት የእግዚአብሔርን ሰዎች እንደተቃወሙና እንዳሳደዱ ያስተውል ነበር፤ ሐ.ሥ. 7፥51-53። ምድራዊ ሕይወቱንም በመሥዋዕታዊ ሞት እንደሚፈጽመው ዐወቀና መከራውን «ጥምቀት» ብሎ ጠራው፤ ማቴ. 20፥22። ኢየሱስ ኀጢአት አልባ ሰው ቢሆንም፥ እንደ እኛ ሰው ነበረና ስለሚመጣው አገልግሎት ሲጸልይ አሳቡ ከባድ ሳይሆንበት አልቀረም፤ በኋላም በጌቴሴማኒ ሳለ ትግሉ ሌላ ሰው ከሚያጋጥመው ይልቅ እጅግ ከባድ መሆኑን ያስተውል ነበር። ከዚህ የተነሣ ሁለት ነገሮችን ማወቅ ይፈልግ ነበር፤ አንደኛው፥ ጥሪው የሚወድደው አባቱ ፈቃድ እንደሆነ፥ ይህም

በጥምቀት ጊዜ ከሰማይ በመጣው ድምፅ ተገለጠለት:: ሁለተኛው፥ ለሚያጋጥመው ሁሉ አሸናፊ እንዲሆን በቂ ኀይል እንደሚኖረው ነው::

መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ክርስቶስ ጥምቀት ሲናገር፥ «መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ» ብሎ በመመስከሩ፥ ርግቡ በኢየሱስ ላይ በመውረዱ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑንና በእርሱ ላይ በመኖሩም ለአገልግሎቱ ኀይል እንደሚኖረው አመላከተ:: ዮሐንስም፥ «መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ» በማለቱ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ እንደሚያርፍና ከዚህ የተነሣ አገልግሎቱን የሚፈጽመው ሌሎችን በመንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ መሆኑን አሳየ፤ ዮሐ. 1፥32-33:: እንግዲህ ኢየሱስ በጥምቀቱ ለሚያጋጥመው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረትና ኀይል እንደሚኖረው ተረጋገጠ:: እርሱ ንጹሕ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነበረውና ጊዜው ሲደርስ በመንፈስ ቅዱስ ለማጥመቅ ቻለ፤ ዮሐ. 3፥33-34:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ በቆርኔሌዎስ ቤት፥ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኀይልም ቀባው» ብሎ፥ ኢየሱስ ከአብ የመንፈስ ቅዱስን ቅብዐት እንደተቀበለና በኀይሉ መልካምን ሥራ እንደሠራ መሰከረ፤ ሐ.ሥ. 10፥38:: እዚህ ላይ ጴጥሮስ መቀባቱን ከጥምቀቱ ጋር ያያያዘው ስለ መሆኑ አልተጻፈም:: ሆኖም ሐዋርያው ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ሲናገር፥ ከናዝሬት መምጣቱን፥ መልካም ማድረጉንና ለዲያብሎስ የተገዙትን ሁሉ መፈወሱን ስለሚጠቅስ፥ አሳቡ በጥምቀቱ ላይ ያተኮረ የነበረ ይመስላል:: ይህንም ስንል ቀደም ሲል እንደተገለጠው፥ ከመፀነሱ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ መርበቡን እንረሳም፤ መንፈስ ቅዱስን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልንለይ አንችልምና:: በጥምቀት ጊዜ ግን ኢየሱስ ወደ አዲሱ የሕይወቱ ደረጃ ሲገባ፥ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ዐይነት መንገድ መጣለትና ክርስቶስ ሌሎችን በመንፈስ ቅዱስ እንዲያጠምቃቸው እርሱ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ፤ ተቀባም:: መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ የመውረዱ፥ በእርሱ ላይም የመምጣቱ ጉዳይ ጌታ ኢየሱስ ከዚያ በፊት መንፈስ ቅዱስን አልተሞላም ወይም መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር አልነበረም ወደ ማለት የሚመራ ሳይሆን፥ እርሱ ሌሎችን በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅና (ዮሐ. 1፥32-33) የእስራኤል ተስፋ የሚፈጸምበትን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የሚያመጣ (ሉቃ. 4፥1:14:18-21) መሆኑን የሚያመለክት ነው (7):: መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ የልጅነትና የአለኝታ መንፈስ ነው:: እርሱ ከክርስቶስ መንፈስ ጋር የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን ይመሰክራልና በጌቴሴማኒ በመስቀል ላይ እንኳ እግዚአብሔርን «አባት ሆይ» ብሎ እንዲጠራው አስቻለው:: ምእመናን በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናቸው፥ እንደዚህ ዐይነቱን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በከፊል ያውቃሉ፤ ሮም 8፥15-16::

መንፈስ ቅዱስ በርግብ መልክ ለምን እንደተገለጠ ፍጹም ርግጠኛ መሆን አይቻልም:: መንፈስ ቅዱስ ረቂቅ መንፈስ በመሆኑ አይታይም፤ ሆኖም ለመጥምቁ ዮሐንስ (ምናልባት ለደቀ መዛሙርቱም ጭምር ይሆናል) ኢየሱስ መሲሑ መሆኑ ጥርጥር በሌለበት በሚታይ መልክ እንዲገለጥ አስፈላጊ ሆኖ በዚህ አኳኋን የታየ ይመስላል፤ ዮሐ. 1፥31-34:: ለኢየሱስም ሰው በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በሚታይ ሁኔታ ከትስብእታዊ ባሕርዩ ጋር ስለሚስማማ የርግብ ምሳሌነት ለዚህ ምቹ ነበር:: የእግዚአብሔር መንፈስ በፍጥረት በውሃው ላይ እንደ ወፍ ረብቦ ነበር (ዘፍ. 1፥2)፤ በጥፋት ውሃ ጊዜ ርግቡ በእግዚአብሔር ፍርድ ከዓለም «መጥፋት» በኋላ የተነሣውን አዲሱን «ፍጥረት» ዐወጀ፤ ዘፍ. 8፥11-12:21:: መንፈስ ቅዱስ በርግብ መልክ መውረዱ ክርስቶስ «ሁለተኛ ሰው» እና «ኋለኛው አዳም» መሆኑን ምናልባት ያንጸባርቃል፤

እንደዚህ ከሆነ ክርስቶስ አዲሱ ኖኅ በመሆን እግዚአብሔር ለቀጣት ምድር ዕረፍትን በመጨረሻ ይሰጣል፣ ዘፍ. 5፥29፣ ኢሳ. 63፥14፣ ማቴ. 11፥28-30:: በእስራኤል ትውፊት የእስራኤል ሕዝብ ዐርማ ርግብ ነበረና ክርስቶስ እውነተኛው የእግዚአብሔር አገልጋይና አዲሱ እስራኤል ነው:: በተጨማሪም ርግብ የድኾች የኀጢአት መሥዋዕት ነበረና ክርስቶስ የእኛ ኀጢአት መሥዋዕት ነው፣ ዘሌ. 5፥7፣ ሉቃ. 2፥22-24፣ 2ቆሮ. 5፥21:: ርግብ እነዚህን አሳቦች ሊያሳስብ ይችላልና ለክርስቶስ አገልግሎት ምቹ ምሳሌ ነው::

የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የክርስቶስ ጥምቀት ዋና ክሥተት ነውና ኢየሱስ «ዘመኑ ተፈጸመ» ብሎ «የተወደደችው የጌታ ዓመት» መድረሷን ገለጠ፣ ማር. 1፥14-15፣ ሉቃ. 4፥17-19:: እንግዲህ በዚህ ዐይነት ከጥምቀቱ ጋር ብዙ የትምህርተ መለኮት አሳቦች (8) ተያይዘዋል፣ እንደዚሁም ከጥምቀቱ በኋላ ወዲያውኑ የተፈጸመው የመፈተኑ ሁኔታ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ ያሳስባል::

2. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ መፈተን

«ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው»፣ ማር. 1፥12::

«ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው»፣ ማቴ. 4፥1::

«ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፣ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ»፣ ሉቃ. 4፥1-2::

እንግዲህ ከጥምቀቱ በኋላ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚከተሉት እንደተከሠቱ ከእነዚህ ከሦስቱ ወንጌላውያን መረዳት ይቻላል:-

ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንደነበረበት፣

ለ) መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ እንደ «አወጣው»፣ እንደወሰደውና እንደመራው፣

ሐ) መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ወደ ተጋድሎ እንዲገባ እንዳደረገው::

እንደዚህ የተደረገውም የሰይጣንን ኀይል መቋቋም መቻሉን ለማረጋገጥ ሳይሆን፥ ሰይጣንን ማሸነፍ የመጀመሪያ ርምጃ መሆኑን ለማመልከት ነበረ:: ሰይጣን ግን ተንኰለኛ በመሆኑ ወዲያውኑ ኢየሱስን አልተፈታተነውም፣ እስኪርበው ድረስ አርባ ቀን ጠበቀ::

ወንጌላዊው ሉቃስ በጌታችን ጥምቀትና ፈተና ታሪክ መካከል ከኢየሱስ እስከ አዳም ድረስ ያለውን የትውልድ ሐረግ በመዘርዘሩ፥ በአዳምና በኢየሱስ ፈተና መካከል የነበረውን የሁኔታና የውጤት ልዩነት ያሳስባል፣ ሉቃ. 3፥23-38:: አዳም በምቾት እየኖረ ሳለ እግዚአብሔር በተከለው በዔድን ገነት ሲፈተን ወደቀ፣ ክርስቶስ ግን ሁለተኛው አዳም ሆኖ ለሰይጣን በሚመቸው በተረገመ ምድረ በዳ በድካመት ሲፈተን አልወደቀም:: የትግሉ ውጤት እንደሚከተለው ነበር:-

ሀ) ሰይጣንን እንዲሄድ አዘዘው (ማቴ. 4፥10)፣

ለ) ሰይጣን ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከኢየሱስ ተለየ (ሉቃ. 4፥13)፣

ሐ) ኢየሱስ በመንፈስ ኀይል ወደ ገሊላ ተመለሰ (ሉቃ. 4፥14)፣

መ) ኢየሱስ፥ «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው» ብሎ የኢሳይያስ የትንቢት ቃል በእርሱ በመፈጸም ላይ መሆኑን ተናገረ (ሉቃ. 4፥17)፣ በፈተናውም፥

«የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ» የሚለውን ወደ ጥርጥር የሚያስገባ የተንኰል ንግግር ለአንድ አፍታ እንኳ ባለመቀበሉ ማንነቱን ማወቁን አሳየ፡፡ እንደዚሁም ለእግዚአብሔር ቃል ሳይታዘዝና በሌላ መንገድ ያለ መሥዋዕትነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ባለመሞከሩ፥ ለፈተናው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በቂ መሆኑን አረጋገጠ፤

ሠ) አሁን በእርሱ ነጻነት እንዳለ ሰበከ (ሉቃ. 4፥18-19)፤

ረ) ስብከቱ የሥልጣን ስብከት ነበረ (ሉቃ. 4፥32)፤

ሰ) ቃሉ በሥልጣኑ ርኵሳን መናፍስትን ከሰዎች አወጣ (ሉቃ. 4፥33-36)፤

ሸ) ዳሰሳው ሁሉን ፈወሰ (ሉቃ. 4፥40)፡፡

3. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ አገልግሎት

የወንጌል ታሪክ የክርስቶስ ታሪክ ነው፡፡ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የኅብረት ዐውድ ውስጥ እንደሚፈጸም ሲታወቅ፥ አንዳንድ ጊዜ ወንጌላውያን ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ በመሥራቱ ላይ ያተኵራሉ፡፡ ኢየሱስ፥ «በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች» ብሎ በመናገር በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ኅብረት የሚሠራ መሆኑን አሳየ፡፡ ይህም ሥራ ግልጥ በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሰይጣን ሥራ ነው ብለው እንደነዚያ ፈሪሳውያን የሚሳደቡ ኀጢአታቸው አይሰረይላቸውም፤ ምክንያቱም እውነትን ቢያውቁም የራሳቸውን አሳብ ስለሚከተሉ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይፈልጉምና መንፈስ ቅዱስን ይሳደባሉ፤ ማቴ. 12፥22-32፡፡

በዚህ ምዕራፍ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኅብረት በጥበብ እንዳደገ አይተናል፤ ይህንም ጥበብ በተፈተነበት ጊዜና በሕይወቱ ሁሉ ገለጠው፡፡ ስለ ማናቸውም ጥያቄ ወይም ጕዳይ ከብሉይ ኪዳን ትክክለኛ ቃልን ጠቀሰ፤ የሰውንም ልብ ዐውቆ እንደ ሰው ሁኔታ ተግሣጽና ማስጠንቀቂያ፥ ማጽናኛና ምክር መስጠት ቻለ፡፡

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኅብረት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሲያድግም፥ «ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ»፤ ዕብ. 5፥8፡፡ እርሱ የሐዋርያት መሪ ሲሆን በምድራዊ ገዥ አመራር መሠረት አልሄደም፤ በዚህም ፈንታ እርሱ፥ «እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ፥ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤ ፍርድንም ለአሕዛብ ያወራል፡፡ አይከራከርም፤ ... የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም፡፡ አሕዛብም በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ» የሚለውን የኢሳይያስን ትንቢት እየፈጸመ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ሆኖ በጥበብ፥ በገርነትና በማስተዋል አስተማረ፤ ኢሳ. 42፥1-4፤ ማቴ. 12፥18-21፡፡ ይህ ዐይነቱ ባሕርይ በእርሱ ላይ መታየቱ በክርስቲያን ላይ መታየት የሚገባውን «የመንፈስን ፍሬ» ያሳስባል፤ ገላ. 5፥22-23፡፡

«በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገ...» የሚለው ጥቅስ ደግሞ የክርስቶስ ምስጋናና ደስታ «በመንፈስ ቅዱስ» መሆኑን ያሳያል፤ ሉቃ. 10፥21፡፡ እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ሁሉ ላይ እንደነበረ አይተናል፡፡ ጕዳዩ ምሥጢር ቢሆንም፥ ክርስቶስ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኅብረት አይገኝም ነበር፡፡

### ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በክርስቶስ ሞት፥ ትንሣኤና ዕርገት

አራቱ ወንጌላውያን ክርስቶስ ያደረገው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተደረገ መሆኑን በታሪክ አቀራረባቸውና በተወሰኑ ጥቅሶች አማካይነት ይገልጣሉ። ሆኖም በክርስቶስ ሞት፥ ትንሣኤና ዕርገት መንፈስ ቅዱስ የተሳተፈ ስለ መሆኑ የሚናገሩ ጥቅሶች እጅግ ጥቂት ናቸው። ዐልፎ ዐልፎም አንድ ጥቅስ መንፈስ ቅዱስ ማለትን ትቶ «መንፈስ» በሚልበት ጊዜ፥ ስለ ክርስቶስ ትስብእታዊ መንፈስ ወይም ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገር መሆኑን ለመለየት ቀላል አይደለም። አንዳንዶች ደግሞ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተገለጠው መንፈስ የሚለው ቃል መንፈሳዊ ሁኔታን እንደሚያመለክት ያስተምራሉ።

1. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ሞት

«(ክርስቶስ) ነውር የሌለው ሆኖ በዘላዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ...» በሚለው ጥቅስ ውስጥ «የዘለዓለም መንፈስ» የሚለው ሐረግ መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ይመስላል፤ ዕብ. 9፥14። ሆኖም በክርስቶስ ሕማማት ስለ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የሚናገር ሌላ ጥቅስ አይገኝምና ምሥጢሩን በዚህ መንገድ ማየትና መተው አለብን።

2. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ትንሣኤ

የክርስቶስ ትንሣኤ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ የአብ ተግባር ሆኖ የሚገለጥ ሲሆን (ሐ.ሥ. 2፥32፤ 17፥31፤ ሮም 8፥11፤ 1ቆሮ. 15፥15)፥ ወልድ ደግሞ ሰውነቱን እንደሚያነሣና ይህን የማድረግ ሥልጣን እንደነበረው ተናገረ፤ ዮሐ. 2፥19-21፤ 10፥17-18። መንፈስ ቅዱስም በክርስቶስ ትንሣኤ መሳተፉን ከአንዳንድ ጥቅሶች ማየት ይቻላል፤ ሆኖም በእነዚህ ጥቅሶች ትርጒም ሊቃውንት እርስ በርሳቸው አይስማሙም። በተለይ ሦስት ጥቅሶችን ቀጥሎ እንመልከት:-

ሀ) «ክርስቶስ... በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ»፤ 1ጴጥ. 3፥18።

ለ) «በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ...»፤ 1ጢሞ. 3፥16።

ሐ) «...በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ፥ እንደ ቅድስና (በቅድስና) መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኀይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ...»፤ ሮም 1፥3-4።

በእነዚህ ሦስት ጥቅሶች በሥጋና በመንፈስ መካከል ንጽጽር አለ። «ሥጋ» ከመሞቱ በፊት የክርስቶስን ትስብእታዊ ኑሮ ሲገልጥ፥ «መንፈስ» ከትንሣኤው በኋላ መንፈሳዊ ሁኔታውን ወይም ኑሮውን ሊገልጥ ይችላል (9)። አንዳንዶች ይህን ትርጒም የማይቀበሉት ክርስቶስ በሥጋ በመነሣቱ ነው፤ ሆኖም ሐዋርያው ስለ ምእመናን ትንሣኤ ሁኔታ መንፈሳዊ አካል እንደሚኖራቸው ይናገራል፤ 1ቆሮ. 15፥54።

አንዳንዶች «በቅድስና መንፈስ» የ«ሥጋ» ንጽጽር እንደሆነ ስለሚያስቡ፥ የክርስቶስ ትንሣኤ በቅድስና ሁኔታ የሚታይ መሆኑን ይናገራሉ። ሌሎች ግን መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል በማለት ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደተነሣ ያስተምራሉ። ይህንም አሳብ «ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ» (ሮም 8፥11) ከሚለው ሐረግ ጋር አገናኝተው መንፈስ ቅዱስ የአብ መንፈስ በመሆኑ፥ በሌላም ሥራ ሁሉ አዲስ ሕይወትን መስጠት የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሚና ሆኖ በመታወቁ ላይ ትርጒማቸውን ያጸናሉ። ሆኖም «የቅድስና መንፈስ» በዚህ ቍጥር ብቻ ይገኛልና የሐዋርያው አሳብ መንፈስ

ቅዱስ ከሆነ የተለመደውን «መንፈስ ቅዱስ» የሚለውን ያልተጠቀመበት ምክንያት አይታይም። ትርጉሙ በመንፈስ ቅዱስ ከሆነ «በሥጋ» ከሚለው ጋር ያለው ንጽጽር ግልጥ አይደለምና «እንደ ቅድስና መንፈስ» በመንፈሳዊ ሁኔታ የሚተረጉም መሆኑ የተሻለ አማራጭ ይመስላል።

«በመንፈስ የጸደቀ» የሚለውን ክርስቶስ በመንፈሳዊ ሁኔታ እንደጸደቀ መተርጐም ቢቻልም፥ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጸደቀ ማለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አረጋገጠ (ገለጠ) ማለት ነው። ይህም ለክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር እጅግ ይስማማልና በዚህ ጥቅስ ላይ «መንፈስ» መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት ይመስላል፤ ይህ ትርጉም እዚህ ላይ ከንጽጽሩ ጋር የሚስማማ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈሳዊ ሁኔታ እንደተነሣ ግልጥ ነው፤ እነዚህ ጥቅሶችም ይህን ያስተምራሉ። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንደተነሣ እነዚህ ጥቅሶች በግልጥ ያስተምራሉ ማለት ባንችልም፥ ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ተነሣ ማለታችን አይደለም፤ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በግብር በአንድነት ይሠራሉ፤ ሁሉም በልዩ አሠራር አብረው ይሠራሉና መንፈስ ቅዱስ ዕቅዱን ወደ ፍጻሜ ያደርሰዋል።

## 3. መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ዕርገት

ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ የመረጣቸውን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ እንዳዘዛቸው እናነባለን፤ ሐ.ሥ. 1፥1-2። ከክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገሩ አንዳንድ ጥቅሶች አሉ፤ ስለ አተረጓጐማቸውም ልዩ ልዩ አሳብ አለና ቀጥሎ እነርሱን በዐጭሩ ልናብራራቸው እንሞክራለን።

ሀ) «... ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ... አላቸው»፤ ዮሐ. 20፥22።

መጥምቁ ዮሐንስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፤ ማቴ. 3፥11፤ ዮሐ. 1፥33። ክርስቶስ በትምህርቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ነገርን ቢያስተምርም፥ ከሙታን በተነሣበት ቀን ግን መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ብሎ በማዘዙ አገልግሎቱ ወደ አዲስ ደረጃ መሸጋገሩን ያሳያል። እንግዲህ ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የተቀበሉት በትንሣኤው ዕለት ነው ወይስ በበዓለ ኀምሳ ቀን? በበዓለ ኀምሳ ቀን ጥምቀቱን ከተቀበሉት፥ በትንሣኤው ዕለት ምንን ተቀበሉ? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ።

አንዳንዶች ክርስቶስ በተነሣበት ቀን ሐዋርያት ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ እንደተወለዱ ያስተምራሉ። እንደዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የተደረገውን የሽግግር ሁኔታ ካለማስተዋል የመጣ ይመስላል (10)። ክርስቶስ በጸሎተ ኀሙስ ሐዋርያት ንጹሓን እንደሆኑ ተናግሮ ስለነበር (ዮሐ. 13፥10-11፤ 15፥3) ከዚያ በፊት በልዩ ልዩ መንገድ ምእመናን አድርጎ በመቍጠር ተመለከታቸው፤ ማቴ. 16፥15-17፤ ማር. 4፥11-12፤ ሉቃ. 12፥32፤ ዮሐ. 10፥14-16፤ 17፥6-8።

ክርስቶስ ካልከበረ መንፈስ ቅዱስ እንደማይወርድ ለማሳየት (ዮሐ. 7፥39)፥ «እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ» (ዮሐ. 16፥7) ብሎ በጸሎተ ሐሙስ ተናግሮ ነበር፤ በተጨማሪም በትንሣኤው ቀን ጧት፥ «ገና ወደ አባቴ አላረግሁም» ብሎ

ለመግደላዊት ማርያም በመናገሩ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን በዚያ ዕለት እንደሚቀበሉ ማሰብ አመክንዮታዊ አልነበረም፤ እርሱ ገና ከእነርሱ አልሄደም ነበርና፤ ዮሐ. 20፥17:: እንግዲህ በዚህ ጊዜ አገልግሎታቸውን ሲገልጥላቸው የሚሠሩት በመንፈስ ቅዱስ መሆኑንና በትንቢታዊ አገላለጥ በቅርብ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን በአዲስ ዐይነት የተቀበሉ መሆናቸውን እንደሚያሳይ ማሰብ ይሻላል፤ ቃሉ ከሰባት ሳምንት በኋላ ተፈጸመ:: እፍ በማለትም እግዚአብሔር ለአዳም ሕይወትን እንደሰጠ በማሳሰብ፥ የሐዋርያት አገልግሎት የአዲስ ፍጥረት ሥራ መሆኑን ገለጠ፤ ዘፍ. 2፥7:: በሥራቸው የእርሱ ወኪሎች ሆነው ኀጢአትን ይቅር ለማለት መሾማቸውንም እዚህ ላይ አሳየ፤ ዮሐ. 20፥23::

ለ) «...ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፏል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ»፤ 1ቆሮ. 15፥45::

በዚህ አንቀጽ ሐዋርያው የትንሣኤውን አካል ሁኔታ ያብራራል፤ 1ቆሮ. 15፥44:: «ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ» የሚለው አረፍተ ነገር የሚከተሉትን አሳቦች ያሳስባል:-

1) ከትሥጉቱ ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንፈሳዊ ዓለም ተዘጋጅቶ ነበር፤

2) ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሰዎች ሁሉ ከኖረ በኋላ ሞተ፤

3) ከሙታን ሲነሣ አስቀድሞ ሲከተሉት የነበሩ ዐወቁት፤

4) ከሙታን በመነሣቱ ከሞት ሥልጣን ሥር ወጣ፤

5) ወደ ሰማይ ሲያርግ በመንፈሳዊ ሁኔታ ኖረ፤ ይኖራልም (ምእመናን በዳግም ምጽአት ተለውጠው በዚህ ሁኔታ ይኖራሉ፤ 1ቆሮ. 15፥50-52)፤

6) ኢየሱስ ክርስቶስ ለምእመናን ትንሣኤ መንፈሳዊ ሁኔታ ጥቅልል ምሳሌ ነው፤

7) ሕይወት በራሱ በመኖሩ ሕይወትን የሚሰጥ ነው (ዮሐ. 5፥21:26)፤

8) ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ይህም በትንሣኤውና በዕርገቱ ፍጹም ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ በማጥመቁ ተገልጧል::

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከፅንሰቱ ጀምሮ ካደረበት በኋላ፥ «ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ» በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ክብሩ ሲገባ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ተቀብሎ በሕዝቡ ላይ አፈሰሰ፤ ዮሐ. 7፥38-39፤ 15፥26፤ ሐ.ሥ. 2፥33:: በዚህ መሠረት መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ ተብሏል፤ ሮም 8፥9::

ለእኛ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ በአገልግሎታቸው አንድ ናቸው፤ ክርስቶስንም ስንቀበል፥ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለንና:: በአካል (በማንነት) ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ ሁለት አካላት ቢሆኑም፥ አገልግሎታቸው አንድ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ ሌላ አጽናኝ ነውና፤ ዮሐ. 14፥16::

የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ አንድነት በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ይታያል::

ሐ) «ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ዐርነት አለ:: እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያበለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን»፤ 2ቆሮ. 3፥17-18::

አብና ወልድ አንድ እንደሆኑ ሁሉ (ዮሐ. 10፥30)፥ ጌታና መንፈስ ቅዱስም አንድ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ ካለው ወስዶ በመግለጡ (ዮሐ. 16፥14) ክርስቶስ ሰዎችን ይለውጣቸዋል፤ በዚህ ዐይነት የተለወጥን በመሆናችን በክርስቶስ ሥራና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ መካከል ልዩነት ማድረግ አንችልም፤ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ ነው፤ ክርስቶስም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው። ከዚህ የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል» በማለቱ እርሱ ከዋክብቱን እንደሚይዝ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስንም በሙላት በመያዝ መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ መሆኑን ያሳያል (10)፤ ራእ. 3፥1።

## መ) የመንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ አገልግሎት ተከታታይነት

ዮሐንስ የመንፈስ ቅዱስንና የክርስቶስን አገልግሎት አንድነት በተለይ በክርስቶስ የመሰናበቻ ንግግር ላይ መዝግቦታል። ይህንም ሲያደርግ፥ ዓላማው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የክርስቶስን አገልግሎት መቀጠል እንደሆነ ማረጋገጥ ነው (ሉቃስ ደግሞ «መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ» በማለቱ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን አገልግሎት ተከትሎ መቀጠሉን አሳየ፤ ሐ.ሥ. 1፥1-2)። ይህ ተከታታይነት በዮሐንስ ወንጌል እንደሚከተለው ይታያል:-

1) እንደ ኢየሱስ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተላከ ነው (20፥21፤ 15፥26)፤

2) ኢየሱስ እውነት ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነውና ምእመናንን ወደ እውነት ሁሉ ይመራቸዋል (14፥6፤ 15፥26፤ 16፥13)፤

3) ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ፥ መንፈስ ቅዱስም ያንኑ አገልግሎት ከፍጻሜ ያደርሳል (14፥23:26፤ 16፥12-13)፤

4) ኢየሱስ አብ የላከው ምስክር እንደሆነ ሁሉ (18፥37)፥ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ተልኮ ይመሰክራል (15፥26)፤

5) ዓለም ክርስቶስን እንዳላወቀው ሁሉ (5፥43፤ 12፥48)፥ መንፈስ ቅዱስንም አያውቀውም (14፥17)።

በዚህ መሠረት ኢየሱስ፥ «ወደ እናንተ እመጣለሁ» ብሎ የተናገረው ትንሣኤን ወይም በዓለም መጨረሻ የሚሆነውን ዳግም ምጽአቱን የሚያመለክት ሳይሆን፥ በመንፈስ ቅዱስ መምጣቱን የሚያሳይ ነው፤ 14፥18። በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ የተቀራረበ ነውና መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ክርስቶስ አብሮ ይመጣል፤ አብም እንዲሁ አብሮ ይመጣል፤ 14፥23።

መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር አብሮ በመኖሩ፥ ወደ ሰው ሲመጣ፥ ሰው ክርስቶስን እንዲመስል ያደርጋል፤ ይህም በእማኙ ውስጥ የሚያከናውነው ዋና ሥራው ነው፤ 2ቆሮ. 3፥17-18። እስካሁን የተገለጠውን እውነት ቅዱስ አትናቴዎስ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ያብራራው መሆኑ ተነግሯል:- «እኛ መንፈስ ቅዱስን እንድንቀበል ቃሉ የትስብእትን መልክ ነሣ፤ ሰዎች መንፈሱን ተሸካሚዎች እንዲሆኑ እግዚአብሔር የትስብእት ተሸካሚ ሆነ» (11)።

# ማስታወሻ

(1) በዚህ ምዕራፍ የሚገኘው ትምህርት የTHS ምዕራፍ ሁለትን አቀራረብ ይከተላል።

(2) በም. 72ሐ2 ስለ ጰራቅሊጦስ በጻፍነው በ1ዮሐ. 2፥1 መሠረት ክርስቶስ የምእመናን ጰራቅሊጦስ መሆኑን አሳይተናል።

(3) THS ገጽ 37 ይመ.

(4) ይህ ትምህርት በእንግሊዝኛ Adoptionsim ይባላል።

(5) ስለ ውርስ ኀጢአት ም.43ለ ይመ.

(6) THS ገጽ 45 ይመ.

(7) CT ገጽ 122 ይመ.

(8) ምሳሌ እንዲሆን ከጥምቀቱ ጋር ትምህርተ ሥላሴ ተያይዟል፤ ም. 25ለ2 ይመ.

(9) ለምሳሌ THS በገጽ 53 መንፈስ ቅዱስን፥ Alan Stibbs ደግሞ በ1ኛ ጴጥሮስ ትርጓሜው (IVP) የክርስቶስን ትስብእታዊ ነፍስ ማመልከቱን ይጽፋሉ።

(10) Bavinck ገጽ 387 ይመ.። የBavinck ትምህርት በከፊል በTHS ገጽ 55 ላይ ተጠቅሷል።

(11) THS ገጽ 6 ይመ.

# ምዕራፍ 82 - መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ሥላሴ

እስከ አሁን በዚህ ጥናት የእግዚአብሔርን መንፈስ ግብር ከብሉይ ኪዳን ዘመን ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በጋርዮሽ ጸጋ የመንፈስ ቅዱስን ተሳትፎ፥ እንደዚሁም ከትሥጉቱ ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ ከክርስቶስ ጋር የመንፈስ ቅዱስን መገኘትና ትብብር መርምረናል:: ይህን ስናደርግ ግን ምንም እንኳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎተ ኀሙስ በሰፊው ስለ ሌላው አጽናኝ ቢያስተምርም፥ የመንፈስ ቅዱስ ቀን በዓለ ኀምሳ መሆኑን ተረድተናልና ከቀድሞው ይልቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምንማረው በሐዋርያት ሥራ ከዚያ ቀን ጀምሮ ከተጻፈ አስተርእዮ ታሪክና ከዚያም በኋላ ከተጻፉ መልእክታት ነው::

ትምህርተ ሥላሴን ባጠናንበት ጊዜ አብን፥ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በአንድነት ተመለከትናቸው (1):: በዚህ ጥናት ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ ብቻ እየተመለከትን ትምህርታችንን እንቀጥላለንና አንዳንድ ጥቅሶችን ከዚህ አቅጣጫ ስንመረምር ተጨማሪ ትምህርት እናገኛለን:: ከምዕራፍ 25-28 ካገኘነው ትምህርት ውስጥ ለዚህ ምዕራፍ አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ) አንድ አምላክ ብቻ አለ::

ለ) በአንዱ አምላክ ሦስትነት አለ፤ ይህም በሦስቱ አካላት ማለት በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ተገልጧል::

ሐ) አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በህላዌ፥ በባሕርይ፥ በባሕርይ መገለጫዎች፥ በመለኮትና በፈቃድ አንድ ናቸውና ይተካከላሉ፤ አይበላለጡምም::

መ) አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በስም፥ በአካል (በአካልነት) እና በግብር ይለያሉ::

ሠ) የስም አጠራርና ቅደም ተከተል አለ፤ ይህም አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚለው ነው::

ረ) ሦስቱ አካላት በግብራቸው ይታወቃሉ፤ ይህም ምግባራዊ ሦስትነት ተብሏል::

ሰ) ከምግባራዊ ሦስትነት በስተ ጀርባ ህላዌያዊ ሦስትነት ይገኛል (2)::

ሸ) ከአርጌንስ ጀምሮ ከአበው መካከል ልዩ ልዩ ሊቃውንት የእግዚአብሔርን አንድነት ለመጠበቅ የሦስቱ ህላዌ በአብ መመሥረቱን አስተማሩ:: የደማስቆው ዮሐንስ ግን በተለይ የእግዚአብሔር አካልነት፥ አንድነትና ህላዌ በሦስቱ አካላት በአንድነት መሆኑን አስተማረ፤ ይህም የበለጠ ተቀባይነት ያለው ነው (3)::

የዚህ ምዕራፍ ዋና አሳብ፥ «ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፥ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» የሚለው ነው፤ ዮሐ. 15፥26:: በዚህ ጥቅስ ጌታችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ግብር ሐዋርያትን አስተምሯል፤ ሲያስተምርም ስለ ምግባራዊ ሦስትነት ልዩ ልዩ ነገሮችን ገልጧል:: ሊቃውንት ግን በዚህ ጥቅስ መሠረት ስለ ህላዌያዊ ሦስትነት ማስተማር በሚገባቸው ትምህርት ምንነት ላይ ላይስማሙ ይችላሉ:: ጥቅሱ መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሚወጣ (እንደሚሠርፅ) በግልጥ ያስተምራል፤ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ሁለት ዐይነት አስተሳሰብ አለ:: ይኸውም አንደኛው አስተሳሰብ ከወልድ ጭምር መሥረፁን የሚመለከት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ ሥርፀቱ ከወልድ ጭምር ነው ከተባለ አሠራረፁ ከአብ በሚሠርፅበት አኳኋን ነው ወይስ በሌላ ዐይነት መንገድ? የሚል ነው (4)::

እንግዲህ ከዚህ በፊት የጻፍነውን በዝርዝር ሳንደግም፥ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት፥ ፍጹም አምላክነትና ሥርፀት እንመርምር።

## ሀ) የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት

መንፈስ ቅዱስ መንፈስ በመሆኑ ባሕርዩ ረቂቅ (የማይታይ፥ የማይዳሰስ) ነው። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርና የሰው አካላዊነት አንድ ባይሆንም፥ ብዙ ግንኙነት አለ፤ ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯልና (5)። አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር መንፈስ መካከል ያለው ግንኙነት በፀሐይና በፀሐይ ብርሃን ወይም ሙቀት መካከል ያለውን ግንኙነት እንደሚመስል ያስባሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ግን በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት አካላዊ እንደሆነ በግልጥ ያስረዳል። ይህም በሚከተሉት ሁኔታዎች ይታያል:-

### 1. የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ በሥላሴ ግብር

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ አዘዘ፤ ማቴ. 28፥19-20። ከዚህ ትእዛዝ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ መሆን የሚያረጋግጡ በተለይ ሦስት ምክንያቶች ይታያሉ:-

ሀ) አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም እንጂ ስሞች ተብለው በብዙ ቁጥር ባለመቈጠራቸው ልዩ ግንኙነት እንዳላቸውና አንድ ዐይነት መሆናቸውን ማሰብ አመክንዮታዊ ነው።

ለ) አብና ወልድ አካላውያን መሆናቸው መንፈስ ቅዱስም አካላዊ እንደሆነ ማሰብን ያስከትላል።

ሐ) ሰዎች በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቃቸው ከእያንዳንዱ የሥላሴ አካል ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል፤ ከአብና ከወልድ ጋር የሚደረገው ይህ ግንኙነት አካላዊ እንደመሆኑ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው የሰው ግንኙነትም አካላዊ መሆኑ የማያጠራጥር ነው።

በማቴዎስ 28፥19-20 አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት እንደተጠቀሱ ሁሉ፥ በብዙ ሌሎች አንቀጾችም ግብራቸውና ግንኙነታቸው በአንድነት ይብራራል። በዚህ ሁኔታ ሲጠቀሱም በአካልነታቸው መካከል ልዩነት እንዳለ የሚጠቍም ምንም ፍንጭ አይገኝም። በዚህ ጥቅስ ግብራቸው አንድ ነው፤ ይኸውም ሰዎች በእነርሱ ስም ይጠመቃሉ። በብዙ ሌሎች አንቀጾች ግብራቸው ልዩ ልዩ ቢሆንም፥ ሥራቸው ወደ አንድ ግብ እንደሚመራ ይታያል። ለምሳሌ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ፥ «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔርም (የአብም) ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» ይላል፤ 2ቆሮ. 13፥14። እዚህ ላይ የሦስቱ አካላት በረከቶች (ጸጋ፥ ፍቅር፥ ኅብረት) የተለያዩ ቢሆኑም፥ ሦስቱ አካላት ለምእመናን አንድ ዓላማ ያላቸው መሆኑ ግልጥ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስም በመልእክቱ መክፈቻ ላይ «...ለእግዚአብሔር ምርጦች፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመታዘዝ በደሙ ለተረጨትና በመንፈስ አማካይነት ለተቀደሱት...» ብሎ ለምእመናን ሲጽፍ፥ አብ አስቀድሞ ዐውቆ እንደመረጣቸው፥ ወልድ ደሙን እንዳፈሰሰላቸውና መንፈስ ቅዱስ እንደቀደሳቸው በድኅነት የሦስቱን አካላት ግብር አብራርቷል፤ 1ጴጥ. 1፥1-2 አ.መ.ት.። እንደዚሁም ሦስቱ አካላት በአንድ አንቀጽ ሲጠቀሱ፥ አካልነት አንድ ዐይነት መሆኑንና ግብራቸው ልዩ ልዩ ቢሆንም፥ ግባቸውና ዓላማቸው አንድ መሆኑን ማየት ጠቃሚ ነው፤ ይህም ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ታላቅ ማረጋገጫ ነው (6)።

## 2. ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት

መንፈስ ቅዱስ «ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው» የእርሱ (የእግዚአብሔር) መንፈስ ነው፤ ሮም 8፥11:: እርሱም «ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ» ነው፤ ዮሐ. 15፥26:: ከአብ የሚወጣ (የሚሠርፅ) በመሆኑ ሁልጊዜ የሚወጣ እንጂ አንድ ጊዜ የወጣ እንደሆነ የሚያሳይ አይደለም፤ ግሱ የአሁን ጊዜ ግስ ነውና:: እንግዲህ አንድ ሰው፥ መንፈስ ቅዱስ እንደ ፀሐይ ብርሃንና ሙቀት ኢአካላዊ ኀይል ነው ማለት አይቻልምን? ብሎ ቢከራከር፥ መልሳችን እርሱ የእውነት መንፈስ ተብሏል፤ ደግሞም ቅዱስ መንፈስ ነው፤ ከዚህ የተነሣ መንፈስ ቅዱስ ኢአካላዊ ነው አይባልም ብለን መልስ መስጠት እንችላለን::

«የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር... ይመረምራል... ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም» (1ቆሮ. 2፥10-11) የሚለው ጥቅስ የመንፈስ ቅዱስን አምላካዊ አካልነት ይገልጣል፤ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ፥ «... እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና» በማለቱ ምእመናን በጸሎት ሲደክሙ በልባቸው እየኖረ እንደሚያግዛቸው እናስተውላለን፤ ይህም በአብ ፊት አካላዊ የሆነ ሥራ ነው፤ ሮም 8፥26-27::

## 3. ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት

በምዕራፍ 81 መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ጋር የሚሠራውን ሥራና ትብብራቸውን በዝርዝር መርምረናልና ይህ ግንኙነት አካላዊ እንደነበረና ይኸውም በሁለት አካላት መካከል ያለ ግንኙነት እንደሆነ አይተናል:: ጌታችን «ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» በማለቱ ይህ አጽናኝ እንደ እርሱ ያለ ሌላ አጽናኝ መሆኑን ገልጧል፤ ዮሐ. 14፥16:: ክርስቶስ «ሌላ» ሲል በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም መሠረት እንደ እርሱ ያለውን ወይም ከእርሱ የተለየውን ሊያመለክት ይችላል:: ሆኖም በግሪክ ቋንቋ ለእነዚህ ሁለት አሳቦች ሁለት ቃላት አሉና በዚህ ጥቅስ የግሪኩ ቃል «አሉስ» እንደ እርሱ ያለውን ያመለክታል (7)::

ደግሞም መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ አጽናኝ በመሆኑ፥ እንደዚሁም አጽናኝ ሆኖ ሐዋርያትን ሁሉ በማስተማሩ፥ ክርስቶስ የነገራቸውን ሁሉ በማሳሰቡ፥ ስለ ክርስቶስ በመመስከሩ፥ ሐዋርያትን ወደ እውነት በመምራቱ፥ የሚመጣውን በመናገሩ፥ ክርስቶስን በማክበሩና ለክርስቶስ ካለው በመውሰዱ አካላዊ መሆኑ ግልጥ ነው፤ ዮሐ. 14፥16:26፤ 15፥26፤ 16፥13::

## 4. ከምእመናን ጋር ያለው ግንኙነት

መንፈስ ቅዱስ ከምእመናን ጋር የሚገናኘው እነርሱ በክርስቶስ ስለሆኑ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪከበር ድረስ መንፈስ ቅዱስ ለምእመናን ራሱን አልገለጠም ነበር፤ «ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደምና» ተብሎ ተጽፏልና፤ ዮሐ. 7፥39:: ክርስቶስም፥ «እርሱ ያከብረኛል፤ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና:: ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና አልሁ» በማለቱ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ለሚኖሩ ራሱን መግለጥ ይወዳልና በሌላ መንገድ ራሱን ለመግለጥ የማይፈልግ ይመስላል፤ ዮሐ. 16፥14-15:: እርሱ የምእመናን አጽናኝና የእውነት መንፈስ በመሆኑ ለምእመናን ይናገራል (ዮሐ. 14፥26)፤ ይመራቸዋል (ሐ.ሥ. 8፥29:39፤ 10፥19-20፤ 16፥6)፤ እነርሱም የመንፈስ ቅዱስን እሳት ማዳፈን (1ተሰ. 5፥19)፥ ማሳዘን (ኤፌ. 4፥30) እና በእርሱ ፊት መዋሸት ይችላሉ፤ ሐ.ሥ. 5፥3:: መንፈስ ቅዱስ ኢአካላዊ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ አመክንዮታዊ ትርጉም አይኖራቸውም ነበር::

5. ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው፥ ሰዎች በክርስቶስ እስኪቈጠሩ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ለዓለም ሰዎች ራሱን አይገልጥም:: ሆኖም ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲደርሱ ይሠራልና እነርሱ በክርስቶስ አምነው በክርስቶስ ናቸው:: መንፈስ ቅዱስ ይህን ሲያደርግ ዓለምን ስለ ኀጢአት፥ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሣል:: ይህንም ሥራ ሲሠራ ስለ ክርስቶስና ስለ ሰይጣን ሰዎች ያላቸው አሳብ ሲለወጥ፥ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ዘንድ የሚሠራውን ላያስተውሉ ይችላሉ፤ ዮሐ. 16፥8-11፤ ሐ.ሥ. 7፥51:: በዚህ ምክንያት ሰዎች በክርስቶስ እስኪያምኑ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ኢአካላዊ ኀይል እንደሆነ ማሰብ ይችላሉ::

6. ከአስተርእዮ ጋር ያለው ግንኙነት

የእግዚአብሔር መንፈስ በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ለነቢያት እንደገለጠ በሰፊው አብራርተን ገልጠናል (8):: በአዲስ ኪዳንም እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ሲገልጥ ብዙ ጊዜ ይታያል:: እውነትንም የሚገልጠው በአካላዊ መንገድ መሆን አለበት፤ እንደዚህ ባይሆን ኖሮ፥ ሰው አካላዊ በመሆኑ ነገሩን አያስተውለውም ነበር:: በዚህ መሠረት በኢየሩሳሌም ጉባኤ ውሳኔ፥ «... ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል» ተብሎ ተጽፏል፤ ሐ.ሥ. 15፥28 አ.መ.ት.::

ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጽፉም፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲጽፉ ይመራቸውና ስሕተትን ከመጻፍ ይጠብቃቸው ነበር (9)፤ በዚህ መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ... ይጠቅማል» በማለት ጽፏል፤ 2ጢሞ. 3፥16-17:: መንፈስ ቅዱስ ኢአካላዊ ኀይል ቢሆን ኖሮ፥ ይህን ሥራ መፈጸም አይችልም ነበር::

7. የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነትና የተሰነዘረበት ተቃውሞ

የአርዮስና የሰባልዮስ ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት አያምኑም:: እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ካልሆነ እንዴት ያለ ነው? ብለን ብንጠይቃቸውና ምናልባት አንድ ዐይነት የእግዚአብሔር ኀይል ነው ቢሉ፥ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስና በኀይልም ቀባው» የሚለው በመንፈስ ቅዱስና በኀይሉ መካከል ማለት በማንነቱና በግብሩ መካከል ልዩነት እንዳለው ያሳያል (ሐ.ሥ. 10፥38፤ እንደዚሁም ሉቃ. 1፥35፤ 4፥14፤ ሮም 15፥13፤ 1ቆሮ. 2፥14 ይህን ልዩነት ይገልጣሉ)::

ሌሎች ደግሞ «ፕኑማ» በግሪክ ቋንቋ ኢጾታዊ ቃል ነውና በዚህ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ እንደ ማናቸውም ዐይነት «ነገር» አካላዊነቱ ሊታሰብ አይቻልም ይላሉ (10):: እውነት ነው፤ ፕኑማ ኢጾታዊ ነው፤ ሆኖም በዮሐንስ 16፥14 «እርሱ» ተብሎ የተተረጐመው የግሪኩ ቃል «ኤካይኖስ» ተባዕታይ ጾታ እንጂ ኢጾታዊ አይደለም፤ እንደዚሁም በኤፌሶን 1፥14 «እርሱ» በመባል የተተረጐመው የግሪኩ ቃል «ሆስ» መንፈስ ቅዱስ በተባዕታይ ጾታ የሚነገር መሆኑን ያሳያል:: ከዚህም ሁሉ በላይ መንፈስ ቅዱስ እንደ ክርስቶስ ያለ ሌላ «ፓራክሊቶስ» (ጰራቅሊጦስ፥ አጽናኝ) ነው:: ክርስቶስ በ1ኛ ዮሐንስ ፓራክሊቶስ (እዚህ ላይ በአማርኛ «ጠበቃ» ተብሎ ተተርጕሟል) ቃሉ ምቾት ወይም ማጽናኛ ተብሎ መተርጐም አይችልምና ይህ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት የሚያረጋግጥ ነው::

## ለ) የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክነት

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ መንፈስ መሆኑንና ከአብ የሚወጣ መሆኑን ከተረዳን፥ እርሱ መለኮታዊ የመሆኑ አሳብ ተከትሎ ይመጣል፤ ዮሐ. 15፥26:: በሌላ አነጋገር አምላክነቱና አካልነቱ የተያያዙ ናቸው፤ ይህንም በምዕራፍ 26ሀ3 በብዙ ጥቅሶች ውስጥ አይተነዋል:: እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ፍጹም አምላክ መሆኑን እንዴት ማስተዋል እንደሚያስፈልገን ማተት ይገባናል::

የሦስቱን አካላት አንድነት፥ በተለይ በፈቃድ፥ በባሕርይና በህላዌ በምዕራፍ 26ለ፥ ልዩነታቸውን ደግሞ በምዕራፍ 26ሐ ላይ መርምረናል:: የሦስቱን ልዩነት የምናውቀው በራሳችን ሕይወት በሚያከናውኑት ግብራቸው ነው፤ ይህም በዐጭሩ አብ በክርስቶስ የመረጠን በመሆኑ (ኤፌ. 1፥4)፥ ወልድ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ የተሸከመልን በመሆኑ (1ጴጥ. 2፥24) እና መንፈስ ቅዱስ በእውነት ቃል የወለደን በመሆኑ ላይ (ዮሐ. 3፥5፤ ያዕ. 1፥18) የሚታይ ነው:: ከዚህ ላይ የሚታየው ምግባራዊ ሦስትነትም ወደ ህላዌያዊ ሦስትነት ያመለክተናል (11)::

«አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው፥ እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና» (ዮሐ. 5፥26) ብሎ በመናገሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወት በራሱ ስላለው ለሌሎች ሕይወትን መስጠት ይችላል፤ ዮሐ. 5፥26-29:: ክርስቶስ በራሱ ሕይወትና ግብር እንዳለው ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ሲወጣ በራሱ ሕይወትና ግብር እንዳለው ማሰብ ይገባናል፤ ዮሐ. 15፥26:: እርሱን የአብ መሣሪያ አድርገን ልንመለከተው አይገባም፤ በራሱ ሕይወት አለ፤ ራሱን የቻለም ነው (12):: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል...» የሚለውን ሲያብራራ፥ «በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም» በማለቱ እስትንፋስ እግዚአብሔር ለአስተርእዮ ያለውን አስፈላጊነት ሲገልጥ፥ የመንፈስን ፍጹም አምላክነትም ጭምር ያሳያል:: ምክንያቱም የሰው መንፈስ በውስጡ ያለውን በመጠኑ መርምሮ ሲያውቅ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ግን ልዩ አካል በመሆኑ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሊመረምር ይችላል፤ 1ቆሮ. 2፥10-12::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲጠመቁ በማዘዙ፥ የመንፈስ ቅዱስን ህላዌና ፍጹም አምላክነት አረጋገጠ፤ ማቴ. 28፥18-20:: አገላለጡ አብ ህላዌ እንዳለው ሁሉ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ህላዌ እንዳላቸው፥ እንደዚሁም አብ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሁሉ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አምላክ መሆናቸውን ያሳያል:: ቅዱስ አትናቴዎስ ከአርዮሳውያን ጋር የተከራከረበትን የመንፈስ ቅዱስን ሙሉ ህላዌና ፍጹም አምላክነት በዚህ አንቀጽ ማየት አለብን፤ አለበለዚያ የሰው ጥምቀት በእግዚአብሔር ስምና በሁለት ፍጡራን በመፈጸሙ ላይ የሚያተኩር ይሆናል (13)::

## ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ሥርፀት

ትምህርተ ሥላሴን በመረመርን ጊዜ በምዕራባውያንና በምሥራቃውያን መካከል ከጥንት ጀምሮ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርፀት ከፍ ያለ መለያየት እንዳለ አይተናል፤ ይህም ልዩነት ሊታይ የቻለው፥ ምዕራባውያን መንፈስ ቅዱስ

ከአብና ከወልድ ይሠርጻል ሲሉ፥ ምሥራቃውያን ከአብ ብቻ እንደሚሠርፅ በማስተማራቸው ነው (14)። የዚህን ልዩነት መንሥኢ ምክንያቶች ማስተዋልና መፍትሔ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ማሰብ ይገባናል (15)።

በመጀመሪያ ማስተዋል የሚገባን ሁለቱም ወገኖች በዮሐንስ 15፥26 መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከአብ በመውጣቱና በክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተላከ በመሆኑ ላይ የሚስማሙ መሆናቸውን ነው፤ በሌላ አነጋገር ስለ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ምግባራዊ ግንኙነት ያላቸው አሳብ አንድ ነው። ልዩነት ያላቸው በህላዌያዊ ግንኙነታቸው ላይ ነው።

አውግስጢኖስ የእግዚአብሔር ህላዌ ፍቅር መሆኑን በመቀበል መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ መካከል የፍቅር አገናኝ መሆኑን በማመኑ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ መሥረፁን አመነ፤ እንደዚህ ሲያስተምር መንፈስ ቅዱስ በተለይ ከአብ በመሥረፁ ላይ አተኰረ። ከአውግስጢኖስ ቀጥለው ምዕራባውያን ሊቃውንት ሥርፀቱ ከአብና ከወልድ ሲሆን በአንድነት በመሆኑ ላይ አተኰሩ። ምሥራቃውያን ግን ለዚህ የምዕራባውያን አጽንዖት ትኩረት አልሰጡም።

ምሥራቃውያን ጣምራ ሥርፀት የእግዚአብሔርን አንድነት ያፈርሳል የሚል ሥጋት ነበረባቸው። ምክንያቱም ሊቃውንታቸው አብ የመለኮት ምንጭና ራስ መሆኑን ሲያምኑ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አምላክነታቸውን ከአብ እንደተቀበሉ አሰቡ። እንግዲህ ሥርፀቱ ከአብና ከወልድ ከሆነ፥ በሥላሴ ሁለት ምንጮች አሉና በእግዚአብሔር አንድነት ላይ የተሰጠው ትምህርት ውድቅ ሊሆን እንደሚችል ገመቱ። ምዕራባውያን የምሥራቃውያንን ትምህርት ሲመረምሩት፥ አብ የመለኮት ምንጭ ከሆነ፥ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ተገዢነት፥ እንደዚሁም በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እኩልነት ላይ ችግር እንዳያስከትል ይፈሩ ነበር።

ዮሐንስ ካልቪን ስለ ቅድስት ሥላሴ ሲያስተምር ሦስቱ አካላት በማናቸውም ደረጃ እኩል መሆናቸውና አምላክነታቸው ውሳጣዊ የእርስ በርስ ኅብረታቸውና ህላዌያቸው መሆኑን አሳየ (16)።

የምዕራባውያን የጣምራ ሥርፀት ትምህርት በሁለት በኩል ያለ መለኮትን የማሳየት ጥቅም ያለው ይመስላል። የመጀመሪያው፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ በመላኩ፥ እግዚአብሔር በህላዌው እንዴት እንዳለ ራሱን በግብሩ ይገልጣል። ሁለተኛው፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት ምግባራዊ ብቻ ሳይሆን ህላዌያዊ መሆኑን ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን በግብሩ ላይ ያተኵራል፤ ምክንያቱም ሰዎች እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ የሚደርሱት በግብሩ ነው። እንግዲህ ከዚህ የሚመነጨው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ህላዌ ሥርፀት ያስተምራልን? የሚለው ነው። የዚህ ጥያቄ መልስ በዮሐንስ 15፥26 ትርጕም ውስጥ የሚገኝ ነውና ዛሬ ከሊቃውንት የሚበዙቱ ጥቅሱ ይህን አያስተምርም ይላሉ። አሁን አመክንዮታዊ አስተሳሰብ ሆኖ የሚታየው ግን ከአውግስጢኖስ ዘመን ጀምሮ የተገኘው አሳብ ነው። ለዚህ ትርጕም በተለይ ቀጥሎ ያሉትን ሁለት ሐረጎች እንመልከት፦

«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ...»፤ ዮሐ. 14፥26።

«እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፥ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ...»፤ ዮሐ. 15፥26።

ከእነዚህ ሐረጎችም የሚከተሉትን እውነቶች መረዳት እንችላለን:-

1. የመንፈስ ቅዱስን «መላክ» በሁለት መንገድ ልንመለከተው እንችላለን:-

ሀ) አብ መንፈስ ቅዱስን በክርስቶስ ስም ይልካል (14፥26)፤

ለ) ወልድ መንፈስ ቅዱስን ከአብ ዘንድ ይልካል (15፥26)፤ «ከአብ ዘንድ» በማለቱ በአብ ስም መላኩን ያሳያል ማለት አይከብድም።

ስለዚህ አብና ወልድ በአንድ «ስም» ማለት በአንድነት መንፈስ ቅዱስን ይልካሉ። ይህም ስለ መንፈስ ቅዱስ ጣምራ ሥርፀት አንሰልም ያስተማረው መሠረታዊ ትምህርት ነው (17)።

2. መንፈስ ቅዱስ «ከአብ የሚወጣ» (15፥26) ነው፤ ሁልጊዜ ከአብ እየወጣ የሚኖር ማለት ነው፤ ይህም የግል አካልነት ገንዘብ፥ ማለትም ወደ የሚያደርገው ነው። ደግሞም መንፈስ ቅዱስ «ይላካል»፤ በአብና በወልድ ተልኳልና መላኩ በበዓለ ኀምሳ ቀን ተፈጸመ። ስለዚህ ከአብ መውጣቱ ሁልጊዜ የሚኖር ሲሆን፥ መላኩ በዓለም ታሪክ አንድ ጊዜ የተፈጸመ ነው። ሌላም ልዩነት አለ፤ ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ከአብ በመሥረፁ ገቢር (አድራጊ) ሲሆን፥ መላኩ ግን ተገብሮ (ተደራጊ) ነው።

በዮሐንስ 15፥26 መሠረት የመንፈስ ቅዱስ «ሥርፀት» እና «መላክ» የተያያዙ ናቸውና ምግባራዊ «መላኩ» ዘለዓለማዊውን የህላዌ መውጣት እንደሚገልጥ ማሰብ አመክንዮታዊ ነው፤ አለበለዚያ ምግባራዊ መላኩ የእግዚአብሔርን ህላዌ ይሸፍነዋል፤ አያብራራውምም።

3. መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለሚሠርፅ «የአብ» ነው፤ እንደዚሁም «የልጁ» (ገላ. 4፥6) እና «የልጅነት መንፈስ» (ሮም 8፥15) ነው። መንፈስ ቅዱስ በአብ ለግብር ከመላኩ በፊት፥ ከአብ በህላዌ ይወጣ የነበረ በመሆኑ፥ በወልድ ከመላኩ በፊት፥ ከወልድ እየወጣ መኖሩን ማሰብ ተገቢ ይመስላል።

4. ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር ነበረ፤ እግዚአብሔርም ብቻ ነበረና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ወጥቶ ወዴት ይሄዳል? ተብሎ ቢጠየቅ፥ መልሳችን ወደ ወልድ ይሄዳል ሊሆን ነው፤ ከወልድስ ወዴት ይሄዳል? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ወደ አብ ይመለሳል የሚል ሊሆን ነው። ይህም በውስጣዊ የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ካለው አስተሳሰብ ጋር ሊስማማ ይችላል (18)።

ቅድስት ሥላሴ ምሥጢር ነውና ከግብሩ ይልቅ ህላዌው ምሥጢር ነው። መንፈስ ቅዱስ ከወልድ አይሠርፅም የሚል አመለካከት ያላቸው አሉ። በዚህ አሳብ ላይ ሁለት ዐይነት አስተሳሰብ ቢኖርም፥ ለአብያተ ክርስቲያናት መለያየት በቂ ምክንያት የሚሆን አይመስለንም (19)። በሥርፀቱ ጉዳይ መለያየትን ከመፈለግ ይልቅ ወደሚያስማማ ነጥብ መምጣቱ ተመራጭ ነው፤ ለዚህም በሠለስቱ ምእት ቅዳሴ የተጻፈውን ምስክርነት ማስተዋሉ ሊረዳ ይችላል:-

«በመጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ በተለይ በሠለስቱ ምእት ቅዳሴ ቍጥር 41 ላይ፥ «... መንፈስ ቅዱስም ከአብ እንደ ወጣ (እንደሠረፀ)፥ ከወልድም እንደነሣ ይናገራል» የሚለው በዚህ ጉዳይ ላይ ባሉት ሁለት አመለካከቶች ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን መለያየት የማጥበብ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።» መጽሐፈ ቅዳሴ ገጽ 99 ቍ. 41።

## መ) ግብረ መንፈስ ቅዱስ (20)

እግዚአብሔር አንድ ነውና በእግዚአብሔር ዘንድ ያሉ የሦስቱ አካላት ፈቃድና ዓላማ አንድ ነው:: የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ግብር ልዩ ሲሆን፥ የወልድ ግብር የአብን ግብር እንደሚከተል ሁሉ፥ የመንፈስ ቅዱስም ግብር የወልድን ግብር ይከተላል:: ሰው ይህን ካልተረዳ፥ ያለ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ ቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ሊደርስ እንደሚችል ሳያስብ አይቀርምና በተለያዩ ልምምዶችና መንፈሳውያት ምሥጢራት ሊሳተፍ ይችላል፤ ለምሳሌ፥ ወደ መናፍስት ጠሪዎች፥ ምዋርተኞች፥ ሞራ ገላጮች፥ አስማተኞች፥ መተተኞች... ወዘተ ሊሄድ ይችላል:: የእግዚአብሔር ሰው ግን በማናቸውም ዐይነት ባዕድ አምልኮ ሳይሳተፍ፥ በክርስቶስ አምኖ ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ራሱን በማዘጋጀት በሰው ፍልስፍናና ሥርዐት ሳይወሰድ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይመራል:: ምክንያቱም አማኙ፥ የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ሚና በአብ ፈቃድ መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገለጠውን የክርስቶስን ሥራ ወደ ፍጻሜ ማድረስ መሆኑን ያውቃል::

መንፈስ ቅዱስ በፍጥረትና በመግቦተ እግዚአብሔር ለዓለም ሕይወትንና ኀይልን ይሰጣል፤ ዘፍ. 1፥2-3፤ ኢዮብ 26፥13፤ መዝ. 33፥6፤ 104፥30:: የፍጥረት የመጨረሻ መልክ፥ ውበትና ጽናት ከመንፈስ ቅዱስ የተገኙ መሆናቸው ይታያል:: እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በሳይንስ፥ በኪነ ጥበብ፥ በአስተዳደርና በተሰማሩበት የሥራ መስክ ሁሉ እንደሚያነቃቃቸውና ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው እንመለከታለን፤ ዘጸ. 28፥3፤ 31፥2-6፤ 35፥35፤ 1ሳሙ. 11፥6፤ 16፥13-14:: ይህም የጋርዮሽ ጸጋ ሥራ እንደሆነ በምዕራፍ 80 መርምረነዋል::

ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ድኅነት መንፈስ ቅዱስ የሚያከናውነውን ሥራ ከፍተኛ ስፍራ ሰጥቶ ይገልጠዋል:: መንፈስ ቅዱስ በድኅነት የሚሠራውን ሥራ በአራት ከፍለን በዐጭሩ በመግለጥ ልንደመድመው እንችላለን:-

1. ለሰው ድኅነት የሚያስፈልገው አስተርእዮ ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲጻፍ በማድረግ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል... እንናገራለን...» (1ቆሮ. 2፥13)፤ ሐዋርያው ጴጥሮስም፥ «... በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ...» (2ጴጥ. 1፥21) ብለው በመጻፋቸው አስተርእዮተ እግዚአብሔር እንዴት ወደ እኛ እንደደረሰ አሳይተዋል፤ «ትምህርተ አስተርእዮ» የሚለውን አንደኛውን ጥናት ይመልከቱ::

2. ለክርስቶስ ሥጋን በማዘጋጀቱና በሕይወቱ ሁሉ አብሮ በመገኘቱ፤ ክርስቶስ ለኀጢአት መሥዋዕት እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ ሥጋን አዘጋጀለት (ሉቃ. 1፥35፤ ዕብ. 10፥5-7)፤ በጥምቀት ጊዜ በክርስቶስ ላይ ወረደና በእርሱም ላይ ኖረ (ዮሐ. 1፥32፤ 3፥34)፤ ምዕራፍ 81 ይመልከቱ::

3. ክርስቶስ የሞተላቸውን ሰዎች አንድ በአንድ ወደ ድኅነት በማድረሱ፤ መንፈስ ቅዱስ ይህን ሥራ የጀመረው በብሉይ ኪዳን ዘመን ሲሆን፥ አሁን ይህንኑ በማከናወን ይቀጥላል፤ በክርስቶስ ዳግም ምጽአትም የተሟላ ያደርገዋል:: በዐጭሩ ለሰዎች አዲስ ልደት በመስጠቱና በእነርሱ ውስጥ በመኖሩ ይህን ሥራ ይፈጽመዋል ማለት እንችላለን፤ ዮሐ. 3፥3-6፤ 14፥15-17፤ ቲቶ 3፥5-7:: የድኅነትን ግብር በዚህ ጥናት በሰፊው ልንገልጠው እንሞክራለን::

4. ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ሁሉ ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ኀይል እንዲኖራት በምእመናን ላይ በመውረዱና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመኖሩ፤ ክርስቶስ በምድር ላይ፥ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ... እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» በማለት በመጨረሻ ጊዜ የተናገረውን የተስፋ ቃል መንፈስ ቅዱስን በማፍሰስ ፈጸመው፤ ሐ.ሥ. 1፥8፤ 2፥33:: መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲኖር፥ ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል (ዮሐ. 15፥26፤ ሐ.ሥ. 5፥32)፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራል (ዮሐ. 16፥13-14)፤ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያድላል (1ቆሮ. 12፥4-13፤ ዕብ. 2፥4)፤ በወንጌል አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ይመራታል (ሐ.ሥ. 8፥29፤ 13፥2-4፤ 16፥6-7)፤ ከስሕተትም ይጠብቃታል፤ 1ዮሐ. 2፥27::

# ማስታወሻ

(1) ትምህርተ ሥላሴ በዐጭሩ (ም. 26ሀ) ለዚህ ትምህርት ምቹ መግቢያ ይሆናል::

(2) ምግባራዊና ህላዌያዊ ሦስትነት በም. 25ሀ2 እና በም.26.4 ተብራርቷል::

(3) ስለ እግዚአብሔር ህልውና በተለይ በም. 26መ እና 27ሀ5 ይመ.

(4) ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርፀት ም.16ለ፥ ም.26ሐ 3ሐ (እና ማስታወሻ 4) ም.27ለ3 ይመ.

(5) ስለ አካል ትርጉም ም.25መ1 ይመ.

(6) ስለ ሦስቱ አካላት የሚገልጡ አንቀጾችንና በአንቀጾች ውስጥ ስላለው ቅደም ተከተል ም. 25ለ-ሠ ይመ.

(7) በዮሐ. 14፥16 ስለ «አሎስ» (የሌላ) ትርጉም THS ገጽ 54 እና ማስታወሻውን ይመ.

(8) ም. 7መ ይመ.

(9) «መጽሐፍ ቅዱስና እስትንፋሰ እግዚአብሔር» የሚለውን ም.7 ይመ.

(10) በእንግሊዝኛ በልዩ ልዩ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ «it» ተብሎ ተገልጧል፤ ሆኖም እርሱ አካላዊ በመሆኑ «He» ብሎ መግለጥ ትክክለኛ ነው::

(11) ም. 25ለ2 ይመ.

(12) ከሦስቱ አካላት መካከል እያንዳንዱ ራሱን የቻለ እንደሆነና ይህ Autotheos በመባል የሚታወቅ መሆኑን በም.26ሀ3 መጨረሻ ላይ አትተናል::

(13) THS ገጽ 31 ይመ.

(14) ም. 27ሀ5 ይመ.:: «... እና ከወልድ» ማለት Filioque የሚለው የላቲን ቃል በኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት በ589 ዓ.ም. ከሦስተኛው ቶሌዶ ጉባኤ ጀምሮ ተጨምሯል::

(15) በዚህ ንኡስ ርእስ ሥር አቀራረባችን በተለይ በTHS ገጽ 72-78 ላይ የተመሠረተ ነው።

(16) ስለ ቅድስት ሥላሴ የሚሰጠውን የካልቪንን ትምህርት በም.27ሀ7 ለማሳየት፥ የሦስቱን አካላት መንፈሳዊ ግንኙነት ደግሞ በም.26መ ለማብራራት ሞክረናል።

(17) አንሰልም፥ ምሥራቃውያን ትምህርታቸውን በዮሐንስ 15፥26 ላይ ብቻ በመመሥረታቸው፥ ወደ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዳልደረሱ በማመን ወቀሣቸው። ስለ አንሰልም ትምህርት Church Society ያሳተመውን Churchman Vol. 118 No 3 2004 ገጽ 219-234 ይመ.። ለምሥራቃውያን አሳብ ት.መ. ገጽ 59-63 ይመ.

(18) ም. 26መ እና ከሐተታ ጋር የቀረበውን ንድፍ ይመ.

(19) ም. 26 ማስታወሻ (4) ይመ.

(20) በዚህ ንኡስ ርእስ Berkhof ገጽ 98c ላይ ያለውን አቀራረብ እንከተላለን።

# ምዕራፍ 83 - መንፈስ ቅዱስና የድኅነት ጸጋ

ስለ ጋርዮሽ ጸጋና ስለ ልዩ ጸጋ መናገር የተለመደ እንደሆነ አይተናል፤ ልዩ ጸጋ የሚያድን ጸጋም ተብሏል (1)። ይህም ጸጋ «የእግዚአብሔር ጸጋ» (ሐ.ሥ. 11፥23፤ 13፥43፤ 14፥26፤ 15፥40፤ 20፥24) እና «የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ» (ሐ.ሥ. 15፥11፤ 2ቆሮ. 13፥14) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፥ አንዳንድ ጊዜ ከሦስቱ አካላት የማን እንደሆነ ሳይነገር በሰዎች ላይ «ጸጋ» እንደነበረ እናነባለን፤ ሐ.ሥ. 4፥33፤ 18፥27። ዐልፎ ዐልፎ ደግሞ የወንጌል መልእክት «የጸጋ ቃል» ተብሏል፤ ሐ.ሥ. 14፥3፤ 20፥32።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ሲናገር፥ ስለ መዳኑ፥ «በጸጋው የጠራኝ እግዚአብሔር...»፥ ስለ ሐዋርያነቱ፥ «በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም»፥ ስለ አገልግሎቱ፥ «የተሰጠኝን ጸጋ»፥ ሌሎች መረዳታቸውን እና ችግሩን መቋቋም ስለ መቻሉ፥ «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ በድካም ይፈጸማልና» በማለት ጽፏል፤ ገላ. 1፥15-16፤ 1ቆሮ. 15፥10፤ ገላ. 2፥9፤ 2ቆሮ. 12፥9። እንግዲህ በሐዋርያው ታሪክ ጸጋ በእርሱ ውስጥ፥ በእርሱ አማካይነት (በአገልግሎቱ)፥ በእርሱ ላይና ለእርሱ እንደሠራ እናያለን።

ብዙ ጊዜ እንደተመለከትነው የድኅነት ጸጋ ወይም ድኅነት በሰው ሕይወት እንዲፈጸም ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ መንፈስ ተብሏልና፤ ዕብ. 10፥29።

አብዛኛውን ጊዜ «ጸጋ» በክርስቶስ ሥራ የተገኘውን ቤዛነት በሰው ሕይወት ውስጥ በሥራ ላይ የሚያውለውን የእግዚአብሔርን ሞገስ ያመለክታል። ጸጋ ሰው በመጽደቁ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚደረግለትን ይቅርታና ያለውን ተቀባይነትም ያሳያል፤ ሮም 3፥24፤ 5፥2:20-21፤ ቲቶ 3፥5-7። በተጨማሪም ጸጋ የእግዚአብሔርን ስጦታዎች ሁሉ፥ ጠቅላላ የድኅነትን በረከትና የምእመናን ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚያፈራውን ፍሬ ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል፤ ሐ.ሥ. 11፥23፤ 18፥27፤ ሮም 5፥17፤ 2ቆሮ. 9፥14፤ ኤፌ. 4፥7፤ 1ጴጥ. 3፥7፤ ያዕ. 4፥6። ይህ ጸጋ ሕያውና የሚሠራ ኀይል ነው፤ 1ቆሮ. 15፥10፤ 2ቆሮ. 12፥9፤ 2ጢሞ. 2፥1። በዚህ አሳብ መሠረት በጸጋና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ልዩነት እጅግ አነስተኛ ነው፤ ለምሳሌ ሐዋርያት «መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች» ለአገልግሎት መምረጥ በፈለጉ ጊዜ፥ ከተመረጡት መካከል እስጢፋኖስ «ጸጋንና ኀይልን ተሞልቶ» በሚል ሐረግ ተነግሮለት እናገኛለን፤ ሐ.ሥ. 6፥3:5:8። እንግዲህ በአዲስ ኪዳን በተለይ በድኅነት ዐውድ ስለ ጸጋ ስናስብ፥ በሰው ዘንድ ምንም ምክንያት ሳይገኝ፥ ጸጋ ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የሚገኝ ሞገስ መሆኑንና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሰው የሚያገኘው ድኅነት መሆኑን መገንዘብ ይገባናል (2)።

## ሀ) የድኅነት ጸጋ ዐውድ

ሰው በኀጢአት በመበከሉና ፍጥረት ከሰው ጋር ዐብሮ ክብሩን በማጣቱ፥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድስ መንፈስ ነው። መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ በአዲስ ፍጥረት ራስ ማለት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ወረደ፤ ክርስቶስም ሁለተኛው ሰውና የኋለኛው አዳም ሆኖ የጽድቅን መንግሥት እንደገና ይመሠርታል፤ 1ቆሮ. 15፥45-49፤ ዘፍ. 1፥26-28፤ መዝ. 8፥3-8። ይህ ትንቢት ገና አልተፈጸመም (ዕብ. 2፥8)፤ «ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ ዐብሮ

በመቃተትና በምጥ መኖሩን» እና ምእመናን የሰውነታቸው «ቤዛ የሆነውን ልጅነት» በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን እንመለከታለን፤ ሮም 8፥22-25:: ስለዚህ አሁን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ገና ስላልተሟላ ፍጹም እንዲሆን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ይጠባበቃል (3)::

እንግዲህ ከበዓለ ኀምሳ ቀን ጀምሮ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ፥ የእያንዳንዱን ሰው ለውጥ፥ የቤተ ክርስቲያንንና የዓለምን አስተዳደር፥ በመጨረሻም አዲሱን ዘመን የማስገባቱን ተግባር ያጠቃልላል:: በ«ሐዋርያት ሥራ» ታሪክ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዴት እየፈጸመ እንዳለ እንመለከታለን:: ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ክርስቶስን እንደ ጌታቸውና እንደ አዳኛቸው አድርገው እንደሚያምኑበት እናነባለን፤ ሐ.ሥ. 1፥8:: አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች በአንድነት ሲድኑ (ሐ.ሥ. 2፥41፤ 5፥14፤ 6፥7፤ 8፥14፤ 11፥21-24)፥ በሌላ ጊዜ አንድ ሰው ብቻ ማመኑ ተተርኳል፤ ሐ.ሥ. 8፥36-38፤ 9፥10-12:: በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር አምኖ ሲጠመቅ እንመለከታለን፤ ሐ.ሥ. 10፥24:44-48፤ 16፥14-15:28-34:: ስለዚህ አዲሱ የምእመናን ኅብረተሰብ በመንፈስ ቅዱስ ተግሣጽ፥ ኀይል፥ ምሪትና አስተዳደር ይሰበሰባል፤ ይጸናል፤ ይስፋፋልም፤ 5፥3-4፤ 6፥3:5፤ 7፥55፤ 10፥19:44-48፤ 13፥2-4፤ 15፥28-29፤ 16፥6-10:: በሐዋርያት፥ አገልግሎትና የሚመጣው ዘመን ኀይላት በአሁኑ ዘመን ተገለጡ፤ ሐ.ሥ. 2፥43፤ 3፥1-10፤ 5፥12፤ 2ቆሮ. 12፥12፤ ዕብ. 2፥4:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትሥጉቱ የጀመረውን አገልግሎት ቀጠለ፤ ማቴ. 16፥18፤ ሐ.ሥ. 1፥1-2::

በበደልና በኀጢአት የሚገኝ ሰው በክርስቶስ ክብር እንዲሳተፍ ረጅም ጉዞ መሄድ እንዳለበት ግልጥ ነው:: ይህን እንድናስተውል፥ በመጀመሪያ የሰውን ሁኔታ፥ ቀጥሎም አስፈላጊውን ለውጥ ማጥናት ያስፈልገናል::

## ለ) የድኅነት ጸጋ አስፈላጊነት

ይህን ንኡስ ክፍል በምናጠናበት ጊዜ፥ ከዚህ ቀጥሎ ለተጻፉት አራት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይረዳናል (4):-

1. ሰው ለምን ተፈጠረ?

«እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ:: እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው»፤ ዘፍ. 1፥26-27::

በፍጥረት የእግዚአብሔር ባሕርይ ተገልጧል:: ከፍጥረት ታሪክ (ዘፍ. 1፥1-31) እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ መሆኑን፥ ውበትን፥ ሥርዐትንና የተለያየ መሆንን የሚወድ፥ የሚናገር፥ የሚያዘዝና የሚገዛ፥ መልካምንና ክፉን የሚለይ፥ እንደዚሁም አእምሮ ካላቸው ከሌሎች ፍጡራን ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያውቅና የሚከታተል መሆኑን እናስተውላለን:: ሰውም ደግሞ እነዚህ ባሕርያት አሉትና በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የእግዚአብሔር መልክ ይታይበታል:: በአዲስ ኪዳንም ምእመናን፥ «ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ» ተብለው በመታዘዛቸው (ኤፌ. 4፥24)፥ ሰው እንደ እግዚአብሔር ጻድቅና ቅዱስ መሆን እንደሚገባውና በመጀመሪያ ከእነዚህ ባሕርያት ጋር እንደተፈጠረ እናስተውላለን::

እንግዲህ ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ በሕይወቱ ሁሉ እግዚአብሔርን መምሰል ይገባዋል፤ ይህንም በማድረግ እግዚአብሔርን ያከብራል። ሰው እግዚአብሔርን እንዴት ያከብራል? በኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ በተለይ ሦስት ነገሮችን እንመለከታለን:-

ሀ) ሰው በሥራው እግዚአብሔርን ያከብራል፤ እግዚአብሔር ሠራተኛ ነውና ሰው ምሳሌውን መከተል አለበት። ሥራ የሰው ውድቀት ውጤት ሳይሆን ከመጀመሪያ ጀምሮ ለፍጥረቱ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ነበረ፤ ዘፍ. 2፥1-3፤ ዘጸ. 20፥8-9። ሰው ገነትን እንዲያበጃትና እንዲጠብቃት ታዘዘ፤ ሥራውም ተመጣጣኝና አስደሳች ነበረ። እዚያም ሳለ አዳም፥ እግዚአብሔር ላቀረበለት ነፍስ ላለው ሁሉ ስም ሰጠ፤ በዚህም በፍጥረት ላይ ሥልጣኑን አሳየ፤ ዘፍ. 2፥15:19-20።

ለ) ሰው በማረፉ እግዚአብሔርን ያከብራል፤ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ከሠራ በኋላ በሰባተኛው ቀን ከመፍጠር እንዳረፈ ሁሉ፥ ሰውም በሰባተኛው ቀን እንዲያርፍ ታዘዘ፤ ዘፍ. 2፥2-3፤ ዘጸ. 20፥10-11። ሰው ከሥራው ሲያርፍ ደስ ይለዋል፤ ሆኖም በዕረፍት ቀን የሚያደርገው ልዩ ልዩ ነገር አስደሳች ቢሆንም፥ ሁሉን በእግዚአብሔር ፊት ያደርገዋልና ለእግዚአብሔር ክብር ሊያደርገው ይገባል።

ሐ) ሰዎች ወንዶችና ሴቶች ሆነው በግንኙነታቸው እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ በመልኩ ስለፈጠራቸው እኩልነታቸውን አረጋገጠ። ሴት ለወንድ በመፈጠሯና ወንድ ከሴት በመወለዱ የተለያየ ሚና ቢኖራቸውም፥ ተፈላላጊነት አላቸው፤ 1ቆሮ. 11፥8-12። አንድነታቸውና ተፈላላጊነታቸው የሚገለጠውም በጾታዊ ግንኙነታቸው በውብት መንገድ ነው፤ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ተብሏልና፤ ዘፍ. 2፥24። ጾታዊ ግንኙነታቸው አስደሳች ስለሆነ፥ ለአዳምና ለሔዋን እግዚአብሔር የሰጣቸው የመጀመሪያው ትእዛዝ፥ «ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት» የሚለው ነበር፤ ዘፍ. 1፥28። ስለዚህ ሲገናኙ ይደሰታሉ፤ በግንኙነታቸውም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለሚፈጽሙ እግዚአብሔርን ያከብራሉ።

ፍጥረትን ለመመርመር የሰው ልጅ የወሰደው ልዩ ልዩ ርምጃ በራሱ ብቃት አልነበረውም። ሰው ለሥራ ተፈጠረ፤ ነገር ግን ዕረፍት ለሰው ደስታ ብቻ የሚውል መሆን የለበትም። ሰው ጾታዊ ግንኙነት እንዲኖረው ተፈጠረ፤ እንደዚህ የተደረገው ግን እንዲደሰትበት ብቻ አይደለም። ሰው በሚያደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን ማክበር አለበት። ይህም በዌስትምንስተር ዐጭር ካታኪዝም (በጥያቄና መልስ መልክ የቀረበ የክርስትና ትምህርት) የመጀመሪያ ጥያቄና መልስ ላይ በተገቢ አባባል ተገልጧል (5):-

ጥያቄ:- 1 የሰው ዋና ዓላማ ምንድን ነው?

መልስ:- የሰው ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበርና በእርሱ ለዘለዓለም መደሰት ነው፤ መዝ. 73፥24-26፤ ሮም 11፥36፤ 1ቆሮ. 10፥31።

2. ሰው ለምን ድኅነት ያስፈልገዋል?

ሰው እግዚአብሔርን ማክበር ያለበት ለእርሱ ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ ነው። ሰው ይህን እንደሚፈጽመው ለማየት ሲል እግዚአብሔር ፈተናን ሰጠው። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው:- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና»፤ ዘፍ. 2፥16-17።

እግዚአብሔር ሁሉን መልካም አድርጎ በመፍጠር ሰውን በገነት ሲያኖረው፥ ሁሉ እጅግ መልካም ነበረ፤ ዘፍ. 1፥3:: ለምግብ በገነት ውስጥ ዛፎች በየዐይነቱ እንደ ልብ ይገኙ ነበር:: በገነት መካከል ግን ሁለት የተለዩ ዛፎች ነበሩ:: ከሁለቱ አንዱ የሕይወት ዛፍ ነበረና ከዚህ ዛፍ ለመብላት የሚገባው ሰው የዘለዓለም ሕይወት እንዳለው አመላከተ፤ ዘፍ. 2፥9፤ 3፥22:: ሌላው ዛፍ ደግሞ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ ሲሆን፥ አዳም ለእግዚአብሔር ክብርን ሁሉ እየሰጠ ከዚህ ዛፍ ካልበላ መታዘዙን፥ ከበላ ደግሞ አለመታዘዙን የሚገልጥበት ፈተና ነበረ::

አዳም የመብላት ነጻነት ነበረው:: ከሌሎች ዛፎች ሁሉ እንዳይበላ የሚከለክለው ነገር አልነበረም፤ ከዚህ ዛፍ ግን እንዳይበላ ተከለከለ፤ ከባድ ማስጠንቀቂያም ተሰጠው:: በልቶ ከተገኘ ወደ ሞት የሚያደርሰው ስለሆነ፥ ማስጠንቀቂያው ሕይወት ከሰጠው አምላክ የሚለየው መሆኑን አሳየ፤ ስለዚህ መብላቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን በራሱ ፈቃድ መመራትን የመረጠ መሆኑን አሳየ:: የሰው ነጻነት በእግዚአብሔር ልዕልና ውስጥ ስፍራ ይኖረዋል፤ እግዚአብሔር ግን ለሰው ነጻነትን ሲሰጥ፥ ኀላፊነትንና ተጠያቂነትን ዐብሮ ሰጥቷል:: የቤተ ክርስቲያን አባት አውግስጢኖስ አዳምና ሔዋን «ኀጢአት ያለማድረግ ችሎታ» እንደነበራቸው ጽፏል:: የእንግሊዙ ባለ ቅኔ ምልቶንም «ለመቆም ከቻሉ፥ ለመውደቅ ነጻነት ነበራቸው» ብሏል (6):: አዳምና ሔዋን መልካም ሆነው ተፈጠሩ፤ ሆኖም መልካም ሆነው ሊቈዩ ይችሉ የነበረው ለእግዚአብሔር ክብር መኖርን መርጠው ፈተናውን በማለፍ ነው:: ይህን ቢያደርጉ ኖሮ ኀጢአትን መሥራት ወደማይቻልበት ሁኔታ ይሸጋገሩ ነበር::

ሔዋን በሰይጣን በተፈተነች ጊዜ የተከለከለውን ፍሬ ወስዳ በላች፤ ለባሏም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም ከእርሷ ጋር በላ:: ይህ ታሪክ ልብ ወለድ አይደለም፤ የተፈጸመ ድርጊት ነውና የአዳምንና የዘሩን ሁሉ ሁኔታ ለወጠ:: አዳምም በሰው ትውልድ ሐረጎች የመጀመሪያ ሰው ሆኖ ተጠቅሷል፤ ዘፍ. ም. 5፤ ሉቃ. 3፥23-38:: አዲስ ኪዳንም ክርስቶስ ለሰው ድኅነት ያደረገውን ሲያብራራ፥ አዳም ካደረገው ጋር ያነጻጽረዋል፤ ሮም 5፥15:17፤ 1ቆሮ. 15፥21-22::

የአዳምንና የሔዋንን ድርጊት በብዙ መንገድ ልንመለከተው እንችላለን:- መተላለፍ ነበረ፤ እልከኛነትና እምቢተኛነት ያለበት ሲሆን፥ ዐመፅም ነበረ፤ የሕይወትን ቃል ኪዳን የማፍረስ ድርጊት ነበረ፤ በእግዚአብሔር ፊት በቀጥታ ከመቆም ይልቅ መውደቅ ነበረ:: ምን ዐይነት ኀጢአት ነበረ? አውግስጢኖስ የሔዋን የኀጢአት ምንጭ ኵራት እንደሆነ ተናግሯል:: በሌላ አመለካከት ፍሬውን መብላት ከዐሠርቱ ቃላት መካከል የሚበዙትን አለማክበር ነበረ፤ ምክንያቱም ስርቆትና ክፉ ምኞት ነበረበት፤ መብላት ደግሞ ራስን እንደ ጣዖት በማምለክ በእግዚአብሔር ፈንታ ሌላ አምላክ ማበጀት ነው:: ድርጊቱም ሰይጣን ስለ እግዚአብሔር በተናገረው ውሸት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራትና በሐሰት መመስከር ነው፤ የዚህ ውጤት ለዘራቸው ሁሉ ሞት በማምጣቱ ነፍስን እንደ መግደል የሚቈጠር ነበር:: በሌላ ዐይነት አስተሳሰብ ሔዋን በፈጣሪዋ ፈንታ ከፍጥረት አንዱን አዳመጠች፤ የታዘዘችውንም ትታ ስሜቷን ተከተለችና ራሷን ከፍ ማድረግ ዋና ዓላማዋ ሆነ:: ከዚህም ሁሉ ጋር ኀጢአታቸው የእግዚአብሔርን ክብር ለመስረቅ መሞከር ነበረ፤ ሔዋን የእግዚአብሔርን ክብር ለማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን፥ ክብሩን ሙሉ በሙሉ ለራሷ ፈለገች:: እግዚአብሔርን ማክበር ሳይሆን እግዚአብሔርን መሆን ፈለገች:: ይህም ዛሬ ዋናው የሰዎች ኀጢአት ነው፤ ሰው ለራሱ ክብር

እንጂ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር አይፈልግምና። እግዚአብሔር እስኪያድነው ድረስ ሰው እግዚአብሔርን ማክበር የማይፈልግና የማይችል ኀጢአተኛ ነው።

*3. ሰው ከምንና ከምን መዳን ያስፈልገዋል?*

አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ አይተፋፈሩም ነበር። ፍሬውን ከበሉ በኋላ ግን ዕራቁታቸውን እንደሆኑ ዐወቁ፤ የፍሬው ጣዕም ገና ከአፋቸው ሳይጠፋ ኀጢአተኞች መሆናቸውን ተረዱና ከተፈጠሩበት ክብር የወደቁ መሆናቸው ተሰማቸው። ይህንም በማወቃቸው ነውራቸው በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም አስፈርቷቸው ከእርሱ ሸሽተው በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።

ሰዎች ሁሉ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ረገድም ከአዳም ጋር ግንኙነት አላቸውና «በአዳም» ናቸው። በሌላ አነጋገር አዳም በገነት የሰው ሁሉ ወኪል ነበረና እርሱ ያደረገው ለሰው ሁሉ ስለሚቈጠር በእግዚአብሔር ፊት በደለኞች ናቸው። ከዚህም የተነሣ የሰው ጠባይ በኀጢአት ተበክሏልና ሰው ኀጢአትን ይሠራል። እንግዲህ ሰዎች በአዳም ሆነው ኀጢአተኞች ናቸውና ልዩ ልዩ ኀጢአትን ይሠራሉ እንጂ ኀጢአት በመሥራታቸው ኀጢአተኞች አይደሉም። የኀጢአትም ውጤት ሞት ነውና ሰው ከሞት በታች ይወሰዳል ማለት ሞት የሚገዛውና የሚቈጣጠረው የሞት ባሪያ ነው ማለት ነው፤ ሰው በአዳም ነውና፤ ሮም 5፥12:15:17:19፤ 1ቆሮ. 15፥21-22።

እግዚአብሔር፥ «... ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» የሚለው ማስጠንቀቂያ አዳምና ሔዋን በወደቁበት ቀን ተፈጸሟል። በዚያ ዕለት ከእግዚአብሔር ጋር ከነበራቸው ቅርብ ግንኙነት ወጥተው በመንፈሳቸው ሞቱ፤ በበደላቸውና በኀጢአታቸውም ሙታን ሆኑ፤ ዘፍ. 2፥17፤ ኤፌ. 2፥1። በዚያ ቀንም በሥጋቸው ውስጥ ሞት ገብቶ ወደ ዐፈር እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስ እየተበከሉ ሄዱ፤ ዘፍ. 3፥19።

ወደ ሞት ሁኔታ በመግባታቸው የሰው ቤተሰባዊና የሥራ ሁኔታዎች እጅግ ተለወጡ። ቀድሞ ምንም ዐይነት ሥቃይና መከራ ሳይደርስባቸው እርስ በርስ ተስማምተውና ተደስተው ይኖሩ ነበር። አሁን ግን ሴት በጭንቅ ትወልዳለችና ከባሏ ጋር የሚኖራት ግንኙነት ከባድ ሊሆን ይችላል። ምድሩም በመረገሙ የወንድ ሥራ እጅግ አድካሚና ዐልፎ ዐልፎ ፍሬ ቢስ ይሆናል፤ ዘፍ. 3፥16-19። ይህ ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር ቸርነት ልጅ መውለድና ሥራ መሥራት በረከቶች ናቸው (ዘፍ. 4፥1፤ መዝ. 127፥3-5፤ ምሳ. 5፥18፤ መክ. 3፥22፤ 9፥7-9)፤ ሆኖም እነዚህ ያለ ችግርና ያለ መከራ መሳካት ስለማይችሉ ሸክም ሆነዋል።

እንግዲህ ሰው በአዳም ሆኖ ከሞት በታች ስለሚኖር፥ የኀጢአት ውጤት ምን እንደሆነና ሰው ከምን መዳን እንደሚያስፈልገው ቀጥሎ በዐጭሩ መግለጥ እንችላለን:-

ሀ) ኀጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ያርቀዋል፤ ከቍጣው በታች እንዲኖርም ያደርጋል፤ «... በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፤ እንዳይሰማም ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል»፤ ኢሳ. 59፥2። «በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል»፤ ዮሐ. 3፥36። ወንጌል ግን ሰውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል (1ጴጥ. 3፥18)፤ ክርስቶስም «የኀጢአታችን ማስተስረያ ነው»፤ 1ዮሐ. 2፥2።

ለ) ኀጢአት ሰውን ከባልንጀራው ያርቀዋል፤ አዳም በኀጢአት ከወደቀ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ልጁ ቃየን ወንድሙን ገደለ፤ ዘፍ. 4፥8። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ

ሰዎች በወንድሞቻቸው ላይ ልዩ ልዩ የከፋት ድርጊት መፈጸም ጀመሩ፤ ገላ. 5፥19-21:: ወንጌል ግን በጠላትነት ይኖሩ የነበሩትን በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ያደርጋል፤ ኤፌ. 2፥14-16፤ ቆላ. 1፥21-22::

ሐ) ኀጢአት ሰውን ከራሱ የተፈጥሮ ባሕርይ እንዲወጣ ያደርገዋል፤ ሰው ውስጡ በክፋት የተበከለ መሆኑን ባያስተውልም (ኤር. 17፥9)፥ ብዙ ኀጢአት ከልቡ ፈልቆ ይወጣል፤ ማር. 7፥21-23:: ይህም ሁሉ ከሌሎች የተማረው ሳይሆን፥ የአዳም በደል ስላለበት (ሮም 5፥12) እና አዳማዊ ጠባይን ስለወረሰ ነው፤ ዘፍ. 8፥21:: ሰው ኀጢአትን ሲሠራ፥ ኅሊናው ይወቅሠዋልና የሚገባውንና የሚፈልገውን ለማድረግ ባለመቻሉ የልብ ሰላም አይኖረውም፤ የኀጢአት ባሪያ ነውና፤ ዮሐ. 8፥34:: ወንጌል ግን ሰውን ከኀጢአት ኀይል ነጻ ያወጣል፤ ሮም 6፥14::

መ) ኀጢአት ሰውን ወደ ሰይጣን ግዛት ያስገባዋል፤ ሰይጣን ሰዎችን ይገዛልና እንደ እርሱ ፈቃድ ይመላለሳሉ፤ ኤፌ. 2፥1-2:: ወንጌል ግን ሰዎችን ከሰይጣን የጨለማ ግዛት ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ልጅ መንግሥት ያሻግራል፤ ቆላ. 1፥13-14::

ሠ) ኀጢአት ሥጋዊ ሞትን ያስከትላል፤ «የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና»፤ ሮም 6፥23:: ወንጌል ግን፥ ሰው በሥጋ ቢሞትም፥ ከሞት ፍርሀት የተነሣ በባርነት የታሰሩትን ነጻ ያወጣቸዋል፤ ምክንያቱም የሞት መውጊያ ኀጢአት፥ የኀጢአትም ኀይል ሕግ ቢሆንም (1ቆሮ. 15፥56-57)፥ ክርስቶስ የሕግን ርግማን ደምስሷል፤ ገላ. 3፥13፤ ቆላ. 2፥14::

ረ) ኀጢአት ለፍርድና ለኵነኔ ይዳርጋል፤ ይህም ሞት ነውና ሁለተኛ ሞት ተብሏል፤ ወንጌል ግን በሕይወት መጽሐፍ ተጽፈው የሚገኙ ሁሉ በእሳት ባሕር እንደማይጣሉና ለዘለዓለም እንደሚኖሩ ያስተምራል፤ ማቴ. 25፥46፤ ራእ. 20፥14-15::

### 4. ሰው ራሱን ማዳን ለምን አይችልም?

ሰው በራሱ ኀይል የፈለገውን ነገር ለማድረግ እንደሚችል ማሰብ የተለመደ ነው:: ሰዎችም በዐሠርቱ ትእዛዛት ኀጢአት እንዳይሠሩ ስለ ታዘዙ፥ የመታዘዝ ዐቅም ያላቸው ሊመስላቸው ይችላል:: ይሁን እንጂ ለመታዘዝ ቢሞክሩም፥ እግዚአብሔር ኀይል ካልሰጣቸው፥ መታዘዝ እንደማይችሉ ያስተውላሉ:: ኢሳይያስ የእስራኤልን መታዘዝ አለመቻል በምዕራፍ 59 ያብራራልና የሰው መታዘዝ አለመቻል ከኀጢአቱ የተነሣ መሆኑን ይገልጣል:: ይህንም አሳብ ስንመረምር በአራት ነጥቦች ላይ ብናተኵር በቂ የሆነ ግንዛቤ ማግኘት እንችላለን:-

ሀ) ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ናቸው፤ የሰው ዐቅመ ቢስ መሆን እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ካለመሆኑ፥ ወይም ፈቃደኛ ካለመሆኑ የተነሣ የሚመጣ አይደለም፤ ኢሳ. 59፥1-2:: የሰው ችሎታ ቢስነት ኀጢአቱ ራሱና ኀጢአቱ የሚያመጣው ውጤት ነው:: የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በትምህርቱ ተገርመው፥ «እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል?» ብለው በጠየቁት ጊዜ፥ ኢየሱስ፥ «ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል» ብሎ መለሰላቸው፤ ማቴ. 19፥25-26::

ለ) ሰው ስለ ራሱና ስለ ዓለም ሁኔታ ዕዉር ነው፤ ኢሳይያስ፥ «እንደ ዕውሮች ወደ ቅጥሩ ተርመሰመስን፤ ዐይን እንደሌላቸው ተርመሰመስን፤

በቀትር ጊዜ በድንግዝግዝታ እንዳለ ሰው ተሰናከልን፤ እንደ ሙታን በጨለማ ስፍራ ነን» በማለት የሰዎችን አለማስተዋል ያብራራል፤ ኢሳ. 59፥10:: ችግሩ የብርሃን ዕጦት ሳይሆን፥ ማየት አለመቻል ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነው» በማለት ጽፏል፤ 1ቆሮ. 2፥14:: እግዚአብሔር የሰውን ሁኔታና የመዳንን መንገድ ካልገለጠ፥ ሰው ሊያስተውል አይችልም::

ሐ) የሰው ሁለንተና በኀጢአት ተበክሏል፤ ኢሳይያስ፥ «እጃችሁ በደም፥ ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፤ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሯል... የግፍም ሥራ በእጃቸው ነው:: እግሮቻቸውም ወደ ክፋት ይሮጣሉ... አሳባቸው የኀጢአት አሳብ ነው፤ ጕስቍልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ...» ብሎ የተናገረው ኀጢአት የሰውን እጅ፥ ጣት፥ እግርና አሳብ ማለትም ጠቅላላ ሁለንተናውን እንደበከለ አሳይቷል፤ ኢሳ. 59፥3-8:: በተጨማሪም ነቢዩ የሰውን ብክለት ሲደመድም፥ «ዓመፃችን ባንተ ፊት በዝቷልና፤ ኀጢአታችን መስክሮብናልና» ብሎ ጻፈ፤ ኢሳ. 59፥12:: የሰው ሁለንተናዊ ብክለት ወደ ሌላ ዕንቅፋትም ይመራል::

መ) ሰው ከኀጢአቱ እንዲድን አይፈልግም፤ ኢሳይያስ፥ «ዓመፃችን በአንተ ፊት በዝቷል... ዓመፃችን ከእኛ ጋር ነውና... ዐምፀናል...» በማለቱ የሰው ፈቃድ እግዚአብሔርን የሚቃወም መሆኑን ያሳያል፤ ኢሳ. 59፥12-13:: የሰው ክፋት ድክመት፥ አላዋቂነት ወይም ድንቍርና ብቻ ሳይሆን፥ ዓመፅም ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና... («ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው...»፤ ሮም 8፥7)፤ «... እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም» (ሮም 3፥11) በማለቱ ሰው ራሱን ማዳን አለመቻሉንና መዳን እንኳ አለመፈለጉን አሳይቷል:: ሐዋርያው ይህን የተናገረው የዳዊትን አሳብ በመገንዘብ ሳይሆን አልቀረም፤ መዝ. 14፥1-3::

እውነት ነው፤ ሰው ራሱን ለማዳን ብዙ የሃይማኖትን ሥርዐት ሊከተል ይሞክራል፤ ነገር ግን ሰዎች በዚህ መንገድ ጽድቅ የሚገኝ ቢመስላቸውም፥ ኢሳይያስ፥ «ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፤ ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው...» ብሎ ለድኅነት የሰው ሥራ ከንቱ መሆኑን ገልጧል፤ ኢሳ. 64፥6:: ሰው ለመዳንና ጽድቅን ለማግኘት በተወሰነ መንገድ መሳተፍ ቢችል ኖሮ፥ ምናልባት ሊደሰት ይችላል፤ በእግዚአብሔር መንገድ መዳን ግን አይፈልግም፤ የእግዚአብሔር የማዳን መንገድ በጸጋ ብቻ ነው፤ ሮም 3፥24፤ 2ጢሞ. 1፥9::

እንግዲህ እግዚአብሔር ሰው በጸጋ እንዲድን ዳግመኛ ይወልደዋል፤ በዚህም ሥራ የሰው አእምሮ ተከፍቶ እንዲያስተውል፥ ልቡም እንዲነጻና በአዲስ መንገድ እንዲራመድ የሰው ፈቃድ ይለወጣል፤ ሕዝ. 36፥25-27፤ ዮሐ. 3፥3-8:: ሰው በዚህ መንገድ በጸጋ ሲለወጥ ኀጢአቱን ተረድቶ ንስሓ ይገባል፤ ወንጌልንም ሰምቶ ያምናል፤ ዮሐ. 1፥12-13:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን እውነት፥ «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም» እና «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» በማለት በተለየ መንገድ ገልጦታል፤ ዮሐ. 6፥44፤ 15፥5::

እውነት ነው፤ በብዙዎች ዘንድ ይህ ትምህርት ተቀባይነት አይኖረውም:: ሰዎች ወንጌሉን እንዲመርጡ ታዝዘዋል ይላሉ፤ «የተጠማም ይምጣ፤ የወደደም የሕይወትን ውሃ እንዲያው ይውሰድ» (ራእ. 22፥17)፤ «ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም» (ዮሐ. 6፥37) የሚሉትንና

የመሳሰሉትን በመጥቀስ የትምህርታቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይሞክራሉ። ሰው በምርጫ እንዲመጣ ይጋበዛል፤ ችግሩ ግን የሰው ፈቃድ ካልተለወጠ ወደ እግዚአብሔር መምጣት አይፈልግም። ይህ ዐይነቱ ጠባይ «የፈቃድ ባርነት» ተብሏልና የሰው ፈቃድ የተበከለ በመሆኑ ለመምረጥ ነጻነት ቢኖረውም እንኳ፥ ልቡ የእግዚአብሔርን መንገድ አይመርጥም። ሰዎች ኀጢአተኞች ናቸውና በአንድ መንገድም ሆነ በሌላ የልባቸው ዝንባሌ ኀጢአትን መምረጥ ነው፤ የሰው ልብ ተንኰለኛ፥ እጅግም ክፉ ነውና፤ ኤር. 17፥9።

## ሐ) የድኅነት ጸጋ አሠራር

ድኅነትን በሦስት ደረጃዎች መመልከት የተለመደ ነው፦ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ከኀጢአት ኵነኔ ይድናል፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከኀጢአት ኀይል ይድናልና ክርስቶስ ሲመለስ ከኀጢአት ዓለም ይድናል።

ሰው ይድን ዘንድ ማድረግ የሚገባው ግልጥ ነው። በበዓለ ኀምሳ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ንስሐ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» ብሏል፤ ሐ.ሥ. 2፥38። ጃንደረባው፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ» በሚለው ቃል መሠረት ተጠመቀ፤ ሐ.ሥ. 8፥37። የፊልጵስዩስ ወህኒ ጠባቂ፥ «እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ብሎ ሲጠይቅ፥ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን» የሚል መልስ ተሰጠው፤ ሐ.ሥ. 16፥30-31። ዐዋቂ ሰው ከመጠመቁ በፊት ማመን ያለበት መሆኑ ግልጥ ነው። ስለዚህ በዐጭሩ ሰው እንዲድን ንስሐ መግባትና በወንጌል ማመን አለበት፤ ማር. 1፥14-15።

ሰው እንዲድን ማድረግ የሚገባውን ማወቅ ቀላል ሊመስለን ይችላል። ሆኖም የሰውን አዳማዊ ሁኔታ ስንመለከት፥ ወንጌልን አስተውሎ ሊቀበለው እንዲፈልግ፥ ከዚያም በኋላ እስከ ሞት ድረስ በክርስቶስ መንገድ መራመድ እንዲችል፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊ እንደሆነ ማሰብ አይከብድም። አዲስ ኪዳን ስለ ሰው ድኅነት ሲናገር በብዙ ቃላትና በብዙ ምሳሌዎች ይጠቀማል። እነዚህ አባባሎች የትኛውን የድኅነት ደረጃ እንደሚያመለክቱ፥ እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚዛመዱና ከዘመናችን የቤተ ክርስቲያን ቃላት አጠቃቀም ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ለይቶ ማሳየት ቀላል ላይሆን ይችላል።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሊቃውንት ብዙ ጊዜ ትምህርተ ሥጋዌን ከመረመሩ በኋላ ወደ ትምህርተ ጥምቀት ጥናት መግባታቸው የተለመደ ሆኗል፤ ይህም በተለይ በኢትዮጵያ «አምስቱ አዕማደ ምሥጢር» በሚለው መጽሐፍ ይታያል። በምዕራባውያን የተሐድሶ ዘመን ግን በተለይ ከሉተርና ከካልቪን አንሥቶ የድኅነት ትምህርት መጠናት ጀምሯል። እውነት ነው፤ ክርስቶስ ሥጋው አዳኝ ሆኖ በሕማማቱ ለሚያምኑበት አስፈላጊውን ሁሉ ፈጸመ። ከዚያም ቀጥሎ እያንዳንዱ ሰው ወደ እምነት እንዴት እንደሚደርስ፥ አምኖም ወደ ምን ዐይነት አቋምና አኗኗር ውስጥ እንደሚገባ፥ ለመንግሥተ ሰማያትም እንዴት እንደሚበቃ ማሰብ ያስፈልጋል። ይህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ መሆኑ፥ ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ እንዴት አጸፋ መስጠት እንዳለበት እናስባለን። ከዚህ በታች በመጀመሪያ በአዲስ ኪዳን ትምህርት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንዴት እንደሚገለጥ፥ ቀጥሎም የመንፈስ ቅዱስ ስም በተለይ ሳይጠቀስ የእግዚአብሔር ሥራ፥ የሰው አጸፋ፥ የአማኙ አዲስ አቋምና አዲስ አኗኗር እንዴት እንደተብራሩ እንመለከታለን።

1. በሰው ድኅነት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

ሀ) በአማኙ ይኖራል፤ «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም»፤ ሮም 8፥9::

ለ) አጽናኝ ነው፤ «እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘለዓለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል»፤ ዮሐ. 14፥16::

ሐ) ልጅነትን ያረጋግጣል፤ «አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ...»፤ ሮም 8፥15::

መ) ድካምን ያግዛል፤ «መንፈስ ድካማችንን ያግዛል... በማይነገር መቃተት ይማልድልናል»፤ ሮም 8፥26::

ሠ) ስጦታዎችን ይሰጣል፤ «... እንዲሁም እንደ ፈቃዱ በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስለዚሁ ነገር መስክሯል»፤ ዕብ. 2፥4 አ.መ.ት.::

ደግሞም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሰዎች ላይ እንደሚከተለው ይገለጣል:-

ረ) በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ይወለዳሉ፤ «...ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም»፤ ዮሐ. 3፥5::

ሰ) በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ፤ «... እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና:: ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል»፤ 1ቆሮ. 12፥13::

ሸ) በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ፤ «መንፈስ ይሙላባችሁ»፤ ኤፌ. 5፥18::

ቀ) በመንፈስ ቅዱስ ይቀባሉ፤ «እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል»፤ 1ዮሐ. 2፥27::

በ) በመንፈስ ቅዱስ ይታተማሉ፤ «በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው»፤ ኤፌ. 1፥13-14::

ተ) በመንፈስ ቅዱስ ይቀደሳሉ፤ «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ...»፤ 1ጴጥ. 1፥1-2::

ቸ) በመንፈስ ቅዱስ ይታደሳሉ፤ «ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን»፤ ቲቶ 3፥5::

2. በሰው ድኅነት የእግዚአብሔር ሥራ

የሚከተሉት ተግባራት የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መሆናቸውን ሳናስብ አንቀርም፤ ሆኖም በጥቅሶቹ የመንፈስ ቅዱስ መሆናቸው አልተገለጠም::

ሀ) አብርሆት፤ ይህም ሰዎች እንዲያስተውሉ መንፈሳዊ ዐይናቸውን ማብራት ማለት ነው፤ «የኀጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን፥ ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዐይናቸውን ትከፍት ዘንድ...» (ሐ.ሥ. 26፥17-18)፥ «ይህም የልባችሁ ዐይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን... ታውቁ ዘንድ ነው» ኤፌ. 1፥18-19::

ለ) ስበት፤ «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም»፤ ዮሐ. 6፥44::

ሐ) አዲስ ልደት፤ «እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን»፤ ቲቶ 3፥5::

መ) አዲስ ፍጥረት፤ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው»፤ 2ቆሮ. 5፥17።

ሠ) መባረክ፤ «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን...»፤ ኤፌ. 1፥3።

ረ) መምረጥ፤ «ዓለም ሳይፈጠር፥... በክርስቶስ መረጠን»፤ ኤፌ. 1፥4።

ሰ) አስቀድሞ መወሰን፤ «... ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን»፤ ኤፌ. 1፥5።

ሸ) ሕይወትን መስጠት፤ «ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን»፤ ኤፌ. 2፥5።

ቀ) ከክርስቶስ ጋር ማስነሣትና በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር ማስቀመጥ፤ «ከእርሱ (ከክርስቶስ) ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ (ከእግዚአብሔር) ጋር አስቀመጠን»፤ ኤፌ. 2፥6-7።

በ) ልብን መክፈት፤ «ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልቧን ከፈተላት»፤ ሐ.ሥ. 16፥14።

ተ) ከጨለማ መንግሥት ወደ ክርስቶስ መንግሥት ማሻገር፤ «እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም እርሱንም የኀጢአትን ስርየት ወዳገኘ ንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን»፤ ቆላ. 1፥13-14።

ቸ) መጥራት፤ «ነገር ግን በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ...»፤ ገላ. 1፥15-16።

ኀ) ማወቅ፥ መወሰን፥ መጥራት፥ ማጽደቅና ማክበር፤ «አስቀድሞ ያወቃቸውን... ወሰናቸው... ጠራቸው... አጸደቃቸው፤... አከበራቸው»፤ ሮም 8፥29-30 አ.መ.ት.።

ነ) ጥበብን፥ ጽድቅን፥ ቅድስናንና ቤዛነትን ማድረግ፤ «ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ፥ ቅድስናም፥ ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው»፤ 1ቆሮ. 1፥30-31።

### 3. ለእግዚአብሔር ጸጋ ትክክለኛ የሰው አጸፋ

ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ ትክክለኛ ምላሽ ሲሰጥ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ዐብሮ እንደሚሠራ እናስተውላለን።

ሀ) ንስሐ መግባት፤ «... ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ»፤ ማር. 1፥14-15።

ለ) መመለስ፤ «... ኀጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ፤ ተመለሱም»፤ ሐ.ሥ. 3፥19-20።

ሐ) ማመን፤ «... በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ»፤ ሐ.ሥ. 16፥31።

መ) መጠመቅ፤ «... ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ»፤ ሐ.ሥ. 22፥16።

ሠ) ከጣዖታት ወደ እግዚአብሔር መመለስ፤ «ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳላችሁ ይናገራሉ»፤ 1ተሰ. 1፥9-10።

ረ) ለእውነት መታዘዝ፤ «ለእውነት እየታዘዛችሁ... እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ»፤ 1ጴጥ. 1፥22።

ሰ) ለተሰጠው ትምህርት መታዘዝ፤ «... ለተሰጣችሁለት የትምህርት ዐይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ፥ ከኀጢአትም ዐርነት ወጥታችሁ ለጽድቅ ስለተገዛችሁ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን»፤ ሮም 6፥17-18፤ 12፥1-2።

4. የአማኙ አዲስ አቋም

ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ ትክክለኛ አጸፋ ሲሰጥ አዲስ አቋም አለው:-

ሀ) እውነትን ሲያውቅ ነጻነት ይኖረዋል፤ «እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ዐርነት ያወጣችኋል»፤ ዮሐ. 8+32::

ለ) ጻድቅ ነው፤ «ለማይሠራ+ ኀጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል»፤ ሮም 4+5::

ሐ) የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል»፤ ሮም 8+16::

መ) የእግዚአብሔር ወራሽ ነው፤ «ልጆች ከሆንን... የእግዚአብሔር ወራሾች ነን»፤ ሮም 8+17::

ሠ) የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ነው፤ «... ቤዛነቱንም+ እርሱንም የኀጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን»፤ ቆላ. 1+13-14::

ረ) የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም»፤ 1ዮሐ. 5+12::

ሰ) ቅዱስ ነው፤ «... ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን+ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት...» ተብሎ ተጽፏል፤ 1ቆሮ. 1+2::

5. የአማኙ አዲስ አኗኗር

ሰው ለእግዚአብሔር ጸጋ ትክክለኛ አጸፋ ሲሰጥ ወደ አዲስ አኗኗር ይገባል:-

ሀ) አዲስ ኅብረት አለው፤ «እናንተ ግን... ቅዱስ ሕዝብ+ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ...»፤ 1ጴጥ. 2+9-10::

ለ) አዲስ አገልግሎት አለው፤ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ+ የንጉሥ ካህናት... ናችሁ»፤ 1ጴጥ. 2+9::

ሐ) አዲስ ምግብ አለው፤ «ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ»፤ 1ጴጥ. 2+2-3::

መ) አዲስ አካሄድ አለው፤ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ+ እናንተ ደግሞ በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»፤ 1ጴጥ. 1+15-16::

ሠ) አዲስ ምስክርነት አለው፤ «... ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት:: በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ...»፤ 1ጴጥ. 3+15::

ረ) አዲስ ትግል አለው፤ «በመጠን ኑሩ፤ ንቁም፤ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሣ ይዞራልና»፤ 1ጴጥ. 5+8::

ሰ) አዲስ ዋስትና አለው፤ «... ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኀይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል»፤ 1ጴጥ. 1+3-5::

ሸ) አዲስ የአስተሳሰብ አድማስ አለው፤ «በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘለዓለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፤ ያጸናችሁማል፤ ያበረታችሁማል»፤ 1ጴጥ. 5፥10::

ከ1ኛ ጴጥሮስም ሆነ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የአማኙን ሁኔታ የሚያብራሩልንን ተጨማሪ ነጥቦች ማከል ከባድ አይሆንም:: ሆኖም ከዚህ በላይ በተጻፉት ዝርዝሮችና ጥቅሶች የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ለአማኙ የተሰጡ በረከቶች፥ በአማኙ ሕይወት የሚታዩ ጠባያትም በብዙ መንገድ እንደሚገለጡ ይታወቃል:: በምዕራፍ 86 ዋና ዋናዎቹንና ቀደም ተከተላቸውን ከመመርመራችን በፊት፥ የሰው ድነት በክርስቶስ በሚከናወነው አጠቃላይ ተግባር በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል::

# ማስታወሻ

(1) ም. 80ሐ ይመ.

(2) Berkhof ገጽ 42 ጀ.

(3) የዚህ ንኡስ ርእስ በተለይ በTHS ገጽ 93-94 ባለው አሳብ ላይ ተመሥርቷል::

(4) «ትምህርተ ሰብእ» በሚለው በአራተኛው ጥናት ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ ክብሩን፥ በኃጢአት በመውደቁም ውርደቱን በሰፊው መርምረናል:: እዚህ ላይ ለትምህርተ ድኅነት መሠረት እንዲሆን ስለ ሰው አንዳንድ ትምህርቶችን በዐጭሩ እንከልሣለን:: ይህን ስናደርግም በPhilip Graham Ryken (P.G.R.) በተጻፈውና IVP ባሳተመው The Message of Salvation በሚለው መጽሐፍ እንጠቀማለን፤ በዚህ ንኡስ ርእስ ከገጽ 17-60 ይመ.

(5) እምነታችን ገጽ 67 ይመ.

(6) P.G.R. ገጽ 25 ይመ.

# ክፍል 2 - መንፈስ ቅዱስና የሰው ድኅነት
## ምዕራፍ 84 - የሰው ድኅነት በክርስቶስ መሆኑ

መንፈስ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ይመሰክራልና ከክርስቶስ ጋር አንድነት እንዲኖረው ሰውን ወደ ክርስቶስ ያደርሰዋል:: ይህ አንድነት ብዙ ጊዜ በክርስቶስ የሚገኝ በመሆኑ፥ አንዳንድ ጊዜ በክርስቶስ በአማኙ ዘንድ መገኘት ወይም በክርስቶስ ከሰው ጋር መሆን ይገለጣል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል» በማለት ይህን አንድነት በሁለት አመለካከቶች ገልጦታል፤ ዮሐ. 15፥5:: በይበልጥ ሲያብራራውም፥ «እኔ በአባቴ እንዳለሁ፥ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፥ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ» ብሎ በመናገር አንድነቱን በአብ ካለው ከእርሱ አንድነት ጋር ስላመሳሰለው፥ በክርስቶስና በተከታዮቹ መካከል ያለው አንድነት፥ መንፈሳዊ፥ ምሥጢራዊ፥ ሕያው አካላዊና የፍቅር አንድነት መሆኑ ተገልጧል፤ ዮሐ. 14፥20::

ክርስቶስ በወይን ግንድ (ክርስቶስ) እና በቅርንጫፎች (ምእመናን) መካከል (ዮሐ. 15፥1-11)፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ በሕንጻ ድንጋዮች (ምእመናን) እና በማእዘኑ ራስ ድንጋይ (ክርስቶስ) መካከል (ኤፌ. 2፥19-22፤ ደግሞ 1ጴጥ. 2፥4-5 ይመ.)፥ በሰው አካል ክፍሎች (ምእመናን) እና በባሏ (ክርስቶስ) መካከል (ኤፌ. 5፥22-23)፥ እንደዚሁም በሰዎች ሁሉና በቃል ኪዳናዊው ራሳቸው በአዳም መካከል (ሮም 5፥12-19፤ 1ቆሮ. 15፥22:48-49) ካለው አንድነት ጋር በማነጻጸር ምእመናን ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን አንድነት ያብራራሉ:: ይህ ዐይነቱ አንድነት በአብና በወልድ አንድነት የተመሠረተ መሆኑ ተገልጧል፤ ዮሐ. 14፥20:23፤ 17፥20-23:: ከዚህ የተነሣ የዚህ አንድነት ይዘት ጥልቀት እንዳለው፥ ምሥጢራዊ መሆኑ፥ በብዙ አቅጣጫም ሊመረመር መቻሉና ለምእመናን በረከቱን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑ ይታያል::

ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ለክርስቶስ ግብር ሁሉ ጥቅልል ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝበናል (1):: ሆኖም ክርስቶስ ነቢይ፥ ካህንና ንጉሥ መሆኑ የተሻለ ጥቅልል ምሳሌ እንደሆነ ተመልክተናል፤ ምክንያቱም ይህ ከአንድነቱ ምሳሌ በስተ ጀርባ ያለውን የክርስቶስ ግብር ስለሚያብራራው ነው:: ይሁን እንጂ ከክርስቶስ ጋር የሚኖር አንድነት የሚለው ሐረግ የድኅነትን በረከትና መንገድ ሁሉ ስለሚያጠቃልል ለድኅነት ትምህርት መሠረታዊ ነው:: አሳቡ እጅግ ሰፊ ነውና አማኙ በክርስቶስ፥ ክርስቶስ በአማኙ፥ ክርስቶስ ከአማኙ ጋርና አንድነቱን በሚመለከት የተፈጠሩ ስሕተቶች በሚሉት አራት አርእስት ሥር ትምህርቱን ልናቀርበው እንሞክራለን (2):-

### ሀ) አማኙ በክርስቶስ

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው» በማለቱ አማኙ ወደ አዲስ ዓለም ማለት ወደ አዲስ አቋምና አዲስ አኗኗር እንደገባ አሳይቷል:: በዚህ አዲስ ዓለም «አሮጌው ነገር ዐልፏል»፤ «ሁሉ አዲስ ሆኗል»፤ ክርስቲያን ዋጋ ያለው አዲስ ፍጥረት ብቻ መሆኑን ያውቃልና «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ» ያደርጋል፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ገላ. 6፥15፤ ኤፌ. 2፥10:: በዚህ አዲስ ሁኔታ ውስጥ የሚኖር ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ መፈጠሩን ያውቃል፤ ሆኖም ይህን አንድነት መግለጥ ቀላል አይደለም:: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ሰዎች ከቃል ኪዳናዊ ራሳቸው ጋር አንድ

በመሆናቸው፥ የቃል ኪዳኑ ራስ ሥራ ለእነርሱ የሚቈጠርላቸው ከመሆኑ ጋር ያብራራዋል:: በዚህ መሠረት ሰዎች በአዳም ሆነው በእርሱ ኀጢአት ምክንያት ይሞታሉና በተቃራኒው ደግሞ ምእመናን በክርስቶስ ሆነው ከጽድቁ የተነሣ ይኖራሉ፤ 1ቆሮ. 15፥22፤ ሮም 5፥12-19:: በሌላ ጊዜ ደግሞ ክርስቶስ ራስ ሆኖ እያንዳንዱ አማኝ እንደ አካል ክፍል ከራሱ ጋር እየተገናኘና የግል ሥራውን እየፈጸመ ከአካሉ ሁሉ ጋር እንደሚያድግ ይጽፋል፤ ኤፌ. 4፥15-16:: በሌላ ስፍራ ደግሞ፥ «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል» ብሎ በሰውና በልብሱ መካከል ባለው ግንኙነት የክርስቶስንና የአማኙን አንድነት ያሳያል፤ ገላ. 3፥27:: ሐዋርያው የእግዚአብሔርን ሥራ ሲገልጥ፥ «በ» በሚለው መስተዋድድ 160 ጊዜ ያህል አማኙ በክርስቶስ ያለውን አንድነት ይጠቅሳል:: ይህንም በልዩ ልዩ መንገድ እንደሚከተለው ሲገልጠው ማየት እንችላለን:-

**1. በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅድ**

«ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን»፤ ይህም «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው»፤ ኤፌ. 1፥4:12:: በኋላም እግዚአብሔር ያዳነንና በቅዱስ አጠራር የጠራን «እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው»፤ «ይህም ጸጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን»፤ 2ጢሞ. 1፥9:: እግዚአብሔር በመጀመሪያ የመረጠን በኋላ በክርስቶስ እንድንሆን ሊያደርገን አልነበረም፤ ምርጫው የነበረው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: ስለዚህ ከመወለዳችን በፊት ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር አሳብ ነበርን፤ ይህም አሳብ «በክርስቶስ» ነበረ፤ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሲያስብ ከክርስቶስ ለይቶ አይመለከተንም:: እግዚአብሔር እንደዚህ ሲያስብ ይደሰት ነበር፤ ምክንያቱም ይህ ለክብሩ ምስጋና ነው::

ምእመናን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በክርስቶስ ቢመረጡም፥ በክርስቶስ እስኪያምኑ ድረስ በበደላቸውና በኀጢአታቸው ሙታን፥ በሰይጣን ሥልጣን ቍጥጥር ሥር የሆኑና የቍጣ ልጆች ናቸው:: በዕቅዱ መሠረት እግዚአብሔር በክርስቶስ ሕይወት እስኪሰጣቸው ድረስ ከሌሎች ሰዎች የሚሻሉ አይደሉም፤ ኤፌ. 2፥1-3::

**2. ክርስቶስ በምድር ሳለ**

በቤዛ ቃል ኪዳን (3) መሠረት አብ ለወልድ ልጆችን ሰጠው፤ ክርስቶስ በምድር ሳለ፥ «እነሆኝ እኔን እግዚአብሔር የሰጠኝንም ልጆች» ብሎ ተናገረ፤ ዕብ. 2፥13:: እንግዲህ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ለማዳን የመጣው ኢየሱስ ስለ ልጆቹ ያስብ ነበር፤ እነርሱም እንደዚሁ በእግዚአብሔር አሳብ በክርስቶስ ሕይወት ሁሉ ይኖሩ ነበር:: ክርስቶስ የመጣው ለእነርሱ ነበር፤ ድኅነትን በተመለከተ የእነርሱ ራስና ወኪል ነው፤ እነርሱም «በክርስቶስ» ነበሩ:: ከእነርሱ የሚበዙቱ ገና አልተወለዱም ነበር፤ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ክርስቶስን ሲመለከት፥ እነርሱንም በክርስቶስ ተመለከታቸው::

ኢየሱስ በሕይወቱ ሁሉ ለእግዚአብሔር ሲታዘዝ፥ እኛም እንደታዘዝን ተቈጠረ፤ ሐዋርያው፥ «በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ» (ሮም 5፥19) በማለት ጽፏልና በክርስቶስ ጻድቃን ሆነናል፤ 1ቆሮ. 1፥30-31፤ ፊል. 3፥8-9::

እግዚአብሔር እኛ በክርስቶስ እንደሆንን በማሰብ፥ ኀጢአታችንን በክርስቶስ ላይ አደረገ፤ «እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ»፤ «ኀጢአት

ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው»፤ ኢሳ. 53፥6፤ 2ቆሮ. 5፥21:: በዚህም ምክንያት ክርስቶስ ሞተ፤ 1ጴጥ. 2፥24፤ 1ቆሮ. 15፥3:: ኀጢአታችንን በክርስቶስ ላይ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ያሉ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀሉም እግዚአብሔር ማሰቡ በሚከተሉት ጥቅሶች ይታያል:- «አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን»፤ «እናንተ ደግሞ ለኀጢአት እንደሞታችሁ... ቍጠሩ»፤ «አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ»፤ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ»፤ ሮም 6፥6:11፤ 2ቆሮ. 5፥14፤ ገላ. 2፥20::

በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ምእመናን በክርስቶስ ሆነው ከክርስቶስ ጋር ተቀብረዋል፤ ተነሥተዋል፤ ወደ ሰማይ ዐርገዋል፤ በአብ ቀኝም ተቀምጠዋል፤ ሮም 6፥4-11፤ 1ቆሮ. 15፥22፤ ኤፌ. 2፥4-7፤ ቆላ. 2፥12-13::

እንግዲህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንግሥተ ሰማያት በተመለሰ ጊዜ፥ ለምእመናን መንፈሳዊ በረከትን ሁሉ አግኝቶላቸዋልና ምእመናን ሁሉ ከሐዋርያው ጋር፥ «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» ማለት ይገባቸዋል፤ ኤፌ. 1፥3::

3. በአማኞች ተመክሮ

ሰው በመንፈስ ከተወለደና ካደገ በኋላ ከዘለዓለም የነበረው በክርስቶስ የሆነው ከአሁን ጀምሮ በሕይወቱ ለውጥ እንዲያመጣ አስፈላጊ ነው፤ ይህንም በተለይ እርስ በርስ በተያያዙ አራት አመለካከቶች ሥር ልንመረምረው እንችላለን:-

ሀ) እኛ ከክርስቶስ ጋር ሞተናልና እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር አስነሥቶናል

ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር በክርስቶስ ስለመረጠን ነው:: ሐዋርያው፥ «እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን:: ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» ብሎ በመጻፉ፥ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በሕይወታችን በአንድ ዐይነት መንገድ ይደግመዋል፤ ሮም 6፥4-5:: ክርስቶስ «መሞትን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኀጢአት ሞቷልና» (ሮም 6፥10)፥ አማኙ በክርስቶስ ሆኖ ለኀጢአትና ለዓለም እንደሞተ ራሱን ሊቈጥር ታዝዟል፤ ሮም 6፥11፤ 7፥6፤ ገላ. 2፥20፤ 5፥24፤ 6፥14፤ ቆላ. 2፥20-21:: በአማኙ ሕይወት የሚፈጸመው ይህ ብቻ አይደለም፤ በክርስቶስ በመሆኑም ከክርስቶስ ጋር ወደ አዲስ ሕይወት ተነሥቷል፤ ስለዚህ ሐዋርያው፥ «በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ» ብሎ አዝዞናል፤ ሮም 6፥11:: የእኛ ትንሣኤ ፍጹም የሚሆነው በዳግም ምጽአቱ ጊዜ ሲሆን፥ አሁን ግን በክርስቶስ በመሆናችን ወደ ትንሣኤ ሕይወት አኗኗር ገብተናልና በአዲስ ሕይወት እንመላለሳለን፤ ሮም 6፥4፤ ቆላ. 2፥10-13፤ 1ጴጥ. 2፥24:: ከክርስቶስ ጋር በመሞታችንና በመነሣታችን በሕይወታችን ያለውን ኀጢአት እያሸነፍን መኖር እንችላለን (ሮም 6፥12-14:19)፤ በክርስቶስ ወደ ሕይወት ሙላት ደርሰናል፤ ቆላ. 2፥9-10:: በሌላ አነጋገር በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነንና አሳባችንን ክርስቶስ ባለበት በላይ ባለው ማድረግ ይገባናል፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ቆላ. 3፥1:4::

ለ) በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ይኖረናል

እግዚአብሔር «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ» ባርኮናል፤ ኤፌ. 1፥3:: በረከት ሁሉ በእርሱ ነውና ክርስቶስ አሁን በእርሱ ላሉት ሁሉ በረከትን በሙሉ ይሰጣቸዋል:: ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት ሰጠን፥ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው» ብሎ ጽፏል፤ 1ዮሐ. 5፥11 አ.መ.ት.:: ሐዋርያው ጳውሎስም በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚሆነው የሕይወት ተስፋ ተናግሯል (2ጢሞ. 1፥1)፤ በክርስቶስ «እምነትና ፍቅር» (1ጢሞ. 1፥14፤ 2ጢሞ. 1፥13)፥ «ጸጋ» (2ጢሞ. 2፥1)፥ «መዳን» (2ጢሞ. 2፥10)፥ «የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ» (ቆላ. 2፥3) እና የሚያስፈልገን በሙሉ (ፊል. 4፥19) እንደሚገኙ ተጽፏል::

መንፈሳዊ ሕይወታችን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለው በክርስቶስ ነው፤ በክርስቶስ ለድኅነት እንጠራለን (1ቆሮ. 7፥22)፤ በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ይሰጠናል (ኤፌ. 2፥10)፤ በክርስቶስ እንጸድቃለን (ሮም 8፥1፤ 2ቆሮ. 5፥21፤ ገላ. 2፥16)፤ በክርስቶስ እንሞታለን (1ተሰ. 4፥14:16፤ ራእ. 14፥13) እና በመጨረሻ በክርስቶስ እንነሣለን፤ 1ቆሮ. 15፥22::

ሐ) በክርስቶስ የምናደርገውን ሁሉ ማድረግ እንችላለን

ማናቸውንም ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእርሱ ክብር ስናደርግ «በክርስቶስ» እናደርጋለን:: በዚህ መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ እውነትን በክርስቶስ ይናገራል (ሮም 9፥1፤ 2ቆሮ. 2፥17፤ 12፥19)፤ በክርስቶስ በሠራው ሥራ ይመካል (ሮም 15፥17፤ 1ቆሮ. 15፥31)፤ በክርስቶስ ስለሚራመድበት መንገድ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያሳስባል (1ቆሮ. 4፥17)፤ በክርስቶስ ጢሞቴዎስን ወደ ፊልጵስዩስ ለመላክ ተስፋ ያደርጋል (ፊል. 2፥19)፤ በክርስቶስ ደስ ይለዋል (ፊል. 4፥10) እና ሌሎችን ምእመናን በክርስቶስ ይለምናል፤ ያዝዛል፤ ይመክራልም፤ 1ተሰ. 4፥1፤ 2ተሰ. 3፥12:: ከዚህ የተነሣም፥ «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» ብሎ ይመሰክራል፤ ፊል. 4፥13::

ደግሞም ሐዋርያው ምእመናን ድካማቸው በጌታ ከንቱ እንደማይሆን (1ቆሮ. 15፥58)፥ ልጆች ለወላጆቻቸው በጌታ መታዘዝ እንደሚገባቸው (ኤፌ. 6፥1)፥ ሚስቶች በጌታ ለባሎቻቸው መገዛት እንዳለባቸው (ቆላ. 3፥18) እና ምእመናን ሁሉ በጌታ እንዲበረቱ (ኤፌ. 6፥10)፥ እንዲደሰቱ (ፊል. 4፥4)፥ እንዲስማሙ (ፊል. 4፥2)፥ እንዲቆሙ (ፊል. 4፥1)፥ እግዚአብሔርን እንዲመስሉ (2ጢሞ. 3፥12) እና መልካም አካሄድ እንዲኖራቸው (1ጴጥ. 3፥16) ያሳስባቸዋል:: ምእመናንም በጌታ ይደክማሉ (ሮም 16፥12)፤ ይደፍራሉ (ፊል. 1፥14) እና ይፈተናሉ (ሮም. 16፥10):: ምእመናን ከክርስቶስ ጋር ሲመላለሱና ሥር ሰድደው ሲታነጹ (ቆላ. 2፥6-7)፥ ሰውን ሁሉ በክርስቶስ ፍጹም አድርጎ የማቅረብ የጳውሎስ ዓላማ ይፈጸማል፤ ቆላ. 1፥28-29:: እንደዚሁም ሐዋርያው ዮሐንስ ምእመናንን በክርስቶስ እንዲኖሩ ያበረታታቸዋል፤ 1ዮሐ. 2፥28፤ 3፥6:24::

መ) እኛ በክርስቶስ አንድ አካል ነን

ምእመናን በክርስቶስ ሲሆኑ፥ እያንዳንዱ ለየብቻው በክርስቶስ አይደለም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ የአካሉ ራስ በመሆኑ (ኤፌ. 5፥2-3)፥ በክርስቶስ ያሉ ሁሉ በአካሉ እርስ በርሳቸው ግንኙነት አላቸው:: ይህም ግንኙነት አንድ አካል፥ እርስ በርሳችንን ወይም እያንዳንዳችንን የሌላው ብልቶች ያደርገናል፤ ሮም 12፥5፤ 1ቆሮ. 10፥17፤ 12፥27:: ከዚህም የተነሣ፥ «አንድም ብልት ቢሠቃይ፥

ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል»፤ 1ቆሮ. 12፣26። የኅብረት ትስስሮች እጅግ ጠንካራ ናቸውና ምእመናን «በጌታ» ብቻ እንዲጋቡ ይፈቀዳል፤ 1ቆሮ. 7፣39። በዚህ አካል የቀድሞ ጥላቻዎች ይቀራሉ፤ ኀጢአት የሚገኝበት መለያየት ይወድቃልና ስለ ማዕርግና ስለ ዘር ልዩነት ዓለም ያለው አስተያየት ስፍራ አይኖረውም፤ ምክንያቱም፣ «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና»፤ ገላ. 3፣28፤ ኤፌ. 2፣13-22።

ሁላችን በክርስቶስ አካል በመሆናችን፣ በአንድ አገር ያሉ ማኅበሮች በክርስቶስ ሊሆኑ ይችላሉ (ገላ. 1፣22፤ 1ተሰ. 2፣14)፤ በዓለምም ሁሉ ያሉ እውነተኛ ምእመናን አንዲት ቤተ ክርስቲያን በመሆናቸው የክርስቶስ ሚስት ተብለው ተመስለዋል፤ ኤፌ. 5፣31-32፤ 1ቆሮ. 6፣17። የክርስቶስ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኒቱን ማንጻትና ለእርሱ ክብር እንድታመጣ፣ የእርሱን ባሕርይ እንድታንጸባርቅም ማድረግ ነው፤ ኤፌ. 5፣25-27።

ምእመናን ደግሞ ወደ ክርስቶስ በመቅረባቸው፣ ሕያዋን ድንጋዮች ሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ በሚያሰኝ ቤተ መቅደስ ተመስለዋል፤ 1ጴጥ. 2፣4-5። በዚህ መሠረት አንድ ይሆናሉና እየተደጋገፉ ይኖራሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «አንድ ይሆኑ ዘንድ... አንተ አባት ሆይ፣ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ» ብሎ በመጸለዩ (ዮሐ. 17፣20-21)፣ አንድነታችን በአብና በወልድ መካከል እንዳለው ፍጹም አንድነት እንዲሆን ይፈልጋል። ሆኖም አብና ወልድ ሁለት አካላት እንደሆኑ ሁሉ፣ ምእመናንም ወደ ፍጹም አንድነት ሲደርሱ እያንዳንዳቸው የራሳቸው ባሕርይ፣ ስጦታ፣ ችሎታ፣ አሳብ፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት፣ ስሜቶችና ግቦች ይኖሯቸዋል።

## ለ) ክርስቶስ በአማኙ

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስን፣ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» ይላል፤ ዮሐ. 1፣12። በአንዳንድ አገር ባህል መሠረት ክርስቶስን መቀበል ማለት ተገቢ አገላለጥ እንዳይደለ ይታሰባል፤ ምክንያቱም ታናሹ ወደ እርሱ ሲሄድ ታላቁ ይቀበለዋል እንጂ ታናሹ ታላቁን መቀበል እንደማይችል ይታመናልና ሰው ክርስቶስን ይቀበላል ቢልም፣ ሰውን ከክርስቶስ በላይ እንደ ማድረግ ነው ይላሉ። ይህ ባህል ከአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አሳብ የራቀ ይመስላል፤ ለምሳሌ ዘኬዎስ ኢየሱስን «ተቀበለው» ተብሎ ተጽፏል፤ ሉቃ. 19፣6። ደግሞም ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ራሱን «ባዶ አደረገ» (ዝቅ ዝቅ አደረገ)፤ ፊል. 2፣7። ክርስቶስ ራሱ ከሰማይ ሲናገርም፣ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ፣ ደጁንም ቢከፍትልኝ፣ ወደ እርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» ብሎ ከሰዎች ጋር ምን ዐይነት ግንኙነት እንደሚፈልግና ወደ ሰዎች እንዴት እንደሚቀርብ ያሳያል፤ ራእ. 3፣20።

ሰው በክርስቶስ ሲያምን ክርስቶስ ወደ ሕይወቱ ይገባልና በዚህ «በእኔ የሚኖር፣ እኔም በእርሱ፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል» የሚለው ቃሉ ይፈጸማል፤ ዮሐ. 15፣5። ሐዋርያውም በራሱ ተመክሮ፣ «ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» ብሎ መሰከረ፤ ገላ. 2፣20። አንድ ክርስቲያን እውነተኛ የሚሰኘው

ክርስቶስ ሲኖርበት ነው፤ ሮም 8፥10፤ 2ቆሮ. 13፥5፤ ራእ. 3፥20:: ከጥንት ጀምሮ በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰወረ ምሥጢር ነበር፤ ይኸውም እንደ አይሁድ ሁሉ አሕዛብን የማዳን የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበረ፤ ክርስቶስ ስለመጣ ግን፥ «የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው» የሚለው ምሥጢር ለአሕዛብ ተገለጠ፤ ቆላ. 1፥27:: ክርስቶስ በእኛ ይኖራል ማለት ከእርሱ አሳብ ጋር እንስማማለን ወይም የእርሱን ትምህርት እናውቃለን ማለት ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈሳዊና በምሥጢራዊ ሁኔታ እርሱ ራሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል ማለት ነው፤ «ክርስቶስ በልባችሁ በእምነት» ይኖራል፤ «ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?» ተብሎ ተጽፏልና፤ ኤፌ. 3፥17፤ 2ቆሮ. 13፥5:: ክርስቶስ በምእመናን ሁሉ ውስጥ ስለሚኖር፥ ለአንድ ወንድም የምናደርገውን ነገር ሁሉ ለክርስቶስም ጭምር እናደርገዋለን፤ ክርስቶስ፥ «እውነት እላችኋለሁ፤ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት»፤ «ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?» ብሎ ተናግሯልና፤ ማቴ. 25፥40፤ ሐ.ሥ. 9፥4::

ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና» በማለቱ ይህ በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ትልቅ ድጋፍ የሚሆን ነው፤ 1ዮሐ. 4፥4:: በእኛ ውስጥ የክርስቶስን መኖር መገንዘብ ትዕቢታችንን ያጠፋል፤ አለኝታችንን ያጠነክራልና በራሳችን ሳይሆን በእርሱ ኃይል ሥራችንን መፈጸም እንድንችል ተስፋ ይሰጠናል፤ ገላ. 2፥20፤ ሮም 15፥18-19፤ ፊል. 4፥13:: «ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም ይኖርበታል፤ በዚህም በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን» የሚለው ጥቅስ ደግሞ ሰው በመታዘዙና በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በክርስቶስ መሆኑንና ክርስቶስ በእርሱ መኖሩን ሊያውቅ እንደሚችል ያረጋግጣል፤ 1ዮሐ. 3፥24::

ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመለስ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይቀበላልና መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ይኖራል፤ ሐ.ሥ. 2፥38፤ ሮም 8፥9፤ 1ቆሮ. 6፥19-20፤ ገላ. 3፥2-5:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን በሰማይ ነው፤ ከአብ የላከልን ሌላ አጽናኝ በእኛ ዘንድ ይኖራል፤ እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ዮሐ. 14፥26-28:: የክርስቶስ መንፈስም በመሆኑ ክርስቶስ በእርሱ አማካይነት በውስጣችን ይኖራል (ገላ. 4፥6)፤ ደግሞም በእርሱ አማካይነት አብና ወልድ ወደ እኛ ይመጣሉ፤ በእኛም መኖሪያ ያደርጋሉ፤ ዮሐ. 14፥23:: ስለዚህ በመንፈሳዊ ሁኔታ ክርስቶስ ወይም መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንደሚኖር ማሰብ እንችላለን፤ ስንጸልይ ግን ክርስቶስ ሊቀ ካህናታችን ሆኖ በአብ ቀኝ ተቀምጦ እንመለከተዋለን፤ ሮም 8፥34፤ ዕብ. 7፥24-25::

ክርስቶስ ወደ ሰው ሕይወት በመግባቱ ሰው መለወጥ እንደሚጀምር ማሰብና ማመን አያስገርምም:: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «... መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» በማለት ጽፏል፤ 2ቆሮ. 3፥18:: የእግዚአብሔርም ዓላማ፥ «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኲር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ» ነው (ሮም 8፥29) እና ክርስቶስ ሲመለስ፥ እነርሱ ስለሚያዩት እርሱን እንዲመስሉ ያውቃሉ፤ 1ዮሐ. 3፥2::

አማኙ ወደ ክርስቶስ መልክ እንዴት እንደሚለወጥ ትምህርተ ቅድስናን ስናጠና በይበልጥ ማስተዋል እንችላለን:: አሁን ግን ክርስቶስን ለመምሰል እንዴት እንደምንታዘዝ እናስባለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» ብሎ የራሱን ተመክሮ ለሌሎች አርአያ አድርጎ በማቅረቡ፥ ምእመናን ሁሉ በተራቸው ክርስቶስን የመምሰል ምሳሌዎች

እንዲሆኑ ያደፋፍራል፤ 1ቆሮ. 11፥1። ሐዋርያው ዮሐንስም፥ «በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል» ብሎ ጽፏል 1ዮሐ. 2፥6። እንግዲህ ክርስቲያናዊ ኑሮ በምናደርገው ሁሉ ክርስቶስን እንድንመስል ጥረት የምናደርግበት ሊሆን ይገባዋል። «ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደተቀበላችሁ፥ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ» (ሮም 15፥7)፤ «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ» (ኤፌ. 5፥25)፤ «ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ» (ቆላ. 3፥13) ተብለን ታዝዘናል። መሠረታዊ አሳቡ፥ «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና... እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል» የሚለው ነው፤ 1ዮሐ. 3፥16።

ክርስቶስን መምሰል የሚታየው ብዙ ጊዜ መከራንና ፈተናን በመታገሣችን ውስጥ ነው። ክርስቶስ፥ «ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ ዕወቁ... ከዓለም ስላይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል» (ዮሐ. 15፥18-19) እና «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» (ዮሐ. 16፥33) ብሎ አስጠንቅቆናል። መከራን በተመለከተም የክርስቶስን ፈለግ እንድንከተል ተጠርተናል (1ጴጥ. 2፥21) እና የሐዋርያው ጳውሎስ ግብ የክርስቶስ መከራ ተካፋይ መሆንና በሞቱ እርሱን መምሰል ነበረ፤ ፊል. 3፥10፤ 1ተሰ. 1፥6። ከዚህም በላይ መከራችን በክርስቶስ ዘንድ ካለው መከበር ጋር የተያያዘ ነው፤ ምክንያቱም፥ «... የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በርግጥ የመከራው ተካፋዮች» እንሆናለን፤ ሮም 8፥17 አ.መ.ት.። ያዕቆብ ደግሞ፥ «ወንድሞች ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ ዐውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት» ብሎ ይመክራል፤ በመከራና በፈተና መንገድ በይበልጥ ክርስቶስን መስለን «ፍጹማንና ምሉኣን» እንሆናለንና፤ ያዕ. 1፥2-4። እንደዚህም በማለት ክርስቶስ የተስፋ ቃልን ይሰጣል:- «እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ፥ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ»፤ ራእ. 3፥21።

የአማኙ ሕይወት የክርስቶስን ሕይወት መምሰል ብቻ አይደለም፤ ከዚህ ባሻገር ያለው የክርስቶስ ዓላማ እኛ ወደ እርሱ ባሕርይ እየተለወጥን እንድንሄድ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎት ግብ፥ ምእመናንን፥ «የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ» እንዲያድጉ ማድረግ ነው። ይህም ሲሆን ቅዱሳን «አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን» ይሆናሉ፤ ኤፌ. 4፥11-13። አዎን፥ በዚህ ዐይነት አማኙ ቅዱስ ይባላል፤ ተገቢውን ሥራ ይሠራልና ከሌሎች ጋር በራሱ «ፍጹም» ይሆናል። ምእመናን ፍጹማን ሲሆኑ ክርስቶስን ይመስላሉ እንጂ ክርስቶስ አይሆኑም ወይም በክርስቶስ አይዋጡም። አማኙ እየተለወጠ ክርስቶስን ሲመስል፥ በይበልጥ በራሱ ፍጹም ሰው ይሆናል፤ ልዩ ልዩ ችሎታዎችንና ስጦታዎችን ይቀበላል፤ 1ቆሮ. 12፥4-27። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ሲያድጉ በሰልፍ ላይ እንዳሉ ወታደሮች አንድ ዐይነት ሳይሆኑ፥ በጠባይና በአገልግሎት የተለያዩ ይሆናሉ። ይህ ዐይነቱ ባሕርይ የሚታይበት ክርስቶስ፥ «ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል» (ማቴ. 10፥39)፤ «የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል» (ዮሐ. 10፥3) እና «... ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፤ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፏል» ብሏል፤ ራእ. 2፥17።

## ሐ) ክርስቶስ ከአማኙ ጋር

አማኙ በክርስቶስ፥ ክርስቶስም በአማኙ እንደሆነ አይተናል። በክርስቶስና በአማኙ መካከል ያለውን አንድነት በሦስተኛው አመለካከት መሠረት ልንመረምረው እንችላለን፤ ይኸውም ክርስቶስ ከአማኙ ጋር ወይም አማኙ ከክርስቶስ ጋር መሆኑን ነው። ይህ አሳብ አማኙ ከክርስቶስ ጋር ባለው ኅብረት ላይ ያተኩራል።

ሰው ክርስቲያን እንዲሆን፥ «ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት» ይጠራል፤ 1ቆሮ. 1፥9። ክርስቶስም፥ «እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ. 28፥20)፤ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በመካከላቸው እሆናለሁና» (ማቴ. 18፥20) ብሎ ከምእመናን ጋር ኅብረት እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጠ። እርሱ በሥጋ ወደ ሰማይ ስላረገ፥ ኅብረቱ በመንፈሳዊ መንገድ የሚፈጸም መሆኑ ግልጥ ነው። በዚህ ኅብረት ከእርሱ ጋር እንሠራለን (2ቆሮ. 6፥1)፤ እናውቀዋለን (ፊል. 3፥8-11) እና እርሱ ያስተምረናል (ማቴ. 11፥29)፤ ያጽናናናል (2ተሰ. 2፥16-17)፤ በእርሱም ፊት በሕይወት እንኖራለን፤ 2ቆሮ. 2፥10፤ 1ጢሞ. 5፥21፤ 6፥13። እንደ ማንኛውም ኅብረት ሁሉ ኅብረቱ ጠንካራ ወይም ልል ሊሆን ይችላልና ሐዋርያው፥ «ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን» (2ተሰ. 3፥16) እና «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስህ ጋር ይሁን» (2ጢሞ. 4፥22) በማለት የሰጠው ባርኮት በክርስቶስና በአማኞቹ መካከል ያለው ግንኙነት ከፊት ይልቅ እንዲጸና መመኘቱን ያሳያል።

ከዚህም ሁሉ ጋር በአምልኮ በማናስተውለው ሁኔታ ወደ መንግሥተ ሰማያት፥ «ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ... ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ» እንደርሳለን፤ ዕብ. 12፥22-24። እውነት ነው፤ እኛም በእምነት ካልሆነ በቀር በዐይን አይተን በዚህ አንጓተፍም፤ እዚያም ያሉት ፍጡራን ሊያዩን የሚችሉ መሆናቸው አልተገለጠም (4)።

ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት እያደገ ይሄዳል። አሁን ለእኛ ብሎ ወደ ሰማያት ከገባው ከጌታችን ጋር ኅብረት አለንና ጸሎታችንን ይሰማል፤ 1ዮሐ. 1፥3። ከሞትን በኋላ ከእርሱ ጋር የበለጠ ኅብረት ይኖረናል፤ 2ቆሮ. 5፥8፤ ፊል. 1፥23። ክርስቶስ ሲመለስም ኅብረቱ ቀድሞ ከነበረው ሁሉ ይበልጣል፤ 1ተሰ. 4፥17፤ 1ዮሐ. 3፥2። ክርስቶስ ደግሞ ከእኛ ጋር የሚኖረውን ኅብረት ይጠባበቃል፤ ዮሐ. 17፥24።

## መ) አንድነቱን በሚመለከት የተፈጠሩ ስሕተቶች (5)

በክርስቶስና በምእመናን መካከል ስላለው አንድነት ልዩ ልዩ ስሕተቶች ተከሥተዋል፤ ስሕተቶቹም በተለይ የሚከተሉት ናቸው (6)፦

1. አንድነቱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ ዓለምን በመፍጠሩ ከፍጥረት ሁሉ ጋር ያለው አንድነት ነው፤ ለዚህ አሳብ ዮሐንስ 1፥3 ሊጠቀስ ይችላል። ይህን የሚመስለው ሌላው ስሕተት ደግሞ፥ አንድነቱ «ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን» ነው የሚለው ነው፤ ለዚህም አሳብ ዮሐንስ 1፥9 ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ሰዎች በክርስቶስ ባያምኑም

እንኳ፥ ክርስቶስ በሰዎች መንፈሶች ይገኛል። የዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ስሕተት አንድነቱን ከክርስቶስ የድኅነት ሥራ ለይቶ መመልከቱ ነው።

2. አንድነቱ ሰው በክርስቶስ የተዋጠ ከመሆኑ የተነሣ የተገኘ አንድነት ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት አንድ ሰው «አእምሮዬ የክርስቶስ አእምሮ ነው» ወይም «እኔ ክርስቶስ ነኝ» ማለት ይችላል። ስሕተቱ የክርስቶስ አካልና የሰው አካል ሁለት አካላት መሆናቸውን አለመገንዘብ ነው።

3. አንድነቱ በክርስቶስና በአማኙ መካከል ግብረገባዊና ፍቅር ዐዘል አንድነት ነው። ይህም አንድነት በመምህርና በተማሪ መካከል ወይም በሁለት ጓደኞች መካከል ያለውን አንድነት የሚመስል ነው። ክርስቶስ በሰው ውስጥ እንዲኖር አስፈላጊ አለመሆኑን መቀበል የዚህ ዐይነቱ አንድነት አስተሳሰብ ስሕተት ነው።

4. አንድነቱ የሚገኘው፥ ሰው ስለሚጠመቅና ሥጋ ወደሙን ስለሚቀበል ነው። የዚህ አስተሳሰብ ስሕተት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በራሳቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ አካትተው እንደሚይዙ ማሰብ ነው። ሆኖም የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በረከት አስቀድሞ በተፈጸመው በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በተገኘው አንድነት ላይ የተመሠረተ ነው።

## *መደምደሚያ*

በክርስቶስ በመሆናችን፥ ክርስቶስ በእኛ በማደሩና ከእኛ ጋር በመኖሩ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም አንድነት አለን። በአብ ነን (ዮሐ. 17፥21፤ 1ተሰ. 1፥1፤ 1ዮሐ. 2፥24)፤ በመንፈስ ቅዱስም ነን፤ ሮም 8፥9፤ 1ቆሮ. 3፥16፤ 6፥19-20። አብ በእኛ ነው (ዮሐ. 14፥23)፤ መንፈስ ቅዱስም በእኛ ነው፤ ሮም 8፥9:11። እኛ አብን እንመስላለን (ማቴ. 5፥44-45:48፤ 1ጴጥ. 1፥15-16)፤ መንፈስ ቅዱስን እንመስላለን፤ ሮም 8፥3-6፤ ገላ. 5፥22-23፤ ዮሐ. 16፥13። ከአብ ጋር ኅብረት አለን (1ዮሐ. 1፥3፤ ማቴ. 6፥9)፤ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር እንዲሁ ኅብረት አለን፤ ሐ.ሥ. 15፥26-29፤ ሮም 8፥16፤ 2ቆሮ. 13፥14፤ ኤፌ. 4፥30። ስለዚህ ስናስብ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ያላቸው አንድነት የተያያዘ ቢሆንም፥ ከአብ ጋር በሰማያዊ አባትነት፥ ከወልድ ጋር በአዳኝነትና በጌትነት፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋርም ኀይላችን ሆኖ እንገናኛለን። አሁንም አብና ወልድ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ እኛ ይመጣሉ፤ አብና ወልድ በሰማያት ናቸውና። ይህን ስንልም በልባችን ውስጥ የሚፈጸመውን ተግባር ብንመለከት፥ ይህ የአብ፥ ያ የወልድ ወይም ደግሞ ያኛው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ብለን ሥራቸውን ልንለይ አንችልም፤ ፈቃዳቸውና ዓላማቸው አንድ ነው፤ «ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱ ነውና» ተብሎ ተጽፏል፤ ሮም 11፥36።

# ማስታወሻ

(1) ምዕራፍ 65 መ ይመ.

(2) እዚህ ላይ የምናቀርበው በGrudem ገጽ 841-847 እና በP.G.R. ገጽ 178-189 በሚገኘው ክፊል አሳብ ላይ ተመሥርቷል::

(3) ምዕራፍ 47ለ ይመ.

(4) «እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን...» (ዕብ. 12፥1) ሲል፥ በምዕራፍ 11 የተዘረዘሩት ምስክርነታቸውን የሰጡ የእምነት ጀግኖች ታሪክ ለእኛ ትዕግሥት ታላቅ አርኣያነት ያለው መሆኑን ያሳስባል፤ ዕብ. 12፥1-2:: እነርሱ ወደ ኢየሱስና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይመለከታሉ:: በሰማያት የእኛ ታሪክ ቢታወቅም፥ ምስጋናችን ቢሰማም (ሉቃ. 15፥10)፥ የምንተያየው ግን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ እንደሆነ ተገልጧል፤ 1ተሰ. 2፥19::

(5) በክርስቶስና በአማኙ መካከል የሚኖረው ግንኙነት በእንግሊዝኛ The Mystical Union ተብሎ ሊጠራ ይችላል:: አንዳንዶች ስለዚህ አንድነት በሚናገሩበት ጊዜ፥ በአማኙ ተመክሮ የሚሆነውን ብቻ ሲመለከቱ፥ ሌሎች ደግሞ አማኙ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ የመመረጡን ጉዳይ አጠቃልለው ያሳያሉ፤ Berkhof ገጽ 447 ይመ.

(6) Berkhof ገጽ 451 ይመ.

# ምዕራፍ 85 - የሰው ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑ

እግዚአብሔር፥ «ለሙሴ:- የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ፤ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና:: እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፤ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ»፤ ሮም 9፥15-16::

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እስራኤልና ስለ አሕዛብ ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሲያብራራ፥ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል በይስሐቅና በያዕቆብ በኩል የሚፈጸም መሆኑን ያሳያል፤ ሮም 9፥6-13:: ይህንም ሲያደርግ፥ ከአብርሃም ዘር የሚገኙት ሁሉ መንፈሳውያን ልጆች አለመሆናቸውን «በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል» በሚለው ቃል አረጋገጠ (ቍ. 7፤ ዘፍ. 21፥12)፤ ከዚህም በላይ መንፈሳዊ ዘር የሚገኘው ከጠሪው እንጂ ከሥራ አለመሆኑን ለማሳየት፥ «ያዕቆብን ወደድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ» የሚለውን አሳብ በድፍረት ጠቀሰ፤ ቍ. 13፤ ሚል. 1፥2-3:: ይህ ጥቅስ የተመሠረተው ለርብቃ በተሰጠው «ታላቁ ለታናሹ ይገዛል» በሚለው የትንቢት ቃል ላይ ነበረ፤ ቍ. 12፤ ዘፍ. 25፥23:: ይህም ሁሉ የሆነው፥ «በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ» ነው፤ ቍ. 11:: እንግዲህ ስለ ምርጫ ከሮም ምዕራፍ 9 የሚከተሉትን ነጥቦች መረዳት እንችላለን:-

ሀ) ምርጫ የእግዚአብሔር አሳብና አሠራር መሠረታዊ ሐቅ ነው (ቍ. 11)፤

ለ) ምርጫ በተለይ ምሕረት የሚቀበሉትን («የምሕረት ዕቃዎች») ያመለክታል (ቍ. 15-16:22-24)፤

ሐ) ምርጫ ከእግዚአብሔር አሳብ በጸጋ የሚተገበር እንጂ ሰው በሚያደርገው ተወስኖ የሚከናወን አይደለም (ቍ. 11)፤

መ) ምርጫ ሌላ (ወይም ሌሎች) የሚቀር ወይም የሚተው እንደሆነ ያሳያል፤ እንግዲህ እግዚአብሔር ያዕቆብን ሲመርጥ ዔሳውን ስለተወው፥ «የሚወደውን ይምረዋል፤ የሚወደውንም እልከኛ ያደርገዋል» ተብሏል (ቍ. 18)፤

ሠ) ምርጫ ለሰው በተለይ ላላመነ ሰው ምሥጢር ነውና ስለ ምርጫ ከፈጣሪው ጋር ሰው መከራከር አይገባውም፤ ሥልጣኑ የእግዚአብሔር ነውና (ቍ. 20-21)፤

ረ) ምርጫ ለእግዚአብሔር ክብር ነው፤ በቍጣው ኀይሉን ሲገልጥና በቍጣ ዕቃዎች ላይ ትዕግሥትን ሲያሳይ እንኳ ክብሩ ይታያል (ቍ. 22-23)::

የእግዚአብሔርን ዕቅድ በመረመርን ጊዜ ነጻ (እንደ ራሱ አሳብ፥ ፈቃድና ባሕርይ እንጂ በሌላ ነገር ላይ አልተመሠረተም)፥ አንድ፥ ጥበብ ያለበት፥ ዘለዓለማዊ፥ አይቀሬና ሁሉን የሚያጠቃልል መሆኑን አይተናል (1):: ምርጫ «የእግዚአብሔር ዕቅድ» የሚል ርእስ በተሰጠው ምዕራፍ ሊመረመር ይችል ነበር፤ ሆኖም ምርጫ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሰው ድኅነት ጋር ብዙ ጊዜ ተያይዞ በመገኘቱና የሰውን ድኅነት በተመለከተ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ርምጃ በመሆኑ፥ ከድኅነት ትምህርት ጋር ዐብሮ ቢጠና የበለጠ እንደሚመች ብዙ ሊቃውንት ያስባሉ (2)::

እግዚአብሔር «እንደ እርሱ አሳብ ሁሉን የሚሠራ አምላክ» ነውና ምርጫው እንዲፈጸም የተመረጡትን እንደ እርሱ አሳብ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ኤፌ. 1፥11:: በአመክንዮታዊ አስተሳሰብ ከቅደም ተከተል አንጻር ምርጫ አስቀድሞ ከመወሰን ይቀድማል፤ ሐዋርያው በኤፌሶን 1፥4 «... በክርስቶስ መረጠን» ካለ በኋላ ቀጥሎ በሚገኘው በቍ. 5 ላይ «... ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን» ብሎ ጽፏልና:: ከምርጫው ጋር የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ ተያይዞ ይታያል፤ «አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ» እንደወሰናቸው (ሮም 8፥29) እና «እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት...» ተብሎ ተጽፏል፤ 1ጴጥ. 1፥1-2:: በእግዚአብሔር ዕውቀትና ምርጫ መካከል ያለውን ግንኙነት ቈየት ብለን እናትታለን::

በነገረ መለኮት ላይ ምሥጢር እንዳለበት ሁሉ፥ በምርጫ ላይም ምሥጢር አለ:: መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ስለ ምርጫ ሲናገር፥ በሚገልጠው አሳብ ላይ የክርክር ነጥብ አይታይበትም፤ ሆኖም ከዚህ በላይ እንዳየነው በሮም ምዕራፍ 9 ብቻ ለአንዳንድ የተቃውሞ ጥያቄዎች መልሶችን ይሰጣል:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ግን ስለ ምርጫ ብዙ ጥያቄና ልዩ ልዩ አስተሳሰብ፥ ተቃውሞም እንኳ ተነሥቷል:: እንግዲህ ስለ ምርጫ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገኘውን ከዘረዘርን፥ በምርጫ ላይ የሚሰነዘሩ ልዩ ልዩ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችንም ከገለጥን በኋላ ለምእመናን የምርጫን ጥናት በረከት ለማቅረብ እንሞክራለን:: ይህም ታላቅ ትምህርት ነው፤ ምክንያቱም እንደ እግዚአብሔር ቃል አገላለጥ ምርጫ ከከባድ ማስጠንቀቂያ ይልቅ ታላቅ ማጽናኛ፥ ከፍተኛ የቅድስና መቀስቀሻ፥ ዐቢይ የምስጋና ምክንያትና ወንጌልን ለማሠራጨት ዐይነተኛ ማበረታቻ ነው::

## ሀ) ምርጫ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መገኘቱ

### 1. ምርጫ በብሉይ ኪዳን

እግዚአብሔር የሕዝቡ አባት እንዲሆን አብርሃምን በመምረጥ ከከለዳውያን አገር ወጥቶ ወደማያውቀው አገር እንዲገባ ጠራው:: አስቀድመን እንዳየነው ከእርሱ ዘር በመጀመሪያ እስማኤልን ሳይሆን ይስሐቅን፥ ቀጥሎም ዔሳውን ሳይሆን ያዕቆብን መረጠ:: ከያዕቆብ የዐሥራ ሁለቱ ነገድ አባቶች ተገኙ:: ሙሴ ለዚህ ሕዝብ ሲናገር፥ «እግዚአብሔርም የወደዳችሁና የመረጣችሁ ከአሕዛብ ሁሉ በቍጥር ስለበዛችሁ አይደለም፤ እናንተ ከአሕዛብ ሁሉ በቍጥር ጥቂቶች ነበራችሁና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን መሐላ ስለጠበቀ ስለዚህ እግዚአብሔር በጽኑ እጅ አወጣችሁ...» ብሎ በመናገሩ የእግዚአብሔር ምርጫ በሕዝቡ ታላቅነት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚፈጸም መሆኑን አሳየ፤ ዘዳ. 7፥7-8:: ሙሴና ነቢያት ስለ እስራኤል ሲናገሩ፥ ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ምርጫና ለሕዝቡ ባለው ልዩ ፍቅር ላይ አተኵሩ፤ ዘዳ. 4፥37፤ 9፥4-5፤ 10፥15፤ 1ሳሙ. 12፥22፤ 2ሳሙ. 22፥20፤ መዝ. 44፥3፤ ኢሳ. 43፥4፤ ሕዝ. 20፥5፤ ሶፎ. 3፥15:: ስለሚሰጠው ክብር ከመናገሩ በፊት እግዚአብሔር ዳዊትን፥ «አንተ መንጋውን ስትከተል በሕዝቤ በእስራኤል ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ ከበግ ጥበቃ ወሰድሁህ» በማለት ቀድሞ የነበረውን ዝቅተኛ ሕይወት አሳሰበው፤ 2ሳሙ. 7፥8::

እንደዚሁም ሰዎች ለመሪነት በእግዚአብሔር እንደተመረጡና ለተመረጡበት አገልግሎትም ብቁዎች አለመሆናቸውን ተረዱ፤ ዘጸ. 3፥4-12፤ 4፥10፤

ኢሳ. 6፥5-9፤ ኤር. 1፥4-6፤ ሐጌ 2፥23:: ከዚህም ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዳኝ መረጠ፤ እርሱም የሚያድነው የመረጠውን ሕዝብ ነው፤ ኢሳይያስ እንደሚከተለው ጽፏል:- «... ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ»፤ «እግዚአብሔር ለቀባሁት... ለቂሮስ እንዲህ ይላል»፤ «... እኔም የመረጥኋቸው ይወርሷታል»፤ «... እኔም የመረጥኋቸው በእጃቸው ሥራ ረጅም ዘመን ደስ ይላቸዋልና»፤ ኢሳ. 42፥1፤ 45፥1፤ 65፥9:22::

## 2. ምርጫ በክርስቶስ ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወይን አትክልትንና የሰርግ ግብዣ ምሳሌዎችን ከተረከ በኋላ፥ «የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና» በማለቱ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጥሪ በጆሮ ከሚሰሙት ይልቅ በልብ የሚቀበሉት ጥቂቶች ናቸውና እነርሱ በእግዚአብሔር የተመረጡ መሆናቸውን አሳየ፤ ማቴ. 20፥16፤ 22፥14:: ከዚህም ጋር «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» የሚለው የክርስቶስ ማስጠንቀቂያ ይስማማል፤ ማቴ. 11፥15፤ 13፥9:16:43፤ ማር. 7፥16፤ ሉቃ. 14፥35፤ ራእ. 2፥7:11:17:29፤ 3፥6:13:22::

ክርስቶስ በትምህርቱ ስለ «ምርጦቹ» ተናገረ (ሉቃ. 18፥7)፤ በትንቢታዊ መልእክቱም እግዚአብሔር በ«መረጣቸው ምርጦች» ምክንያት የመከራን ጊዜ እንዳሳጠረና የሰው ልጅ ሲመጣ ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ «የተመረጡትን» እንደሚሰበስባቸው አስተምሯል፤ ማር. 13፥20:27፤ ደግሞ ማቴ. 24፥22:31 ይመ.::

ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፤ ከእነርሱም ዐሥራ ሁለት መረጠ፤ ሐዋርያት ብሎም ሰየማቸው»፤ ሉቃ. 6፥13:: በተያዘበት ሌሊት፥ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» ብሎ ምርጫው የእነርሱ ሳይሆን የእርሱ በመሆኑ ላይ አተኰረ፤ ዮሐ. 15፥16:: ሁኔታቸውንም እንዲያስተውሉ በልዩ ልዩ ጊዜ መመረጣቸውን አሳሰባቸው፤ ዮሐ. 6፥70፤ 13፥18፤ 15፥19::

ክርስቶስ አብ ስለሰጠው ሰዎች ብዙ ጊዜ ተናግሯል፤ አንዳንድ ጊዜ ስለ ዐሥራ ሁለቱ ሲናገር (ዮሐ. 17፥6-12)፥ ዓለም ሳይፈጠር በቤዛነት ቃል ኪዳን (3) አብ ለወልድ ስለሰጣቸው ሁሉ እንደሚከተለው ተናገረ:-

«አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል... ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው» (ዮሐ. 6፥37-39)፤

«በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ እኔ የዘለዓለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም... እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል» (ዮሐ. 10፥27-28 አ.መ.ት.)፤

«ለሰጠኸው ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው» (ዮሐ. 17፥1-2)፤

«አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ፥ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ» (ዮሐ. 17፥24)::

እንግዲህ በአብ ለወልድ የተሰጡ ሰዎች ሁሉ በአብ የተመረጡና እነርሱ የዘለዓለምን ሕይወት አግኝተው በአብ ፊት ከክርስቶስ ጋር ለዘለዓለም እንዲኖሩ የተመረጡ መሆናቸው ግልጥ ነው።

### 3. ምርጫ በጳውሎስ መልእክታት

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ድኅነት ሲጽፍ የአብን፥ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ግብር በአንድነት ያቀርበዋል፤ ይህም በተለይ በኤፌሶን 1፥3-14 ተጽፎ ይታያል። እግዚአብሔር አብ የድኅነት ዐቃጅ፥ እግዚአብሔር ወልድ የድኅነት አደራጅና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የድኅነት ፈጻሚ ነው (4)። በዚህ አንቀጽ ሐዋርያው አብን በቊ. 3-6፥ ወልድን በቊ. 7-12፥ መንፈስ ቅዱስን በቊ. 13-14 ያመሰግናል። ድኅነት ከአብ ይመነጫል። አብ «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ» እንደባረከን የሚገልጠውን አጠቃላይ አሳብ በቊ. 3 ካቀረበ በኋላ፥ «ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን» በማለት ምእመናንን አብ የመረጣቸው በክርስቶስ እንደሆነና፥ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፥ ቅዱሳን ሆነው እንዲገኙ መሆኑን ገልጧል። ይህንም በፍቅር ተግባራዊ ለማድረግ በክርስቶስ የእርሱ ልጆች እንዲሆኑ ወሰናቸው (ቊ. 5)፤ ሁሉም ከሰው ሳይሆን እንዲያው በጸጋው ይሰጣቸዋልና ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ታላቅ ምክንያት ሆኗል (ቊ. 6)። ውሳኔው ደግሞ ከንቱ አይሆንም፤ ምክንያቱም «እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን» ይሠራል፤ ቊ. 11።

በዚህ ስፍራ ብቻ ሳይሆን፥ በሐዋርያው ትምህርት ሁሉ ምርጫ ከፍ ያለ ስፍራ ይኖረዋል። ምርጦች ከዓለም ሞኝ ነገር የተገኙ (1ቆሮ. 1፥27)፥ በእምነታቸው (ቲቶ 1፥1-2) እና በሕይወታቸው መለወጥ የሚታወቁ (1ተሰ. 1፥2-4)፥ ለመዳን የተመረጡ (2ተሰ. 2፥13)፥ በእግዚአብሔር የጸደቁ (ሮም 8፥33-34)፥ የእግዚአብሔር በመሆናቸው ለቅድስና ሕይወት የተጠሩ (ቆላ. 3፥12) ናቸው፤ ስለ እነርሱ ሐዋርያው በነገር ሁሉ ጸና፤ 2ጢሞ. 2፥10። የተመረጡት ሰዎች ብቻ አይደሉም፤ መላእክትም ከሰይጣንና ከወደቁት መላእክት ተለይተው እንዲታወቁ ተመርጠዋል፤ 1ጢሞ. 5፥21።

ሐዋርያው ስለ እስራኤል ሕዝብ ሲናገር፥ በኤልያስ ዘመን እንደነበረው ሁሉ በአሁኑ ጊዜም እንደዚሁ በጸጋ «የተመረጡ ትሩፋን» እንዳሉ ሲያትት፥ «እጥብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት ግን አገኙት፤ የቀሩትም ልባቸው ደነደነ» ብሎ የምርጫውን ውጤት ገለጠ፤ ሮም 11፥5-7 አ.መ.ት.። ሆኖም ለእስራኤል ተስፋ አለ፤ ምክንያቱም ሐዋርያው፥ እስራኤል «በወንጌል በኩል ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፤ በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው» ብሎ ጽፏል፤ ሮም 11፥28።

### 4. ምርጫ በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

ወንጌላዊ ሉቃስ «የሐዋርያት ሥራን» ሲተርክ፥ «ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያት... ካዘዛቸው በኋላ» ብሎ መጽሐፉን ይጀምራል፤ 1፥1-2። ጳውሎስ «የተመረጠ ዕቃ» መሆኑን እናነባለንና (9፥15) ሐዋርያው ሲሰብክ እግዚአብሔር የእስራኤልን አባቶች እንደመረጠ ተናገረ፤ 13፥17። ሉቃስም በኢየሩሳሌም ከአይሁድ «እግዚአብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማኅበራቸው ይጨምር ነበር» እና በአንጾኪያ ከአሕዛብ «ለዘለዓለም ሕይወት የተመረጡትም ሁሉ አመኑ» ብሎ በማተቱ፥ ሰዎች የሚድኑት በእግዚአብሔር ምርጫ በመሆኑ ላይ አተኰረ፤ ሐ.ሥ. 2፥47፤ 13፥48 ቀ.አ.።

ሐዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን፥ «ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶቅያም፥ በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች» እንደጻፈና ምንም እንኳ እነርሱ በየአገሩ ቢገኙም፥ «የተመረጠ ትውልድ» አድርጎ እንደቈጠራቸው እናነባለን፤ 1ጴጥ. 1፥1-2፤ 2፥9:: ምእመናንንም በአንድነት ሲገኙ እንደተመረጠች ቤተ ክርስቲያን ይቈጥራቸዋል፤ 1ጴጥ. 5፥13:: እርሱ ደግሞ «... ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ» ብሎ በማዘዙ፥ ምእመናን በእግዚአብሔር እንደተጠሩና እንደተመረጡ እየገለጠ በአዲሱ ጠባያቸውና አኗኗራቸው መጠራታቸውንና መመረጣቸውን እንዲያረጋግጡ ያደፋፍራቸዋል፤ 2ጴጥ. 1፥5-11::

ሐዋርያው ዮሐንስ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያንና ለአባሎቿ ሲጽፍ «ለተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ» በማለትና በመጨረሻም «የተመረጠች የእኅትሽ ልጆች ሰላምታ ያቀርቡልሻል» ብሎ መልእክቱን ስለሚደመድመው በእግዚአብሔር የምእመናን መመረጥ መሠረታዊ እውነት መሆኑ ይታያል፤ 2ዮሐ. 1-2:13::

በ«ዮሐንስ ራእይ» የእግዚአብሔር ዕቅድና ምርጫ ከዘለዓለም መሆኑን ስለ «ሕይወት መጽሐፍ» ከሚሰጠው ትምህርት ይታያል:: የሚድኑ ሰዎች ስሞች በዚህ መጽሐፍ ተጽፈዋል፤ ክርስቶስም፥ «ድል የነሣው... ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም» ብሎ ተስፋ ሰጥቷል፤ ራእ. 3፥5:: ደግሞም ይህ መጽሐፍ «የታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ» ይባላልና የምእመናን ስሞች ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በመጽሐፉ ተጽፈዋል፤ «በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ» ይጣላል፤ ራእ. 13፥8፤ 17፥8፤ 20፥12:15፤ 21፥27:: ሙሴ፥ ኢሳይያስ፥ ዳንኤል፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ጳውሎስ ስለዚህ መጽሐፍ አስቀድመው ተናግረው ነበር፤ ዘጸ. 32፥32፤ ኢሳ. 4፥3-4፤ ዳን. 12፥1፤ ሉቃ. 10፥20፤ ፊል. 4፥3::

## 5. ከምርጫው የተተዉ

ሰዎች ሲመረጡ፥ ያልተመረጡ ሌሎች የተተዉ ትሩፋን ይገኛሉ (5):: እንግዲህ እግዚአብሔር ለድኅነት ሰዎችን ሲመርጥ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስላልተመረጡ ምን እንደሚያስተምር ማወቅ ይገባናል፤ እንደዚሁም እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመለከታቸው ማስተዋል ያስፈልጋል:: እውነት ነው፤ ይህ ትምህርት አስፈሪ ነውና ልንቀበለው አንፈልግም፤ ሆኖም አሳቡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በመገኘቱ ልንክደው አንችልም:: ስላልተመረጡት ስናስብ ሁለት ነገሮችን መገንዘብ አለብን:- ሀ) ሰዎች ሁሉ በአዳም በመሆናቸው በኀጢአት፥ በሞትና በኵነኔ ሥር ናቸውና ስለ ሁኔታቸው የሚያመካኙበት የላቸውም (ሮም 3፥19-20)፥ ለ) እግዚአብሔር በኀጢአተኞች ሞት ያዝናል እንጂ አይደሰትም፤ ሕዝ. 18፥32፤ 33፥11፤ ሉቃ. 13፥34፤ 19፥41-44::

መጽሐፍ ቅዱስ ከምርጫ ስለተተዉት እንደሚከተለው ይናገራል:-

- «እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለራሱ ዓላማ ሠርቷል፤ ክፉዎችንም እንኳ ለጥፋት ቀን አዘጋጅቷል» (ምሳ. 16፥4 አ.መ.ት.)፤
- «እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ...የማያምኑ ...በቃሉ ይሰናከሉበታልና ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው» (1ጴጥ. 2፥7-8)፤
- «ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ...»፤ ይሁዳ 4::

የእግዚአብሔር፥ ሰዎችን የመተው ዓላማ ምን እንደሆነ ብንጠይቅ፥ የሐዋርያው ጳውሎስ መልስ እንደሚከተለው ነው:- «መጽሐፍ ፈርዖንን:- ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ፥ ስሜም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ለዚህ አስነሣሁህ ይላልና:: እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል፤ የሚወደውን እልከኛ ያደርገዋል»፤ ሮም 9፥17-18:: ከዚያም በኋላ በመልስ ዐዘል ጥያቄ፥ «... እግዚአብሔር ቍጣውን ሊያሳይ ኀይሉንም ሊገልጥ ወዶ፥ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለ ጠግነት ይገልጥ ዘንድ፥ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቍጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግሥት ከቻለ እንዴት ነው?» ብሎ በተተዉት ክብርን ማግኘቱን ያሳያል፤ ሮም 9፥22-23:: እንግዲህ ክብሩ ባልተመረጡት አማካይነት የሚታየው፥ በፍርዱ ኀይሉንና ጽድቁን በማሳየት፥ ደግሞም በምሕረቱና በቍጣው መካከል ያለውን ንጽጽር በማንጸባረቅና የምሕረቱን ባለ ጠግነት በመግለጥ ነው:: ይህ ዐይነት ልዩነት ክርስቶስ፥ «አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ» ብሎ በመወደስ፥ በማያምኑት ላይ በመፍረድና የሚያምኑትን በመባረክ ደስታውን በገለጠበት ቃል ይታያል፤ ማቴ. 11፥25-26::

እግዚአብሔር ሰዎችን በጸጋው ሲመርጥ፥ ሌሎቹን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን መንገድ አይፈልጉምና:: በብዙ መንገድ በጋርዮሽ ጸጋ ይባርካቸዋል፤ ከኀጢአታቸውም ይገታቸዋል (6):: አንዳንዶችን ግን እልከኞች ያደርጋቸዋል፤ ይህ በተለይም ለክፉ ምኞታቸው ዐልፈው መሰጠታቸው የዘለዓለም ፍርድ የመጀመሪያ ርምጃ መሆኑ ይታያል፤ ሮም 1፥24:26:28፤ 9፥18::

አንዳንድ ሰዎች ይህን ትምህርት ሲሰሙ እንግዲህ፥ እግዚአብሔር አንዳንዶችን ለዘለዓለም ድኅነት፥ ሌሎችንም ለዘለዓለም ኵነኔ ይመርጣል ይላሉ (7):: ይህ ዐይነት አባባል ትክክለኛ አይደለም፤ ምክንያቱም፥ ሀ) እግዚአብሔር በተመረጡት ላይ ምሕረቱን፥ ባልተመረጡት ላይ ደግሞ ጽድቁን ያሳያል፤ ለ) የተመረጡት በረከት ከእግዚአብሔር ምሕረት ሲገኝ፥ ያልተመረጡት ኵነኔ የራሳቸው ኀጢአት ውጤት ነው፤ ሐ) እግዚአብሔር ለጥፋት በተዘጋጁት የቍጣ ዕቃዎች ላይ ፍርዱን በማሳየቱ፥ በበለጠ ንጽጽር ለክብር በተዘጋጁት የምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ገልጧል::

እንግዲህ ምርጫ ከፍ ያለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ ታላቅ ክፍልም እንደሆነና የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገለጥበት መሆኑን አይተናል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ምርጫን እንደሚከተለው ገልጦታል:- «ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን»፤ 2ጢሞ. 1፥9:: ይህ ትምህርት ብዙ ምሥጢር አለበትና ምርጫን በሚመለከት የሚሰነዘሩ ልዩ ልዩ አሳቦችን በመጠኑ ማተት ይገባናል::

## ለ) ስለ ምርጫ የተሰጡ ልዩ ልዩ አስተያየቶች

ስለ ምርጫ የሚነሣው ዋና ጥያቄ በምርጫ ላይ ወሳኙ እግዚአብሔር ነው ወይስ ሰው? የሚለው ነው:: ወሳኙ እግዚአብሔር ከሆነ፥ እግዚአብሔር ያዳላልና ሰው እንደ ነጻ ፈቃዱ መምረጥ ባለመቻሉ ኀላፊነት የለበትምና እግዚአብሔር በፍትሕ በሰው ላይ መፍረድ አይችልም የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም:: ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ወሳኙ ሰው እንዲሆን ልዩ ልዩ

አስተያየቶችንና ትምህርቶችን ያቀርባሉ፤ በመጠኑም ቢሆን እነዚህን አስተያየቶችና ትምህርቶች ከዚህ ቀጥሎ እንመረምራቸዋለን:-

1. ምርጫ ለአገልግሎት እንጂ ለድኅነት አይደለም

እውነት ነው፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ለልዩ ልዩ አገልግሎት ይመርጣቸዋልና እያንዳንዱ ክርስቲያን በዓለምም ሆነ በቤተ ክርስቲያን የተጠራለትን ማወቅ ያስፈልገዋል:: ሆኖም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አገልጋዮቹን (ነቢያት፥ ካህናት፥ ነገሥታት) ከሕዝቡ መካከል መረጠ፤ እንደዚሁም ክርስቶስ ሐዋርያትን ከደቀ መዛሙርቱ ውስጥ መረጠ:: ዛሬም እግዚአብሔር ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሰዎችን ከምእመናን ማለት ከዳኑት መካከል ይመርጣል:: ብዙ ጥቅሶች ሰዎች ለድኅነት እንደተመረጡ ይገልጣሉ:: አብ ለወልድ ሰዎችን የሰጠው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ» ነበር (ዮሐ. 6፥37-40)፤ ሉቃስ «ለዘለዓለም ሕይወት የተመረጡትም ሁሉ አመኑ» (ሐ.ሥ. 13፥48 ቀ.አ.) አለ፤ ጳውሎስም፥ «እግዚአብሔር ለቊጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ»፤ «እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና» በማለት የተሰሎንቄን ምእመናን አጽናና፤ 1ተሰ. 5፥9፤ 2ተሰ. 2፥13::

2. ምርጫ ለሰዎች ሁሉ ይሰጣል

ይህ አስተሳሰብ በሦስት መንገድ ይታያል:-

ሀ) «ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ» ተብሎ በትንቢት ተነግሯል፤ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ እንደተመረጡ ይታሰባል:: ሆኖም ይህ የትንቢት ቃልና የጴጥሮስ ስብከት የእግዚአብሔር በረከት ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን፥ ለዓለም ሕዝቦችና ወገኖች ሁሉ የሚሰጥ መሆኑን ያሳያል እንጂ አንድ ሳይቀር እያንዳንዱ ሰው እንደተመረጠ አያሳይም፤ ሐ.ሥ. 2፥17:: በዚህ መሠረት ሐዋርያው፥ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» የሚለውን የኢዩኤልን ትንቢት ጠቅሶ አድማጮቹ እንዲድኑ፥ ንስሓ እንዲገቡና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ ነገራቸው፤ ሐ.ሥ. 2፥21:38:: በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ሰዎች ሁሉ ቢመረጡም፥ የሚድኑት የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያምኑት ብቻ ናቸው:: በዚህም መሠረት ምርጫ፥ ሰው ለእግዚአብሔር ጥሪ መልስ እንዲሰጥ ኃይል ይሰጠዋል እንጂ ድኅነትን አያስገኝለትም:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ ምርጫ እንደዚህ አይናገርም::

ለ) የሚጠመቁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ጸጋ ይቀበላሉና የተመረጡ ናቸው:: ይህ አሳብ የማይጠመቁትን አያካትትም፤ በዚህ ትምህርት መሠረት ሰው ከተጠመቀ በኋላ ዐውቆ ኃጢአትን ቢሠራ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ግቡ አይደርስም:: እንግዲህ በዚህ አስተሳሰብ ምርጫ የሚፈጸመው ለጥምቀት ሲባል ነው፤ ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጥምቀት ለእግዚአብሔር ሥራ የሰው አጸፋ ነው እንጂ ሰዎች የሚመረጡበት መነሻ አይደለም::

ሐ) ካርል ባርት እግዚአብሔር ክርስቶስንና በክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ እንደመረጠ አስተማረ (8):: እውነት ነው፤ ሰዎች በክርስቶስ ይመረጣሉ፤ ነገር ግን በክርስቶስ የተመረጡ ሰዎች እግዚአብሔር «አስቀድሞ ያወቃቸው» የተወሰኑ ሰዎች እንጂ ሁሉም ሰዎች አልነበሩም፤ ሮም 8፥29::

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አስተያየቶች ከዓለም ሰዎች ሁሉ ሳይመረጡ የቀሩ ወይም የተተዉ ሰዎች ባለመገኘታቸው «ምርጫ» እንዳለ አያሳዩም::

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ያልተመረጡ ወይም የተተዉ እንዳሉ ያሳያል፤ በዚህ ምዕራፍ ላይ ሀ5 ይመ.።

3. ምርጫ በእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ ላይ ይመሠረታል

ይህ አስተሳሰብ ሰዎች ወንጌሉን ሲሰሙ የሚያምኑትን እግዚአብሔር አስቀድሞ በማወቁ መረጣቸው የሚል ነው። ስለዚህ አስተሳሰብ ምን ማለት እንችላለን?

ሀ) የእግዚአብሔር ዕውቀት ከሰው ዕውቀት የተለየ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል፤ ሁሉንም «አሁን» ያውቃልና «አስቀድሞ ዐወቀ» የሚለው አባባል የድኅነት ቅደም ተከተል ለሰው ግልጥ እንዲሆን ነው (9)።

ለ) ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ በተለየ መንገድ ያውቃቸዋል። ስለ እስራኤል፥ «እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን ዐውቄአችኋለሁ» ሲል ሌሎችን ሕዝቦች ሳይሆን የእስራኤልን ሕዝብ በልዩ መንገድ እንዳወቃቸው ሲገልጥ፥ የራሱ ሕዝብ በመሆኑ ላይ አተኲሪ፤ አሞጽ 3፥2። በዚህ ዐይነት አስተሳሰብ የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅና መምረጥ እጅግ ይቀራረባሉ (10)። አዲስ ኪዳን ደግሞ፥ «ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው»፤ «አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ...» እና «ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል» በማለቱ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ ምእመናንን እንደሚያውቅ ያሳያል፤ 1ቆሮ. 8፥3፤ ገላ. 4፥9፤ 2ጢሞ. 2፥19።

ሐ) ሐዋርያት ስለ ምርጫ ሲጽፉ ሰዎችን እንጂ ጠባያቸውን ወይም ሥራቸውን አያመለክቱም። እንግዲህ ሐዋርያው «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና፤ አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው... አጸደቃቸው... አከበራቸው» ብሎ በመጻፉ የተመረጡትን ሰዎች ከበኩራቸው ክርስቶስ ጋር ያዛምዳቸዋል፤ ሮም 8፥29። እንደዚሁም፥ «ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን» ሲል «እኛ» በክርስቶስ እንደተመረጥንና የተፈለገው ጠባይ የምርጫ ምክንያት ሳይሆን የምርጫ ውጤት መሆኑን ያሳያል፤ ኤፌ. 1፥4።

መ) መጽሐፍ ቅዱስ እምነት የምርጫ ምክንያት እንደሆነ አይናገርም፤ ለዚህ አሳብ አንድንም ፍንጭ እንኳ አይሰጥም። ነገር ግን የምርጫ መነሻ ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ የተሰወረ ምሥጢር ነውና ስለ ያዕቆብና ስለ ዔሳው፥ «ልጆቹ ገና ሳይወለዱ፥ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ፥ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ ለእርሷ (ለእናታቸው):- ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት» በማለት፥ ምርጫ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል፤ ሮም 9፥11። ጳውሎስ ስለ ምርጫ ምክንያት፥ «በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ» (ኤፌ. 1፥5-6) በማለት በእግዚአብሔር ልዑላዊ ፈቃድና በጸጋው ላይ፥ «ያዳነን... እግዚአብሔር ነውና፤ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን» (2ጢሞ. 1፥9) በማለትም በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ አሳብና ጸጋ ላይ ያተኲራል። በእነዚህ ጥቅሶች ጸጋ እንዲሰጥ የእምነትን ሚና የሚያሳይ አንዳች አሳብ አይገኝም። በዚህ ፈንታ ሐዋርያው፥ «እግዚአብሔር በመንፈስ (ቅዱስ) መቀደስ

እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና» (2ተሰ. 2፥13) በማለት መዳን የምርጫ ውጤት ብቻ ሳይሆን፥ እውነትን በማመን የሚገኝ መሆኑንና ይህም እምነት በመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው መቀደስ የሚረጋገጥ መሆኑን ጭምር ያሳያል:: ምርጫ መቶ በመቶ ከእግዚአብሔር ነው፤ ሐዋርያው ስለ እስራኤል ሲጽፍ፥ «... እንደዚሁም በአሁኑ ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች (ትሩፋን) አሉ» ብሎ ምርጫ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ እንጂ ሰው በሚኖረው እምነት ወይም ሥራ ላይ የሚመሠረት አለመሆኑን ገልጧል፤ ሮም 11፥5:: እንግዲህ፥ «የእግዚአብሔር ምርጫ የሚገኘው በሰው ፈቃድና በሰው ሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ምሕረት ነው» (ሮም 9፥16 ቀ.አ.) የሚለው አተረጓጐም «ለወደደ» እና «ለሮጠ» የሚለውን የተለመደ አተረጓጐም ያብራራል::

ሠ) ምርጫ የሰው ጉዳይ ቢሆን ኖሮ፥ አንድም ሰው አይድንም ነበር፤ ምክንያቱም፥ «እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም»፤ መዝ. 13፥1-3፤ ሮም 3፥11::

### 4. ምርጫ ሰዎች አንድ በአንድ መመረጣቸውን ሳይሆን ሁሉም በአንድነት መመረጣቸውን ያሳያል

እውነት ነው፤ ሰዎች በአንድነት በክርስቶስ ተመርጠዋል፤ አዲስ ኪዳን ስለ ሁሉም ምርጦች በአንድነት ይናገራልና:: አንዳንዶች ይህን ሲያስተምሩ ሁኔታውን በአውቶቡስ እንደሚጓዙ መንገደኞች ይመለከቱታል (11):: አውቶቡስ ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀስ፥ አዳዲስ መንገደኞች ይሳፈሩበታል፤ አንዳንድ ጊዜም ሌሎች ሰዎች ከአውቶቡሱ ይወርዳሉ:: በምሳሌው መሠረት በአውቶቡስ ውስጥ ያሉ ሁሉ አንድ ቡድን ናቸው:: በክርስቶስ ያሉ ሁሉ ምርጦችም አንድ ቡድን ናቸው፤ እነርሱ በክርስቶስ አምነው በአንድነት ወደ መንግሥተ ሰማያት በመጓዝ ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው:: ይህ አመለካከት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር መስማማቱ በልዩ ልዩ ነገር ይታያል:-

ሀ) የመጽሐፍ ቅዱስ አጽንዖት በምርጦቹ አንድነት ላይ ቢሆንም፥ የእያንዳንዱ አማኝ ምርጫ እንዳለ ደግሞ ግልጥ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዓውን፥ «ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ» ብሎ አደፋፈራቸው፤ ሉቃ. 10፥20:: እያንዳንዱ ሰው የራሱ የግል ስም አለው፤ በዚህ ስም ይታወቃል፤ ይጠራልም፤ ስሙም ሲጠራ፥ አቤት ብሎ ይመልሳል:: እንግዲህ በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ዓለም ሳይፈጠር የሰው ስም ከተጻፈ፥ እርሱ በዚያ ስም ከዓለም መፈጠር በፊት ጀምሮ በእግዚአብሔር ታውቋል፤ በሌላ አነጋገር ሰውዬው ተመርጦ ስሙ ተጽፏል፤ ራእ. 13፥8፤ 17፥8፤ 20፥15::

ለ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ከሰጠኸኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው...» (ዮሐ. 6፥39) በማለት የአብ ፈቃድ በመሆኑ ላይ በማተኰሩ የእያንዳንዱ አማኝ ምርጫ ከፍ ያለ ዘለዓለማዊ ዋጋ እንዳለው አሳይቷል:: ክርስቶስም ሰዎችን ዐውቆ አንድ በአንድ በስም ጠራቸው (ሉቃ. 19፥5፤ 22፥31-32)፤ ይህም አንድ በአንድ ከመመረጣቸው ጋር ይስማማል፤ ለእያንዳንዳቸውም አዲስ ስም ይሰጣቸዋል፤ ራእ. 2፥17::

ሐ) ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር መመረጡን ዐውቆ፥ «አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» ብሎ ጻፈ፤ ገላ. 2፥20::

እንግዲህ የአውቶቡሱ ምሳሌ ለአንዳንድ ትምህርት ጠቃሚ ቢሆንም፥ ሰዎች በጅምላ ሳይሆን፥ አንድ በአንድ የሚታወቁ መሆናቸውን ማስተዋል ይገባናልና እያንዳንዱ ክርስቲያን በእግዚአብሔር የተመረጠ በመሆኑ ላይ ርግጠኛ ሊሆን ይገባል፤ 2ጴጥ. 1፥10።

እግዚአብሔር በልዕልናው መሠረት ሰዎችን የመረጠ መሆኑን የማይቀበሉ ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ልዩ ልዩ አሳቦችንና አስተያየቶችን ያቀርባሉ፤ በተለይ የአርሚኒዮስ ተከታዮች ምርጫ በሰው እምነት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ያስተምራሉ። ከእነርሱም ጥቂቶች ያይደሉ ሰው በራሱ ኀይል ማመን አይችልም፤ በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ለሰው ኀይልን ይሰጣልና በዚያን ጊዜ እንደ ነጻ ፈቃዱ ክርስቶስንና ወንጌሉን መቀበልም ሆነ አለመቀበል ይችላል ይላሉ። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የሰው ድኅነት በእግዚአብሔር ጸጋና በሰው ችሎታ ተመሥርቷል (12)፤ ይሁን እንጂ ወሳኙ ሰው ነው።

5. ምርጫ በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፈቃድ የተወሰነ ነው

ከአውግስጢኖስ በፊት የነበሩ አበው ስለ ምርጫ ብዙ አላተቱም። አውግስጢኖስ ግን የሰዎች ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፥ ያልተመረጡትንም በኀጢአታቸው እንደተዋቸው በግልጥ አስተማረ (13)። ብዙ ሰዎች የአውግስጢኖስን ትምህርት በሙሉ ወይም በከፊል ቢቃወሙትም፥ አንዳንድ መሪዎች ለምሳሌ እንደ አኲናስ ያሉት ከሞላ ጐደል ተቀበሉት። ሉተር፥ ካልቪንና የተሐድሶ መሪዎች ግን በአንድነት ትምህርቱን በሙሉ ተቀበሉት። የአርሚኒዮስ ተከታዮች የተሐድሶ ተከታዮችን በተቃወሙአቸው ጊዜ፥ ትምህርቱ በዶርት ሲኖዶስ ተወሰነ (14)።

በተሐድሶ አመለካከት ስለ እግዚአብሔር ምርጫ ዋናው ትምህርት በሮም ምዕራፍ 9 እና በኤፌሶን 1፥3-14 ላይ ተመሥርቷል (15)። ትምህርቱን እንደሚከተለው በዐጭሩ መዘርዘር እንችላለን:-

ሀ) የእግዚአብሔር ልዑላዊ ፈቃድ ነው (ኤፌ. 1፥5:11፤ 2ጢሞ. 1፥9)፤

ለ) በክርስቶስ የሚፈጸም ነው (ኤፌ. 1፥4:10፤ 2ጢሞ. 1፥9)፤

ሐ) በፍቅር የሚፈጸም ነው (ዮሐ. 3፥16፤ 1ዮሐ. 4፥9-10)፤

መ) ዘለዓለማዊ ነው (ኤፌ. 1፥4፤ 2ጢሞ. 1፥9)፤

ሠ) የማይለወጥ ነው (ሮም 8፥29-30፤ 2ጢሞ. 2፥19)፤

ረ) ለእግዚአብሔር ክብር ነው (ሮም 9፥22-23፤ ኤፌ. 1፥6:12:14)፤

ሰ) ለሰው መዳን ነው (ሐ.ሥ. 13፥48 ቀ.አ.፤ ሮም 11፥7፤ 2ተሰ. 2፥13፤ 1ዮሐ. 4፥9)፤

ሸ) ለቅድስና ነው (ኤፌ. 1፥4፤ 1ተሰ. 4፥3)፤

ቀ) በሰው ችሎታ፥ ፈቃድ፥ ሥራ ወይም ጠባይ ላይ አልተመሠረተም (ማቴ. 11፥25-26፤ ሮም 9፥11-12፤ 1ቆሮ. 1፥27-28፤ 1ተሰ. 1፥4፤ 2ጢሞ. 1፥9፤ 1ዮሐ. 4፥10)፤

በ) ሌሎች ሳይመረጡ እንደቀሩ ያሳያል (ማቴ. 20፥16፤ 22፥14፤ ሮም 11፥7)።

በተሐድሶ ተከታዮች መካከል በእግዚአብሔር አሳብ ዘንድ ስለ ምርጫና ስለ ሰው ውድቀት ቅደም ተከተል ልዩ ልዩ አሳብ ተነሣ። አንዳንዶች ምርጫን በአመክንዮታዊ አስተሳሰብ ከፍጥረትና ከውድቀት በፊት እንደነበረ ሲገልጡት (16)፥ ሌሎች ከፍጥረትና ከውድቀት በኋላ የተከናወነ መሆኑን አስተማሩ (17)። እንደነዚህ ዐይነቶቹን አሳቦች የሚደግፉ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጥቅሶች የሚገኙ

ላይመስለን ይችላል፤ ይህ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነውና። ግሩደም ይህን ጥናት ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም (18)። በርክሆፍ ግን በሰፊው ሊያብራራው ሞክሯል (19)።

## ሐ) ስለ ምርጫ የሚሰነዘረው ተቃውሞ

ከዚህ በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምርጫ የሚሰጠውን ትምህርት አትተናል። ይህ የተሐድሶ ትምህርት ነው፤ ሆኖም ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ትምህርት እንደማይቀበሉት መካድ አንችልም። በተለይ የዚህ ትምህርት ተቃዋሚ ያዕቆብ አርሚኒዮስ ነውና የተሐድሶ ትምህርትን የማይቀበሉት ብዙ ጊዜ አርሚኒዮሳውያን ተብለው ይጠራሉ። ትምህርቱን በማይቀበሉት መካከልም ቢሆን ልዩ ልዩ አስተሳሰብ አለ። አርሚኒዮሳውያን ሁሉ የእግዚአብሔር ምርጫ በሰው ምርጫ መመሥረቱን ያምናሉ፤ ትምህርታቸውን ላለመቀበል ምክንያት የሆኑትን በለ3 ሥር ገልጠናቸዋል። በተጨማሪም ሌላ የተለያየ ተቃውሞ ስላለ ይህንን ተቃውሞ በአምስት አርእስት አጠቃልለን ከዚህ በታች ልንገልጠው እንሞክራለን:-

### 1. ምርጫው ኢ-ግብረገባዊ ነው

ይህ ተቃውሞ በልዩ ልዩ ዐይነት ይቀርባል:-

ሀ) ይህ ትምህርት ሰውን እንደ አሻንጕሊት (ፓፐት፥ ሮቦት) ያደርገዋል፤ ሰው ቢፈልግም፥ ባይፈልግም አማኝ ለመሆን ይገደዳል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ልዑላዊ ፈቃድና የሰው ነጻ ፈቃድ አብረው እንዴት መኖር እንደሚችሉ ምሥጢር ቢሆንም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱን በግልጥ ያስተምራል። ይህም የምርጫ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የመግቦተ እግዚአብሔር ትምህርት ምሥጢር ነው (20)።

ለ) አንዳንዶች ሰው ሁሉ ካልተመረጠ ብዙዎቹ ዕድል የላቸውም ይላሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ «... እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት ዐጡ» በማለቱ የሚፈረድባቸው ባለመመረጣቸው ሳይሆን የተገለጠላቸውን ባለመቀበላቸው ነው፤ ሮም 1፥20-21።

ሐ) አንዳንዶች ደግሞ ሰው የእግዚአብሔርን ምርጫ እስከ መጨረሻ መቃወም አይችልም ይላሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ግን ሰው እግዚአብሔርን የማይፈልግ ከሆነ የእግዚአብሔርን የመምረጥ ሥራ ለጊዜው መቃወም ይችላል፤ እግዚአብሔር ግን ምርጫው እንዲፈጸም ሰው የምርጫውን ሥራ በመልካም ፈቃድ እንዲቀበለው አሳቡን፥ ስሜቱን፥ ፈቃዱንና ልቡን ይለውጣል፤ ሐዋርያው፥ «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» ብሏልና፤ ፊል. 2፥13። እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ሲሠራ፥ ሰው እግዚአብሔርንና ጽድቁን እንዲፈልግ ያደርጋል፤ ከዚያም በኋላ ሰው ወድዶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይከተለዋል።

### 2. ምርጫው ኢ-ፍትሓዊ ነው

እግዚአብሔር አንዳንዶችን ብቻ በመምረጥ ያደላል። ለዚህ ተቃውሞ ሁለት መልሶች አሉ:-

ሀ) አንድም ሰው በእግዚአብሔር ፍርድ ላይ የሚያቀርበው ምክንያት የለውም፤ ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ናቸውና፤ ሮም 3፥19-20። ሰው በፍትሕ የመርታት መብቱ እንደተነካ ማሳየት ያስፈልገዋል። ኀጢአተኛ ግን

በእግዚአብሔር ፊት መብት የለውም:: ከዚህ የተነሣ ምርጫ የምሕረት እንጂ የፍትሕ ጉዳይ አይደለም፤ ሮም 9፥16:: «እግዚአብሔር ኀጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው... በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ» እንደሰጣቸው ሁሉ (2ጴጥ. 2፥4)፥ አንድን ሰው ብቻ መርጦ ባያድን እንኳ ጻድቅ ይሆን ነበር፤ ነገር ግን መሓሪ እንደ መሆኑ ብዙ ሰዎችን ለማዳን መረጠ:: ሰዎችን ሁሉ ያልመረጠበት ምክንያት በጥበቡ ውስጥ የተሰወረ ምሥጢር ነው::

ለ) ይህ ዐይነቱ ተቃውሞ እግዚአብሔር ኀጢአትን የሚያደርጉትን፥ የሚኰንኑትንና የማይድኑትን ሰዎች ዐውቆ መፍጠሩ ትክክለኛ አይደለም እንደ ማለት ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ አሳብ መልስ ሲሰጥ ለሰው ትዕቢት ምንም ስፍራ አይሰጥም:: «እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል፤ የሚወደውንም እልከኛ ያደርገዋል» ብሎ ከጻፈ በኋላ፥ «እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል?» የሚለውን የሰው ክርክር ጥያቄ ይጠቅሳል:: ለዚህ ጥያቄ መልሱ በዐጭሩ እግዚአብሔር ልዑላዊ ፈጣሪ በመሆኑ፥ አንዱን ለክብር፥ አንዱንም ደግሞ ለውርደት ማድረግ የእርሱ ሥልጣን ነውና ፍጥረቱ ፈጣሪውን ስለዚህ መጠየቅ አይገባውም፤ ሮም 9፥18-24:: ክርስቶስ ደግሞ በወይን አትክልት ሠራተኞች ምሳሌ መጨረሻ፥ «... በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን?... የተጠሩ ብዙዎች የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና» በማለቱ የእግዚአብሔር ውሳኔና ምርጫ በሥልጣኑና በመብቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አሳይቷል፤ ማቴ. 20፥15-16::

### 3. ምርጫው ኢ-መንፈሳዊ ነው

የምርጫው ትምህርት ሰውን ትዕቢተኛ፥ ትምክሕተኛ፥ ጉረኛና ጥጋበኛ ያደርገዋል የሚሉ አሉ:: ሰው እንደዚህ ከሆነ የምርጫን ትምህርት አላስተዋለም ማለት ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ምሥጢር የተገለጠው፥ ለጥበበኞችና ለአስተዋዮች ሳይሆን «ለሕፃናት» ነው (ማቴ. 11፥25)፤ ለድኅነት «እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፥ ኀያላን የሆኑ ብዙዎች፥ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም»፤ እግዚአብሔርም «የዓለምን ሞኝ ነገር» እና «የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ»፤ 1ቆሮ. 1፥26-27:: ስለዚህ ሰው መመካት የሚገባው በእግዚአብሔርና በክርስቶስ መስቀል ነው፤ 1ቆሮ. 1፥30-31፤ ገላ. 6፥14::

### 4. ምርጫው ኢ-ተልእኮታዊ ነው

የሰው ድኅነት በእግዚአብሔር ምርጫ ከተወሰነ፥ ወንጌልን መስበክ ምንም ለውጥ አያመጣም:: ለዚህ ተቃውሞ መልስ የሚሆኑ ነጥቦችን እንደሚከተለው መዘርዘር እንችላለን:-

ሀ) የተመረጡትን እግዚአብሔር እንጂ እኛ አናውቅም::

ለ) ምርጫን ብናስተውለውም ባናስተውለውም ወደ ፍጥረት ሁሉና ወደ ሕዝቦች ሁሉ ሄደን ወንጌልን ልንሰብክ ታዝዘናል፤ ማቴ. 28፥19-20፤ ማር. 16፥15፤ ሉቃ. 24፥47-48፤ ዮሐ. 20፥21-23፤ ሐ.ሥ. 1፥8::

ሐ) ምርጫ የሚፈጸመው የእግዚአብሔር ቃል ተሰብኮ ሰዎች አምነው ሲድኑ ነው፤ 1ጴጥ. 1፥23-25::

መ) ሰዎች በእግዚአብሔር ተልከው ወንጌልን ሲሰብኩ፥ ሥራቸውና ድካማቸው ከንቱ ሆኖ አይቀርም፤ ምክንያቱም አገልጋዮች ታማኞች በመሆናቸው፥ ብዙዎችም ሆኑ ጥቂቶች የተመረጡት ሲያምኑ በታላቅ ደስታ

ያያሉ፤ ሐ.ሥ. 18፥9-10፤ 1ተሰ. 1፥4-5፤ 2፥19-20:: እንግዲህ ምርጫ የወንጌል ሥራ በከንቱ የሚቀር አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፤ 1ቆሮ. 15፥58:: ምርጫ ምእመናን በጸሎት እንዲጋደሉ ትልቅ ምክንያት ነው::

ሠ) ካላመነ ሰው ጋር ስንገናኝ፥ ይህ ሰው እንደ እኛ በእግዚአብሔር መልክ መፈጠሩን ብቻ ማወቅ ሳይሆን፥ ምናልባት ለድኅነት በእግዚአብሔር የተመረጠ ሊሆን ስለሚችል፥ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለእርሱ የምናቀርብበትን መንገድ በትሕትና መፈለግ ይገባናል::

5. ምርጫው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው

የምርጫ ትምህርትን ከአንዳንድ ጥቅሶች ጋር ማዛመድ እንደማይቻል ይነገራል፤ ስለዚህም በተለይ ሁለት ጥቅሶች ይጠቀሳሉ:-

ሀ) «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው»፤ 1ጢሞ. 2፥3-4:: ከዚህ ጥቅስ ሦስት ነገሮችን መገንዘብ አለብን:- 1ኛ፥ የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ፈቃድና የተገለጠ ፈቃድ አሉና አንዳንድ መምህራን ይህ ጥቅስ የተገለጠውን ፈቃድ እንጂ ምሥጢራዊውን ፈቃድ አያመለክትም ይላሉ (21):: 2ኛ፥ ሰው ወደ ነፍስ ድኅነት የሚደርሰው እውነትን በማወቅ ነውና እዚህ ላይ «ሊድኑ» የሚለው ቃል አስቀድሞ በመጻፉ ከልዩ ልዩ አደጋ፥ ችግርና ሁኔታ የሚታደገውን ምድራዊውን ድኅነት (ትድግና) ያመለክታል የሚሉ አሉ:: ይህም አተረጓጐም ከአንቀጹ አሳብ ጋር ይስማማል፤ ምክንያቱም ጸሎት የቀረበው ጸጥታን ማስከበር ለሚገባቸው ለምድራውያን ባለ ሥልጣናት ነው (ቍ. 1-2 ይመ.):: እግዚአብሔር በምድራዊም በመንፈሳዊም መንገዶች የሚያድን መሆኑ በግልጥ ይታወቃል፤ 1ጢሞ. 4፥10:: 3ኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ «ሁሉ» ሲል፥ አንድ ሰው ስንኳ ሳይቀር ሰዎችን በሙሉ በየማዕርጉ ወይም በየወገኑ ሊያመለክት ይችላል፤ ይህም ከአንቀጹ ጋር ይስማማል (ቍ. 1-2:7፤ «ሁሉ» በመቅመቃ. ይመልከቱ)::

ለ) «... ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል»፤ 2ጴጥ. 3፥9:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ምርጫ ያስተማረው ትምህርት ግልጥ በመሆኑ (1ጴጥ. 1፥1-2፤ 2፥9፤ 2ጴጥ. 1፥10)፥ ምርጫ ከዚህ ጥቅስ አሳብ ጋር የሚጋጭ ስለ መሆኑ ምንም ፍንጭ አይገኝም:: ሐዋርያው ጴጥሮስ በእነዚህ መልእክታት መመረጣቸውን ለሚያውቁ ምእመናን ይጽፋልና በተለይ በዚህ አንቀጽ (3፥8-10) እግዚአብሔር የሚታገሥ፥ ሰዎችም ወደ ንስሓ እንዲደርሱ የሚፈልግ በመሆኑ ላይ ያተኵራል፤ ስለዚህ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ሌሎች ሰዎች ወደ ንስሓና ወደ ድኅነት ደርሰው ከተመረጡት ጋር አንድ ሆነው እንደሚቈጠሩ የሚጽፍላቸው ምእመናን ተስፋ ማድረግ ይገባቸዋል (22)::

እንግዲህ አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ጥቅሶች የምርጫን መሠረታዊ ትምህርት የሚቃረን አሳብ ያላቸው ቢመስላቸውም፥ በአተረጓጐም ምክንያት ሌሎች ለዚህ ተቃውሞ በቂ ምክንያት የሌለ መሆኑን እንደሚያስቡ መረዳት ይኖርባቸዋል::

ስለ ምርጫ ማናቸውም ዐይነት ተቃውሞ ሲነሣ፥ «ነገር ግን፥ አንተ ሰው ሆይ፥ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ?» (ሮም 9፥20) የሚለውን ማስጠንቀቂያ መስማት ይገባናል፤ አለበለዚያ ማንነታችንን በፈጣሪያችን ፊት መርሳት እንችላለን::

## መ) ምርጫ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ምሥጢራዊ ተመክሮ

ምእመናን ብቻ የምርጫን ትምህርት በትክክል ሊያስተውሉትና ሊጠቀሙበት ይችላሉ:: ይህ ትምህርት ለእግዚአብሔር ሰዎች በአስደሳች፥ በጣፋጭና ሊነገር በማይቻል የማጽናናት ቃል የተሞላ ነው:: ምርጫ አማኙ በሚደሰትበት በዘለዓለማዊ ድኅነቱ እምነትን ያጸናል፤ ያረጋግጣልም፤ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅርም የጋለ እንዲሆን ያደርጋል:: በሌላ አንጻር ግን ይህ ትምህርት የማያምኑትን ወደ ተስፋ ቢስነትና ወደሚያስነውር አኗኗር እንዲገቡ የሚያደርግ አደገኛ ትምህርት ነው (23):: ከዚህ የተነሣ የማያምኑ ሰዎች ካሉ፥ በዚህ ትምህርት ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ አይደለም::

አንዳንድ ሰዎች ለዚህ ትምህርት ይህን ያህል ትኩረት ለምን ይሰጣል? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ (24):: መልሳችን እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል:- ትምህርቱ፥ ሀ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ፥ ለ) ለድኅነት መነሻ በመሆኑ፥ ሐ) ለምእመናን እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ፥ መ) ከትዕቢት፥ ከማናቸውም የወሮታ ወይም የትሩፋት ትምህርት ስለሚጠብቅ፥ ሠ) የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚመለከቱትንና ሌሎችን ተመሳሳይ ትምህርቶች ስለሚያብራራ፥ ረ) ግቡ የእግዚአብሔር ክብር ስለሆነ ነው::

ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ» ብሎ ወንድሞቹን አዘዘ፤ 2ጴጥ. 1፥10:: ሰው በመጀመሪያ ሲያምን እግዚአብሔር እንደጠራው ያውቃል፤ ትንሽ ቈይቶ ለምን እንደተጠራ ሲጠይቅ፥ በአጸፋው እግዚአብሔር እንደመረጠው ሊያስተውል ይችላል:: ስለ ምርጫው ሲያሰላስል ሳለ በተለይ ስለ ሦስት ነገሮች ሊያስብ ይችላል:-

### 1. ምርጫ ለአማኙ ታላቅ መጽናኛ ነው

አማኙ እግዚአብሔር በሕይወቱ ሥራውን በመጀመሩ የተመረጠ መሆኑን ያውቃል፤ 1ተሰ. 1፥4:: በሕይወቱ ችግር ሲከሠት፥ «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚለውን የተስፋ ቃል ልብ ያደርጋል፤ ሮም 8፥28:: ከዚያም ቀጥሎ እግዚአብሔር «መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንደሚፈጽመው» በመረዳቱ ድኅነቱ እንደማይጠፋበት ታላቅ መጽናኛ አለው፤ ፊል. 1፥6:: ምርጫውም አይለወጥም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ያከብራቸዋል፤ ምርጫው ከዘለዓለም ነውና በክርስቶስ ነው፤ ሮም 8፥29፤ ኤፌ. 1፥4::

### 2. ምርጫ ታላቅ የምስጋና ምክንያት ነው

አማኙ በአንድ በኩል ድኅነቱ ከራሱ ደግነት የተነሣ የተገኘ አለመሆኑን ሲያውቅ፥ በራስ መመካት ወይም ስለ እምነቱ መመስገን ሞኝነት መሆኑን ያስተውላል፤ 2ጢሞ. 1፥9:: በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሰዎችን ስለመረጠ እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: በዚህ መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ተሰሎንቄ ምእመናን እንደሚከተለው ምስጋና ያቀርባል:- «... እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሁላችሁ ምክንያት እናመሰግናለን፤ በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ ዐውቀናልና» (1ተሰ. 1፥2-4)፤ «... ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፤ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና»፤ 2ተሰ. 2፥13::

የእግዚአብሔር ዕቅድ ዋና ግብ እንዲከበር ነውና ሐዋርያው ለኤፌሶን ምእመናን ሲጽፍ፥ አብ ምእመናንን በክርስቶስ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ስለባረካቸው «ይባረክ» ብሎ ተናገረ:: ደግሞም ከምርጫውና ከውሳኔው የተነሣ (1፥4-5) በውድ ልጁ እንዲያው የሰጣቸው የጸጋው ክብር እንዲመሰገን (1፥6) እና ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ በመታተማቸውና ይህም የርስታቸው መያዣ በመሆኑ ለክብሩ ምስጋና እንዲሆን በመመኘት ገለጠ፤ 1፥13-14::

3. ምርጫ ሃይማኖታዊ አኗኗርን የሚያጸና ታላቅ መሣሪያ ነው

እግዚአብሔር ምእመናንን በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌላቸው እንዲሆኑ በክርስቶስ መረጣቸው፤ ኤፌ. 1፥4:: ምርጫው ከእግዚአብሔር በመሆኑ የሚኰሩበት የላቸውምና ትሑታን ይሆናሉ:: ስለመረጣቸው እግዚአብሔርን ይወዳሉ፤ ሌሎች ምርጦችንም ያፈቅራሉ:: ከመመረጣቸው የተነሣ ደስተኞች ይሆናሉና በአካሄዳቸው እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይመኛሉ:: ስለሚመጣው ሁሉ ተስፋና ሰላም አላቸው:: ስለ ምርጦች በክርስቶስ ያለውን መዳን ከዘለዓለም ክብር ጋር እንዲያገኙ መከራን ሁሉ ይቀበላሉ፤ 2ጢሞ. 2፥10:: እስከ መጨረሻ ይጸናሉና የተመረጡት እነማን እንደሚሆኑ ባያውቁም፥ ከምስክርነታቸው የተነሣ ሰዎች እንደሚያምኑ ያውቃሉ፤ በጸሎትም ይተጋሉ::

ምእመናን በሃይማኖታዊ አኗኗር በሚያሳዩት ትጋት መጠን ስለ መመረጣቸው ርግጠኞች ይሆናሉ፤ ይህም የሚሆነው ለእምነታቸው በጎነትን፥ ዕውቀትን፥ ራስን መግዛትን፥ መጽናትን፥ እግዚአብሔርን መምሰልን፥ ወንድሞችን መውደድንና ፍቅርን በመጨመር ነው፤ እነዚህን ሲያደርጉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣቸዋል፤ 2ጴጥ. 1፥5-11::

# ማስታወሻ

(1) ም. 29፥ በተለይም ም. 29ለ ይመ.

(2) ም. 29መ ይመ.

(3) ም. 47ለ2 ይመ.

(4) P.G.R. ገጽ 61-67 ይመ.

(5) ይህ ትምህርት በእንግሊዝኛ Reprobation ይባላል፤ ያልተመረጠ ሰው Reprobate ነው:: Grudem ገጽ 684-687 ይመ.

(6) ስለ ጋርዮሽ ጸጋ ም. 80 ይመ.

(7) ይህ አስተሳሰብ በእንግሊዝኛ Double Predestination ዕጥፍ አስቀድሞ መወሰን ይባላል::

(8) Grudem ገጽ 677፥ Berkhof ገጽ 111 ይመ.

(9) የእግዚአብሔር ዕውቀት እንዴት እንደሆነ በም. 24ለ ለማብራራት ሞክረናል:: በተጨማሪም «የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር» (አዕማድ መጻሕፍት ቍ. 24) ገጽ 38-41 ይመ.

(10) ቀለል ያለው አማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕም በተለመደው «አስቀድሞ ዐወቃቸው» ፈንታ በ«አስቀድሞ መረጣቸው» ሮም 8፥29ን እና 1ኛ ጴጥሮስ 1፥1-2ን ይተረጕማል::

(11) ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ በKJV Full Life Study Bible The New Testament 1990 Zondervan ገጽ 428 ይብራራል:: ደግሞም «የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር» ገጽ 36-37 ይመ.

(12) Grudem ገጽ 678::

(13) Berkhof ገጽ 109-110::

(14) ም. 46ሠ ይመ.

(15) በተሐድሶ ትምህርት መሠረት ምርጫ ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው ባለመሆኑ በእንግሊዝኛ Unconditional Election ተብሏል::

(16) እንደዚህ የሚያስተምሩት በእንግሊዝኛ Supralapsarians ይባላሉ፤ የድኅነት ቅደም ተከተላቸው ምርጫ፥ ፍጥረት፥ ውድቀት፥ ቤዛነት፥ ጥሪ፥ ክብር የሚል ነው::

(17) እንደዚህ የሚያምኑት በእንግሊዝኛ Infralapsarians ይባላሉ፤ የድኅነት ቅደም ተከተላቸው ፍጥረት፥ ውድቀት፥ ምርጫ፥ ቤዛነት፥ ጥሪ፥ ክብር የሚል ነው:: የAmyraldus ተከታዮች ቅደም ተከተል ደግሞ ፍጥረት፥ ውድቀት፥ ቤዛነት፥ ምርጫ፥ ክብር የሚል ነው::

(18) Grudem ገጽ 679-680 ማስታወሻ 12 ይመ.

(19) Berkhof ገጽ 118-125::

(20) ም. 34-37፥ በተለይ ም. 36ሐ የነጻነት ትርጕም ይመ.

(21) ም. 24ሸ፥ በተለይ ክፍል 3 ይመ.

(22) ም. 24 ገጽ 202-206 ደግሞ ይህን ጥቅስ ያመለክታል::

(23) ከዚህ በላይ የተጻፈው ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጾች ቍጥር 17 በዐጭሩ የተወሰደ አሳብ ነው::

(24) ስለ ምርጫ ትምህርት በBerkhof ከገጽ 109-125፥ በGrudem ደግሞ ከገጽ 669-687 በጥሩ አኳኋን ተብራርቷል::

# ምዕራፍ 86 - የግብረ መንፈስ ቅዱስ ቅደም ተከተል

እያንዳንዱ ክርስቲያን የራሱ መንፈሳዊ ተመክሮ አለው። አንዳንዶች የሌላው መንፈሳዊ ተመክሮ እንደ ራሳቸው ካልሆነ፥ የዚያ ተመክሮ ባለቤት እውነተኛ ምእመን አይመስላቸውም። ብዙዎቹ ግን በመንፈሳዊ ዕውቀት ሲያድጉ፥ ዋናው ነገር እግዚአብሔር ያደረገው እንጂ የራሳቸው ተመክሮ እንዳይደለ ያስተውላሉ። ትንሽ ቈይተውም ተመክሮአቸው እጅግ የተለያየ ቢመስልም እንኳ እግዚአብሔር ባደረገላቸው የሚመሠረቱ በመሆናቸው፥ ባጋጠማቸው ሁሉ የተወሰኑ ሐቆችን መመልከት ይችላሉ።

ሌሎች ሰዎች የመንፈስ ቅዱስንና የድኅነትን ሥራ ለመረዳት በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዐት ይወሰናሉ። ባላቸው አስተሳሰብ መሠረት ሰው ክርስቲያን የሚሆነው በጥምቀት ነውና የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው የሚሰጠው በጥምቀቱና በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት በኩል ነው። ይህን ትምህርት ከሚያስተምሩት አንዳንዶች ሰው በሕፃንነቱ ካልተጠመቀ፥ ለጥምቀት ከመብቃቱ በፊት ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ሥራ በሕይወቱ ሊከናወን ያስፈልጋል ይላሉ (1)። ሆኖም በመጀመሪያ አመለካከት ይህ ሁሉ የድኅነትን ቅደም ተከተል የሚያመለክት አይመስለንም። የተወሰኑት ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ሳይሆን በሰው አጸፋ በተለይም በእምነት ላይ ትኩረት ያደርጋሉና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ቅደም ተከተል በሰፊው አያስተምሩም (2)።

የአጠቃላይ ነገረ መለኮት ትምህርት ሥራ በአመክንዮታዊና ሰው በቀላሉ በሚያስታውስበት መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ሁሉ በቅደም ተከተል ማቅረብ ነው። «የድኅነት ጸጋ አሠራር» በሚለው ርእስ (ም. 83ሐ) መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ድኅነት የሚጠቀምባቸውን ቃላትና ሐረጎች ሁሉ ለመዘርዘር ሞክርን። በቃላቱና በሐረጎቹ ላይ ተመሥርተን አንድን ዐይነት ቅደም ተከተል ከማዘጋጀታችን በፊት በአንዳንድ ነገሮች ላይ ማተኮር ይገባናል።

1. ድኅነት በክርስቶስ ነው። ይህ የምዕራፍ 84 ትምህርት ነው። እንግዲህ ማናቸውም የድኅነት አሳብ ከክርስቶስ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ መርሳት አይገባም፤ አለበለዚያ ወደ ስሕተት ቶሎ መግባት ሊያጋጥም ይችላል።

2. ድኅነት ከእግዚአብሔር ነው። ይህ ደግሞ የምዕራፍ 85 ትምህርት ነው። ምርጫ ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዕቅድ የተወሰነ ነውና የድኅነት ቅደም ተከተል በምድራዊ ሕይወትና በሰው ተመክሮ ውስጥ ይፈጸማል (3)።

3. ሰው መንፈሳዊ ተመክሮውን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ማጽናት አለበት እንጂ ተመክሮውን መሠረት አድርጎ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጐም አይገባውም፤ አለበለዚያ ሁሉም ይዘበራረቅበታል።

4. አብ ድኅነትን ሲያቅድ፥ ወልድ ሲያደራጀው፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ ፍጻሜ ያደርሰዋል።

## ሀ) የድኅነት ቅደም ተከተል መሠረታዊ ጥቅስ

«ንስሐ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ»፤ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ»፤ «ንስሐ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» የሚሉትና የመሳሰሉት ጥቅሶች በድኅነት ውስጥ የሁነት

ቅደም ተከተል እንዳለ ያሳያሉ፤ ማር. 1፥15፤ ሐ.ሥ. 2፥38፤ 16፥31:: ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ያለውን የምእመናንን ሁኔታ ሲያብራራ፥ «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና፤ አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው» በማለቱ የድኅነትን ቅደም ተከተል በዐጭሩ አሳየ፤ ሮም 8፥29-30:: በዚህ አንቀጽ አንዳንድ ነጥቦችን ልብ እናድርግ (4):-

1. ዐወቃቸው፥ ወሰናቸው፥ ጠራቸው፥ አጸደቃቸው፥ አከበራቸው የሚሉት ግሶች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተከታትለው ተቀምጠዋል:: ሰው መክበሩ ወደፊት የሚፈጸም ቢሆንም፥ ብዙ ጊዜ በትንቢት መልክ እንደሚደረገው በኃላፊ የግስ አንቀጽ ተገልጧል፤ በእግዚአብሔር አሳብ የተፈጸመ ጉዳይ ነውና::

2. እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸው ሰዎችና ያከበራቸው ሰዎች አንድ ናቸው፤ በሂደት ላይ አንድም ሰው አልተጨመረም፤ የቀረም የለም::

3. የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅና መወሰን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ተመሠረቱ፤ ስለዚህ በዚህ ዝርዝር በሰው ተመክሮ ውስጥ የሚታዩት መጠራት፥ መጽደቅና መክበር ናቸው::

4. መክበር የመጨረሻው የድኅነት ደረጃ በመሆኑ በዓለም ታሪክ የድኅነት ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ርምጃ መጥራት ሊሆን ይችላል፤ በጥቅሱ ውስጥ ይህ ቃል የእግዚአብሔርን ውሳኔ አስከትሎ ተገልጧልና::

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሦስት ርምጃዎች መሠረት አድርገን ሌሎችን ከእነርሱ ጋር ማዛመድ እንችላለን::

## ለ) የድኅነት ቅደም ተከተል ውቅር

መጠራት፥ መጽደቅና መክበር ቋሚ የድኅነት ርምጃዎች ናቸው፤ እንግዲህ በዚህ ላይ ምን ምን ሊጨመር ይችላል?

### 1. ንስሐ መግባትና ማመን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ» ብሎ አዘዘ፤ ሐዋርያው ጳውሎስም በኤፌሶን ስለነበረው አገልግሎቱ ሲናገር፥ «... ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሓንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ...» ብሎ በምን አኳኋን የክርስቶስን ትእዛዝ እንደፈጸመ ገለጠ፤ ማር. 1፥15፤ ሐ.ሥ. 20፥20-21::

እንግዲህ ንስሐ መግባትና እምነት የተያያዙ ናቸው፤ ሁለቱ በአንድነት ሲጠቀሱም ንስሐ መግባት ቀዳሚ ርምጃ መሆኑን እናያለን::

ንስሐ መግባት ለእግዚአብሔር ጥሪ የሰው ትክክለኛ አጸፋ በመሆኑ በውቅሩ ከመጠራት በኋላ ይገኛል:: ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቈጥራለንና»፤ «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን...»፤ «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ... በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» በማለት በጻፋቸው ጥቅሶች (ሮም 3፥28፤ 5፥1፤ ገላ. 2፥16) ጽድቅ ከእምነት እንደሚመነጭ ስለሚታይና

እምነትም በድኅነት የሂደት ቅደም ተከተል ከመጽደቅ በፊት ስለሚገኝ፥ ንስሐ መግባትንና እምነትን:-

መጠራት፥ ንስሐ መግባት፥ ማመን፥ መጽደቅ፥ መክበር በሚል የቅደም ተከተል ውቅር ልንገልጠው እንችላለን::

2. ዳግመኛ መወለድ

ሰው ዳግመኛ ተወልዶ ያምናል ወይስ አምኖ ዳግመኛ ይወለዳል? እነዚህ ሁለት አሳቦች በምእመናን መካከል አሉና መልስ ከመስጠታችን በፊት፥ ዳግመኛ መወለድ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕይወት የሰጠበት መንገድ ምሳሌ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል፤ ኤፌ. 2፥5:: ኒቆዲሞስ፥ «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማሕፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?» ብሎ በመጠየቁ (ዮሐ. 3፥4) የክርስቶስን ቃል እንደ ምሳሌ ሳይሆን፥ እንደ ቋሚ ቃል ሊያስተውለው ባለመቻሉ የክርስቶስን ማስጠንቀቂያ አልተረዳም:: ዳግመኛ መወለድ ታላቅ ምሳሌ ቢሆንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚጠቀምበት ልንጠቀምበት ይገባል:: ዳግም ልደትን በሚከተለው ምዕራፍ በሰፊው እንመለከተዋለን፤ አሁን ግን ዳግመኛ መወለድ በውቅራችን ያለውን ስፍራ ለማወቅ አንዳንድ ጥቅሶችን እናያለን::

«ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም (እነዚህም) ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም»፤ ዮሐ. 1፥12-13:: ከዚህ ጥቅስ ሦስት ነጥቦችን ማተት ይገባናል:-

ሀ) ሰዎች ከእግዚአብሔር ዳግመኛ ይወለዳሉ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» ብሎ ሰው ከመንፈስ (ቅዱስ) ዳግመኛ መወለዱን በግልጥ አስተማረ፤ ዮሐ. 3፥5-6:: እንደዚሁም ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ ስድስት ጊዜ ዳግመኛ ስለ መወለድ ሲያስተምር ከእግዚአብሔር መሆኑን በግልጥ ተናገረ፤ 1ዮሐ. 2፥29፤ 3፥9፤ 4፥7፤ 5፥1፤ 5፥4፤ 5፥18::

ለ) «እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ...» የሚለው አረፍተ ነገር እነዚህ ሰዎች ዳግመኛ የተወለዱት ካመኑ ባኋላ፥ ባመኑ ጊዜ ወይም ከማመናቸው በፊት ነው ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: ይህ ጥቅስ ሰዎቹ ስላመኑ ዳግመኛ ተወለዱ ብሎ አይናገርም፤ በዚህ ፈንታ፥ «ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» ስለሚል፥ ዳግመኛ መወለድ ከሰው ባለመሆኑ ላይ የሚያተኵር ይመስላል:: ዳግመኛ ስለ መወለድ የሚናገሩ ጥቅሶች ሁሉ ከእግዚአብሔር መሆኑን ሲገልጡ፥ የእግዚአብሔር ሥራ ለሰው እምነት መልስ ስለ መሆኑ ግን አንድም ፍንጭ አይሰጡም:: በዚህም ፈንታ፥ «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» ከሚለው፥ ዓለምን የሚያሸንፈው እምነት፥ ሰው ዳግመኛ ከተወለደ በኋላ የሚያገኘው መሆኑ ግልጥ ነው፤ 1ዮሐ. 5፥4:: ክርስቶስም፥ «ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» በማለቱ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁኔታ ማስተዋል ባለመቻሉ ላይ አተኰረ፤ ዮሐ. 3፥3:: በዚህ ምዕራፍ ስለ ዳግመኛ መወለድ ከተገለጠ በኋላ ግን እምነት የተሰቀለውን ክርስቶስን ይመለከታልና በእርሱ የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝ መሆኑን ያስተምራል፤ ዮሐ. 3፥14-16:: እንግዲህ ሰው ከማመኑ በፊት ዳግመኛ እንዲወለድ አስፈላጊ መሆኑ ይታያል:: (5)

እውነት ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» ብሏል፤ ያዕቆብም፥ «(እግዚአብሔር)... በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» በማለቱ ለዳግም ልደት የእግዚአብሔር ቃል መሣሪያ እንደሆነ እንግራለን፤ 1ጴጥ. 1፥23፤ ያዕ. 1፥18:: የልደት ግብ ሰው ወደ ሕይወት እንዲገባ ማድረግ ነው፤ የዳግመኛ መወለድ ግብም እንደዚሁ ሰው እንዲያምን ማድረግ ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ አመለካከት ዳግመኛ መወለድና እምነት ጐን ለጐን የሚሄዱ ናቸው፤ ወይም መተንፈስ የልደት ፍጻሜ እንደ መሆኑ መጠን፥ እምነትም የዳግመኛ መወለድ ፍጻሜ ነው ማለት ይቻል ይሆናል:: ሆኖም ሐዋርያት በምሳሌው የተጠቀሙት ይህን ለማስተማር አስበው እንደሆነ ርግጠኞች መሆን አንችልም::

ሐ) ዮሐንስ 1፥12-13ንም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶችን ከቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር ማዛመድ ይገባናል:: ለምሳሌ ክርስቶስ «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም» በማለቱ፥ ንስሐ ከመግባትና ከማመን በፊት የአብ «የመሳብ ሁኔታ» እንዳለ ያሳያል፤ ዮሐ. 6፥44:: ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ... እግዚአብሔር... በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን» (ኤፌ. 2፥1-5) በማለቱ፥ በሰው ሕይወት የድኅነትን ሥራ የሚጀምረው እግዚአብሔር መሆኑ ይታያል:: ስለዚህ ዳግመኛ መወለድን ከንስሓና ከእምነት በፊት በውቅራችን ላይ ማሳየት አመክንዮታዊ ነው::

በሌላ በኩል ግን ዳግመኛ መወለድን ከመጠራት በኋላ ማስቀመጥ አመክንዮታዊ ነው፤ ምክንያቱም ብዙዎች ቢጠሩም እንኳ በክርስቶስ አምነው በአዲስ ሕይወት መራመድ የሚችሉት ጥቂቶች ናቸውና ዳግመኛ መወለድ የመጠራት አንድ ክፍል እንደሆነ ማሰብ ይቻላል:: እንግዲህ እስካሁን ድረስ በውቅራችን ላይ የሚገኙት:- መጠራት፥ ዳግመኛ መወለድ፥ ንስሐ መግባት፥ ማመን፥ መጽደቅና መክበር ናቸው (6)::

### 3. መቀደስ

በአዲስ ኪዳን ሰው ካመነ በኋላ ብዙ ጊዜ እየተቀደሰና እየተለወጠ እንደሚሄድ ይታሰባል:: ሆኖም ምእመናን በክርስቶስ የተቀደሱ ቅዱሳን ናቸው፤ ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር በሚቈጥርላቸው መሠረት ነው፤ 1ቆሮ. 1፥2፤ 2ቆሮ. 1፥1፤ ኤፌ. 1፥1:: ሐዋርያው፥ «የኀጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ...» በማለቱ (ሐ.ሥ. 26፥17-18)፥ ምእመናን የኀጢአትን ስርየትና ጽድቅን በማግኘታቸው የተቀደሱ መሆናቸው ይታያል፤ ስለዚህ መቀደስን (ደረጃው) በውቅሩ ላይ ከመጽደቅ በኋላ እናስቀምጠዋለን:: መቀደስ እንደ አማኙ አኗኗር እስከ ሞት ድረስ የሚቀጥል ሲሆን፥ በውቅሩ ላይ የሚኖረው አቀማመጥ ከመክበር በፊት ይሆናል:: እንግዲህ ውቅራችን እስካሁን ድረስ የሚከተለውን መልክ መያዝ ችሏል:-

መጠራት፥ ዳግመኛ መወለድ፥ ንስሐ መግባት፥ ማመን፥ መጽደቅ፥ መቀደስ (ደረጃው)፥ መቀደስ (አኗኗሩ)፥ መክበር::

### 4. ልጅነትን ማግኘት፥ መንፈስ ቅዱስን መቀበልና መጽናት

ሰው ሲያምን ወዲያውኑ ይጸድቃል፤ ይቀደሳል፤ ወዲያውኑም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖአልና (ዮሐ. 1፥12፤ ሮም 8፥16-17) የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይቀበላል፤ ሐ.ሥ. 2፥38፤ ሮም 8፥9፤ ገላ. 3፥2:: ክርስቶስ፥ «እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል» (ማር. 13፥13) ስላለ፥ መጽናትን

ከመክበር በፊት ማስቀመጥ አመክንዮታዊ ነው:: እንግዲህ ውቅራችንን እንደሚከተለው ማሳየት እንችላለን:-

*መጠራት፥ ዳግመኛ መወለድ፥ ንስሐ መግባት፥ ማመን፥ መጽደቅ፥ መቀደስ (ደረጃው)፥ ልጅነትን ማግኘት፥ መንፈስ ቅዱስን መቀበል፥ መቀደስ (አኗኗሩ)፥ መጽናት፥ መክበር* (7)::

## ሐ) የድነት ቅደም ተከተል አምስት ክፍሎች

ድነትን ስናጠና የቅደም ተከተል ውቅሩን ከወሰንን በኋላ እያንዳንዱን ነጥብ መመርመር እንችላለን:: ሆኖም ዐሥራ አንድ ነጥቦችን ብቻ በአምስት ክፍለን በሚከተለው አኳኋን አስቀምጠን ብንመለከታቸው፥ የድነትን ዕቅድ በይበልጥ ማስተዋል እንችላለን:: ይህን ስናደርግ ደግሞ ሁሉም ነገር የሚፈጸመው ሰው በክርስቶስ እንዲሆን ወይም በክርስቶስ በመሆኑ እንደሆነ ልንዘነጋ አይገባም::

1. ሰው እንዲያምን እግዚአብሔር የሚያከናውነው ሥራ

በዚህ ክፍል ሥራው የእግዚአብሔር ነውና ሰውን ወደ ድነት ያደርሰዋል::

ሀ) ጥሪ፤ በዚህ አመለካከት ጥሪው ውጤታማ ጥሪ ነው፤ ውጤታማ የሚያደርገው ዳግም ልደት ነው::

ለ) ዳግም ልደት፤ ይህም ልቡናን መክፈትንና ፈቃድን መለወጥን ያጠቃልላል::

2. ሰው በእግዚአብሔር ኀይል የሚሰጠው አጸፋ

ሐ) ንስሐ፤ ንስሐ በእግዚአብሔር ሲሰጥ ሰው ራሱ ንስሐ ይገባል::

መ) እምነት፤ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን ሰው ራሱ ያምናል::

3. ሰው ካመነ በኋላ የሚያገኛቸው በረከቶች

ሰው በክርስቶስ ሲያምን፥ እግዚአብሔር እነዚህን አራት በረከቶች ወዲያውኑ ይሰጠዋል:: አማኙ ወዲያውኑ ቢቀበላቸውም፥ በሕይወቱ ሁሉ እነርሱን እየተረዳ፥ እየተደነቀባቸው ይኖራል::

ሠ) ጽድቅ፤ በክርስቶስ ሞት የአማኙ ኀጢአት ተደምስሷልና የክርስቶስ ጽድቅ በእምነቱ መሠረት ይቈጠርለታል::

ረ) የደረጃ ቅድስና፤ በእምነት በክርስቶስ በመሆኑ አማኙ ቅዱስ ነው::

ሰ) ልጅነት፤ በእምነቱ መሠረት አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል::

ሸ) መንፈስ ቅዱስ፤ አማኙ በእምነቱ መሠረት መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል::

4. ሰው ካመነ በኋላ በእግዚአብሔር ኀይል የሚራመድበት አዲስ አኗኗር

ሰው በአዲስ አኗኗር በመራመድ ሲደሰት እየተለወጠ ይሄዳልና አካሄዱ የተሻለ ይሆናል:: ሆኖም ያለ ክርስቶስ ምንም ማድረግ አይችልምና እግዚአብሔር ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በአማኙ ዘንድ ይሠራል::

ቀ) የአኗኗር ቅድስና፤ ይህም የጠባይ ለውጥንና መልካም ሥራን ያጠቃልላል::

ተ) ጽናት፤ የዓለም ተቃውሞ፥ የሥጋ ምኞትና የሰይጣን ፈተና ከባድ ቢሆኑም፥ አማኙ በእግዚአብሔር ኀይል እስከ መጨረሻ ይጸናል::

5. የድነት የመጨረሻ ደረጃ

ክርስቶስ ወደ ዓለም ተመልሶ ሲመጣ እግዚአብሔር ምእመናንን ከሙታን የስነሣቸዋልና (ወይም ምእመናን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሕያዋን ከሆኑ በቅጽበተ ዐይን ይለውጣቸዋል) ወደ ዘለዓለማዊ ሁኔታቸው ያስገባቸዋል።

ቸ) ክብር፤ ምእመናን ክርስቶስን ሲያዩ በትስብእቱ በኩል ሙሉ በሙሉ በክሉራቸውን (የእርሱን) መልክ ይመስላሉ፤ ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋርም ለዘለዓለም በክብር ይኖራሉ፤ ሮም 8፥29-30።

## ማስታወሻ

(1) ለምሳሌ Berkhof ገጽ 421 ይመ.

(2) Berkhof ገጽ 420 ይመ.

(3) የድነት ቅደም ተከተል በላቲን Ordo Salutis በእንግሊዝኛ ደግሞ Order of Salvation ተብሎ ይጠራል።

(4) በዚህ ምዕራፍ የተጻፈው በአብዛኛው በRR ገጽ 704-711 የተመሠረተ ነው።

(5) ግሩደም በአንዳንድ የሃይማኖት መግለጫዎች «ዳግም መወለድ» የሚለው ቃል በቀላሉ በተለወጠ ሕይወት ውስጥ የሚታይ የዳግም ልደት ውጫዊ ማረጋገጫ፥ ማለትም ከሚያድን እምነት በኋላ በርግጥ የሚመጣ ማረጋገጫ ሆኖ እንደተገለጠ ተመልክቷል። በዚህ መሠረት «እንደገና መወለድ» ከአዲሱ ሕይወት መሰጠት የሚመነጭ ጠቅላላ የሕይወት ለውጥ ሆኖ ይታያል እንጂ፥ አዲስ ሕይወትን ከመስጠት ጋር ይያያዛል ተብሎ አይታሰብም። የ«ዳግም መወለድ»ን ትርጉም በዚህ መንገድ ማስተዋል ከተቻለ፥ ዳግም መወለድ ከሚያድን እምነት በኋላ መምጣቱ እውነት ይሆናል።

ይሁን እንጂ፥ ከእውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ የቃላት አጠቃቀም ጋር በእጅጉ የሚስማማውን ቋንቋ መጠቀም ካለብን፥ «ዳግም መወለድ»ን መንፈሳዊ ሕይወት ለእኛ በሚሰጥበት ቅጽበታዊ የመጀመሪያ የእግዚአብሔር ሥራ ላይ ብንወስነው የተሻለ ነው። ከዚህ በመነሣት በሕይወታችን የሚታዩትን የዳግም ልደት ውጤቶችን ብቻ እንጂ ዳግም ልደትን ራሱን የማናየው መሆናችንን በጕሉሕ መግለጽ እንችላለን፤ Grudem ገጽ 703-704።

(6) ዳግመኛ መወለድ ከሚያድን እምነት በፊት ይመጣል በምንልበት ጊዜ ግን አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ ተጠጋግተው እንደሚመጡ፥ በተመሳሳይ ጊዜም የሚከሠቱ እንደሚመስለን ማሰብ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ውጤታማ ጥሪን ሲያቀርብልን፥ ዳግመኛ እንድንወለድ ያደርጋል። እኛም ለቀረበልን ጥሪ በእምነትና በንስሓ ምላሽ እንሰጣለን። እንግዲህ ከእኛ እይታ አንጻር በሁለቱ መካከል የጊዜ ልዩነት እንዳለ መናገር አስቸጋሪ ነው፤ ይህም የሚሆነው፥ በተለይ ዳግመኛ መወለድ በዐይናችን ልናየውና በአእምሯችንም እንኳ ልንረዳው የማንችል መንፈሳዊ ሥራ ከመሆኑ የተነሣ ነው፤ Grudem ገጽ 702።

(7) RR በድነት ቅደም ተከተል ውቅር ላይ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ አያስቀምጥም፤ ሆኖም ቅደም ተከተሉ እኛ የጻፍነውን ቅደም ተከተል የሚመስል ነው።

Grudem የድነትን ቅደም ተከተል በገጽ 670 እንደሚከተለው ጽፎታል:-

1. ምርጫ (ሰዎች እንዲድኑ የእግዚአብሔር ምርጫ)
2. የወንጌል ጥሪ (የወንጌልን መልእክት ማወጅ)
3. አዲስ ሕይወትን ማግኘት (ዳግመኛ መወለድ)
4. መለወጥ (ንስሓና እምነት)
5. መጽደቅ (በሕግ ፊት ትክክለኛ አቋቋም)
6. ልጅነትን ማግኘት (ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ መጨመር)
7. ቅድስና (ትክክለኛ አኗኗር)
8. መጽናት (በክርስቲያንነት እስከ መጨረሻ መኖር)
9. ሞት (ከጌታ ጋር ለመኖር መሄድ)
10. ክብር (የትንሣኤን አካል መቀበል)

# ምዕራፍ 87 - የእግዚአብሔር ጥሪና የሰው ዳግም ልደት

## ሀ) የወንጌል ጥሪ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ብሎ ታላቁን ተልእኮ ለቤተ ክርስቲያን ሰጠ፤ ማር. 16፥15:: ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?» በማለት ጥያቄ በማቅረቡ፥ ሰዎች የወንጌልን ጥሪ የሚሰሙት በሰው አማካይነት መሆኑ ይታያል፤ ሮም 10፥14:: በተጨማሪም ሐዋርያው «በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና» ብሎ ለሰባኪው አገልግሎት ከፍተኛ ግምት ሰጥቶታል፤ 1ቆሮ. 1፥21::

ክርስቶስ ግን፥ «የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና» (ማቴ. 20፥16፤ 22፥14) በማለት፥ ወንጌል ምንም እንኳ ለሰዎች ሁሉ ቢሰበክም፥ የሚቀበሉት ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ አስጠንቅቆናል:: «የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ» በሚለውም ብዙ ሰዎች ቃላትን በሥጋዊ ጆሮ ቢሰሙም፥ በልባቸው «ጆሮ» ጥሪውን እንደማያደምጡ ገልጧል፤ ማቴ. 13፥9:43:: እንግዲህ በዚህ ዐይነት የውጭ ጥሪና የውስጥ ጥሪ አለ ማለት እንችላለን (1)::

የልድያ ታሪክ የውጭና የውስጥ ጥሪን አንድነትና ልዩነት በግልጥ ያስረዳል፤ እርሷ፥ «ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልቧን ከፈተላት» ሐ.ሥ. 16፥14:: እርሷ እንደ ሌሎች ትሰማ ነበር እንድታዳምጥ ማለት ውስጣዊ ጥሪ እንዲደርሳት ጌታ ልቧን ከፈተላት::

ሐዋርያትም ብዙ ጊዜ ስለ «ተጠሩ» ሰዎች ይናገራሉ:: እንደዚሁም ሲያደርጉ ወንጌልን ሰምተው የሚቀበሉትን ያመላክታሉ፤ ሮም 1፥6:7፤ 8፥28:30፤ 9፥24፤ 1ቆሮ. 1፥24፤ ይሁዳ 1፤ ራእ. 17፥14:: እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ጥሪ ውጤታማ የሚሆነው በሁሉ ላይ ሳይሆን በተወሰኑ ሰዎች ላይ ነው (2)::

### 1. ለሰዎች ሁሉ የወንጌል ጥሪ በውጭ ይሰጣል

ይህን ስናስብ የሚከተለውን መገንዘብ ይገባናል:-

ሀ) ለሰው ልቡና ይሰጣልና ሰው በአእምሮው በአመክንዮታዊ መንገድ ሊያስተውለው ይችላል፤ በተለይም:-

1) ጠሪው እግዚአብሔር ነው፤ እርሱም የታመነ (1ተሰ. 5፥24)፤ ቅዱስና ለሰው ፊት የማያደላ (1ጴጥ. 1፥15-17)፥ ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥና የሌለውን እንዳለ አድርጎ የሚጠራ (ሮም 4፥17) ነው:: በመጀመሪያ አመለካከት የሚጠራው እግዚአብሔር አብ ነው፤ ሰዎች የልጁን መልክ እንዲመስሉ (ሮም 8፥29)፥ ወደ ልጁ ኅብረት (1ቆሮ. 1፥9)፥ በክርስቶስ ጸጋ (ገላ. 1፥6) እና በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘለዓለም ክብር (1ጴጥ. 5፥10) ሰዎችን ይጠራልና:: እግዚአብሔር አብ ሁሉን ስለሚሠራ፥ ጥሪው ደግሞ ከወልድ ነው፤ ማቴ. 11፥28፤ ሉቃ. 5፥32፤ ዮሐ. 7፥37:: ክርስቶስ በበኩሉ ደግሞ ሰዎችን በመንፈስ

ቅዱስ (ማቴ. 10፥20፤ ዮሐ. 15፥26) እና ቃሉን በሚናገሩት አማካይነት ይጠራል፤ ሐ.ሥ. 5፥31-32።

2) በጥሪው እግዚአብሔር ሰዎችን «ከጨለማ ወደሚደነቅ» ብርሃን (1ጴጥ. 2፥9)፥ ወደ ልጁ ኅብረት (1ቆሮ. 1፥9)፥ ወደ መንግሥቱና ወደ ክብሩ (1ተሰ. 2፥11-12) ወደ አንድ አካልና ወደ ሰላም (ቆላ. 3፥15)፥ ወደ ዐርነት (ነጻነት፤ ገላ. 5፥13)፥ ወደ ተስፋና (ኤፌ. 1፥18፤ 4፥4) ወደ ቅድስና (1ተሰ. 4፥7)፥ የበጉ ሰርግ (ራእ. 19፥9)፥ የዘለዓለም ርስት (ዕብ. 9፥15) የዘለዓለም ሕይወትም ወደሚገኝበት ሁኔታ (1ጢሞ. 6፥12) ይጠራቸዋል።

3) ጥሪውን የሚቀበሉት የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው (ሮም 1፥6) እና በተጠሩበት መጠራታቸው እንደሚገባ እንዲመላለሱ (ኤፌ. 4፥1)፥ ለርኵሰት ሳይሆን ለቅድስና (1ተሰ. 4፥7)፥ መከራንም በትዕግሥት ለመቀበል (1ጴጥ. 2፥20-21፤ 3፥9) ተጠርተዋል።

4) የሚጠሩ በወንጌል ስብከት ይጠራሉ፤ 2ተሰ. 2፥14፤ ሐ.ሥ. 2፥39።

5) ጥሪው የሚደረገው በሰው ሥራ ምክንያት ሳይሆን፥ በጠሪው (ሮም 9፥11፤ ሐ.ሥ. 2፥39) በክርስቶስ ጸጋ መሠረት (ገላ. 1፥6) ነው።

ለ) የጥሪው መሠረታዊ መልእክት ወንጌል ነው፤ ግልጥ የሆነው ይህ መልእክት የታወቁ ሦስት ክፍሎች አሉት:-

1) የወንጌል ጥሪ የተመሠረተባቸውን ነጥቦች መግለጥ፤ ይኸውም ቢያንስ ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን (ሮም 3፥23)፤ የኀጢአት ውጤት ሞት መሆኑን (ሮም 6፥23)፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ኀጢአት በመስቀል ላይ መሸከሙን (1ጴጥ. 2፥24) እና እግዚአብሔር ልጁን ከሙታን ማንሣቱን (ሮም 10፥9)።

2) የወንጌልን ጥሪ ለሚሰማ ሰው ማቅረብ፤ ይህም በዐጭሩ ንስሓ ግባ፤ ወንጌልንም እመን (ማር. 1፥15፤ ሐ.ሥ. 20፥20-21) የሚለው ሲሆን፥ ጥሪው የቀረበለት ሰው ትምህርቱን ተረድቶ ማመን ብቻ ሳይሆን፥ እርሱ ራሱ ለእግዚአብሔር ኀጢአቱን በመናዘዝና በመተው፥ ለኀጢአቱ ይቅርታም ክርስቶስን ብቻ ተስፋ ማድረጉን በይፋ በመናገር የክርስቶስን ጥሪ መቀበል ይኖርበታል (ማቴ. 11፥28)፤ ይህንም በማድረጉ ክርስቶስ በሕይወቱ ሁሉ ጌታ መሆኑን ተገንዝቦ ያከብረዋል፤ ማቴ. 11፥29፤ ዮሐ. 1፥12፤ ራእ. 3፥20። ስለ ንስሓና ስለ እምነት ምንነት በይበልጥ በሚከተለው ምዕራፍ ማብራሪያ ይሰጣል። እዚህ ላይ ግን እያንዳንዱ ሰው ለወንጌል ጥሪ የግል መልስ መስጠት እንዳለበት በሚያስገነዝበው ጉዳይ ላይ እናተኵራለን።

3) የወንጌል ጥሪ የመቀበልን ውጤት ማብሠር፤ በበዓለ ኀምሳ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ በስብከቱ ንስሓ ለሚገቡና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለሚጠመቁ (ጥምቀት በክርስቶስ ማመናቸውን ይገልጣል) የኀጢአት ስርየትን (ይቅርታን) እና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንደሚቀበሉ ተናግሮ ታላቅ የወንጌል የተስፋ ቃልን ሰጣቸው፤ ሐ.ሥ. 2፥38። አንድ ሰው ክርስቶስን በማመን የዘለዓለምን ሕይወት የሚቀበል መሆኑም ከዚህ ጋር የተያያዘ አሳብ ነው፤ ዮሐ. 3፥16-18:36፤ 5፥24፤ 1ዮሐ. 5፥12።

እነዚህ ሦስት ክፍሎች የወንጌል ጥሪ መሠረታውያን ነጥቦች ናቸው፤ ሰው ግን ስለ ወንጌል ትምህርት የተሳሳተ አስተሳሰብ ስለሚኖረው፥ ወደ ክርስቶስ እንዳይደርስም ዕንቅፋት ሊሆንበት ስለሚችል፥ አንድ ርምጃ ከመውሰዱ በፊት

እውነተኛውን ትምህርት ማስተማር አስፈላጊ ነው፤ ለምሳሌ ዕብ. 11፥6ን ይመልከቱ::

ሐ) ጥሪው የሰውን ኀላፊነት ግልጥና ከባድ ያደርገዋል፤ ሰው ወንጌልን ቢቀበል ይድናል፤ ኀላፊነቱንም በአግባቡ ይወጣል:: ሰው ጥሪውን ባይቀበል ግን ኀላፊነቱ ከባድ ይሆናል:: ክርስቶስ፥ «እናንተ በመጻሕፍት የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም» ብሎ አይሁድን ወቀሣቸው፤ ዮሐ. 5፥39-40:: አይሁድ በሙሴ አመኑ፤ ነገር ግን ሙሴ ስለ ክርስቶስ ስለተናገረ፥ ክርስቶስን ባለመቀበላቸው በሙሴ በእውነት አላመኑምና ሙሴ የሚፈርድባቸው ሆነ፤ ዮሐ. 5፥46፤ 7፥19፤ 9፥28-30:: የአይሁድ፥ እንደዚሁም የወንጌልን ጥሪ የማይቀበሉ ሰዎች ሁሉ ኀጢአት የልብ እልከኛነታቸው ነውና «ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም አንዱ ቢነሣ አያምኑም» ተብሏል (ሉቃ. 16፥31)፤ አሁን ከሙታን አንድ ተነሥቷል፤ ብዙዎችም የክርስቶስን ትንሣኤ እንደሚያምኑ ይናገራሉ፤ በጥምቀታቸውም ማመናቸውን ይገልጣሉ፤ ሆኖም በክርስቶስ መንገድ ባለመራመዳቸው የወንጌልን ጥሪ እንዳልተቀበሉ ያሳያሉና ኀላፊነታቸው ከባድ ነው:: ክርስቶስም፥ «የጌታውን ፈቃድ ዐውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፤ ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም (ሊያስገርፍ የሚገባውን ያህል) ያደረገ ጥቂት ይገረፋል:: ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፤ ብዙ ዐደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል» በማለት ተናግሯል፤ ሉቃ. 12፥47-48:: የወንጌልንም ጥሪ በመስማቱ ሰው የተሻለ ወይም ከነበረው የባሰ ይሆናል፥ የባሰ ከሆነ ደግሞ የባሰ ፍርድ ይጠብቀዋል::

መ) ጥሪው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ይገልጣል፤ በተለይም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ርኅራኄ ያሳያል፤ ዮሐ. 3፥16፤ ሮም 5፥8:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኢየሩሳሌም፥ «... ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም» ብሎ በማዘኑና የከተማዪቱን ውድቀትና ሥቃይ ሲያስብ አይቷት በማልቀሱ፥ የከተማዪቱን ክፋትና ከሕዝቧ ብዙዎቹ የወንጌልን ጥሪ አለመቀበላቸውን ቢያውቅም፥ ፍቅርና ርኅራኄ የሞላበትን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገለጠ፤ ሉቃ. 13፥34፤ 19፥41-44::

እንደዚሁም የወንጌል ጥሪ የክርስቶስን ሞት ምክንያት በመግለጡ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ጽድቅ ከፍ ከፍ ያደርጋል፥ ሮም 3፥25-26፤ 1ቆሮ. 6፥11፤ ቲቶ 3፥5-7:: «ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» ተብሏልና ኀጢአተኛ ሰው ያለ ክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት ሊድን አይችልም ነበርና፤ ዕብ. 9፥22::

ሰዎች የወንጌልን ጥሪ ትምህርት በመጠኑ ማስተዋልና በመጠኑም ሊደሰቱበት፥ ክርስቲያናዊ መንገድንም ለጊዜው ሊከተሉ ይችላሉ፤ ሆኖም በመንፈሳዊ መንገድ አያስተውሉትም (1ቆሮ. 2፥14)፤ በልባቸው አይለወጡምና ችግር ሲያጋጥማቸው፥ አሳባቸው የተዘበራረቀ ስለሚሆን የክርስትናን አሳብ ሁሉ ሊክዱ ይችላሉ፤ ማር. 4፥16-17፤ ዕብ. 6፥4-6::

**2. ለተመረጡት የወንጌል ጥሪ በውስጥ ይሠራል**

የወንጌል ጥሪ ወደተመረጡት ልቡና በኀይል ይመጣል:: ለጊዜው ጥሪውን ሊቃወሙ ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ ግን አሳባቸውና ፈቃዳቸው ተለውጦ በደስታ ጥሪውን ይቀበላሉ (3):: የተመረጡት የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ በተለይ ሦስት ነገሮች በሕይወታቸው ይታያሉ፤ እነርሱም:-

ሀ) ወንጌልን ማስተዋል ይጀምራሉ፤ ይህ የሚሆነውም በአብርሆት ነው (4)። ሰዎች ያለ አብርሆት እንደ ዕዉራን ናቸውና ዐይናቸውን መክፈት የወንጌል መልእክተኛ ተግባር ነው፤ ይህ የሚደረገው ወንጌልን በማስተማርና በመስበክ ነው፤ ሐ.ሥ. 26፥17-18። ሐዋርያው ወንጌልን ሲያስተምር፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ከቃሉ ጋር ዐብሮ በተመረጡት ላይ ይሠራል፤ ይህ በተለይ በልድያ ታሪክ ይታያል፤ ሐ.ሥ. 16፥14-15።

ለ) ስለ ኀጢአታቸው ይወቀሣሉ፤ «እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) መጥቶ ስለ ኀጢአት፥ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሣል፤ ስለ ኀጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ፥ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው» ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ገለጠ፤ ዮሐ. 16፥8-11። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሰውን ኅሊና በመቀስቀስ ይወቅሣል።

ሐ) ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይላሉ፤ ይህ ርምጃ የሚወሰደው በልዩ ልዩ መንገድ ነው፤ በዐጭሩ «ያምናሉ» ማለት እንችላለን፤ ሐ.ሥ. 13፥48፤ 16፥15:31። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሓንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን» ብሎ ገለጠው፤ ሐ.ሥ. 20፥20-21። ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ጳውሎስን፥ «ከጨለማ ወደ ብርሃን፥ ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲል» ብሎ የሕይወትን ለውጥ ዘወር በማለት ምሳሌነት አብራራው፤ ሐ.ሥ. 26፥17-18። ሰው ወንጌልን ማስተዋሉ ብቻ በቂ አይደለም፤ ኀጢአትን መናዘዝም እንኳ አይበቃም። ሰው በሁለንተናው የሕይወቱ አቅጣጫ መለወጥ አለበትና የተመረጡ የወንጌልን ጥሪ ሲያዳምጡና የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስላቸው ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይላሉ።

ሰዎች በክርስቶስ ካመኑ በኋላ በሕይወታቸው የሆነውን ሲመረምሩ፥ የወንጌልን ጥሪ በሰሙ ጊዜ በዚያን ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወታቸው እንደሠራ ያስተውላሉ፤ ይህም የተከናወነው በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፈቃድ መሠረት መሆኑን መረዳት ይችላሉ። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ሲጽፍ በፊት የአይሁድን ትምህርት መከታተሉንና የወንጌል ተከታዮችን በጣም ማሳደዱን ካስታወሰ በኋላ፥ «ነገር ግን በእናቴ ማሕፀን ሳለሁ የለየኝ፥ በጸጋውም የጠራኝ... ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ... » ብሎ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደለየው፥ ቀጥሎ እንደጠራውና በመጨረሻ ክርስቶስን እንደገለጠለት የራሱን ተመክሮ በግልጥ ተረከ፤ ገላ. 1፥15-16።

ከዚህ በላይ እስካሁን ከተገለጠው አንድ ታላቅ ጥያቄ ይነሣል፤ ይኸውም የወንጌል ጥሪ ለሰዎች ሁሉና ለተመረጡት አንድ ሆኖ ሳለ፥ ለተመረጡት ብቻ ውጤታማ የሚያደርገው ምንድን ነው? የሚለው ነው። መልሳችንን ቀጥሎ በሚገኘው ንኡስ ርእስ ሥር እናቀርባለን።

## ለ) የሰው ዳግም ልደት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እናንተስ የተከተላችሁኝ፥ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፥... በዐሥራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ» ብሎ በሚመጣው አዲስ ዓለም ወይም አዲስ ዘመን የሚታየውን የሐዋርያት ሁኔታ ይገልጣል፤ ማቴ. 19፥28። በዚህ ጥቅስ «ዳግም ልደት» ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል «እንደገና መጀመር» ማለት ነው፤ ሌሎች ትርጒሞች በ«አዲስ ዓለም» ወይም በ«አዲስ ዘመን» በማለት

ይተረጕሙታል (5)። በዚህ ጥቅስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ዳግም ልደት ይናገራል፤ ይህም የሚፈጸመው በዳግም ምጽአቱ ነው። ሰዎች በዓለም ዳግም ልደት እንዲሳተፉ ወይም ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ፥ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋቸዋል፤ የዓለም ዳግም ልደት ዋና ክሥተትም የተመረጡ ሰዎች ሁሉ በዓለም መጨረሻ መሰብሰባቸው ነው።

ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ ዓለም እንደተበላሸ በመታወቁ እግዚአብሔር አዲስ ሁኔታ ውስጥ እንደሚያስገባው ተናገረ። በዚህ መሠረት ኢሳይያስ፥ «እነሆ፥ የቀድሞው ነገር ተፈጸመ፤ አዲስ ነገርንም እናገራለሁ፤ አስቀድሞም ሳይበቅል እርሱን አስታውቃችኋለሁ»፤ ኤርምያስ፥ «አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል»፤ ሕዝቅኤልም፥ «ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ፤ ከርኵሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ...» ብለው የተስፋ ቃላትን ተናግረዋል፤ ኢሳ. 42፥9፤ ኤር. 31፥31፤ ሕዝ. 36፥25-27። በተጨማሪም ሕዝቅኤል በደረቅ አጥንቶች ሸለቆ ራእይ ለየት ባለ አቀራረብ ይህን ተስፋ በድጋሚ ገልጦታል፤ ሕዝ. 37፥1-14።

በአዲስ ኪዳን ይህ አዲስ ጅማሬ በልደት ምሳሌነት ይገለጣል፤ ልዩ ልዩ የሚያያዙ ቃላት አሉ፤ እነርሱም በልደት ውስጥ የወንድን ወይም የሴትን ሚናዎች ሊያመለክቱ ይችላሉ፤ ሁሉም «ወለደ» በሚለው የአማርኛ ግስ ይተረጐማሉ፤ ዮሐ. 1፥13፤ 3፥3-7፤ 1ጴጥ. 1፥3:23፤ 1ዮሐ. 2፥29፤ 3፥9፤ 4፥7፤ 5፥1:4:18።

አዲስ ኪዳን ስለ ዳግም ልደት የሚያስተምረውን ትምህርት በሚከተሉት አምስት ርእሶች ለማብራራት እንሞክራለን (6)፦ ርእሶቹ ዳግም ልደት በአዲስ ኪዳን፥ ዳግም ልደት ከእግዚአብሔር መሆኑ፥ ዳግም ልደት በእግዚአብሔር ቃል መሣሪያነት መገኘቱ፥ ዳግም ልደት ውጤታማ መሆኑና ስለ ዳግም ልደት ልዩ ልዩ አስተያየቶች የሚሉ ናቸው፦

1. ዳግም ልደት በአዲስ ኪዳን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስና ለመንፈሳዊ ጓደኞቹ ምን እንደሚያስፈልጋቸው ሲናገር፥ በዳግም ልደት ምሳሌ ተጠቀመ (ዮሐ. 3፥3-10)። ይህ አንቀጽ የታወቀና ለዳግም ልደት ትምህርት ዐቢይ መሠረት ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ መግቢያ (1፥13) እና በመጀመሪያው መልእክቱ ስድስት ጊዜ (1ዮሐ. 2፥29፤ 3፥9፤ 4፥7፤ 5፥1:4:18)፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ሁለት ጊዜ (1ጴጥ. 1፥3:23)፥ ያዕቆብ በመልእክቱ አንድ ጊዜ (ያዕ. 1፥18) እና በተጨማሪም ከልዩ ልዩ አቅጣጫ በምሳሌው ይጠቀማሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በምሳሌው አይጠቀምም። እርሱ በሰው ዘንድ ስለሚከናወነው ስለ አዲሱ የእግዚአብሔር ሥራ ሲናገር፥ «አዲስ ፍጥረት»፥ «አዲስ ሰው»፥ «ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን መስጠት» ወይም «ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር አንድ መሆን» በማለት እንደሚከተለው ይገልጠዋል፦

«ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው» (2ቆሮ. 5፥17)፤

«በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል» (ገላ. 6፥15)፤

«... መልካም ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌ. 2፥10)፤

«የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ» (ኤፌ. 4፥24)፤

«በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን» (ኤፌ. 2፥5፤ ቆላ. 2፥13)፤

«... ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» (ሮም 6፥5)፤

«ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ...» (ቆላ. 3፥1)።

«ለሐዋርው ይህ አዲስ ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ ነው፤ በተለይም ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ ዳግም ልደትን ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር እንደሚከተለው ያዛምደዋል:- «ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ... ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ»፤ 1ጴጥ. 1፥3።

እውነት ነው፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «(እግዚአብሔር) እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን» ብሎ ጽፏል፤ ቲቶ 3፥5። እዚህ ላይ በአዲስ ልደት የተተረጐመው የግሪክ ቃል በማቴዎስ 19፥28 ላይ እንዳለው «እንደገና መጀመር» የሚል ነውና የጳውሎስ አጻጻፍ «ዳግመኛ መወለድ» ብለው ከጻፉት ሌሎች ሐዋርያት በመጠኑ ይለያል (7)። የጥቅሱ ትርጉም የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ መታጠብ አዲስ ልደት ነው፤ መታጠብ አዲስ ልደትን ያመጣል፤ መታጠብ የአዲስ ልደት ምሳሌ ነው ወይም መታጠብና መታደስ አንድ ዐይነት ድርጊት ናቸው ማለት የመጨረሻው አማራጭ ይሆናል። እንደዚህ ከሆነ ሐዋርያው «መታደስ» በሚለው ግስ ከሚጠቀምበት፥ «... በልባችሁ (በአእምሮአችሁ) መታደስ ተለወጡ» ከሚለው አንድ ሌላ ጥቅስ አጠቃቀም ጋር ይስማማል፤ ሮም 12፥2።

## 2. ዳግም ልደት ከእግዚአብሔር መሆኑ

የድነትን ውቅር ለማሳየት ዳግም ልደትና እምነት እንዴት እንደሚገናኙ ማሰብ አስፈላጊ ነበርና በምዕራፍ 86ለ ዳግም ልደት ከእግዚአብሔር በመሆኑ ላይ በማተኮር ከእምነት መቅደሙን ማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አማራጭ እንደሆነ ማየት ችለናል። አሁን ግን ዐቢይ ጥቅሶችንን ከመመርመራችን በፊት የሚከተለውን ምሳሌ በሚገባ ብናስተውለው ሊረዳን ይችላል።

ልጆች በሥጋ መፀነሳቸውን ወይም ከእናታቸው መወለዳቸውን ዐውቀው በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ዐይነት ትብብር አያደርጉም። በበደላቸውና በኀጢአታቸው ሙታን የሆኑትም እንደዚሁ መንፈስ ቅዱስ በሚያከናውነው የሕይወት ሰጭነት ተግባር ውስጥ መተባበር እንደሚችሉ ማሰብ አመክንዮታዊ አይደለም፤ ኤፌ. 2፥1-10። ክርስቶስም፥ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው» (ዮሐ. 3፥6) በማለቱ፥ እነዚህ ሁለት ልደቶች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም፥ እያንዳንዱ የራሱ መነሻ እንዳለውና የተደበላለቀም እንዳልሆነ አሳይቷል። በዮሐንስ ወንጌል «ሥጋ» የሰውን ትስብእታዊ ሁኔታ እንጂ (ዮሐ. 1፥13-14) የሰውን ኀጢአተኛነት ላያመለክት ይችላል (ይህ አጠቃቀም በሮም 8፥1-13 ይታያል)። እንግዲህ ዳግመኛ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ ምሥጢራዊ ሥራ ነው። ክርስቶስም ሐዋርያትም ዳግመኛ መወለድ ፍጹም አስፈላጊ በመሆኑ ላይ ሲያተኩሩ፥ በመንፈሳዊ ምሳሌው

«ተወለድ» የሚለውን ትእዛዝ አንቀጽ ሕፃኑ እንዲወለድ ሲጠቀሙበት አይታይም፤ ምክንያቱም መወለድ ከወላጅ እንጂ ከሚወለደው አይደለም።

እንደዚሁም ዳግመኛ መወለድ የእግዚአብሔርን ጥሪ እንደ መቀበል አይደለም። የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ ሰው ልቡና ይደርሳል፤ ሰውም ጥሪውን አስቦ ይቀበለዋል ወይም አይቀበለውም። ዳግም ልደት የሚሠራው ግን በሰው ልብ ውስጥ ነው፤ በልብ ውስጥ አዲስ ሁኔታ ይፈጠራል። ሰው ዳግመኛ ሲወለድ፥ ለውጥ እንዳለ ሊያስተውል ይችላል፤ ነገር ግን ዳግመኛ መወለዱን ሊቃወም ወይም ሊሳተፍበት አይችልም፤ አማኙ በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ይደሰታልና (8)። ነቢዩ ሕዝቅኤል፥ «አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ» በማለቱ፥ እግዚአብሔር በዳግም ልደት የሚያደርገውን ታላቅ ለውጥ በትንቢት ገለጠ፤ ሆኖም ይህን እንዴት እንደሚያከናውነው አልገለጠም፤ ይህ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነውና፤ ሕዝ. 36፥26።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተናገራቸው ስለ ሁለት ሌሎች ነጥቦች ማተት ያስፈልገናል:-

1ኛ፥ «ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም»፤ ዮሐ. 3፥5። ክርስቶስ ይህን የተናገረው ኒቆዲሞስ ላቀረበለት ጥያቄ መልስ እንዲሆን ነው። መልሱ ለኒቆዲሞስ ግልጥ መሆን ነበረበት፤ ምክንያቱም እርሱ በእስራኤል መምህር ነበረና ብሉይ ኪዳንን በሰፊው አጥንቶ ነበር፤ ዮሐ. 3፥10።

«ውሃ» እና «መንፈስ» በአንድነት የሚጠቀሱት በሕዝቅኤል 36፥25-27 ውስጥ ነው። በዚያም ላይ እግዚአብሔር፥ «ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ፤ እናንተም ትጠራላችሁ፤ ከርኵሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ» (ቍ. 25) በማለቱ፥ ሰው አዲስ ልብ እንዲያገኝ በመጀመሪያ መንጻት አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ይሰጣል ወይም በሌላ አነጋገር የድንጋዩም ልብ (እልከኛ የሆነው ልብ) ከሥጋው ይወጣልና በዚያ ፈንታ የሥጋን ልብ (ተቀባይ የሆነን ልብ) ይሰጣል (ቍ. 26)። ከዚያም ቀጥሎ እግዚአብሔር የራሱን መንፈስ በሰው ልብ ውስጥ ያኖራልና የሰው አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ተከትለው ለእግዚአብሔር ይታዘዛሉ፤ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይጠብቃሉ፤ ፈቃዱንም ይፈጽማሉ (ቍ. 27)። ሰው እንደዚህ ሲሆን ዳግመኛ ተወልዶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያያል (የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ያስተውላል) እና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባል (ገብቶ የመንግሥቱን ሕግ ያከብራልና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይመላለሳል)፤ ዮሐ. 3፥3:5። ስለዚህ ሰው «ከውሃና ከመንፈስ» ዳግመኛ መወለዱ በሕዝቅኤል ትንቢት መሠረት ሲተረጐም «ውሃ» መንጻትን ሲያሳይ፥ «መንፈስ» ደግሞ በሰው ልብ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያመለክታል።

እውነት ነው፤ ብዙ ሰዎች «ውሃ» ጥምቀትን እንደሚገልጥ ይናገራሉ፤ ጥምቀት ከመንጻት ጋር ቅርብ ግንኙነት ያለው መሆኑ ግልጥ ነው (ለምሳሌ ሐ.ሥ. 22፥16 ይመ.)። የክርስቶስ አሳብ ሥርዐተ ጥምቀትን የሚመለከት ቢሆን ኖሮ፥ «ከጥምቀትና ከመንፈስ» ማለት ይችል ነበር፤ የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት በግልጥ ይታወቅ ነበርና።

ሌሎች ሰዎች ደግሞ «ውሃ» የእግዚአብሔርን ቃል ያመለክታል ይላሉ:: እውነት ነው፤ ቀጥሎ እንደምናየው ዳግመኛ መወለድ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይገናኛልና ውሃ ከልዩ ልዩ የብሉይ ኪዳን አንቀጾች ጋር የተያያዘ ቢሆንም (ለምሳሌ መዝ. 1፥2-3)፥ የክርስቶስ አሳብ ይህ ከሆነ፥ በውሃ ፈንታ «ከእግዚአብሔር ቃልና ከመንፈስ» ማለት ይችል ነበር:: ከዚህ ይልቅ የክርስቶስ አሳብ ከሕዝቅኤል ትንቢት ጋር በተሻለ መንገድ ይቀራረባልና ውሃ መንጻትን ያመለክታል ማለት ምክንያታዊ አማራጭ ነው::

2ኛ፥ «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» (ቊ. 8):: ይህ ቃል፥ «የነፋስ መንገድ እንዴት እንደሆነች፥ ዐጥንትም በእርጉዝ ሆድ እንዴት እንድትዋደድ እንደማታውቅ፥ እንዲሁም ሁሉን የሚሠራውን የእግዚአብሔርን ሥራ አታውቅም» የሚለውን ጥቅስ ያሳስባል፤ መክ. 11፥5::

ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ሁሉ፥ ይህ ምሳሌ ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን፥ ምሥጢራዊ መሆኑን፥ ሰው እንዲጀመር ሊያደርገው፥ ሊቈጣጠረው፥ ሊቃወመው ወይም ሊተባበርበት የሚችል አለመሆኑን ያሳያል::

3. ዳግም ልደት በእግዚአብሔር ቃል መሣሪያነት መገኘቱ

ዳግመኛ መወለድ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት በሰው ልብ ውስጥ የሚፈጸም ሲሆን መፈጸሙን የምናውቀው፥ አዲስ ሕይወትና አዲስ ኀይል ከልብ ፈልቀው ወደ ልቡና በመግባት ሰው በአዲስ መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሲቀበል ነው፤ ይህ የዳግም ልደት ፍጻሜ ነው (9):: ሐዋርያው ጴጥሮስ የሚከተለውን ጽፏል:- «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ::... በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው»፤ 1ጴጥ. 1፥23-25:: ያዕቆብም፥ «ለፍጥረቱ የበኵራት ዐይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» ብሏል፤ ያዕ. 1፥18:: ከእነዚህ ጥቅሶች ቢያንስ አራት አሳቦችን ማውጣት እንችላለን:-

ሀ) ዳግመኛ መወለድ «ከ» እግዚአብሔር የሚሰጥ ዕድል ሲሆን፥ የሚገኘ ው «በ» ቃሉ መሣሪያነት ነው::

ለ) ቃሉ በወንጌል የተሰበከ እውነተኛ ቃልና ጥሪ ነው::

ሐ) ቃሉ በዘር ተመስሏል፤ ሕያው ነውና በመልካም መሬት ላይ ሲወድቅ ፍሬ ያፈራል፤ በዚህ አስተሳሰብ መሠረትም «መልካም መሬት» በዳግም ልደት የተዘጋጀው «መልካምና በጎ ልብ» መሆኑን ልናስብ እንችላለን፤ ሉቃ. 8፥8:15::

መ) የጌታ ቃል እንደ ሣር ሳይሆን፥ የማይጠፋና ለዘለዓለም የሚኖር ዘር በመሆኑ፥ የሚሰጠው ሕይወት ዘለዓለማዊና የማይጠፋ መሆኑን ማሰብ አመክንዮታዊ ነው፤ 1ጴጥ. 1፥24-25::

በአንዳንድ ሰዎች አመለካከት መሠረት፥ ሰው የወንጌልን ጥሪ ሲቀበል፥ ቃሉ ወደ ልቡ ይገባልና ሕይወቱን ሁሉ ይለውጣል:: እነዚህ ሰዎች ቃሉና መንፈስ ቅዱስ አብረው እንደሚሠሩ ሲያስቡ ግን ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ መወለዱንና መለወጡን አይክዱም:: ሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔርን ጥሪ ውጤታማ የሚያደርጉት ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመወለዳቸው ላይ በማተኮር ነው፤ ይህ እኛም የምንጋራው አመለካከት ነው::

4. ዳግም ልደት ውጤታማ መሆኑ (10)

ሰው ዳግመኛ ሲወለድ ወዲያውኑ ልዩ ልዩ ውጤት መታየት ጀምራል፤ ከዚያም በኋላ በሂደት የዳግም ልደት ለውጥ በሕይወቱ ሁሉ ይታያል:: ይህን ለውጥ በአራት አርእስት ከፍለን እንደሚከተለው እናቀርበዋለን::

ሀ) የልቡና አብርሆት፤ ሰው ዳግመኛ ሲወለድ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት ይጀምራል (ዮሐ. 3፥3:6)፤ በፊት በሥጋ ብቻ በመሆኑ ምንም ማስተዋል አይችልም ነበር፤ 1ቆሮ. 2፥14:: ቀድሞ በጨለማ ይኖር ነበር፤ አሁን ወደ ብርሃን መጥቷል፤ ዮሐ. 3፥19-20፤ ሐ.ሥ. 26፥17-18፤ ቆላ. 1፥13-14:: ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን አብርሆት ሲገልጠው፥ ምእመናን ከእግዚአብሔር «ቅባት» ተቀብለዋልና እውነትን ያውቃሉ፤ አሁንም ሰው እንዲያስተምራቸው አያስፈልጋቸውም ይላል፤ 1ዮሐ. 2፥20:27:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች በነቢያት፥ በካህናትና በነገሥታት አማካይነት መንፈሳዊ ዕውቀትን ያገኙ ነበር፤ አሁን ግን ቀጥታ በቅባቱ ያውቃሉ:: ነቢዩ ኤርምያስ ስለ አዲስ ኪዳን ዘመን ሁኔታ ትንቢት እንደሚከተለው ተናግሮ ነበር:- «ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ… እያንዳንዱ ሰው… ወንድሙን:- እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና ይላል እግዚአብሔር»፤ ኤር. 31፥33-34::

ይህም፥ ክርስቲያን አብርሆትን ሲቀበል፥ መምህር ወይም ምክር አያስፈልገውም ማለቱ አይደለም፤ ዮሐንስ ራሱ አንባቢዎቹን ያስተምርና ይመክር ነበር:: እንደዚሁም ዕውር የነበረው ማየት ሲጀምር ሁሉን ቢያይም፥ የሚያየውን ወዲያውኑ ያስተውለዋል ማለት አይደለም:: በመንፈሳዊ ረገድ አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል እያጠና እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ይማራል:: ነገር ግን ሰው ዳግመኛ ተወልዶ አብርሆትን ሲቀበል፥ በመንፈሳዊ በኩል፥ «ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር ዐውቃለሁ» የሚለውን የተመከሮ ምስክርነት መስጠት ይችላል፤ ዮሐ. 9፥25:: አብርሆትን የተቀበለ ሰው አሁን ያውቃል፤ እንደሚያውቅም ያውቃል፤ አንድ ነገርን ብቻ ቢያውቅም፥ ያ ነገር ዋና ነገር መሆኑን ያውቃልና መንግሥቱን ያያል፤ መንግሥቱን ቢያይም ለወደፊት ስለ መንግሥቱ ብዙ ሌላ ነገርን እንደሚማር ሊያስተውል ይችላል:: ቀድሞ በጨለማ ይኖር ነበር፤ አሁን ግን የሚያየውን መለየትና ማመዛዘን ይችላል፤ እውነትን አግኝቷልና፤ ዮሐ. 8፥32፤ 14፥6፤ 16፥13::

ለ) የፈቃድ ነጻነት፤ ክርስቶስ፥ «ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኀጢአት ባሪያ ነው» ብሏልና ሰው ነጻነት የለውም፤ ዮሐ. 8፥34:: ችግሩ ሰው ለኀጢአቱ ይገዛልና እግዚአብሔርንና ጽድቅን አይፈልግም፤ ማመንም አይችልም፤ ሮም 3፥11:: ሰው ዳግመኛ ሲወለድ ግን ፈቃዱ ከኀጢአት ባርነት ነጻ ይወጣልና ወደ ብርሃን ይመጣል፤ እግዚአብሔርንና ድኅነት መቀበልን ይወዳል፤ ወንጌልን ያደምጣልና በክርስቶስ ያምናል:: ሰውዬው በሰውነቱ ያው ነው፤ ነገር ግን ፈቃዱ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተለውጧልና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባል፤ ዮሐ. 3፥5፤ ሐ.ሥ. 16፥14:: የፈቃድ ዐርነት (ነጻነት) ማግኘት ማለት ሰው ለተፈጥሮ የሚመቸውንና ለሕይወት የሚገባውን ማድረግ ይችላል ማለት ነው:: ዳግመኛ ከመወለዱ በፊት በኀጢአት ባርነት ምክንያት ይህን ማድረግ አይችልም፤ አይፈልግምም ነበር፤ ዮሐ. 3፥5:20::

ሐ) ከበደል መንጻት፤ ሰው ኀጢአትን በማድረጉ ርኩስ ነውና መታጠብና መጥራት ያስፈልገዋል:: ከዚህ በላይ እንደገለጥነው በዮሐንስ 3፥5 «ውሃ» ይህን የሚያመለክት ይመስላል፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ስለ አማኞች

«ታጥባችኋል» (1ቆሮ. 6፥11) እና ስለ አዲስ ልደት «መታጠብ» (ቲቶ 3፥5) ብሎ ጽፏል።

መ) የጠቅላላ ሕይወት ለውጥ፤ ዳግም ልደት የሰውን ጠባይና አኗኗር ሁሉ እስከ ሞት ድረስ ይዳስሳልና ይህ ለውጥ በሰው ሕይወት ካልታየ፥ ሰው ዳግመኛ እንዳልተወለደ ማሰብ አይከብድም። ዮሐንስ በመጀመሪያው መልእክቱ እንደሚከተለው ጽፏል:-

1) «ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደተወለደ ዕወቁ» (1ዮሐ. 2፥29)፤ ይህ ጥቅስ ዳግመኛ የተወለደ ሰው ሕይወት አጠቃላይ ሁኔታ ጽድቅን ማድረግ ይታይበታል እንጂ ስሕተት የለበትም የሚል ትርጉም የለውም፤ ም. 1፥8-10 ይመ.። በግሪክ ቋንቋ ግሱ የአሁን ጊዜ አንቀጽ ያለው ሲሆን የሚዘወተር ልማድን ሊያመለክት ይችላል።

2) «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ስለሚኖር ከእግዚአብሔር ተወልዷልና ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም» (3፥9)፤ በ2፥29 ላይ ስለ የአሁን ጊዜ የግስ አንቀጽ በተመለከትነው መሠረት ይህ ጥቅስ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሰው ኀጢአትን እንደማያዘወትር ወይም በአንድ ዐይነት ኀጢአት ሁልጊዜ እንደማይሸነፍ ያስተምራል፤ ይኸውም አማኙ ኀጢአት ፈጽሞ አይሠራም ማለት አይደለም፤ 1ዮሐ. 1፥7-2፥1። ለዚህ ዐይነቱ አዲስ አኗኗር ምክንያት አለ፤ ይኸውም፥ «ዘሩ በእርሱ ይኖራልና» የሚለው ነው፤ ከዚህም ላይ ዳግም ልደት በዘር ተመስሏልና ይህ ዘር የእግዚአብሔር በመሆኑና፥ በሰው ውስጥ በመገኘቱ ሁልጊዜ በሰው ሕይወት ፍሬ ያፈራልና ኀጢአትን እየተቃወመ ይገታዋል፤ 1ጴጥ. 1፥23 እና ከዚያ በላይ በ3ሐ ሥር የተጻፈውን ይመ.።

3) «ወዳጆች ሆይ፥ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ» (4፥7)፤ ይህ ጥቅስ ክርስቲያናዊ ፍቅር በሰው ሁሉ ዘንድ ከሚታየው ፍቅር የተለየ መሆኑን ያሳያል። ይህ ፍቅር ምእመናን ሁሉ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናቸውና እግዚአብሔርን በማወቃቸው እርስ በርሳቸው እንደሚዋደዱ ያሳያል። በተጨማሪም የዳግም ልደት ዋና ምልክት፥ መረጃና ማረጋገጫ ነውና የዓለም ሰዎች እንኳ ይህን ፍቅር በማየት ምእመናኑ የክርስቶስ ተከታዮች መሆናቸውን ያውቃሉ፤ ዮሐ. 13፥34-35።

4) «ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል፤ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል» (5፥1)፤ ይህ ጥቅስ እንደ ፊተኛው ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር የተወለደው ከእግዚአብሔር የተወለዱትን በሙሉ መውደዱን በማስገንዘብ ላይ ያተኩራል። ሰው ኢየሱስን በትክክል ማመኑ፥ በተለይም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ በመሆኑ ላይ ርግጠኛ መሆን የዳግም ልደት ውጤት ነው።

5) «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው» (5፥4)፤ ይህ ጥቅስ ዓለም በተንኰል በመሳብ ወይም በኀይል በማስፈራራት ዳግመኛ የተወለደው ሰው ተቃዋሚና ጠላት መሆኑን ሲያሳስብ፥ ክርስቲያን በዓለማዊ ዘዴ ሳይሆን፥ በእምነቱ ዓለምን እንደሚያሸንፈው ይገልጣል። በተጨማሪም ከዳግም ልደት ውጤቶች እምነት አንዱ መሆኑ ከዚህ ጥቅስ ይታያል።

6) «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን (ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ይጠብቀዋል፤ ሰይጣንም አይነካውም)» (5፥18)፤ ዋና ዋናዎቹ የጥንት ቅጆች በዚህ ጥቅስ ላይ የተለያየ አሳብ እንዳላቸው ቢታወቅም፥ ሁለቱ እውነትን ይገልጣሉ (11)፤ ሆኖም የዚህ ዘመን ሊቃውንት በቅንፍ ውስጥ ያለውን የተሻለ አማራጭ ያደርጉታል (ቀ.ኢ. እና አ.መ.ት. ይመ.)፡፡ ይህ ጥቅስ በ3፥9 ላይ እንደተሰጠው ትምህርት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ በኃጢአት እንደማይኖር ያሳስባል፡፡ ሰይጣን ግን ክፉ ነውና አማኙን ሊጥለው ይፈልጋል፡፡ አንደኛው ቅጅ የሚለው ከእግዚአብሔር የተወለደው ሰው ራሱን ይጠብቃል፤ በጥንቃቄም ስለሚሄድ ሰይጣን ሊነካው አይችልም፡፡ ሰው ራሱን እንዴት እንደሚጠብቅ ልዩ ልዩ ጥቅሶች ይናገራሉ፤ 1ዮሐ. 3፥3፤ 1ጢሞ. 5፥22፤ ያዕ. 1፥27፤ ይሁዳ 21፡፡ በሁለተኛው ቅጅ አገላለጥ መሠረት ግን ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተወለደውን ሰው ይጠብቃልና ሰይጣን ሊነካው አይችልም፡፡

እንግዲህ በዐጭሩ በእነዚህ ስድስት ጥቅሶች ዳግመኛ የተወለደው ሰው በኃጢአት፥ በዓለምና በሰይጣን ላይ አሸናፊ መሆኑንና በጽድቅ እየተራመደ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሌሎችን ሁሉ የሚያፈቅር መሆኑን እናያለን፡፡ ዳግም ልደት የአዲስ ሕይወት መነሻ ብቻ ሳይሆን፥ ዘሩ በአማኙ ስለሚኖር እስከ መጨረሻ በሕይወቱ ወሳኝ ነውና አካሄዱን ሁሉ ይዳስሳል፡፡ የሰው ውድቀት የሰውን ሁለንተና በኃጢአት እንደበከለ ሁሉ፥ ዳግም ልደትም የሰውን ሁለንተና ይዳስሳል፤ ሰው በአዳም ሲሆን ሁለንተናው ሙሉ በሙሉ ኃጢአት እንዳልሆነ ሁሉ፥ በዳግም ልደትም በአካሄዱ መቶ በመቶ ፍጹም አይደለም፡፡ ሆኖም ዳግመኛ የተወለደ ሰው በመንፈሳዊነት እያደገና እየተለወጠ መሄድ ይችላል፤ መለወጥም ይኖርበታል፤ 2ቆሮ. 3፥18፤ 4፥17፡፡

## 5. ስለ ዳግም ልደት ልዩ ልዩ አስተያየቶች

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለ ወንጌል ጥሪና ስለ ዳግም ልደት ብዙ ትርምስ ያለበት ሁኔታ ተከሥቷል፡፡ ምክንያቱም «ዳግም ልደት» አንዳንድ ጊዜ በኃጢአተኛ ሰው ልብ የእግዚአብሔርን የመጀመሪያ ሥራ፥ በሌላ ጊዜ ሰው እስኪያምን ድረስ የሰውን ተሳትፎ ያጠቃልላል፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በሰው ሕይወት ሁሉ የሚደረገውን ጠቅላላ ለውጥ ያመለክታል፡፡ እንደ ሽለይርማከር ያሉት ሌሎች ደግሞ ዳግም ልደት በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ላይ የሚደረገውን ለውጥ ሳይሆን፥ የጠቅላላ ኅብረተሰብን ለውጥ ያመለክታል ይላሉ (12)፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ዳግመኛ መወለድንና መጽደቅን በአንድነት አጣምረው አስተምረዋል፡፡ ከዚህ የተነሣ ሁለት ሰዎች የሚስማሙ ሳይመስሉ፥ አሳባቸው አንድ ሊሆን ይችላል፡፡

እንደ እኛ አስተሳሰብ ከሆነ ዳግመኛ መወለድና መጽደቅ የተለያዩ አሳቦች ናቸውና በነገረ መለኮት ለየብቻቸው ሊመረመሩ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም መጽደቅ በእግዚአብሔር ፊት የአማኙን አቋም፥ ዳግመኛ መወለድ ደግሞ በሰው ልብ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም በትምህርተ መለኮት ዳግም ልደትን በሁለት አቅጣጫ ብንመለከተው ይረዳናል፤ በወንድ ሚና ምሳሌነት የእግዚአብሔር ሥራ በሰው ሕይወት መጀመሩ የመጀመሪያው ሲሆን፥ በሴት ሚና ምሳሌነት ሰው ወደ ንስሓና ወደ እምነት መድረሱ ደግሞ ሁለተኛው አቅጣጫ ነው (13)፡፡

በአበውና በምዕራባውያን ትምህርተ መለኮት ዳግም ልደት በግልጥ የተወሰነ አሳብ አልነበረውም (14)። ሐረጉ ከኀጢአት መንጻት ጋር የሚገኘውን ለውጥ ሲያመለክት፥ በዳግም ልደትና በመጽደቅ መካከል ግልጥ የሆነ ልዩነት አልነበረም። አውግስጢኖስ ዳግም ልደትንና የሰውን ወደ እግዚአብሔር መመለስ (ንስሓንና እምነትን) የተመለከታቸው በመለያየት ነው። በትምህርቱ መሠረት ዳግም ልደት መጀመሪያ የልብን ለውጥና የኀጢአትን ስርየት ሲያጠቃልል፥ ወደ እግዚአብሔር ከመመለስ በኋላ የሚወሰድ ርምጃ ነበረ። እንግዲህ ዳግም ልደት ሰው የማይሳተፍበትና ሊቃወመው የማይችል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚፈጸም ሥራ ነው። ፔላጊዮስ ግን ዳግም ልደት የአዲስ ጠባይ ጅማሬ ሳይሆን፥ በጥምቀት የኀጢአት ስርየት፥ በእውነት ልባዊ አብርሆትና በአምላካዊ ተስፋ ቃላት የልብ መቀስቀስ መሆኑን አስተማረ። ከአውግስጢኖስ በኋላ በዳግም ልደትና በመጽደቅ መካከል የነበረው ልዩነት ከመጨመሩ የተነሣ ትርምሱ እየሰፋ ሄደ። ሆኖም በመጀመሪያ በጥምቀት የእግዚአብሔር ጸጋ ይሰጣልና በዚህ መሠረት የኀጢአት ስርየት ይገኛል የሚለው የአኩናስ ትምህርት ቀስ በቀስ ተቀባይነት አገኘ። በዚህ ትምህርት መሠረት ይህ መንፈሳዊ በረከት ሁሉ በጥምቀት ሥርዐት ለሰው ይሰጣል። ከዚህ ትምህርት በስተ ጀተርባም አንድ መሠረታዊ አሳብ አለ፤ እርሱም ሰውን ማጽደቅ በፍትሓዊ ውሳኔ ሰው ጻድቅ መሆኑን ማወጅ ሳሆን፥ በጠባይ ሰውን ጻድቅ ማድረግ የሚለው ነው (15)።

ማርቲን ሉተር በዳግም ልደትና በመጽደቅ መካከል ያለውን የአሳብ ትርምስ በሙሉ አልፈታውም። ካልቪን ዳግም ልደትን በሰፊው አመለካከት ሲጠቀምበት፥ ሰው በመጀመሪያ አዲስ ሕይወትን የሚቀበልበትን፥ ንስሓን፥ እምነትንና ቅድስናን በአንድነት አጠቃልሎ ተመለከተ። ከዚያም በኋላ አንዳንድ ሊቃውንት በዳግም ልደትና በመመለስ (በንስሓና እምነት) መካከል ልዩነት መኖሩን አላመለከቱም።

የተሐድሶ ተከታዮች ዳግም ልደትን በሁለት አቅጣጫ መመልከትና ከሰው አጸፋና ከመጽደቅ ለይቶ ማየትን ቀስ በቀስ እየለመዱት ሄደዋል፤ በዚህ መጽሐፍ የሚታየው የእኛ አቀራረብ ከዚህ ጋር ይስማማል።

አንዳንድ ሰዎች ለተመረጡት ብቻ እንጂ ለሰዎች ሁሉ የወንጌልን ጥሪ ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን በማመናቸው፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የመጀመሪያ ምልክቶች በሰው ሕይወት እስኪታዩ ድረስ ወንጌልን አይሰብኩም። እነዚህን ምልክቶች በትክክል መለየት ቢቻልም እጅግ ከባድ ነው፤ ከዚህም በላይ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንጂ ለተመረጡት ብቻ ለመስበክ አልታዘዝንም፤ ማቴ. 28፥18-19፤ ማር. 16፥15። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ጥሪም ለሰዎች ሁሉ ነው:- «መንፈስና ሙሽራዪቱም:- ና ይላሉ። የሚሰማም ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፤ የወደደም የሕይወትን ውሃ እንዲያው ይውሰድ»፤ ራእ. 22፥17።

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በዳግም ልደት የሰው መንፈስ ሕያው በመሆኑ ላይ ያተኩራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ሰውነታችሁ በኀጢአት ምክንያት የሞተ ነው፤ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው» በማለት የጻፈው፥ የሰው መንፈስ ብቻ ሕያው መሆኑን የሚያመለክት አይመስልም፤ ሮም 8፥10። በሌላ ቦታ ጳውሎስ ምእመናን በበደላቸውና በኀጢአታቸው ሙታን እንደነበሩ ሲያስተምር፥ የሰው ሁለንተና ከሞት ኀይል በታች መሆኑን ገለጠ፤ ኤፌ. 2፥1-3። እንደዚሁም፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር ዐልፏል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኗል» በማለቱ ዳግም ልደት ሁለንተናን የሚዳስስ መሆኑን ያሳያል፤ 2ቆሮ. 5፥17። እውነት ነው፤ ሥጋችን ይሞታል፤

ይቀበራልም፤ ክርስቲያን ግን ሲሞት ወዲያውኑ ወደ ክርስቶስ ይሄዳል (ፊል. 1፥21-23)፤ በትንሣኤው ዕለትም በሥጋ ይነሣል።

ልደት በተወሰነ ወቅት አንድ ጊዜ በሰው ሕይወት የሚፈጸም እንደ መሆኑ መጠን፥ ዳግም ልደትም አንድ ጊዜ በተወሰነ ወቅት እውን ይሆናል። እንዴትና መቼ እንደሚሆን ባይታወቅም፥ አማኙ ዳግመኛ እንደተወለደ ያውቃልና በምሥጢራዊው ሥራ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

ክርስቲያን የወንጌል ጥሪና ዳግም ልደት እንዴት እንደሚገናኙ ሲያስተውልና ዳግም ልደት በእግዚአብሔር ቃል መፈጸሙን ሲያውቅ በተስፋ ተሞልቶ ይሰብካል፤ ያስተምራል፤ ይመሰክራልም። ይህንም በተለያየ መንገድና በብዙ ዘዴ ሊፈጽመው ይችላል፤ ሲፈጽመውም የሰውን ስሜት ለመቀስቀስ አይሞክርም፤ ምክንያቱም ሰው ስሜታዊ እየሆነ በሄደ መጠን የቃሉን እውነት መለየትና መረዳት አዳጋች ሊሆንበት ይችላል። በዚህም ፈንታ ክርስቲያን የቃሉን ግልጽነት በአቀራረቡ ለማሻሻል ጥረት ያደርጋል። የቃሉንም አቀራረብ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ሥራ ውጤታማ መሆኑን ያውቃልና ቃሉን ከማቅረቡ ጋር እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲፈጽም ሳይታክት ይጸልያል።

## ማስታወሻ

(1) በእንግሊዝኛ እነዚህ ጥሪዎች External Call እና Internal Call ይባላሉ።

(2) ውጤታማ ጥሪ በእንግሊዘኛ Effective Call ይባላል።

(3) የተመረጡት የወንጌልን ጥሪ መቀበላቸው Irresistible Grace በሚለው የእንግሊዝኛ ሐረግ ተገልጧል።

(4) አብርሆት በእንግሊዝኛ Illumination ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

(5) ይህ አሳብ በእንግሊዝኛ Regeneration በሚለው ቃል ይተረጐማል፤ በመሠረቱ ቃሉ ህልው ስሆነ ነገር ወይም ሁኔታ አዲስ ሕይወት መስጠትን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ሊቃውንት በየዘመኑ በልዩ ልዩ መንገድ ይጠቀሙበታል፤ THS ገጽ 116-118 ይመ.

(6) Berkhof ገጽ 456-479፥ THS 116-126፥ Grudem 699-706፥ RR 714-720 ይመ.

(7) THS ገጽ 117 ይመ.

(8) አዲስ ልደት እውን የሚሆነው በልቡና ሳይሆን በልብ (Subconscious) ነው። በዚህ መንገድ የአዲስ ልደት እውን መሆን የIrresistible Grace አንድ ክፍል ነው።

(9) ይህ አቀራረብ ከB.B. Warfield በተገኘው አሳብ ላይ የተመሠረተ ነው፤ THS ገጽ 125 ይመ.

(10) ይህ ክፍል በተለይ በTHS ገጽ 121-123 ላይ ተመሥርቷል።

(11) John Stott በTyndale N.T. Commentaries The Epistles of John 1964 IVP ይመ.

(12) Berkhof ገጽ 465-468 ይመ.

(13) በእንግሊዝኛ የወንድ ሚና Beget በሚለው ግስ ሲገለጥ፥ የሴት ሚና Bear ወይም Give Birth በሚሉት ቃላት ይገለጣል:: ሆኖም በአዳዲሶቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች «ወለደ»ን በመጠቀም ፈንታ «አገሌ የእገሌ አባት ነበረ» ማለት ተለምዷል፤ ለምሳሌ ማቴ. 1፥1-16 ይመ.:: በትምህርተ መለኮት አንዳንዶች የመጀመሪያ ሁኔታን በRegenerate፥ ፍጻሜውን ደግሞ በBe Born Again ይገልጣሉ፤ ሆኖም እስከ አሁን ድረስ በስፋት የተለመደ አባባል የለም:: ከዚህ የተነሣ የዓለም ሰዎች Born Again የሚለውን ሐረግ ለማናቸውም ዐይነት አዲስ የጋለ ሁኔታ ሲጠቀሙበት እንሰማለን፤ ለምሳሌ A Born Again Politician ወይም A Born Again Organisation ተብሏል:: ክርስቲያኖች በአባባላቸው ላይ ጥንቃቄ አለማድረጋቸው አንድ ችግር ሆኖ ይታል::

(14) Berkhof፥ ዳግም ልደትን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከገጽ 465-468 ለማብራራት ይሞክራል:: እኛም በዐጭሩ አገላለጡን ለመከተል እንሞክራለን::

(15) ሰውን ስለ ማጽደቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ትምህርት በም. 89 በሰፊው ለመመርመር እናስባለን::

# ምዕራፍ 88 - ንስሐ መግባትና እምነት

እግዚአብሔር የእርሱ ታላቅ ነቢይ የሆነውን ኢሳይያስን፥ «ሂድ፤ ይህን ሕዝብ:- መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው:: በዐይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸው እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፥ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፤ ጆሮአቸውንም አደንቊር፤ ዐይናቸውንም ጨፍን» ብሎ አዘዘው፤ ኢሳ. 6፥9-10:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላና በኢየሩሳሌም ሲያስተምር፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ በሮም የእስራኤልን ተወካዮች ሲያሰናብት ይህን ጥቅስ ጠቅሰውታል፤ ማቴ. 13፥14-15፤ ዮሐ. 12፥39-40፤ ሐ.ሥ. 28፥25-27:: የአይሁድ ሕዝብ ከክርስቶስም ሆነ ከጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት አልፈለጉም፤ ወደ እግዚአብሔር መመለስም አልወደዱምና ልባቸውን አደነደኑ::

ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «ክፉ ሰው መንገዱን፥ በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ፤ እርሱም ይምረዋል፤ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ» ብሎ የእስራኤል ሕዝብ እንዲመለስ አደፋፈረ፤ ሌሎች ነቢያትም በዚህ መንፈስ ደጋግመው ተናግረዋል፤ ኢሳ. 55፥6፤ ኤር. 8፥6፤ ሕዝ. 33፥11፤ ኢዩ. 2፥12-13:: ሆኖም ዳዊት፥ «የመድኀኒታችን አምላክ ሆይ፥ መልሰን» እና ነቢዩ ኤርምያስ፥ «ቀጣኸኝ፤ እኔም እንዳልተገራ ወይፈን ተቀጣሁ፤ አንተ እግዚአብሔር አምላኬ ነህና መልሰኝ፤ እኔም እመለሳለሁ»፤ «አቤቱ፥ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን» ብለው በመጻፋቸው፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ በሕዝቡ ካልሠራ፥ እነርሱ ወደ እግዚአብሔር እንደማይመለሱ አሳይተዋል፤ መዝ. 85፥4፤ ኤር. 31፥18፤ ሰ.ኤ. 5፥21:: ክርስቶስ ደግሞ፥ «እውነት እላችኋለሁ፤ ካልተመለሳችሁ፥ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» ብሎ ደቀ መዛሙርቱን አስጠነቀቃቸው፤ ማቴ. 18፥3:: ጳውሎስ ግን ወደ ኢየሩሳሌም ጉባኤ ሲሄድ ስለ «አሕዛብ መመለስ» መናገር ቻለ፤ ሐ.ሥ. 15፥3::

መመለስ ልዩ ልዩ ዐይነት ሊሆን ይችላል:: ብሔራዊ መመለስ አለ፤ ይህም እስራኤላውያን በአንድነት ከኀጢአታቸው ሲመለሱ፥ ብዙ ጊዜ በታሪካቸው ይታያል፤ ከዮናስ ስብከት የተነሣም የነነዌ ሕዝብ ከክፋታቸው እንደተመለሱ እናነባለን፤ ዮናስ 3፥5-10::

ጊዜያዊ መመለስ አለ፤ ይህም በተለይ በዘሪው ምሳሌ በጭንጫ መሬት ላይ በተዘራው ዘር ይታያል:: ሰዎች ቃሉን ሲሰሙ፥ ለጊዜው በደስታ ይቀበሉታል፤ በኋላ ግን መከራ ወይም ስደት ወይም ሌላ የማያስደስት ነገር ሲደርስባቸው፥ ወዲያውኑ ይሰናከላሉ፤ ማቴ. 13፥5-6:20-21:: ጳውሎስ በእምነት ነገር ስለጠፉት ስለ ሄሜኔዎስና ስለ እስክንድሮስ (1ጢሞ. 1፥19-20፤ 2ጢሞ. 2፥17-18)፥ ዓለምን ስለወደደው ስለ ዴማስ (2ጢሞ. 4፥10)፥ የአሁኑንም ጭምር በሐዘን ጽፏል:: ሐዋርያው ዮሐንስም፥ «... ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ፥ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ» በማለት አንዳንዶች ለጊዜው ምእመናን መስለው እንደታዩና ነገር ግን በእውነቱ እንዳልተመለሱ አሳየ፤ 1ዮሐ. 2፥19:: ክርስቶስም፥ የሰዎች ሕይወት መሠረት ስለማይታወቅ፥ አንድ ዐይነት ፈተና እስኪመጣባቸው ድረስ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የጸና የእምነት አቋም ያላቸውን ከሌላቸው ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን በዓለትና በአሸዋ ላይ በተሠሩት ቤቶች ምሳሌ ገልጧል፤ ማቴ. 7፥24-27:: ሰው እውነተኛ የክርስቶስ

ተከታይ ከሆነ በኀጢአት ቢወድቅም ሊመለስ ይችላል፤ ለምሳሌ ክርስቶስ ጴጥሮስን፥ «አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» አለው፤ ሉቃ. 22፥32።

የሥነ ልቡና ሊቃውንት ስለ ሰው መመለስና ስለ ሰው ሕይወት መለወጥ ብዙ ምርምር አድርገው ጽፈዋል። አንዳንድ ጊዜ ትምህርታቸው ከክርስቲያናዊው የመመለስ አሳብ ጋር ግንኙነት ይኖረዋል፤ በትምህርተ መለኮት ግን በእግዚአብሔር ኀይል ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መመለሳቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ማጥናት ዋና ተግባራችን ነው (1)።

ነገረ መለኮትን በተመለከተ መመለስ የሚለው ርእስ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ መመለሱ የሚጠናበት ርእስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ዐይነቱ መመለስ ብዙ ምሳሌዎችን ይሰጣል፤ ለምሳሌ ንዕማን (2ነገ. 5፥15)፥ ምናሴ (2ዜ.መ. 33፥12-13)፥ ዘኬዎስ (ሉቃ. 19፥8-9)፥ ሳምራዊቷ ሴት (ዮሐ. 4፥29:39)፥ ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው (ዮሐ. 9፥38)፥ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፥ ጳውሎስ፥ ቆርኔሌዎስና ልድያ (ሐ.ሥ. 8፥27-39፤ 9፥5-18፤ 10፥1-48፤ 16፥14) የታወቁ ናቸው።

በክርስቲያናዊ መመለስ ውስጥ በተለይ ሁለት የተያያዙ ክፍሎች አሉ፤ እነርሱም ንስሓ መግባትና ማመን ናቸው። እነዚህን ነጥቦች የንስሓና የእምነት ግንኙነት፥ የእውነተኛ ንስሓ ደረጃዎች፥ የእውነተኛ እምነት ደረጃዎችና እንደዚሁም ንስሓና እምነት የክርስቲያናዊ አኗኗር ባሕርያት መሆናቸው በሚሉት አርእስት እናጠናቸዋለን።

## ሀ) የንስሓና የእምነት ግንኙነት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ሲሰብክ፥ «ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ» በማለት የሰውን ትክክለኛ አጸፋ ገለጠ፤ ማር. 1፥15። ሐዋርያው ጳውሎስም የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲያሰናብት፥ «ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሓንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች...» በማለት ስለመሰከረ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኑን ተናገረ፤ ሐ.ሥ. 20፥20-26። አንዳንድ ጊዜ የወንጌል ጥሪ «ንስሓ ግቡ» የሚለው ብቻ ነው (ማቴ. 3፥2፤ ሐ.ሥ. 17፥30)፤ በሌላ ጊዜም ደግሞ «ንስሓ ግቡ፤ ተመለሱም» (ሐ.ሥ. 3፥19-20) የሚል ሆኖ ይታያል። በልዩ ልዩ ጊዜ ደግሞ «ታዘዙ» የሚለው ቃል አጸፋ ንስሓ በቃላት ደረጃ ሳይገኝበት «እመን» የሚል ብቻ ተጽፎ ይገኛል፤ ዮሐ. 3፥16፤ ሐ.ሥ. 16፥31፤ ሮም. 10፥9። እንግዲህ በአጸፋነት ንስሓ ብቻ ቢታዘዝም፥ እምነት አለበት፤ ምክንያቱም ንስሓ ወደ እግዚአብሔር መመለስ በመሆኑ፥ ሰው እግዚአብሔር እንዳለና ንስሓን እንደሚቀበል ካላመነ ንስሓ ትርጉም የለውም። እመን ብቻ ተብሎ ቢታዘዝም፥ ሰው በክርስቶስ የሚያምነው፥ በፊት ተስፋ ያደረገበት ነገር ከንቱ መሆኑን ተገንዝቦ ተስፋ ካደረገበት ከንቱ ነገር ወደ ክርስቶስ በንስሓ እንደተመለሰ ያሳያል። እንግዲህ ንስሓና እምነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው፤ አንዱ ካለ ሌላው አለ፤ አንዱ ያለ ሌላው ሊኖር አይችልም። በዚህ መሠረት ሉቃስ፥ በአቴና እግዚአብሔር «ንስሓ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዝዛል» በማለት ጳውሎስ እንደተናገረ በመጠቈሙ፥ በአቴናም ጳውሎስ ስላስገኘው የአገልግሎት ውጤት ሲጽፍ፥ «አንዳንዶች ወንዶች ግን ተባብረው አመኑ» በማለቱ ንስሓ መግባትና ማመን የተያያዙ መሆናቸውን አሳይቷል፤ ሐ.ሥ. 17፥30:34።

ስለ ሰው መመለስ በአመክንዮታዊ መንገድ ስናስብ፥ ሰው በመጀመሪያ ንስሓ ይገባል፤ ምክንያቱም ከነበረበት ሁኔታ ዘወር ብሎ ይመለሳልና በአዲስ አስተሳሰብ በመመራት በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናል። በሰው የመመለስ ተመክሮ አንዳንድ ጊዜ ለንስሓ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለእምነት ትኩረት ይሰጣል። ለምሳሌ በዘኬዎስ መመለስ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው ለንስሓው ነው፤ ሆኖም ክርስቶስን «ጌታ ሆይ» በማለቱ እንዳመነበት ግልጥ ነው፤ ሉቃ. 19፥8። በሌላ አንጻር በፊልጵስዩሱ የወህኒ ጠባቂ መመለስ ላይ ትኩረት የሚሰጠው ለእምነቱ ነው፤ ሆኖም የወህኒው ጠባቂ የጳውሎስንና የሲላስን ቍስል በማጠቡ ንስሓንም ጨምሮ ገለጠ፤ ሐ.ሥ. 16፥30-34።

## ለ) የእውነተኛ ንስሓ ደረጃዎች

ለወንጌል ጥሪ ሰው መጀመሪያ በሚሰጠው አጸፋ ውስጥ ንስሓ ያለውን ታላቅ ስፍራ መገንዘብ አለብን፤ አንዳንድ ሰዎች ንስሓን ያቃልሉታልና። ንስሓ መግባት በመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት (ማቴ. 3፥1-2)፥ በክርስቶስ ስብከት (ማቴ. 4፥17)፥ በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስብከት (ማር. 6፥12)፥ ጴጥሮስ ለአይሁድ ባቀረበው ስብከት (ሐ.ሥ 2፥38፤ 3፥19-20)፤ ጳውሎስ ለአይሁድና ለአሕዛብ በሰጠው ትምህርት (ሐ.ሥ 17፥30፤ 20፥20-21፤ 26፥20) እና ከሰማያት ለአምስቱ አብያተ ክርስቲያናት በተሰጠው የክርስቶስ መልእክት ውስጥ (ራእ. 2፥5:16:22፤ 3፥3:19) መሠረታዊና የመጀመሪያ ትእዛዝ ነበረ። የእውነተኛ ንስሓን ደረጃዎች ከመመርመራችን በፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሦስት አንቀጾችን ብንመለከት ሊረዳን ይችላል።

ሀ) ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ጸጸት የሌለበትን፣ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሓ ያደርጋልና፤ የዓለም ሐዘን ግን ሞትን ያመጣል» በማለቱ በእውነተኛ ንስሓና ባልተሟላ ንስሓ መካከል ያለውን ልዩነት አሳየ፤ 2ቆሮ. 7፥10። የዓለም ሰዎች በሚፈጽሙት ድርጊት እጅግ ሊያዝኑ ይችላሉ፤ ይህም ቅጣት በመፍራታቸው፥ ወይም ጥቅምን በማጣታቸው ወይም ድርጊቱ ተገቢ አለመሆኑን እንኳ በማወቃቸው ሊሆን ይችላል። ሐዘናቸው ግን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ ሞትን ያመጣል። ለዚህ ጕዳይ ዐይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ክርስቶስን አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው። ስለ እርሱ እንደሚከተለው ተጽፏል:- «በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፤ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌዎች መልሶ:- ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን:- እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ። ብሩን በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ»፤ ማቴ. 27፥3-5።

ለ) ንጉሥ ዳዊት በመዝሙር 51 ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የሚመጣ ሐዘንን በሰፊው ያብራራዋል። እዚህ ላይ በምንም ነገር ሳያመካኝ ክፋቱን ጕላ አድርጎ ይገልጠዋል።

በዚህ መዝሙር ዳዊት ያደረገውን መተላለፍ፥ በደል፥ ኀጢአትና ክፋት በሚሉት ቃላት ሲገልጠው (ቍ. 1-4)፥ ምንጩ ከአዳም የወረሰው ዐመፃ መሆኑን ያውቃል (ቍ. 5)። ይህን ሁሉ ሲል እግዚአብሔር ጻድቅና ንጹሕ መሆኑን ያስተውላልና ምንም እንኳ ሰውን በድሎ፥ «አንተን ብቻ በደልሁ» በማለቱ ዐመፃው ጻድቅና ንጹሕ በሆነው አምላክ ላይ እንደሆነ በትኩረት ያሳያል (ቍ. 4)። ይህም አምላክ እውነትን የሚወድድ፥ ጠቢብም ነውና ዳዊት አሁን በእውነትና በእግዚአብሔር ጥበብ መሠረት መራመድ ይፈልጋል (ቍ. 6)። ከዚህም ሁሉ ጋር ኀጢአቱ አደገኛ ነውና እግዚአብሔር እንዳይጥለውና መንፈስ

ቅዱስን ከእርሱ እንዳይወስድበት ይለምናል (ቊ. 11)። ስለዚህ «ማረኝ»፤ «መተላለፌን ደምስስ»፤ (ቊ. 7)፤ «ከኀጢአቴም ፊትህን መልስ፤ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ። አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ» (ቊ. 9-10) ብሎ ከልቡ ይጮኻል።

ዳዊት ይህን ጸሎት በጸለየ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው ነበርና ንስሓ በክርስቲያን እኗኗር ሁሉ አስፈላጊ መሆኑ ይታያል። እውነተኛ ንስሓ የሚገባ ሰውም የተሰበረ መንፈስና የተዋረደ ልብ እንደሚኖረው ተገልጧል (ቊ.17)፤ ምክንያቱም ኀጢአቱና ክፋቱ ይሰማዋልና ከእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት በስተቀር ምንም ተስፋ እንደሌለው ያውቃል፤ በሕይወቱም ለኩራት ስፍራ እንደሌለ ግልጥ ይሆንለታል።

ከንስሓ ጸሎት የተነሣ ዳዊት ኀጢአቱና በደሉ እንደሚደመሰስ (ቊ. 1:9)፥ እንደሚነጻ (ቊ. 7)፥ ንጹሕ ልብ እንደሚፈጠርለት (ቊ. 10)፥ ታዛዥ መንፈስ በውስጡ እንደሚኖረው (ቊ. 10:12) እና እንደገና በደስታ እንደሚሞላ (ቊ. 8:12) ያምናል። በዚህ መሠረት ለሕግ ተላላፊዎች የእግዚአብሔርን መንገድ ያስተምራል (ቊ. 13)፤ በእግዚአብሔር ጽድቅ ተደስቶ ምስጋናውን ያቀርባል (ቊ. 13-14) እና ኀጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ (ቊ. 13)። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የሚፈልገው መሥዋዕት ይሠዋል (ቊ. 16-19)።

ሐ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ታናሽ ልጅ ወደ አባቱ በተመለሰበት በማይረሳ ምሳሌ ንስሓ ምን እንደሆነ ገልጧል፤ ሉቃ. 15፥11-24። በዚህ ታሪክ ልጁ በተለይ ሁለት ርምጃዎችን ወሰደ፤ የመጀመሪያው፥ ልጁ ወደ ልቡ ተመለሰ (ልብ ገዛ፤ ስሕተቱን ተገነዘበ፤ ቊ. 17)፤ ሁለተኛው፥ ወደ አባቱ መጣ (ቊ. 20)። ማስተዋል ሲጀምር፥ ሁኔታውን በትክክል ተረዳ፤ በፊት የነቀፈውን የአባቱን ቤት ምቾትና ደስታ ተመኘና በደሉን ገልጦ ወደ አባቱ ተመልሶ ለመሄድ ወሰነ (ቊ. 17-19)። ወደ አባቱ በመጣ ጊዜ አባቱ ከፍ ባለ ደስታ ተቀበለው፤ እንደ ልጁ አከበረውና ታላቅ ደስታ ሆነ (ቊ. 20-24)። ክርስቶስ በዚህ ምሳሌ ሲያስተምር፥ ብዙ ጊዜ የሃይማኖት መሪዎች በኀጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር መመለስ ስለማይደሰቱ፥ ወይም እንዲመለሱ ስለማይፈልጉ ማስጠንቀቂያ ሰጠ (15፥25-32)።

እንግዲህ በእውነተኛ ንስሓ ሦስት ደረጃዎች አሉ ማለት ነው፤ እነዚህን ደረጃዎችና ውጤታቸውን ስንመረምር፥ በትምህርተ መለኮት በተለይ ሰው በመጀመሪያ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ዋናውን ትኵረት የምንሰጠው እንደሚከተለው ነው፦

**1. በአእምሮ ማስተዋል**

ሰው ንስሓ ሲገባ እውነተኛ ሁኔታውን በመጠኑ ያስተውላልና ወደ እግዚአብሔር በመመለስ በአዲስ ሁኔታ እንደሚኖር፥ በአዲስ መንገድ እንደሚራመድ፥ እንደዚሁም ለአዲስ ጌታ እንደሚታዘዝና አዲስ ተስፋና መድረሻ እንዳለው ያስተውላል። ዓለማውያን እንኳ ይህን በመጠኑ ሊያስተውሉት ይችላሉ፤ ሆኖም ባሉበት ሁኔታ ለመኖር ደስተኞች ናቸውና ሌሎች ከእነርሱ ጋር በኀጢአት አብረው ሲሳተፉ ሊደሰቱ ይችላሉ፤ ሮም 1፥32።

**2. በስሜት መስማማት**

ሰው ንስሓ ሲገባ ወደ እግዚአብሔር ከመመለስ ጋር በስሜት ይስማማል፤ ማለት የፊተኛውን ሁኔታና ኀጢአት ይጠላል፤ በሰው ላይ በሠራው ነገር ያዝናል፤ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን (በእግዚአብሔር መንገድ አለመሄዱን)

እንደ ታላቅ ኀጢአት ይቈጥረዋል፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ይደሰታል፤ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መሄድ እንደ ትልቅ መብት ይታየዋልና መልካምን ሥራ ማድረግ ይፈልጋል።

የአስቆሮቱ ይሁዳ ኀጢአቱን ዐወቀ፤ ስሕተቱን ተናግሮ ሠላሳ ብሩን መለሰ፤ ነገር ግን ስሜቱ ከክርስቶስ ጋር አልነበረምና ንስሓ በመግባት ፈንታ ራሱን ገደለ፤ ማቴ. 27፥3-5። አጋንንት ስለ እግዚአብሔር መጠነኛ ዕውቀት ሊኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን ስሜታቸው ወደ እግዚአብሔር ያዘነበለ አይደለም፤ ይንቀጠቀጣሉና፤ ማር. 1፥24፤ ያዕ. 2፥19። ኢየሱስ በዐጭር ጊዜ ውስጥ ከሁለት ሀብታም ሰዎች ጋር ተገናኘ። ሁለቱም ሁኔታቸውን ተረዱ፤ የመጀመሪያው ሀብቱን በመውደዱ ክርስቶስን ትቶ እያዘነ ሄደ፤ ሁለተኛው ማለት ዘኬዎስ ግን በደስታ ተቀበለው፤ ሉቃ. 18፥18-23፤ 19፥5-6።

### 3. በፈቃድ መወሰን

የወንጌል ትእዛዝ ንስሓ ግቡ የሚል ነው፤ ሐ.ሥ. 8፥22። ንስሓ በመግባት እውነትን ማወቅ (2ጢሞ. 2፥25) እና ጸጸት የሌለበት ሐዘን (2ቆሮ. 7፥10) አለ፤ ነገር ግን ሰው ኀጢአቱን እስኪናዘዝባትና እስኪተዋት ድረስ (ምሳ. 28፥13) ንስሓ አልገባም፤ ምሕረትንም አላገኘም። የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ለመመለስ ወሰነና ሄደ። ብዙ ሰዎች በእነርሱ አመለካከት ምቹ ጊዜ ባለመሆኑ፥ ወይም በይሉኝታ ወይም በሌላ ምክንያት በሁለት አሳብ መካከል ያመነታሉ። መወሰን ያስፈልጋቸዋልና ወስነው ትክክለኛውን ነገር ማድረግ አለባቸው። መጥምቁ ዮሐንስ፥ «እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» ብሎ ሕዝቡን አዘዘ፤ ሉቃ. 3፥8። ሐዋርያው ጳውሎስም በንጉሥ አግሪጳ ፊት፥ «... ለአሕዛብም ንስሓ ይገቡ ዘንድና ለንስሓ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ» ብሎ ስለ አገልግሎቱ ማብራሪያ ሰጠ፤ ሐ.ሥ. 26፥20። እንግዲህ ለእውነተኛ ንስሓ የአእምሮ ማስተዋልና የልብ ትክክለኛ ስሜት ብቻ በቂ ባለመሆናቸው፥ ድርጊትም ጭምር አስፈላጊ መሆኑን እናስተውላለን። ዋናው ነገር ወደ እግዚአብሔር ዘወር ማለት ነው፤ ሆኖም ለአንዳንድ ሰዎች በልዩ ልዩ ሁኔታ ከሰው ይቅርታ አስቀድሞ መጠየቅ አስፈላጊ ይሆናል፤ ማቴ. 5፥23-24።

በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን ንስሓ እንዲገቡ ልዩ ልዩ ሥርዐቶች ተደንግገዋል። በእነዚህ ሥርዐቶች ውስጥ ለኀጢአት ማዘን፥ ኀጢአትን መናዘዝ፥ ለኀጢአት የሚገባውን ዋጋ መስጠትና መፍታት ዋና ዋና ክፍሎች ናቸው (2)። በሥርዐቱ የሚደረገው ሐዘን ስለ ውርስ ኀጢአት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ መተላለፍ፥ የቤተ ክርስቲያንንም ሥርዐቶችና ደንቦች ስላለመፈጸም ነው። ሰው ለኀጢአቱ የሚገባውን ዋጋ እንዲሰጥ ቁሱ ቀኖናን ይሰጠዋል፤ ይህም ብዙ ጊዜ በተግባር ለመተርጐም የማያስደስት ወይም የሚያስቸግር ሆኖ ይታያል። አስቸጋሪ ቢሆንም፥ በዚህ መሠረት ሰው ከኀጢአቱ የተፈታ መሆኑ ይነገራል። ለኀጢአተኞች፥ በተለይም በኀጢአታቸው ምክንያት የኅሊና ዕረፍት ለማያገኙ «የነፍስ አባቶች» ወይም «የአማካሪዎች» ወይም «የመጋብያን» በየቤተ ክርስቲያኑ መገኘት አስፈላጊ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ። በብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ለእነዚህ ሰዎች የተለየ ሥርዐት ተደንግጓል። ሆኖም ጥቂቶች ያይደሉ በተለይ ንስሓን በሚመለከት በእንደዚህ ዐይነቱ ሥርዐት ላይ ጥያቄዎች አሏቸው፤ ለምሳሌ፥ በሐዋርያት ሥራ ወይም በመልእክታት ውስጥ እንደዚህ ዐይነቱ ሥርዐት ስለ መኖሩ ምን ፍንጭ አለ? ሰው ወደ ነፍስ አባቱ ሄዶ ስሕተቱን መናገሩና ቀኖናውን መቀበሉ በእውነት ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲል ይረዳዋልን? ይህ ሥርዐት ሰውን ከክፉ

አሳብ፥ ከትዕቢት፥ ከፍትወትና ከሌላ የልብ ኀጢአት ሁሉ እንዲገታ ያደርጋልን? የልብ ቅድስናን በሕይወቱ ለማሳደግስ ይረዳዋልን? ይህ ዐይነቱ ሥርዐት እውነተኛ ንስሓን ከሚሰጠው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ምን ዐይነት ግንኙነት አለው? ሥርዐቱ ሰውን ወደ አስታራቂው ወደ ክርስቶስ ይመራዋልን?

#### 4. የእውነተኛ ንስሓ ምልክቶች

መጥምቁ ዮሐንስ፥ «ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አድርጉ» ብሎ ካዘዘ በኋላ ሕዝቡ፥ ቀራጮቹና ወታደሮች «ምን እናድርግ?» ብለው ሲጠይቁት፥ እንደየሁኔታቸው ትእዛዝ ሰጣቸው፤ ሉቃ. 3፥8:10:: ዛሬም ሰው ንስሓ ሲገባ እንደየሁኔታው ሦስት ነገሮች ሊታዩበት ይጀምራሉ (3):-

#### ሀ) በኀጢአት ላይ ያለ አዲስ አመለካከት

የእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን ስለ ኀጢአቱ ለመውቀሥ ሲጀምር፥ ብዙ ጊዜ በአንድ ኀጢአት ላይ ያተኩራል:: ሰውም ንስሓ ሲገባ፥ ስለ ሠራው ኀጢአት ያዝናልና ያንኑ ኀጢአት እንደገና እንዳይሠራ ጥረት ያደርጋል:: ከዚያም በላይ ንስሓ ከመግባቱ በፊት በጠቅላላ ሕይወቱ ኀጢአት እንደነበረበት ስለሚያስተውል፥ በሚያደርገው ሁሉ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ይረዳል:: ይህ ሲሆን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ መፈጸም ስላለበት፥ አንዳንድ ነገሮችን መተውና አዳዲስ ነገሮችን ማድረግ እንደሚገባው ያውቃል:: ከዚህም በላይ በሕይወቱ አንድ የተለየ ነገር ከእግዚአብሔር ቍጥጥር ውጭ የተፈጸመ መሆኑን ሊያስተውል ይችላልና ንስሓ መግባት ይህን የኀጢአተኛነት ሁኔታ ይዳስሳል:: ይህ ሁኔታ ኀጢአት እንዳይሆንበት ነገሩን ፈጽሞ መተው ወይም በጉዳዩ ላይ ያለውን አመለካከት መለወጥ የግድ አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ፥ ሀብታሙ ወጣት ሀብቱን ፈጽሞ መተውና ክርስቶስን መከተል ነበረበት፤ ሌላው ሀብታም ዘኬዎስ ግን ከሀብቱ እኩሌታውን ለድኾች ጥቅም በመተውና በሕገ ወጥ መንገድ የወሰደውን በዕጥፍ በመመለስ የቀረውን በእርሱ ቍጥጥር ማድረግ ኀጢአት አለመሆኑን ተረዳ፤ ሉቃ. 18፥22፤ 19፥8:: ይህ አዲስ አመለካከት ደግሞ በሕይወት ዘመን ሁሉ የሚታይ እንጂ አንድ ጊዜ ብቻ ተከሥቶ የሚጠፋ አይደለም::

#### ለ) በራስ ላይ ያለ አዲስ አመለካከት

ሰው ንስሓ ሲገባ፥ አስቀድሞ በራሱ በመኩራራትና ራሱን ከፍ ከፍ በማድረግ ፈንታ የተሰበረ መንፈስና የተዋረደ ልብ ሊኖረው ይጀምራል፤ መዝ. 51፥17፤ ማቴ. 5፥3:: አንድ ሰው ንስሓ ሲገባ ራሱን ይክዳልና መስቀሉን ዕለት ዕለት ተሸክሞ ክርስቶስን ይከተላል፤ ሉቃ. 9፥23:: ይህን የሚያደርገውም የራሱን ኑሮ ርግፍ አድርጎ በመተው ሳይሆን፥ «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር» ገፍፎ በመጣልና የሚታደሰውን «አዲሱን ሰው» በመልበስ ነው፤ ቆላ. 3፥9-10፤ ኤፌ. 4፥22-24:: እውነት ነው፤ «ሥጋ በመንፈስ ላይ፥ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ» ስለሚል፥ አዲሱ ሰው የሚወደውን ማድረግ አይችልም፤ ገላ. 5፥17:: ከባድ ትግል አለና አሸናፊ እንዲሆን ንስሓ የሚገባ ሰው «ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር» ሰቅሏል (ገላ. 5፥24)፤ ይህም አዲሱ ሰው «ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ» አንድንም ነገር አያስብም፤ አያደርግምም ማለት ነው፤ ሮም 13፥14::

እንግዲህ በአንድ በኩል ክርስቲያን ለኀጢአት እንደሞተና በክርስቶስ ለአዲስ ሕይወት እንደተነሣ ራሱን ይቈጥራል:: በሌላ በኩል ግን ይህ ለውጥ ገና ፍጹምና የተሟላ አለመሆኑን ያውቃል:: ስለዚህ ይህ ትግልና

የሚያስከትለው ለውጥ በአዲሱ ሰው ሕይወት በሚታዩት ባሕርያት መካከል እስከ ሞት ድረስ አንድ ሆነው ይታያሉ፤ እነዚህን አሳቦች በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመረምራቸዋለን::

ሐ) በእግዚአብሔር ላይ ያለ አዲስ አመለካከት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእስራኤልን ሰዎች፥ «... ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ» ብሎ ደጋግሞ አስጠንቀቃቸው፤ ሉቃ. 13፥1-5:: ንስሐ የሚገባ ሰው ከዚህ ቃል በስተ ጀርባ የተሰፋ ቃል እንዳለ ያስተውላል፤ ይኸውም ንስሐ የሚገባ ሰው ይቅርታን የሚቀበል፥ የማይጠፋ የዘለዓለም ሕይወትንም የሚያገኝ መሆኑን ነው:: እግዚአብሔር መሐሪ ነውና ዳዊት፥ «አቤቱ ኀጢአትንስ ብትጠባበቅ፥ አቤቱ ማን ይቆማል? ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና» ብሎ ጻፈ፤ መዝ. 130፥3-4::

እግዚአብሔር የኀጢአትን ስርየት የሚሰጠው በንስሐ መንገድ ነው (ሐ.ሥ. 2፥38፤ 3፥19-20)፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ይህን (ክርስቶስን) እግዚአብሔር ለእስራኤል ንስሐን የኀጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ ራስም (መሪም) መድኀኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው» በማለቱ ንስሐ ወደ ኀጢአት ስርየት መምራቱን እንደ ይቅርታ ንስሐ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን፥ ይህ ስጦታ በመንግሥተ ሰማያት በከበረው በክርስቶስ መሰጠቱና ክርስቶስ በአብ ቀኝ በመቀመጡ ለሰው የሚሰጠው ንስሐ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጥ መሆኑን እናስተውላለን፤ ሐ.ሥ. 5፥31፤ ደግሞም 2፥33 ይመ.:: ሰው ንስሐ ይገባል፤ ሆኖም ይህን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ለማድረግ በመቻሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና፥ የእስራኤል ምእመናን በቆርኔሌዎስ ቤት የሆነውን በሰሙ ጊዜ፥ «እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ» ተብሎ ተጽፏል፤ ሐ.ሥ. 11፥18::

እንግዲህ ሰው ንስሐ የሚገባው በመዳኑ ስለሆነ፥ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ይሰጣል:: ከትምህርተ መለኮት አንጻር ደግሞ ንስሐ የዳግም ልደት ፍሬና ከእምነት ጋር የተያያዘም እንደሆነ እናስተውላለን::

ሐ) የእውነተኛ እምነት ደረጃዎች

እምነት የሚለው ቃል እንደየሁኔታው እጅግ የተለያዩ አሳቦች ሊኖሩት ይችላል:: አንድ ሰው፥ «እምነቴ እንደዚህ ነው» ቢል፥ የሚገልጠው የራሱን አሳብ ነው፤ አሳቡ የግል አሳብ ስለሆነ ምናልባት ሌላ ሰው ይህ ዐይነቱ አሳብ አይኖረውም፤ እንደዚህ ዐይነቱ ግላዊ አሳብ ይልቁንም ከቋሚ ነገር ጋር የተያያዘ ላይሆን ይችላል፤ በመጨረሻም መሠረት የሌለው የሰው ስሜት ሆኖ ይገኛል::

ሌላ ሰው ስለ እምነቱ ቢናገር፥ እምነቱ የተመሠረተው በሌሎች ሰዎች እምነት፣ በመጽሐፍ በተጻፈ ትምህርት ወይም በራሱ ተመክሮ ላይ ይሆናል:: የዚህ ዓለም ሃይማኖቶች፥ እንደዚሁም የጥንቴላ ትምህርትና ሥርዐት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሰው እምነቶች ይሆናሉ:: ሰዎች በዚህ መንገድ በማመን እንደየእምነታቸው መጠን ትምህርተ ሃይማኖታቸውን ሊከተሉ ይችላሉ::

የክርስትና ሃይማኖትን በተመለከተ ልዩ ልዩ ዐይነት እምነት ሊገኝ ይችላል:: ለምሳሌ፥ 1) የታሪክ እምነት:- ማለት ሰዎች የአዳምን፥ የአብርሃምን፥ የሙሴን በተለይም የክርስቶስን ታሪኮች ያምናሉ፤ 2) ጊዜያዊ እምነት:- ማለት

ሰዎች ለጊዜው ያምናሉና ክርስቲያኖች የሆኑ ይመስላሉ፤ በኋላ ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ይተዉታል፤ ማር. 4፥5-6:16-17፤ 1ዮሐ. 2፥19:: 3) የተአምር እምነት፦ ማለት ሰዎችን ክርስቶስ ሲፈውሳቸው ያምናሉ፤ ከእነዚህም ብዙዎቹ ከተፈወሱ በኋላ ክርስቶስን ይከተላሉ፤ ከምእመናንም ጋር ይተባበራሉ፤ ማር. 10፥52፤ ሐ.ሥ. 3፥8፤ 4፥14:: 4) የሚያድን እምነት፦ ማለት በሰው ልብ ውስጥ በሚከናወነው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሚገኘው ዳግም ልደት የተነሣ፥ ሰው በወንጌል እውነት እያመነ ለድኅነት ያለውን ተስፋ በክርስቶስ ላይ ብቻ ያደርጋል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አብርሃምን የእውነተኛ አማኝ ምሳሌ አድርገው ቈጠሩት:: ክርስቶስ፥ «አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፤ አየም፤ ደስም አለው» ብሎ መሰከረለት፤ ዮሐ. 8፥56:: ጳውሎስና ያዕቆብም፥ «አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት» ብለው ኦሪት ዘፍጥረት 15፥6ን በመጥቀስ የእውነተኛ እምነትን ሁኔታና ውጤት አብራሩ፤ ሮም 4፥3-5፤ ገላ. 33፥6-14፤ ያዕ. 2፥21-23:: የዕብራውያን ጸሐፊም የአብርሃምን እምነት ጕላ አድርጎ ገለጠው፤ ዕብ. 11፥8:: አማኞች ሁሉ የአብርሃም እውነተኛ ልጆች ናቸው፤ ሮም 4፥12፤ 16፥17፤ ገላ. 3፥9:29:: በትንቢተ ዕንባቆም ውስጥ የሚገኘው፥ «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው መሠረታዊ የድኅነት ሐቅም በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ይገኛል፤ ዕን. 2፥4፤ ዮሐ. 3፥36፤ ሮም 1፥17፤ ገላ. 2፥16፤ 3፥11-12፤ ዕብ. 10፥38፤ 1ዮሐ. 5፥10-12:: እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት እምነት የድኅነት ቋሚ መሣሪያ ነውና ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ «ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ፥ እግዚአብሔር እንዳለ፥ ለሚፈልጉት ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና»፤ ዕብ. 11፥6::

እምነት ለክርስቲያን በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፥ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እምነትን እንደየአንባቢዎቻቸው ሁኔታ በሚከተለው አኳኋን ይገልጡታል (4)፦

ሀ) ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ፥ ሰዎች ወደ ኢየሱስ ሲቀርቡ በእርሱ ያላቸውን እምነት በልዩ ልዩ መንገድ ያሳያሉ፤ ክርስቶስም በእምነታቸው ላይ ሐተታ ሰጥቷል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚፈወሱት ሰዎች ለምሳሌ፥ ደም ለሚፈሳት ሴት እምነትሽ አድኖሻል (ማቴ. 9፥22)፤ ለሁለት ዕውሮች እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ (ማቴ. 9፥29)፤ ለከነዓናዊቷ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው (ማቴ. 15፥28)፤ ለዕውሩ በርጤሜዎስ እምነትህ አድኖሃል (ማር. 10፥52)፤ ከዐሥሩ ለምጻሞች ወደ እርሱ ተመልሶ ለመጣው ሳምራዊ እምነትህ አድኖሃል (ሉቃ. 17፥19) በማለቱ የእርሱ ኀይል ቢፈውሳቸውም፥ እምነታቸው ከክርስቶስ ኀይል ጋር መገጣጠሙን አሳየ:: ባደገበት በናዝሬት ግን ሕዝቡ ባለማመናቸው ክርስቶስ ተደነቀ፤ ማር. 6፥5-6::

የተፈወሱት ሰዎች ከኀጢአታቸውም ጭምር ድነዋል? የሚል ጥያቄ ሊመጣ ይችላል:: በአይሁድ ዘንድ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ፈውስ መካከል ብዙ ልዩነት የነበረ ላይመስለን ይችላል:: አራቱ ሰዎች የተሸከሙትን ሽባ ሲያመጡለት፥ ከመፈወሱ በፊት ክርስቶስ፥ «እምነታቸውን (ይህም አራቱንና ሽባውን ሊያመለክት ይችላል) አይቶ ሽባውን፦ አንተ ልጅ ኀጢአትህ ተሰረየችልህ አለው»:: ከዚያም በኋላ፥ «አንተን እልሃለሁ፤ ተነሣ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ» በማለት ሥጋዊው ፈውስ የመንፈሳዊው ፈውስ ማረጋገጫ መሆኑን አስተማረ፤ ማር. 2፥1-12:: ክርስቶስ ኀጢአተኛ ስለነበረችዋና እግሩን

ሽቱ ስለቀባችዋ አንዲት ሴት፥ «እጅግ ወዳለችና ብዙው ኃጢአትዋ ተሰርዮላታል» ብሎ በመመስከር፥ ፍቅሯ የምስጋና ውጤት መሆኑን ሲያሳይ፥ «እምነትሽ አድኖሻል በሰላም ሂጂ» በማለትም የኀጢአት ይቅርታ በእምነት መንገድ የሚገኝ መሆኑን አረጋገጠ፤ ሉቃ. 7፥36-50:: የበርጤሜዎስ ታሪክም የአንድ ዕውር ፈውስ ታሪክ ብቻ የሚገኝበት አይመስልም፤ እርሱ «የዳዊት ልጅ ሆይ» ብሎ በኢየሱስ ፊት በመጮኹ፥ በኢየሱስ ጽኑ እምነት እንዳለው ሰው ሆኖም፥ «ጌታ ሆይ» በማለት ስለጠራው፥ ክርስቶስ የእስራኤል መሲሕ መሆኑን እንዳመነ ማሰብ አይከብድም:: ኢየሱስም «እይ እምነትህ አድኖሃል» ሲለው በማየቱ ይህ የመዳኑ ማረጋገጫ የነበረ ሊመስለን ይችላል፤ ሉቃ. 18፥35-43::

የአንድ በሽተኛ ልጅ አባት፥ «አምናለሁ አለማመኔን ርዳው» (ማር. 9፥24) በማለቱና ኢየሱስ ኢያኢሮስን፥ «አትፍራ፤ እመን ብቻ ትድንማለች» (ሉቃ. 8፥50) ብሎ ያደፋፈረበት ሁኔታ እምነት ብዙ ጊዜ ትግል ያለበት መሆኑን ያሳያል:: ክርስቶስ ስለ እምነት ሁኔታ ሲያስተምር፥ «የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ:- ከዚህ ወደዚያ ዕለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም» (ማቴ. 17፥20) እና «እምነት ቢኖራችሁ፥ ባትጠራጠሩም... ይህን ተራራ እንኳ:- ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፤ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» (ማቴ. 21፥21) በማለቱ የእምነት ኀይል የሚገኘው እምነትን በሚሰጥ በእግዚአብሔር እንጂ በሚያምነው ሰው አለመሆኑን እናያለን:: እንግዲህ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ቀርቦ ለሁሉም በእርሱ ማመን አለበት::

ለ) ዮሐንስ በወንጌሉ እምነት በክርስቶስ በመሆኑ ላይና በተለይም መንፈሳዊ በረከት በክርስቶስ በመሆኑ ላይ ያተኩራል:: ለምሳሌ፥ ክርስቶስ እንደሚከተለው የተናገረ መሆኑን ጽፏል:-

- «እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁ» (ዮሐ. 8፥24)፤

- «አንተ እንደላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ» (ዮሐ. 11፥42)፤

- «እኔ በአብ እንዳለሁ፤ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» (ዮሐ. 14፥11)፤

- «ከእግዚአብሔር ዘንድ እኔ እንደወጣሁ ስላመናችሁ፥ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና» (ዮሐ. 16፥27)፤

- «... ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል» (ዮሐ. 20፥31)::

ዮሐንስ የተለያየ እምነት እንዳለ ዐወቀ:: በኢየሩሳሌም ሰዎች ክርስቶስ ያደረጋቸውን ምልክቶች በማየታቸው፥ «በስሙ አመኑ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር... አይተማመናቸውም ነበር»፤ ዮሐ. 2፥23-25:: ኒቆዲሞስም፥ «መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን» ሲለው፥ ክርስቶስ ዳግመኛ መወለድና በመስቀሉ ትርጉም ማመን አስፈላጊ መሆኑን አስረዳው፤ ዮሐ. 3፥1-16:: እንደዚሁም አንድ ሹም ልጁ በመታመሙ ወደ ኢየሱስ ሲሄድ፥ እምነቱ ክርስቶስ ሰውን እንደሚፈውስ ከማመን (ዮሐ. 4፥46-47)፥ በክርስቶስ ቃል ወደ ማመን (4፥48-50) እና ከቤተሰዎቹ ሁሉ ጋር ክርስቶስን ወደ ማመን (4፥51-53) አደገ::

በዚህ ወንጌል ውስጥ እምነት በብዙ መንገድ ተብራርቷል። እምነት፦ ክርስቶስን በመቀበል (1፥12)፥ ወደ እርሱ በመመልከት (3፥14-15)፥ ወደ እርሱ በመሄድ (6፥35:37፤ 7፥37)፥ በመብላት (6፥35:51:53-54) እና በመጠጣት (6፥35:53-54፤ 7፥37) ምሳሌዎች ተገልጧል። እውነተኛ እምነት ሰው ተቀምጦና ዝም ብሎ የሚቀበለው ሳይሆን፥ የሚፈጽመውና የሚሠራው መሆኑ በእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ በተቀመጡ ግሶች ይታያል።

በዚህ ወንጌል ሐዋርያው ዮሐንስ «ማመን» በሚለው ግስ ዘጠና ጊዜ በመጠቀሙ ክርስቲያናዊ እምነት ከሁሉም ቀድሚያ እንዳለውና ታላቅም እንደሆነ ይታያል፤ ምክንያቱም ሰው በእምነት መንገድ ከሞት፥ ከፍርድና ከጥፋት ድኖ የዘለዓለም ሕይወት ይኖረዋል፤ ዮሐ. 3፥16-18:36፤ 5፥24።

ሐ) የሐዋርያት ሥራ ትምህርት ስለ እምነት በወንጌላት የተሰጠውን ትምህርት ተከትሎ ይቀጥላል። ሐዋርያው ጴጥሮስ በእናቱ ማሕፀን ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ አርባ ዓመት ዐንካሳ ሆኖ የኖረው ሰው በኢየሱስ ስም ሲያምን መፈወሱን ተናገረ፤ ሐ.ሥ. 3፥16። በሐዋርያት ሥራ ሰዎች ከኀጢአታቸው የሚድኑት በክርስቶስ በማመን ነው (13፥39፤ 16፥30፤ 26፥17-18)፤ እግዚአብሔርም የሰውን ልብ የሚያነጻው በእምነት መንገድ ነው፤ 15፥9።

የወንጌል ተከታዮች «እምነት» እና «አመነ» በሚሉት ቃላት በሐዋርያት ሥራ ይታወቃሉ። «ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት (ለእምነት) የታዘዙ ሆኑ»፤ ምእመናን፥ «በሃይማኖት (በእምነት) ጸንተው እንዲኖሩ» እና «እግዚአብሔር... ለአሕዛብም የሃይማኖትን (የእምነትን) ደጅ እንደከፈተላቸው» እናነባለን፤ 6፥7፤ 14፥22:27። በዚህ ምዕራፍ አመነ/አመኑ ሲባል ሰው ወይም ሰዎች በክርስቶስ አመነ/አመኑ መባሉ ነው፤ 2፥44፤ 4፥4:32፤ 14፥1፤ 17፥12:34። አመነ የሚለው ግስ ብዙ ጊዜ እውነተኛ አማኞችን ሲያመለክት፥ አንዳንድ ጊዜ እንደ ሲሞን የልብ ለውጥ ያልታየባቸውን (8፥13)፥ በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁትን ደቀ መዛሙርት (19፥1-3) ወይም የጨለማ ሥራን ያልተዉትን አማኞች (19፥17-19) ሊያመለክት ይችላል።

ሰዎች የሚያምኑት ከእግዚአብሔር ሥራ የተነሣ ነው። ይህም የሚሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነው (15፥11)፤ ሰዎች በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት «ለዘለዓለም ሕይወት» ተዘጋጅተው ወደ እምነት ይደርሳሉ፤ 13፥48።

ወንጌል ሲስፋፋ ስለ እምነት ሁኔታና ሥራ ልዩ ልዩ ትምህርትና ጥያቄ ተነሣ፤ ስለዚህም ጉዳይ ሐዋርያት በመልእክቶቻቸው ጽፈዋል።

መ) ያዕቆብ ባገለገለበት ዘመን የነበሩ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስት እምነት ባለቤት ለመሆን ትምህርቱን መቀበል ብቻ በቂ የሆነ መሰላቸው። ይህ እምነት ግን ተፈላጊው ሥራ አይታይበትም ነበርና በዚህ ምክንያት እንደዚህ ዐይነቱ እምነት የሞተ ነው፤ ትክክለኛ እምነትም አይደለም፤ ያዕ. 2፥18-26። ስለ እምነት ያዕቆብ የሰጠው ትምህርት ሐዋርያው ጳውሎስ ከሰጠው ትምህርት የተለየ አይደለም፤ ሆኖም ያዕቆብ ከሚያገለግልበት ሁኔታ የተነሣ እውነተኛ እምነት ሥራን አስከትሎ መገለጥ የሚገባው በመሆኑ ላይ አተኰረ።

ሠ) ሐዋርያው ጳውሎስ በተለይ በአይሁድ መካከል ሲዘዋወር፥ ስለ ሕግ ያላቸውን አሳብ መቃወም ግድ ሆነበት። «ሕጉ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» ብሎ ጻፈ፤ ሮም 7፥12። «በዕውቀት አይቅኑ

እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና፡፡ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ፥ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም፡፡ የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና» ብሎ ከአይሁድ ጋር ያካሄድ የነበረውን ከባድ ትግል ገለጠ፤ ሮም 10፥2-4፡፡

በዚህ ምክንያት ጳውሎስ በመልእክቶቹ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትንና ጽድቅን የሚያገኘው በእምነት ብቻ እንደሆነ በአጽንዖት አስገነዘበ (ሮም 3፥20-22:28፤ 4፥5፤ ገላ. 2፥16፤ 3፥11፤ ፊል. 3፥9)፤ ከዚህም የተነሣ ሰው በጸጋ መጽደቁን አስተማረ፤ ሮም 3፥24፤ 4፥16-17፤ 11፥6፤ ገላ. 5፥4፡፡ በዚህ ትምህርት ላይ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ሰፊ ልዩነት እንዳለ የታወቀ ነውና በሚቀጥለው ምዕራፍ በዝርዝር ልንመረምረው እንሞክራለን፡፡

ረ) የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፥ ሰው በክርስቶስ ማመን ይገባዋል፤ «ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል»፤ ሰው በእምነቱ የጽድቅ ወራሽ ይሆናል በማለት አስተማረ፤ ዕብ. 10፥38፤ 11፥7፡፡ ጸሐፊው ሰዎች ተስፋ ቢስ ሆነው ከእምነት ወጥተው ወደ ይሁዲነት እንዳይመለሱ አስጠነቀቃቸው፡፡ ይህንም ሲያደርግ የእምነትን ኀይል እንደሚከተለው አሳሰባቸው:- «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው»፤ 11፥1፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች በየዘመኑ አሸናፊዎች መሆናቸውን ጸሐፊው በሰፊው ገልጧል፤ 11፥2-40፡፡ ሰዎች ከሚታየው ወደማይታየው፥ ከአሁኑ ወደሚመጣው፥ ከጊዜያዊው ወደ ዘለዓለማዊው በእምነት አሳባቸው እንዲያተኩር በማድረግ፥ መከራቸውን እንዴት መታገሥ እንደሚችሉም አሳይቷል፡፡

ሰ) ሐዋርያው ጴጥሮስ ለተሰደዱ ክርስቲያኖች ሲጽፍ፥ እምነታቸውን በመንግሥተ ሰማያት በሚያገኙት ክብር ላይ አድርገው በተስፋ መከራቸውን እንዲታገሡ አደፋፈራቸው፤ 1ጴጥ. 1፥3-5፡፡ በሁለተኛ መልእክቱም አንባቢዎቹ በልዩ ልዩ የስሕተት ትምህርት እንዳይጠመዱ እምነታቸውን አጽንተው በመያዝ ላይ ያተኩራል፤ 2ጴጥ. 1፥12፤ 3፥14-18፡፡

ሸ) ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቶቹ ግኖስቲካዊ አሳቦችን ሲቃወም፥ ሰው የወንጌልን ትምህርት በማመን (1ዮሐ. 4፥16)፥ ሰፋ ባለው በረከት በዚህ ዓለም ተደስቶ እንደሚኖር በሚመጣው ዓለምም ወደ ዘለዓለማዊ ብፅዕና እንደሚገባ ያስተምራል፡፡ በግኖስቲካዊ አስተሳሰብ መሠረት ልዩ በሆነውና ከፍ ባለው ዕውቀት ሰው ወደዚህ ሁኔታ መግባት አይችልም፡፡ ከዚህም በኋላ ዮሐንስ በማመንና በማወቅ (1ዮሐ. 4፥16፤ 5፥13)፥ በማመንና በመታዘዝ (1ዮሐ. 3፥23)፥ በማመንና ርግጠኛ በመሆን (4፥15፤ 5፥13-15) መካከል ቅርብ ትስስር እንዳለ ያስተምራል፡፡

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እምነት የሚሰጠው ትምህርት በልዩ ልዩ ሁኔታዎች እንደሚገለጥ የተገነዘብን በመሆናችን፥ የእውነተኛ እምነትን ደረጃዎች እንደሚከተለው ማቅረብ እንችላለን:-

*1. አእምሮታዊ ዕውቀት*

አንዳንዶች እንደሚያስቡት እውነተኛ እምነት ሰው በፈጣሪው እንደሚደገፍ የሚገለጥበት ማንኛውም ዐይነት አሳብ ወይም ስሜት አይደለም፡፡ እውነተኛ እምነት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ክርስቶስ፥ ስለ ሰውም ኀጢአታዊ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን መቀበል ነው፡፡ ሰው ይህን እንዲያውቅ በአንድ በተወሰነ መንገድ መስማት ያስፈልገዋል፤ ሮም 10፥14:17፡፡

ሰው እምነት እንዲኖረው የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ሁሉ መስማትና ማወቅ አይጠበቅበትም፤ ነገር ግን ኀጢአተኛ መሆኑን፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ለሰው ኀጢአት መሞቱንና ከሙታን መነሣቱን ማወቅ አለበት፤ 1ቆሮ. 15፥3-4።

ሊበራሎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ቢያውቁም፥ አያምኑበትም። ለምሳሌ፥ የታወቀው ሊቅ ሩዶልፍ ቡልትማን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሰፊው የሚያውቅ ቢሆንም፥ ኢየሱስ ከድንግል መወለዱን፥ ተአምራትን ማድረጉን፥ የኀጢአት መሥዋዕት ሆኖ በመስቀል ላይ መሞቱንና ከሙታን መነሣቱን አላመነም (5)። የእምነት ዕውቀት «ትምህርት»ን ማወቅ ሳይሆን፥ ትምህርቱ እውነት መሆኑን ማመን ነው። ሊበራሎች ግን ለአእምሮአቸው የሚመቸውን ወይም የሚያስደስተውን ተቀብለው ለማመን «ሙከራ» እንደሚያደርጉ ሊናገሩ ይችላሉ።

ሮበርት ሰንድማንን (1718-1771) የመሳሰሉት ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ቢወዱትም፥ እውነተኛ እምነት እውነትን ዐውቆ ማመን ብቻ እንደሆነ አስተምረዋል (6)። የሚያድን እምነት የወንጌልን ትምህርት ዐውቆ እውነት መሆኑን ማመን ነው፤ ቢሆንም ይህ የእውነተኛ እምነት መጀመሪያ ደረጃ ብቻ ነው።

2. ስሜታዊ ስምምነት

ያዕቆብ፥ «እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ፤ ይንቀጠቀጡማል» በማለት ሰው እንዲድን ተገቢ በሆነ ስሜት እውነትን መቀበል አስፈላጊ መሆኑን አሳይቷል፤ ያዕ. 2፥19። የክርስቶስ ወንጌል እውነት መሆኑን ማመን ትልቅ ነገር ነው፤ ሆኖም ሰው ወንጌልን ሲሰማ፥ ይህ እውነት ነው፤ ወንጌል እንደዚህ መሆን አለበት፤ ከወንጌል የተነሣ ምን ማድረግ አለብኝ ሊልና ደስ ሊሰኝበትም ያስፈልጋል።

ብዙ ሰዎች፥ የቤተ ክርስቲያንም አባላት ሳይቀሩ እውነቱን እንደ እውነት የሚያምኑበት ቢመስሉም፥ በትክክለኛ ስሜት አይቀበሉትም። ኒቆዲሞስና ወዳጆቹ በክርስቶስና በሥራው ቢደሰቱም፥ ከነበራቸው ሃይማኖታዊ ማዕርግና ሥልጣን የተነሣ ፍጹም ለውጥ ለእነርሱ አስፈላጊ መሆኑን እስኪቀበሉ ድረስ ከባድ ትግል ነበረባቸው፤ ዮሐ. 3፥1-12። ጳውሎስ ፊልክስን ማመን እንዳለበት አሳሰበው፤ ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት፥ ስለሚመጣውም ኩነኔ እየነገረው ሳለ ፊልክስ ፈራ፤ ምክንያቱም ፊልክስ የጳውሎስን ትምህርት ቢቀበልና ወንጌልን ቢከተል፥ የግል አኗኗሩን መተዉ አስፈላጊ መሆኑን ተረዳ፤ ሐ.ሥ. 24፥24-26። ንጉሥ አግሪጳ የነቢያትን ትምህርት ቢቀበልም፥ ምናልባት በፖለቲካ ምክንያት ቃላቸውን ጠብቆ ለመከተል ፈቃደኛ አልነበረም፤ ሐ.ሥ. 26፥26-29። ሀብታሙ ወጣት የክርስቶስን ጥሪ መቀበል ያልቻለው ባለማመኑ ሳይሆን፥ ሀብቱን ትቶ እርሱን ለመከተል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነበር፤ ሉቃ. 18፥21-23። ለጌታ ኢየሱስ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ አንድ ጸሓፊ እውነትን ዐውቆ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቀ እንዳልነበረ ተነግሯል፤ ይሁን እንጂ ከማመን ምን እንደከለከለው አልተገለጠም፤ ማር. 12፥28-34። በርጤሜዎስና ዘኬዎስ ግን የአገራቸው ባህልና ልማድ ሳይጕትታቸው፥ ክርስቶስንና መንገዱን በደስታ ለመቀበል ዝግጁ ነበሩ፤ ሉቃ. 18፥35-19፥10።

አንዳንዶች ሁለተኛው ደረጃ የአንደኛው ደረጃ አንድ ክፍል መሆኑን ማሰብ የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ። እውነት ነው፤ ሰው ወንጌልን በትክክል ሊረዳው፥

ቃሉንም በትክክለኛ ስሜት ሊቀበለው የሚችለው ዳግመኛ ሲወለድ ብቻ ነው:: ዕውቀትን በአእምሮና በስምምነት በስሜት ለመለየት አስቸጋሪ ቢሆንም፥ እነዚህን አሳቦች እንደ ሁለት ደረጃዎች መቍጠር የተለመደ ነው (7)::

**3. ልባዊ ውሳኔ**

ሰው እንዲድን ሁኔታውን ተረድቶና የነበረውን ሌላ ተስፋ ሁሉ ትቶ ወደ ክርስቶስ ይሄዳል፤ በዚህ ዓለምም ሆነ ለዘለዓለም ተስፋውን ሁሉ በክርስቶስ ላይ ይጥላል:: ይህም ዋና የርምጃ ደረጃ ነውና አንድ ሰው ስለ ማመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፥ ብዙ ጊዜ ይህን ርምጃ ያመለክታል:: አንዳንድ ሰዎች ይህ ዐይነቱ የእምነት ርምጃ በጨለማ እንደ መዝለል ይቈጠራል፤ ሰውንም ወደ ክርስቶስ እንዳይዞር ይገፋፋል ይላሉ:: ስለዚህ የእምነት ደረጃ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ማተኰር ይገባናል:-

ሀ) ትግል ያለበት ስለ መሆኑ፤ ክርስቶስ፥ «ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፤ ግፈኞችም ይናጠቋታል (የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤ አ.መ.ት.)» እና «በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም» በማለት ሰው በቀላሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገባ አስጠነቀቀ፤ ማቴ. 11፥12፤ ሉቃ. 13፥24:: ጥቂት ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ሲሰሙ ያምናሉ፤ ብዙዎች ግን ወደ እውነተኛው እምነት የሚደርሱት ከከባድ ትግል በኋላ ነው:: ይህም ትክክለኛ ትምህርትን ካለመስማታቸው፥ ከሥጋዊ ምኞታቸው፥ ከሰይጣን የማሳወርና የማስፈራራት ድርጊት፥ ከሰዎች ምክር፥ ከባህል ተጽዕኖ፥ ከፍቅረ ንዋይ... ወዘተ የተነሣ ሊሆን ይችላል:: በሩ ጠባብ ነው፤ ሰዎች አንድ በአንድ ይገባሉና ጓዝ ይዞ መግባት አይቻልም::

ለ) አመክንዮታዊ ስለ መሆኑ፤ የሚያምን ሰው ኀጢአተኛ መሆኑንና ከኀጢአት ሊያሳርፍ የሚችለው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ያውቃል:: ለምሳሌ በርጤሜዎስ ዕውር መሆኑን፥ እንዲያይ የሚያደርገውም ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ዐወቀ፤ በዚህ ምክንያት ሰዎች እንዳይናገር ቢከለክሉትም፥ «የዳዊት ልጅ፥ ኢየሱስ ሆይ ማረኝ» እያለ መጮኹ አመክንዮታዊ ነበረ፤ ሉቃ. 18፥35-43::

ሐ) የእግዚአብሔር ስጦታ ስለ መሆኑ፤ እውነተኛ እምነት የዳግም ልደት ውጤት ነው:: ከዚህ በላይ ንስሓ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን አይተናልና ንስሐና እምነት የተያያዙ በመሆናቸው፥ እምነትም የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን ማሰብ ከባድ አይደለም፤ ሐ.ሥ. 5፥31፤ 11፥18፤ 2ጢሞ. 2፥24-25:: አጵሎስ በአካይያ፥ «ከጸጋው የተነሣ አምነው ለነበሩት ትልቅ ረዳት ሆናቸው» የሚለውን ስንመለከት፥ ሰዎች የሚያምኑት ከእግዚአብሔር የተነሣ እንደሆነ ግልጥ ነው፤ ሐ.ሥ. 18፥27 (አ.መ.ት.)::

እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ስለ መሆኑ ከሁሉም በጣም የታወቀው ጥቅስ፥ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም» የሚለው ነው፤ ኤፌ. 2፥8-9:: አንባቢ ይህን ጥቅስ በአንቀጹ ውስጥ (2፥5-10) ሲመለከተው፥ «ይህም» የሚለው ሐረግ እምነትን እንደሚያመለክት ግልጥ ሆኖ ሳይታየው እንደማይቀር ይታሰባል፤ ምክንያቱም ሀ) በጥቅሱ «ይህም» ለእምነት ቅርብ ነው:: ለ) ጸጋው የእግዚአብሔርን ስጦታ የሚመለከት ነውና «ይህም» ጸጋውን የሚመለከት ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ማለት ድግግሞሽ ይሆናል:: ሐ) የጳውሎስ አሳብ አቀራረብ ከዚህ ጋር ይስማማል (8):: ሐዋርያው እምነትና ማመን የእግዚአብሔር ስጦታ

መሆናቸውን በሌሎች አንቀጾች ያስተማረ መሆኑ ይታያል፤ ኤፌ. 6፥23፤ ፊል. 1፥29፤ 2ተሰ. 2፥13።

መ) የሰው ትክክለኛ አጸፋ ስለ መሆኑ፤ ወንጌል ንስሐ ግቡ እንደሚል ሁሉ፥ እመኑም ብሎ ያዝዛል። እንደ ንስሐ እምነትም ከሰው የሚጠበቅ በድርጊት የሚገለጽ ኀላፊነት ነው። ሰው ይህን የሚያደርገው ከእግዚአብሔር በሚሰጠው ኀይል ነው። ይህም ኀይል ከዳግም ልደት ይመነጫል። ይህ በሰው ዘንድ የሚከናወን የእግዚአብሔር አሠራር ነው፤ አውግስጢኖስ «እግዚአብሔር የሚያዝዘውን ይሰጣል» ብሏል።

4. ተመክሮታዊ አለኝታ

የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» በማለቱ እውነተኛ እምነት መጠነኛ አለኝታ እንደሚገኝበት ያሳያል፤ ጸሐፊው ብዙ የእምነት ምሳሌዎችን በምዕራፉ ውስጥ ገልጧል፤ ዕብ. 11፥1። ይህ ጥቅስ የእምነትን ውጤት በሁለት አቅጣጫ ያብራራል። 1ኛ፥ ሰው ወደ ሦስተኛው ደረጃ ሲደርስ የሚጠብቀው ተስፋ እንደሚፈጸምለት ያውቃል። እንግዲህ ሰው በእምነት ለድኅነት ክርስቶስን ብቻ አለኝታ ሲያደርግ፥ ማመኑ ተስፋውን ስለሚያረጋግጥ፥ ክርስቶስ ኀጢአቱን እንደተሸከመና ይቅር እንዳለው ይገነዘባል፤ ቀድሞ ከነበረበት ሸክምም ነጻ ይወጣል፤ ወደ አዲስ ሕይወት በደስታ ይገባል፤ ክርስቶስንም ያውቃል፤ ማቴ. 11፥28-30፤ ራእ. 3፥20። 2ኛ፥ የዘለዓለም ሕይወትን «ማየት» ባይችልም፥ አዲስ ሕይወትን በክርስቶስ በመቀበሉ የሚመጣው በረከት ሁሉ እውን መሆኑንና ይህም እንዴት እንደሆነ በመጠኑ ይረዳል፤ ዮሐ. 3፥16፤ 1ዮሐ. 5፥12።

ሰው በመጀመሪያ ንስሐ ገብቶ ሲያምን፥ ከባድ ትግል ሊከሰት ይችላል፤ ቈይቶ ግን የሚደርስበት የእምነት ደረጃ እውነተኛ መሆኑ ይሰማዋል፤ ያውቃልም። አንዳንድ ሰው ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ ልቡ በደስታ ይሞላልና እግዚአብሔር እንደተቀበለው ያውቃል፤ ምንም ጥርጥር አይኖረውም። ለዚህ ልዩነት መፈጠር ልዩ ልዩ ምክንያት ሊኖር ይችላል። በዚህ ላይ ቢያንስ ሁለት ነጥቦችን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል። ሰው በክርስቶስ ሲያድግ፥ ከተመክሮው የተነሣ አለኝታውን እያሳደገው ይሄዳል። በመሠረቱ በእውነተኛ እምነት ውስጥ አለኝታ አለ፤ ሆኖም ከፈተና ወይም ከኀጢአት የተነሣ የሰው እምነት ሊዳከም ወይም ለጊዜው የጠፋም እንኳ ሊመስል ይችላል። የሰው ስሕተት ብዙ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ሳይሆን፥ ወደ ራሱ መንፈሳዊ ሁኔታ ብቻ መመልከቱ ነው። የሚከተሉት ምዕራፎች ይህን ትምህርት ይተነትናሉ።

አራተኛው ደረጃ የሦስተኛው ደረጃ አንድ ክፍል ሆኖ ሊታይ ይችላል፤ ብዙ ጊዜ ሁለቱም የእምነት ደረጃዎች ወደ እግዚአብሔር በሚመለስ ሰው ተመክሮ አንድ ላይ ተጣምረው ይታያሉ (9)

## መ) ንስሐና እምነት የክርስቲያናዊ አኗኗር ባሕርያት መሆናቸው

በዚህ ምዕራፍ ሰው በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ማድረግ ባለበት ላይ አጽንዖት አድርገናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ ራሱ ሲስብ፥ እንደየሁኔታቸው ትኩረቱ አንዳንድ ጊዜ በንስሐ ላይ፥ ሌላም ጊዜ በእምነት ላይ ነበረ። ትኩረቱ በንስሐ ላይ ቢሆንም የእምነት ጉዳይም ዐብሮ ይጠቀሳል፤ ትኩረቱ በእምነት ላይ ከሆነም፥ ንስሐ አለ። ይህ እውነት

በበርጤሜዎስና በዘኬዎስ ታሪክ ይታያል፤ ዘኬዎስ ንስሓ ሲገባ፥ የእምነት ፍንጭ እንደ ነበረ ይታያል፤ በርጤሜዎስም በእምነት ወደ ክርስቶስ ሲሄድ፥ የቀድሞ ሕይወቱን ሲተወው የወሰነ ስለ መሆኑ ፍንጭ አለ፤ ሉቃ. 18፥35-19፥10::

ሰው ወደ ድነት እንዲደርስ መጽሐፍ ቅዱስ ጉሉሕ የጸሎት ምሳሌ አይሰጥም፤ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደየሁኔታው የተገለጡ የመመለስ ጸሎት ምሳሌዎች ይገኛሉ፤ ሉቃ. 15፥18-19፤ 18፥13፤ 23፥42:: እንግዲህ እያንዳንዱ ሰው ንስሓንና እምነትን ያካተተ ጸሎት ለራሱ እንደ ሁኔታው እንዲያዘጋጅ መምከር የተሻለ መሆኑን ማሰብ ቀላል ነው:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ብዙዎች እንደሚያደርጉት፥ ንስሓንና እምነትን የሚያጠቃልል ጸሎት መስጠት ሰዎችን እንደሚረዳ የሚያስቡ ሰዎች አሉ:: እዚህ ላይ በዚህ መንገድ ጸሎትን መስጠት፥ መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ውስጥ እንዲሠራ ዕድል ይሰጣልን? ሰባኪው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መሥራት ይችላልን? ብለን መጠየቅ ይገባናል:: ሰው የራሱን ጸሎት ወይም የሰባኪውን ጸሎት በመጸለይ አይድንም:: ጸሎት ከልብ ከቀረበ፥ የልብ መለወጥን ያሳያልና ልቡ የተለወጠ ሰው ድኗል ማለት ነው:: ይህን ጸሎት በመጸለዩ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ይሄዳል ወይም ክርስቶስን ይቀበላል፤ መለወጡንም ያረጋግጣል::

ሦስት ነጥቦችን በመደምደሚያነት እናቀርባለን::

1. ሰው ክርስቲያናዊ ጉዞ ሲጀምር፥ ንስሓና እምነት ዐብረው በተጓዳኝነት ይገኛሉ፤ ይህንም በክርስቶስና በሐዋርያት ታሪክና ትምህርት በሰፊው አይተናል:: ሆኖም አንዳንዶች በንስሓ ላይ ትኩረት በማድረግ ሰው በጸጋና በእምነት ሳይሆን፥ በሥራ እንደሚድን ሰባክያን ያስተምራሉ ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች ላላመኑት ክርስቶስን እንደ መድኅኒት ብቻ አድርጎ ማሳየትና መስበክ ይገባል ይላሉ:: በእነርሱ ትምህርት መሠረት ክርስቶስና ሐዋርያት «ንስሓ ግቡ» ብለው ያስተማሩት አሳብን መለወጥ ማለት ነው:: የሚያድን እምነት ክርስቶስ ከኀጢአት እንደሚያድን ብቻ ማመን ማለት ነውና ክርስቶስን እንደ ጌታ መቀበል ግን ሰው ከዳነ በኋላ የሚወስደው ሁለተኛው ርምጃ ሊሆን ይችላል ይላሉ (10):: ከዚህ በላይ በገለጽነው መሠረት ለዚህ ዐይነቱ ትምህርት የምንሰጠው መልስ ከዚህ የሚከተለው ሊሆን ይችላል:-

ሀ) ሰው በክርስቶስ ሲያምን ወደ ክርስቶስ ይሄዳል (ወይም ክርስቶስን ይቀበላል):: የክርስቶስን ሥራ በተመለከተ ሰው የክርስቶስ ሥራ ሁሉ ተካፋይ ይሆናል እንጂ በተወሰነ የሥራ ክፍል ብቻ ተሳታፊ አይደለም:: ክርስቶስ የአማኙ ነቢይ፥ ካህንና ንጉሥ ነውና የአማኙ መድኅኒት እንጂ ጌታ አይደለም ማለት ክርስቶስን መክፈል ነው:: ሰው በክርስቶስ ሲያምን እርሱንና ሥራውን ሁሉ ያምናል፤ ያከብራልም::

ለ) ሰው ንስሓ ሲገባ በአእምሮ፥ በስሜትና በፈቃድ ማለት በሁለንተናው ቀድሞ ከነበረበት ዘወር በማለት በክርስቶስ መንገድ ይራመዳል፤ ንስሓና እምነት የተያያዙ ናቸውና::

ሐ) ሰው በክርስቶስ ሲያምን አዲስ ሥራ ይሠራል:: ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚሆነው በእምነት ነው፤ አዲስ ሥራውም የእምነቱ ማረጋገጫ ነው::

መ) ሰው ከኀጢአት የሚድነው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገው እምነቱ ነው::

2. ንስሓና እምነት የክርስቲያናዊ አኗኗር ሁሉ መሠረታውያን ሐቆች ናቸው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎት ጥቅልል ምሳሌው ውስጥ «በደላችንን ይቅር በለን» ብሎ በማስተማሩ ንስሓ መግባት የአማኙ የዘወትር ተግባር መሆኑን አሳየ:: እንደዚሁም ከሰማይ «ንስሓ ግቡ» ብሎ አብያተ ክርስቲያናትን አዘዘ፤ ራእ. 2፥5፡16፡21-22፤ 3፥3፡19:: እንደዚሁም ጳውሎስ ስለ ንስሓ አስተማረ፤ 2ቆሮ. 7፥8-10::

ሐዋርያው ጳውሎስ እምነት በምእመናን ጸንቶ የሚኖር መሆኑንም አስተማረ (1ቆሮ. 13፥13)፤ ስለ ራሱም ሲናገር፥ «አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው» ብሏል፤ ገላ. 2፥20:: አብርሃምም፥ «በእምነቱ ሳይደክም ተመስክተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ በእምነት በረታ...» ብሎ በማሳሰብ ክርስቲያኖች ሁሉ የእምነታቸውን «አባት» ተከትለው በእምነት ማደግ እንደሚገባቸው ጳውሎስ አስተማረ፤ ሮም 4፥20-21:: ሰው በእምነት ቢበረታም፥ ኀይሉ የሚገኘው ከእምነቱ ሳይሆን እምነቱን ከሚሰጠው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ ሉቃ. 17፥6::

3. ሰባክያነ ወንጌል፥ መምህራንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸው ንስሓና እምነት ጐን ለጐን እንዲሄዱ ማድረግ ይገባቸዋል:: ሁልጊዜ በንስሓ ላይ ብቻ ትኲረት ቢደረግ፥ ሰዎች ተስፋ ሊቈርጡ ይችላሉ:: ሁልጊዜ በእምነት ላይ ብቻ አጽንዖት ከተደረገም፥ አካሄዳቸውን ማስተካከል አይችሉምና ድርቀት ውስጥ ይገባሉ:: ንስሓና እምነት ሚዛናዊነትን ጠብቀው ሲሄዱ የእግዚአብሔር በረከት ይታያል::

# ማስታወሻ

(1) መመለስ በእንግሊዝኛ በConversion፥ በConvert እና በBe Converted ሊተረጐም ይችላል:: የሥነ ልቡና ሊቃውንት ስለ ብዙ ዐይነት Conversion ይጽፋሉ፤ የሃይማኖት ሊቃውንትም Conversion በሚለው ቃል የሚጠቀሙ ሲሆን፥ ፕሮቴስታንቶች በዚህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው ለወንጌል የሚሰጠውን አጸፋ ሲያመለክቱ፥ ካቶሊኮች ቃሉ የመጀመሪያ አጸፋን ብቻ ሳይሆን፥ የለውጥን ሂደት ሁሉ (ቅድስናን) ጭምር ሊያጠቃልል ይችላል የሚል አመለካከት አላቸው::

(2) Berkhof ገጽ 486 ይመ.:: ይህ ሥርዐት በእንግሊዝኛ Penance ይባላል::

(3) THS ገጽ 135-138 ይመ.

(4) የሚከተለው በBerkhof ገጽ 499-500 ተመሥርቷል::

(5) RR ገጽ 728 ይመ.

(6) Berkhof ገጽ 503፥ Sandemanians በNIDCC ይመ.

(7) Berkhof 504-505፤ P.G.R. 168-169 ይመ.

(8) THS (ገጽ 126-128) እና RR (ገጽ 732) የተሰጠውን አተረጓጐም ይቀበላሉ:: ችግሩ በግሪክ «ይህ» የተተረጐመበት ቃል ኢጾታዊ ነውና እምነት፥ ጸጋና ድኅነት የሚተረጐሙባቸው ቃላት የአንስታይ ጾታ አላቸው:: THS እና RR በሰዋስዋዊ አገባብ መሠረት «ይህ» ከ«እምነት» ጋር በጥንት አመለካከት ከጾታ ጋር ተስማምቶ በልዩ ልዩ ምክንያት መገለጥ እንደሌለ ያስተምራሉ:: Grudem (ገጽ 730 ማስታወሻ 14) «ይህ» ሰው «ከጸጋ በእምነት መዳኑን» እንደሚያመለክት ያስተምራል:: ይህም ትክክለኛ ከሆነ እንኳ እምነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው የሚገኝ መሆኑን አያሳይም:: «አስደናቂው ልውውጥ» በሚሰኘው መጽሐፍ ገጽ 66-68 ይመ.

(9) ሦስቱ ደረጃዎች በእንግሊዝኛ፥ Knowledge፥ Belief እና Trust ይባላሉ፤ P.G.R. ገጽ 168-170:: Berkhof ስለ እምነት ክፍሎች ሲጽፍ፥ የአእምሮ ክፍል፥ የስሜት ክፍልና የፈቃድ ክፍል እንዳሉ ያትታል፤ Berkhof ገጽ 503-506::

(10) ግሩደም እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑና የሳንደማናውያንን ትምህርት በብዙ አቅጣጫ ደግመው እንደሚያስተምሩ ያሳያል፤ Grudem ገጽ 714-715 በተለይ ማስታወሻ 5 ይመ.

# ምዕራፍ 89 - ጽድቅና ቅድስና፥ የቅድስና ደረጃ

ትምህርተ እግዚአብሔርን በተመለከተ በእምነት ውጤትነት እርስ በርስ የተያያዙ ሦስት ታላላቅ ነገሮች አሉ፤ እነርሱም የጽድቅ፥ የቅድስና ደረጃዎችና የእግዚአብሔር ልጅነት ናቸው:: ሰው ሲያምን እነዚህ ሦስት ደረጃዎች በሕይወቱ እንደሚከናወኑ ይታሰባል፤ ወይም በሌላ አገላለጥ በክርስቶስ የሚገኙ ናቸውና ለዘለዓለም ከምእመናን አይለዩም:: የእግዚአብሔር ልጅነትን በሚከተለው ምዕራፍ እናጠናዋለን:: ብዙ ሰዎች ስለ ቅድስና ሲናገሩ፥ አሳባቸው የሚያተኲረው በአማኝ አኗኗር ላይ ነው፤ ይህ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው፤ ሆኖም አማኙ በክርስቶስ በመሆኑ ቅዱስ ነውና በዚህ ምዕራፍ የቅድስና ደረጃን እንመለከታለን:: በዚህ ምዕራፍ ዋናው ጥናታችን የሚያተኲረው ሰው በክርስቶስ ሲያምን በክርስቶስ በሚሰጠው ጽድቅ ላይ ነው (1)::

ስለዚህ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ ትርምስና መለያየት እንደተፈጠረ መካድ አንችልም፤ እስከ አሁንም ድረስ ይህ ችግር ይታያል:: እንግዲህ ወደ ዋናው ትምህርታችን ከመግባታችን በፊት፥ ጽድቅ፥ ጻድቅ፥ ጸደቀና አጸደቀ የሚሉት ተዛማጅ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ እንመለከታለንና በዚህ ምክንያት ዋና ዋና የአተረጓጐም ችግሮችን ለይቶ ለማቅረብ እንሞክራለን::

1. ጽድቅ፥ ጻድቅ፥ ጸደቀና አጸደቀ በመጽሐፍ ቅዱስ

እነዚህ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ ይገኛሉ:: በአዲስ ኪዳን ቤዛና ቤዛነት፥ ስርየትና ማስተስረያ፥ ዕርቅም ከነግሶቻቸው በአነስተኛ መጠን ሲገኙ፥ ጽድቅና ጻድቅ ከግሶቻቸው ጋር ከሁለት መቶ ጊዜ በላይ ተጠቅሰዋል:: በዚህ መሠረት ጽድቅ በትምህርተ ድኅነት ዋናና መሠረታዊ አሳብ ያለው ቃል እንደሆነ ይታሰባል (2)::

በምዕራፍ 71 ላይ ከቍጣ ወደ ስርየት የቤተ መቅደስ፥ ከባርነት ወደ ነጻነት የንግድ፥ ከጥል ወደ ዕርቅ የቤተሰብ፥ ከኀጢአት በደል ወደ ጽድቅ የፍርድ ቤት አገላለጥ መሆናቸውን ገልጠናል:: ይህም በብዙ ጥቅሶች ይታያል:-

- «በሰዎች መካከል ጠብ ቢሆን፥ ወደ ፍርድም ቢመጡ፥ ፈራጆች ቢፈርዱባቸው፥ ጻድቁን:- ደኅና ነህ፤ የበደለውንም:- በደለኛ ነህ ይበሉአቸው»፤ ዘዳ. 25፥1:: እንግዲህ የዳኛ ኀላፊነት ሰዎች በፈጸሙት ድርጊት መሠረት የተወሰነውን ማወጅ ነው::

- «ኀጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ፥ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው»፤ ምሳ. 17፥15:: እግዚአብሔር ማንኛውንም ኢፍትሐዊ ውሳኔ ይጠላል፤ በተለይ በጉቦ የተወሰነ ውሳኔ እግዚአብሔር ከሚጠላቸው መካከል አንዱና ዋናው ነው፤ ምሳ. 17፥23::

ጽድቅ የፍርድ ውሳኔን የሚያመለክት ሲሆን፥ በተጨማሪም ለተቃራኒ አሳብ ጥቅም ላይ በሚውለው ኵነኔ በሚለው ቃል ይታያል:-

- «... ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ»፤ ማቴ. 12፥36-37::

- «... ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፤ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ»፤ ሮም 5፥16::

- «... እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ የሚኰንንስ ማን ነው?» ሮም 8፥33-34::

እንግዲህ ዳኛ በምድር ወይም እግዚአብሔር በሰማያት ሰውን ሲያጸድቅ ሰውዬው ከሕግ ነጻ መሆኑን እንደሚያውጅ እናያለን:: የምድራዊ ዳኛ ሥራ የሰውን ጠባይ ወይም አካሄድ መለወጥ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የማጽደቅ ሥራ ሲናገር፥ እግዚአብሔር የሰውን ጠባይና አካሄድ በመለወጥ ሰውን እንደሚያጸድቅ ያስተምራልን? የሚለው ጥያቄ ይነሣል:: እንደገና ደግሞ በአንዳንድ ጥቅሶች ውስጥ የሚታየውን የጽድቅ አጠቃቀም እንመልከት:-

- «የሰሙትም ሕዝብ ሁሉ... እግዚአብሔርን አጸደቁ»፤ ሉቃ. 7፥29:: እዚህ ላይ ሕዝቡ እግዚአብሔር ጻድቅ (ትክክለኛ) መሆኑን ዐወጁ እንጂ እግዚአብሔርን የለወጡ አለመሆኑ ግልጥ ነው:: እግዚአብሔር ሰውን መልካም በማድረጉ አጸደቀው ማለት እንግዲህ ከቃሉ አጠቃቀም እጅግ የተለየ ነው::

- «ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለምና ከባሪያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ»፤ መዝ. 143፥2:: ዳዊት በሕግ ፊት ጻድቅ አለመሆኑን በማወቁ፥ እግዚአብሔር እንዳይፈርድበት እንጂ በማጽደቅ ሥራ እንዲለውጠው አልለመነም::

- «አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው፤ ኀጢአት በሕግ ይታወቃልና»፤ ሮም 3፥19-20:: ይህም ጥቅስ ሰው የማይጸድቅበት ምክንያት አለመለወጡ ሳይሆን፥ ሕግን አለመፈጸሙ እንደሆነ በግልጥ ያሳያል::

ዳኛ የተከሰሰውን ሰው አጸደቀ እንላለን፤ ማለት ክሱን ከመረመረ በኋላ በሕግ በኩል ምንም እንደሌለበት በሥልጣን ተናገረ፤ ዐወጀ ማለት ነው:: ብዙ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ላይ የሚታየው የዚህ ቃል ትርጕም ይህ ነው፤ ሐ.ሥ. 13፥38-39፤ ሮም 3፥20-28፤ 4፥5-7፤ 5፥1፤ ገላ. 2፥16፤ 3፥11:: ሕጋዊ ትርጕም እንዳለው ሲታይ፥ ሀ) በብዙ አንቀጾች ሌላ ትርጕም ሊኖረው አይችልም (ሮም 3፥28፤ 4፥5-7፤ 5፥1፤ ገላ. 2፥16፤ 3፥11፤ 5፥4)፥ ለ) በተቃራኒነት ከኵነኔ ጋር ይነጻጸራል (ሮም 8፥33-34)፥ ሐ) ተመሳሳይ አንቀጾች የሕግ አሳብ ይኖራቸዋል (ዮሐ. 3፥18፤ 5፥24፤ ሮም 4፥6-8፤ 2ቆር. 5፥19)፥ መ) ቃሉ ይህ ትርጕም ከሌለው በጽድቅና በቅድስና መካከል ልዩነት አይኖርም (3)::

## 2. የጽድቅ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ (4)

በልዩ ልዩ ቦታ እንደገለጥነው፥ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች በትምህርታቸው ለምሥጢረ ሥላሴና ለምሥጢረ ሥጋዌ ዐቢይ ትኵረት ሰጥተዋል:: ከአበው መካከል አንዳንዶች ሰው በእምነት መጽደቁን ቢጽፉም፥ ይህን ትምህርት በሰፊው የመረመሩ ወይም ጽድቅና እምነት እንዴት እንደሚገናኙ ያስተማሩ አይመስልም:: እነዚህ አባቶች በዳግም ልደትና በጽድቅ መካከልም ልዩነት መኖሩን በግልጥ አላሳዩም:: ብዙዎቹ ዳግም ልደት በጥምቀት ተግባራዊ ይሆናልና ሥርዐቱ የኀጢአትን ስርየት ያጠቃል
ቅዱስ አውግስጢኖስም እንኳ በሰው ቤዛነት የእግዚአብሔር ጸጋ

አኗኗን በሰው ሥራ ላይ ሳይመሠረት፥ ልዑላዊ፥ ነጻና ውጤታማ መሆኑን በግልጥ ቢያስተምርም፥ በጽድቅ (እንደ ሕጋዊ ውሳኔ) እና በቅድስና (እንደ ግብረገባዊ ለውጥ) መካከል ግልጥ ያለ ግንዛቤ አልነበረውም:: በምዕራባውያን ዘንድ ስላለው ልዩነት በጽድቅና በቅድስና መካከል ያለውን ልዩነት ባለማስተዋል የመጓዝ ሂደት ለረጅም ጊዜ ቀጥሏል:: ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን እነ ቶማስ አኩናስ በጽድቅ ውስጥ ሁለት ክፍሎች እንዳሉ አስተማሩ፤ ሲያስተምሩም የሰው ኀጢአት ከእግዚአብሔር ቸርነትና ከሰው አካሄድ የተነሣ ስለሚሰረይ ሰው ጻድቅ ይደረጋል አሉ:: ሰው ጻድቅ የሚሆነው ከሚሰጠው የጸጋ ሥራ የተነሣ ነው፤ በተሰጠውም ጸጋ መሠረት ይቅርታን ይቀበላል:: ከዚህ ትምህርት የተነሣ ሰው በከፊል በራሱ ሥራ እንደሚጸድቅ ማስተማር እየተለመደ ሄደ:: በጽድቅና በቅድስና መካከል የመፋለስ ሁኔታ በመከሠቱ አንዳንዶች ጽድቅ በተወሰነ ጊዜ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ ሲገልጡ፥ ሌሎች ደግሞ በሰው ሕይወት ሁሉ የሚፈጸም ሂደት መሆኑን አስተምረዋል::

የተሐድሶ ተከታዮች ይህን ትምህርት ስላልተቀበሉት ትምህርታቸው በጽድቅ ዋና የተሐድሶ ምንጭና እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩር ሆነ:: ስለዚህ ሁሉም የተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪዎች እንደሚከተለው አስተማሩ:-

ሀ) እግዚአብሔር የሚያከናውነው ሰውን የማጽደቅ ሥራ በእርሱ ፊት የሰውን ሕጋዊ ደረጃ መለወጥ እንጂ ሰውን ራሱን መለወጥ አይደለም:: ይህን በማስተማራቸው በጽድቅና በቅድስና መካከል የነበረውን ትርምስ አስወግደዋል::

ለ) በዚህ ሕጋዊ ለውጥ ውስጥ ሁለት ክፍሎች አሉ፤ 1ኛው፥ በኀጢአት ምክንያት የሰው በደል ይወገዳል የሚል ሲሆን፤ 2ኛው፥ የክርስቶስ ጽድቅ ለኀጢአተኛው ይቈጠራል የሚል ነው:: በዚህ ትምህርታቸው የሰው ጽድቅ ከፊል የሰው መልካም ሥራ የሌለበት መሆኑን አሳዩ::

ሐ) ሰው የሚጸድቀው በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሥራ ሲያምን ነው::

መ) ሰው የሚጸድቀው ወዲያውኑ ሲያምን ነው፤ በዚህ ጽድቅም ላይ ምንም የሚጨመር ነገር የለም፤ የሚቀነስም አይኖርም::

3. ጽድቅና ቅድስና (5)

አሁን ደግሞ በጽድቅና በቅድስና ረገድ እግዚአብሔር የሚያከናውነውን ሥራ እንደሚከተለው ለይተን ማሳየት እንችላለን:-

ሀ) እግዚአብሔር በጽድቅ ሥራው የኀጢአትን በደል አስወግዶ ለኀጢአተኛው የልጅነትን መብት ሁሉ ይሰጠዋል:: በቅድስና ሥራ ደግሞ የኀጢአትን ብክለት እያፈረሰና ኀጢአተኛውን በራሱ መልክ እያደሰው ይሄዳል::

ለ) እግዚአብሔር ለጽድቅ የሚሠራው ሥራ ከሰው ውጭ በራሱ የፍርድ ሸንጎ የሚፈጸም ነው:: የቅድስና ሥራው ግን በሰው ውስጥ የሚሠራ ሲሆን፥ ይህን ተግባር የሚፈጽምበትን ሰው ሕይወት ሁሉ ቀስ በቀስ ይለውጠዋል::

ሐ) እግዚአብሔር ሰውን የሚያጸድቀው አንድ ጊዜ ለዘለዓለም ነው፤ የሚደጋገም ተግባር አይደለም፤ ሂደት የለውም፤ አይጨመርበትም፤ አይቀነስለትምም:: ሰው ጸድቋል ወይም አልጸደቀም፤ አማካይ ደረጃ የለውም:: በቅድስና ሥራ ግን ሰው እየተለወጠ ይሄዳል::

መ) በግብረ እግዚአብሔር ኀጢአተኛው ጻድቅ መሆኑን እግዚአብሔር አብ ያውጃል፤ መንፈስ ቅዱስም ይቀድሰዋል። እነዚህ ሁለት ግብሮች በወልድ ሥራ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

## 4. የጽድቅ ጊዜ (6)

«... ኀጢአተኛውን በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል»፤ «እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ»፤ ሮም 4፥5፤ 5፥1። እንግዲህ እግዚአብሔር ሰውን ያጸድቃል፤ ሰው ጻድቅ መሆኑን መቼ እንደሚያውጅ ግን ምናልባት ግልጥ አይደለም። ሰው ሲያምን ጻድቅ መሆኑን ያውቃልና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ይኖረዋል፤ ሮም 5፥1። ሊቃውንት የእግዚአብሔርን የማጽደቅ ሥራ ከዘለዓለም፥ ከክርስቶስ ትንሣኤ፥ ሰው ክርስቶስን ከሚያምንበት ጊዜና ከዓለም መጨረሻ ፍርድ ጋር አያይዘው ይመለከቱታል። እያንዳንዱን አመለካከት በዐጭሩ እንመልከት።

### ሀ) ጽድቃችን ዓለም ሳይፈጠር ታቅዷል

ሰውን የማጽደቅ ዓላማ ከዘለዓለም በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እንዳለ የማይካድ ነው፤ ለዚህ ብዙ ማስረጃ አለና:- አብርሃም መጽደቁን አወቀ (ዘፍ. 15፥6)፤ ሕግና ነቢያት የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ይመሰክራሉና (ሮም 3፥21) ዓለም ሳይፈጠር እግዚአብሔር አማኞችን በሰማያዊ ስፍራ ስለባረካቸው፥ ስለመረጣቸውና ልጆቹ እንዲሆኑ ስለወሰናቸው፥ እንደዚሁም «እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ» አምላክ በመሆኑ (ኤፌ. 1፥3-5:11)፥ መጽደቃቸው በዕቅዱ ውስጥ ከፍ ያለና የታወቀ ስፍራ እንዳለው ግልጥ ነው። ሆኖም በሮም 8፥29-30 በድኅነት ቅደም ተከተል «አጸደቃቸው» በ«ጠራቸውና» እና በ«አከበራቸው» መካከል ተወስኗል፤ ስለዚህ ሰው በምድራዊ ሕይወት ስለሚጠራ በእግዚአብሔር ዕቅድና በእግዚአብሔር ዕቅድ ፍጻሜ መካከል ልዩነት መኖሩን ማሳየት የሚያስፈልግ ይመስላል፤ ሰው ከመጠራቱ በፊት አይጸድቅምና።

### ለ) ጽድቃችን በክርስቶስ ትንሣኤ ተረጋግጧል

«ተቈጠረለት» የሚለው ቃል ስለ አብርሃም ብቻ አልተጻፈም፤ ስለ እኛም ጭምር እንጂ፤ «ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቈጠርልን ዘንድ አለው» (ሮም 4፥23-25) የሚለው ሐረግ፥ ክርስቶስ የተነሣው አብርሃምንና ምእመናንን ሁሉ ለማጽደቅ መሆኑን ያስተምራል። የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተያያዙ ናቸውና በመሥዋዕታዊ ሞቱ ክርስቶስ ለሚያምኑት የኀጢአታቸውን ዕንቅፋት አስወገደና እግዚአብሔር በፍትሕ ሊቀበላቸው ቻለ፤ ሮም 3፥25-26። መጽደቃችንን በተመለከተ የክርስቶስ ትንሣኤ ከሚያብራራቸው ነገሮች ሦስቱን እንመልከት:- 1) ክርስቶስ ባይነሣ ኖሮ እግዚአብሔር ለኀጢአታችን ልጁ ያቀረበውን መሥዋዕት መቀበሉን ማወቅ አንችልም ነበር። ጳውሎስም እንኳ፥ «ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኀጢአታችሁ አላችሁ» በማለት ክርስቶስ ባይነሣ ኖሮ ሞቱ ምንም እንደማይጠቅመን ገልጧል፤ 1ቆሮ. 15፥16-17። 2) ክርስቶስ የተነሣውና ወደ ሰማይ ያረገው መንፈስ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ላይ ለማፍሰስና ኀጢአተኞች አምነው ይጸድቁ ዘንድ፥ የድኅነትን ስብከት ለመምራት ነው፤ ማቴ. 28፥16-20፤ ሉቃ. 24፥46-49፤ ሐ.ሥ. 1፥8፤ 2፥33። 3) ክርስቶስ ሕያው በመሆኑ አማኙ

ከእርሱ ጋር በአንድነት ይኖራልና፤ ዮሐ. 15፥4-5፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ገላ. 2፥20:: ከክርስቶስ በፊት እነ አብርሃም አመኑ፤ በእምነታቸውም ጸደቁ:: ስለዚህ እነርሱ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ በክርስቶስ ትንሣኤ ጸደቁ ማለት ትክክል አይደለም:: ሆኖም ያመኑና የሚያምኑ ሁሉ ያለ ክርስቶስ ትንሣኤ እንደማይጸድቁ ግልጥ ነው፤ ምክንያቱም ከእርሱ ጋር አንድ ሆነዋል::

ሐ) ጽድቃችን ባመንበት ጊዜ ተቈጥሮልናል

አብርሃም ታላቅ የእምነት ሰው በመሆኑ ለምእመናን ሁሉ ምሳሌ ነው:: እምነቱ በልዩ ልዩ ደረጃ ይታያል፤ በተለይም፥ «ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፤ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ» (ዕብ. 11፥8)፤ በድንኳን እየኖረ በእንግድነት በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በእምነት ተቀመጠ (ዕብ. 11፥9)፤ ከዚህም ጋር፥ «መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና»፤ ዕብ. 11፥10::

የአብርሃም እምነት ጐልቶ የሚታየው በይስሐቅ ታሪክ ላይ ነው:: ዐሥር ዓመት በምድሩ ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ዘሩ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደሚሆን ተስፋ ሲሰጠው፥ «አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት»፤ ዘፍ. 15፥6:: ከዚህ በፊት ለእግዚአብሔር በእምነት የታዘዘ ይመስላል:: አሁንም እግዚአብሔርን አመነ ማለት እግዚአብሔር የእርሱ አምላክ እንደሆነ አምኖ አስፈላጊው ነገር ሁሉ እንደሚፈጸምለት ርግጠኛ ሆነ ማለት ነው፤ ይህ ዐይነቱ እምነት ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት:: ይስሐቅ የሚወለድበት ጊዜ ሲደርስ፥ ምንም እንኳ የመቶ ዓመት ሽማግሌ ቢሆንም፥ «በእምነቱ ሳይደክም... ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ...»፤ ሮም 4፥19-21፤ ዕብ. 11፥12:: ዋናውም የእምነቱ መፈተን አንድ ልጁን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡ ነበር፤ አብርሃም ግን እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንደሚችል ተገንዝቧል፤ ልጁንም ከሞት የመነሣት ምሳሌ ሆኖ አገኘው»፤ ዕብ. 11፥17-19፤ ዘፍ. 22፥5፤ ያዕ. 2፥21-22::

ዛሬ ሰው በክርስቶስ ሲያምን በትንሣኤም ማመን አለበት፤ ምክንያቱም የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለድነታችን መሠረታውያን እውነቶች ናቸው፤ ሮም 10፥9-11፤ 1ቆሮ. 15፥3-4:: ሰው ይህን እውነት አምኖ ሲቀበልና በዚህ መሠረት ወደ ክርስቶስ ሲጠጋ፥ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል:: የሚያምን ሰው ኀጢአተኛ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ሥራ መሠረት ለሚያምን ሰው ጽድቅ ስለሚቈጥርለት ያጸድቀዋል፤ ሮም 4፥3-5:: አማኙ ስለ መጽደቁ ዐዋጅ ባይሰማም እንኳ እንደጸደቀ ያውቃልና በዚህ መሠረት ይኖራል፤ ሮም 5፥1-5:: በዚህ ረገድ ሲኖርም፥ ጽድቁ ለዓለም የሚገለጥበትና የሚታወጅበት ዕለት ይመጣል::

መ) ጽድቃችን በፍርድ ቀን ይገለጣል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ በክብሩ ዙፋን ላይ ሲቀመጥ፥ ጻድቃንን በቀኙ ያቆማቸዋልና፥ «እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» ይላቸዋል፤ ማቴ. 25፥31-34:45:: ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ቀን፥ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም» በማለት ጽፏል፤ 2ጢሞ. 4፥8::

እንግዲህ የጽድቅ ጊዜ መቼ እንደሆነ ስናስብ፥ እንደ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅድ በክርስቶስ ትንሣኤ መሠረት ምእመናን ሁሉ በዳግም ምጽአቱ ጻድቃን መሆናቸው በዓለም ሰዎች ሁሉ ፊት የሚታወጅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፤ ሆኖም ምእመናን አስቀድሞ ባመኑበት ጊዜ ጽድቅ እንደተቈጠረላቸው ያውቃሉ፤ ይህም ውሳኔ የእግዚአብሔር በመሆኑ የማይለወጥባቸውና ርግጠኛ የሚሆኑበት ውሳኔ ነው።

እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱ አራት ነጥቦችን ከተረዳን፥ ዋናውን የጽድቅ ትምህርት በሚከተለው አኳኋን ለማስተዋል አዳጋች እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን።

## ሀ) የጽድቅ ምንጭ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (7)

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው» (ሮም 3፥20) በማለት በእግዚአብሔር ፊት ሰው የሚገኝበትን ሁኔታ ከገለጠ በኋላ፥ «አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ («ከሕግ ውጭ የሆነ»፤ «ከሕግ ነጻ የሆነ») ተገልጧል፤ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው» በሚለው አስገራሚ መልእክቱ ሰው ለሚገኝበት ሁኔታ እግዚአብሔር የሰጠውን አጸፋ ይገልጣል፤ ሮም 3፥21-22። ስለ ምእመናንም፥ «በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ...» የሚለውን ከገለጠ በኋላ፥ «ነገር ግን እግዚአብሔር... በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና» ብሎ ጻፈ፤ ኤፌ. 2፥1-5።

ምእመናን የሚጸድቁበት «የእግዚአብሔር ጽድቅ» ሁለት ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል፤ 1ኛ፥ ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን ጽድቅ፥ 2ኛ፥ ምእመናን የሚጸድቁበትን የእግዚአብሔርን የራሱን ጽድቅ። ሁለቱም ነጥቦች እውነት ናቸውና ሐዋርያው በአንዱ ሐረግ ሁለቱን አጣምሮ የገለጠ ይመስላል (8)።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለምእመናን የተሰጠው በክርስቶስ መምጣት እንደሆነ ተገልጧል፤ ሮም 1፥3-4:16-17፤ 3፥22። ብሉይ ኪዳን ሰው በራሱ ጽድቅ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጽድቅ መጽደቁን አስቀድሞ መስክሯል፤ ኤር. 23፥6። ይህም የሚሆነው ሰው ሕግን መፈጸም በመቻሉ አይደለም፤ ምክንያቱም ሰው ሕግን መፈጸም ባለመቻሉ ሕግ ይኰንነዋል እንጂ አያጸድቀውም፤ ሮም 3፥19-20:21፤ ገላ. 3፥10። ስለዚህ ሰው የሚጸድቀው በሌላ መንገድ ማለት ክርስቶስን በማመን በእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ሮም 3፥22፤ 4፥5፤ 1ቆሮ. 1፥30-31። ሰው የሚጸድቅበት መንገድ ለሰዎች ሁሉ አንድ ዐይነት ነው፤ ምክንያቱም፥ «ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሏቸዋልና» ይላል፤ ሮም 3፥22-23፤ 4፥12፤ ገላ. 3፥28-29። እንግዲህ ድነት ሁሉ የሚገኘው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጸጋ ነው፤ ኤፌ. 2፥5:8-9።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ሲጽፍ በሁለት ነጥቦች ላይ ለማተኰር ፈልጓል፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ፥ ጸጋ ከእግዚአብሔር ነው፤ ምእመናን፥ «እንዲያው በጸጋው» እንደሚጸድቁ (ሮም 3፥24)፥ የዘለዓለም ሕይወትን በጸጋ ስጦታነት እንደሚቀበሉ (ሮም 6፥23)፥ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ ሲመረጡ፥ «በውድ ልጁም እንዲያው» የተሰጠው ጸጋ ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚሆን (ኤፌ. 1፥4-6)፥

ድኅነታቸው እንደ እግዚአብሔር አሳብና ጸጋ መጠን... ይህም ጸጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ እንደተሰጣቸው (2ጢሞ. 1፥9)፥ እናነባለን::

2ኛ፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ሰው በሚሠራው ሥራ ላይ አልተመሠረተም፤ ከዚህ የተነሣም፥ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» (ኤፌ. 2፥8-9)፤ «ይህም (ድኅነት) እንደ ሥራችን መጠን አይደለም» (2ጢሞ. 1፥9)፤ «እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም» (ቲቶ 3፥5) ተብሎ ተጽፏል:: በእነዚህ ሁለት አሳቦች መሠረት ሐዋርያው ስለ ራሱ፥ «በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ» («በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን የሆንሁትን ሆኛለሁ»፤ 1ቆሮ. 15፥10 አ.መ.ት.) የሚለውን መጻፉ አያስገርምም::

እነዚህ ጥቅሶች፥ እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ሰዎች ምን እንደሚሠሩ ወይም በ«ነጻ ፈቃዳቸው» የወንጌልን ቃል ሰምተው እንደሚቀበሉት ወይም እንደማይቀበሉት በማየቱና በማወቁ ረገድ፥ ሰዎችን ለድኅነት መርጦ ጸጋ ሊሰጣቸው ወስኗል ለሚለው አስተሳሰብ ስፍራ እንደሚሰጡ ማሰብ ይከብዳል:: ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ከእግዚአብሔር ምርጫ ሁኔታ ጋር (2ተሰ. 2፥13) እና በአዳም ካለው ከሰው ብክለት ጋር (ሮም 3፥11-18) እንደማይስማማ አስቀድመን አይተናል:: ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና» በማለት ጽፏል፤ ዮሐ. 1፥16::

## ለ) የጽድቅ መሠረት የክርስቶስ ደም ነው (9)

ሰው ኀጢአተኛ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፍ ፍጡር ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ጻድቅ ነውና ሕጉ ሲጣስ ተላላፊውን በቸልታ እንዲሁ ይቅር ማለት አይችልም:: እንግዲህ እግዚአብሔር ኀጢአተኛውን ሊያጸድቅ እንዴት ይችላል? የሚለው ጥያቄ ይነሣል:: «የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና» (ሮም 6፥23) ኀጢአተኛ ለራሱ ኀጢአት ከሞተ ወይም ንጹሕ የሆነ ሰው ከተገኘ፥ በኀጢአተኛው ስፍራ ሲሞት የሕግ ቅጣት ስለተከፈለ የኀጢአት ስርየት ሊገኝ ይችል ነበር:: ሌላ መንገድ አልነበረም፤ ምክንያቱም በማናቸውም የመንጻት ሥርዐት፥ «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብ. 9፥22) የሚለው መሠረታዊ ሐቅ አለ:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምእመናንን ኀጢአት በመሸከሙ (2ቆሮ. 5፥21፤ 1ጴጥ. 2፥24፤ 3፥18) የሕግ ዕዳን ከፈለላቸው (ሮም 3፥24፤ ገላ. 3፥13)፤ እግዚአብሔርም ጻድቅ ስለሆነ ሊያጸድቃቸው ቻለ፤ ሮም 3፥25-26:: ስለዚህ ምእመናን ኀጢአተኞችን በሚያጸድቅ አምላክ ያምናሉና ጽድቅ ይቈጠርላቸዋል፤ ሮም 4፥5:: በዚህ መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን» ብሎ ተስፋቸውንና ዋስትናቸውን ያረጋግጣል፤ ሮም 5፥9::

## ሐ) የጽድቅ መገኛ የክርስቶስ ሕይወት ነው (10)

እስረኛ በዳኛ ከፍርድ ነጻ ሲሆን፥ ቅጣት የለበትምና በሕግ ከመጠየቅ ነጻ ነው፤ ሆኖም በኅብተረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል:: እግዚአብሔር ግን ምእመናንን በክርስቶስ ስለመረጣቸው በክርስቶስ ይመለከታቸዋል፤ ወይም የክርስቶስ ጽድቅ ይቈጠርላቸዋል:: ነቢዩ ኤርምያስ ስለዚህ ታላቅ የተስፋ ቃል፥ «እግዚአብሔር ጽድቃችን ነው» ብሎ ተነበየ፤ ኤር. 23፥6፤ 33፥16:: ይህ ጽድቅ በአማኙ ጠባይ ወይም ሥራ መሠረት የሚገኝ አይደለም፤ ኢሳይያስ ደግሞ፥ «ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፤ ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ

ነው» ብሎ መስክሯል፤ ኢሳ. 64፥6፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በራሱ ጻድቅ ነውና፥ «በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ (ከእግዚአብሔር) የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፥ ጽድቃችንና ቅድስናችን፥ ቤዛችንም ሆኗል»፤ 1ቆሮ. 1፥30 አ.መ.ት.፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ዓላማ በክርስቶስ መሥዋዕታዊ ሞት መፈጸሙን ያሳያል፤ «እኛ በእርሱ (በክርስቶስ) ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኀጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው» ተብሎ ተገልጧል፤ 2ቆሮ. 5፥21፡፡ ይህ ትምህርት፥ እግዚአብሔር የክርስቶስን ጽድቅ ለኀጢአተኛው በመቍጠር (ሮም 4፥5) የኀጢአተኛውን ጠባይ ስመለወጥ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ጽድቅ ጻድቅ እንደሆነ በማወጅ እንደሚያጸድቅ በትኩረት ያስገነዝባል፡፡

## መ) የጽድቅ ማረጋገጫ መልካም ሥራ ነው

እግዚአብሔር ሰውን ያጸድቃል፤ ሆኖም ሰው መጽደቁን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ ሰው በራሱ ስለ ራሱ ሁኔታ በልዩ ልዩ መንገድ ሊያውቅ ይችላል፤ አብዛኛውን ጊዜ ሰው ካመነ በኋላ ወዲያውኑ ሁሉ ነገር አዲስ ይሆንለታል (2ቆሮ. 5፥17)፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ከመንፈሱ ጋር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ይመሰክራል (ሮም 8፥16፤ ገላ. 4፥6)፤ አሳቡ ከቀድሞው ይልቅ እግዚአብሔርንና ሰውን ወደ መውደድ ያዘነብላል፡፡ ሆኖም ትንሽ ቈይቶ አካሄዱ ካልተለወጠ ማለት መልካምን ሥራ መሥራት ካልጀመረ፥ ስለ ጽድቅ የተሰጠውን ትምህርትና ሁኔታውን ሊመረምር ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ብዙዎቹ እንደ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር ሰዎች እንደሆኑ እያሰቡ ቢኖሩም እንኳ፥ በእውነት የእግዚአብሔር አይደሉም፤ ሉቃ. 3፥7-9፤ ዮሐ. 8፥39-46፤ ሮም 2፥17-24፤ 9፥6-7፡፡

ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት እንደጸደቁ ለማወቅ ስንፈልግ የምናረጋግጠው፥ እግዚአብሔር ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ስጦታን ወይም አስተርእዮን ካልሰጠ በቀር፥ መልካም ሥራቸውን በማየት ብቻ ነው፡፡ ሰዎች ስለ እምነታቸው ሊመሰክሩ ይችላሉ፤ ሆኖም እምነታቸው ወደ መልካም ሥራ ባይመራቸው፥ የእምነታቸውን እውነተኛነት መጠራጠራችን አይቀርም፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘሪው ምሳሌ ስለ አራት ዐይነት መሬት ተናገረ፤ መልካምን ፍሬ ያፈራው ግን አንዱ ብቻ ነው፤ ማር. 4፥3-20፡፡ ያዕቆብ ደግሞ፥ «ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ብሎ ያስጠነቅቀናል፤ ያዕ. 2፥26፡፡

አንዳንድ ሰዎች ስለ መልካም ሥራ ሲያስቡ በመጀመሪያ ስለ ሃይማኖት ያስባሉ፡፡ ፈሪሳውያንም እንደዚህ ነበሩ፤ ሕግና ነቢያት በእጃቸው ነበሩ፤ በራሳቸው አተረጓጐም መሠረትም ሕግን አከበሩ፤ ትክክለኛ ትምህርት አስተማሩ፤ የሕጉን ሥርዐት በተለይ የግዝረትንና የሰንበትን ሥርዐት ጠበቁ፤ ይጾሙና ይጸልዩ፥ ወደ ምኵራብና ወደ ቤተ መቅደስም ይሄዱ ነበር፤ ዐሥራት እያወጡ ይሰጡ ነበር፤ ሥርዐት ጠበቁ፤ መንፈሳዊው ባህላቸው የሚፈቅደውን ልብስ በመልበስም ሰላምታ ሲሰጧቸው ኖረዋል፤ ሰዎችን ያከብሩ ነበር... ወዘተ፤ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች አልተቀበላቸውም፡፡

የተወሰኑ ሰዎች ስለ መልካም ሥራ ሲያስቡ፥ ስለ ሰው ልግስና፥ ችግረኞችን በጊዜ፥ በጕልበት፥ በሌላም መንገድ ስለ መርዳት፥ በኅብረተሰብ ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው የትብብር መንፈስ... ወዘተ ያስባሉ፡፡ እውነት ነው፤ የእግዚአብሔር ሰው ሰውን ይወዳል፤ ሆኖም የመጀመሪያው ትእዛዝ እግዚአብሔርን መውደድ ነውና ሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ቸርነትን ማሳየት ይችላል፡፡

የቀሩት ደግሞ የሰውን ጠባይና በጠባይም ውስጥ እውነተኛ ለውጥ መታየት እንዳለበት ለመመልከት ይሞክራሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ» ወይም በዐጭሩ፥ «ዛፍ በፍሬዋ ትታወቃለች» ብሎ የሰው ጠባይ በቃላቱና በአካሄዱ የሚታይ መሆኑን ገልጧል፤ ማቴ. 12፥33-37።

እንግዲህ «መልካም ሥራን» (ኤፌ. 2፥10) ከአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት አይገባንም። ምክንያቱም ሰው በክርስቶስ ሲያምን፥ ከክርስቶስ ጋር አንድነት አለውና ይህ አዲስ ግንኙነት በሰው ሕይወት ሁሉ መታየት ይጀምራል። በዚህ መሠረት ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ እግዚአብሔር ሰዎች፥ ስለ ኀጢአት፥ ስለ አኗኗር ሁሉ፥ ስለ ሰውም ሁሉ አዲስ አማኝ ያለው አመለካከት ይለወጣል (2ቆሮ. 5፥17)፤ አዲሱ አመለካከትም በጻድቅ ቃላትና በአካሄድ ሁሉ ይገለጣል።

## ሠ) የጽድቅ መንገድ እምነት ብቻ ነው (11)

ሰው እንዴት ሊጸድቅ ይችላል? ለሚለው ጥያቄ ሦስት ዐይነት መልሶች ይሰጣሉ። መጽደቅ የሚቻለው በሥራ ነው ብለው መልስ የሚሰጡ የሃይማኖት ክፍሎች አሉ። ክርስቲያኖች ግን ኀጢአተኞች መሆናቸውን ተገንዝበውና ጽድቅ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሆኑን አስተውለው፥ ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ ነው ወይም በእምነትና በሥራ ነው ይላሉ። በእነዚህ ሁለት መልሶች መካከል ከፍ ያለ ልዩነት አለና ምዕራባውያን በተለይ ፕሮቴስታንቶች በእምነት ብቻ ነው ማለታቸው፥ ከካቶሊኮች ለመለየታቸው ዋና ምክንያት አድርገው ይቈጥሩታል። እንደ ካቶሊኮች ሁሉ ከምሥራቃውያን የሚበዙቱ ጽድቅ በእምነትና በሥራ መሠረት የሚሰጥ መሆኑን ያስተምራሉ።

እስካሁን ስለ ጽድቅ ምንጭ፥ መሠረት፥ መገኛና ማረጋገጫ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ትምህርት አተተናል። አሁን ደግሞ ስለ ጽድቅ መንገድ በሚከተሉት አራት ነጥቦች ላይ የተሰጠውን ትምህርታዊ ማብራሪያ ለማሳየት እንሞክራለን። ይህን ማሳየት ግን ቀላል አይደለም፤ ምክንያቱም ሰዎች ስለ «ጽድቅ»፥ ስለ «እምነት»፥ ስለ «መልካም ሥራ»... ወዘተ ሲናገሩ፥ አንድ ዐይነት አሳብ የላቸውም። ይህ ልዩነት በሐዋርያው ጳውሎስና በያዕቆብ የቃላት አጠቃቀም ላይ ሳይቀር ይታያል፤ ስለዚህ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናል።

### 1. ሰው በእምነት ብቻ ስለ መጽደቁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች

የዚህ ትምህርት ዋና አንቀጽ ሮም 3፥21-31 ነው። ከዚህ አንቀጽ ቀደም ብሎ አይሁድ ሕግን በመፈጸም እንደሚጸድቁ ማመናቸው ከንቱ እንደሆነ ሐዋርያው አስገንዝቧል፤ ምክንያቱም እስራኤላውያን በእውነት ሕግን አልፈጸሙምና ሕግ እነርሱን በማጽደቅ ፈንታ ኰነናቸው። አሕዛብም የተፈጠረውን በማምለክ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥተዋል፤ ሮም 1፥18-3፥20። ዋናው የጳውሎስ ክርክር ከአይሁድ ጋር ያደረገው ነበረና ወደ ጽድቅ መንገድ ተመልሶ፥ «የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና» ብሎ ስለ እነርሱ በመናገር የጽድቅ መንገድ በእምነት ብቻ በመሆኑ ላይ እንደገና አተኰረ፤ ሮም 10፥3-4። በሮም 3፥21-26 ሰው እንዴት በእግዚአብሔር ጸጋና በክርስቶስ ደም እንደሚጸድቅ ከዚህ በላይ አሳይተናል፤ ሐዋርያው አሁንም ሰው በእምነት መንገድ መጽደቁን ደጋግሞ

ሲያስተምር የሕግ ሥራ (እዚህ ላይ ሕግ ስንል ሕገ ልቡናን፥ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን ሊያጠቃልል ይችላል) በሰው መጽደቅ ውስጥ ስለ መኖሩ እንዳችም ፍንጭ ባለመስጠት፥ ሕግን መፈጸም ያለበት መሆኑን ውድቅ አድርጎታል። በመጀመሪያ ሐዋርያው ሕግና ነቢያት ቢመሰክሩለትም፥ የእግዚአብሔር ጽድቅ (ለሰው የሚቈጠረው የእግዚአብሔር ጽድቅ) «ያለ ሕግ» («ከሕግ ውጭ የሆነ»፥ «ከሕግ ነጻ ሆኖ»፤ ቍ. 21 አ.መ.ት. እና ቀ.አ.) በክርስቶስ መምጣት እንደተገለጠ ያሳያል። ከዚያም በኋላ ሰው በእምነት እንደሚጸድቅ በሚከተለው አኳኋን ደጋግሞ ይገልጣል:-

- «<u>ለሚያምኑ</u> ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ <u>በማመን</u> የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ» (ቍ. 22)፤

- «እርሱንም (ክርስቶስንም) እግዚአብሔር <u>በእምነት</u> የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው» (ቍ. 25)፤

- «ራሱም (እግዚአብሔርም) ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም <u>የሚያምነውን</u> እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው» (ቍ. 26)፤

- «ትምክሕት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቷል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም <u>በእምነት</u> ሕግ ነው» (ቍ. 25)፤

- «ሰው ያለ ሕግ ሥራ <u>በእምነት</u> እንዲጸድቅ እንቈጥራለንና» (ቍ. 28)፤

- «እግዚአብሔር... የተገረዘን ስለ እምነት፥ ያልተገረዘንም <u>በእምነት</u> የሚያጸድቅ... አምላክ ነው» (ቍ. 29-30)፤

- «እንግዲህ ሕግን <u>በእምነት</u> እንሽራለንን? አይደለም ሕግን እናጸናለን እንጂ»፤ ቍ. 3።

ማርቲን ሉተር ቍጥር 28ን ሲተረጕም፥ «ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት ብቻ እንዲጸድቅ እንቈጥራለንና» ብሎ እንደጻፈ የታወቀ ነው። «ብቻ» የሚለው ቃል በግሪክ አይገኝም፤ ሆኖም ሉተር ይህን ጥቅስ በዚህ ዐይነት በመተርጐም በሐዋርያው አሳብ ላይ እንዳተኰረ ብዙዎች ይስማማሉ፤ ጠቅላላ አንቀጹ የጽድቅ መንገድ በእምነት ብቻ መሆኑንና የሕግ ሥራም በጽድቅ ውስጥ ስፍራ እንደሌለው (በተለይ ቍ. 21፡27፡28፡31 ይመ.) ይገልጣልና።

በቍጥር 29-30 ላይ እንዳየነው አይሁድና አሕዛብ በአንድ መንገድ ማለት በእምነት እንደሚጸድቁ ተመልክተናልና በምእመናን መካከል ልዩነት እንዲኖር ማድረግ ከፍ ያለ ስሕተት ነው። በዚህ ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ በአንጾኪያ ኀይለኛ ወቀሣ በጴጥሮስ፥ በበርናባስና በሌሎች አይሁድ ላይ ሰነዘረ፤ ገላ. 2፥14-21። በወቀሣው ውስጥ፥ «ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን ዐውቀን ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» ብሎ የጽድቅ መንገድ በሕግ በኩል ያለመሆኑንና በእምነት የመሆኑን አሳብ ደግሞ ተናገረ፤ ቍ. 16። ንግግሩንም ሲጨርስ፥ «የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ» በማለት ክርክሩን ደመደመ፤ ቍ. 21።

በሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት ውስጥ ሰው ሁሉ በእምነት ብቻ መጽደቁ መሠረታዊ ሐቅ ነው። ይህም ለምሳሌ፥ «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» በሚለው ጥቅስ ይታያል፤ ኤፌ. 2፥8-9።

ሮም 4፥5፤ 2ተሰ. 2፥13፤ 2ጢሞ. 1፥9 እና ቲቶ 3፥5 ይህን እውነት የሚያሳዩ ሌሎች ጥቅሶች ናቸው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኀይል ለተጠበቃችሁ...» በማለቱ፥ ትምህርቱ ከጳውሎስ ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆኑ ይታያል፤ 1ጴጥ. 1፥3-5 ደግሞም 1፥18-19 ይመ.:: ከሁሉም በላይ «እምነትህ አድኖሃል» የሚለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ከዚህ ትምህርት ጋር እንደሚስማማ ግልጥ ነው::

## 2. ሰው በእምነት ብቻ መጽደቁ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ (12)

ከታወቁት አበው መካከል አንዳንዶች ይህን ትምህርት እንደሚቀበሉት ይታወቃል፤ ማስታወሻ 10 እና 11 ይመ.:: ሆኖም እስከ ፔላጊዮስ ዘመን ድረስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ጽድቅ መንገድ ብዙ ክርክር አልነበረምና በዚህ ትምህርት ላይ የጠራ አቋም የነበራቸው ላይመስለን ይችላል:: በተለይም እምነትና ጽድቅ እንዴት እንደሚገናኙ አላብራሩም፤ ዳግመኛ በመወለድና በመጽደቅ መካከል ልዩነት መኖሩንም በግልጥ አላሳዩም:: ብዙዎች ሰው ሲጠመቅ ዳግመኛ ይወለዳልና ይህ የኀጢአት ስርየትን እንደሚያጠቃልል አስተማሩ:: አውግስጢኖስ ምንም እንኳ በሰው ድኅነት ውስጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ነጻ፥ ልዑላዊና ውጤታማ መሆኑን በግልጥ ቢያስተምርም፥ ማጽደቅ ሕጋዊ ዐዋጅ መሆኑንና ከመቀደስ ግብረገባዊ ሂደት የተለየ እንደሆነ አላሳየም:: በምዕራባውያን ዘንድ እስከ ተሐድሶ ዘመን ድረስ ማጽደቅና መቀደስ ተደበላልቀው ይታዩ ነበር:: አኩናስ በማጽደቅ ውስጥ ሁለት ክፍሎች እንዳሉ አስተማረ፤ እነርሱም:- ሰው ጻድቅ እንዲሆን ይደረጋልና ኀጢአቱ ይሰረይለታል፤ እንዲሁም በዚህ ሥራ መሠረት ጸጋ በሰው ስለሚተከል፥ ይህ ከፊል ጸጋ ስለ ኀጢአቱ ይቅርታ ያስገኝለታል የሚሉት ናቸው:: ይህም ትምህርት፥ «የሰው መልካም ሥራ ዋጋ አለው» ለሚለው ትምህርት ምቹ መንገድ ከፈተ:: ከዚህም ሁሉ ጋር አንዳንዶች ማጽደቅ አንድ ጊዜ የሚፈጸም ድርጊት እንደሆነ ሲያስተምሩ፥ የቀሩት ማጽደቅን እንደ ሂደት ቈጠሩት::

የተሐድሶ መሪዎች ከዚህ በላይ ባተትነው መሠረት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት ተከትለው የጽድቅን ትምህርት አስተማሩ:: ይህም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚለዩበት ዋና መታወቂያቸው ሆነ:: ማርቲን ሉተር በእምነት ብቻ የመጽደቅ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን የምትጸናበት ወይም የምትወድቅበት ትምህርት መሆኑን ገለጠ:: ዮሐንስ ካልቪንም ይህን ትምህርት፥ ሃይማኖት የተለየ አቅጣጫ እንዲይዝ የተደረገበት ዋና ነጥብ አድርጎ ገለጠው (13):: በፕሮቴስታንቶች ዘንድ በዚህ የተሐድሶ መሪዎች ትምህርት ላይ አዳዲስ ነጥቦች አልተጨመሩም:: አንዳንዶች ይህን ትምህርት ቢጠቅሱትም፥ ልዩ ልዩ ነጥቦችን በማጣጣል አይቀበሉትም::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰው በእምነትና በሥራ እንደሚጸድቅ ማስተማር የተለመደ ሆኗል:: ይሁን እንጂ በሁሉም ዘንድ ባይሆንም፥ ሰው የሚጸድቀው በሥራው ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው የሚለው ትምህርትም ይታወቃል:: ከዚህ በላይ በአበው ትምህርት ውስጥ ይህ እውነት መኖሩን አይተናል:: በ1935 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ታትሞ በኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደገና ታርሞ በቅርብ ጊዜ በተዘጋጀው «የቤተ ክርስቲያን ጸሎት» በሚለው መጽሐፍ ገጽ 93-94 ላይም፥ ስለ ጽድቅ ትምህርት የተጻፉ አንዳንድ አረፍተ ነገሮችን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን (14):-

«የጽድቅ መንገድ

«ስለዚህ እኛ ሁላችን ይህንን የማያሳስት እውነተኛውን የጽድቅ መንገድ ክርስቶስን ብቻ ይዘን ከሄድን ዘወትር እየናፈቅን አባታችን ሆይ፤ እያልን ከምንጠራው ከሰማያዊ አባታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ሰማያዊት አገራችን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደርሳለን፤ ዳግም በሥራችን እንጸድቃለን፤ መንግሥተ ሰማያት እንገባለን ብለን አንመካም፤ የምንጸድቅበት ሃይማኖታችን ክርስቶስ ብቻ ነው።...

«ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ጽድቅ በሃይማኖት (በእምነት) እንዲገኝ ሥራ በመሥራት እንዳይገኝ በጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ ያስተምረናል። «ሰው ሥራ ሳይሠራ በሃይማኖት ብቻ እንዲጸድቅ እናውቃለን» ብሏል፤ ሮም 3፥28 (ከቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ትርጉም በፊት ከተዘጋጀው ከመጽሐፈ ጸሎት የተወሰደ)።

«ስለ መልካም ሥራ

«ሰው ሁሉ የሚጸድቀው በእግዚአብሔር ጸጋና በክርስቶስ ሞት፥ በሃይማኖትም ነው እንጂ በሥራው ለመጽደቅ አይችልም ብለናል። ነገር ግን በሃይማኖት ብቻ እንጸድቃለን ስላልን የታዘዘውን በጎ ሥራ አንሠራም ማለት አይደለም። እውነተኛው ሕያው ሃይማኖት ያለ መልካም ሥራ አይገኝም። ዛፍ በፍሬው እንዲታወቅ እንዲሁም ሃይማኖታችን በሥራችን ይታወቃል፤ ማቴ. 7፥16-21።

«የሃይማኖትና የመልካም ሥራ ትርጓሜያቸው ይህ ነው፤ ሃይማኖት ለመጽደቂያ፤ መልካም ሥራ የሃይማኖት መገለጫ ነው። መልካም ሥራ የሠራን እንደሆነ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መሆናችን ይታወቃል፤ ዮሐ. 15፥8።»

3. በዚህ ትምህርት ላይ የተነሣ የተቃውሞ ክርክር

ሰው በእምነት ብቻ ይጸድቃል ስለሚለው ትምህርት ብዙ ክርክር ተነሥቷልና ትምህርቱን የተቃወሙት ብዙ ዐይነት ምክንያት ያቀርባሉ። ብዙዎቹ፥ ሰው በእምነት ብቻ ከጸደቀ መልካም ሥራ መሥራት አያስፈልገውም ይላሉ። የትምህርቱ ደጋፊዎች ግን ሰው በእምነት ብቻ ይደጸድቃል፤ ይህ እምነት ግን ያለ መልካም ሥራ አይኖርም የሚል አቋም አላቸው፤ ምክንያቱም «ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ተብሏል፤ ያዕ. 2፥26። የዚህ ትምህርት ተቃውሞ በተለይ በአራት አርእስት ላይ የሚያተኩር ነውና አንድ በአንድ አርእስቱን ብንመረምራቸው አሳባችንን የጠራ ለማድረግ ሊረዳን ይችላል (15)።

ሀ) ሕግና ፍርድ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚፈጽሙ እንደሚባረኩ፥ የማይፈጽሟቸው ደግሞ እንደሚፈረድባቸው አስጠንቀቀ፤ እንደዚሁም የመጨረሻው ፍርድ ሰዎች በሠሩት ሥራ መሠረት የሚሰጥ መሆኑን ገለጠ፤ ይህም በተለይ በምሳሌዎቹ ይታያል። «ሰው በእምነት ብቻ ይጸድቃል» የሚለውን ትምህርት የሚቃወሙ ሰዎች እንግዲህ ሰው በእምነትና በሥራ ይጸድቃል ይላሉ።

ይህን ሲያስቡ የሕግ ሥራ ምን እንደሆነ የረሱ ይመስላል። ሕግ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጣልና ባሕርያቱን ያንጸባርቃል። የአዳም ዘር የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም ያለመቻሉንና ያለመፈለጉን ጠባይ ሲያስተውል

ይጀምራልና ወደ ክርስቶስ ወንጌል እንዲደርስ ሕግ «ሞግዚቱ» ሆኗል፤ ገላ. 3፥23-24:: ሰው ክርስቶስን ወደ ማመን ደርሶ እግዚአብሔርን ማስደሰት ይፈልጋልና የእግዚአብሔር ሕግና ፈቃድ የአዲሱ ሕይወት መሪ ናቸው:: መሪ የሚሆኑትም በመልካም ሥራው ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ፥ በክርስቶስ ደምና በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ምስጋና ስለሚያቀርብ እንጂ እንዲጸድቅ አይደለም::

ለ. እምነት

ትምህርታችንን የሚቃወሙ ሰዎች የበጎችንና የፍየሎችን ምሳሌ ሊጠቅሱ ይፈልጋሉ፤ ማቴ. 25፥31-46:: በበጎች የተመሰሉት የክርስቶስን ወንድሞች በችግራቸው ሁሉ ስለረዱ፥ ጻድቃን ሆነው ወደ ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ፤ በፍየሎች የተመሰሉት ግን ወንድሞቹን በችግራቸው ባለመርዳታቸው፥ ርጉማን ሆነው ወደ ዘለዓለም ቅጣት ይሄዳሉ በማለት በጎች በመልካም ሥራቸው እንደጸደቁ ያትታሉ:: እውነታቸውን ነው፤ ይሁን እንጂ ይህ አሳብ በፊደላዊ ትርጉም የምሳሌውን ሰም ብቻ በመመልከት ወርቁን ከመሳት የተነሣ የሚነገር ነው:: በምሳሌው የክርስቶስ ወንድሞች እነማን ናቸው? በጎች ለምን ረዷቸው? ፍየሎችስ ያልረዷቸው ለምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ፥ ወደ ወርቁ መግባት እንችላለን:: ይህ ምሳሌ ለደቀ መዛሙርት የተነገረ መሆኑን መገንዘብ ይገባናልና ከዚያ በፊት ክርስቶስ፥ «... እነሆ እናቴ ወንድሞቼም:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ ነው፤ እኅቴም እናቴም» በማለት የእርሱ ወንድሞች እነማን እንደሆኑ ሲናገር ደቀ መዛሙርቱ ሰምተውት ነበር፤ ማር. 3፥34-35:: በዚህ መሠረት በጎቹ፥ ደቀ መዛሙርቱ የተቸገሩ ወንድሞቻቸው መሆናቸውን ዐውቀዋል፤ የክርስቶስ ወንድሞች ነበሩና እነርሱ በአስፈላጊው ነገር ሁሉ ወንድሞቻቸውን ለመርዳት ልባዊ ፍላጎት ነበራቸው:: ፍየሎቹ ግን ከክርስቶስ ወንድሞች ጋር ምንም ዝምድና የላቸውምና እነርሱን ለመርዳት ምንም ስሜት አልነበራቸውም:: ከዚህም ቀጥሎ በምሳሌው ክርስቶስ ከወንድሞቹ ጋር ራሱን አንድ ያደርጋልና ለእነርሱ የተደረገ ነገር ሁሉ ለእርሱ እንደተደረገ የሚቈጠር መሆኑን እንመለከታለን፤ ከዚህም የተነሣ የበጎች ጽድቅና የፍየሎች ቅጣት ምክንያት በይበልጥ ይታያል:: የምሳሌውን ወርቅ በሚገባ ከተረዳነው፥ ምንም እንኳ የተለመደ ቢሆንም፥ ማናቸውንም የተቸገረ ሰው ሁሉ ስለ መርዳት በዚህ ምሳሌ መሠረት ማስተማር ትክክለኛ አተረጓጐም አለመሆኑን ማስተዋል ይቻላል፤ ይህንኑ ከመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ ተነሥተን ማስተማር ይገባናል፤ ሉቃ. 10፥ 29-36:: የዐሥሩ ቈነጃጅትና የመክሊቶቹ ምሳሌዎች (ማቴ. 25፥1-13:14-30) እጅግ ተመሳሳይነት አላቸው:: በቈነጃጅቱ መካከል የነበረው ልዩነት ለሙሽራው የነበራቸው የወዳጅነት ደረጃ ሲሆን፥ በባሪያዎች መካከል የነበረው ልዩነት ደግሞ ለጌታቸው የነበራቸው የአክብሮት ደረጃ ነበረ:: እንደዚሁም በጎቹ ክርስቶስን ዐውቀው ስለወደዱት ሌሎች ወንድሞቻቸውን ወደዱ፤ ፍየሎቹ ግን ክርስቶስን አልወደዱትምና የክርስቶስን ወንድሞች አልወደዱም:: ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «... ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?» በማለት መልስ ዐዘል ጥያቄ አቅርቧል፤ 1ዮሐ. 4፥20::

ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር የተመሠረተውን ይህን ግንኙነት «በክርስቶስ» ብሎ ደጋግሞ ይገልጠዋል፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ኤፌ. 1፥3-6:9-13:: «ሰው በክርስቶስ» እንዴት ይሆናል? ተብለን ብንጠየቅ፥ መልሳችን በእምነት ነው የሚል ሊሆን ይገባል፤ ስለ ክርስቶስ ማንነትና ግብር የሚሰጠውን ትምህርት በአሳብ ደረጃ መቀበልን ብቻ ሳይሆን፥ ከልብ መላ ሕይወትን ለእርሱ

ማስረከብንና ተስፋን ሁሉ በእርሱ ላይ መጣልን ጭምር የሚመለከት ነው፤ ገላ. 3፥26፤ ኤፌ. 1፥13:: እውነተኛና ሕያው የሆነው ይህ እምነት አማኙን ከክርስቶስ ጋር አንድ ያደርገዋል፤ ስለዚህ «በክርስቶስ ነው»:: በዚህ ዐይነት እምነት መሠረት እንደ አብርሃም ለሚያምነው ሁሉ ጽድቅ ይቈጠራል፤ ዘፍ. 15፥6፤ ሮም 4፥3:: ጽድቅ የመቈጠሩ ጉዳይ እንደ ዋጋ ወይም እንደ ውጤት የሚታይ አይደለም (ሮም 4፥5)፤ ምክንያቱም እምነት ከክርስቶስ ጋር የሚደረግ የግንኙነት ትስስር ነው እንጂ እንደ ሥራ የሚቈጠር አይደለም:: ለአማኙ የሚቈጠርለት ጽድቅም የአማኙ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር፥ በተለይም የክርስቶስ እንደሆነ ከዚህ በላይ ያየን መሆናችንን መርሳት የለብንም::

አንዳንዶች የክርስቶስ ጽድቅ ለአማኝ መሰጠቱ «ሕጋዊ መላምት» ይመስል ይላሉ:: ሆኖም ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት ነውና ኀጢአቱንና የልቡን ፍጹም ብክለት ለማወቅ የጀመረ አማኝ ከራሱ ጽድቅ እንደሚገኝ ሲያስብ እንዴት የበለጠ ቅዠት ይመስለው!

ሐ) ጽድቅ

ሌሎችም፥ «ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ» (ያዕ. 2፥24) በማለት ያዕቆብ የተናገረውን ይጠቅሳሉ:: እውነት ነው፤ በመጀመሪያ አመለካከት ያዕቆብ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አይስማማም፤ ሆኖም አስቀድመን እንዳየነው ያዕቆብ «እምነት» ሲል አሳቡ ትክክለኛ ትምህርትን እንጂ የልብን ዝንባሌና ፈቃድ አያጠቃልልም:: «ጻድቅ» እና «መጽደቅ» በተባሉት የቃላት አጠቃቀም የያዕቆብ አሳብ ከጳውሎስ አሳብ መጠነኛ ልዩነት ይታይበታል:: የያዕቆብ ትኵረት እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነውና በሰዎች ዘንድ እውነተኛ እምነት በሥራ ይታወቃል በሚለው ላይ ነው:: ያዕቆብ እንግዲህ አብርሃም የሰማንያ አምስት ዓመት ሰው ሆኖ በእግዚአብሔር እንዳመነና እምነቱ ጽድቅ ሆኖ እንደተቈጠረለት ያውቃል (ያዕ. 2፥23)፤ ከዚያም በኋላ አብርሃም የመቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ገደማ ሰው ሳለ፥ «እምነት ከሥራው ጋር ዐብሮ ያደርግ እንደነበር በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን?» በማለት ስለ አብርሃም ያቀረበውን መልስ ዐዘል ጥያቄ ጽፏል፤ ያዕ. 2፥22:: አብርሃም ከዚህ በፊት በአካሄዱ የእምነት ሰው እንደነበረ ቢታወቅም፥ ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ታዛዥ መሆኑ አልተገለጠም፤ ይህ የታየው ሳይከራከር ቃል ኪዳን የሚፈጸምበትን አንድያ ውድ ልጁን ለመሠዋት ፈቃደኛ በመሆኑ ነው፤ ይህንም ሲያደርግ እምነቱ ፍጹም ሆኗል:: ይህ ዐይነቱ አባባል ስለ ክርስቶስም ተደግሞ ተጽፏል:: ክርስቶስ ሲወለድ ፍጹም አምላክ፥ ፍጹምም ሰው ነበረ:: ባደረገው ሁሉ ለወልድነቱ፥ ለአምላክነቱ ወይም ለትስብእቱ ምንም አልተጨመረም፤ ሆኖም ስለ እርሱ፥ «ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ» ተብሎ ተመሰከረ፤ ዕብ. 5፥8:: ከመጀመሪያ አንሥቶ እግዚአብሔር የአብርሃም እምነት እውነተኛ መሆኑን ዐወቀ፤ ከዚህ የተነሣ ለሌሎች ሰዎች ምናልባትም ለአብርሃም ለራሱ ጭምር ቢላዋ አንሥቶ ልጁን ለመሠዋት ፈቃደኛ መሆኑ ተገለጠ፤ እግዚአብሔርም ፍጹም ታዛዥ መሆኑን መሰከረለት፤ ዘፍ. 22፥12-18::

መ) ይቅርታ

ሌሎች ደግሞ፥ ሰው በእምነት ከጸደቀ ለኀጢአቱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲጠይቅ ለምን ይጠበቅበታል? እርሱ ጻድቅ አይደለምን? ብለው መጠየቅ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፥ «በኀጢአታችን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ይላል፤ 1ዮሐ. 1፥9:: ሆኖም

ይቅርታ የሚጠየቅባቸው ሁለት ዐይነት ሁኔታዎች አሉ:: ሰው በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ ሲቀርብ ከእግዚአብሔር ቀጥ እንዲድን (ሐ.ሥ. 16፥30-31) ይለምናል:: ካመነ በኋላ ግን ከእግዚአብሔርና ከሌሎች አማኞች ጋር ያለው ኅብረት ይታደስ ዘንድ ከእግዚአብሔር አባታዊ ተግሣጽ እንዲድን ይለምናል እንጂ፥ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን አይለምንም፤ 1ዮሐ. 1፥5-2፥21::

በዚህ ትምህርት መሠረት አማኞች የእግዚአብሔር ልጆች፥ ወራሾችና ጻድቃን መሆናቸውን፥ ለዘለዓለምም እንደማይጠፉ ዐውቀው በዋስትናቸው መደሰት ይችላሉ:: ይህም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ሁሉ በማመናቸው የሚሆን እንጂ ዐጉል ድፍረት አይደለም:: ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን እውነት ለማሳየት የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈ፤ 1ዮሐ. 5፥13::

## 4. ሰው በእምነትና በሥራ ስለ መጽደቁ የሚሰነዘር አንዳንድ አስተያየት

ሰው በእምነትና በሥራ መጽደቁን የሚያምኑ ስለ እግዚአብሔር ልዕልናና ስለ ቅድስናው፥ ስለ ሰው በኀጢአት መበከል ወይም ስለ እግዚአብሔር የድኅነት ምርጫ ብዙ አይናገሩም:: ትምህርታቸው በተለይ የሚያተኩረው ሰው በሥራ በመጽደቁ ላይ ነው:: ሆኖም ሰው በሥጋ ምክንያት ስለደከመ በሥራው ጒድለት ይኖርበታልና ሕጉን አይፈጽምም:: ከዚህም በላይ ሰው በሥራ በመጽደቁ ተግባር ከተካፈለ በቂ ሥራ እንደሠራ በምን ሊያውቅ ይችላል? እግዚአብሔር በልዩ አስተርእዮ ካልገለጠለት ሰው ይህን ሊያውቅ አይችልም፤ ስለዚህ ብዙ ሰው ስለ መዳኑ ርግጠኛ ሊሆን አይችልም፤ አለኝታም አይኖረውም፤ ስለ መዳኑም ምስጋና ማቅረብ አይችልም፤ ምስጋና ካለማቅረቡ የተነሣም እግዚአብሔርን ለማስደሰት አይሞክርምና በጠቅላላውም ደስተኛ አይሆንም:: ከዚህ በላይ ግን ምእመናን ስለ መዳናቸው ርግጠኞች እንዲሆኑ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አይተናል:: ሐዋርያት ስለ መዳናቸው ጥርጥር አልነበራቸውም፤ ስለዚህ ጴጥሮስ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን... ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኀይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል» (1ጴጥ. 1፥3-5)፤ ዮሐንስም፥ «አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን... እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን» (1ዮሐ. 3፥1-2)፤ ጳውሎስ ደግሞ፥ «ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብዬአለሁ፤ ነገር ግን አላፍርበትም፤ ያመንሁትን ዐውቃለሁና፤ የሰጠሁትን ዐደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ»፤ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም» (2ጢሞ. 1፥12፤ 4፥8) ብለው ጽፈዋል::

## ረ) የቅድስና ደረጃ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ነው

ምእመናን ሁሉ «ቅዱሳን» ናቸው (ሐ.ሥ. 20፥32፤ ኤፌ. 1፥1፤ ፊል. 1፥1፤ ቆላ. 1፥2)፤ ምክንያቱም «የተቀደሱት» (ሐ.ሥ. 26፥18-19፤ 1ቆሮ. 1፥2) እና «ተቀድሳችኋል» (1ቆሮ. 6፥11) ተብለዋል፤ ይህም የሆነው በተለይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ በመሆናቸው ነው፤ ሐ.ሥ. 26፥18፤ 1ቆሮ. 1፥2፤ 6፥11:: እንግዲህ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ወዲያውኑ ወደ ቅድስና አቋም ይገባል፤ ቅዱስ ነው፤ እንደ ጽድቅ ሁኔታ አንድ ጊዜ ለዘለዓለም የተፈጸመ ጒዳይ ነው::

ስለዚህ ሁኔታ ብዙ ጥቅሶች ይናገራሉ፤ በተለይም:-

«ለኀጢአት የሞትን... አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን» (ሮም 6፥2:6)፤

«አስቀድማችሁ የኀጢአት ባሪያዎች ከሆናችሁ... ከኀጢአት ዐርነት ወጥታችሁ» (ሮም 6፥17-18)፤

«በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል... ለሌላው ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ... ለእርሱ ለታሰርንበት ስለሞትን ከሕግ ተፈትተናል፤ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም» (ሮም 7፥4-6)፤

«ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ ተሸከመ» (1ጴጥ. 2፥24) የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከእነዚህና ከሌሎች ጥቅሶች አማኙ በክርስቶስ በመሆኑ፥ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተባብሮ ከኀጢአት ኀይል፥ ከሕግ ባርነትና ከሞት መንፈሳዊ ቅጣት ተፈትቷልና ወደ ጽድቅ አቋም፥ ወደ ዐርነት፥ ወደ ዘለዓለም ሕይወትና ወደ ቅድስና አኗኗር ገብቷል። ይህ አቋም በተለይ በሦስት መንገድ ይታያል:-

1. ሰው ወደዚህ አቋም የሚገባው፥ በክርስቶስ መንፈሳዊና ምሥጢራዊ መንገድ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆኑ ከሞቱና ከትንሣኤው ጋር ራሱን አንድ በማድረጉ ነው፤ ሮም 6፥1-14፤ 2ቆሮ. 5፥14-15።

2. ሰው ወደዚህ ሁኔታ ሲገባ ከቀድሞ ሁኔታው በመሠረቱ ይለያል፤ አሮጌው ሰው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል፤ ሮም 6፥6። ይህም በአኗኗሩ ፈጽሞ ቅዱስ አኗኗር ይኖረዋል ማለት አይደለም፤ ሆኖም ለኀጢአት እንደሞተና ለእግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ ሊቈጠር ታዝዟልና ብልቶቹን ለዐመፃ ባርነት ሳይሆን፥ ለጽድቅ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል (ሮም 6፥11:19)፤ ምክንያቱም እንደ በፊቱ ኀጢአት አይገዛውም፤ ጸጋ የሚገዛው እንጂ ሕግ የሚገዛው አይደለምና፤ ሮም 6፥14።

3. መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ ይኖራል፤ አማኙም የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው (ዮሐ. 14፥17፤ 1ቆሮ. 6፥19-20)፤ በእርሱ ኀይል በክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቅድስና መንገድ ፍጹም እስኪሆን ድረስ እየበረታ ይሄዳል፤ 1ተሰ. 4፥4-8፤ 5፥23-24።

# ማስታወሻ

(1) በም. 24ሠ እና 24ረ ስለ እግዚአብሔር ቅድስናና ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ሰፊ ትንታኔ አቅርበናል፤ በም. 71ሐ ከኀጢአት በደል ወደ ጽድቅ - የፍርድ ቤት አገላለጥ በሚለው ንኡስ ርእስ ክርስቶስ በመስቀል ሞት ሥራ እንዴት እንዳጸደቀን ገልጠናል። በ«አስደናቂው ልውወጥ» (አዕማድ መጻሕፍት ቍ. 21) ሰውን ስለ ማጽደቅ የእግዚአብሔር ሥራ ብዙ አትተናል። ሰውን የማጽደቅ የእግዚአብሔር ሥራ በእንግሊዝኛ Justification ይባላል።

(2) P.G.R. በገጽ 191 Leon Morris The Apostolic Preaching of the Crossን ይጠቅሳል።

(3) Berkhof ገጽ 510 - 511 ይመ.

(4) ይህ ክፍል በተለይ በBerkhof ገጽ 511-513 ላይ የተመሠረተ ነው::

(5) ይህ ክፍል ደግሞ በተለይ በBerkhof ገጽ 513-514 ላይ ተመርኩዞ የቀረበ ነው::

(6) Berkhof ገጽ 517-520፤ «አስደናቂው ልውውጥ» ም. 10 ይመ.

(7) ስለ ጽድቅ ምንጭ «አስደናቂው ልውውጥ» (አዕማድ መጻሕፍት ቍ. 21) በሚለው መጽሐፍ ም. 3 ላይ በሰፊው ጽፈናል::

(8) P.G.R. ገጽ 194-195 ይመ.

(9) ሰው በክርስቶስ ደም ስለ መጽደቁ በም. 69 እና 70 በሰፊው ጽፈናል:: «አስደናቂው ልውውጥ» ም. 4 ደግሞ ይመ.

(10) ሰው በክርስቶስ ሕይወት ጻድቅ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚገኝ በም. 54 እና 71 በሰፊው ጽፈናል:: «አስደናቂው ልውውጥ» ም. 4 ገጽ 64-65 ደግሞ ይመ.:: አበው የምእመናን ጽድቅ በክርስቶስ የተገኘ መሆኑን ለማሳየት እንደሚከተለው ጻፉ:-

ሀ) ኤራኒዮስ፥ «ከድንግል በተወለደው በአንዱ ሰው መታዘዝ ብዙዎች ጸድቀው ድኅነትን ይቀበላሉ::»

ለ) አምብሮዝ፥ «ከእግዚአብሔር የራቀ ሰው፥ ማለት ከአሕዛብ ወገን የሆነ፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ሳይሠራ፥ በክርስቶስ ሲያምን፥ ለአብርሃም እንደሆነው፥ ለእርሱም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠራል::»

ሐ) ዮሐንስ አፈወርቅ፥ «እግዚአብሔር ምን አደረገ? ኀጢአተኞች እንዲሆኑ ጻድቅ የሆነውን (ክርስቶስን) ኀጢአተኛ አደረገው... በሥራ ሳይሆን... በጸጋ ስንጸድቅ ኀጢአት ሁሉ ይጠፋል፤ ይህም የእግዚአብሔር ጽድቅ ሥራ ነው::» እነዚህ ጥቅሶች በJames Buchanan ከተጻፈው "Not Guilty" (1990 Grace Publications Trust ገጽ 38:39:40) ከተሰኘው መጽሐፍ የተተረጐሙ ናቸው::

(11) «አስደናቂው ልውውጥ» ም.5 ይመ.:: አበው የጽድቅ መንገድ በመልካም ሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ መሆኑን እንደሚከተለው መስክረዋል:-

ሀ) አርጌንስ፥ «ከክርስቶስ ጋር የሞተው ወንበዴ ያለ ሕግ ሥራ በእምነት ጸደቀ... ይህ የሚያሳየን፥ አስቀድሞ የሠራውን ጌታው ሳይጠይቀው፥ ካመነ በኋላም አንድ መልካም ሥራ መሥራት ሳይጠበቅበት በቃሉ መሠረት በመጽደቁ በገነት የራሱ ጓደኛ አደረገው::»

ለ) ቅዱስ አትናቴዎስ፥ «ሰው በሥራው ሳይሆን እንደ አብርሃም በእምነት ይጸድቃል::»

ሐ) ቅዱስ ሄሬኔዎስ (ጀሮም)፥ «ከእግዚአብሔር መንገድ ርቆ የሚሄድ ሰው ከክፋቱ ሲመለስ፥ ሊሠራው ባልቻለ መልካም ሥራ ሳይሆን በእምነት ብቻ እግዚአብሔር ያጸድቀዋል::» "Not Guilty" ገጽ 39:40 ይመ.

(12) ይህ ክፍል በተለይ በBerkhof አሳብ ላይ የተመሠረተ ነው:: «አስደናቂው ልውውጥ» ም. 6 ደግሞ ይመ.

(13) RR ገጽ 755 ይመ.

(14) «አስደናቂው ልውውጥ» ገጽ 63 - 65 ይመ.

(15) ሰው በእምነት ብቻ ይጸድቃል በሚለው ላይ ስለተነሣው ተቃውሞ በአቶ ዓሥራት ገብረማርያም ከተጻፈው «ትምህርተ መለኮት» ገጽ 255-274 ይመ.:: ደግሞም RR ገጽ 748-754 ይመ.

# ምዕራፍ 90 - ልጅነት

ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ብለው የሚያስተምሩ አሉ፤ ሆኖም ይህ አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የራቀ ነው። እውነት ነው፤ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ስለተፈጠሩ አዳም «የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሏል፤ ሉቃ. 3፥38። አዳም በኃጢአት በመውደቁ እርሱና ዘሩ በእግዚአብሔር ልጆች መካከል እንዳሉ አይቈጠሩም። በእነርሱ ስፍራ በእግዚአብሔር የሚድኑት የእርሱ ልጆች ሆነዋል። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ፈርዖንን፥ «እስራኤል የበኵር ልጄ ነው፤ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ እልሁህ...» አለው፤ ዘጸ. 4፥22። አዲስ ኪዳንም ስለ ዓለም ሰፋ ያለ አመለካከት አለው፤ ቢሆንም፥ ሰዎች ሁሉ ሳይሆኑ፥ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ዐውቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ ስፍራ ሞቶ እንዳዳናቸውና ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱም ሕያው ጌታቸው እንደሆነ የሚያምኑት ብቻ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ልጅነት በተለይ በአምስት ቦታዎች ላይ ጽፏል:- «አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሀት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና»፤ ሮም 8፥15። «...ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃተታለን»፤ ሮም 8፥23። «እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር... ለእነርሱ ናቸውና»፤ ሮም 9፥4። «እግዚአብሔር... ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ...»፤ ገላ. 4፥4-5። «በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን»፤ ኤፌ. 1፥5።

በእነዚህ ጥቅሶች ሐዋርያው ይህን ልጅነት በአንድ ቃል ያብራራዋል፤ ቃሉ የግሪክ ቃል ቢሆንም፥ በሮም ሕግ መሠረት አንድ የታወቀ ሥርዐት መኖሩን ሊያሳስበን ይችላል (1)። ሥርዐቱም እንደሚከተለው ነው፤ አንድ ሀብታም ሮማዊ ባላባት ልጅ ካልወለደና ወራሽ ከሌለው፥ ስሙ እንዳይጠፋ ከራሱ ባሪያዎችም ሆነ ከሌሎች ባሪያዎች አንድ የባሪያ ልጅ ለመግዛት ይወስናል። ወደ ባሪያው ልጅ አባት ሄዶ የባሪያውን ልጅ ለመግዛት፥ እንደዚሁም በልጁ ላይ ዕዳ ካለ ዕዳውን ሁሉ ለመክፈል ከልጁ አባት ጋር ይስማማል። ከተስማሙ በኋላ የልጅነት ሥርዐቱ በሕግ ይፈጸማል። ሀብታሙ ባላባት፥ ባሪያው ልጅና አባቱ በአካባቢው ሮማዊ ዳኛ ፊት ይቆማሉ። ሦስት ጊዜ የልጁ ሥጋዊ አባት ልጁን ወደ አዲሱ አባት ሲያስተላልፍ ዳኛው ይመለከታል። ከሦስተኛው የማስተላለፊያ ቃል በኋላ ዳኛው አዲሱን አባት፥ «ይህ ልጅ በልጅነት ሥርዐት ልጅህ ሆኗል» ብሎ ያውጃልና አዲሱ አባት ገንዘቡን ሁሉ ለሥጋዊው አባት ይሰጣል። ይህ ሥርዐት ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ልጁ በአዲሱ አባት ስም ይታወቃል፤ በሕጉ መሠረት ልጁና ወራሹ ነውና። አዲሱ አባት ልጁን ያሳድገዋል፤ ያሠለጥነዋልም። ሲሞትም ርስቱን ሁሉ ይወርሰዋል። ከዚህ በኋላ ልጁ የሮም መንግሥት ነጻ ኗሪ ነው፤ ምንም ዕዳ የለበትም፤ አዲስ ስም፥ አዲስ ቤተሰብና አዲስ ሕይወት አለው። በሮም ሕግ መሠረት በሚገኘው ልጅነትና በክርስቶስ ባለን ልጅነት መካከል ብዙ ተመሳሳይነት አለና ሐዋርያው የአማኙን በረከት «ልጅነት» ብሎ መግለጡ የሚያስገርም አይደለም፤ የክርስቲያን ታሪክ ከባርነት ተነሥቶ በልጅነት ሊደመደም የሚችል ታሪክ ነውና። በክርስቶስ ከማመናችን በፊት ወላጆች እንደሌላቸውና እንደ ባሪያዎች እንኖር ነበር፤ ብዙ የኃጢአት ዕዳ ነበረብን እግዚአብሔርንም እንደ አባታችን አላወቅነውም፤ የሰይጣን ልጆች ነበርንና። ጊዜው ሲደርስ ግን የእግዚአብሔር

ልጅ ሰው ሆኖ ኀጢአታችንን ተሸክመልንና በእርሱ ባመንን ጊዜ በልጅነት ከሰይጣን ሥልጣን ወጥተን የእግዚአብሔር ልጆች ሆንን።

በፊተኛው ምዕራፍ አማኙ በክርስቶስ በመጽደቁ ኀጢአት እንደተደመሰሰለት፥ ጽድቅና ቅድስናም እንደተቈጠረለት አትተናል። ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔርና በሕጉ ፊት አማኙ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመለክታሉ። ልጅነት ግን በጽድቅና በቅድስና መሠረት በአማኙ አዲስ አኗኗር ላይ ያተኵራል፤ በተለይ አማኙ የእግዚአብሔር ውድ ልጅ እንደሆነና እግዚአብሔርም አባት መሆኑን ይገልጣል። ስለዚህ ልጅነት ከሁሉ በላይ ከፍ ያለ የአማኝ በረከት፥ ክብርና መብት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን በመረዳት በሮም 3፥21-8፥11 እና በገላትያ 2፥11-3፥22 ላይ ስለ ጽድቅ መንገድ ከጻፈ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን በሮም 8፥12-39 እና በገላትያ 3፥23-4፥7 ላይ ያብራራል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጥቅሶች ምእመናን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ይናገራሉና ስለ ልጅነት የሚሰጡትን ትምህርት፦ የልጅነት ምንጭ፥ የልጅነት ሁኔታ፥ የልጅነት በረከትና የልጅነት ኀላፊነት በሚሉት አርእስት ለማጠቃለል እንሞክራለን።

## ሀ) የልጅነት ምንጭ

«በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን» (ኤፌ. 1፥5) ብሎ በመጻፉ ሐዋርያው የድኅነታችንን ምንጭና ዋና ውጤት ይገልጣል። ምንጩ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ውሳኔ ሲሆን ዋናው ውጤት ልጅነት ነው። በዚህ መልእክት ጳውሎስ ከመጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር «እኛ»ን በሰማያዊው ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን (1፥3)፥ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ የመረጠን (1፥4) እና በክርስቶስ ሥራ የወሰነን (1፥5) መሆኑን በመግለጥ ከምእመናን ሁሉ ጋር የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ላይ ያተኵራል። ሰው ልጅነትን የሚቀበለው በክርስቶስ ሲያምን ነው። ልጅነት ከእግዚአብሔር ጸጋ ይሰጣል (ኤፌ. 1፥6፤ 2፥6-8)፤ እምነታችን ራሱም እንኳ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ 2፥8-9። በዚህ መልእክት ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር «አባት» መሆኑን ሐዋርያው ያስገነዝባል፤ 1፥2-3:17፤ 2፥18፤ 3፥14-15፤ 4፥6፤ 5፥20፤ 6፥23። እንደዚሁም ሐዋርያው የተወደዱ ልጆች የአባታቸውን የእግዚአብሔርን አርአያ እንዲከተሉ በማዘዝም የልጅነትን ምንነት በአጽንዖት ይገልጣል (2)።

ልጅነታችን እውን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር፥ አንደኛ፥ የኀጢአት ይቅርታ እንድናገኝና ለመዳን ከሚያስፈልገው ዝግጅት ሁኔታ ነጻ እንድንወጣ ልጁን ለመላክ (ገላ. 4፥1-2:4-5)፥ ሁለተኛ፥ ልጆቹ መሆናችንን እንድናውቅና አባ አባት ብለን እንድንጮኽ የልጁ መንፈስ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን በልባችን ለማኖር (ገላ. 4፥6፤ ሮም 8፥16) እና ሦስተኛ፥ በመከራ ውስጥ ብናልፍ እንኳ ሳንፈራ ችግሩን ሁሉ ተቋቁመን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የልጅነታችን ፍጻሜ የሆነውን ዘለዓለማዊ ርስታችንን እንደምንቀበል መንፈስ ቅዱስ እንዲመሰክርልን ለማድረግ ዐቀደ፤ ሮም 8፥15:23፤ ገላ. 4፥7።

## ለ) የልጅነት ሁኔታ

በብሉይ ኪዳን ዘመን እነ አብርሃም የተሟላ ልጅነት አልነበራቸውም። የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ከወጣ በኋላ በልዩ ልዩ ስፍራ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ተቈጠረ፤ ዘጸ. 4፥22፤ ኢሳ. 1፥2፤ ሆሴዕ 11፥1። ጳውሎስም ስለ እስራኤል ብሔራዊ ልጅነት ይናገራል፤ ሮም 9፥4። የተሟላ ልጅነት የተገኘው

ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኀጢአት መሥዋዕታዊ ሥራ ከፈጸመ በኋላና መንፈስ ቅዱስን በምእመናን ላይ ካፈሰሰ በኋላ ነው::

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ልጅነት የአባት ሕጋዊ ሥርዐት እንጂ የሰውን ጠባይ የሚለውጥ አለመሆኑን ጠቊመናል:: እንደዚሁም ሐዋርያው ዮሐንስ እግዚአብሔር ለምእመናን፥ «የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ኀይልን ሰጣቸው አይልም) በማለቱ ልጅነት ሕጋዊ ሁኔታን የሚያመለክት መሆኑን ያሳያል፤ ዮሐ. 1፥12:: እውነት ነው፤ ምእመናን «ከእግዚአብሔር» ይወለዳሉ (ዮሐ. 1፥13)፤ ይሁን እንጂ ይህን ሥራ የተመለከትነው፥ ሰዎችን ወደ እምነት የሚያደርስ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ አድርገን ነው፤ ዮሐ. 3፥3-8:14-16:: ልጅነት እንግዲህ ከዳግመኛ መወለድ የተለየ የእግዚአብሔር ሥራ ነው:: ዳግመኛ መወለድ ከእምነት በፊት የሚፈጸም ሲሆን፥ ልጅነት እውን የሚሆነው ከእምነት በኋላ ነው:: ዳግመኛ መወለድም የሰውን ጠባይ የሚለውጥ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሥራ ሲሆን፥ ልጅነት የሰውን አቋም ይለውጣል:: በተጨማሪ ልጅነት ከጠባይ መቀደስም የተለየ ነው::

አንዳንድ ሰዎች ልጅነትን እንደ ጽድቅ ወይም ከጽድቅ ክፍሎች እንደ አንዱ ይቈጥሩታልና፥ በሚጽፏቸው መጻሕፍት ስለ ጽድቅ በሰፊው ከገለጡ በኋላ ስለ ልጅነት አያትቱም:: እውነት ነው፤ ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት የምእመናን አቋሞች ናቸው:: ሰው በክርስቶስ ሲያምን ይጸድቃል፤ በክርስቶስም ጻድቅ ነው፤ እንደዚሁም በእግዚአብሔር ፊት ቅዱስ ነው:: ሆኖም የአማኝ ጽድቅና ቅድስና የእግዚአብሔርን ባሕርይና ሕግ ያመለክታሉ:: ልጅነት የሚያመለክተው ግን የእግዚአብሔርን ማንነት ነው፤ ምክንያቱም አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: መላእክት በፍጥረት ጻድቃንና ቅዱሳን ናቸው፤ ምእመናን ግን ከክፋት ባርነት ነጻ ወጥተው በእግዚአብሔር ጸጋና በልጅነት ሥርዐት የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው:: ከዚህ ሁሉ የተነሣ ከምእመናን በረከቶች ሁሉ ልጅነት ዋናው እንደሆነ ይታያልና በትምህርተ መለኮት ከፍ ያለ ስፍራ ሊኖረው ይገባል::

## ሐ) የልጅነት በረከት

እግዚአብሔር የልጆቹ አባት ነው፤ እነርሱም ከቅዱሳን ጋር የእርሱ ቤተሰብ ናቸው፤ ኤፌ. 2፥19:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕዝቡ እግዚአብሔርን «ጌታ» («ያህዌ») ብለው ጠሩት፤ በአዲስ ኪዳን ግን «አባ አባት» ብለው ይጠሩታል:: አንዳንድ ሰዎች ምድራውያን አባቶቻቸውን ፈጽሞ አያውቁም፤ የተወሰኑት ደግሞ አባቶቻቸውን የሚያውቁ ቢሆኑም እንኳ፥ ስለሚጨክኑባቸውና የክፋት ሥራ ስለሚፈጽሙባቸው እውነተኛ አባትነት ምን እንደሆነ አያስተውሉም:: እግዚአብሔር አብ ግን በተለይ ከወልድ ጋር ባለው ግንኙነት እውነተኛ አባትነትን ገልጧል (3):: ስለዚህ ልጅነትን የተቀበሉ ሁሉ ከሐዋርያው ጋር፥ «በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት» ይንበረከካሉ፤ ኤፌ. 3፥14-15::

ሰው አምኖ ልጅነቱን ሲያገኝ፥ ወዲያውኑ ስለ ልጅነቱ አራት ነገሮችን ማወቅ ይገባዋል፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:-

### 1. የአብ አባትነት

የአባትነት ሁኔታ በተለይ በክርስቶስ ምስክርነት የሚገለጥ ሲሆን እርሱም በአራት ነገሮች ሊደመደም ይችላል (4):-

ሀ) ሥልጣን፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና»፤ «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ»፤ «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው» በማለቱ፥ በሚያደርገው ሁሉ ወደ አብ እየተመለከተ የአብን ፈቃድ ለመፈጸም ለአብ ወዶ መታዘዙን በማሳየት ምኞቱን ገለጠ፤ ዮሐ. 6፥38፤ 17፥4፤ 4፥34።

ለ) ፍቅር፤ ክርስቶስ፥ «አብ ወልድን ይወዳል፤... አብ... ወደደኝ» ብሎ በአብ ፍቅር ሁልጊዜ የተከበበ መሆኑን አሳየ፤ ዮሐ. 5፥20፤ 15፥9።

ሐ) ኅብረት፤ ክርስቶስ፥ «የላከኝ ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም»፤ «... ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን አይደለሁም» ብሎ በሚሆነው ሁሉ አብ ከእርሱ ጋር በመሆኑ ላይ አተኰረ፤ ዮሐ. 8፥29፤ 16፥32።

መ) ክብር፤ አብ ልጁን ከፍ ከፍ ማድረግ ይወዳል፤ ክርስቶስ፥ «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው» ብሏልና፤ ዮሐ. 5፥22-23።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ከአብ ሥልጣን፥ ፍቅር፥ ኅብረትና ክብር እንደተቀበለ ሁሉ ልጅነትን ያገኙ እንደየሁኔታቸው በመጠኑ እነዚህን በረከቶች ይቀበላሉ።

## 2. የክርስቶስ ወንድምነት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሕማማቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ፥ «ከእንግዲህ ወዲህ ባሪያዎች አልላችሁም... ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁ» ብሎ ተናገረ፤ ዮሐ. 15፥15። ከትንሣኤው በኋላ ግን መግደላዊት ማርያምን፥ «... ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ:- እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው» አላት፤ ዮሐ. 20፥17። እዚህ ላይ ደቀ መዛሙርቱን ወንድሞቼ ብሎ ሲጠራቸው፥ በራሱ የባሕርይ ልጅነትና እነርሱ ባላቸው ልጅነት መካከል ልዩነት መኖሩን በጥንቃቄ አሳይቷል። በኋላም ለሌሎች ሴቶች፥ «አትፍሩ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፤ በዚያም ያዩኛል» አላቸው፤ ማቴ. 28፥10። እንግዲህ ክርስቶስ የምእመናን ወንድም ነው፤ ሆኖም የእርሱን ወንድምነት ለመረዳት ከፍ ያለ ማስተዋልን ይጠይቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ተረድቶ፥ «የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ ዐብረንም ደግሞ እንድንከበር ዐብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር ዐብረን ወራሾች ነን»፤ «ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና» ብሎ ጽፏል፤ ሮም 8፥17:29። ጌታችን ወንድማችን ሲሆን፥ የብኵርናን መብት ሁሉ እንድንጠብቅና የእርሱን መልክ እንድንመስል ያስፈልጋል፤ እርሱ ያደረገልንን ስንገነዘብ ይህን በሙሉ ልብ ለመፈጸም እንፈልጋለን። የዕብራውያን ጸሐፊ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህ ዓለም ሲገባ፥ «ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ» ማለቱን ያሳስበናል፤ ዕብ. 2፥13።

## 3. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት

ሰው ሲያምን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላልና ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች አንዱ አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ

በተለይ ይህን ተግባር የሚፈጽመው «የልጅነት መንፈስ» በመሆን «ከመንፈሳችን ጋር» የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን በመመስከር ነው፤ ሮም 8፥15-16:: አማኙ እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በሦስት መንገዶች ሊያውቅ ይችላል፤ አንደኛ፥ የወንጌልን ትምህርት ሲቀበልና ለዚህ ንስሐ በመግባትና በማመን ትክክለኛ አጸፋ ሲሰጥ የወንጌልን ትእዛዝ እንደፈጸመ በመረዳቱ፥ ሁለተኛ፥ በራሱ መንፈስ ሕይወቱን ሲመረምር፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ የለውጥ ምልክቶችን በማየቱ፥ ሦስተኛ፥ ከራሱ መንፈስ ጋር የመንፈስ ቅዱስን ምሥጢራዊ ምስክርነት በመቀበሉ:: ይህ ዕውቀት አለኝታ እንደሆነ ይታወቃልና የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የአለኝታ ዐቢይ ደረጃ ነው (5)::

### 4. የርስት ዋስትናነት

ልጅነትን የሚቀበለው በዚህ ዓለም የሚገኝ የመንግሥተ ሰማያት ወራሽ ነው፤ ሆኖም ገና ወደ ርስቱ አልገባም፤ ሮም 8፥23:: ይህ ርስት አይጠፋበትም፤ ምክንያቱም ርስቱ «ዕድፈት የሌለበት» እና «የማያልፍ» ነው፤ እግዚአብሔርም ይጠብቅለታል:: ይህም የአማኙ ርስት ዋስትና ነው፤ 1ጴጥ. 1፥3-5:: እውነት ነው፤ አማኙ እስከ መጨረሻ መታገሥ አለበት፤ አማኙ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ የክርስቶስ ወንድምም ስለሆነ ደካማ ቢሆንም እንኳ፥ እግዚአብሔር ልጆቹን አይተዋቸውምና ከእርሱ ወይም ከክርስቶስ እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም፤ ዮሐ. 10፥28-29::

ልጅነት ያለው ወደ ሰማያዊ ርስት ሲገባ፥ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብና ክብር አይታ «እኩሌታውን አልነገሩኝም» በማለት የተሰማት ሳይሰማው አይቀርም፤ 2ዜ.መ. 9፥6:: ሐዋርያው ጳውሎስም፥ «ዐይን ያላየችው፥ ጆሮም ያልሰማው፥ በሰውም ልብ ያልታሰበው፥ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው...»፥ «ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና... ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ሁሉ የእናንተ ነውና፤ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው» ብሎ ጽፏል፤ 1ቆሮ. 2፥9፤ 3፥21-23::

ልጅነትን የተቀበለ ሰው ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ የአብን አባትነት፥ የወልድን ወንድምነት፥ የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነትና የርስት ዋስትናነት በመጠኑ ሊያውቅ ይችላል፤ ከዚያም በኋላ ታላቅ ወንድሙን በመከተል ሲኖር፥ እነዚህን በረከቶች በይበልጥ እየተገነዘበ ይሄዳል:: ከእነዚህ በረከቶች ሁሉ ጋርም አማኙ ክርስቶስን የመከተል ሕይወትን በመምራት ሲቀጥል፥ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን በረከቶች እየተቀበለ ይኖራል::

### 5. የአብ ርኅራኄ

እግዚአብሔር አባታችን እኛን ያውቀናል፤ ዳዊት፥ «አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል፤ ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና» በማለት ስርኅራኄው አጽንዖት ይሰጠዋል፤ መዝ. 103፥13-14:: እንደዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው...» ብሎ ጽፏል፤ 1ቆሮ. 10፥13::

### 6. የአብ ልግስና

እግዚአብሔር አባታቸው ለልጆቹ ምን እንደሚያስፈልጋቸው፥ በተለይም ምግብና ልብስ እንዲሰጣቸው ከመለመናቸው በፊት ያውቃልና ስለ እንደነዚህ

ዐይነት ነገሮች መጨነቅ አይገባቸውም፤ ማቴ. 6፥31-32:: ከዚህም ጋር እግዚአብሔር ልጆቹ ሲለምኑት፥ መልካም ነገርን ይሰጣቸዋል (ማቴ. 7፥11)፥ በተለይም መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል፤ ሉቃ. 11፥13:: ክርስቶስም፥ «እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» ብሎ ለበጎቹ ተስፋ ሰጣቸው፤ ዮሐ. 10፥10:: እዚህ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዘለዓለም ሕይወት ይናገራልና ወንድሞቹ በዓለም አስተያየት ድኾች፥ ችግረኞችና ስደተኞች ቢሆኑም፥ «ሕይወት እንዲበዛላቸውም» በማለቱ፥ ዓለም ማሰብ የማይችለው ልዩ ደስታ እንደሚኖራቸው ገለጠ፤ 1ጴጥ. 1፥6-9፤ ያዕ. 1፥2-3:: እግዚአብሔር ልጆቹን ይወዳልና እነርሱን በመባረክ እጅግ ደስ ይለዋል:: የእግዚአብሔር ልጆች ደስታ ከምድራዊ ብልጽግና የሚመነጭ አይደለም፤ ክርስቶስ፥ «አንተ ታናሽ መንጋ፥ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ:: ያላችሁን ሽጡ፤ ምጽዋትም ስጡ... በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ከረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ...» ብሎ አዝዟልና፤ ሉቃ. 12፥32-33::

7. የአብ ተግሣጽ

ልጅነትን የተቀበሉ አብን ቢወዱና በመንገዱ መራመድ ቢፈልጉም፥ ገና ፍጹማን አይደሉም፤ በቀላሉ ከአባታቸው መንገድ አፈንግጠው ሊወጡ ይችላሉና የውድ አባታቸው ቊጥጥርና ተግሣጽ ያስፈልጋቸዋል:: ምእመናን በሰማያዊ አባታቸው ልግስና ሲገረሙ፥ ስለሚወዳቸው እንደሚገሥጻቸው ሊረሱ፥ ሲቀጣቸው ደግሞ ሊደነግጡ ይችላሉ:: ሆኖም ተግሣጽ የሚወድዳቸው አባት ተግባር ነው:: የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ እንደሚከተለው ያሳስበናል:- «ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቃልል፤ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፤ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል»፤ ዕብ. 12፥5-6:: ቀጥሎም ጸሓፊው የአብን ተግሣጽ ሲያብራራው፥ ተግሣጽ ራሱ እውነተኛ ልጆች ከሚታወቁባቸው ምልክቶች አንዱ እንደሆነ (ቊ. 7-8)፥ ልጆች ከቅጣቱ የተነሣ ምድራውያን አባቶቻቸውን እንደሚያከብሩ ሁሉ፥ ሰማያዊ አባታቸውንም አብልጠው ማክበር እንደሚገባቸው (ቊ. 9)፥ ምድራውያን አባቶች በልዩ ልዩ ምክንያት ልጆቻቸውን ቢቀጧቸውም፥ እግዚአብሔር አብ ልጆቹን የሚቀጣው ግን ከቅድስናው እንዲካፈሉ ለጥቅማቸው (ቊ. 10) እና ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን ቢሆንም፥ በኋላ «ለሰመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን» የሚያፈራላቸው እንደሆነ ያስተምራቸዋል (ቊ. 11)::

## መ) የልጅነት ኀላፊነት

የልጅነት መብትና በረከት ጉዳይ ታላቅ ቢሆንም፥ የልጅነትን ኀላፊነት በሦስት አርእስት በዐጭሩ ለማጠቃለል እንሞክራለን:-

1. በፍቅር መመላለስ

በእግዚአብሔር የተሰጠችዋ ፊተኛዪቱ ትእዛዝ፥ «አንተም በፍጹም ልብህ፥ በፍጹምም ነፍስህ፥ በፍጹምም አሳብህ፥ በፍጹምም ኀይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት»፤ «ሁለተኛዪቱም ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል ናት»፤ ማር. 12፥29-31:: የእነዚህን ሁለት ትእዛዛት ቅደም ተከተል ሳንረሳ፥ መፈጸማቸውም ሆነ አለመፈጸማቸው በተለይ የሚታየው በሁለተኛዪቱ ነው፤ ምክንያቱም፥ «ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?» በሚለው መልስ ዐዘል ጥያቄ ተገልጧል፤ 1ዮሐ. 4፥20::

እንግዲህ ፍቅራችንን ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው እንዴት እናሳያለን? እንዴትስ እናጠነክረዋለን? በፍቅር መናገራችን ፍቅራችንን ከምንገልጥባቸውና ከምናሳድግባቸው መንገዶች አንዱ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረን ጸሎት፥ «አባታችን ሆይ፥ በሰማያት የምትኖር» ብለን ማንነቱን፥ ክብሩንና ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት ከገለጥን በኋላ «ስምህ ይቀደስ» በማለታችን የእርሱ ህላዌና ባሕርይ በሁሉ ዘንድ ታውቆ እንዲከበር መመኘታችንን እናሳያለን፤ ይህንም በተለይ በአምልኮአችን እንገልጠዋለን:: ከዚያም ቀጥሎ፥ «መንግሥትህ ትምጣ» የሚለው ሐረግ፥ ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲስፋፋና በታላቁ ተልእኮ ያለንን ድርሻ እንድንፈጽም፥ እንደዚሁም ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ በዓለም ሁሉ ላይ እንዲነግሥ መጠባበቃችንን እናሳውቃለን፤ ማቴ. 6፥9-10::

**2. በብርሃን መመላለስ**

«እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» ተብሎ ተገልጧልና በብርሃን መመላለስ የእግዚአብሔር ልጆች ተግባር ነው፤ 1ዮሐ. 1፥5-7:: ልጅነት ያለው የእግዚአብሔርን ብርሃንነት እያሳየ የዓለምን ፍሬ የለሽ ጨለማ ሥራ መግለጥ አለበት፤ ይህንም የሚያደርገው ብርሃኑን እየተመለከተ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እያጠናና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያወቀ፥ መልካም ሥራን ሁሉ እየሠራና ወንጌልን እየተናገረ ጨውና ብርሃን በመሆን ነው፤ ማቴ. 5፥13-16፤ 6፥10፤ ኤፌ. 5፥8-11:: ልጅነት ያለው በየዕለቱ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ሲለምን አባቱ እንደሚሰጠው በማሳወቅ አባቱን ያከብራል፤ እንደዚሁም አባቱ ከክፉ ነገር እንዲያድነው የሚጠይቅ በመሆኑ ሕይወቱ ሁሉ በአብ ጸጋ ላይ የተደገፈ መሆኑን ገልጦ ያከብረዋል፤ ኤፌ. 6፥11:13::

**3. በኅብረት መመላለስ**

የልጅነት ኅብረት በመጀመሪያ «ከአባት ጋር፥ ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሲሆን»፥ ቀጥሎ ልጅነት ካለው ሁሉ ጋር ነው፤ 1ዮሐ. 1፥1-4:: ይህ ኅብረት በይቅርታ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ክርስቶስም፥ «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን» በማለት አስተምሯል፤ ማቴ. 6፥12:: ልጅነት ባላቸው መካከል ልዩነት የለም፤ ሁሉም በጸጋ የኀጢአታቸውን ይቅርታ ተቀብለዋልና፤ ስለዚህ ለመኩራት ወይም ከፍ ያለ ስፍራን ወይም ክብርን ለመፈለግ ምክንያት የለም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ:: እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» በማለት ክርስቲያናዊ ኅብረት በፍቅር ላይ የተመሠረተ መሆኑን በአጽንዖት ተናገረ፤ ዮሐ. 13፥34-35:: ሐዋርያው ጳውሎስም የዚህን ፍቅር ምክንያት እንደሚከተለው አብራርቶታል:- «እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፤ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዐዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ»፤ ኤፌ. 5፥1-2::

ይህን ምዕራፍ ለመደምደም መንፈሳውያን አባቶች በነገረ መለኮት አገላለጥ በጽሑፍ ያሰፈሩትን ከዌስትምንስተር የሃይማኖት መግለጫ ምዕራፍ 12 እንጠቅሳለን:-

«በጸጋው ያጸደቃቸውን ሁሉ በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የልጅነትን ጸጋ እንዲቀበሉ ሰጥቷቸዋል። በዚህም የእግዚአብሔር ልጆች ሆኖ መቈጠርና የእግዚአብሔር ልጅነትን መብት ተካፋይ ይሆናሉ። ስሙን ይቀበላሉ፤ የልጅነትን መንፈስ ይቀበላሉ፤ በድፍረት ወደ ጸጋው ዙፋን ለመግባት ይፈቀድላቸዋል፤ እግዚአብሔርን አባ አባት ብለው የመጥራት መብት ይሰጣቸዋል፤ እግዚአብሔር ይራራላቸዋል፤ ይንከባከባቸዋል፤ የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣቸዋል፤ እንደ ልጅ በእርሱ ይቀጣሉ እንጂ ፈጽመው አይጣሉም፤ ለመዳንም ቀን ታትመዋል፤ የተስፋዎቹ ወራሾች ናቸው፤ የዘለዓለምንም የደኅንነት ተስፋ ይወርሳሉ» (6)።

# ማስታወሻ

(1) በዚህ ሥርዐት ዐውድ ልጅነት በእንግሊዝኛ Adoption ይባላል (ግሱም Adopt ነው)። Mark Stibbe, From Orphans To Heirs በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ ይህን ሥርዐት በገጽ 29-31 በሰፊው አብራርቶታል፤ መጽሐፉ በጠቅላላ ስለ ልጅነት የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በጥሩ አኳኋን ይገልጣል። ይህ መጽሐፍ በ1999 በThe Bible Reading Fellowship የታተመ ነው።

(2) RR ገጽ 760 ይመ.

(3) የአብን አካላዊ ባሕርይ በም.26ሐ1 ለማሳየት ሞክረናል።

(4) Knowing God በJ.I. Packer ተጽፎ በ1973 በHodder & Stoughton ከታተመው ም.19 ገጽ 228-229 ይመ.

(5) በአማኙ ዘንድ ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና አሰኻታ በሚከተሉት ምዕራፎች እናጠናለን።

(6) እምነታችን ገጽ 30-31 ይመ.

# ምዕራፍ 91 - የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ

ሐዋርያው ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ስብከቱ፥ «ንስሐ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» የሚለውን ትእዛዛዊ የተስፋ ቃል ለእስራኤል ሕዝብ ሰጣቸው፤ ሐ.ሥ. 2፥38:: ብዙ ሊቃውንት ስለ ነገረ መለኮት ሲጽፉ፥ በድኅነት ትምህርት የአጻጻፍ ቅደም ተከተላቸው ላይ ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተለየ ትኩረት አይሰጡም:: ሊቃውንቱ ስለ አዲስ ልደት በሰፊው ይጽፋሉና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ዳግመኛ ከመወለድና ከአዲስ ልደት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለየት ያለ ስፍራ ሲሰጠው አይታይም (1)፤ ሌሎችም ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲጽፉ፥ የሚያተኩሩት በመንፈስ ቅዱስ ሥርጸት ላይ ነው:: ግሩደም ግን ስለ ቅድስና ከጻፈ በኋላ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በሰፊውና በጥሩ አኳኋን አትቷል (2):: በእኛ በኩል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከልጅነት ጋር የተያያዘ እንደ መሆኑ ከጽድቅና ከልጅነት ቀጥሎ ሐተታ ልንሰጥበት ፈልገናል::

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በበዓለ ኀምሳ ቀን ተሰጠ፤ ከዚህ በፊት አይሰጥም ነበር፤ ምክንያቱም፥ «ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና»፤ ዮሐ. 7፥39:: ሐዋርያትና ሌሎች ደቀ መዛሙርት ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት እግዚአብሔር በሕይወታቸው ይሠራ እንደነበር ዐውቀዋል፤ በአዲስ ኪዳን አገላለጥ መሠረትም «ዳግመኛ ተወለዱ» ማለት እንችላለን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም» ብሎ ተናገረ፤ ዮሐ. 6፥44:: ሐዋርያት ምንም እንኳ ብዙ ነገርን የማስተዋልና የእምነት ድክመት ቢታይባቸውም፥ ወደ ክርስቶስ መጥተው ተከተሉት:: ጴጥሮስ፥ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» በማለቱ ኢየሱስ፥ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ» ብሎ በጴጥሮስ ሕይወት እግዚአብሔር የሚሠራውን አረጋገጠ፤ ማቴ. 16፥16-17:: ክርስቶስም ለሐዋርያት፥ «እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል ንጹሓን ናችሁ» ብሎ ተናገረ (ዮሐ. 15፥3)፤ ሲጸልይም፥ «የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና እነርሱም ተቀበሉት» ብሎ ማመናቸውን መሰከረ፤ ዮሐ. 17፥8:: ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት ሐዋርያት በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት ኖሩ፤ ቢሆንም እግዚአብሔር ልባቸውን ለውጦላቸው ነበርና በክርስቶስ አመኑ:: ሐዋርያት በበዓለ ኀምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለው ወደ አዲስ ኪዳን ኑሮና ተመክሮ ተሻገሩ:: ደግሞም በዳግመኛ መወለድና በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መካከል ልዩነት እንዳለ ማሳየት እንችላለን:: በዳግመኛ መወለድ መንፈስ ቅዱስ የልብ ዝንባሌ ወደ እግዚአብሔር እንዲሆን ያደርጋል፤ በአዲስ ኪዳን ስጦታ ግን መንፈስ ቅዱስ ራሱ የአማኙን ሕይወትና ልብ መኖሪያ ያደርገዋል::

እኛም ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ ተወልደን የምንኖር ነንና እንደ ሐዋርያት በሽግግር ዘመን ውስጥ አናልፍም:: ስለዚህ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን በበዓለ ኀምሳ ቀን ብርሃን መመርመር ይገባናል:: የበዓለ ኀምሳ ቀን የአማኙ የግል ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ጠቅላላውን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት ይመለከታልና:: ሆኖም የድኅነትን ቅደም ተከተል በማጥናት ላይ በመሆናችን በዓለ ኀምሳን ከአማኙ የግል አመለካከት አንጻር አሁን እንመረምረዋለን:: እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ የተካተተውን ትምህርት የበዓለ ኀምሳ ቀንና አማኙ፥

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአማኙ ሕይወት፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክና መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ኑሮ በተባሉ አርእስት ለማጠቃለል እንሞክራለን።

## ሀ) የበዓለ ኀምሳ ቀንና አማኙ

ክርስቲያን ስለ ኀጢአት ይቅርታ ሲያስብ፥ ወዲያውኑ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንደሚያስብ ሁሉ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማሰላሰል ሲጀምርም፥ በበዓለ ኀምሳ ቀን የመንፈስ ቅዱስን መውረድ መገንዘብ ይገባዋል። የሐዋርያት ሥራ ስለዚያ ልዩ ቀን ሲተርክ በተለይ በሦስት ቃላት ይጠቀማል፤ ሦስቱ ቃላት በዚያ ቀን የሆነውን ያብራራሉ።

### 1. የተስፋ ቃል

ሐዋርያው ጴጥሮስ በስብከቱ፥ «በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው» ብሎ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ አብራራው፤ ሐ.ሥ. 2፥33። ሐዋርያው ስብከቱን የመሠረተው በነቢዩ በኢዩኤል የትንቢት ቃል ላይ ነው (ኢዩ. 2፥28-32፤ ሐ.ሥ. 2፥16-21)። ነቢዩ ሕዝቅኤልም «አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ» የሚለው፥ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ሁሉ እንደሚኖር አስቀድሞ መናገሩን ያሳያል። ከዚህ ሐረግ በፊትም አዲስ ልብን፥ አዲስ መንፈስንና የድንጋዩን ልብ አውጥቶ የሥጋን ልብ በመስጠቱ፥ የዳግመኛ መወለድን ሥራ አስቀድሞ ገለጠ፤ እዚህም ላይ በዳግመኛ መወለድና በሰው ልብ ውስጥ በእግዚአብሔር መኖር መካከል ያለው ልዩነት ይታያል፤ ይኸውም ዳግመኛ መወለድ የመንፈስ ቅዱስን መኖሪያ ማዘጋጀቱ ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ይኖራል፤ ሕዝ. 36፥26-27።

የመጥምቁ ዮሐንስ ዋና መልእክት ስለሚመጣው ክርስቶስ፥ «እኔ በውሃ አጠመቅኋችሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» የሚል ነበር፤ ማር. 1፥8። ክርስቶስ ራሱም፥ «... በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?»፤ «እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም... የእውነት መንፈስ ነው፤... በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ»፤ «ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ»፤ ሉቃ. 11፥13፤ ዮሐ. 14፥16-17፤ ሐ.ሥ. 1፥5። ደግሞም ሉቃ. 24፥49፤ ዮሐ. 15፥26-27፤ 16፥13-15 ይመልከቱ። እንግዲህ በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው አስቀድሞ በነበረው የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ መሠረት ነው።

### 2. ስጦታ

ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ» የሚለውን የተስፋ ቃል በስብከቱ መጨረሻ ላይ ገለጠ። ስጦታው የሚሰጠው ከሙታን በተነሣውና ወደ ሰማያት ዐርጎ በአብ ቀኝ ከፍ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ሐ.ሥ. 2፥33። ንስሐ የሚገቡና በክርስቶስ አምነው የሚጠመቁ የኀጢአትን ይቅርታ እንደሚያገኙ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ይቀበላሉ፤ ሐ.ሥ. 2፥38። መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበለ አማኝ የለም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» ብሏል፤ ሮም 8፥9። ይህም ስጦታ የሚገኘው ከሰው ደግነት፥ ሥራ ወይም

ኀይል የተነሣ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነውና ሐዋርያው ይህን ለማሳየት የሚከተሉትን መልስ ዐዘል ጥያቄዎች ይጠይቃል፤ «በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን?... በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጸማላችሁን?... እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም ዘንድ ተኣምራት የሚያደርግ፥ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ ከእምነት ጋር በሆነ መስማት ነው?»፤ ገላ. 3፥2-5::

3. ጥምቀት

ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልዩ ልዩ አሳብና ትምህርት አለ፤ ስለዚህ እኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥምቀት የሚሰጠውን ትምህርት በጥንቃቄ ማጥናት ይገባናል:: በሐዋርያት ዘመን ብዙ ጥምቀቶች ነበሩ (ዕብ. 6፥1-2)፤ አዲስ ኪዳን በተለይ ለኀጢአት ስርየት ሲባል ስለ ንስሓ ጥምቀት ማለት ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት (ማር. 1፥4)፥ ስለ ክርስቶስ የመከራ ጥምቀት (ማቴ. 20፥22-23፤ ማር. 10፥38-39፤ ሉቃ. 12፥50)፥ ስለ ምእመናን የውሃ ጥምቀት (ማቴ. 28፥19-20)፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት (ሐ.ሥ. 1፥5) እና የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ከግብጽ ወጥተው ሲሄዱ፥ «ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር» ስለ መጠመቃቸው ይናገራል፤ 1ቆሮ. 10፥2:: ከእነዚህ ጥምቀቶች አራት ነገሮችን ማየት እንችላለን፤ እነርሱም፥ ሀ) አጥማቂ (እግዚአብሔር፥ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ክርስቶስ) መኖሩን፥ ለ) የሚጠመቅ (ቤተ እስራኤል፥ ንስሓ የሚገቡ፥ ክርስቶስ ራሱ፥ ምእመናን) መኖሩን፥ ሐ) የሚጠመቅበት ነገር (ደመናና ባሕር፥ ውሃ፥ መከራ፥ መንፈስ ቅዱስ) ያለ መሆኑን፥ መ) የሚጠመቅ ከአንድ ሁኔታ ወጥቶ ከፍ ወዳለና አዲስ ወደ ሆነ ሁኔታ (ከባርነት በሙሴ ወደሚመራ ወደ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሕዝብ፥ የኀጢአት ይቅርታ ወዳለበት መሲሑን ወደሚጠብቅ ማኅበር፥ ከማናቸውም ሁኔታ፥ ኀይል ወዳለበት ወደ አዲስ ኪዳን ሕዝብ፥ ከዓለም ወደ ቤተ ክርስቲያን) የሚገባ መሆኑን::

አራቱ ወንጌሎች መጥምቁ ዮሐንስን እንደሚከተለው ይገልጡታል:-

«እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ... ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል»፤ ማቴ. 3፥11::

«እኔ በውሃ አጠመቅኋችሁ፤ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል»፤ ማር. 1፥8::

«እኔስ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን... ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል»፤ ሉቃ. 3፥16::

«የላከኝ እርሱ:- መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ»፤ ዮሐ. 1፥33::

በእነዚህ አራት ጥቅሶች ላይ ክርስቶስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቃቸው በግልጥ ቢታይም፥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ምን እንደሆነ አልተገለጠም:: የሚከተሉት ሁለት ጥቅሶች ቀጥታ በበዓለ ኀምሳ ቀን የተፈጸመውን ያመለክታሉ:-

«ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና፤ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ»፤ ሐ.ሥ. 1፥5::

«ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ»፤ ሐ.ሥ. 11፥16:: እዚህ ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት የሆነውና በበዓለ ኀምሳ ቀን የተፈጸመው አንድ ዐይነት የክርስቶስ ሥራ መሆኑን አሳየ::

ከበዓለ ኀምሳ ቀን ሃያ አምስት ዓመታት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚከተለው ለቆሮንቶስም ምእመናን ጻፈ፤ «እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና:: ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል»፤ 1ቆሮ. 12፥13:: ይህ ጥቅስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአዲስ ኪዳን ሰባተኛውና የመጨረሻው ነው:: እዚህ ላይ አጥማቂው ባይገለጥም፥ በሌሎች ጥቅሶች ላይ ክርስቶስ መሆኑ ስለተገለጠ፥ እዚህም ደግሞ ክርስቶስ ነው ብለው አንባቢዎች ሳያስቡ እንደማይቀሩ ግልጥ ነው:: የሚጠመቁት ከሐዋርያው ጀምሮ ምእመናን ሁሉ ናቸው:: ምእመናን የሚጠመቁት በመንፈስ ቅዱስ ነውና የዚህ ውጤት አንድ አካል መሆን ነው:: ስለ ጥምቀት የጳውሎስ አጻጻፍ በዚሁ መልእክት በአንድ ተመሳሳይ ጥቅስ ይታያል:- «ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ»፤ 1ቆሮ. 10፥2:: እንደገና በዚህ ጥቅስ የአጥማቂው ማንነት ባይገለጥም፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ይጠመቃሉ፤ በመንፈስ ሳይሆን በውሃና በባሕር ተጠመቁና በውጤቱ አንድ ሕዝብ ሆነው ከመሪያቸው ከሙሴ ጋር ተባበሩ:: ይህ ብቻ ሳይሆን ተጠምቀው በኖሩበት ሁኔታ «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ» ሲል፥ ሐዋርያው ከቆሮንቶስ ምእመናን ጋር «ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል» ይላል::

ከ1ቆሮንቶስ 12፥13 በመነሣት ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ማስተማር እንችላለን:-

ሀ) ምእመናን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ:: በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁና በመንፈስ ቅዱስ ያልተጠመቁ መኖራቸውን የሚያመለክት አሳብ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ባለመጠመቃቸው ደካሞች ናቸው የሚል በአዲስ ኪዳን አይገኝም::

ለ) በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ሁሉ አንድ አካል ናቸው:: ሐዋርያው በዚህ መልእክት በክርስቶስ ባላቸው አንድነት ላይ አስቀድሞ ትኵረት አድርጓል፤ 1ቆሮ. 10፥17፤ 12፥12:: አንድ ክርስቲያን «ከሌሎች ምእመናን ጋር በአንድነት መተባበር አያስፈልገኝም» ቢል ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአንድ የተለየ ወገን ጋር ቢተባበር፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጣ መሆኑ ግልጥ ነው፤ ሰዎች በአንዱ መንፈስ ማለት በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ፤ አንዱን መንፈስም ይጠጣሉ::

ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሰው ሲያምን የሚፈጸም ክሥተት ብቻ ሳይሆን፥ ምእመናን አንድ አካል እንዲሆኑና መንፈስ ቅዱስን በሕይወታቸው ሁሉ እንዲያውቁ የሚያደርግ ነው፤ ያሙኑት «የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ» ናቸውና፤ 1ቆሮ. 6፥19-20:: እንግዲህ ሐዋርያው፥ «ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል» ብሏል::

አንዳንድ ሰዎች በዚህ አተረጓጐም እንደማይስማሙ እናውቃለን፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቁት ካመኑ በኋላ ረጅም ጊዜ ቈይተው ነው፤ ሌሎች ደግሞ ቢያምኑም በመንፈስ ቅዱስ አይጠመቁም ይላሉ:: ከዚህም የተነሣ እነርሱ አስቀድሞ በተጠቀሱት ስድስት ጥቅሶችና በ1ቆሮንቶስ 12፥13 መካከል ልዩነት መኖሩን በልዩ ልዩ መንገድ ይገልጣሉ:: ሆኖም ከዚህ

በላይ የሰጠነው አተረጓጐም ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚስማማ እንደሆነ አሳይተናልና የሰውን ተመክሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መመዘን አለብን:: በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስን በሰው ተመክሮ መሠረት ማስተዋል አደገኛ ነው:: በተጨማሪም በሰባቱ ጥቅሶች ላይ የሚገኙ የግሪክ ቃላትና አጠቃቀማቸው አንድ ነውና የ1ቆሮንቶስ መልእትን ትምህርት ከሌሎች ስድስት ጥቅሶች ለመለየት የሚያስችል በቂ ምክንያት ያለ አይመስልም (3):: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የሚከተለውን የትምህርት ዐይነት ወደ መመልከት እንመለሳለን::

## ለ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአማኙ ሕይወት

በበዓለ ኀምሳ ቀን ሦስት ልዩ ክሥተቶች ታይተዋል፤ እነርሱም፥ ሀ) «ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት ሁሉ ሞላው»፤ ለ) «እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው»፤ ሐ) «በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር» የሚሉ ናቸው፤ ሐ.ሥ. 2፥2-4:: በሐዋርያት ሥራ ታሪክ መሠረት ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ብዙዎች በልሳን ተናገሩ እንጂ ሌሎቹ ሁለት ክሥተቶች አልተሰጡም:: እንግዲህ ከዚህ ቀን በኋላ ሰዎች ሲያምኑ በእነርሱ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይወርድ እንደነበር ማጥናት ይገባናል::

ወንጌላዊው ሉቃስ የተለያዩ ሰዎችን ታሪክ ሲተርክ፥ መንፈስ ቅዱስን ስለ መቀበላቸው ብዙ አይናገርም፤ በሐዋርያው ጳውሎስ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ታሪክ ውስጥ ግን አንዳንድ ፍንጮች አሉ:: ሐናንያ ወደ እርሱ ሲሄድ፥ «ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ ጌታ፥ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፤ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ»፤ «... አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ፤ ከኀጢአትህም ታጠብ» አለው፤ ሐ.ሥ. 9፥17፤ 22፥16:: ከዚህ የተነሣ፥ ሰው መንፈስ ቅዱስን ከመቀበሉ በፊት ከኀጢአቱ መንጻት አለበትና አምኖ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ወዲያውኑ ምን ዐይነት ውጤት እንደሚያስከትል አይገልጥም::

ብዙ ሰዎች በአንድነት በወንጌል ሲያምኑ፥ ሉቃስ በይበልጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይናገራልና በሦስት ቦታዎች በተፈጸሙ ክሥተቶች ላይ ማተት ይገባናል::

*1) በሰማርያ (ሐ.ሥ. 8፥4-25)*

ወንጌላዊው ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሰማርያ ሲሰብክ ብዙ ሰዎች አምነው ተጠመቁ:: «በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው:: እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና:: በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ»፤ ቍ. 14-18:: መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ፥ ጠንቋዩ ሲሞን መንፈስ ቅዱስን ለሌሎች ሰዎች እንዲሰጥ ለሐዋርያት ገንዘብ አመጣላቸው (ቍ. 19):: ሲሞን «ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ» ባይኖረውም ክሥተቶችን አየ፤ በልሳን መናገራቸው ወይም ትንቢት መናገራቸው

ወይም ሌላ ክሥተት መሆኑ አልተገለጠም፤ ሆኖም መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ ዐወቀ::

ከፊልጶስ አገልግሎት የተነሣ ሳምራውያን ለምን በመንፈስ ቅዱስ አልተጠመቁም? የሚለው እዚህ ላይ የሚነሣ ጥያቄ ነው:: ሉቃስ ለዚህ ጥያቄ መልስ አይሰጥም፤ የእርሱ ዓላማ በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ወንጌል ወደ ሰማርያ እንዴት እንደደረሰ ማሳየት ነበረና፤ ሐ.ሥ. 1፥8:: ሆኖም ብዙ ሊቃውንት የሚስማሙት፥ የአይሁድ ቤተ ክርስቲያንና የሰማርያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባሎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር የሐዋርያት መሪ የነበረው ጴጥሮስና ተከታዩ ዮሐንስ እስኪመጡ ድረስ መንፈስ ቅዱስን ሳይወርድ እንዲቈይ ያደረገው በመሆኑ ላይ ነው::

2) በቆርኔሌዎስ ቤት (ሐ.ሥ. 10፥1-11፥18)

ቆርኔሌዎስ «እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ፥ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚጸልይ» ከአይሁድ ጋር ቅርርብ የነበረው የአሕዛብ ወገን ነበረ፤ በእግዚአብሔር ፊት ግን አልዳነም ነበር፤ 10፥1-3:34-35፤ 11፥13-14:: እርሱና ቤተሰቡ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ የመጀመሪያዎቹ የአሕዛብ ወገኖች ነበሩ::

ሐዋርያው ጴጥሮስ ገና ወንጌልን ሲሰብክ ሳለ፥ «ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ:: ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምእመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ፤ በልሳኖች ሲናገሩ፥ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና»:: ጴጥሮስ ይህን አይቶ እነዚህ አሕዛብ በክርስቶስና በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም አንድነትን እንደ አይሁድ ምእመናን መቀበላቸውን ተረድቶ በውሃ እንዲጠመቁ አዘዘ፤ 10፥44-48:: ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ በቆርኔሌዎስ ቤት ስለሆነው በተጠየቀ ጊዜ ጴጥሮስ፥ «ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው:: ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ» ብሎ መሰከረ፤ 11፥15-16:: በዚህ ቃል ጴጥሮስ የአይሁድና የአሕዛብ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ መሆኑን አሳየ፤ የኢየሩሳሌም ምእመናንም፥ «እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሓን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ»፤ 11፥18::

3) በኤፌሶን (19፥1-7)

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሲደርስ ዐሥራ ሁለት ያህል «ደቀ መዛሙርት» አግኝቶ «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» አላቸው:: እነርሱም በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው ነበርና የእርሱን ትምህርት ደቀ መዛሙርቱ በተረዱበት ዐይነት ይከተሉ ነበር፤ ይሁን እንጂ «መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም» አሉ፤ 19፥2:: ሐዋርያው ይህን ሰምቶ የዮሐንስን መልእክትና አገልግሎት በይበልጥ አስረድቷቸው፥ ወንጌልን ስለ ክርስቶስ ካብራራላቸው በኋላ በኢየሱስ ስም አጠመቃቸው፤ «እጁንም በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በልሳኖችም ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ»፤ 19፥6:: ከዚህ ታሪክ ሐዋርያው ሰው ሲያምን የመንፈስ ቅዱን ስጦታ እንደሚቀበል ማመኑና እነዚህ «ደቀ መዛሙርት» በክርስቶስ ያመኑ እንደሆኑ አለመቀጠሩ ግልጥ ነው፤ ምክንያቱም በኢየሱስ ስም አጥምቋቸዋል፤ ክርስቶስም በመንፈስ ቅዱስ መውረድ እንደተቀበላቸው አሳየ::

በዚህ ንኡስ አንቀጽ እስካሁን ድረስ የሚከተሉትን ነገሮች ለማሳየት ሞክረናል:-

ሀ) የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ሰው መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ይብራራሉ::

ለ) ሰው ሲያምን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል፤ መንፈስ ቅዱስም ይሞላዋል::

ሐ) አማኙ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ወደ በዓለ ኀምሳ ቀን በረከት ሁሉ ይገባል::

መ) ሰዎች አምነው መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት አንድ ዐይነት ነውና በእኩልነት ተቀባብለው መኖር ይገባቸዋል፤ ሁሉ በክርስቶስ ናቸውና አንዱን መንፈስ ተቀበሉ::

ይህን እውነት ከተረዳን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ዘንድ እየኖረ ምን እንደሚያደርግለት መዘርዘር ይገባናል::

በምዕራፍ 79 የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዴት እንደነበረ መረመርን:: በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን እጅግ ሰፋ ያለና የተሟላ፥ ምእመናንም ሁሉ በአዲስ ዐይነት መንገድ በበረከቱ ሁሉ ሲሳተፉ ሁሉ በእነርሱ ዘንድ ይኖራል:: ይህም እንዴት እንደሆነ በአምስት አርእስት አጠቃልለን ለማሳየት እንሞክራለን:-

1. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት

ሀ) ስለ ክርስቶስ ያለው ምስክርነት፤ ታላቁ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስለ ክርስቶስ መመስከር ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» የሚለውን የተስፋ ቃል ሰጥቷል፤ ዮሐ. 15፥26:: በዚህ መሠረት ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ፥ ወደ ሰማይ እንዳረገ፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎ የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል እንደተቀበለ ከመሰከረና ካስተማረ በኋላ የበዓለ ኀምሳ ስብከቱን፥ «እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ» በማለት ደመደመው:: እግዚአብሔር ኢየሱስን ጌታ አደረገው ማለት እርሱ ከሁሉ በላይ ነው ማለት ነው፤ እግዚአብሔር፥ «ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» ብሏልና፤ ሐ.ሥ. 2፥33-36:: መንፈስ ቅዱስም ወርዶ ለሚቀበሉት ይህን ይመሰክራል:: እግዚአብሔር ኢየሱስን፥ ክርስቶስ አደረገው ማለት ደግሞ ለሰው ኀጢአት መሥዋዕት በማድረግና በማስነሣት ለሰው ድኅነት አስፈላጊው ሁሉ መፈጸሙን ማረጋገጥ ማለት ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ለሚቀበሉት ይህን ደግሞ ይመሰክራል::

ለ) ስለ እውነት የሚሰጠው ምስክርነት፤ መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው:: እዚህ ላይ እውነትን በትክክል መናገር ብቻ ሳይሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እውነታ ነው፤ ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ የሚገልጸው ክብደት ያላቸው ዋና ዋና የዓለም ነገሮች ምን እንደሆኑ፥ በተለይም የክርስቶስ ትሥጉትና መሥዋዕታዊ ሞት ከትንሣኤው ጋር የዓለም ታሪክ ሁሉ እምብርት መሆናቸውን ነው፤ ዮሐ. 14፥17፤ 15፥26፤ 16፥8-15::

ሐ) ለአማኙ የሚሰጠው ምስክርት፣ ሰው ሲያምን ክርስቶስ ለኀጢአተኞች እንደሞተ ማወቅ ብቻ ሳሆን፥ ኀጢአቱ እንደተሰረየለት፥ የዘለዓለም ሕይወትን እንደተቀበለና በጸጋ የእግዚአብሔር ውድ ልጅ መሆኑን ለመረዳት ይጓጓል:: ይህም አሳብ በተለይ በምዕራፍ 80 ላይ በሰፊው ተተንትኗል::

በብሉይ ኪዳን ዘመን በትንቢት መልክ መንፈስ ቅዱስ ስለ እነዚህ እውነቶች በመጠኑ መስክሯል፣ በበዓለ ኀምሳ ቀን ትንቢት ስለተፈጸመ በአስገራሚ ኀይልና ርግጠኛነት ምስክርነቱ ግልፕ ሆኖልናል::

2. የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም

ማኅተም ባለቤትነትን ያሳያል፤ ለምሳሌ፥ በፊርማ ወይም በዕቃ ላይ ማኅተም ሲታይ፥ ፊርማውም ሆነ ዕቃው የማን እንደሆነ ያረጋግጣል:: የእግዚአብሔር ማኅተም መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው:: ይህን ትምህርት የሚያስረዱ ዋና ዋና ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው:-

«በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን፥ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው»፤ 2ቆሮ. 1፥22::

«እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም ብክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል»፤ ኤፌ. 1፥13-14::

ከእነዚህ ጥቅሶች ሦስት ነገሮችን ልብ ማድረግ ይገባናል:-

ሀ) ሰው ሲያምን መንፈስ ቅዱስ ይሰጠዋልና ይህ የእግዚአብሔር ማኅተም ነው፤ ማለት በአማኙ ልብ የእግዚአብሔር መንፈስ በመኖሩ አማኙ የእግዚአብሔር ገንዘብ መሆኑን ያውቃል::

ለ) መንፈስ ቅዱስ በልቡ በመኖሩ ለአማኙ መያዣ (ዋስትና) ነው፤ ማለት የእግዚአብሔርና የመንግሥተ ሰማያት በረከት ወራሽ መሆኑን ያረጋግጥለታል:: በዚህ ዓለም ወደ ሰማያዊ ርስታችን አንገባም፤ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ በልባችን በመኖሩ ወደ ሰማያዊ ርስታችን የምንገባ ለመሆናችን ዋስትና ነው፤ ሌላውንም ሁሉ እንደምንወርስ እናውቃለን፤ እግዚአብሔር «የመንፈሱን መያዣ ሰጠን» ተብሎ ተጽፏልና፤ 2ቆሮ. 5፥5::

ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የሚሠራው «ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ» ነው:: ሆኖም ሐዋርያው፥ «ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» ብሎ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል፤ ምክንያቱም ከቅድስና መንገድ ከወጣን፥ ምንም እንኳ ለዳግም ምጽአት ቀን ብንታተምም፥ በአሁኑ ኑሮ ብዙ በረከት፥ ደስታና አለኝታ ሊታጣ ይችላል፤ መፈሱንም እናሳዝናለን፤ ኤፌ. 4፥30::

3. የመንፈስ ቅዱስ አጽናኝነት (4)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «... ለዘለዓምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» በማለቱ እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ ያደረገውን መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ስፍራ ሆኖ እንደሚያደርግላቸው የተስፋ ቃል ሰጣቸው፤ ዮሐ. 14፥16:: የእርሱ ሥራ በአማኙ ዘንድ ብዙ ነው፤ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በአንዳንድ ሥራዎቹ ላይ እናተኩራለን:-

ሀ) መንፈስ ቅዱስ የተቀደሰ መንፈስ ነውና ከሁሉ በላይ የሚፈልገው ቅዱሳን እንድንሆን ማለት በቅድስና እንድንኖር ነው፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና» ብሎ ጽፏል፤ 1ተሰ. 4፥3:: እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ በመሆኑ ከቤት ሳሚስ ሰዎች ጋር፥ «በዚህ በቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል?» ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው፤ 1ሳሙ. 6፥20::

ሰው ዳግመኛ ሲወለድ እግዚአብሔር አዲስ «ዘር»፥ አዲስ መሠረት፥ አዲስ የሕይወት ምንጭ በልቡ ያኖራልና ሕይወቱ ወደ እግዚአብሔር ያዘነብላል፤ 1ዮሐ. 3፥9:: በእግዚአብሔር በማመን መንፈስ ቅዱስ በሰው ልብ ያድራልና አማኙ የመንፈስ ፍሬን ማፍራት ይጀምራል፤ ገላ. 5፥22:: አማኙ በሕይወቱ ለውጥ እያሳየ ይሄዳል፤ ይህም «መንፈስ ከሚሆን ጌታ» ነው፤ 2ቆሮ. 3፥18:: ቅድስና የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው፤ ሮም 8፥3-4፤ 2ተሰ. 2፥13፤ 1ጴጥ. 1፥1-2:: በመንፈስ ቅዱስ ኀይልም «የሰውነትን ሥራ ልንገድል እንችላለን»፤ ሮም 8፥13::

አንዳንድ ሰዎች ዛሬ በተመሰጠ መሬት ላይ ቢወድቁ መንፈስ ቅዱስ እንደሚቀድሳቸው ያምናሉ:: ሆኖም ይህን ክሥተት እንደ ሌሎች ክሥተቶች ሁሉ በሕይወታቸው ለውጥና አካሄድ መመዘን ያስፈልጋል (5):: በሚከተለው ምዕራፍ ስለ ቅድስና በሰፊው እናጠናለን::

ለ) መንፈስ ቅዱስ ያጽናናናል፤ ይህ ተግባር የሚከናወነው በብዙ መንገድ ነው፤ 2ቆሮ. 1፥21-22:: ክርስቲያን ከዓለም፥ ከሥጋና ከሰይጣን ጋር ትግል አለበት:: ከሥጋ ጋር የሚደረገው ትግል የውስጥ ነውና የቅድስና ትምህርት በተለይ ይህን ያመለክታል:: ከዓለምና ከሰይጣን ጋር ትግሉ በተለይ ከሰውነት ውጭ ነውና መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ኀይለኛ ጠላቶች ፊት እንድንቆም ያደፋፍረናል:: ይህንም በተለይ በምዕራፍ 93 እንመለከተዋለን::

ሐ) መንፈስ ቅዱስ ይመራናል፤ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና»፤ ሮም 8፥14:: ሰው ካመነ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተባበረ ምሪቱን በደስታ ይከተለዋል፤ ፊል. 2፥12-13፤ ቆላ. 1፥29:: መንፈስ ቅዱስ የእውነታ መንፈስ በመሆኑ የጥበብ መንፈስ ነውና አማኙን በጥበብ አሠልጥኖ ያሳድገዋል፤ ኢሳ. 11፥2፤ ቆላ. 1፥9:: ስለዚህ አማኙ በጥበብ እያደገ የራሱን ሕይወት ለመቈጣጠርና አገልግሎቱን በሌሎች ዘንድ ለመፈጸም ይችላል:: ከዚህም የተነሣ የአማኙ አለኝታ እየጸና ይሄዳል::

## 4. የመንፈስ ቅዱስ ቅባት

በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት ለማዕረጋቸው በዘይት ይቀቡ ነበር:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ተቀባ፤ ሐ.ሥ. 4፥27፤ 10፥38:: «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኀይልም ቀባው»፤ ከዚህ የተነሣ፥ «እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስ የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና»፤ ኢሳ. 61፥1፤ ሉቃ. 4፥17-19፤ ሐ.ሥ. 4፥27፤ 10፥38:: እንግዲህ «እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ» የሚለው ቃልም ኢየሱስ በቅባቱ እጅግ መደሰቱን የሚያሳይ ነው፤ ዕብ. 1፥9::

ምእመናንም የተቀቡ ናቸው፤ 2ቆሮ. 1፥22፤ 1ዮሐ. 2፥27:: አማኙ በራሱ ደካማ ነው፤ ነገር ግን ክርስቶስ በመጨረሻ ከማረጉ በፊት፥ «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ... ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»

ብሎ ለምስክርነታቸው የሚያስፈልጋቸውን ኀይል ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚቀበሉ ለሐዋርያት ተናገረ፤ ሐ.ሥ. 1፥8:: ይህ ኀይል ሐዋርያትን ከብዙ ተቃውሞና ስደት አላዳናቸውም፤ ሆኖም በምስክርነታቸው ውስጥ ትልቅ ድፍረት፥ ርግጠኛነትና ደስታ ይታያል፤ ሰዎች በክርክር ሊያሸንፉአቸው አይችሉም ነበርና መንፈስ ቅዱስ በአንደበታቸው እየሠራ፥ ብዙ ሰዎች አምነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ::

5. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

በበዓለ ኀምሳ ቀን «በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ» የሚለውን ቃል እናነባለን፤ ሐ.ሥ. 4፥31:: እንግዲህ በብርጭቆ ውስጥ ያለ ውሃ መጠን እንደሚቀንስ ምእመናን ያገኙት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ቀንሶ ይሆን? ከዚህ የተሻለ ምሳሌ የሚሆነን ፊኛ ነው:: ፊኛ በአየር የተሞላ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ሰው እፍ ብሎ በትንፋሽ ሲሞላው መጠኑ ትልቅ ሊሆን ይችላል:: ክርስቲያንም እንደዚሁ እያደገ ሲሄድ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ደረጃዎች ከፍ ከፍ እያሉ ሊሄዱ ይችላሉ::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለልዩ ልዩ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ እናነባለን:: ለምሳሌ፥ ኤልሳቤጥና ዘካርያስ ትንቢት ለመናገር (ሉቃ. 1፥41:67)፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ የሕዝብን አለቆችና ሽማግሌዎች ዐንካሳው ስላገኘው ፈውስ ለማስተማር (ሐ.ሥ. 4፥8)፥ እስጢፋኖስ የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጥ (ሐ.ሥ. 7፥55-56)፥ ሐዋርያው ጳውሎስ ጠንቋዩን በርያሱስን ለመቅጣት (ሐ.ሥ. 13፥9-11) በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ እንመለከታለን:: ስለ ሌሎች ሰዎችም በአጠቃላይ ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ እናነባለን:: መጥምቁ ዮሐንስ፥ «ገናም በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል» ተባለለት (ሉቃ. 1፥15)፤ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ ያለባቸው ሰባት ሰዎች መበለቶችን ለማገልገል ሲፈለጉ፥ «እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበት» ሰው እስጢፋኖስ ተመረጠ (ሐ.ሥ. 6፥3-5)፤ በርናባስም «መንፈስ ቅዱስ፥ እምነትም የሞላበት» ሰው ነበረ፤ ሐ.ሥ. 11፥24::

የመንፈስ ፍሬ ደስታ በመሆኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ ከኖሩ፥ «በደቀ መዛሙርትም ደስታና መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው» የሚለው ቃል አያስገርምም፤ ሐ.ሥ. 13፥52:: ኢመንፈሳውያን ሰዎች ደስታ በምግብና በመጠጥ ሊገኝ እንደሚችል ያስባሉ:: መጠጥ ይጠጣሉ፤ ለጊዜውም ቢሆን አንድ ዐይነት የተወሰነ ደስታ ሊኖራቸው ይችላል፤ በኋላ ግን ስካርን፥ ራስ ምታትንና ብዙ ሌላ ጥፋትን ያስከትላል፤ ሐዋርያው «ይህ ማባከን ነውና» ብሏል:: በአንጻሩም፥ «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» በማለት ለምእመናን ቋሚ ትእዛዝ ሲሰጥ ይታያል፤ ኤፌ. 5፥18::

ምእመናን መንፈስ ቅዱስን «ማሳዘን» እንደሚችሉና በውጤቱም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንደማይታይባቸው መገንዘብ አለባቸው:: የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለምእመናን የግል አካሄድ (ገላ. 5፥22)፥ ለአምልኮ፥ ለማስተማር፥ ለማስተዳደር፥ ለምስክርነትና ለተግሣጽ አስፈላጊ ነው፤ ኤፌ. 5፥17-21፤ ቆላ. 3፥12-17:: እንደዚሁም ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አሉና እነርሱ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ይሰጣሉ፤ ሮም 12፥3-8፤ 1ቆሮ. 12፥4-13:27-31፤ ኤፌ. 4፥7-16:: እንግዲህ ያለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የሚያስብ ሰው «ሞኝ» ነው፤ ኤፌ. 5፥17::

ከዚህ በላይ ስለ በዓለ ኀምሳ ቀንና ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተሰጠው ትምህርት የተሟላ አለመሆኑን እናስተውላለን፤ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ

ጥምቀት በሐዋርያት ላይ በጋራ የተፈጸመ ነበረና በዚያ ዕለት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን፥ ቤተ እስራኤል ከመሆን የቤተ ክርስቲያን ሕዝብ ወደ መሆን ተሻገረ። ከዚያ በኋላ ግን ሰው በክርስቶስ አምኖ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደሚያገኘው መብትና በረከት ሁሉ ውስጥ ይገባል፤ መንፈስ ቅዱስንም ይቀበላል። እውነት ነው፤ ሰው ወደሚታየው የቃል ኪዳን ሕዝብ በውሃ ጥምቀት ይገባልና ብዙ ሊቃውንት ትምህርታቸውን በውሃ ጥምቀት መጀመር ይወዳሉ። በዚህ መጽሐፍ ግን የድኅነትን ቅደም ተከተል ጠብቀን በመሄድ ላይ ነንና ጾምን፥ ጸሎትን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርትና የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት ሳንክድና ሳንነቅፍ ጥናቱን እንደሚከተለው በማተት እናቀርባለን።

ከዚህ በላይ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ስለሚሠራው ሥራ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቀውን ትምህርት ለመግለጥ ሞክረናል፤ ሌሎች አሳቦች እንዳሉም ስለምናውቅ፥ እነርሱን አሁን መመልከት ይገባናል።

## ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ ትምህርቶች አሉ። አንዳንዶቹ ልዩ አስተርእዮ እንዳላቸውና የራሳቸው «ነቢያት» ሲኖራቸው፥ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው የራሳቸውን «እውነተኛ» ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋም ሞክረዋል፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን እየተዳከሙ ስለሄዱ፥ ለቤተ ክርስቲያን ምንም ዐይነት ለውጥ አላመጡም፤ አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን «መናፍቃን» ብላ ስለምትጠራቸው፥ እነርሱን እንደገና ለመቀበል ብዙ ክርክር ተካሂዷል። በዘመናችንም ቢሆን ልዩ ልዩ ወገኖች ስላሉ፥ መቼ እንደተነሡና ትምህርታቸውም ምን እንደሚመስል በዐጭሩ ለመዘርዘር እንሞክራለን።

### 1. በምሥራቃውያንና በምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት

ስለ ምሥጢረ ሥላሴና በተለይ ስለ ትምህርተ ክርስቶስ በአበው መካከል ክርክርና ትግል የተካሄደ መሆኑን ብዙ ጊዜ ገልጠናል፤ እኛም ስለ መንፈስ ቅዱስ ባቀረብነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም ትግል ከነበረበት ከጥንቱ ትምህርት የወጣን አይመስለንም። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን ያላት ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሲሆንና፥ ስደት ሲቀር አበውም ለትምህርታቸው በሥርዐት ክብር ለማስጠት ሲፈልጉ፥ በውጤቱ መሠረታዊው ትምህርት ራሱ እየተረሳና በሰዎች ሕይወት መገለጡ እየቀነሰ የሄደ ሊመስለን ይችላል። በዚያን ጊዜ ጾም፥ ጸሎት፥ የቃለ እግዚአብሔር ጥናትና የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የጸጋ መንገዶች ከመሆን ዐልፈው ራሳቸው እንደ ጸጋ ተቈጥረው ታዩ። ዛሬም ቢሆን በብዙ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስና ስለ ሙላቱ ምንም የሚሰማ ቃል የለም።

### 2. በተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት

የመንፈስ ቅዱስ በረከት ለአማኞች የሚሰጠው በሁለት ደረጃዎች እንደሆነ የሚቀርበው ትምህርት ከአራት መቶ ዓመታት በፊት መሰማት ተጀመረ። ይህን በአራት ዓይነት እንመለከተዋለን።

*ሀ) ቶማስ ጉድውን (1600-1680)፤* በተለይ በኤፌሶን 1፥13-14 ላይ ተመርኩዞ ትምህርቱን ሰጥቷል። ትምህርቱ ሰው ካመነ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ሊታተም ይችላል የሚል ነው። ይህም ማለት ሰው ምንም እንኳ ሲያምን መንፈስ ቅዱስን ቢቀበልም፥ በመንፈስ ቅዱስ በመታተሙ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ከፍ ባለ አለኝታ ይረጋገጣል። ይህ ልዩ በረከት በእግዚአብሔር ልዕልና

የሚፈልገው ይሰጣል፤ ሆኖም የኤፌሶን ሰዎች ይህን በረከት ስለተቀበሉ፥ የእምነን ሁሉ ይህን ስጦታ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ከልባቸው መለመን ይገባቸዋል ብሎ አስተምሯል። ይህ ተመክሮ የነበራቸው ለአገልግሎታቸው በተለይም ለስብከታቸው አዲስ ኃይል እንደተሰጣቸው መስክረዋል፤ በቅርብ ጊዜ ደግሞ ዶክተር ማርቲን ሎይድ ጆንዝ (1899-1981) ይህ ትምህርት በሮም ምዕራፍ 8 እና በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ትርጓሜዎች ላይ በስፋት እንዲያተኩር አድርጓል። ይሁን እንጂ ኤፌሶን 1፥13-14ን በዚህ መንገድ ለመተርጐም ቢቻልም እንኳ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መታተም የሚናገሩ ሌሎች ጥቅሶች ይህ በረከት ለምእመናን አስቀድሞ የተሰጠ መሆኑን እንጂ ካመኑ በኋላ ቈይተው የሚቀበሉት እንደሆነ አያሳዩም፤ 2ቆሮ. 1፥21-22፤ 5፥5፤ ኤፌ. 4፥30። በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን መልእክታት፥ «ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ መታተም አለባቸው» የሚለው ትእዛዝ ተጽፎ አይገኝም (6)።

ለ) ዮሐንስ ወስሊና ተከታዮቹ፤ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጊዮርጊስ ውትፊልድ (1714-1770) እና ዮሐንስ ወስሊ (1703-1791) በእንግሊዝ አገር በአዲስ እንቅስቃሴ ታላላቅ መሪዎች ነበሩ (7)። ውትፊልድ የተሐድሶ ተከታይ ነበረ፤ ወስሊ ግን ወደ አርሚኒዮስ ትምህርት አዘነበለ። በወስሊና በተከታዮቹ ስለ ቅድስና ብዙ ዐይነት ትምህርት ተጀመረ። እነዚህ ሰዎች በቅድስና ለመኖር በጣም ይጓጉ ነበርና ሰው ካመነ በኋላ ፍጹም ወደሚሆን የቅድስና ኑሮ ሊደርስ እንደሚችል አስተማሩ። አማኙ ወደዚህ ሁለተኛ ደረጃ ሲደርስ፥ ለኀጢአት ሞቷል፤ «አሮጌው ሰው» ሞቷል (ሮም 6፥6፤ ኤፌ. 4፥22)፤ አንዳንዶች ደግሞ ፍጹም ኀጢአት አልሠራም ወይም አሁን ኀጢአት ለመሥራት የሚያነሣሣ ፈተና የለብኝም ይሉ ይሆናል። እንደዚህ የሚያስተምሩት ለግዙፍ ኀጢአት አሳብ ወይም ስሜት ላይኖራቸው ይችላል፤ ሆኖም ኵራት፥ ቅናት፥ ፍትወትና የተደበቁ የልብ ኀጢአቶች እንዳሉባቸው ልንጠይቃቸው ይገባል። ይህ ዓይነቱ ኀጢአት ካለባቸው «የሥጋ ፈቃድ» እና የሰውነት ሥራ (ሮም 8፥13) ገና ስለሚኖር አሮጌው ሰው ፈጽሞ አይሞትም።

ዋናው ጥያቄያችን አማኙ በዚህ ዓለም ወደዚህ ቅድስና ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል የሚያስረዳ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አለ? የሚለው ነው። የሰው ልብ እጅግ ተንኰለኛ ነውና አማኙን ራሱን እንኳ ሊያታልለው ይችላል። ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን በመረዳት፥ «ኀጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን... ኀጢአት አላደረግንም ብንል... ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» ብሎ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶናል፤ 1ዮሐ. 1፥8-10። ሐዋርያው ይህን የጻፈልን ኀጢአት እንዳንሠራ ነው፤ ሰው ኀጢአትን ቢሠራም እንኳ ከዚያ የሚዳንበትን መንገድ ገልጧል፤ 1ዮሐ. 2፥1-2። ሐዋርያው የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም፥ ልቡ ፍጹም እንደማይሆን በማሰብ ራሱን ከአንባቢዎቹ ጋር አንድ አድርጎ ቈጠረው። እውነት ነው፤ አማኙ ሁልጊዜ የጽድቅ ሥራን እንደሚሠራና ኀጢአት እንደማይፈጽም አስተማረ (1ዮሐ. 2፥29፤ 3፥9)፤ ይህ ግን ፍጹም ቅዱስ ሊሆን ይችላል ማለት አይደለም።

ከወስሊና ከተከታዮቹ ብዙ ትምህርቶች፥ ተቋሞችና እንቅስቃሴዎች ተመሥርተዋል፤ አያሌ ተከታዮችም ተገኝተዋል፤ በዚህ አመለካከት መሠረት በኢትዮጵያ መመሥረቱ የሚታወቀው ቤተ ክርስቲያን የናዝሬን ቤተ ክርስቲያን ነው።

ሐ) ጴንጠቆስጤያውያንና ካሪዝማቲኮች፤ የጴንጠቆስጤያውያን እንቅስቃሴ በ1906 ዓ.ም. በአሜሪካ ተጀመረ። የዚህ እንቅስቃሴ መሪዎች በቅድስና እንቅስቃሴ ውስጥ ስለነበሩ፥ መሠረታዊ ትምህርታቸው ወደ አርሚኒዮስ

አመለካከት የሚያዘነብል መሆኑ አያስገርምም:: በትምህርታቸው ከሌሎች ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚለዩት በሚከተሉት አራት ነጥቦች ነው:-

1) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚሰጠው ሰው ካመነ በኋላ ብዙ ጊዜ ቆይቶ ነው::

2) በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ነው::

3) የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመቀበል በር ይከፍታል::

4) በመንፈስ ቅዱስ የተሞላች ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይገኙባታል::

የጰንጠቆስጤያውያት አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ የአስተዳደር ሥርዐት አላቸው፤ በዓለም ውስጥ በጣም የታወቀችዋና የተስፋፋችዋ ጰንጠቆስጤያዊት ቤተ ክርስቲያን «ጉባኤ እግዚአብሔር» ናት (8)::

ጰንጠቆስጤያውያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሲናገሩ፥ አዲስ ኀይል እንዳገኙ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በተለየ መንገድ ሕያው እንደሚሆን፥ በግልና በጋራ ስብሰባዎች ላይ የሚቀርበው ጸሎት ደስታ እንደሆነ፥ ከፊት ይልቅ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚወዱና በክርስቲያናዊ ኑሮአቸው በመሥዋዕትነት ክርስቶስን እንደሚከተሉ ይናገራሉ:: ሌሎች ሰዎች ሲመለከቱአቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ትልቅ ርምጃ የተራመዱ መሆናቸውን ሊመሰክሩላቸው ይችላሉ:: ይህ እንቅስቃሴ ባለበት በልሳን መናገር፥ ትንቢትን («መገለጥ») መተንበይ፥ የፈውስ አገልግሎትና አጋንንትን ከሰዎች ማስወጣት ይታያል::

የካሪዝማቲኮች እንቅስቃሴ ከጰንጠቆስጤያውያን እንቅስቃሴ የተነሣ በ1970 ዓ.ም. ገደማ ከጥንት ጀምሮ በተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሰፊው መታየት ጀመረ:: ካሪዝማቲኮች ካደጉባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሊወጡ አልፈለጉምና የጰንጠቆስጤያውያንን አዲስ ትምህርት በየቤተ ክርስቲያናቸው ለማስፋፋት ሲሞክሩ፥ አብያተ ክርስቲያናቱ አዲስ መንፈሳዊ ኀይል እንደሚያገኙ ተስፋ አደረጉ::

ካሪዝማቲኮች ከትውፊታውያን ተቃውሞ ያጋጠማቸው መሆኑ አያስገርምም፤ በትዕግሥትና በፍቅር መንፈስ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ግን በኦርቶዶክስ፥ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በመጠኑ ተቀባይነትን ማግኘት ችለዋል::

**1. ጰንጠቆስጤያውያን ለትምህርታቸው የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች**

ሀ) የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ትንሣኤ በፊት በእርሱ አመኑ፤ ሆኖም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ብሎ አዝዟአቸዋል፤ ሉቃ. 24፥49፤ ሐ.ሥ. 1፥ 5፡8:: ደቀ መዛሙርቱ አዲስ ኀይልን ለአገልግሎታቸው ለመቀበል በኢየሩሳሌም ቆዩ::

ለ) ደቀ መዛሙርት ዐሥር ቀን ከቆዩ በኋላ፥ «መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር»፤ ሐ.ሥ. 2፥4::

ሐ) ምእመናን ዛሬ እንደ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ ያስፈልጋቸዋል:: አማኙ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዲቀበል ከመጠየቁ በፊት፥ ዐውቆ የሠራውን ኀጢአት ሁሉ እንዲናዘዝ፥ በሕይወቱ

ለቀረው ሌላ ኀጢአት ንስሓ እንዲገባ፥ ክርስቶስ ኀጢአቱን ሁሉ ይቅር እንዳለ እንዲያምን፥ ሕይወቱን ሁሉ ለእርሱ አሳልፎ እንዲያስረክብና ክርስቶስ ለአገልግሎቱ አዲስ ኀይልና አዲስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደሚሰጠው እንዲያምን ለማድረግ ሊደፋፈር ይችላል። በዚህ መንገድ ራሱን ካዘጋጀ በኋላ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ እንዲያጠምቀው አማኙ ሲጠይቅ መበረታታትን ሊቀበል ይችላል።

መ) ደቀ መዛሙርት በሁለት ደረጃዎች የክርስትናን ሙሉ በረከት መቀበላቸው፥ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሚገኙ በሌሎች ታሪኮችም ይታያል። የሰማርያ ሰዎች የፊልጶስን መልእክት ተቀብለው በውሃ ተጠመቁ። በኋላ ሐዋርያት ወደ እነርሱ ሲላኩ ሰማርያውያኑ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ ሐ.ሥ. 8፥12-17። ቆርኔሌዎስ በእግዚአብሔር የሚያምን መንፈሳዊ ሰው ነበረ፤ የጴጥሮስን ስብከት ሲሰማ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቀ፤ ሐ.ሥ. 10፥34-48። በኤፌሶን የነበሩ «ደቀ መዛሙርት» በዮሐንስ የንስሓ ጥምቀት አመኑ፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲሰሙም በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፤ ሐ.ሥ. 19፥1-7። እንግዲህ ከዚህ የተነሣ ዛሬ ሰዎች በሁለት ደረጃዎች የክርስትናን ሙሉ በረከት ሊቀበሉ ይችላሉ።

ሠ) ይህ የአዲስ ኪዳን ኀይል ለደቀ መዛሙርቱ በምስክርነታቸውና በአገልግሎታቸው የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ (ሐ.ሥ. 1፥8፤ ኤፌ. 4፥8:11-13)፥ በምእመናን ሕይወት ሁሉ ላይ የሚመጣውን የኀጢአት ተጽዕኖ እንዲቋቋሙና እንዲያሸንፉ (ሮም 6፥11-14፤ 8፥13-14፤ ገላ. 2፥20፤ ፊል. 3፥10-11)፥ ምእመናንን የሚያጠቁ የሰይጣንንና የአጋንንትን ኀይላት ድል እንዲነሡ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ኀይልን ሰጣቸው፤ 2ቆሮ. 10፥3-4፤ ኤፌ. 1፥19-21፤ 6፥10-18፤ 1ዮሐ. 4፥4። አስቀድሞ ታይተው በማይታወቁና ለምእመናን ሁሉ በተሰጡ እጅግ በርካታ በሆኑ ስጦታዎች ውስጥ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በውጤታማነት ተግባራዊ ሆኗል፤ ሐ.ሥ. 2፥16-18፤ 1ቆሮ. 12፥7፤ 1ጴጥ. 4፥10፤ ከዘኍ. 11፥17:24-29 ጋርም ያስተያዩ። ስጦታዎቹ የቤተ ክርስቲያንን እድገት እውን ለማድረግ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው (1ቆሮ. 12፥7፤ 14፥12)፤ የስጦታዎቹ አገልግሎትም ወንጌል ለአይሁድ ብቻ እንዲሰበክ ሳይሆን፥ ሕዝቦች ሁሉ በክርስቶስ አምነው በቤተ ክርስቲያን እንዲሳተፉና የእግዚአብሔር ክብር እንዲታይ አድርጓል (9)።

## 2. የጥንቱን ትምህርት የሚከተሉ ወገኖች የጰንጠቆስጤያውያንን መሠረታዊ ትምህርት የማይቀበሉበት ምክንያት

ሁለቱ ወገኖች በብዙ መልክ በልዩ ልዩ ትምህርት የሚስማሙ ሆነው ቢታይም፥ የጰንጠቆስጤያውያን መሠረታዊ ትምህርት አደገኛ ሆኖ ተገኘ (10)።

የጰንጠቆስጤያውያን እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት በቅድስና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በቤተ ክርስቲያን «የተቀደሱ ምእመናን» እና «ተራ ምእመናን» እንደሚገኙ ይታመን ነበር። ጰንጠቆስጤያውያን ከዚህ ዐውድ ስለወጡ፥ ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁና ያልተጠመቁ ተብለው መጠራታቸው አያስገርምም። በሌሎችም ዘንድ እንደዚሁ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና ያልተሞሉ፥ መንፈሳውያንና ሥጋውያን፥ ደቀ መዛሙርትና ተራ ምእመናን፥ ቅዱሳንና ተራ ምእመናን በመባል እየተጠሩ ይገኛሉ።

የጥንቱን ትምህርት ለሚከተሉ ወገኖች ግን በዚህ ዐይነት ምእመናንን ለያይቶ ማየቱ አደገኛ ሆኖ ይታያቸዋል። ምክንያቱም ወደ ልዩ የቅድስና ደረጃ የደረሱት ሊታበዩ፥ ያልደረሱት ደግሞ ቅናት ሊያድርባቸው ይችላል (11)።

ከሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት የሚሻለው እንደሚከተለው ነው፤ ሰው በሚያምንበት ጊዜ እንደተወለደ ሕፃን ነውና እያደገ እንዲሄድ ተጠርቷል፤ 1ጴጥ. 2፥2-3፤ 2ጴጥ. 3፥18:: ይህ እድገት በብዙ በኩል ሊታይ ይችላል:: ሆኖም ምእመናን በዚህ እድገት እርስ በርሳቸው መወዳደር ሳይሆን፥ ትሑታን መሆንና ክርስቶስን መምሰል አለባቸው፤ ፊል. 2፥4-5:: ክርስቲያን የራሱን ወይም የሌላውን የእድገት ደረጃ በትክክል መመዘን የሚችል መሆኑ አጠራጣሪ ነው፤ ኤር. 17፥9::

ለጴንጠቆስጤያውያን ግን ልዩነታቸው ከሌሎች ምእመናን በሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ በልዩ ልሳን በመናገር፥ በትንቢት፥ በፈውስ ወይም በተአምራት እንደሆነ ሊታያቸው ይችላል:: ምክንያቱም እንቅስቃሴያቸው በተለይ የስሜትና የተመክሮ እንጂ የትምህርት እንቅስቃሴ አይደለም:: የጥንቱን ትምህርት የሚከተሉት ግን ትምህርታቸውን የሚጀምሩትና የሚያጸኑት በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው፤ ይህን ካረጋገጡ በኋላም የማናቸውንም እንቅስቃሴ ክሥተቶች በሚገባ ይመለከታሉ:: በዚህ ምዕራፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ ከጥንት ጀምሮ የመጣውንና የተለመደውን ትምህርት ለመግለጥ ሞክረናል:: ለእነዚህ ወገኖች ስለ ሁለቱ ደረጃዎች የሚሰጠው ትምህርት ብዙ ድክመት እንዳለበት ይታያቸዋል:: እውነት ነው፤ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የመንፈስ ቅዱስን ኀይል የተቀበሉት በሁለት ደረጃዎች ነው፤ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ሕግና ሥርዐት መሠረት ተወልደው አዲስ ኪዳን ሲገባ ሙላትን ተቀብለዋልና:: እኛ ግን ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ በመወለዳችን ቀጥታ ወደ አዲስ ኪዳን በረከትና ኀይል እንገባለን:: በሰማርያ፥ በቆርኔሌዎስ ቤት ወይም በኤፌሶን ከሆነው ለሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት በቂ መሠረት አይገኝም፤ በመልእክታትም የሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት አልተጻፈም::

እንግዲህ ጴንጠቆስጤያውያን (እና ካሪዝማቲኮች) በሁለቱ ደረጃዎች ላይ ስላላቸው ተመክሮ ሲመሰክሩ ምን ማለት እንችላለን? እግዚአብሔር ባርኮአቸዋልና በዚህ መደሰት ይገባናል:: ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ትምህርት በማይሰጥባቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ካደጉ፥ የእነርሱ የሁለተኛ ደረጃ ተመክሮ ወደ ክርስቶስ መመለሳቸው ሊሆን ይችላል:: ስለ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥባቸው አብያተ ክርስቲያናት ያደጉ ሌሎች ካሉ ደግሞ፥ እንደ ጴንጠቆስጤያውያን ሥርዐት በጸሎት፥ በጥናት፥ ራስን አሳልፎ ለእግዚአብሔር በመስጠት... ወዘተ የተዘጋጁ ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን አዲስ በረከት መቀበላቸው አያስገርምምና በግል ሕይወታቸው ታላቅ ርምጃ ወስደዋል ማለት ነው:: በዚህም መሠረት ሦስተኛ፥ አራተኛ... ወዘተ ደረጃዎች ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ::

ስለ አንድ ክርስቲያን ስንናገር፥ «በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ» ብንል ስለ ሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት ማሳሰባችን ነው:: «በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ» ነው ካልን ግን የመጽሐፍ ቅዱስን አሳብ እንከተላለን ማለት ነው (ሐ.ሥ. 6፥3:5፤ 11፥24)፤ በሁለቱ ደረጃዎች ትምህርት ላይ አናተኩርምና ምእመናን ሁሉ ይህ ኀይል ሊኖራቸውና ሊጨመርላቸው የሚችል መሆኑን እንዲቀበሉ እናደፋፍራቸዋለን::

መ) የሦስተኛው «ማዕበል» እንቅስቃሴ፤ ጴንጠቆስጤያውያንና ካሪዝማቲኮች አንደኛና ሁለተኛ «ማዕበሎች» ሲሆኑ፥ ሦስተኛው ማዕበል ከታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ከዮሐንስ ዊምበር (1934-1997) ጋር የተያያዘ ነው (12):: ይህ መምህር ራሱን እንደ ጴንጠቆስጤያዊ ወይም እንደ ካሪዝማቲክ አልቈጠረም፤ ሆኖም ጉባኤዎችና ከጉባኤዎቹ አገልግሎት የተነሣ የተመሠረቱ

አብያተ ክርስቲያናት ከ1ኛና ከ2ኛ ማዕበል ሥርዐትና ክሥተቶች ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የዊምበርና የተከታዮቹ ትምህርት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የሚያተኩር ነው:-

1) ሰው በክርስቶስ ሲያምን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል፤ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃል፤ ስለዚህ በምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ሁለት ደረጃዎች መኖራቸው አይታይም፡፡

2) ከወንጌል ስብከት ጋር «ምልክቶችና ተአምራት» እንዲታዩ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው፤ እነዚህም በተለይ በአዲስ ልሳን መናገር፥ ትንቢት፥ ፈውስ፥ በመንፈስ «መገደል» (በተመሰጠ በመሬት ላይ መውደቅ)... ወዘተ ናቸው፡፡ ዊምበር ብዙ ጥናት አድርጎ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሲደረግ እነዚህ ክሥተቶች እንደታዩ ለማረጋገጥ ሞክሯል፡፡ ሌሎች ግን እነዚህ ክሥተቶች ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ የታዩ ቢሆንም፥ ለረጅም ዘመናት እውን ሆነው እንዳልቈዩ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል በተሐድሶ ዘመን በዋናው እንቅስቃሴ ውስጥ አልታዩም፤ በነውትፊልድና በነወስሊ በተነሣው እንቅስቃሴም ጐልተው አልተንጸባረቁም፡፡ በተጨማሪም በሌሎች ልሳኖች መናገርና ትንቢት መተንበይ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ 1900 ዓ.ም. ገደማ ድረስ ስለ መኖራቸው የሚያስረዱ ብዙ ፍንጮች አይገኙም፡፡

3) መንፈሳዊ ስጦታዎችን በሚመለከት የተለየ አጠቃቀም አለ፤ ለምሳሌ፥ በልሳኖች መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ሳይሆን፥ ለአገልግሎትና ለጸሎት የሚጠቅም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ይላሉ፡፡ ይህን አሁን እንመረምረውም፤ ሆኖም ከዚህ ትምህርት ሁሉ ጋር አንድ ቀዳሚና መሠረታዊ አሳብ አለ፤ ይኸውም «ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች» (2ቆሮ. 12፥12) ሁልጊዜ የሚሰጡ መሆኑ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው የተስፋ ቃል ነው የሚለው ነው፡፡

ሌሎች ግን በቃል ኪዳን ውስጥ የኀጢአት ስርየትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አሉ (ሐ.ሥ. 2፥38)፤ ሆኖም «ምልክቶችና ድንቅ ነገሮች» እንደ እግዚአብሔር ልዕልና ይሰጣሉ እንጂ (1ቆሮ. 12፥11፤ ዕብ. 2፥4) ለሰዎች ሁሉ፥ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉና በየዘመኑ ሁሉ እንደሚሰጡ አልተገለጠም ይላሉ፡፡ ይህ የሐዋርያት ሥራ የሦስተኛው ማዕበል ትምህርት አንድ አተረጓጐም ነው፤ ብዙ ፕሮቴስታንቶችም በተለይ በኢትዮጵያ ይህን የሚቀበሉት ይመስላል፤ በትምህርተ መለኮት መምህራን ዘንድ ግን ተቀባይነት ላይኖር ይችላል፤ ምክንያቱም ለዚህ አሳብ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድጋፍ ማግኘት ያስቸግራል፤ ስለ ሐዋርያት ሥራ አተረጓጐም የተሻለ አሳብ ስለሚያገኙ ይህ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክና ከራሳቸው ተመክሮ ጋር ብዙ የሚስማማ አይደለም፡፡

### መ) መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያናዊ ኑሮ

ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ እጅግ ሰፊና ጥልቀት ያለው በመሆኑ፥ ምእመናን ካመኑበትና ከአጠቃላዩ መሠረታዊ ትምህርት በቀላሉ ወደ ልዩ ልዩ የተዛቡ ትምህርቶች ሊሳቡ ይችላሉ፡፡ ይህ እንዳይሆንና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ምእመናን የሚከተሉትን ነጥቦች በሚገባ መገንዘብ እንዲችሉ ትምህርታቸው:-

1. ሥላሴያዊ ይሁን፤ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ይተካከላል፤ እነርሱ አይበላለጡምና፡፡

2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማእከላዊ ያድርግ፤ ሰው ወደ አብ የሚደርሰው በክርስቶስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ወደ ራሱ ሳይሆን፥ ወደ ክርስቶስ ያመለክታል።

3. አካላዊ ይሁን፤ መንፈስ ቅዱስ የራሱ ማንነት አለው፤ አማኙም ይህን መገንዘብ አለበት። በራሱ ሕይወትም ይህ የክርስቶስ ሥራ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ተለይቶ መታወቅ ባይችልም፥ ዋናው ነገር ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ እርሱ የሚመጣ መሆኑን ማስተዋል ነው።

4. ሕይወትን ሁሉ አመልካች ይሁን፤ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአማኙ የግል ሕይወት፥ በአምልኮቱ፥ ከሌሎች መአመናን ጋር በአንድነት ሲኖር፥ በቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይም በሌሎች ስጦታዎች ሲያገለግል፥ በኅብረተሰብ ውስጥ እየተመላለሰ ሲመሰክር ኑሮው የተሟላ ይሆናል። ይህንም ሲያደርግ ከዚህ በላይ በንኡስ ርእሱ መጨረሻ ላይ የተጻፉትን አምስት ዋና ዋና ነገሮች ያስተውል።

5. ንጹሕ ይሁን፤ ኀጢአት መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናልና።

# ማስታወሻ

(1) RR ገጽ 764 ይመ.

(2) Grudem ገጽ 763-785 ይመ.

(3) Grudem ሰባቱ ጥቅሶች አንድ ትምህርት መያዛቸውን በሰፊው ጽፏል፤ ገጽ 767-768 ይመ.። የጰንጠቆስጤያውያን አተረጓጎም «The Holy Spirit - An Introduction» በሚል ርእስ በDavid Petts ተጽፎ «ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» ተብሎ ወደ አማርኛ በተተረጐመው መጽሐፍ ተሰጥቷል።

(4) የ«አጽናኝ» ትርጉም በም. 81 ላይ ተብራርቷል።

(5) ይህ ክሥተት ብዙ ጊዜ በእንግሊዝኛ Being Slain in the Spirit (በመንፈስ መገደል) ተብሏል። በመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር ክብር ፊት የወደቁ መሆናቸውን እናነባለን፤ ሆኖም ይህ ክሥተት «በመንፈስ መገደል አልተባለም»። Grudem ገጽ 640 ይመ.

(6) ቶማስ ጉድውን ትምህርቱን ለመደገፍ በክርስቶስና በምእመናን መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ጠቅሷል። ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ሰው ከሆነ በኋላ በመንፈስ ቅዱስና በኀይሉ ተጠመቀ፤ ምእመናንም በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ከተወለዱ በኋላ በመንፈስ ቀዱስ ሊጠመቁ ይችላሉ። ይህን አባባል ሁሉ ብንቀበልም እንኳ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እንደዚሁም በምእመናን ሞትና ትንሣኤ መካከል ግንኙነትና ተመሳሳይነት እንዳለ ያስተምራል (ሮም 6፥3-6፤ ቆላ. 2፥11-13፤ 3፥1)፤ ሆኖም ምእመናን ከክርስቶስ ትሥጉትና ጥምቀት ጋር ግንኙነት ወይም ተመሳሳይነት እንዳላቸው አያስተምርም። ስለዚህ ይህ አሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ሲመዘን መሠረት ያለው ሆኖ አይታይም። በኤፌሶን 1፥13-14 ላይ በመመርኰዝ የቀረበውን የቶማስ ጉድውንን ስብከት ይመ.

(7) ውትፊልድ በአብያተ ክርስቲያናት ወንጌልን የመስበክ በር ሲዘጋበት በሜዳ ላይ ላልተማሩትና ለድኾች ሰበከ:: ብዙ ሺህ ሰዎች ስብከቱን ሰምተው በክርስቶስ አመኑ:: አገልግሎቱ እየተስፋፋ ሲሄድም በሜዳ እንዲሰብክ ወስሊን አለማመደው:: ወስሊም በበኩሉ ያመኑትን ሰዎች በማኅበር አደራጅቶና አሠልጥኖ የመቶዲስት ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት አደረገ:: ወስሊ በተሐድሶ ትምህርት ምክንያት ከውትፊልድ ተለየ:: ውትፊልድ ሰባት ጊዜ ወደ አሜሪካ ሄዶ ስለነበር፥ ከነዮናታን ኤድዋርድስ ጋር በተደረገው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ታላቅ ስፍራ ነበረው::

(8) ጳንጠቆስጤ ማለት በግሪክ ቋንቋ በዓለ ኀምሳ ማለት ነው:: Grudem በም. 39 ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ሙላት ጽፏል፤ እንደዚሁም በIVP በታተመው «The Church» በሚለው መጽሐፍ Edmund P. Clowney ስለዚህ አሳብና ስለ እንቅስቃሴዎቹ በም. 16 ላይ በጥሩ አኳኋን አትቷል::

(9) ይህ አንቀጽ በተለይ በGrudem ገጽ 771-772 በዝርዝር ተገልጧል:: ጳንጠቆስጤያውያን ይህን የሚያስተምሩ ቢሆንም፥ ምእመናን ሁሉ ትምህርቱን በአዲስ ኪዳን ትምህርት መሠረት መርምረው ሊያውቁትና ሊቀበሉት ይገባል::

(10) ክርስቲያን ወደ ሙሉ በረከት የሚገባው በሁለት ደረጃ መሆኑን ስለ ማስተማር Grudem በገጽ 775-777 አትቷል::

(11) Grudem ገጽ 775-777 ይመ.

(12) «ሦስተኛ ማዕበል» የሚለው ስም ለዚህ እንቅስቃሴ የተሰጠው በFuller Seminary ፕሮፌሰር በC. Peter Wagner ነበረ:: ዊምበር የAssociation of Vineyard Churches መሪ ነበረ:: ዋና መጻሕፍቱ Power Evangelism (1992) እና Power Healing (1987) ናቸው:: Grudem ገጽ 763 ማስታወሻ ይመ.

# ምዕራፍ 92 - ቅድስና

## መግቢያ

በምዕራፍ 89 መጨረሻ ላይ የቅድስናን ደረጃ አትተናል:: በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ጻድቅ የሆነና መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ የእግዚአብሔር ልጅ በዚህ ዓለም እንዴት መኖር እንደሚገባው እንመረምራለን:: የቅድስና አኗኗር በሁለት አቅጣጫ ይታያል፤ ይኸውም የመጀመሪያው በክርስቶስ ሞት በመተባበር ለኀጢአትና ለክፋት ሁሉ መሞት ሲሆን፥ ይህ አሉታዊ ነው፤ ሁለተኛው አዎንታዊ ሲሆን፥ የክርስቶስ ትንሣኤ ተካፋይ በመሆን በአዲስ ሕይወት መኖር ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች እነዚህን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንዲያደርጉ የሚያስገድዷቸው በተለይ ሦስት ታላላቅ ምክንያቶች አሉ (1)፤ ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-

1. የእግዚአብሔር ቅድስና

ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» የሚለውን የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ በወንጌል ለተጠሩት ያብራራል፤ ዘሌ. 11÷44-45፤ 19÷2፤ 1ጴጥ. 1÷15-16:: ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯልና በጸጋ እንደገና ለእውነት በሚሆን ጽድቅና ቅድስና፥ በዕውቀትም ይፈጠራል፤ ኤፌ. 4÷24፤ ቆላ. 3÷10::

የክርስቲያንን አኗኗር በተመለከተ ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ስናስብ፥ ከኀጢአትና ከክፋት ሁሉ ዐይኖቹን እንኳ ማራቁን ብቻ ሳይሆን (ዕን. 1÷13)፥ ፍጹም የመሆኑን አሳብ ጭምር ማሰላሰል ይገባናል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ምሕረቱ፥ «እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ» እና ስለ ርኅራኄው፥ «አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩኆች ሁኑ» የሚሉትን ትእዛዛት ለተከታዮቹ ሰጠ፤ ማቴ. 5÷48፤ ሉቃ. 6÷36::

2. የእግዚአብሔር ትእዛዛት

እግዚአብሔር ቤተ እስራኤልን ከግብጽ አውጥቶ ወደ ራሱ አመጣ:: በምድረ በዳ ታላቅ የተስፋ ቃልን ሰጣቸው፤ «...አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፥ ኪዳኔንም ብትጠብቁ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» በማለቱ የያዕቆብ ዘር ለእርሱ ልዩና ቅዱስ ሕዝብ እንዲሆን ዓላማውን ገለጠ፤ ዘጸ. 19÷3-6:: ከዚያም በኋላ ኪዳናውያቱን ዐሠርቱ ቃላትን በታላቅ ክብር ሰጣቸው፤ ዘጸ. 20÷1-17:: እነዚህ ቃላት በጽላት ተጽፈው በታቦት ውስጥ ኖሩ፤ በአሪት የተሰጡት ትእዛዛት ሁሉ በዐሠርቱ ቃላት ተመሥርተው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት እንደሚፈጸም ገለጡ እንጂ በመሠረታዊው ቃል ኪዳን ላይ ምንም አዲስ ነገር አልጨመሩም:: ሕዝቡ ሕጉን በመጠበቅ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ነበራቸው:: በእኛ ዘንድ ሕጉን ግብረ ገባዊ፥ ብሔራዊና ሥርዐታዊ ብሎ መከፈል የተለመደ ቢሆንም፥ አንድ ሕግ ነው:: እግዚአብሔር በአርባ ዓመታት ውስጥ በምድረ በዳ ሕጉን አስተምሮ አሠለጠናቸው፤ በመጨረሻም ወደ ቅድስቲቱ አገር ከመግባታቸው በፊት፥ በአዲስ ዐውድ እንዲጠብቁት ዐሠርቱ ቃላት ለአዲስ ትውልድ በድጋሚ እንዲሰጡ ሙሴን አዘዘው፤ ዘዳ. 5÷1-21::

ከምድረ በዳው ጉሮ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ የነበረው የቤተ እስራኤል ታሪክ ግን አሳዛኝ ነበር። እግዚአብሔር ከባረካቸው በኋላ እስራኤል ኪዳኑን ረስተው ወደ ባዕድ አምልኮ ዞሩ፤ እግዚአብሔር በቀጣቸው ጊዜ ምሕረትን ሲለምኑ፥ እግዚአብሔር አዳናቸው፤ ሆኖም ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደገና ከኪዳኑ ወጡ። ይህ ዐይነት ቅደም ተከተል:- በረከት፥ ክሕደት፥ ቅጣት፥ ልመና፥ ምሕረትና በረከት... ወዘተ ብዙ ጊዜ በእስራኤል ታሪክ ተደጋግሞ ይታያል፤ መሳ. 2፥10-19።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕግንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣም፤ ለመፈጸም እንጂ። ለሕግና ለነቢያት ፍጹም ታዛዥ በመሆን «ከእናንተ ስለ ኀጢአት የሚወቅሠኝ ማን ነው?» ብሎ እስከ መጠየቅ ደረሰ፤ ዮሐ. 8፥46። ክርስቶስ ሕጉን የፈጸመልን በብዙ መንገድ ነው፤ በዐጭሩ ዋና ዋና ነጥቦችን እንደሚከተለው መዘርዘር እንችላለን:-

ሀ) ሕጉን በመፈጸም ጽድቃችን ሊሆንልን ቻለ፤ 1ቆሮ. 1፥30-31።

ለ) የኀጢታችንን ቅጣት በመሸከም ከሕግ ርግማን ዋጀን፤ ገላ. 3፥10:13።

ሐ) ከኀጢአት ባርነት፥ ከሕግ ሥልጣን፥ ከሞት ፍርሀትና ከሰይጣን ኀይል በማውጣት እግዚአብሔርን ለመከተል ነጻነት ሰጠን፤ ዮሐ. 8፥32:34፤ ሐ.ሥ. 15፥10፤ ሮም 8፥2-4፤ ዕብ. 2፥14-15።

መ) የሕጉን ትእዛዛት በማብራራት ሕጉን በፊደል ብቻ ሳይሆን እንደ ዐውዱ በመንፈሳዊ መንገድ መጠበቅ እንዳለብን አዘዘን፤ ማቴ. 5፥21-26:27-30:33-37።

ሠ) እውነተኛ ፍቅር ለደቀ መዛሙርቱ በማሳየት ለእግዚአብሔርና ለሰው ሕጉን በደስታ ለመፈጸም ስሜትም፥ ኀይልም መስጠቱን ገለጠልን፤ ዮሐ. 13፥34-35፤ 15፥9-10።

ክርስቶስ ሕጉን በማክበሩና የአባቱን ፈቃድ በመጠበቁ ለምትመሠረተዋ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ ምሳሌነትን አሳይቶ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ መቶ ዓመታት ዐሠርቱ ቃላትን በግብረገባዊ መሠረትነታቸው አከበረቻቸው፤ አስተማረቻቸውም።

ዛሬ ግን ስለ ሕግና ስለ ዐሠርቱ ቃላት ሌላ ዐይነት ትምህርት በልዩ ልዩ ስፍራ በቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ ይሰማል። እነዚህ ሰዎች ከሚናገሩት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

ሰው በእምነት እንጂ ሕጉን በመፈጸም አይጸድቅም፤ ሕግ የብሉይ ኪዳን ጉዳይ ነው፤ የዐሠርቱ ቃላት ጉዳይ እኛን አይመለከተንም፤ ለእኛ ፍቅር ብቻ ያስፈልገናል። እውነት ነው፤ ፍቅር ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ዋናው መሆኑን የአዲስ ኪዳን ትምህርት በሚያረጋግጠው መሠረት ሁላችን እንስማማለን (ማር. 12፥30-32፤ 1ቆሮ. 13፥13፤ ገላ. 5፥22)፤ ሆኖም የሕግ፥ የትእዛዛትና የዐሠርቱ ቃላት ጉዳይ አይመለከተንም ማለት ሌላ ትምህርት ነው። ለእነዚህ ሰዎች መልሳችን ምን መሆን አለበት?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ» በማለት የተናገረው፥ ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቃችንን የምንገልጥበት የፍቅራችን መግለጫና መገምገሚያ መሆኑን ያሳያል፤ ዮሐ. 15፥14፤ ክርስቶስ በትምህርቱ ብዙ ትእዛዛትን ሰጥቶናል፤ ከዚያም በኋላ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የክርስቶስን ፈቃድ በትምህርታቸው

ገለጡ። ሐዋርያው ጳውሎስም እንግዲህ፦ «እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና። አታመንዝር÷ አትግደል÷ አትስረቅ÷ በውሸት አትመስክር÷ አትመኝ የሚለው ከሌላዪቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሏል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው» በማለት ፍቅርና ትእዛዛቱ ግንኙነት እንዳላቸው ጽፏል፤ ሮም 13÷8-10። በዚህ አንቀጽ ላይ ሐዋርያው ዕዳ ለክርስቲያን መልካም ነገር አለመሆኑንና ካለበትም ቶሎ ዕዳውን ሁሉ መመለስ እንዳለበት በማስተማሩ ምእመናን እርስ በርሳቸው ዕዳ እንዳለባቸው ገልጧል፤ ይህም ዕዳ የዘወትር መዋደድ ነው። ዕዳ ክፉትን በቀላሉ ሊፈጥር ይችላል፤ ስለዚህ በሰጪውና በተቀባዩ መካከል መለያየት እንዳይመጣ ተቀባዩ ዕዳውን ሳይጠየቅ ቶሎ መመለስ ይገባዋል። ሐዋርያው ከዐሠርቱ ቃላት የመጨረሻዎቹን አምስቱን ትእዛዛት በቅደም ተከተላቸው መሠረት በመጥቀሱ (ዘጸ. 20÷13-17፤ ዘዳ. 5÷17-21)÷ እንደዚሁም ፍቅር የሕግ ፍጻሜ መሆኑን በማሳሰቡ÷ ሕግና ዐሠርቱ ቃላት በክርስቲያናዊ ኑሮ ከፍ ያለ ስፍራ እንዳላቸው ያሳያል። እነዚህ ትእዛዛት በአሉታዊ አገላለጥ ቢጻፉም÷ በአዎንታዊ አገላለጥ በሚጻፈው «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» በሚለው ትእዛዝ ተጠቅልለዋል፤ ይህም ትእዛዝ በመጀመሪያ በሕግ ውስጥ መጻፉን መርሳት አይገባንም፤ ዘሌ. 19÷18። ሐዋርያው ደግሞ «ከሌላዪቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር» በማለቱ ብዙ ትእዛዛት እንዳሉ ያሳስበናልና ሁሉ የተጻፉት ለእኛ መመሪያ እንዲሆኑ ነው።

ከዐሠርቱ ቃላት የመጀመሪያዎቹ አምስቱ ትእዛዛት ደግሞ በአዲስ ኪዳን እንደሚከበሩ በልዩ ልዩ አንቀጾች ውስጥ እናያለን (2)። ለምሳሌ÷ 5ኛው ትእዛዝ ልጆች ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ ይናገራል፤ ኤፌ. 6÷1-3። 1ኛ÷ 2ኛና 3ኛ ትእዛዛት ለብዙ አንቀጾች መሠረታውያን ናቸው፤ ለምሳሌ÷ ሮም 1÷21-30፤ 2÷22፤ 1ቆሮ. 6÷9፤ ኤፌ. 5÷5፤ ቆላ. 3÷5፤ ያዕ. 2÷7:19፤ ራእ. 21÷8 ይመ.። ወንጌል በአሕዛብ መካከል ሲሰበክና ምእመናን በአኗኗራቸው ምክንያት እንደፈለጉ መሰብሰብ ባለመቻላቸው÷ የ4ኛውን ትእዛዝ ዋና መንፈስ «በጌታ ቀን» እንደጠበቁ ማየት እንችላለን፤ ኢሳ. 58÷13፤ ሐ.ሥ. 20÷7፤ 1ቆሮ. 16÷2፤ ራእ. 1÷10። እንግዲህ ፍቅርን ከሕግ ጋር በቀጥታ ማዛመድ እንዳለብን እንረዳለን።

በዚህ አንቀጽ ስለ ጽድቅ መንገድ ለመግለጥ በማሰብ ላይ አይደለንም፤ ይህን በምዕራፍ 89 በሰፊው አትተናል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሰው በእምነት ከጸደቀ ጻድቅ ሆኖ በቅድስና መኖር ይጀምራል፤ በዚህም ንኡስ አንቀጽ የእግዚአብሔር ትእዛዛት በቅድስና እንድንኖር እንደሚያደርጉ ከሦስቱ ታላላቅ ምክንያቶች አንዱን በማሰብ ላይ ነን።

### 3. እውነተኛ ፍቅር የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለማቃለል ሙንሥኢ አይሆንም

አንዳንዶች ግን ፍቅር ብቻ ያስፈልገናል በማለታቸው ይህን ሐቅ ይቃወማሉ። ክርስቶስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ከፍ ያለ ስፍራ ሲሰጡና ፍቅርን ከትእዛዛት ጋር ሲያዛምዱት አይተናል። እንግዲህ ፍቅር ብቻ ያስፈልገናል የሚለው አስተሳሰብ ስሕተት ምንድን ነው?

እውነተኛ ፍቅር ስሜትና ትልቅ ምኞት ብቻ አይደለም። ያለ ፍቅር ሕጉንና ትእዛዛቱን መጠበቅ የሰውን ሕይወት ያደርቃልና ከባድ ሸክም ነው፤ ማቴ. 11÷28፤ ሐ.ሥ. 15÷10። ሰው ክርስቶስን መውደድ ሲጀምር ግን÷ ፈቃዱን ማድረግና ትእዛዛቱን መፈጸም ትልቅ ደስታ ይሰጠዋል፤ ይህም

እውነተኛ ዐርነት ነው፤ ማቴ. 11÷29-30፤ ዮሐ. 8÷32፤ 15÷10-11:: እውነተኛ ፍቅር በሥራ ላይ መዋል አለበትና ምእመናን ፍቅራቸው እውነተኛ መሆኑን የሚያውቁት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሲፈጽሙ ነው፤ አለበለዚያ ስሜታቸውና ምኞታቸው ወደ ክፋት ሊመራቸው ይችላል:: «ሕጉ ቅዱስ ነው፤ ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት» (ሮም 7÷12) ስለዚህ አማኙ ሊደሰትባቸው ይገባዋል፤ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ይሆናል:: ትእዛዛቱ እንግዲህ እውነተኛ ፍቅር ምን እንደሆነ እናስተውል ዘንድ ይረዱናል::

«ፍቅር ብቻ ያስፈልገናል» የሚለው አባባል ኀጢአትንና ክፋትን ለመሸፈን ሊያገለግል ይችላል:: ለምሳሌ÷ «አታመንዝር» የሚለው ትእዛዝ ከጋብቻ ውጭ ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙ ሰዎች ኅሊናቸው እንዳይወቅሣቸው «ፍቅር ብቻ ያስፈልገናል» የሚለውን አባባል እየጠቀሱ ያለ ቅድስና ሊመላለሱ ይችላሉ:: እውነተኛ ፍቅር ምን እንደሆነ አያውቁም፤ እነርሱ እግዚአብሔር ሕጉንና ግብረ ገባውያት ትእዛዛቱን ለሰው ሁሉ መስጠቱን ይክዳሉ:: ፍቅር አለን፤ ወይም እግዚአብሔር ይህን የፍቅር ስሜትና ምኞት ስለሰጠን÷ እርስ በርሳችን ልንፈጽመው ይገባናል ይላሉ:: ከዚህም በላይ ሁለት ክርስቲያን ወንዶች ወይም ሴቶች ፍጹም ሕገ ወጥ ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግና በዚያም ሁኔታ መኖር እንደሚችሉ ያምናሉ:: ከጋብቻ ውጭ የሚደረገውን ወሲባዊ ግንኙነት በሚመለከትም የእውነተኛ ፍቅርና የሥጋ ምኞት ወሰን የት ድረስ እንደሆነ ይገልጣሉ:: ክርስቶስ÷ «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ÷ ትወደኛለህን?» በማለት ሦስት ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስን በማሳዘን በተናገረው በአገልግሎትና በቅድስና አኗኗር ውስጥ ፍቅር ያለውን ታላቅ ስፍራ አሳየ (ዮሐ. 21÷17)፤ ሆኖም የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ሁሉ በአንድነት መመልከትና መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ይህ የስሕተት አስተሳሰብና ሌሎች ተመሳሳይ ትምህርቶች ያሳዩናል::

## 4. የክርስቶስ አርኣያ

ክርስቶስ «ከሕግ በታች» (ገላ. 4÷4) በመወለዱና የሕጉን ትእዛዛት ሁሉ በመፈጸሙ÷ እንደዚሁም ምእመናን ሁሉ «የልጁን መልክ እንዲመስሉ» (ሮም 8÷29) ከዘለዓለም የአብ ውሳኔ በመሆኑ÷ በክርስቶስ አርኣያ ሕጉን መፈጸም ለቅድስና ታላቅ ምክንያት ሆኖ መቈጠሩ አያስገርምም:: ስለዚህ ክርስቶስ÷ «እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ÷ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ» (ዮሐ. 13÷15)፤ ጳውሎስም÷ «በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን» (ፊል. 2÷5)፤ ጴጥሮስም÷ «ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏል» (1ጴጥ. 2÷21) ብለው ተናገሩ (3)::

በቅድስና የክርስቶስ አርኣያ ዋና ዓላማ አማኙ ከክብር ወደ ክብር ሲያድግ÷ ወደ እግዚአብሔር ክብር የሚያደርስ በመሆኑ ላይ ያተኵራል፤ 2ቆሮ. 3÷18:: ይህን እንድናስተውል የሚከተሉት ጥቅሶች ሊረዱን ይችላሉ:-

- «በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም (ማለት የመጨረሻ መከበራችን) ተስፋ እንመካለን»፤ ሮም 5÷2::

- «... ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ...»፤ ፊል. 1÷9-11::

- «ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና...»፤ 1ተሰ. 2÷11-12::

- «በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘለዓለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ... ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፤ ያጸናችሁማል፤ ያበረታችሁማል»፤ 1ጴጥ. 5÷10::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅድስና የሚሰጠውን ዋና ትምህርት በሚከተሉት ሰባት አርእስት በዐጭሩ አቅርበነዋል:- ሀ) የቅድስና ዐውድ÷ ለ) ቅድስና በሮም መልእክት ምዕራፍ 6-8÷ ሐ) ቅድስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ÷ መ) ቅድስና በዚህ ዓለም ፍጹም አለመሆኑ÷ ሠ) ቅድስና በአማኙ ሕይወት እያደገ መሄዱ÷ ረ) ቅድስና በአማኙ አኗኗር በሦስት ደረጃዎች የሚገለጥ መሆኑ÷ ሰ) የነፍስ ፍጹም ቅድስና÷ ሸ) የሥጋ ፍጹም ቅድስና::

## ሀ) የቅድስና ዐውድ

### 1. የጋርዮሽ ጸጋ

የሕይወት ሁሉ ዐውድ የጋርዮሽ ጸጋ ነውና አማኙ በቅድስና ሲኖር በጋርዮሽ ጸጋ ይከበባል:: ከጋርዮሽ ጸጋ የተነሣ በየአገሩና በየአካባቢው ያለው የትምህርትና የሳይንስ ደረጃ÷ የአስተዳደር ዐይነትና አፈጻጸም÷ የኀጢአት መገታት የተለያየ ነው:: ይህን ስንል እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን ለልባቸው ክፋትና ግፍ አሳልፎ የሚሰጣቸው መሆኑን÷ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሁሉንም በአንድነት የማይገታቸው መሆኑን አንረሳም፤ ሮም 1÷22-32::

ሰው ሲያምን÷ አንዳንድ ነገር ወዲያውኑ ኀጢአት መሆኑን ቢያስተውልም÷ በአካባቢው ብዙ ዐይነት አሳብ÷ አስተሳሰብና ድርጊት በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ እንደሆነ አያስተውልምና የእግዚአብሔርን ቃል በይበልጥ እስኪማር ድረስ እነዚህ ነገሮች ከቅድስና ኑሮ ጋር የማይስማሙ መሆኑን አይረዳም:: ለምሳሌ÷ በብዙ ሕዝብ ባህል በቀል÷ ትዕቢት÷ ውሸት÷ የሰውን ክብር መዳፈር... ወዘተ የተለመዱ ናቸው:: ከዚህም ጋር በብዙ አገር ለክርስቲያን ብዙ ነጻነት የለውምና በጌታ ቀን ማረፍና በግልጥ ከሌሎች ምእመናን ጋር መሰብሰብ የማይቻል በመሆኑ የቅድስና ኑሮ ውሱን ይሆናል::

### 2. ጽድቅ

በምዕራፍ 89 እንዳየነው የቅድስና አኗኗር በአማኙ የጽድቅ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው:: አማኙ በክርስቶስ ጻድቅ ነው፤ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ተቀባይነት አለው፤ የእግዚአብሔርም ውድ ልጅ ነው:: በክርስቶስ በመሆኑ ደግሞ የደረጃ ቅድስና ስላለው÷ ምእመናን ሁሉ ቅዱሳን ተብለዋል:: ይህን ልብ ማድረግ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት÷ ሰው በቀላሉ በራሱ ጽድቅ መሳተፍ ስለሚፈልግ ነው:: ይህ ሲሆን ደግሞ ስለ ቅድስና ያለው አመለካከት እጅግ የተሳሳተ ይሆናል፤ ምክንያቱም አማኙ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ እግዚአብሔርን ማገልገሉ እግዚአብሔር እንዲቀበለው አይደለም፤ ወይም እንዲጸድቅ ወይም ከቅጣትና ከኵነኔ እንዲያመልጥ አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች ሰው እንዲታዘዝ ይህ ዐይነቱ ፍርሀት መኖሩ አስፈላጊ ነው ይላሉ:: ተሳስተዋል፤ ምክንያቱም ከፍርሀት ይልቅ የፍቅር ኀይል ይበልጣል፤ «ፍጹም ፍቅር ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሀት የለም፤ ፍርሀት ቅጣት አለውና የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም» ተብሏል፤ 1ዮሐ. 4÷18::

### 3. ዳግመኛ መወለድ

ሰው በክርስቶስ ሲሆን ዳግመኛ ተወልዷልና የሕይወቱ ሁኔታና አኗኗር ተለውጧል:: አማኙ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁኔታ ማስተዋል ይጀምራልና ወደ መንግሥቱ ይገባል (ዮሐ. 3÷3:5)፤ ጽድቅን ያደርጋል (1ዮሐ. 2÷29)፤

ኀጢአትን አያደርግም (1ዮሐ. 3፥9፤ 5፥18)፤ ምእመናንን ይወዳል (1ዮሐ. 4፥7)፤ በኢየሱስ ያምናል (1ዮሐ. 5፥1)፤ ዓለምን ያሸንፋል፤ 1ዮሐ. 5፥4:: አማኙ በዚህ ዓለም ሳለ ይህን ሁሉ ባይፈጽም፥ እነዚህ ጠባያት የሕይወቱን አጠቃላይ ሁኔታ ያመለክታሉ::

ሰው ዳግመኛ ከመወለዱ በፊት እንደ ሥጋ ፈቃድ ይመላለሳል፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ይኖራል፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ያስባል፤ ይህ በእግዚአብሔር ፊት ጥል ነበረ፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አልተገዛም፤ መገዛትም ተስኖታልና በመጨረሻ የደረሰበት ሞት ነበረ፤ ሮም 8፥3-8:: በዚህም አመለካከት ዓለምና ሰይጣን ሥጋዊ አኗኗር ካለው ሰው ጋር ስለሚተባበሩ ክርስቶስንና ወንጌሉን ይጠላሉ፤ ኤፌ. 2፥1-3::

እግዚአብሔር፥ «ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም እርሱንም የኀጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን» በሚለው ቃል መሠረት የአማኙን መንግሥት ቀይሮታልና ዳግመኛ የተወለደው ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሁን መፈጸም ይፈልጋል፤ ቆላ. 1፥13-14:: በቅድስና ኑሮ የፈቃድ ለውጥ እንደሚመጣ የሚከተለው ጥቅስ ይገልጣል:- «... በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና»፤ ፊል. 2፥12-13:፤ እንግዲህ በመጀመሪያ አማኙ የእግዚአብሔርን በጎ ፈቃድ እንዲያደርግ እግዚአብሔር በልቡ ይሠራል፤ ቀጥሎም ያን ፈቃድ ለመፈጸም ኀይልን ይሰጠዋል:: በሌላ አነጋገር የአማኙ አዲስ ፈቃድ ከእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ጋር አንድ በመሆን ይተባበራል:: ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ አገልግሎቱ ሲገልጥ፥ «ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኀይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ» በማለት በአንድ በኩል እግዚአብሔር በኀይል ሲሠራ፥ በሌላ በኩል እርሱ እንደ እግዚአብሔር አመራርና አሠራር ታላቅ ተጋድሎ አድርጎ እንደደከመ አስገንዝቧል፤ ቆላ. 1፥29:: እንግዲህ ከዚህ አሳብ የተነሣ የቅድስና አኗኗርና አገልግሎት ቀላል አይደሉም:: ምእመናን «በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ» እንደዚሁም እስኪደክሙ ድረስ በሙሉ ኀይላቸው በእግዚአብሔር መንገድ መራመድ አለባቸው፤ ይህም እውን የሚሆነው በራሳቸው ተፈጥሮታዊ ኀይል ሳይሆን እግዚአብሔር በሚሰጣቸው ኀይልና አሠራር ነው::

ከዚህ በላይ በአካባቢው ሁኔታና በሥጋ ተጽዕኖ ምክንያት አማኙ የቅድስናን መንገድ ብዙ ጊዜ እንደማያስተውል አይተናል:: መንገዱን ቢያውቅም እንኳ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም አይፈልግምና የልቡ ፈቃድ እስኪለወጥለት ድረስ እግዚአብሔርን ይቃወመዋል:: ነገር ግን በመሠረቱ ዳግመኛ ስለተወለደና የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፥ በመጨረሻ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይቀበላልና በቅድስና መንገድ ከቀድሞው በበለጠ ደስታ ይራመዳል፤ እግዚአብሔር «... መፈለግንም» ይሠራልና::

#### 4. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

የእግዚአብሔር ፈቃድ የምእመናን መቀደስ ነውና (1ተሰ. 4፥3) አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሥራ ይሳተፋሉ፤ 1ተሰ. 5፥23-24:: አብ ልጆቹን በቅድስና እንዲካፈሉ በአባታዊ ተግሣጽ ይቀጣቸዋል (ዕብ. 12፥10)፤ በወልድም በኩል ምእመናን ደስ በሚያሰኘውና በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን እንዲሆኑ ይሠራል (ዕብ. 13፥20-21)፤ ምክንያቱም ክርስቶስ በተመላለሰበት አኳኋን ምእመናን ሊመላለሱ ይገባል፤ 1ዮሐ. 2፥6:: ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ

የቅድስና መንፈስ በመሆኑ (ሮም 1፥3-4)፥ ምእመናን በመንፈስ ይቀደሳሉ፤ 2ተሰ. 2፥13፤ 1ጴጥ. 1፥1-2:: ይህ ሥራ ታላቅ ነው፤ «ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ፤ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፤ ያለ እርሱ (ቅድስና) ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» የሚለው ማስጠንቀቂያ ተጽፏልና፤ ዕብ. 12፥14::

መንፈስ ቅዱስ የቅድስና ሥራ ሲሠራ፥ «ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት» የተባሉትን መልካም ጠባያት በምእመናን ሕይወት ውስጥ ያፈራል፤ ገላ. 5፥22:: ምእመናን በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መሠረት መመላለስ፥ መኖርና ማሰብ ይገባቸዋል (ሮም 8፥3-6)፤ እንደዚሁም በእርሱ ይመራሉ፤ 8፥14:: በሐዋርያት ሥራ መንፈስ ቅዱስ ምእመናንን ሲመራቸው በልዩ ልዩ ታሪክ ይታያል፤ ሐ.ሥ. 8፥29:39፤ 10፥19-20፤ 11፥12፤ 13፥2፤ 15፥28፤ 16፥6-7::

## ለ) ቅድስና በሮም መልእክት ምዕራፍ 6-8

የሮም መልእክት አከፋፈል ብዙ ዐይነት ቢሆንም (4)፥ መግቢያ (1፥1-17)፥ እግዚአብሔር ሰውን በቀጣ ኵነኔ (1፥18-3፥20)፤ እግዚአብሔር ሰውን በጸጋ አጸደቀው (3፥21-7፥25)፤ እግዚአብሔር ሰውን በፍቅር አከበረው (8፥1-39)፤ እግዚአብሔር ሰውን በምሕረት መረጠው (9፥1-11፥36)፤ እግዚአብሔር በልዕልናው ሰውን አደፋፈረው (12፥1-15፥13)፤ መደምደሚያ (15፥14-16፥27) የሚለው የአከፋፈል ዐይነት ሊረዳን ይችላል:: የሮም ምዕራፍ 6 ዋና አሳብ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከሕግ ሥልጣን ይፈታልና የምዕራፍ 8 ደግሞ አማኝ ከኵነኔ ወጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በአዲስ ሕይወት ይኖራል (8፥1-17)፤ የማይጠፋውም ተስፋ ሲኖረው አማኙ በአለኝታ መበረታታት ይገባዋል (8፥1-39) የሚሉት ናቸው ማለት ይቻላል:: ቅድስና እነዚህ ምዕራፎች የሚያተኵሩበት ዋና ትምህርት ባይሆንም፥ በዋናው ትምህርት ዐውድ ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ ተገንዝበን ስለ ቅድስና ብዙ መሠረታዊ ትምህርት ማግኘት እንችላለን::

### 1. ቅድስና በሮም ምዕራፍ 6

ድኅነት በክርስቶስ ነውና ይህን በሞቱ፥ በትንሣኤውና በክብሩ ልንመረምረው እንችላለን:: ከክርስቶስ ጋር ምእመናን ያላቸው አንድነት በአካላዊ (በሥጋዊ) ሁኔታ የሚታይ ሳይሆን (2ቆሮ. 5፥17) በመንፈሳዊ ሁኔታ የሚገለጥ ታላቅ ምሥጢር ነው፤ ለምሳሌ፥ አማኞች በቀራንዮ መስቀል ላይ ከክርስቶስ ጋር በአካላዊ ሁኔታ አልነበሩም፤ አሁንም በዚሁ ሁኔታ በመንግሥተ ሰማያት አይኖሩም::

#### ሀ) የአማኙ አንድነት በክርስቶስ ሞት (6፥1-11)

በሮም 6፥1-11 አማኙ «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?» (ቊ. 3)፤ «... ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» (ቊ. 4)፤ «ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን...» (ቊ. 5)፤ «አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን» (ቊ.6)፤ «ከክርስቶስ ጋር ከሞትን...» (ቊ. 7-8)፤ «... እናንተ ደግሞ ለኀጢአት እንደሞታችሁ፥... ቊጠሩ» (ቊ. 11) በሚሉት ጥቅሶች ሐዋርያው ምእመናን ከክርስቶስ ጋር በመሞታቸው ላይ ያተኵራል:: «ቊጠሩ» ያለውም የምእመናንን እውነተኛ ሁኔታ የሚያሳይ እንጂ ማስመሰል ያለበት መሆኑን የሚገልጥ አይደለም::

አማኞች ከክርስቶስ ጋር በመሞታቸውና በሞቱ በመተባበራቸው (ቊ. 5) ለኀጢአት ሞተዋል (ቊ. 2:11)፤ ምክንያቱም ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለኀጢአት ፈጽሞ በመሞቱ ሁለተኛ አይሞትም (ቊ. 9-10)። ሐዋርያው÷ «ለኀጢአት የሞትን» (ቊ. 2) ሲል ምን ማለቱ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ለኀጢአት ካልሞትን በክርስቶስ መኖር አንችልም (ቊ. 2)። በዚህ አንቀጽ አራት አሳቦች ያሉ ይመስላል፤ እነርሱም የተቀራረበ ግንኙነት ያላቸው ሲሆኑ÷ ሁሉም ቅድስናን የሚያመለክቱ ናቸው፤ አራቱ በተለይ በክርስቶስ ሞትና በክርስቶስ ትንሣኤ ይታያሉ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው (5):-

1) ፍትሓዊ አሳብ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለምእመናን ሲሞት÷ እነርሱ ደግሞ በእግዚአብሔር ዐይን ለኀጢአት ሞቱ፤ ኀጢአታቸው በክርስቶስ መሥዋዕት ተደምስሶላቸዋል፤ እነርሱ ጸድቀዋል፤ በእነርሱ ላይ የነበረ የኀጢአትና የሕግ ኀይል ፈረሰ። እንደዚሁም በክርስቶስ ትንሣኤ እነርሱ ተነሥተዋል፤ «ሞታችኋልና÷ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯል» በማለት ሐዋርያው ስለዚህ እውነት ጽፏል፤ ይህ የእግዚአብሔር ልዑላዊ ውሳኔ ነውና፤ ቆላ. 3÷3።

2) ጥምቀታዊ አሳብ፤ ጥምቀት የምእመናን ሁኔታ መግለጫ÷ ምስክር÷ ማኅተምና ማረጋገጫ ነው (ቊ. 3:4)። አማኙ በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ እንደሆነ÷ ለኀጢአት ኑሮ እንደሞተና አዲስ ሕይወት በክርስቶስ እንዳለው ይመሰክራል፤ ቊ. 3-5፤ ቆላ. 3÷1-4።

3) ግብረገባዊ አሳብ፤ ምእመናን ነጻነት ተሰጥቷቸዋልና በየዕለቱ ኀጢአታዊ ጠባያቸውን እየገደሉ (ሮም 8÷13) ለኀጢአት ለመሞትና በየዕለቱ ለእግዚአብሔር እየታዘዙ በአዲስ ሕይወት ለመኖር ተጠርተዋል። ወንጌልንም የተረዱ በሙሉ ኀይላቸውና በአኗኗራቸው እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደሚመለከታቸው እያሰቡ የመኖር ዕዳ አለባቸው።

4) ሰማያዊ አሳብ፤ ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ሲመጣና ሙታን ሲነሡ ከክርስቶስ ጋር በክብር ይኖራሉ፤ ምንም ኀጢአት አይኖርባቸውም፤ ፍጹማንም ይሆናሉ።

እነዚህ አራት አሳቦች የተለያዩ ቢሆኑም እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው፤ አራቱም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የምእመናንን አኗኗር ይገልጣሉ። ሐዋርያው «አሮጌው ሰዋችን» ሲል (ቊ. 6) አማኙ ከማመኑ በፊት እንዴት እንደነበረ ያመለክታል፤ አማኙም ለኀጢአት ይገዛ ነበርና የኀጢአት ሥጋ በአዲሱ ሰዋችን ላይ እንዳይገዛ እርሱ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ ስለ ሞተ ራሱን እንደ ሞተ መቊጠር አለበት። እኛም በዚህ ዓለም ፍጹማን ባለመሆናችን÷ «ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፤ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፤ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ» ተብለን ታዝዘናል፤ ኤፌ. 4÷22-24። አንድ ሰው ከማመኑ በፊትና ካመነ በኋላ ያው አንድ ሰው ነው፤ ሆኖም አሮጌው ሰው አዲስ ሰው እየሆነና እየተለወጠ ይሄዳልና «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ÷ ሁሉም አዲስ ሆኗል» (2ቆሮ. 5÷17)፤ እና÷ «እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» የሚሉት ጥቅሶች የቅድስና ሥራ የእግዚአብሔር መሆኑን ያሳያሉ፤ ኤፌ. 2÷10።

ለ) የአማኙ አንድነት በክርስቶስ ትንሣኤ (ሮም 6፥1-11)

በአሉታዊ መንገድ የቅድስና መጀመሪያ ርምጃ ለኀጢአት መሞት ነው:: አንዳንድ ሰዎች የኀጢአተኛነት ስሜት ሲሰማቸው፥ ኀጢአታቸውን ለመግታት ከመብልና ከመጠጥ እንደዚሁም ፍላጎታቸውን ከሚያረካ ነገር ሁሉ ይሸሻሉ፤ ሌሎችም ከኀጢአታቸው ለማምለጥ ወደ ገዳም ሊገቡ ወይም ባህታውያን እንኳ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ ሁሉ ግን ሙሉ በሙሉ አይሠራም፤ ምክንያቱም ኀጢአት ያለው በልብ ውስጥ ነውና የትም ቢሄዱና ማናቸውንም ነገር ቢያደርጉ ልባቸው ከእነርሱ ጋር ይሄዳል፤ ሰይጣንም በልዩ ልዩ መንገድ ሊፈትናቸው ይችላል::

በአዎንታዊ መንገድ የቅድስና ሁለተኛ ርምጃ አማኙ ከክርስቶስ ጋር በትንሣኤው መኖሩን (ቊ. 2)፥ ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ከእርሱ ጋር መተባበሩን (ቊ. 5)፥ በሕይወት መኖሩን (ቊ. 7-8)፥ እንደዚሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታው ሆኖ ለእግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ ራሱን መቊጠሩን (ቊ. 11) የሚመለከት ነው:: ይህ ሁኔታ እውነተኛ መሆኑን እንጂ ማስመሰል አለመሆኑን እንደገና ልብ ማድረግ አለብን::

ሐ) የአማኙ አንድነት በክርስቶስ ክብር

በክብር ከክርስቶስ ጋር መሆን መፈጸሙ የማይቀር የአማኙ ታላቅ ተስፋ ነው፤ ሮም 5፥2፤ 8፥21:30:: እዚያም የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱ መቀደሱ ይፈጸማል፤ 1ተሰ. 4፥3:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን እንድናይና በእርሱ አንድ እንድንሆን ከመሰቀሉ በፊት ጸለየ (ዮሐ. 17፥22-24)፤ ጸሎቱ የጌታችን ጸሎት በመሆኑ ይፈጸማል (6):: አሁንም በዚህ ዓለም አማኙ የክርስቶስን መልክ መምሰል ይጀምራልና ከክብር ወደ ክብር ይለወጣል፤ 2ቆሮ. 3፥18::

በሮም 6፥12-23 አማኙ በሁኔታው መሠረት እንዲኖር ሐዋርያው ልዩ ልዩ ምክርና ምክንያታዊ አሳብ ያቀርባል::

አንደኛ፥ በቊ. 12-14 ሐዋርያው «... በሚሞት ሥጋችሁ ኀጢአት አይንገሥ» በሚል ትእዛዝ አሳቡን ሲከፍት፥ «ኀጢአት አይገዛችሁም...» የሚለውን ታላቅ ተስፋ ይሰጣል:: በዚህ ምዕራፍ «ሥጋ» ሲል ሰው ከአዳም የወረሰው ኀጢአት ሁለንተናውን እንደሚገዛ እንጂ ከሰው አካል ያልሆነ ዐጥንትን አያመለክትም:: እንግዲህ ከዚህ አንቀጽ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ትግል እንዳለ፥ ኀጢአትም በሙሉ ወይም በከፊል ሊገዛው እንደሚችል እንረዳለን፤ ሆኖም አማኙ በክርስቶስ በመሆኑ ኀጢአት በመጨረሻ አይገዛውም:: አማኙ ለጊዜው በሁለት መንገዶች በ«ብልቶቹ» ሊጠቀም ይችላል፤ የዓመፃ ጦር ዕቃ ወይም የጽድቅ ጦር ዕቃ አድርጎ ሊገለገልባቸው ይችል ይሆናል፤ ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን ኀጢአት እንደማይገዛው ዐውቆ ለቅድስና ኑሮ ራሱን ማቅረብ አለበት::

ሁለተኛ፥ በቊ. 15-19 አማኙ ሁለንተናውን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብ፥ ለኀጢአት ባርነትና ለሞት ወይም ሊቀደስ እውነተኛ ዐርነት ለሚሆን የመታዘዝ ባርነት ራሱን ማቅረብ መቻሉ ይታያል:: ሰው በተለመደ አነጋገር ሁለት መንገዶች ብቻ አሉት፤ ሆኖም አማኞች በማመናቸው የጽድቅን መንገድ ብቻ መርጠዋልና ብልቶቻቸው እንዲቀደሱ ለጽድቅ ባሪያ አድርገው አሁን እንዲያቀርቡ ታዝዘዋል::

ሦስተኛ፥ በቊ. 20-23 ሁለት ዐይነት ፍሬ ብቻ እንዳለ ተገልጧል:: አማኙ በፊተኛው አኗኗሩ ያፍራል፤ ይህ አኗኗር ምንም ጥቅም አልነበረውም፤

ፍጻሜው ሞት ነው። ከኀጢአት ባርነት ዐርነት ሲወጣ ግን ለእግዚአብሔር እየተገዛ ሲቀደስ ፍሬ አለው፤ መጨረሻውም የዘለዓለም ሕይወት ነው። ምክንያቱም፥ «የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘለዓለም ሕይወት ነው»፤ ሮም 6፥23።

**2. ቅድስና በሮም ምዕራፍ 7**

ስለ ሮም ምዕራፍ 7 የተለያየ አተረጓጐም አለ፤ ለዚህም ዋና ምክንያቱ በምዕራፍ 7 እና በምዕራፍ 8 አሳብ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ መሆኑ ነው። ለምሳሌ፥ በምዕራፍ 7 መጨረሻ ላይ ሐዋርያው «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ፤ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ብሎ በሐዘን ስሜት ሲጽፍ (ቊ. 24)፥ በምዕራፍ 8 መጨረሻ ላይ ደግሞ፥ «... ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ቊ. 39) ብሏል።

ከዚህ የተነሣ አንዳንዶች ሮም ምዕራፍ 7 የምእመናንን ሁኔታ አያመለክትም፤ ሌሎችም ምዕራፉ ደካማ ምእመናንን ያመለክታልና ምእመናን ከምዕራፍ 7 ሁኔታ ወደ ምዕራፍ 8 ሁኔታ በፍጥነት ሊሸጋገሩ ይገባል፤ የተወሰኑትም ሁለቱ ምዕራፎች በተለያየ ጊዜ የነበረን የምእመናን ሁኔታና ተመክሮ ያመለክታሉ፤ የቀሩት ደግሞ ሮም 7፥5-13 በኀላፊ ጊዜ ግስ ስለ ተጻፈ ከማመኑ በፊት ጳውሎስ የነበረውን ተመክሮ የሚተርክ ሲሆን፥ ሮም 7፥14-25 ደግሞ በአሁን ጊዜ ግስ በተለይም፥ «እኔ ግን ከኀጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ» (ቊ. 14) ስለሚል፥ ካመነ በኋላ የነበረውን ተመክሮ እንደሚገልጥ ያስባሉ።

የሮም 7 ዋና አሳብ ሕጉ፥ «ቅዱስ ነው፤ ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት፥ በጎም ናት» (ቊ. 12) የሚለው ቢሆንም፥ አማኙ ከሕግ ሥልጣን በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድሏል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንዲያፈራ ለሌላው (ለክርስቶስ)፥ ከሙታን ለተነሣው አንድ እንዲሆንና (ቊ. 4) እንዲድን የተደረገው ሕጉን በመፈጸም አይደለም፤ በተለይ ቊ. 1-12 ይመ.።

ሰው በሥጋ ሳለ በሕግ የተቀሰቀሰው የኀጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ያፈራ ነበር (ቊ. 5)፤ ይህም ሰው ከማመኑ በፊት የነበረውን ሁኔታ ያመለክታል፤ ሆኖም፥ «በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና» (ቊ. 22) በማለቱ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት በውስጥ ሰውነቱና በአእምሮው (ቊ. 25) መፈለጉ የአማኝ ተመክሮና ሁኔታ ይመስላል። ችግሩ ግን፥ «በሥጋዬ ግን ለኀጢአት ሕግ እገዛለሁ» በማለቱ እንደ ኀጢአት ሕግ መኖር የሚያስችለው በሥጋ ያለው ኀይል ነበረ (ቊ. 25)። እንግዲያስ ይህ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ የምእመናን ሁሉ ስሜትና ተመክሮ ነው ወይስ የደካማ ክርስቲያኖች ዘወትራዊ ሁኔታ፥ ወይስ ደግሞ የማያምኑ ሰዎች ሁኔታ ነው? ሰው እንደ አተረጓጐሙ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ፥ ወደ ሮም ምዕራፍ 8 ኀይልና ደስታ በመግባትና ስለ ቅድስና ትምህርትም ወደዚሁ ምዕራፍ ሁኔታ በመሸገር እጅግ ሊለያይ ይችላል።

በዚህ ምዕራፍ ስለ ቅድስና ዋና ዋና ትምህርት የሚከተለውን ማለት እንችላለን:-

ሀ) ቅድስና፥ አማኙ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆኑ ላይ ተመሥርቷል፤ በተለይ ሥጋ በክርስቶስ ለሕግ ተገድሏል (ቊ. 4፡6)፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ

እንዲያፈራ ከሙታን ከተነሣው ጋር ታስሯልና ሞቷል (ቊ. 4፡6)፤ ከተስፋ ቢስነት ሊያድነው የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታው ነው (ቊ. 25)።

ለ) ቅድስና፥ አማኙ ከማመኑ በፊት በሥጋ ክፋት ቢስማማም፥ አሁን የሥጋን ሥራ አይፈልግም፤ ይሁን እንጂ ሊቈጣጠረው አይችልም፤ በተለይ አስቀድሞ በሕግ ትእዛዝ ተቀስቅሶ ለሞት ፍሬ እንኳ እያፈራ በብልቶቹ ይሠራ ነበር (ቊ. 5)፤ ካመነ በኋላ ከኀጢአት በታች የተሸጠ የሥጋ ነው (ቊ. 14)፤ በሥጋው በጎ ነገር የለምና በጎ ለማድረግ ቢፈልግም መልካም ለማድረግ ኀይል የለውም (ቊ. 18)።

ሐ) ቅድስና ትግልና ውጊያ፥ መቀዋወምም አለበት። ዐሥር ጊዜ በቊ. 15-25 ሐዋርያው ስለዚህ ሲናገር፥ «የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና» (ቊ. 15)፤ «ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም» (ቊ. 20)፤ «የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፤ በእኔ የሚኖር ኀጢአት ነው እንጂ» (ቊ. 20)፤ «በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፤ ነገር ግን ብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ (ሐቅ) ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኀጢአት ሕግ (ሐቅ) የሚማርከኝን ሌላ ሕግ (ሐቅ) አያለሁ» (ቊ. 23)፤ ይህ ዳግመኛ የተወለደ ሰው አስተያየት አይደለም፤ «እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኀጢአት ሕግ (ሐቅ) እገዛለሁ» ብሎ በትግሉ ክብደት በመጨነቁ፥ ምዕራፉን ሲደመድም (ቊ. 25)፥ «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ» (ቊ. 24) ማለቱ አያስገርምም። በተጨማሪም ሐዋርያው ስለዚህ ትግል ለገላትያ ሰዎች በዐጭሩ እንደሚከተለው አብራራ፤ «... በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋን ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ (በሰው መንፈስ ወይም በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ፥ በሁለቱም ሊሆን ይችላል) መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም» በማለት የገላትያን ምእመናን አስገንዝቧቸዋል፤ ገላ. 5፥17-18። ከዚያም በኋላ ትምህርቱ ግልጥ እንዲሆን ሐዋርያው 17 ዐይነት የሥጋ ሥራንና ይህንም የሚመስል የመንፈስ ፍሬ ከዘረዘረ በኋላ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም በማለት ጽፏል፤ ገላ. 5፥19-23።

ከዚህ ትግል ትምህርት ነጻ ለመሆንና ወደ ሮም ምዕራፍ 8 ሁኔታ ለመሸሽ ሰዎች ልዩ ልዩ አቋራጭ መንገድ መኖሩን ያሳያሉ። ሆኖም በሮም ምዕራፍ 7 ላይ ትምህርቱ ስለሚገኝ፥ አንዳንድ ጊዜ ምእመናን ወደዚህ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገቡ ክርስቲያናዊ ተመክሮ አለ፤ ሐዋርያው ራሱም ከዚህ ትግል አላመለጠም።

### 3. ቅድስና በሮም ምዕራፍ 8

ትምህርተ መለኮትን በተመለከተ የሮም መልእክት ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲሆን፥ ሮም ምዕራፍ 8 ደግሞ በዚህ መልእክት ውስጥ ካሉት ምዕራፎች መካከል ዐይነተኛ ምዕራፍ ነው። የሮም ምዕራፍ 8 ዋና መልእክት፥ አማኝ ከባርነት ነጻ ወጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በአዲስ ሕይወት ይኖራል (8፥1-17)፤ የማይጠፋው ተስፋ ሲኖረውም፥ በዋስትናና በአለኝታ መበረታታት ይገባዋል የሚል ነው፤ 8፥18-39። በተጨማሪም በምዕራፍ 7 ላይ የተገለጠው ትግል እንዳይረሳ፥ «ከሥጋ የተነሣ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን... እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኀጢአትን በሥጋ ኰነነ» (ቊ. 3-4)፤ «ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው» (ቊ. 6) ስለሚል፥ ሁለት

መንገዶች (የሥጋና የመንፈስ) እንዳሉ (በተለይ ቊ. 1-8 እንደዚሁም ቊ. 9-11 ይመ.) ያሳስባል። አማኞች በመንፈስ ፈቃድ ይኖራሉና ሕይወት አላቸው።

ምዕራፉ ዐሥር ጊዜ ስለ ሥጋ፥ ዐሥር ጊዜ ደግሞ ስለ መንፈስ (ወይም መንፈስ ቅዱስ) ይጠቅሳል። ከዚህ ቀጥሎ ስለ ቅድስና ልዩ ልዩ አርእስትን እንመለከታለን።

ሀ) ቅድስናና ሥጋ፤ ቊ. 5-8 «ሥጋ» እና «መንፈስ» በማለት ሁለት መንገዶችን ይገልጣሉ፤ ሥጋና መንፈስ በአሳብም ሆነ በሥራ ምንም ግንኙነት የላቸውም፤ እርስ በርስ የሚቃረኑ ናቸውና። የእግዚአብሔር ዓላማ ምእመናን በቅድስና የክርስቶስን መልክ እንዲመስሉ (ቊ. 29) ነው፤ በዚህም ለሥጋ አሳብ ምንም ስፍራ የለም።

ለ) ቅድስናና መንፈስ፤ አማኙ በቅድስና እንዲራመድ መንፈስ ቅዱስ ኀይል ይሆነዋል፤ የራሱ መንፈስም መንፈስ ቅዱስን በደስታ ይከተላል፤ «እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ» (ቊ. 5)፤ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በአማኙ ዘንድ ይኖራልና እርሱ በሚኖረው መንፈስ ይሠራል (ቊ. 11)፤ በመጨረሻም ለሚሞተው የአማኝ ሰውነት (በትንሣኤ ዕለት) ሕይወትን ይሰጣል (ቊ. 11)። ይሁን እንጂ አሁን ከትግሉ መውጫ መንገድ ይኖራልን? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አዎ አለ የሚል ይሆናል። ሆኖም አሁን ፍጹም አይደለም፥ ትግልም ደግሞ አለበት፤ ምክንያቱም አማኙ በመንፈስ የሰውነትን ሥራ ቢገድል በሕይወት ይኖራል፤ በሥጋም ላይ አሸናፊ ይሆናል (ቊ. 13)፤ በዚህ መሠረት በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ (ቊ. 14) ይታወቃል።

ሐ) ቅድስናና ክብር፤ ለአማኙ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዓላማ በክርስቶስ ትንሣኤ እንዲከበር ነው (ቊ. 30፥ «አከበራቸው» ትንቢታዊ አነጋገር እንደሆነ ይታሰባል)። አማኙ የእግዚአብሔር ወራሽ እንዲሆን ከክርስቶስና ከሌሎች አማኞች ጋር ዐብሮ መከራ መቀበል አለበት (ቊ. 17)። ይህ ሌላው የቅድስናና የክርስቲያናዊ ኑሮ ሐቅ ነው፤ በአንድ በኩል መከራና ሥቃይ (ቊ. 18)፥ በሌላ በኩል ደግሞ በረከትና ክብር አለ። የአሁኑን ክብርና ሥቃይ ከሚመጣው ክብር ጋር ማመዛዘን አይቻልም (ቊ. 18)፤ ነገር ግን ሁለቱም ስለሚኖሩ አንዱ ወደ ሌላው መምራቱ አይቀርም፤ ስለዚህ አማኝ ከትግልና ከመከራ መሸሽ አይገባውም።

አስቀድሞ እንደተገለጠው፥ በክርስቶስ ሕይወት የሚኖር ሰው አሁን በክብሩ በመጠኑ ሊሳተፍ ይችላል፤ አማኙ በልዩ ልዩ ስጦታዎችና በመንፈስ ፍሬ በመሳተፉ ከበሰለ፥ በቅድስና ካደገ፥ ልዩ ጸጋና ጥበብ ይኖረዋል፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መልክም በይበልጥ በአካሄዱ ሊታይ ይችላል (2ቆሮ. 3፥18፤ 4፥1-18)። ፍጹም ክብር የሚገለጠው ግን በክርስቶስ ትንሣኤ ቀን ነው።

## ሐ) ቅድስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ብዙ ዐይነት የቅድስና ትምህርት መኖሩ አስገራሚ አይደለም፤ ለዚህም ቢያንስ አራት ምክንያቶች አሉ፦

ሀ) በልዩ ልዩ ትምህርት ቀደም ሲል እንዳየነው፥ ለዚህ ንኡስ ርእስ በመጽሐፍ ቅዱስ ከፍ ያለ ስፍራ እንደሚሰጥ ሰዎች ይረዳሉ፤ ለምሳሌ፥ «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌ. 19፥2፤ 1ጴጥ. 1፥15-16)፤ «ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና» (1ተሰ. 4፥3)፤ «ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ

ያስ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» የሚሉትና የመሳሰሉት ጥቅሶች ይህን እውነት በግልጥ ያሳያሉ፤ ዕብ. 12÷14::

ለ) እውነተኛ ክርስቲያን በክርስቶስ ድኅነትን አግኝቶ ለክርስቶስ እንደ ቅዱስ ሰው መኖር ይፈልጋል፤ ሆኖም ይህን ማድረግ እጅግ ከባድ መሆኑን ይገነዘባል፤ ሮም 7÷14-25፤ ገላ. 5÷17::

ሐ) እውነተኛ ክርስቲያን ወደ ድል ሕይወት ለመግባትና በዚያ ለመኖር ይጓጓል፤ የዚህን መንፈሳዊ ምሥጢር ጠቃሚነትና ርግጠኛነት ማወቅ ይችላል፤ ሮም 7÷24-25፤ ገላ. 5÷17-18::

መ) አንዳንድ ሰዎች የክርስትናን ምንነት ሲገነዘቡ÷ ከሚገባቸው ፍርድ ያመልጡ ዘንድ ቢያንስ ቢያንስ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ ይፈልጋሉ እንጂ ከዚህ ዐልፈው ምንም ነገር የማድረግ አሳብ የላቸውም:: ምናልባት እውነተኛ ክርስቲያን የሆነ ሰውም እንኳ በዚህ አሳዛኝ አስተሳሰብ ውስጥ ሊዘፈቅ ይችላል::

1. ቅድስና በምሥራቃውያን ዘንድ:- የመቃርዮስ ትምህርት

ከአውግስጢኖስ በፊት የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ቅድስና ብዙ አልጻፉም፤ ምክንያቱም ዋና ትኩረታቸውና ክርክራቸው በቅድስት ሥላሴና በትሥጉት አሳብ ላይ ነበረ:: በምሥራቃውያን ዘንድ በተለይ አንድ ዐይነት ትምህርት አደገ፤ ይህም ለመንፈሳዊ መሪዎች የሚሆን ግብረገባዊ ትምህርት ነበረ:: የዚህ ትምህርት ዋና ባለቤት ግብጻዊው መቃርዮስ እንደሆነ ቢነገርም÷ ይህ ሰው በአራተኛው መቶና በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ይኖር የነበረ ሦርያዊ መነኩሴ ነው (7):: ኤፍሬም ሰይረስ የዚህ ሰው ዋና ጓደኛ ነበረ::

የነመቃርዮስ አሳብ ሰው ኀጢአት የሌለበት ሕይወት እንዲኖረው የሚያስገነዝብ ሳይሆን÷ አጠቃላይ መንፈሳዊ የሕይወት ለውጥ እንዲታይበት የሚገፋፋ ነበረ:: መቃርዮስ ዐምሳ መንፈሳውያን ስብከቶችን ጽፏል:: በእነዚህ ስብከቶች የግል ተመክሮና በራሱ ሕይወት በልቡ ውስጥ የቀረ የራሱ ልምምድ ተገልጠዋል:: ይህ አቀራረብ ከፍጹም ቅድስና ትምህርት ጋር እንደሚስማማ ይታያል:: ከጊዜ በኋላ ዮሐንስ ወስሊ ይህን ትምህርት ከሌሎች ግሪካውያን አበው ትምህርት ጋር በማደባለቅ ስለ ልዩ ልዩ ሌላ ፍልስፍና አዳዲስ አሳብ ጨምሮ ስለ ፍጹም ቅድስና አስተማረ:: የመቃርዮስን ትምህርት ስንመለከት መነኩሴ በመሆኑ በትምህርቱ ሁለት ደረጃዎች መኖራቸውና÷ ይኸውም÷ መንፈሳዊ መሪዎችንና ተራ የቤተ ክርስቲያን አባሎችን እንደሚመለከት ልብ እናደርጋለን (8)::

2. ቅድስና በምዕራባውያን ዘንድ:- የአውግስጢኖስ ትምህርት

ነገረ መለኮትን በተመለከተ አውግስጢኖስ (354-430 ዓ.ም.) እና ትምህርቱ የሁለት ትምህርት ጥናት መነሻ ሆኑ:: በአንድ በኩል በተሐድሶ ጥናት መሠረት በሰው ድኅነት ላይ ለቀረበው የጸጋ ትምህርት በሕይወት ሳለ በፕሮቴስታንቶች መካከል መሪው÷ በኋላም በመጻሕፍቱ ዋና መልካም ተጽዕኖ ሆነ:: በሌላ በኩል ደግሞ በካቶሊኮች መካከል በቤተ ክርስቲያንና በምሥጢራቷ ስላለው የእግዚአብሔር ጸጋ የተሰጠው የእርሱ ትምህርት ዋና ምንጭና መሪ ሆነ:: ብዙ ሊቃውንት እርስ በርሳቸው ስለ አውግስጢኖስ ትምህት እየተከራከሩ መጻሕፍትን እስከ ዛሬ ድረስ ይጽፋሉ!

ቅድስናን የሚመለከተው ትምህርቱ ከፔላጊዮስ ጋር ከነበረው ክርክር መነጨ:: ፔላጊዮስ ሰው የሚድነው ከራሱ እንደሆነ አስተምሯል:: አውግስጢኖስ ይህን አሳብ በመቃወም፥ «እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገውን እምነትና ፍቅር ይሰጣል» ብሎ በግልጥ ተናገረ:: የአውግስጢኖስ ተከታዮች ግን በሕይወት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የአውግስጢኖስን ትምህርት በሙሉ መቀበል ስለከበዳቸው «ከፊል ፔላጊዮሳውያን» ተብለዋል (9)::

የተሐድሶን ትምህርት በተመለከተ የአውግስጢኖስን ትምህርት ግልጥ የሆነና ያልሆነ በማለት በሁለት አርእስት በዐጭሩ ልንገልጠው ብንሞክር ለግንዛቤ ሊረዳን ይችላል:-

ሀ) ግልጥ የሆነው የአውግስጢኖስ ትምህርት አርእስት

1) በሰው ድኅነት (እንደዚሁም በፍጥረትና በእግዚአብሔር መጋቢነት) እግዚአብሔር ልዕልና ያለው መሆኑን፥

2) በአዳም ውድቀት ሰው ሙሉ በሙሉ መሳተፉን፥

3) ያለ ጸጋ ሰው እግዚአብሔርን ማስደሰት አለመቻሉን (በሰው መልካም ሥራ ሁሉ በጸሎት እንኳ የኀጢአት ግብ፥ ዓላማ፥ ምኞት፥ ክፋት... ወዘተ ተደባልቆ ሊገኝ ይችላል)፥

4) ሰው በክርስቶስ ብቻ መዳን መቻሉን፥

5) እግዚአብሔር በምርጫውና በውሳኔው መሠረት ማዳኑን፥

6) «እግዚአብሔር ከሰው የሚፈልገውን እምነትና ፍቅር» መስጠቱን (10)::

እነዚህ ስድስት አንቀጾች ከብዙ ዓመታት በኋላም ቢሆን ለተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት እምነት (በተለይ ለፕረዝቢቴርያውያን አብያተ ክርስቲያናት) መሠረት ሆነዋል:: ከ1559-1566 ዓ.ም. በልዩ ልዩ አገሮች ያሉ የተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ አካሂደው ለየአገሮቻቸው የሃይማኖት መግለጫዎችን አዘጋጁ:: በ1619 ዓ.ም. ሆላንድ በሚገኘው በዶርት ከተማ የሃይማኖት መሪዎች ተሰብስበው በ«የዶርት ሲኖዶስ ቀኖናዎች» የጋራ እምነታቸው ተዘጋጅቶ በየአገሩ ተግባራዊ እንዲሆን ጸደቀ:: የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በ39 አንቀጾች (በ1562 እና በ1571 ዓ.ም.) እና በዌስትምንስተር የሃይማኖት መግለጫ (በ1647 ዓ.ም.፤ በአማርኛ «እምነታችን» ተብሎ ተተርጉሟል) እምነቷን ገለጠች:: ከዶርት ሲኖዶስም «የካልቪንዝም አምስት ነጥቦች» ደግሞ ተገኙ (11)::

ለ) ግልጥ ያልሆነው የአውግስጢኖስ ትምህርት አርእስት

ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ምሥጢራቷ እየተለመደ የመጣ ልዩ ልዩ ትምህርት ስፍራ አግኝቶ ነበርና አውግስጢኖስ የራሱን ትምህርት ለመወሰንና ለመግለጥ ግድ ሆነበት::

በዚያ ዘመን ሰው ይድን ዘንድ ግብረገባዊ ሕይወትን መኖር እንዳለበት ይታመን ነበር:: ሰው በእምነትና በመልካም ሥራ ተስፋ ማድረግ ነበረበት:: ከመጠመቁ በፊት ሰው የሠራው ኀጢአት በጥምቀት ሥርዐት እንደታጠበ ይታመን ነበር፤ ከተጠመቀ በኋላ ግን ለኀጢአቱ ቀኖናን መፈጸምና መልካም ሥራ ማድረግ ለሰው አስፈላጊ ነበረ:: በመልካም አኗኗር በጌታ ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ይችላል:: እንግዲህ ከዚህ በላይ በተገለጡ አሳቦች መሠረት የሰው ድኅነት ከክርስቶስ ቤዛነት እየወጣና እየራቀ ሄደ:: በዚህ ዐውድ ስለ ኀጢአት፥ ስለ ሕግና ስለ አከባበሩ፥ ስለ ክህነት ሥራ፥ ስለ ቤተ

ክርስቲያንና ስለ ምሥጢራቷ እንደዚሁም ስለ ምንኩስና ልዩ ልዩ የተሳሳቱ ትምህርቶች ተስፋፉ:: በዚህ ዘመን ኀጢአትን ለመግታት የተለያየ ሥርዐት በመደንገጉና በማደጉ ይህ ሁሉ ለቅድስና አስፈላጊ እንደሆነ ይቈጠር ነበር::

አውግስጢኖስ ስለ ቅድስና ማስተማር ሲጀምር÷ የሕዝብን ትኵረት ምን ያህል ስቦ እንደነበር ለማወቅ ቀላል አይደለም፤ ሆኖም በትምህርቱ የሚከተሉት አርእስት ከላይ ከተጠቀሱት ግልጥ ትምህርቶች ጋር የሚጋጩ እንደሆኑ መመልከት እንችላለን:-

1) በጽድቅና በቅድስና መካከል ያለ ግንኙነትና ልዩነት፤ አውግስጢኖስ በጽድቅና በቅድስና መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት በትክክል ለይቶ አላሳየም፤ እርሱ ትልቅ ትኵረት የሰጠው ለጽድቅ ነበረ፤ ቅድስና የጽድቅ አንድ ክፍል ነው፤ ሰው በቅድስና ሲኖር ጽድቁ ይጨምራል:: አውግስጢኖስ ጽድቅ ቋሚ ሁኔታ÷ ቅድስና ደግሞ የበጎ ሥራና የመልካም ጠባይ እድገት መሆናቸውን ለይቶ አላመለከተም::

2) በእግዚአብሔር ጸጋና በጽድቅ መካከል ያለ ግንኙነት፤ አውግስጢኖስ በአንድ በኩል የክርስቶስ ፍቅርና የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው መንፈሳዊ በረከት ሙሉ በሙሉ አስፈላጊ መሆናቸውን ባይረሳም÷ ቅድስና እንደ ተጨማሪ ስጦታ ይቈጠር ነበር:: የዚህ ስጦታ መልካም ሥራ÷ ፍሬ ቢስ ወይም ለሞት የሚያደርሱ ኀጢአቶችን ሊያጠፋ ይችላል፤ ሆኖም ከጥምቀት በኋላ ከኀጢአት የተገኘ ዕዳ ማለትም መጠነኛ ዐይነት ኀጢአት (የእግዚአብሔርን ጸጋ በከፊል የሚያስቀር) ቅዱስ ቍርባንን በመቀበልና ለከባድ ኀጢአት የቀኖናን ምሥጢር በመፈጸም ሊወገድ ይችላል (በኀጢአት መካከል ልዩነት ስለ መኖሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የት እንደሚገኝ መጠየቅ እንችላለን):: እነዚህን ሥራዎች ያለ እግዚአብሔር ጸጋ መፈጸም አይቻልም:: በአውግስጢኖስ የተዘራው ይህ ትምህርት÷ በተለይ በቶማስ አኩናስ ትምህርት (1225-1274 ዓ.ም.) እና በትሬንት ስብሰባ (1545-1563 ዓ.ም.) ውሳኔዎች ፍሬ አፍርቶ ታይቷል:: እንግዲህ በአንድ በኩል የአውግስጢኖስ የተሐድሶ ትምህርት ፍሬ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ የሚታይ ሲሆን÷ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ ቤተ ክርስቲያንንና ምሥጢራቷን በሚመለከት የትምህርቱ ጥቅም ካቶሊካውያንንም አዳርሷል:: ዋና ልዩነቱ በጽድቅና በቅድስና ትምህርት መካከል ያለው ነው (12)::

3) ቅድስና በተሐድሶ መሪዎች አመለካከት÷ የሉተር (1483-1546 ዓ.ም.) እና የካልቪን (1509-1564 ዓ.ም.) ትምህርት፤ ሉተርና ካልቪን የተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪዎች በመሆን መጽሐፍ ቅዱስን ሲመረምሩ÷ ትምህርቱ ግልጥ ከሆኑት ከአውግስጢኖስ ትምህርቶች ጋር አንድ ሆኖ አገኙት:: እነርሱ መሠረት አድርገው የተነሡት÷ በክርስቶስ ብቻ በማመን ጽድቅ ለአማኙ ይቈጠርለታል የሚለውን እውነት ነው:: ጽድቅ አቋም ወይም ሁኔታ እንጂ የሚጨመርበት ወይም የሚቀነስለት የለውም:: ቅድስና ግን ሰው በክርስቶስ በማመን ጸድቆ በመልካም ሥራና በጠባይ የሚያድግበት አኗኗር ነው፤ ቅድስና እየጨመረ የሚሄድ ቢሆንም÷ ፍጹም አይደለም:: ከዚህ በላይ እንዳተትነው የሉተርና የካልቪን ተከታዮች ሁሉ እምነት ይህን ይመስል ነበረና የአርሜኒዮሳውያን ተቃውሞ ሲነሣ÷ በዶርት ሲኖዶስ የተሐድሶ ትምህርት መመሪያ እንዲጸድቅ ተደረገ:: በፕሮቴስታንቶች ዘንድም እስከ ዛሬ ድረስ የተሐድሶ ትምህርት ተቀባይነትን አግኝቶ እንዳለ ይታያል::

ሉተርና ካልቪን ሰው ሊያድግ የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ እንደሆነ ዐወቁ፤ በተጨማሪም ሰው በራሱ ኀይልና ትግል የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሠራ

አለመቻሉን ተረዱ:: ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ ከደረሰበት የቅድስና ደረጃ መውደቅ እንደሚችልም ተገንዝበዋል፤ ምክንያቱም የአዳም ኀጢአት ገና በአማኙ ሕይወት ብዙ ኀይል አለው:: ለምሳሌ፥ ሙሴ በወጣትነቱ ጊዜ እግዚአብሔርን ሳይጠይቅ በራሱ ኀይል ሰው ገደለ፤ እግዚአብሔርም የአማቱን በጎች አርባ ዓመት በመጠበቅ ትሕትናንና የዋህነትን እንዲማር ወደ ምድረ በዳ ሰደደው:: «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው» ሆነ:: ቢሆንም፥ የእስራኤል ሕዝብ አርባ ዓመት ካስቸገሩት በኋላ፥ በመጨረሻ ሙሴ ተናደደ፤ ተቈጣቸውም:: በዚህ ምክንያት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ቅድስቲቱ አገር ለመግባት አልተፈቀደለትም፤ ዘጸ. 2፥12-15፤ ዘኁ. 12፥3፤ ዘዳ. 32፥48-52:: ዳዊትም ንጉሥ እንዲሆን ከእግዚአብሔር ብዙ ጸጋ ተቀብሎ ነበር፤ ነገር ግን በቤርሳቤህ ምክንያት ወደቀ፤ አመነዘረ፤ ውሸት ተናገረ፤ ሰውም አስገደለ:: ከዚህ የተነሣም በቤቱ ውስጥ በሕይወትም ሆነ ከሞት በኋላ ከባድ ፍርድ ተፈረደበት፤ 2ሳሙ. 11፥1-27፤ 12፥1-25:: ሰዎች በአዳም ኀጢአት ምክንያት የእግዚአብሔርን ብዙ ጸጋ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ብዙ ኀጢአት ሊገቡ ይችላሉና በተለይ መሪዎች መጠንቀቅ እንደሚያስፈልጋቸው ከአብያተ ክርስቲያናት ታሪክ መማር ይገባል፤ ለምሳሌ፥ 1ቆሮ. 1፥4-9 እና 10-17::

### 4. ቅድስናና የዮሐንስ ወስሊ ትምህርት (13)

ወስሊ (1703-1791 ዓ.ም.) ታላቅ የወንጌል ሰባኪ ሲሆን፥ በተለይ አዳዲስ ምእመናንን ለኅብረት፥ ለትምህርት፥ ለጸሎትና ለምስክርነት በቡድን በቡድን በማሠልጠን ረገድ ልዩ ስጦታ ነበረው:: ሆኖም ይህ ከትምህርተ መለኮት አንጻር የነበረበት ጒድለት እስከ ዛሬ ድረስ በተከታዮቹ ዘንድ ይንጸባረቃል::

ቅድስናን በተመለከተ ወስሊ አንድ አዲስ ዐይነት ትምህርት አስተማረ፤ ትምህርቱም፥ ሰው ለመዳን በክርስቶስ ካመነ በኋላ ወደ «ፍጹም ቅድስና» ደረጃ ሊደርስ ይችላል የሚል ነው:: በትምህርቱ መሠረት ሰው ወደዚህ ደረጃ የሚደርሰው በመጀመሪያ እንዳመነ ነው:: አማኙ ንስሐ ይገባል፤ በክርስቶስ ብቻ ተስፋ ያደርጋልና ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር ወደዚህ አዲስ ተመክሮው ያስገባዋል::

በአዲሱ ተመክሮ ውጤት (እንደ ትምህርቱ) ኀጢአት ሁሉ ከሰው ሕይወት ይወገዳልና ኀጢአትን ለመሥራት ፈተና አይደርስበትም፤ ምክንያቱም ለኀጢአት አዳማዊ ሱስ የለውም:: ከዚህም ቀጥሎ አዲስ መንፈሳዊ ሁኔታ ይፈጠርበታል፤ «ፍጹም ቅድስና» ተብሏልና በረከቱን ከተቀበለ በከፍተኛ ደረጃና ሁኔታ ላይ ይኖራል:: በዚህ አዲስ ሁኔታ ውስጥ እያደገና ወደ ክርስቶስ መልክ እየተለወጠ ይሄዳል::

እውነት ነው፤ ሰው ከትልቅ ድል በኋላ ወይም ትልቅ በረከትን ከተቀበለ በኋላ ሰይጣን «ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ» እንደሚለው ምቹ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ ከኢየሱስ ለጊዜው እንደተለየ ከሰው መለየት ይችላል፤ ሉቃ. 4፥13:: ዲያብሎስ ይህን ሲያደርግ፥ ሰውን ለዘለዓለም የሚተወው ሳይሆን፥ ምቹ ጊዜ ፈልጎ እንደገና በመመለስ የሚፈትነው መሆኑ ግልጥ ነው::

ወስሊ አስተዋይ የምእመናን እረኛ ነበረና ከራሱ ተመክሮ በመነሣት ሰይጣን ሰውን ኀጢአት እንዲሠራ ከመገፋፋት ለረጅም ጊዜ እንደማይቈጠብ ዐወቀ:: ምናልባት በዚህ ምክንያት እርሱ እንደዚህ ዐይነቱን አዲስ በረከት እንደተቀበለ አልተናገረም፤ ሆኖም፥ ዐልፎ ዐልፎ ስማቸውን የጠቀሳቸው ሌሎች

ሰዎች እንደተቀበሉትና ለድኅነት በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ይህን በረከት ይቀበሉ ዘንድ መከታተል እንደሚገባቸው አስተምሯል።

አስቀድሞ እንዳየነው ይህ ትምህርት «ፍጹም ቅድስና» አይደለም፤ ምክንያቱም ሰው በረከቱን ከተቀበለ በኋላ በቅድስና ያድጋል። በተጨማሪም እንደዚህ ዐይነቱ በረከት ስለ መኖሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም ፍንጭ የለም፤ ለዚህ አስተሳሰብ ድጋፍ በመስጠት ፈንታ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስተሳሰብ ይቃወማል፤ ሮም 7÷14-25፤ ገላ. 5÷16-17፤ 1ዮሐ. 1÷8-10።

## 5. ቅድስናና የከዚክ ትምህርት (14)

የከዚክ ትምህርት ከሙዲና ሰንኪ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ቀጥሎ በእንግሊዝ አገር በ1875 ዓ.ም. ተጀመረ። ከዚክ በሰሜን እንግሊዝ የምትገኝ በብዙ ሀይቅ የተከበበች ትንሽ ከተማ ናት፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በየዓመቱ በዚያ ስፍራ የሳምንት ስብሰባ ሲደረግ ቈይቷል፤ ከዚያም ትምህርቱ እጅግ እየተስፋፋ ሄዷል። ወስሊ ባስተማረው ትምህርት ፈንታ ስለ ቅድስና የተሰጠው የከዚክ ትምህርት ከሰው ሕይወት የውርስ ኀጢአት ሳይወገድ፥ ክርስቲያን ኀጢአትን በመቃወሙ አሸናፊ ሕይወት ሊኖረው ይችላል የሚል ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ተብሎ ሲጠየቅ፥ መልሱ በመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው የድል ኑሮ ነው። አንዳንዶችን ይህ ትእዛዝ በመጠኑ የሚረዳቸው ቢሆንም፥ ሌሎችን በፍጥነት ወደ ትርምስና ወደ ተስፋ መቍረጥ ይመራቸዋል፤ ውጤታማ ሆኖ አያገኙትምና። ይህ ምክር ከግብጻዊው ከመቃርዮስ ትምህርት ጋር ቅርብ ግንኙነት እንዳለው እናያለን፤ እነርሱ ኀጢአትን ማሸነፍ የግል ኀላፊነት መሆኑን ያስተምራሉ። በራሳችን ኀጢአትን ለመቃወም በቂ ኀይል የለንም፤ ምክንያቱም ትግሉን በዚህ ዐይነት ለእግዚአብሔር ጸጥ ብለን እንድንተወው አልታዘዝንም። ቅድስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሲሆን፥ የጋራ ጉዳይንና የሕግ ጉዳይን ያመለክታል። ስለ እግዚአብሔር ብቻ የሚያስተምሩ በሕይወታቸው ሁሉ በክርስቶስ ከተደገፉና ወደ ራሳቸው ካልተመለከቱ፥ ትርምስ ሊቀንስ ይችላልና ሕይወታቸው ሁሉ ከንቱ ላይሆን ይችላል። ሆኖም በሚከተሉት ንኡሳን አንቀጾች በሙሉ የተሻለ መንገድ እንዳለ ለማሳየት እንሞክራለን።

## መ) ቅድስና፥ ሰባቱ መንፈሳውያን ሐቆች

ከአንዳንድ ክፍሎች በስተቀር አብዛኛው የአዲስ ኪዳን አሳብ ለምእመናን የቅድስና ጥሪ ነው። ይህንም ሁሉ ሲያነቡ አንዳንድ ሊቃውንት የዚህን ጥሪ ሁኔታ በሰባት ንኡሳን አርእስት ለማጠቃለል ሞክረዋል (15)። እነርሱንም እንደሚከተው በዐጭሩ እንመረምራቸዋለን:-

### 1. የሕይወት ለውጥ የሚገኘው አማኙ ሕይወቱን ለቅድስና ሲያስረክብ ነው

ወንጌሎችንና መልእክታትን ስናነብ፥ ለምእመናን ብዙ ትእዛዛት እንደተሰጡ እንመለከታለን። ትእዛዝ ማለት የአማኙ አንድን ነገር ማድረግ (ወይም አለማድረግ) ማለት ነው። አማኙ መታዘዝ ቢፈልግም ባይፈልግም፥ በትእዛዙ መሠረት ሕይወቱን ሲያስረክብ ለውጥና በረከት ይገኛል፤ እግዚአብሔር ይደሰታል፤ አማኙ በቅድስና ያድጋል። ሰው ሕይወቱን ሲያስረክብ፥ ይህን እንዲያደርግ እግዚአብሔር ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም እንደሠራ ያውቃል፤ ፊል. 2÷12-13። እንግዲህ አማኙ በትእዛዙ መሠረት ሲኖር፥ በሕይወቱ በረከትንና ለውጥን ይቀበላል (ማቴ. 5÷3-12፤ 6÷6፤ 7÷7-8፤ ፊል. 4÷4-7)።

2. «መጽደቅ በክርስቶስ ነው» የሚለው የቅድስና ዐውድ ነው

ብዙ ጊዜ ለማስገንዘብ እንደተሞከረው፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው»፤ 2ቆሮ. 5፥17:: ሰው በክርስቶስ የሚሆነው በእምነት ነው:: የእምነት ሥራ የወንጌልን ቃል፥ የእውነትን ቃል መቀበልና ማክበር ነው:: አማኙ ማስተዋል የሚገባው ምሥጢራዊ ከሆነው ከእግዚአብሔር ሥራ የተነሣ ወደ እምነት መድረሱን ነበረና በእግዚአብሔር ጊዜ እምነቱ እውነተኛ ሆነ፤ ዮሐ. 8፥45-46፤ ሐ.ሥ. 13፥48፤ 2ተሰ. 2፥13፤ 2ጢሞ. 3፥15:: «የአዲስ ፍጥረት» የመጀመሪያ ሥራ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ ነው (ዮሐ. 3፥3-8)፤ ቀጥሎ ደግሞ አዲስ ክርስቲያን በእግዚአብሔር መንገድ እንዲያድግ ያደርጋል፤ እስኪሞት ድረስም እግዚአብሔርን ይከተላል:: በክርስቶስ የሚሆነው አማኝ ስለ ክርስቶስ ብዙ ነገር መማር ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስን ራሱን ማወቅም ይጀምራል፤ ዮሐ. 14፥9:21-23፤ 17፥3:: እንግዲህ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከጸደቀ ወደ ቅድስና ሕይወት ገብቷል፤ በክርስቶስ ካላመነ ግን በመቀደስ ሂደት ውስጥ ገና አልገባም፤ መቀደስ አልጀመረም::

3. ከክርስቶስ ጋር በመስቀሉና በትንሣኤው ራስን አንድ ማድረግ የቅድስና መሠረት ነው

በክርስቶስ ያሉ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለዋል (ሮም 6፥1-11)፤ ይኸውም በኀጢአት የተገዛ ሕይወታቸው ቀርቷል ማለት ነው (ሮም 7፥24):: ከክርስቶስ ጋር ተነሥተዋል ማለትም ደግሞ ክርስቶስን ከሞት ያነሣ ኀይል አሁን «በውስጡ ሰውነታቸው» (ሮም 7፥22)፥ «በተሰወረ ልባቸው» (1ጴጥ. 3፥4) ይኖራል ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ተቃውሞ እንደ ቀድሞው ወዲያውኑ አይነሣም፤ ምክንያቱም ምኞታቸው እግዚአብሔርን ማወቅ፥ ማግኘት፥ መውደድ፥ ማክበርና ማስደሰት ነው:: ይህም «አዲስ ልደት» ነው:: እንግዲህ በአማኙ ዘንድ ቅድስና የተለመደ ነው:: ሰው ከማመኑ በፊት የእግዚአብሔርን ሕግ ሲሰማ፥ ልማዳዊ አሳብና ተቃውሞ ቢኖረውም፥ አሁን የሚታየው ግን ሕጉን ያለ ተቃውሞ መቀበል፥ መታዘዝና በሕጉ መደሰት ነው፤ ከውስጣዊው አዲስ ተፈጥሮ ጋር ይስማማልና:: ይህ ክርስቲያናዊ ነጻነት ነው፤ ምክንያቱም የአማኙ ልባዊ ፍላጎትና የእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ በመሆናቸው የሚወደውን ማድረግ ይችላል፤ ይገባዋልም::

4. ቅድስናን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው (16)

«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው:: እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም» (ገላ. 5፥22-23):: መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ዘጠኝ ጠባይዓት (ፍቅር፥ ሰላም፥ ደስታ...) በቀጥታ በሰው ልብ ሊያኖራቸው ይችላል፤ ይህን ሁልጊዜ ቢያደርግም፥ ሰዎች በመንፈሳዊ ማስተዋል አያድጉም ነበር:: እውነት ነው፤ አንዳንድ ጊዜ በልዩ ልዩ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ እንደዚህ ያደርጋል፤ ለምሳሌ፥ የበርናባስና የጳውሎስ ጥሪ ለተለየ አገልግሎት (ሐ.ሥ. 13፥1-3)፥ የፊልጶስ ጥሪ ደግሞ ለቂሣርያ እንደነበረ አስተውሉ፤ ሐ.ሥ. 8፥26-40:: ብዙ ጊዜ ግን መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው በመሣሪያ አማካይነት ነው:: በመሣሪያ የሚሠራውም በሁለት መንገዶች ነው::

ዋናው መሣሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: አማኙ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ሲያጠና መንፈስ ቅዱስ ምሥጢራትን ይገልጥለታል፤ ለምሳሌ፥ ፍቅር ምን ያህል ጠቃሚ ጠባይ መሆኑን ያሳየዋል፤ ከሌሎች ጠባይዓት ጋርም እንዴት እንደሚገናኝ ያብራራለታልና በሥራው፥ በራሱ ሕይወት፥ በቤተሰብ፥ በቤተ

ክርስቲያንና በዓለም ዘንድ በተግባር እንዴት እንደሚተረጐመው ይገልጥለታል፤ በዚህ ዐይነት ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቃል ጥናት መሠረት ስለ ፍቅር የተረዳቸውን አሳቦች የጻፈ አይመስላችሁም? (1ቆሮ. ምዕራፍ 13 እና ሮም 13÷8-10)::

ሁለተኛው መንገድ÷ በየጊዜው (በየሁለት ወርም ሊሆን ይችላል) ጠቅላላ ሕይወታችንን ወደ ፊት እንዴት መምራት እንዳለብን ስንመረምር÷ ስለ ግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ስናስብ÷ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንችላለን:: ለምሳሌ÷ ሙሉውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እናጠናለን÷ ወይስ የሚያስደስቱንን አንቀጾች ብቻ መርጠን እንመለከታለን (ሐ.ሥ. 20÷20-21)?

በእነዚህ ሁለት መንገዶችም ስለ ግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ብቻ ሳይሆን÷ በቤተ ክርስቲያናችን በሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስለ ራሳችን አጠቃቀም÷ እንደዚሁም ስለ ጸሎት÷ ስለ ኅብረታችን÷ ስለ ምስክርነታችን... ወዘተ ግምገማ ማድረግ ይገባናል:: በዚህ ዐይነት በተለይ በቅድስና የሚታየውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እናውቃለን::

5. የቅድስና ተመክሮ ከባድ ነው (17)

«በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ:: ሥጋ በመንፈስ ላይ÷ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና÷ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም»፤ ገላ. 5÷16-17::

አማኝ÷ የነፍሱን ድክመት በአንድ በኩል÷ የሥጋ ኀይልን በሌላ በኩል ሲያስብ÷ የቅድስና ተመክሮ ከባድ ሆኖ ይታየዋል፤ ሮም 7÷24:: በሌላ በኩል ደግሞ በክርስቶስ ያለውን በረከትና ድል መርሳት የለበትም፤ ሮም 8÷1-4:: ይህን ትግል የማያውቅ አንድም ሰው እንኳ ቢኖር÷ የዚያ ሰው ዳግመኛ መወለድ አጠራጣሪ ነው::

6. በእግዚአብሔር የተገለጠው የእግዚአብሔር ሕግ ሁሉ ለቅድስና ነው (18)

«በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፤ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ»፤ ኤፌ. 4÷24::

በዚህ ጥቅስ ጽድቅና ቅድስና እጅግ ይመሳሰላሉ፤ ምክንያቱም ሁለቱ ንጽሕናን ያመለክታሉ:: ጽድቅ በእግዚአብሔር ዘንድ አማኙ ያለውን ደረጃ÷ ቅድስና ደግሞ አማኙ በራሱ ጠባይ ያለበትን ሁኔታ ይገልጣሉ:: ይህ የአማኙ ዓላማ መሆን አለበት:: የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅና ማክበር ዓላማችን ሊሆን ይገባል፤ ሆኖም ሕግን ሁሉ በመጠበቅ የምንድን አይደለንም:: ሕጉን መርምረን በውስጡ መቶ ትእዛዛትን ብናገኝ÷ ሁሉን እንዳልጠበቅን እንረዳለን:: ሕገ ኦሪትን÷ ሕገ ወንጌልን አልጠበቅንምና የጠፋን ሰዎች ነን:: ድኅነት ከጸጋ እንጂ ሕግን ከመፈጸም የተነሣ የሚገኝ አይደለም፤ ከእግዚአብሔር እንጂ÷ ከሰው አይደለም፤ ድኅነት ከእግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ሮም 6÷14፤ ኤፌ. 2÷8-9::

7. የመንፈስ ፍቅር የቅድስና እንብርት (ማእከል) ነው (19)

የመንፈስ ፍሬ ፍቅር... ነው (ገላ. 5÷22)፤ ያለ ፍቅር ዓለም ምንም አይደለም፤ እግዚአብሔር ፍቅርን መስጠት ይወዳል፤ የሚሰጠው ነገር ሁሉ ፍቅር አለበት:: «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል:: ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ:: እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና

በዚህ ፍቅርን ዐውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል»፤ 1ዮሐ. 3፥14-16::

ቅድስና እውነተኛ ሆኖ ከታየ፥ ሰባት ምልክቶች መኖራቸውን ተገንዝበናል:: ከምልክቶችም ጋር ሦስት ውጤቶች ሊታዩ ያስፈልጋል:: የመጀመሪያው ውጤት እውነታ ነው፤ ማለት ሰው በትሕትናና በተሰበረ መንፈስ በእግዚአብሔር ፊት ወድቆ ራሱን በአግባቡ ይመዝናል:: ራሱን ከሌሎች በላይ እንደሆነ ሳይቈጥር፥ በክርስቶስ አካል ለእርሱ የተመደበለትን ስፍራ በደስታ ይቀበላል:: ሁለተኛው ውጤት ለውጥ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር የጸጋ ሥራ የሰውን ልብ ከለወጠ በኋላ ቀስ በቀስ የዚያን ሰው ሕይወትና አኗኗር ሁሉ ይለውጣል፤ በሌላም ሁሉ ዘንድ ለውጥ ያመጣል ማለት ነው:: ሦስተኛው ውጤት እንቅስቃሴ ሲሆን፥ ይኸውም ቅድስና ከኀጢአት የተወረሰውን ስንፍና እያሸነፈ ለጌታ ሥራ በጋለ መንፈስ ዘወትር እንዲተጋ ሰውን ሲገፋፋ እንደሚችል ሲታይ ነው::

ይህን ምዕራፍ ለመደምደም ስድስት ንኡሳን ክፍሎች አሉ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤ አንደኛ:- ምእመናን ሁሉ ለቅድስና ተጠርተዋል:: ሁለተኛ:- ምእመናን ሁሉ በአንድ መንገድ ለቅድስና ተጠርተዋል:: ሦስተኛ:- ፍጹም የሆነ ቅድስና በዚህ ዓለም አይገኝም:: አራተኛ:- ምእመናን ሁሉ ለእድገት ተጠርተዋል:: አምስተኛ:- የእግዚአብሔር ሕዝብ ነፍስ ፍጹም የሚሆነው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: ስድስተኛ:- ሥጋቸውም ፍጹም የሚሆነው በዓለም ፍጻሜ ነው::

## ሠ) ምእመናን ሁሉ ለቅድስና ተጠርተዋል

«ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና»፤ 1ተሰ. 4፥3:: እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና እኛ የተቀደስን እንድንሆን የእርሱ ፈቃድ ነው:: በክርስቶስ ቅዱሳን ነን፤ ስለዚህ አካሄዳችንና አኗኗራችን፥ ተግባራችንና መሠረታዊ ጥሪያችን ከጠባያችን ጋር ሊስማማ ይገባል::

እውነት ነው፤ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ፥ ምኞት፥ ስሜትና ትምህርት ወደ ቅድስና መንገድ ሊጠራን ይችላል፤ ሆኖም የተጠራነው ለአንድ ቅድስና ነው:: ቅድስና በእግዚአብሔር በመሆኑ አንድ ዐይነት ነው፤ እንግዲህ ምእመናን ሁሉ በአንድ ጌታ የተጠሩ በመሆናቸው በአንድ ቅድስና ይሳተፋሉ፤ ስለዚህ በተለይ በአንድ መንገድ ቢቀደሱ የሚያስገርማቸው አይሆንም::

ሰው ቅዱስ መሆንን ሊመኝ ይችላልና በአቋራጭ መንገድ ይጓዛል፤ ሆኖም በራሱ መንገድ ሲሄድ ሊሳሳት ይችላል፤ በዚህ ምክንያት በትምህርታችን ልዩ ልዩ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠት ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ፥ በሚከተለው ትምህርት ላይ ማስጠንቀቂያዎቹን እንጠቊማለን:-

## ረ) ምእመናን ሁሉ በአንድ መንገድ ለቅድስና ተጠርተዋል

የቅድስና መንገድ አንድ ነው፤ ይኸውም ክርስቶስን የመምሰል መንገድ ብቻ ነው፤ ከዚህም ውጭ ሌላ መንገድ የለምና:: ከዚህ የተነሣ ሐዋርያው፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው» ይላል፤ 2ቆሮ. 5፥17:: ሰው ሕፃን ቢሆንም በክርስቶስ ሊኖር ይችላል፤ ሌላ ሰው ደግሞ ከሸመገለ በኋላ ሊቀደስ ይችላል፤ ሆኖም የሚቀደሰው በአንዱ መንገድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ሌላ መንገድ የለም:: ብዙ ሰዎች ቅድስና እንደሚያንሳቸው ሲሰማቸው፥ ሌሎች ደግሞ በቂ ቅድስና እንዳላቸው ይሰማቸዋልና በዚያ መሠረት መኖር ይፈልጋሉ:: «አንተ እንደዚህ እንዴት ልትሆን ቻልህ?» ብለው

አንድን ሰው ሲጠይቁ፥ ያ ሰው ስለ አንድ ተመክሮ፥ ወይም ስለ አንድ አዲስ ትምህርት፥ ወይም ስለ አንድ ጥቅስ አተረጓጐም ይናገራልና የሰሙትን ለመፈጸም ይሞክራሉ:: ዐልፎ ዐልፎ ሰው አዲሱን በረከት ያገኘ ይመስላቸዋል፤ ሆኖም እንደ ቀድሞው ፈተና ያጋጥማቸዋልና ተስፋ ይቈርጣሉ:: እዚህ ላይ ጠቅላላ ስሕተታቸው በቅድስና ላይ በቂ ጥናት አለማድረጋቸው ነው::

## ሰ) ፍጹም የሆነ ቅድስና በዚህ ዓለም አይገኝም

እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም:: እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ ነው፤ ነገር ግን ማናቸውም ፍጡር በቅድስና ለማደግ ይችላል እንጂ ባለበት ሊቈይ አልተጠራም፤ ሆኖም እንደ ፈጣሪው ፍጹም ብሩህ ሊሆን አይችልም፤ ፈጣሪውንም ማንጸባረቅ አይችልም::

ፍጹም ቅድስና በመላእክትም ሆነ በሰው ዘንድ ቢገኝ ኖሮ፥ በፍጥረት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሆኖ መታየት ይመጣ ነበር፤ ነገር ግን እንደ እርሱ ያለ አምላክ የለም:: እንደ እግዚአብሔር ምናልባት ኪሩቤልና ሱራፌል ቅድስና አላቸው ይባል ይሆናል:: ነገር ግን ነቢዩ ኢሳይያስ ሱራፌልን ሲያያቸውና ሲሰማቸው የእግዚአብሔር የልብስ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር:: «ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም እግሮቹን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር:: አንዱም ለአንዱ፦ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር»፤ ኢሳ. 6፥1-3:: እንዴት ያለ ታላቅ ክብር ነው! በእግዚአብሔር ዘንድ ካልሆነ በቀር እንደዚህ ዐይነቱ ፍጹም ክብር የት ሊገኝ ይችላል? በዚህ ክብር ሰው ሊሳተፍበትና ሊቆምበት ይችላልን?

## ሸ) ምእመናን ሁሉ ለእድገት ተጠርተዋል

እድገት ተፈጥሮታዊ ነው፤ ክርስቲያን ሁሉ በመንፈሳዊ ሁኔታ ሊያድግ ተጠርቷል:: ሰው ሊያድግ ይችላል፤ ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ሊቀንስም ይችላል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዐመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ:: ለእርሱ አሁንም እስከ ዘለዓለም ቀን ድረስ ክብር ይሁን አሜን»፤ 2ጴጥ. 3፥17-18:: በዚህ ዓለም የክርስቲያን በተለይም የአንድ መንፈሳዊ መሪ ዋና ጥሪ፥ የራሱን መንፈሳዊ እድገት የሚመለከት እንደሆነ ብዙ ጊዜ ተነግሯል::

## ቀ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ነፍስ ፍጹም የሚሆነው በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው

«ሊዳሰስ ወደሚችል ወደሚቃጠልም እሳት፥ ወደ ጭጋግም፥ ወደ ጨለማም፥ ወደ ዐውሎ ነፋስም፥ ወደ መለከት ድምፅም፥ ወደ ቃሎችም ነገር አልደረሳችሁምና፤ ያንም ነገር የሰሙት ሌላ ቃል እንዳይጨመርባቸው ለመኑ፤ 'እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ ተወግሮ ይሙት' የምትለውን ትእዛዝ ሊታገሡ አልቻሉምና:: ሙሴም፦ እጅግ እፈራለሁ፤ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ፤ ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት

ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት (ተረጨው) ደም ደርሳችኋል»፤ ዕብ. 12፥18-24:: በዚህ አንቀጽ ጸሐፊው ወደ ሲና ተራራ የደረሰውን የእስራኤልን ሁኔታ ወደ ሰማያዊ ሁኔታ ከደረሰው የአዲስ ኪዳን ሕዝብ ሁኔታ ጋር ያነጻጽረዋል:: የሁለቱም በረከት አሁን እንዴት ታላቅ ነው! «ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች... ደርሳችኋል» ይላልና:: ከዚህ የምንረዳው «ነፍስ ፍጹም» ያልነበረ መሆኑን ነው፤ አሁን ከሞት በኋላ ግን የሰው ነፍስ ፍጹም ሆኗል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነፍስ ፍጽምና የሚያገኘው ግን ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ነው::

### ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥጋ ፍጹም የሚሆነው በዓለም ፍጻሜ ነው

ነፍስ እንደተበላሸ ሁሉ፥ የሰው ሥጋም ቈሸሸ፤ ረከሰ፤ ጕደፈ... ወዘተ፤ በፍጻሜው ጊዜ ሁሉ በክርስቶስ አንድ በመሆኑ ሰው አንድ ሥጋና አንድ ነፍስ ነው:: ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! «የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤... የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል»፤ 1ተሰ. 5፥23-24::

# ማስታወሻ

(1) ስለ እነዚህ ሦስት ምክንያቶች RR ገጽ 770-778 ይመ.

(2) ስለ ዐሥርቱ ቃላት ያተትንበትን ምዕራፍ 48ን ይመ.

(3) ይህ ንኡስ አንቀጽ በተለይ በRR ገጽ 778 ላይ ካለው አሳብ ጋር የሚቀራረብ ነው::

(4) መቅመቃ. የሮም መልእክት ይመ.

(5) C.E.B. Cranfield. Romans a Shorter Commentary በ1985 በT&T. Clark የታተመ ገጽ 128-129 ይመ.

(6) ይህን ክብር በይበልጥ በምዕራፍ 93 ልንመለከተው እናስባለን::

(7) በ1984 በIVP ሁለት ጊዜ የታተመው J.I. Packer በጻፈው በKeep In Step With The Spirit ገጽ 138 እና ቀጥሎ በሚገኘው ክፍል (J.I.P.) ይመ.

(8) ስለ ቅድስና ምሥራቃውያን አበው የሚሰጡትን ትምህርት Berkhof ገጽ 529፤ ደግሞም J.I.P. ገጽ 135 ይመ.

(9) በNew Dictionary of Theology በ1988 በIVP በተዘጋጀው Augustine እና Augustianism ገጽ 58-63 ይመ.

(10) Augustine ታላቅ ሰው እንደነበርና በ396 ዓ.ም. የሂፖ ጳጳስ እንደሆነ ት.እግ. ገጽ 238 ይመ.

(11) ስለ ተሐድሶ መስፋፋት «New Dictionary of Theology» ገጽ 569-573 «Reformed Theology» በሚለው ርእስ ሥር ይመ.:: ስለ «አምስቱ የካልቪን ነጥቦች» ትምህርትና ጥቅም በክርስቲያናዊ ኑሮ፥ «ዋስትና» በሚል ርእስ በተጻፈው በምዕራፍ 93 ይመ.

(12) Berkhof ገጽ 529-530 ይመ.

(13) J.I.P. ገጽ 132-169 ይመ.:: ይህ ትምህርት The Higher Life Teaching በሚል ርእስ በመታወቅ በዓለም ሁሉ ተስፋፍቷል:: በአንዳንድ በኩልም ትምህርቱ ለጴንጠቆስጤያውያንና ለካሪዝማቲክ ትምህርት ምቹ በር ከፍቷል፤ ይህ የተረጋገጠውም፥ በተለይ በክርስቲያናዊ ኑሮ ውስጥ ሁለት ደረጃዎች እንዳሉ በማስረዳት በተደረገው እንቅስቃሴ ነው::

(14) J.I.Packer ገጽ 145-150 Keswick Teaching A Halfway House; NIDCC Keswick Convention ይመ.

(15) J.I.P. ገጽ 145-150 ይመ.

(16) J.I.P. ገጽ 108-110 ይመ.

(17) J.I.P. ገጽ 110-112 ይመ.

(18) J.I.P. ገጽ 112-114 ይመ.

(19) J.I.P. ገጽ 114-115 ይመ.

# ምዕራፍ 93 - ዋስትና

ሰው ድነትን ማግኘት ወይም ማጣት ይችላልን? የሚለው ጥያቄ በዚህ ርእስ ሥር የሚቀርብ የተለመደ ጥያቄ ነው። በዚህ ምዕራፍ እንግዲህ አምስት ታላላቅ መልሶችን ዐጠር አድርገን ለመስጠት እንሞክራለን።

## ሀ) ከፍጹም ብክለት ነጻ ስለ መውጣት

«ትምህርተ ክርስቶስ» በሚል ርእስ በተጻፈው በሁለተኛው መጽሐፍ ጥናት 4 ላይ ስለ ሰው ብክለት ተመልክተናል። እግዚአብሔር ከዚያ ጉስቍልና፥ ድክመትና አልከኛነት ሁሉ በኀይሉና በምሕረቱ እንዴት ነጻ እንዳወጣን አይተናል። ይህ ተግባር ዳግመኛ መወለድና አዲስ ልደት በመባል ይታወቃል፤ ሆኖም ይህን እውነት በሚገባ ለመረዳት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ መርፌ እንደሚወጋ ሐኪም ለክርስቲያን አዲስ መድኀኒት አይሰጥም። በዚህ ፈንታ ዳግመኛ የተወለደው ሰው ጠቅላላ ልብና ፈቃድ፥ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ በአንድነት በአዲስና በአስገራሚ አኳኋን ይያዛልና ከዚህ የተነሣ ሕይወት ሁሉ በክርስቶስ አዲስ ይሆናል፤ 2ቆሮ. 5፥17። በዚህ ምክንያት የሕይወት ብክለት አንድ ጊዜ ለዘለዓለም ተወግዷል፤ መመለስ አይችልም። ይህ የሚሆነው፥ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ ነው።

## ለ) የእግዚአብሔር ምርጫ

ወደ እግዚአብሔር ምርጫ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ሁለት ልዩ የእግዚአብሔር በረከቶች መኖራቸውን ለመግለጥ መርሳት አይገባንም፤ እነርሱም:-

1. በእግዚአብሔር ስም መጠራታችን (2ዜ.መ. 7፥14፤ ዮሐ. 17፥11-12)፥
2. የእግዚአብሔር ልጆች መባላችን (1ዮሐ. 3፥1፤ ኤፌ. 1፥5) ናቸው።

የተበከልነው ሙሉ በሙሉ ስለነበረ፥ ጥሪአችን ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ምርጫ እንዲመጣ አስፈላጊ ነው። ሙሴ ስለ እስራኤል ሕዝብ የተናገረው ምስክርነት (ዘዳ. 7፥7) ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእምናን በጻፈው መልእክት ላይ ተረጋግጦ እንመለከታለን፤ 1ቆሮ. 1፥27-28። እውነት ነው፤ ምእመናን ሁሉ የተመረጡት፥ እግዚአብሔር ስለወደዳቸው፥ የራሱም ስም እንዲከበር እንጂ ጠባያቸው ወይም ሥራቸው መልካም ከመሆኑ የተነሣ እንዳልሆነ ማወቅ አለባቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ. 1፥3-5፥ እግዚአብሔር «ባረከን»፤ «መረጠን»፤ «ወሰነን» ብሏል።

ስለ እግዚአብሔር ምርጫ አራት ነገሮችን ብናስታውስ መልካም ነው:-

1. የምርጫው መሠረት፥ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፤ ዘዳ. 7፥7፤ ኤፌ. 2፥4-9፤
2. የምርጫው ጊዜ፥ «ዓለም ሳይፈጠር ነው»፤ ኤፌ. 1፥4፤
3. የምርጫው ዓላማዎች፥ «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ» (ኤፌ. 1፥12)፥
   «የልጁን መልክ» እንድንመስል (ሮም 8፥29)፥
   «የእርሱን በጎነት» እንድንናገር (1ጴጥ. 2፥9) እና
   «በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ» (ኤፌ. 1፥4) የሚሉት ናቸው።

4. የምርጫው ዐውድ፥ በክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር የመረጠን «በክርስቶስ» ነው (ኤፌ. 1፥4) ማለት የእርሱ እንድንሆን፥ ለእርሱም እንድንታዘዝ ለክርስቶስ ስለሰጠን ነው፤ 1ጴጥ. 1፥2።

## ሐ) ውጤታማ ማስተስረያ

ይህን ምርጫ እውን ለማድረግ እግዚአብሔር የማስተስረያን መንገድ አዘጋጀ፤ ይኸውም የኀጢአታችን መሥዋዕት እንዲሆንልን ውድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ተረጋግጧል። ደሙን በማፍሰስ ኢየሱስ በሰው ኀጢአት ምክንያት የመጣውን የእግዚአብሔርን ቍጣ አበረደ፤ የኀጢአታችንን «የዕዳ ጽሕፈት» ደመሰሰ (ቆላ. 2፥14) እና በዚህ ዐይነት ማስተስረያ ሆነልን። ያስገኘልን ማስተስረያ ውጤታማ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያረጋግጥልናል:-

1. መሥዋዕቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን አገኘ፤ ኤፌ. 5፥2፥

2. መሥዋዕቱ ወደ እግዚአብሔር አቀረበን፤ ዕብ. 10፥19-22፥

3. መሥዋዕቱ አንድ ጊዜ ለዘለዓለም የቀረበ ነበረ፤ ዕብ. 7፥27፥

4. መሥዋዕቱ «በደሙ የሆነ ማስተስረያ» ነበረ፤ ሮም 3፥25፥

5. መሥዋዕቱ የፍየሎችና የጥጆች ደም ሊያነጻ ያልቻለውን ኅሊናችንን ያነጻል፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ዮሐ. 1፥7፥

6. መሥዋዕቱ «ብዙ ልጆችን ወደ ክብር» የሚያመጣ ነበረ፤ ዕብ. 2፥10።

እግዚአብሔር አገልጋዩ ለሆነው ለመሲሑ፥ ድካሙ ሁሉ ከንቱ አለመሆኑን ከጥንት ጀምሮ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር፤ ኢሳ. 53፥11-12።

## መ) ሊቃወሙት የማይቻል ጸጋ

የእግዚአብሔርን ጸጋ መቃወም ይቻላል? ሰዎች ሁሉ በጠባያቸው በእግዚአብሔር ፊት ዐመፀኞች ናቸው፤ ሮም 3፥11-12። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሞከረው፥ ሰዎች «የመውጊያውን ብረት» ለተወሰነ ጊዜ መቃወም ሊሞክሩ ይችላሉ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በመጨረሻ ጳውሎስን አሸነፈው፤ «ጌታ ሆይ፤ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» በማለት ለተገለጠለት ለኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አስረከበ፤ ሐ.ሥ. 9፥6። ከዚህ ክሥተት በኋላ በነበሩት ሦስት ቀኖች የእግዚአብሔር ቃል «ድንጋዩንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ» (ኤር. 23፥29) በጳውሎስ ልብ ይሠራ ነበር። ከማይጠፋ ዘር በእግዚአብሔር ቃል ዳግመኛ ተወለደ፤ 1ጴጥ. 1፥23። ወዲያውኑ ከተጠመቀና በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኋላ፥ ስለ እውነተኛው መሲሕ የተጻፈውን የወንጌል ቃል ለመስበክ ወደ ደማስቆ ሄደ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ጳውሎስ ሊቃወሙት በማይቻል የእግዚአብሔር ጸጋ ተደሰተ (1ቆሮ. 15፥10፤ ገላ. 1፥15)፤ ወንጌሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሳያፍር መሰከረ፤ ሐ.ሥ. 20፥24፤ ሮም 1፥16። እኛም የሐዋርያውን አርኣያነት ተከትለን ብንራመድ፥ የእግዚአብሔር በረከት ተካፋዮች እንሆናለን።

## ሠ) ለቅዱሳን የሚደረግ ጥበቃ

አንድ አባት ብዙ መኪና በሚነዳበት መንገድ ላይ ልጁን ይዞ ለመሻገር ቢፈልግ፥ የልጁን እጅ በሁለት መንገድ ጨብጦ ሊይዘው ይችላል። ከታች

በኩል ቢይዘው ልጁ የራሱን አሳብ ተከትሎ ሸሽቶ ሊጠፋ ይችላል:: ከላይ በኩል ቢይዘው ግን ልጁ ከአባቱ እጅ ማምለጥ ስለማይችል ሾልኮ መሄድ አይችልም:: የእግዚአብሔር ልጆች ከዚህ የበለጠ ዋስትና አላቸው፤ ይህም፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘለዓለም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም:: የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም:: እኔና አብ አንድ ነን» ብሎ ከተናገረው በግልጥ ይታያል፤ ዮሐ. 10፥28:29:: የአብ እጅ በክርስቶስ እጅ ላይ ሆኖ ምእመናንን ሁሉ ሲጠብቅ በምንመለከትበት ጊዜ፥ አብና ወልድ ሕዝባቸውን ለማዳን በአሳብ፥ በዓላማና በፈቃድ አንድ ስለ መሆናቸው ርግጠኞች እንሆናለን:: የፈሰሰው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ለገባው አዲስ ኪዳን ማኅተም ነው:: የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኗል» (ዕብ. 7፥22) ብሎ መሰከረ:: የሚሻል ኪዳን፥ መካከለኛ (አስታራቂ) መሆኑን በልዩ ልዩ ስፍራ ጽፏል፤ 8፥6፤ 9፥15፤ 12፥24:: «ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘለዓለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው»፤ 5፥10:: እርሱም፥ «የሕዝቡን ኀጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት» ነው::

የእግዚአብሔር ባሕርይ፥ የተስፋ ቃላቱና መሐላው ለምእመናን መልሕቅ እንዲሆኑላቸው ተሰጥተዋል:: ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቶ ወኪላችን በመሆን ወደ ሰማያዊው መቅደስ፥ «ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ»፤ 6፥20:: እዚያም ተገኝቶ፥ «በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው» (7፥25) እንደሚችል በማብሠር ጸሐፊው ምእመናንን ሁሉ ያጽናናል::

የዕብራውያን ጸሐፊ መልእክቱን ለመደምደም (ዕብ. 13፥20-21) የጻፈውን መሪ ሐሳብ እኛም ለዚህ ጥናት መደምደሚያ ማድረጋችን ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፤ «በዘለዓለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን::»

## 1. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው አንዳንድ የእንግሊዝኛና የሌሎችም ቋንቋዎች ቃላትና ሐረጎች ከነፍቺቻቸው

በዚህ ዝርዝር ትምህርተ መለኮትን በተመለከተ የቃላትን አጠቃቀም ማሳየት እንሞክራለን::

Adoptionism፤ ኢየሱስ ካደገ በኋላ መሲሕ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚገልጥና የእግዚአብሔር ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሰው ሆነ ከሚለው እውነት ጋር የሚቃረን ትምህርት ገጽ 52:61::

Amyraldus፤ በድኅነት ቅደም ተከተል ውስጥ ምርጫ ከፍጥረትና ከውድቀት በኋላ እንደሆነ የሚያምኑ ተከታዮች የነበሩት የነገረ መለኮት ምሁር ገጽ 103:109::

Antinomianism፤ የቅድስና ሕግ ማንኛውንም የግብረገብ ሕግና ትእዛዝ የማውጣት ወይም እያመቻመቹ የመኖር ሕግ ሳይሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ልጅና ወራሽ ሆኖ በነጻነት ሕግ መራመድ መሆኑን የሚያስተምር አመለካከት ገጽ 25:30::

Augustine፤ ገጽ 212 ይመ.

Augustinianism፤ ስለ ቅድስና እና ስለ ሌሎችም ተዛማጅ የነገረ መለኮት ጉዳዮች የአውግስጢኖስና የተከታዮቹ አመለካከት ያለበት ትምህርት ገጽ 204:212::

Being Slain in the Spirit፤ ትርጉሙ በመንፈስ መገደል ማለት ሲሆን፥ አንዳንድ ሰዎች በተመሰጠ ድንገት መሬት ላይ ወድቀው ለተወሰኑ ደቂቃዎች የሚቈዩበትንና በመንፈስ ቅዱስ መቀደስ ይቻልበታል ተብሎ የሚታመንበትን ልምምድ ያመለክታል ገጽ 181:189::

Be Born Again፤ ገጽ 130 ይመ.

Call

- Effective Call፤ የተወሰኑ ሰዎች የወንጌልን ቃል ሰምተው ንስሐ እንዲገቡና በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ የሚያደርግ የእግዚአብሔር ጥሪ ገጽ 117:129::
- External Call፤ ሰው በልቡ ሳይሆን፥ በሥጋዊ ጆሮው ብቻ የሚሰማው የእግዚአብሔር ጥሪ ገጽ 117:129::
- Internal Call፤ የወንጌል ቃል ከተሰበከ በኋላ በልባዊ «ጆሮ» የሚሰማ የእግዚአብሔር ጥሪ ገጽ 117:129::

Conversion, Convert, be converted፤ ገጽ 132:147 ይመ.

Edwards, Jonathan፤ በጩኸት፥ ልዩ በሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ፥ በመዝለል፥ መሬት ላይ በመውደቅና በመሳሰሉት እንግዳ ክሥተቶች አንድ ድርጊት ከመንፈስ ቅዱስ ነው ወይም አይደለም ማለት እንደማይቻል በዝርዝር የጻፈ ታላቅ የነገረ መለኮት ምሁርና ወንጌላዊ ነው:: እንደዚህ ለመጻፍ የቻለው

እነዚህን የመሳሰሉ ድርጊቶችን ለመመዘን የሚያስችል መስፈርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ ባለመገኘቱ ነው ገጽ 27:30::

Election፤ በኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ አማካይነት ከሰዎች መካከል የተወሰኑትን ለማዳን እግዚአብሔር ያለው ዘለዓለማዊ ዕቅድ ገጽ 94::

- Unconditional፤ ሰው ይገባኛል የማይለው ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ሰዎችን የማዳን ምርጫ ገጽ 103:109::

Filioque፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርፀት ለኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት የተጨመረ «እና ከወልድ» የሚለው ሐረግ ገጽ 67:70::

Formalism፤ ደንብና ልማድ በጥብቅ የሚከበርበት ሜዳዊ ሥርዐት ገጽ 25:30::

Grace

- Common፤ ለሰዎች ሁሉ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ጸጋ 42:47::
- Special (Saving)፤ በምርጫ ለሚድኑት የሚሰጥ ልዩ (የሚያድን) የእግዚአብሔር ጸጋ ገጽ 42:47::
- Irresistible፤ የእግዚአብሔር ጥሪ ተቀባይነት እንዲያገኝ በሰው ልብ ውስጥ የሚሠራና ፈቃዱን የሚለውጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ገጽ 119:129::

Higher Life Teaching (The)፤ ገጽ 206:213 ይመ.

Illumination፤ አብርሆት፥ በትምህርተ መለኮት፥ ሰው፥ እግዚአብሔር የገለጠውን እንዲያስተውል መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን ሥራ ያመለክታል ገጽ 120:129::

Infralapsarians፤ ምርጫ ከፍጥረትና ከውድቀት በኋላ የተከናወነ መሆኑን የሚያስተምሩ ገጽ 103:109::

Institutionalism፤ መንፈሳዊ ሕይወትን እስከሚያዳፍን ድረስ ድርጅታዊ አስተዳደርን የመጠበቅ አመለካከት ገጽ 25:30::

Justification፤ ሰውን በክርስቶስ የማጽደቅ የእግዚአብሔር ሥራ ገጽ 148:163::

Keswick፤ በሰሜን እንግሊዝ የምትገኝ በብዙ ሐይቅ የተከበበች ከተማ ገጽ 207::

- Convention፤ በከዚክ የተካሄደ ዓመታዊ ጉባኤ ገጽ 207::
- Teaching፤ የውርስ ኀጢአት ከሰው ልብ ሳይወገድ፥ ክርስቲያን ኀጢአትን በመቃወሙ አሸናፊ ሕይወት ሊኖረው ይችላል፤ ይህም የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው የድል ኑሮ ነው ገጽ 207:213::

Legalism፤ የትእዛዛትን ዝርዝር ማዘጋጀት ወይም ተመችቶና መስሎ መኖር ገጽ 25:30::

Mystical Union (The)፤ በክርስቶስና በምእመናን መካከል ያለው አንድነት ምሥጢራዊና ከሰው አእምሮ በላይ በሆነው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚገኝ ስለሆነ፥ አብዛኛውን ጊዜ ምሥጢራዊ አንድነት በመባል ይታወቃል ገጽ 91:93::

Nationalism፡ ብሔራዊ ወገናዊነት የሚንጸባረቅበት አመለካከት ገጽ 25:30::

Order of Salvation (ORDO SALUTIS)፡ የድኅነት ቅደም ተከተል ገጽ 110:115::

Penance፡ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ምእመናን ንስሓ ሲገቡ የሚፈጸመውን ልዩ ልዩ ሥርዐት ያመለክታል ገጽ 135:147::

Pneumatology፡ ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ ገጽ 23:30::

Reprobation፡ ቃሉ ለድኅነት ሳይመረጡ የቀሩትን ያመለክታል ገጽ 98:108::

Sandemanians፡ እውነተኛ እምነት እውነትን ዐውቆ ማመን ብቻ እንደሆነ የሚያስተምሩ የሮበርት ሰንድማን ተከታዮች ገጽ 142:147::

Sub-Conscious፡ አዲስ ልደት እውን የሚሆንበት በሰው ልብ ከሰው ልቡና በታች ያለው ክፍል ገጽ 123:129::

Supralapsarians፡ በድኅነት ቅደም ተከተል ውስጥ ምርጫ ከፍጥረትና ከውድቀት በፊት እንደሆነ የሚያምኑ ገጽ 103:109::

Traditionalism፡ የሰውን ልብ ሁኔታ ችል በማለት የሃይማኖትን ትውፊት የመከተል ዝንባሌ ገጽ 25:30::

## 2. ከልዩ ልዩ አርእስት ጋር የስሞችና የሐረጎች ማውጫ

ዋና ዋናዎቹ የትምህርት አርእስት በምዕራፍ ማውጫዎች ላይ ይገኛሉ። ከዚህ ላይ ግን የሰው ስሞች ከአርእስቱ ጋር እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።


ሃይማኖት 23 45 137 140 155 156 159 183 204

- የሃይማኖት መሪዎች 53 134
- የሃይማኖት ትውፊት 25
- የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት 23 26 70

ሉተር - ማርቲን 128 157 158 205

ሊበራል (ሊበራሎች) 37 142

ልዕልና

- የእግዚአብሔር 31 75 103 162 183 197 204

ልደት

- አዲስ 35 69 80-81 122 126 129 154 173 208 214
- ዳግም 112-115 120-129 149

ልጅነት

- የልጅነት መብት 150 170 172
- የልጅነት መንፈስ 165 169 172
- የልጅነት ኀላፊነት 166 170
- የብኩርና መብት 168

ሉይድ ጆንስ - ማርቲን 178

ሐዋርያት 35 36 49 58-59 62 64 72 73 96 97 101 113 117 122 145 162 173 192-193

- የሐዋርያት ሥርዐተ ሃይማኖት 23
- የሐዋርያት ሥራ 62 73 97 135 140 174 177 186 188 197
- የሐዋርያት ትምህርት 28

መላእክት 91 97 105 167 211

መስቀል

- የመስቀል ላይ ሥራ 150

መቃርዮስ

- የመቃርዮስ ትምህርት 203 207

መንፈስ ቅዱስ

- የመንፈስ ቅዱስ ሙላት 173 182-183 189-190
- የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት 169 179
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች 26-27 80 182 186
- የመንፈስ ቅዱስ ቅባት 29 181
- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት 26 173 175 176 182-183 185 186 188 189
- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ 181 182 192 201
- የቅድስና መንፈስ 57 196-197
- የእውነት መንፈስ 28 60 62 179
- የጸጋ መንፈስ 42 72
- የፍቅር መንፈስ 29
- የጥበብ መንፈስ 37 181

ማኅተም

- የመንፈስ ቅዱስ 179 180

ምልቶን 75

ምሥጢረ ሥላሴ 149 183

ምሥጢረ ሥጋዌ 149

ምርጫ 42 79 83 94 95 96 97 98-109 162 214-215

ምጽአት

- ዳግም 24 59 60 73 86 93 106 115 153 163 166 180

ሥራ

- መልካም 44 54 107 114 135 150 155-156 159-160 164 171 196-197 216
- የመንፈስ ቅዱስ 23 29 34 38-39 41-42 50-51 54 58 69-70 73 79-81 120 122-123 125 138 168-169 177 196-197 208

ሩአኽ 31-39

- የሩአኽ ሥራ 31 32 36 37

ስርየት (ማስተስረያ) 29 49 76 119 148 157 215

- የኀጢአት 80 81 82 113 118 128 137 149 154 158 175 188 196

ሳንድማን - ሮበርት 142

ቃል ኪዳን

- የቤዛ 85 96
- የጸጋ 42

ቅድስና

- የቅድስና አኗኗር 114 163 191 194 195 196
- የቅድስና ደረጃ 114 148 162 184 186 206

በረከት 42 81 86 100 139 144 167-170 183-184 186 190 202 206-207 209 212 215

በዓለ ኀምሳ 24 34 49 62 73 79 118 173-177 179 182 190

ቡልትማን - ሩዶልፍ 142

ባርት - ካርል 100

ቤተ ክርስቲያን

- የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት 41 92 110 203-205
- የቤተ ክርስቲያን አባቶች (አበው) 49 75 149 203

ቤዛ (ቤዛነት) 32 72 81 85 109 148 149 204

ብኩርና

- የብኩርና መብት 168

ተሐድሶ

- የተሐድሶ ሊቃውንት 37
- የተሐድሶ መሪዎች 26 103 150 158 205
- የተሐድሶ ተከታዮች 41 103 128 150 184
- የተሐድሶ ትምህርት 103-104
- የተሐድሶ ዘመን 79

ትሥጉት 23 34 36 50 51 52 59 62 73 179 189 203

ትውፊታውያን 185

ኀጢአት

- የኀጢአት ብክለት 150
- የሰው ብክለት 78 154 214

አለኝታ 54 169 180-181 197 201

- ተመክሮታዊ 144

አርሚኒዮስ - ያዕቆብ

- የአርሚኒዮስ ተከታዮች (አርሚኒዮሳውያን) 41 103 104 205

አስተርእዮ 23 36 38 39 44 50 53 62 162 183

አባት 74 165-167 170 172 215-216

አባትነት 92 167

– እውነተኛ 167

አብርሆት 36 80 120 125 129

– የልቡና አብርሆት 125

አትናቴዎስ 60 66

አኩናስ - ቶማስ 103 128 150 158 205

አውግስጢኖስ 26 40 67 75 103 128 144 149-150 158 203-205

– የአውግስጢኖስ ትምህርት 203-205

 • ግልፕ የሆነው 204

 • ግልፕ ያልሆነው 204

ኢሬኔዎስ 52

እምነት

– የሚያድን 115 138 142 145

– የተአምር 138

– የታሪክ 137-138

– ጊዜያዊ 137-138

ካልቪን - ዮሐንስ 67 79 103 128 158 205 213

ካሪዝማቲኮች 26 184 185 187

ወስሊ - ዮሐንስ 184 203 206-207

ወንድም

– የምእመናን 168

ወንድምነት

– የክርስቶስ 160 168

ዊምበር - ዮሐንስ 187-188

ውትፊልድ - ጊዮርጊስ 184 188 190

ዋስትና 83 169 180 214-216

ዌስትምንስተር የሃይማኖት መግለጫ 171-172

ዕርቅ 148

ጉድውን - ቶማስ 183-184 189

ግኖስቲካዊ አሳቦች 141

ጥምቀት 175 176

– የመንፈስ ቅዱስ 175 176 178 185-186

– የመከራ 175

– የንስሐ 175

– የውሃ 175-176

– በኢየሱስ ስም መጠመቅ 79 100 110-111 173 177-178

ጥሪ 31 53-54 96 100 106 111 114 116 124 128-129 142 207-208 210 211 214

– ውጤታማ 117

– የወንጌል 117-120 127 128-129 132 133

– የውጭ 117

ጰራቅሊጦስ 49 65

ጰንጠቆስጤ 190

– ጰንጠቆስጤያውያን 26 184-187 189-190 213

ጸጋ

– ልዩ (የሚያድን) 42 46 47 72

– የጋርዮሽ 23 26 42-47 62 72 99 195

– ፍሬውና መሣሪያዎቹ 43-45

ጽድቅ 33 35 36 41 50 52 65 72 73 78 81 82 85 113 114 120 126 128 138 141 148-164 166 199 205 209

- የጽድቅ መንገድ 156-159
- የጽድቅ ሥራ 150 184
- የጽድቅ ትምህርት 149-150 158-159
- የጽድቅ ጊዜ 151 152

ፈቃድ
- የፈቃድ ነጻነት 125

ፍርድ (ኩነኔ) 98-99 104-105 148 159
- የፍርድ ቀን 152 156

ፍትሕ 104-105 151
- ኢፍትሐዊ 104-105 148

ፍጥረት 32 43 51 69 72-75 117 211
- አዲስ 39 51 59 72 81 84 121-122 128 208

ፔላጊዮስ 128 158 204
- የፔላጊዮስ ትምህርት 40-41 204

## 3. ማብራሪያ የተሰጠባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

በዚህ ማውጫ በተለይ በሐተታ የተብራሩና ትምህርቱን የሚያረጋግጡ ጥቅሶች እንጂ በመጽሐፉ የተጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ አልተዘረዘሩም:: ማናቸውም ጥቅስ በአንቀጹና በዐውዱ መሠረት እንዲታይ ያስፈልጋልና አንዳንድ ጊዜ እያንዳንዱ ጥቅስ ሳይሆን አንቀጹ ብቻ ተጠቍሟል:: ከወንጌሎች በተወሰነ ክፍል አንድ ጥቅስ በዝርዝር ተጠቅሶ ካልተገኘ ከሌሎች ወንጌላት የተብራራ አሳብ ያለበትን ተመሳሳይ ጥቅስ መፈለግ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል::


| ኦሪት ዘፍጥረት | ገጽ |
|---|---|
| 1፥2 | 24 32 |
| 1፥2-3 | 69 |
| 1፥26-27 | 73 |
| 2፥7 | 24 32 |
| 2፥15:19-20 | 74 |
| 2፥16-17 | 74 |
| 3፥17-19 | 43 |
| 4፥21-22 | 44 |
| 15፥6 | 151 152 161 |
| 22፥12-18 | 161 |
| 41፥38-39 | 33 |
| 47፥25 | 43 |

| ኦሪት ዘጸአት | |
|---|---|
| 2፥12-15 | 206 |
| 3፥4-12 | 95 |
| 4፥22 | 165 |
| 19፥3-6 | 191 |
| 20፥1-17 | 191 |
| 20፥13-17 | 193 |
| 28፥3 | 69 |
| 31፥2-5 | 24 33 |
| 40፥34-35 | 50 |

| ኦሪት ዘሌዋውያን | |
|---|---|
| 11፥44-45 | 191 |
| 19፥2 | 202 |
| 19፥18 | 193 |

| ኦሪት ዘኍልቍ | |
|---|---|
| 12፥3 | 206 |

| ኦሪት ዘዳግም | |
|---|---|
| 7፥7 | 214 |
| 7፥7-8 | 95 |
| 10፥15 | 95 |
| 25፥1 | 148 |
| 32፥48-52 | 206 |

| መሳፍንት | |
|---|---|
| 2፥10-19 | 192 |
| 6፥34 | 36 |
| 15፥14 | 24 |
| 17፥6 | 45 |

| መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ | |
|---|---|
| 6፥20 | 181 |
| 16፥13 | 24 36 50 |
| 16፥14 | 44 |

| መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ | |
|---|---|
| 11፥1-27 | 206 |
| 12፥1-25 | 206 |
| 23፥2 | 36 37 |

| መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ | |
|---|---|
| 20፥27-29 | 43 |

| መጽሐፈ ነገሥት ካልእ | |
|---|---|
| 10፥28-31 | 44 |

| መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ | |
|---|---|
| 12፥18 | 37 |
| 16፥29 | 33 |

<u>መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ</u>

7፥14 214
33፥12-13 132

<u>መጽሐፈ ኢዮብ</u>

1፥12 44
2፥6 44
26፥13 24
32፥8 24
33፥4 24 32

<u>መዝሙረ ዳዊት</u>

8፥3-8 72
14፥1-3 78
14፥3-6 43
33፥6 24 32
ም. 51 133
51፥10-11 25 31
51፥10-12 34
51፥17 136
85፥4 131
103፥13-14 169
104፥30 24 32
130፥3-4 137
143፥2 149

<u>መጽሐፈ ምሳሌ</u>

17፥15:23 148
28፥13 135

<u>መጽሐፈ መክብብ</u>

11፥5 124

<u>ትንቢተ ኢሳይያስ</u>

6፥1-5 31
6፥9-10 131
11፥1-3 52
11፥1-5 33 37 39
11፥2 181
42፥1 53 96
53፥6 86
53፥11-12 215
55፥6 131
58፥13 193
59፥1-2 77
59፥2 76
59፥10:12-13 78
59፥21 35
63፥7-14 33 34
64፥6 155
65፥9:22 96

<u>ትንቢተ ኤርምያስ</u>

7፥23-25 43
17፥9 77 79 187
19፥7 46
23፥6 153 154
23፥29 215
31፥18 131
31፥33-34 125
33፥16 154

<u>ትንቢተ ሕዝቅኤል</u>

2፥2 24
ም. 16 40
20፥5 95
33፥11 131
ም. 36 40
36፥25-27 24 35 78 121 123
36፥26-27 174

<u>ትንቢተ ዳንኤል</u>

5፥12 33

<u>ትንቢተ ሆሴዕ</u>

11፥1 166

<u>ትንቢተ ኢዩኤል</u>

2፥28-32 38 174

<u>ትንቢተ ዮናስ</u>

3፥5-10 131

<u>ትንቢተ ዕንባቆም</u>

2፥4 96

**ትንቢተ ሐጌ**

2፥23 96

**የማቴዎስ ወንጌል**

1፥23 50
3፥1-2 133
3፥17 48
4፥17 133
5፥3 136
5፥3-12 207
5፥21-26:27-30:33-37 192
5፥23-24 135
5፥44-45 43 45
5፥48 191
6፥9-10 171
6፥12 171
7፥16-21 159
9፥22 138
11፥12 143
11፥25 105
11፥25-26 99
11፥28 117 118 193
11፥28-30 144
11፥29-30 194
12፥22-32 56
12፥33-37 156
12፥36-37 148
13፥5-6:20-21 131
13፥14-15 131
16፥16-17 173
17፥20 139
18፥20 91
19፥25-26 77
20፥15-16 105
20፥16 96 117
20፥22-23 175
21፥21 139
22፥14 96
25፥1-13:14-30 160
25፥31-34:45 36
25፥31-46 37
25፥40 38
27፥3-5 133 135
28፥18-19 128
28፥18-20 66
28፥19-20 63 105 175
28፥20 91

**የማርቆስ ወንጌል**

1፥4 175
1፥8 174 175
1፥14-15 79 81
1፥15 111 132
2፥1-12 138
3፥34-35 160
4፥3-20 155
4፥5-6:16-17 138
6፥12 133
10፥52 138
12፥29-31 170
12፥30-32 192
13፥20:27 96
16፥15 105 117

**የሉቃስ ወንጌል**

1፥15 182
1፥31 50
1፥35 39 50 51
1፥41:67 39 182
2፥49 52
3፥7-9 155
3፥8 135
3፥8:10 136
3፥16 53 175
3፥21-22 52
3፥28 165
4፥1-2 55
4፥1:14:18-21 54
4፥13 206
4፥14 55
4፥14-18 51
4፥17-19 55 181
6፥23 96
6፥36 191
7፥29 149
7፥36-50 139
8፥50 139
9፥23 136

9፥28-36 51
10፥20 102
10፥21 56
10፥29-36 160
11፥13 170 174
12፥32-33 170
12፥47-48 119
13፥1-5 137
13፥24 143
15፥11-24 134
15፥18-19 145
15፥25-32 134
16፥31 119
17፥6 146
17፥19 138
18፥13 145
18፥18-23 135
18፥21-23 142
18፥22 136
18፥35-43 139 143
18፥35-19፥10 142 145
19፥5 102
19፥5-6 135
19፥8 133 136
19፥8-9 132
22፥32 132
24፥46-49 151
24፥49 185


<u>የዮሐንስ ወንጌል</u>

1፥3 91
1፥9 91
1፥12 140 167
1፥ 12-13 78 112 113 121
1፥13 121 167
1፥14 51
1፥16 154
1፥18 38
1፥32 69
1፥32-33 54
1፥33 38
2፥19-22 34
3፥1-12 142
3፥1-16 139
3፥3:5 195
3፥3-8 78 208
3፥3-8:14-16 167
3፥3-10 121
3፥4 112
3፥5 66 80 121
3፥5:20 125
3፥5-6 112
3፥6 122
3፥7-10 35
3፥8 124
3፥8-9 36
3፥14-15 140
3፥14-16 112
3፥16 119 132
3፥16-18:36 118 140
3፥19-20 125
3፥33-34 54
3፥36 36
4፥29:39 132
4፥46-47 139
4፥48-50 139
4፥51-53 139
5፥22-23 168
5፥39-40 119
5፥46 119
6፥27 53
6፥37-39 96
6፥37-40 100
6፥38 168
6፥39 102
6፥44 80 113
6፥70 96
7፥39 38 58 173
8፥23 52
8፥24 139
8፥32 194
8፥34 77
8፥41-46 208
8፥50 138
10፥10 170
10፥27-28 96
10፥28-29 169 216
13፥15 194

13፥34-35 126 171
ም. 14-16 48
14፥9:21-23 208
14፥11 139
14፥16 59 64 80 180
14፥16-17 174
14፥17 28 38 49 179
14፥18 60
14፥23 89
14፥23:26 60
14፥26 64
14፥26-28 89
15፥1-11 84
15፥4-5 152
15፥8 159
15፥9-10 192
15፥14 192
15፥16 96
15፥26 24 28 38 62 64 66 68 70 179
15፥26-27 48
15፥27 49
16፥7 58
16፥8-11 65 120
16፥12-13 60
16፥13 28 125
16፥13-15 38
16፥14 24 28 60 65
16፥27 139
16፥32 168
16፥33 90
17፥1-2 96
17፥3 208
17፥4 168
17፥8 173
17፥11-12 214
17፥20-21 88
17፥21 92
17፥20-23 84
17፥22-24 199
20፥17 168
20፥22 58
20፥31 139
21፥17 194


## የሐዋርያት ሥራ


1፥1-2 60
1፥5 174 175
1፥5:8 185
1፥8 24 70 73 105 151 178 186
2፥2-4 177
2፥4 185
2፥16-18 186
2፥16-21 174
2፥17 100
2፥17-21 24
2፥21:38 100
2፥33 59 151 174
2፥33-36 179
2፥38 79 89 111 113 118 137 173 174
2፥41 73
2፥47 97
3፥16 140
3፥19-20 81 132 137
4፥31 182
5፥31 137 143
5፥31-32 118
6፥3-5 182 187
7፥51 44 64
7፥55-56 182
8፥4-25 177
8፥12-17 186
8፥26-40 208
8፥27-39 132
8፥29:39 64 197
9፥4 89
9፥5-18 132
9፥6 215
9፥17 177
10፥1-11፥18 178
10፥19:24:44-48 73
10፥34-48 186
10፥38 54 165 181
11፥18 137
11፥23 72
11፥24 182 187
13፥1-3 208
13፥2-4 70

13፥9-11 182
13፥38-39 149
13፥39 140
13፥48 97 100 140 208
13፥52 182
14፥16-17 43
14፥22:27 140
15፥9 140
15፥11 140
15፥26-29 92
16፥6 64
16፥14 117 125
16፥14-15 120
16፥30-31 162
16፥30-34 133
16፥31 81 111
17፥10-11 28
17፥30:34 132
18፥9-10 106
18፥27 143
19፥1-7 178 186
20፥7 193
20፥20-21 111 120 209
20፥24 215
22፥16 123 177
26፥17-18 113 120
26፥18-19 162
26፥20 135
26፥26-29 142
28፥25-27 131

ሮም

1፥3-4 57 153
1፥6 118
1፥6-7 117
1፥16 215
1፥18-3፥20 156
1፥21-30 193
1፥22-32 195
1፥29-32 43
1፥32 134
2፥14-15 44
2፥22 193
3፥11 78 125
3፥11-12 215
3፥11-18 154
3፥19-20 104 149
3፥19-20:21 153
3፥20 153
3፥20-22:28 141
3፥21-22 153
3፥21-31 156
3፥23 118
3፥24 141 153 154
3፥25 215
3፥25-26 119 151 154
3፥28 159
ም. 4 35
4፥3 161
4፥3-5 138
4፥4-5 155 161
4፥12 138
4፥19-21 152
4፥20-21 146
4፥23-25 151
5፥1-5 152
5፥2 194 199
5፥2:20-21 72
5፥7 72
5፥8 119
5፥9 154
5፥12-19 84 85
5፥15:17 75
5፥16 149
5፥19 85
6፥1-11 197 199 208
6፥1-14:19 163
6፥2:6 163
6፥4-11 86
6፥6 184
6፥6:11 86
6፥11-14 186
6፥12-14:19 86
6፥12-23 199
6፥14 77 209
6፥23 118 153 154 200
ም. 7 200
7፥4-6 163

7፥12 194
7፥14-25 203 207
7፥22 208
7፥24 208
7፥24-25 203
ም. 8 201-202
8፥1 87
8፥1-4 209
8፥3-4 51 181
8፥3-6 197
8፥3-8 196
8፥9 59 80 92
8፥9-10 49
8፥9:11 92
8፥9-14 24
8፥11 57 64
8፥12-39 166
8፥13 184
8፥13:14 181
8፥15 68 165
8፥15-16 54 169
8፥16 155 166
8፥16:17 82 113
8፥17:29 168
8፥23 165
8፥28 107
8፥29 25 95 100 101 107 117 214
8፥29-30 81 103 111 115 151
8፥32 42
8፥33-34 97 149
8፥34 89
9፥4 165 166
9፥6-13:15-16:22-24 94
9፥11 101
9፥16 102 105
9፥17-18 99
9፥18-24 105
9፥22-23 43
10፥2-4 141
10፥3-4 156
10፥9 118
10፥9-11 152
10፥14 117
10፥14:17 141
10፥27-28 96
11፥5 102
11፥5-7 97
11፥28 97
11፥36 74 92
12፥2 122
12፥5 87
13፥1-7 45
13፥3 44
13፥8-10 193 209
13፥14 136
14፥23 44
15፥17 87

<u>1ኛ ቆሮንቶስ</u>

1፥1-2 113
1፥4-9:10-17 206
1፥9 91 118
1፥21 117
1፥26-27 105
1፥27-28 214
1፥30 155
1፥30-31 105 153 192
2፥9 169 176
2፥10-11 64
2፥10-12 66
2፥12-15 24
2፥14 26 27
3፥21-23 169
4፥4-27 90
4፥17 87
6፥11 162
6፥19-20 163
8፥3 101
10፥2 175 176
10፥17 176
12፥4-13:27-31 182
12፥6-11 26 27
12፥7 186
12፥11 188
12፥12 176
12፥13 176
12፥26 88
ም. 13 209

14፥12 186
15፥3 86
15፥3-4 142 152
15፥10 154 215
15፥16-17 151
15፥21-22 76
15፥22 87
15፥45 59
15፥45:47-49 52
15፥58 106

2ኛ ቆሮንቶስ

1፥21-22 181 184
1፥22 180
2፥10 91
2፥17 87
3፥17-18 59 60
3፥18 89 127 194 199 202
4፥1-18 202
4፥3-4 46
5፥5 180 184
5፥8 91
5፥17 84 86 121 128 155 156 198 208 210 214
5፥21 86 154 155
6፥1 91
7፥10 133 135
9፥8-9:14 42
12፥12 188
13፥5 89
13፥14 63 92

ገላትያ

1፥6 118
1፥15 215
1፥15-16 120
2፥14-21 157
2፥16 111 141
2፥20 86 88 89 102 146 152
3፥2-5 89 175
3፥10:13 192
3፥13 154
3፥23-24 160
3፥23-4፥7 166
3፥26 161
3፥27 85
3፥28 88
4፥4-5 165
4፥6 68 89 155 166
4፥7 166
5፥16-17 207 209
5፥17 136 203
5፥17-18 201 203
5፥19-21 77
5፥19-23 201
5፥22 181 182 192 197 209
5፥22-23 34 208
5፥24 136
6፥14 105

ኤፌሶን

1፥1 113 162
1፥2-3፥17 166
1፥3-5 214
1፥3-5:11 151
1፥3-6:9-13 160
1፥3-14 97 103
1፥4 65 95 101 107 108 214 215
1፥4:12 85
1፥5 165 166 214
1፥5-6 101
1፥6 108
1፥6፤ 2፥6-8 106
1፥11 95
1፥12 214
1፥13 161
1፥13-14 80 108 180
1፥18-19 80
1፥19-21 186
2፥1-3 128 196
2፥1-5 153
2፥1-10 122
2፥4-9 214
2፥5 112
2፥5:8-9 153
2፥5-10 40
2፥6-7 42
2፥8-10 40

2፥10 84 87 122 198
2፥14-16 77
2፥19 167
2፥19-22 84
3፥14-15 167
3፥17 89
4፥1:4:6:10:11:12:14 103
4፥8:11-13 186
4፥11-13 90
4፥22 184
4፥22-24 198
4፥24 191 209
4፥30 24 25 180
5፥1-2 171
5፥2 215
5፥2-3 87
5፥8-11 171
5፥17 182
5፥18 182
5፥31-32 88
6፥1-3 193
6፥10 87
6፥11:13 171

**ፊልጵስዩስ**

1፥6 107
1፥21-23 129
1፥29 40
2፥4-5 187
2፥5 194
2፥7 88
2፥12-13 25 40 196 207
3፥10 90
3፥18-19 46
4፥2:4 87
4፥10:13 87
4፥13 89
4፥19 87

**ቆላስይስ**

1፥13-14 81 196
1፥27 89
1፥28-29 87
1፥29 81 196
2፥6-7 87
2፥13 122
2፥14 77 215
3፥1:4 86
3፥1-4 198
3፥9-10 136

**1ኛ ተሰሎንቄ**

1፥2-4 97 107
2፥11-12 118 194
2፥19-20 106
4፥3 181 199 210
4፥4-8 163
4፥7 118
4፥17 91
5፥9 100
5፥19-21 27
5፥23-24 163 196 212
5፥24 117

**2ኛ ተሰሎንቄ**

2፥13 97 100 103 107 144 154 208

**1ኛ ጢሞቴዎስ**

1፥19-20 121
2፥1-2 45
3፥16 32
4፥3-4 43
4፥10 45
5፥21 91
5፥22 127
6፥12 118
6፥17 43

**2ኛ ጢሞቴዎስ**

1፥1 87
1፥9 85 99 103 154
1፥12 162
2፥10 87 108
2፥19 101
3፥15-17 36
3፥16-17 24 65
4፥8 152 162

**ቲቶ**

1፥1-2 97
2፥11 42
3፥5 80 81 122
3፥5-7 24 42 69 72

**ዕብራውያን**

1፥1-2 38
1፥9 181
2፥4 70 188
2፥10 215
2፥13 168
2፥14-15 192
5፥8 161
5፥10 216
6፥4-6 119
6፥20 216
7፥2 216
7፥24-25 89
7፥25 216
7፥27 215
9፥4 57
9፥15 216
9፥22 119 154
10፥5-7 69
10፥19-22 215
10፥29 42
10፥38 141
ም. 11 35
11፥1 141 144
11፥2-40 141
11፥6 138
11፥8 152
11፥9 152
11፥10 152
11፥17-19 152
12፥5-11 170
12፥10 196
12፥14 197 203
12፥18-24 212
12፥22-24 91
12፥24 216
13፥20-21 196 216

**1ኛ ጴጥሮስ**

1፥1-2 32 63 95 98 106 197 215
1፥3 122
1፥3-5 83 141 158 162 169
1፥3:23 121
1፥6-9 170
1፥10-12 37 38
1፥15-16 82 191 202
1፥22 81
1፥23 113 126 215
1፥23-25 105 124
2፥2-3 187
2፥4-5 88
2፥9 98 106 214
2፥9-10 82
2፥13-14 45
2፥20-21 118
2፥21 90 194
2፥24 86 118 154 163
3፥4 208
5፥8 82
5፥10 195
5፥13 98

**2ኛ ጴጥሮስ**

1፥5-11 98 108
1፥10 103 106
1፥21 24 36 69
2፥7-8 98
3፥17-18 211
3፥18 187

**1ኛ ዮሐንስ**

1፥1-4 171
1፥5-7 171
1፥5-2፥21 162
1፥7-2፥1 126
1፥8-10 184 207
1፥9 161
2፥1-2 184
2፥2 76
2፥6 90

2፥9 131
2፥15-16 28
2፥20፡27 125
2፥26-27 29
2፥27 181
2፥29 112 126 184 195
3፥1 214
3፥1-2 162
3፥2 89 91
3፥9 181 184
3፥14-16 210
3፥14-18 141
3፥16 90
3፥23 141
3፥24 89
4፥4 89
4፥7 196
4፥8-10 40
4፥9 103
4፥16 141
4፥18 195
4፥20 160 170
5፥1 196
5፥4 112 126 196
5፥10-12 138
5፥12 82 144
5፥13 162

**2ኛ ዮሐንስ**

1-2፡13 98

**ያዕቆብ**

1፥2-3 170
1፥2-4 90
1፥18 66 113 121
2፥18-26 140
2፥19 135 142
2፥22-24 161
2፥26 155 159

**ይሁዳ**

4 98
21 127

**የዮሐንስ ራእይ**

2፥5፡16፡21-22 146
2፥5፡16፡22 133
2፥7፡11፡17፡29 96
2፥17 102
3፥1 60
3፥5 98
3፥20 88 89 118 144
3፥21 90
13፥8 98 102
20፥14-15 77
22፥17 128